Pissurleken 41

CENTRO DE ESTUDOS HISTÓRICOS ULTRAMARINOS
OFERTA
LISBOA

ኢትዮጵያ ፖርቱጌዞች እንዳዩዋት

(እኤአ 1520-1526 ዓም)

የጻፈው፤ ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ

የተረጎመው፤ ግርማ በሻህ

1921 P

ያሳተመው

Centro de Estudos Históricos Ultramarinos

ሊዝቦን፤ እኤአ 1966

PREFACE

On the occasion of the International Historical Congress held in Lisbon in 1960 to commemorate the 5th centenary of the death of Prince Henry the Navigator (1460), a suggestion was forwarded and approved: namely that there be an Amharic translation of the well known work by Francisco Alvares «Verdadeira Informação das Terras do Preste João». The edition now presented to the public is the fulfilment of that suggestion.

The kingdom of Prester John played a most important part in the Portuguese expansion. At first the Portuguese did not know just where such a kingdom was to be found. But since Christianity was then encircled by Islam, the former longed to find the famous Eastern Christian Kingdom of Prester John. It may be stated that Eastern Christianity, too, nourished the desire to contact Western Christian powers. They had a common foe — Islam.

As time went by, geographical notions became clearer and deeper. They were given a last touch by Pêro da Covilhã and Afonso de Paiva who received orders from King John II to go to Ethiopia and India. They left Lisbon in 1487, also the year of the departure from the Tagus of Bartholomew Dias who was to skip from the Atlantic to the Indian Ocean, thus concluding a series of voyages to ascertain whether or not Africa could be circumnavigated.

Once in India, the Portuguese lost no time in trying to get in touch with Ethiopia. In 1513 Queen Eleni sent Matthew as her ambassador to Portugal, via Goa. In her message she offered to enter into an alliance with Portugal against Islam. Eleni's proposal

was warmly welcomed in Lisbon. A diplomatic mission was soon dispatched to the court of Emperor Dawit (Libna Dingle) in 1520. The Embassy found Ethiopia fighting hard for its very life. Within a few years the Somalis and the Gallas would thrust into the Empire a series of raids which were to cause a widespread devastation.

Francisco Alvares was the chaplain of the Portuguese Embassy which stayed in Ethiopia for six years. His famous book which is now made available for the first time in Amharic is the only European account of pre-JIHAD Ethiopia. Of course, his limited training did not permit him to bring back an exhaustive account of conditions then prevailing in the country. Speaking of the languages spoken in the country, for instance, he hardly said anything beyond «their language». Similar limitations may be apparent in other particulars. Yet, his descriptions bear the natural curiosity and minuteness shown by other Portuguese travellers of the time when in contact with other peoples and cultures. His remarks on the fauna and flora, on the various ethnic groups, on the local churches, on the customs, on the common life, etc. are of real importance. His critical approach to facts is typical to the Western way of looking into them at this stage of the 16th century. His reliability is unquestionable. Students of Ethiopian history have always found it an invaluable source of information.

The first Portuguese edition, one of the several known versions of this book, was in 1540, just at the time when Christopher da Gama, son of Vasco da Gama, was going to the rescue of Ethiopia, then in the grip of Grañ's JIHAD. The first foreign translation (in Italian) was prepared by Giovanni Battista Ramusio.

This Amharic translation is based on the Portuguese edition of 1943. It is due to Mr. Girma Beshah and Mr. Merid Wolde Aregay, to whom sincere thanks are due.

Lisbon, 17th March, 1966.

A. DA SILVA REGO

በቄስ ዮሐንስ[1] አገር የመግባታችን ታሪክ መጀመርያ

ምዕራፍ አንድ፤ የሕንድ ጠቅላይ ገዥ በነበረው በሎፑ ስዋርሽ ቦታ ዲዮጉ ሎፕሽ ድ ስኬይራ ስለመተካቱና ይህም ማቴዎስን ምጽዋ ወደብ ድረስ ስለመሸኘቱ።

ይህን ለማተት መቻሌ እግዚአብሔር ነፍሱን ይማርና ከድዋርት ጋልቫው ጋር ስለነበርሁ ነው። ይህም የማትተው ነገር ሁሉ የተረጋገጠ ነገር ነው። ሎፑ ስዋርሽ ጠቅላይ የባሕር ኃይል አዛዥና የሕንድ ገዥ በነበረበት ጊዜ ድዋርት ጋልቫው በኮምሮን ደሴት ላይ ስለሞተ ኤምባሲው ሳይሳካ በከንቱ ቀርቶአል፤ ስለዚሁ ጉዳይ ከዚህ በፊት በሰፊው የጻፍሁ በመሆኔ በድጋሜ ማተት አስፈላጊ ስላልሆነ አሁን ዋናውን ነገር አስከትላለሁ። በሕንድ ገዥነት ማዕርግ ዲዮጉ ሎፕሽ ድ ስኬይራ በሎፑ ስዋርሽ ቦታ እንደተተካ የቀድሞው ገዥ ሊፈጽመው ያልፈቀደውን ተግባር ለማከናወን ሲል ፖርቱጋል ደርሶ የተመለሰውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትን አምባሳደር ማቴዎስን ከሐርኪኮ አጠገብ ከምትገኘው ከኢትዮጵያ ወደብ ድረስ ሸኝቶታል። በታላቅና ባማረ የመርከብ ጓድ ታጅበን በቀይ ባሕር ላይ ተጉዘን የትንሣኤ ማግሥት ሳምንት ሰኞ ዕለት ሚያዚያ 7 ቀን 1520 ዓም በምጽዋ ደሴት ደረስን። የኛ መምጣት ከአምስት ወይም ከስድስት ቀን በፊት ተሰምቶ ስለነበር በወደቡ ላይ ብዙ ሰው ተቀበለን።

የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት የሆነው የምጽዋ ደሴት ከኢትዮጵያ ግዛት ከዋናው ምድር ያንድ ወንጥፍ ውርወራ[2] ርቆ የሚገኝ ሲሆን በደሴቱ የሚገኙት እስላሞች ማናቸውንም ሃብታቸውን የሚያከማቹት በዚሁ ነው።

በማግሥቱ ማክሰኞ መርከቦቹ በምጽዋ ደሴትና በዋናው ምድር መካከል በገቡ ጊዜ አንድ ክርስቲያንና አንድ እስላም ከሐርኪኮ ወደኛ መጥተው ክርስቲያኑ ምጽዋ የንጉሠ ነገሥቱ ዜጋ የሆነው የባሕር ነጋሹ ግዛት የነበረችና ነዋሪዎቹም ክርስቲያኖች መሆናቸውን እንዲሁም የዚች ደሴትና የሐርኪኮ እስላሞች ቱርኮችና ሩሚዎች[3] ምጽዋ መምጣታችውን በመስማት ክርስቲያኖችን ያሳደዱዋቸውና እነዚህም ለማጋዝ የቻሉትን ያህል ብቻ ሃብታቸውን ይዘው ወደ ተራሮቹ የሸሹ ሲሆኑ ነገር ግን አሁን በመጡት መርከቦች ውስጥ ያሉት ክርስቲያኖች መሆናቸውን በመስማት ሊሸሹ ያልፈቀዱ መሆቸውን ገለጸልን። የባሕር ኃይል ጠቅላይ አዛዡ በናፍቆት ይጠባበቀው የነበረውን የክርስቲያኖችን ወሬ በመስማት ለእግ ዚአብሔር ምስጋና ከማቅረቡና በጉዞው ላይ ሲተክዝ ለነበረው ለማቴዎስ ደስታውን የገለጸለት ከመሆኑ በላይ ወሬውን ላመጡለት ለክርስቲያኑና ለእስላሙም ጥሩ ዓይነት ልብስ አዘዘላቸው። ይህን ወሬ ማምጣታቸው የተገባ ነገር በመሆኑ አመሰገናቸው። ሐርኮ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛትና የክርስቲያኖችም መኖርያ ስለሆነች ከዚህ ቦታ ክርስቲያኖች እንዳይሸሹ እንዲሁም ክርስቲያኖቹን (ፖርቱጊዞቹን) ወደዚህ ያመጣቸው ዋናው ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱ ወዳጅነትና እርሱንና ሕዝቡን የማገልገል ምኞት መሆኑን ገልጾላቸው መልከም ጊዜ ስለመጣላቸው ምንም ዓይነት ሥጋት እንዳይገባቸው አጽናናቸው።

ምዕራፍ ሁለት፤ የሐርኪኮ ገዥና የደብረ ቢዘን መነኩሴዎች ጠቅላይ ገዥውን ለመተዋወቅ ስለመምጣታቸው።

በማግሥቱ ረቡዕ የሐርኪኮ ገዥ በጠቅላይ ገዥው ፊት ቀርቦ ከተዋወቀ በኋላ አራት ፍሪዳዎች አበረከተ፤ ጠቅላይ ገዥውም ይህን ገጸ በረከት ከተቀበለ በኋላ እርሱም በበኩሉ በደንብ ተቀብሎ አክብሮት ውድ የሆኑ ልብሶች አበረከተው። ወደኛ እንዲመጣ

የላከው ባሕር ነጋሹ መሆኑንና ሐርኪኮም የክርስቲያኖች መኖርያ የነበረች መሆንዋን ለጠቅላይ ገዥው አስረዳው። ይህ ሰው ባማረ እጀጠባብ ላይ ቤዶም[1] ደርቦ ባማረ ፈረስ ተቀምጦ ሰላሳ ፈረሰኞችና ሁለት መቶ የሚሆኑ በእግራቸው የሚሄዱ ሰዎች አስከትሎ ነበር። ጠቅላይ ገዥው አረብኛ ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበረ ከሐርኪኮው ገዥ ጋር በዚሁ ቋንቋ ለረጅም ጊዜ ባስተርጓሚ ከተነጋገሩ በኋላ ገዥውም አጀቡም በደስታ ተመልተው ተመለሱ። ከሐርኪኮ ሰባት ወይም ስምንት ሌግዋ[2] ርቆ በሚገኘው ባንድ ትልቅ ተራራ ላይ የቢዘን ገዳም ይገኛል። ማቴዎስ ስለዚህ ገዳም በማድነቅ ሁል ጊዜ ይናገር ነበር። የኛ መምጣት በገዳሙ ተሰምቶ ስለነበር በማግሥቱ ሐሙስ ሰባት መነኩሴዎች ሊገናኙን ስለመጡ ጠቅላይ ገዥው ከጭፍሮቹ ጋር ከባሕሩ ዳር ወጥቶ መነኩሴዎቹን በደስታ ተቀበላቸው። መነኩሴዎቹም የተደሰቱ መሆናቸውን አሳይተው «ወደዚህ ወደብ ክርስቲያኖች ይመጣሉ፤ በዚያም አንድ ጉድጓድ ይምሳሉ፤ ይህ ጉድጓድ ከተማሰ በኋላ በዚያ እስላሞች አይገኙም፤» የሚል ቃል በመጽሐፋችን ውስጥ ስላለ ይህን በመጠበቅ ላይ ነን ሲሉ ይህን ትንቢትና ሌሎችንም መሰል ትንቢቶች ነገሩን። አምባሳደሩ ማቴዎስ በዚያ ይገኝ ስለነበር በአገር ወግ መሠረት መነኩሴዎቹ እጁንና ትከሻውን በመሳም ታላቅ አክበሮታቸውን ገልጸውለት አብረው ተደሰቱ። የክርስቲያኖች መምጣት ወሬ በናፍቆት ይጠበቅ ስለነበርና የኛ በወደቡ ላይ የመገኘት ወሬ ስለተሰማ እነዚህ እስከ ትንሳኤ ሳምንት በዓል ድረስ አንዳች ሥራ ሳይሠሩ ወይም ወደ ሌላ ቦታ ሳይሄዱ ከጠበቁን በኋላ የኛን ከወደቡ መድረስ እንደሰሙ ከገዳሙ አለቃ ፈቃድ ጠይቀው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ሲሉ ወደዚህ መምጣታቸውን እንዲሁም ባሕር ነጋሹም ምንም እንኳ የኛ መምጣት ቢነገረውም ከተባለው በዓል በፊት ሊመጣ አለመቻሉን ገለጹልን። መነኩሴዎቹን የመቀበሉ ስነ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ዋናው አዛዥ ሌሎቹን የመርከብ ሹማምንትና መነኩሴዎቹን አስከትሎ ወደ መርከቡ ከገባ በኋላ መነኩሴዎቹን ለሁለተኛ ጊዜ በክብር ተቀበላቸው። ከመነኩሴዎቹ መካከል መስቀል የያዙና የአገልግሎት ልብስ የለበሱ ይገኙ ስለነበር መስቀሉን አሳለሙዋቸው። ጠቅላይ ገዥው ከነርሱ ጋር ሆኖ ከያንዳንዱ በኩል በናፍቆት ይጠበቅ የነበረውን ወሬ

በደስታ ከተለዋወጡ በኋላ እንዳይበላሽ በተለይ ተከባክቦ የተያዘ ምግብ ቀርቦ መነኩሴዎቹ በሰፊው ተጋበዙ። ከዚህ በኋላ መነኩሴዎቹ ለአዳራቸው ወደ ሐርኪኮ ሄዱ።

<u>ምዕራፍ ሶስት፤ በታላቁ የምጽዋ መስጊድ ውስጥ ጠቅላይ ገዥው እንዳስቀደሰና ይህም መስጊድ ከዚያ ጊዜ በኋላ የጽንሰታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንዲባል ስለማዘዙ፥ እንዲሁም የደብረ ቢዘንን ገዳም ሰው ልኮ ስለማስጎብኘቱ።</u>

ሚያዚያ 13 ቀን ከትንሳኤ ሳምንት በኋላ አርብ ዕለት በማለዳ መነኩሴዎቹ መጥተው በባሕሩ ዳር ከቀረቡ በኋላ ጠቅላይ ገዥው ከነርሱና ከሌሎቹ የመርከብ ሹማምንት ጋር ሆኖ ወደ ምጽዋ ደሴት ሄዶ ቀኑም አርብ ስለነበር በመስጊዱ ውስጥ ለአምስቱ የክርስቶስ ቁስሎች ክብር እንዲቀደስ አዘዘ። ያ መስጊድም የጽንሰታ ማርያም እንዲባል አዞ ከዚያን ጊዜ በኋላ በየቀኑ በመስጊዱ ቅዳሴ እናደርስ ነበር። ከቅዳሴው በኋላ ወደ መርከቦቹ ስንመለስ ግማሾቹ ከማቴዎስ ጋር ሌሎቹም ከጠቅላይ ገዥው ጋር ሆነው ከሄዱ በኋላ እነርሱ አዘውትረው የሚለብሱትን ልብስ የመሰለ ወፍራም የጥጥ ጨርቅ ለራሳቸው ልዩ የሐር ጨርቅ ስዕሎችና ምርዋዎችም ለገዳሙ ተሰጣቸው። በካህናት ልምድ መሠረት መነኩሴዎቹ መስቀል በእጃቸው ይዘዋል፤ ተራው ሕዝብ ከጥቁር እንጨት የተሠሩ ትንንሽ መስቀሎች በአንገቱ አንጠልጥሎአል። ይህ መስቀል ማንጠልጠል ለኛ አዲስ ነገር ስለነበር የኛ ሰዎች እየገዙ እንደተራው ሕዝብ ባንገታቸው ያደርጉ ነበር። መነኩሴዎቹ ከኛ ጋር ከቆዩ በኋላ ወደመጡበት ሊሄዱ በተነሱ ጊዜ ስለገዳሙ ለጌታችን ለፖርቱጋል ንጉሥ ለመጻፍ እንዲቻል ቢዘንን ጎብኝተው የተጣራና የተረጋገጠ ወሬ እንዲያመጡለት አረብኛ የሚያውቀውን ፍርናው ዲያሽንና የሕንድ ግዛት ዳኛውን ሊቅ ፔሮ ጎምሽ ቴይሼራን ወደ ገዳሙ ላካቸው። ሁለቱም ሰዎች ከጉብኝታቸው ሲመለሱ የያንዳንዳቸውን

አስተያየት በመስጠት የገዳሙን ታላቅነትና መልካምነት ከገለጹ በኋላ ብዙ ምድሮችና ባሕርም አቋርጠን ከመምጣታችን በላይ የክርስትና ጠላቶች በሆኑት ብዙዎች መካከል አሳልፎ ገዳምና ስሙም የሚጠራበት የስግደት ቤቶች ካሉዋቸው ክርስቲያን ጋር ላገናኘን ለእግዚአብሔር አምላካችን ታላቅ ምስጋና ማቅረብ ይገባናል አሉ። ለጌታችን ለንጉሡ እንዲላክ በብራና የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ዳኛው ከገዳሙ አመጣ።

<u>ምዕራፍ አራት፤ የእንደራሴውና የባሕር ነጋሹ መገናኘት፤ ዶም ሩድሪጉ ድሊማ ከማቴዎስ ጋር ወደ ንጉሠ ነገሥቱ እንዲሄድ መታዘዙ።</u>

ማክሰኞ ሚያዚያ 17 ቀን ባሕር ነጋሹ ሐርኪኮ መድረሱን በመግለጽ መልእክተኛ ወደ እንደራሴው ላከ፤ ባሕርነጋሹ መርከቦቹ ወደነበሩበት ቦታ ይመጣል ብሎ በመገመት በባሕሩ ዳር ድንኳን እንዲጣል ልብስ እንዲዘጋጅ መቀመጫም እንዲሠራና ማናቸውም ነገር በሚገባ እንዲዘጋጅ እንደራሴው አዞ ሁሉም ከተከናወነ በኋለ ባሕርነጋሹ የማይመጣ መሆኑን የሚገልጽ መልእክተኛ የዚያኑ ዕለት መጣ፤ ከዚህ በኋላ አንቶኒዮ ሳልዳኛ ሐርኪኮ ሄዶ ከባሕርነጋሹ ከተነጋገረ በኋላ ባሕርነጋሹ ግማሽ መንገድ ድረስ ከመጣን እርሱም እዚያው ድረስ ሊመጣ የሚችል መሆኑን መልእክት ስላመጣ ከእንደራሴው ጋር ለመሄድ ተዘጋጅተን ግማሻችን በባሕር ግማሻችን በምድር እተባለው ቦታ ደርሰን ድንኳን ተጥሎ መቀመጫ ተዘጋጀ። በተወሰነው ቦታ አስቀድሞ የደረሰው ባሕርነጋሹ ድንኳኑ በተጣለበትና መቀመጫም በተዘጋጀበት ቦታ ሊመጣ አልፈቀደም፤ ምንም እንኳ እንደራሴው ከመርከብ ወርዶ እተባለው ቦታ ቢደርስም ባሕርነጋሹ ሊመጣ አለመፍቀዱን ስለተረዳ ድንኳኖቹን ትተው ወንበሮቹን እንዲያስጠጉ አዘዘ፤ ነገር ግን ባሕርነጋሹ አሁንም ከአጀቡ ጋር ወደዚህ ቦታ ሊመጣ አልፈቀደም። እንደራሴው ለሁለተኛ ጊዜ

አንቶኒዩ ሳልዳኛንና አምባሳደር ማቴዎስን ልኮ እነዚህ ሰዎች ሁለቱ ባለሥልጣኖች እንዲገናኙ ውለታ ተደራደሩ። ከዚህ በኋላ በዚሁ ስምምነት መሠረት ወደ አንድ ሰፊ መስክ ሄደው ምንጣፍ አስነጥፈው ተቀምጠው ንግግር ተጀመረ፤ ከብዙ ዋናዋና ጉዳዮች መካከል ስለመገናኘታቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረቡ። ባሕርነጋሹ ንግግሩን በመቀጠል ወደዚያ ወደብ ከሩቅ አገር ክርስቲያን እንደሚመጡና ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዜጎች ጋር እንደሚገናኙና ጉድጓድ እንደሚቆፍሩና እስላሞች በዚያ የማይገኙ መሆናቸውን የሚናገር ትንቢት በመጽሐፍት መጻፉን ይህንንም ትንቢት እግዚአብሔር የፈጸመው መሆኑን በማመን በሁለቱ መካከል ወዳጅነት እንዲጸናና እንዲማማሉ ጠየቀ። ለዚሁ ጉዳይ በዚያ ተዘጋጅቶ ተቀምጦ የነበረውን መስቀል በጁ ይዞ ጌታችን የሱስ ክርስቶስ የተሰቃየበት መሆኑን በሚያስታውስ በዚሁ ምልክት ምስክርነት እንዲሁም በንጉሠ ነገሥቱና በራሱም ስም በመማል ወደዚህ አገርና ወደብ የሚመጡትን እንዲሁም እርዳታ ሊሰጣቸው በሚቻልበት ቦታ ሁሉ የሚገኙትን የፖርቱጋል ንጉሥን ዜጎች ሁሉና የንብረት ሹማምንቱንም የሚረዳ መሆኑን ባሕርነጋሹ ከማረጋገጡም በላይ አምባሳደር ማቴዎስን ተቀበሎ ለወደፊት እንደራሴው ወደኢትዮጵያ የሚልካቸውን በኢትዮጵያ ግዛቶች የሚያልፉ መልእክተኞችንም ሁሉ በሚገባ የሚከባከባቸው መሆኑን በማረጋገጥ ቃሉን በመሃላ አጸና፤ እንደራሴውም በበኩሉ የፖርቱጋል ንጉሥ ዜጎች ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዜጎችና ለባሕርነጋሹም በሚገኙበት ቦታ ሁሉ አስፈላጊውን እርዳታ እንደሚሰጡ በመግለጽ ቃሉን በመሃላ አረጋገጠ። ከዚህ በኋላ የገጸበረከት መለዋወጥ ተደርጎ እንደራሴው ለባሕር ነጋሹ መሣርያዎች፤ ልብስና ጌጥ፤ ባሕርነጋሹም ለርሱ ምርጥ የሆኑ አንድ ፈረስና አንዲት ሰጋር በቅሎ ተሰጣጡ። ይህ ስነሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ሁለቱ ሰዎች በደስታ ተሰነባብተው እንደራሴው ወደ መርከቦቹ ባሕርነጋሹም ወደሐርኪኮ ሄዱ። ባሕርነጋሹ በሁለት መቶ ፈረሰኞችና ሺ እግረኞች ታጅቦ ነበር። ጉዞው በሚያስከትለው ውጤት ብዙ ተስፋ ያልነበራቸው ማቴዎስንም በአታላይነትና በሃሳዊ አምባሳደርነት በመጠርጠር አገሩ ጠረፍ አድርሰውት ለመመለስ መጥተው የነበሩት የኛ መኳንንትና ሹማምንት በእግዚአብሔር ፈቃድ የተከናወነውን ይህን

አስደሳች ዜና በመስማትና ለቅድስት ካቶሊካዊት ሃይማኖት መንገድ መከፈቱን በመረዳት እንደራሴውን ይቅርታ በመጠየቅ ወደኢትዮጵያ በአምባሳደርነት ከማቴዎስ ጋር እንዲልካቸው እያንዳንዳቸው ለመኑት።

ማናቸውንም ነገር በዓይናቸው ካዩ በኋላ ማቴዎስ በእውነት አምባሳደር መሆኑን ተረዱ። ምንም እንኳ በኢትዮጵያ የአምባሳደር ነቱን ቦታ ብዙዎች ቢለምኑም ይህን ሹመት ለመቀበል የተመረጠው ሩድሪጉ ድሊማ ነበር። ከአምባሰደሩ ጋር በሠራተኝነት እንዲሄዱ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሰዎች እንደራሴው ሾመ፤ ጊዮርጊስ ዲአብሬው፤ ሎፑ ደጋማ፤ ሊቀ ዮሐንስ የኤምባሲው ጸሐፊ፤ ዮሐንስ ጎንሳልቨሽ አስተርጓሚና የንብረት ሹም፤ አማኑኤል ድማርሽ አርጋን መች፤ ጴጥሮስ ሎፕሽ፤ መምሕር ዮሐንስ፤ የአምባሳደሩ አሽከሮች ጋስፓር ፕረይራ፤ እስጢፋኖስ ፓልያርት፤ ዮሐንስ ፍርናንድሽ፤ ሰዓሊው አልዓዛር ዲአንድራድ፤ አፎንሱ ሜንድሽና እኔ አነስተኛው ቄስ ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ። ተሰናብተን ወደታዘዝንበት ከመሄዳችን በፊት ሁላችንም በምንገኝበት እንደራሴው ትእዛዝ ሰጠ፤ «ዶም ሩድሪጉ፤ ፍራንሲሽኩ አልቫርሽን ካንተ ጋር አላክሁትም ነገር ግን አንተን ነው ከርሱ ጋር የላክሁት፤ ስለዚህ ያለርሱ ምክር አንዳች ነገር እንዳትፈጽም።» ማቴዎስን ተከትለው የነበሩ ማገሊያኝሽ፤ አልቫሬንጋና ዲዮጉ ፍርናንድሽ የተባሉ ሶስት ፖርቱጌዞችም ነበሩ።

ምዕራፍ አምስት፤ እንደራሴው ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የላከው ገጸበረከት።

የፖርቱጋል ንጉሥ በድዋርት ጋልቨው እጅ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የላከውን ገጸበረከት ሎፑ ስዋርሽ በኮችን (ሕንድ) ስለበታተነው ለሁለተኛ ጊዜ ይዘነው የመጣነው ገጸበረከት በባብኤል መንደብ መግቢያ በአራ ላይ ቅዱስ እንጦንዮስ ከተባለው መርከብ ጋር ሰጥሞአል ብሎ በማመካኘት ለይቅርታ መጠየቂያ ያሀል የያዝነው ቀጥሎ የተመለከተው ምስኪን ገጸበረከት ለንጉሠ ነገሥቱ እነዲላክ

እንደራሴው አዘዘ፤ በወርቅ የተጌጠ አንድ ጎራዴ፤ አንድ ባለወርቅ ጌጥ ሳንጃ፤ አራት የተጌጡ ጥልፍ ጨርቆች፤ የተጌጡ የደረት ጋሻዎችና አንድ የራስ ጋሽ፤ ሁለት አጫጭር መድፎች፤ አራት የጠበንጃ ማሕደሮች፤ ጥቂት የመድፍ አለሎዎች፤ ሁለት በርሜል ባሩድ፤ አንድ የዓለም ካርታና አርጋኖች። የተባሉትን ገጸበረከቶች ይዘን ከመርከብ ወጥተን ወደሐርኪኮ ተጉዘን በዚያ እንደደረስን ባሕርነጋሹን አግኝተን እጅ ከነሳን በኋላ ከዚያ ቦታ የሁለት ወንጭፍ ውርወራ ርቀት ባለው ባንድ ተራራ ጥግ ወደሚገኝ አንድ መስክ ወስደውን አንድ ፍሪዳ፤ እንጀራና ጠጅም ታዘዘልን። ከመካከል አገር ትዕዛዝ እስኪመጣልንና ለጓዛችንም ማጓጉ አጋሰስ ወይም ግመል እስኪመጣልን ድረስ በዚያው ቦታ ቆየን።

በዚያ ቦታ የደረስንበት ዕለት አርብ ነበር፤ የአገሩ ሕዝብ በኦሪት ሕግ ቅዳሜን በሐዲስ ሕግ እሁድን አጣምሮ ስለሚያከብር ሁለቱን የእረፍት ቀኖች በዚያው ቦታ ዋልን። በነዚሁ ቀኖች ማቴዎስ ከሩድሪጉ ጋር ተማክሮ ምንም እንኳ ባሕርነጋሹ ማዕርጉ ከፍ ያለ ሰው መሆኑ የማይካድ ቢሆንም ወደርሱ ከመመለስ ይልቅ ወደቢዘን ገዳም ብንሄድ የተሻለ መሣርያ የሚሰጠን መሆኑን ገልጾልን ወደተባለው ቦታ ለመሄድ ተዘጋጀን።

ይህንኑ ውሳኔ ለማስታወቅ ዶም ሩድሪግሽ ለባሕርነጋሹ መልእክተኛ ላከ፤ ባሕርነጋሹ በዚህ ውሳኔ ምንም ቅር ሳይሰኝ ትቶን ሄደ። ማናቸውም እርዳታ የሚደረግልን በርሱ ትዕዛዝ ስለነበር ስምንት ፈረሶችና ለጓዛችንም ማንሻ ሰላሳ ግመሎች ብቻ ተሰጠን። ማቴዎስን ለማስደሰት ስንል ከባሕርነጋሹ በመለየት ባደረግነው ስህተታችን ተጸጸትን።

<u>ምዕራፍ ስድስት፤ ጉዞአችንን ጀመርን፤ መርከቦቻችን ወደመጡበት ተመለሱ፤ ጉዞአችንን በጀመርንበት ቀን ባንዲት ቦታ አረፍን፤ አንድ መኮንን መጥቶ ተዋወቀን።</u>

በሐርኪኮ አቅራቢያ ከምትገኘው ካረፍንባት መስክ ሰኞ ሚያዚያ 30 ቀን ተነሳን። የኛን ወደመካከል አገር ጉዞ መጀመርና ወዴትም እንደምንሄድ ይጠብቅ የነበረው እንደራሴው እኛ ከባሕሩ መራቃችንን እንዳየ መርከቦቹን አስነስቶ እርሱም ወደመጣበት ለመመለስ ጉዞውን ጀመረ። ከዚያች ቦታ ተነሥተን ግማሽ ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ አልፎ አልፎ ውኃ በተጠራቀመበት ባንድ ደረቅ ወንዝ አጠገብ ዕረፍት አደረግን። በዚህ ቦታ ዕረፍት ያደረግነው ከወደፊታችን ስፊ በረሃ ስለነበር ድርቀቱና ሃሩሩ እንዳያጠቃን ውኃ ለመያዝ ስለሆነ እያንዳንዳችን ለየራሳችን በቅልና በቀርበታ ውኃ ያዝን። በዚህ ደረቅ ወንዝ ዳር ልዩ ልዩ ዕፅዋት ለምሳሌ የቱፋ ዛፍና ሌሎችም ፍሬ የሌላቸው ዛፎች ይገኙ ነበር። በዚህ ቦታ በእረፍታችን ላይ እንዳለን ፍሬመስቀል የተባለ አንድ መኮንን ወደኛ መጥቶ ተዋወቀን፤ ይህ ሰው ምንም እንኳ ጥቁር ቢሆን የጨዋ ልጅ ከመሆኑ ይልቅ የባሕርነጋሹ ባለቤት ወንድም ነበር። በአገር ወግ መሠረት አክብሮት ለማሳየት እንደሚደረገው ሁሉ ይህ ሰው እኛ በነበርንበት ቦታ ከመድረሱ በፊት ከበቅሎው ወርዶ ወደኛ በእግሩ መጣ። አምባሳደር ማቴዎስ የእንግዳውን መቅረብ በማየት ይህ ሰው ንብረታችንን ሊዘርፍ የመጣ ነውና መሣርያችሁን ይዛችሁ ተጠንቀቃችሁ ጠብቁት አለን። ማቴዎስ ወዲያው የራስ ጋሻውን አጥልቆ ጉራዴውን መዘዘ። ፍሬመስቀል በንደዚህ ያለ ማምለጫ በሌለበት ባልታሰበ አደጋ ላይ በመውደቁ ወደኛ ዘንድ ለመምጣት ፈቃድ እንዲሰጠው ብቻ ለመነ። ምንም እንኳ ማቴዎስ መጠራጠሩን ባይተውም ይህ ሰው በእውነተኛው በጨዋ በተማረና በሠለጠነ አኳኋን ወደኛ ቀረበ። ይህ መኮንን አንድ ማለፊያ ፈረስ አስይዞ ባነዲት ሰጋር በቅሎ ሆኖ አራት አሽከሮች አስከትሎ ነበር ወደኛ የመጣ።

ምዕራፍ ሰባት፤ በማቴዎስ ትዕዛዝ ጎዳናውን ትተን በደረቅ ወንዝ፤ በሸለቆና በተራራ ላይ ተጓዝን።

ከዚያ ቦታ ሁላችንም በዚያው ካረፉ ከሌሎች ብዙ ሰዎች ጭምር ተነሥተን ጉዞአችንን ቀጠልን። መኮንኑ በበቅሎው ተቀምጦ ፈረሱን አስከተሎ አምባሳደር ዶም ሩድሪጉ ካለበት ቦታ ተጠግቶ ባስተርጓሚ ንግግር ጀመሩ። ይህ ሰው ባነጋገሩና በጥያቄ አቀራረቡ በመልስ አሰጣጡም ብዙ የሚያውቅና የሠለጠነ መሆኑን ተረዳን፤ ማቴዎስ ግን ይህን ሰው በወንበዴነት በመጠርጠር ሊታገሰው አልቻለም።

እኛና ከኛ ጋር ያረፉት ሰዎችም ተከትለውን ያማረውንና ሰፊውን ጉዳና ይዘን ስንጓዝ ሳለን ማቴዎስ አገሩን ከማንም ይልቅ አጣርቼ የማውቀው እኔ ስለሆንኩ ልትከተሉኝ ይገባል ሲል ስላዘዘን ጎዳናውን ትተን ግመሎቻችንን እያስነዳን በጥሻ ውስጥና በተራራ ላይ መጓዝ ግድ ሆነብን። ፍሬመስቀል ከመንገድ መውጣታችንን በመረዳት ማቴዎስ ይህን ያደረገበትን ጠየቀ። ማቴዎስ ከጎዳና አውጥቶን የያዝነው እቃ እንዲጠፋና እንዲሰበር የተሁላዎች መመላለሻ በሆነ በመጥፎ መንገድ ስለመራን ሁሉም ማጉረምረም ጀመሩ።

ስለዚህ ይህን ማጉረምረምና ቁጣ በመገንዘብ እንደገና ወደመጣንበት እንድንመለስ አዞ አንዳንድ ተራሮችን ዞረን ወደቀድሞው ጎዳና አመራን፤ በዚሁ ጉዞ ላይ ማቴዎስ በድንገት በልብ ውጋት በመውደቁ በጎ እስኪሆን ድረስ ከአንድ ሰዓት በላይ ከጠበቅን በኋላ እንደገና ጉዞአችን ተጀምሮ ማቴዎስን በበቅሎ አስቀምጠን ከግራና ቀኝ በሰው አስደግፈን ፍሬመስቀልና ሁላችንም ከሁለት ሌግዋ በላይ ከተጓዝን በኋላ እንደገና በጎዳናው ገባን። በዚያም እንደደረስን ወንበዴን በመፍራት በአንድነት ወደሐርኪኮ የሚጓዙ የጭነት ግመሎችን የሚነዱ ነጋዴዎችን አገኘን። እነዚህ ነጋዴዎች የመጣንበትን መንገድ ባዩ ጊዜ ተገረሙ። በዚያው አጠገብ ውኃና ለከብቶችም ማረፊያ ቦታ ያለበት አንድ ኮረብታ አግንኝተ እኛም

ነጋዴዎቹም ሠፍረን እርስበርሳችን በመጠባበቅ አደርን። በማግሥቱ ጠዋት ከዚያ ቦታ ተነሥተን የደረቅ ወንዞች ሸለቆችን በመከተልና ተራሮችን በመዞር ጉዞአችንን ቀጠልን፤ በመንገዳችን ላይ ዘንባባና ሌሎችም ዛፎች አየን፤ ዘንባባ እስላሞች እያደረቁ እንደዘቢብ በየገበያው የሚሸጡትና ሆምጣጤም የሚሠሩበትን «ተምር» የተባለ ጣፋጭ ፍሬን የሚሰጥ ዛፍ ነው።

ያለፍንባቸው ደረቅ ወንዞችና መንገዶች ጎርፍ የሰነጣጠቃቸው ጎድጓዳ ቦዮች ይታዩባቸው ነበር፤ እንደነግሩን እነዚህ ቦዮች መንገደኞችን አላስተላልፍ በማለት እምብዛም አያስቸግሩም፤ ወደፊትም እነዚህኑ የመሳሰሉ ብዙ ቦዮች አይተን ነበር፤ እነዚህ ቦዮች በሞሉ ጊዜ መንገደኞች ሁለት ሰዓት ያህል ይጠብቁና ሲጎድሉላቸው ተሻግረው መንገዳቸውን እንደገና ይጀምራሉ። እነዚህ ወንዞች ከተራሮቹ ወጥተው ወደሜዳው ሲደርሱ ባክነው ያልቃሉ። የኢትዮጵያ ወንዞች በባሕር ጠረፍ ሲደርሱ በአሸዋ ተመጠው ይቀራሉ እንጂ ወደቀይ ባሕር የሚገቡ ከቶ የሉም። በየተራሮቹ ልዩልዩ የዱር አራዊት ማለት፤ አንበሳ፤ ዝሆን፤ ነብር፤ አነር፤ ተሁላ፤ ከርከሮና አጋዘን፤ ምጥማጥና ሌሎችም ልዩልዩ በዓለም ላይ የሚገኙ እንስሶች ሁሉ አሉ። ነገር ግን በዚህ አገር ያላየኋቸውና መኖራቸውንም ያልሰማሁ ሁለት እንስሶች ድብና ጥንቸል ናቸው። በዓለም ያሉት አእዋፍ ሁሉ ከዚህ በፊት ያየናቸውና ያላየናቸውም በዚህ አገር ይገኛሉ፤ «ፔጋና ኩኩ» ግን አላየሁም መኖራቸውንም ሲያወሩ አልሰማሁም። ተራሮቹና የወንዞቹ ዳርቻች ሽታው በሚጣፍጥ ሰርዶ ተሸፍነዋል።

ምዕራፍ ስምንት፤ ማቴዎስ እንደገና ከጎዳናው አውጥቶ ወደደብረቢዘን ገዳም መራን።

ምንም እንኳ ጊዜው የእረፍት ማድረጊያችን ቢሆንም ከአውራው ጎዳና ወጥተን ባቋራጭ ወደቢዘን ገዳም እንድንሄድ ማቴዎስ ስለፈቀደ መንገድ ወደሌለበት ወደጥሻና የሚያስፈራራ ገደል

ሊመራን ቆረጠ፤ የመንገዱን አስጊነት በመረዳት ፍሬመስቀልን ሃሳብ ጠየቅነው፤ መንገዱ ጓዛችሁን ተሸክመው ለሚጓዙ ሰዎች ከቶ የማይገፋና የማያዋጣ ነው ሲል ገለጸልን። የክርስቲያንና የእስላም ነጋዴዎች ከነጭነታቸው የሚመላለሱበትን ያን ትተነው የመጣነውን ጎዳና ተከትለን ብንሄድ ምንም ስጋት የማያገኘንና ይልቁንም የእግዚአብሔርንና የንጉሥ ነገሥቱን አገልግሎት ለማከናወን የምንጓዝ ሰዎች በመሆናችን ማንም ሊቃጣብን የማይደፍር መሆኑንም አስገነዘበን። የሆነሆኖ የማቴዎስን ምኞትና ፍላጎት ለመፈጸም ስንል ተከትለነው ተጉዘን በእረፍት ቦታ እንደሠፈርን ወደኋላ እንመለስ ወይም ወደፊት እንቀጥል የሚል ትልቅ ክርክር በማካከላችን ተነሣ። ማቴዎስ ይህን በመረዳት ወደኔ ዘንድ ቀርቦ ስለገዳሙ ከፍ ያለ ግምት ስላለው መንገዳችንን እንድንቀጥልና በዚያም ከስድስትና ሰባት ቀኖች በላይ የማንቆይ መሆናችንን አሳስቦኝ ይህንኑ በማስረዳት አምባሳደር ሩድሪጉንና ሌሎቹንም እንድለምንለት ጠየቀኝ። (ማቴዎስ በገዳሙ እንደደረስን ሞተ።) ንብረቱ ባለበት ቦታ ደርሶ የግል ጉዳዩን አከናውኖ ከተወሰነው ቀን በኋላ መንገዳችንን እንድንቀጥል የሚፈቅድልን መሆኑን ገለጸልን። ስለዚህ ይህንኑ በመግለጽና በተለይም እዚያ እንደደረስን ባንዲት መንደር የምናርፍ መሆናችንን አስረድቼ በኔ ልመና የማቴዎስን ምኞት ለመፈጸም መንገዳችንን ወደገዳሙ ቀጠልን። ከደረስንበት ቦታ በማግሥቱ ተነሥተን ከዚያ በፊት ካጋጠሙን በባሱ ደረቅ ወንዞች ገደላም መንገዶችና በጫካ ውስጥ አድርገን መንገዳችንን ቀጠልን፤ በመንገዱ መጥፎነት ምክንያት በቅሎዎቻችንን ባዶዋቸውን እየነዳን በእግራችን ተጓዝን። ግመሎቻችን አንዳች ነገር ያስፈራራቸው ይመስል መጮህ ጀመሩ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ እንጂ ከማንም ጋር ሊነጋገሩበት በማይቻል በዚያ በሚያስፈራራ ቦታ በመድረሳችን ማቴዎስ ሊያስ ገድለን እንጂ በደህናውስ አላመጣንም በማለት ወደዚህ እንዲመጡ የለመንኋቸው እኔ በመሆኔ የኛ ሰዎች በኔ ማጉረምረም ጀመሩ። ያ ቦታ ወንበዴዎች በቀን የሚሸምቁበትና ቁጥራቸው የበዛ አራዊትም ያለ ፍረሃት የሚዝና ኑበት ነበር። የሆነሆኖ ጉዞአችንን ወደፊት ቀጠልንና የማሽላ እርሻዎችን የሚጠብቁና በየተራሮቹ መካከል የሚገኙትን ድንጋያም ምድሮች እየቆፈሩ የሚዘሩም ገበሬዎችን አየን። በየመስኩ ላይ ማለፊያ የቀንድ ከብቶችና ፍየሎች ይታዩ ነበር፤ ያገሬው ሕዝብ ክርስቲያን ነው፤ ወንዶቹ በጣም የተራቆቱ ስለሆኑ ሰውነታቸው በሙሉ ይታይ ነበር፤ ሴቶቹ ግን ከወንዶቹ ባለባበሳቸው የተሻሉ ናቸው፤ያገሩ ሕዝብ የቆዳው ቀለም ጥቁር ነው። ወደፊታችን ጥቂት እልፍ ብለን ግመሎቻችንን እራግፈን ባረፍንበት ባንድ ጨካ እንደደረስን ስድስት ወይም ሰባት የሚሆኑ ከነርሱም አራቱ ወይም አምስቱ በጣም የሸመገሉ መነኩሴዎች ወደኛ መጡ፤ እነዚህ መነኩሴዎች በጣም የሚያከብሩትና እጁንም የሚስሙት አንድ እጅግ የሸመገል መነኩሴ በመካከላቸው ይገኝ ነበር። ይህ ሰው አቡን ነው ሲል ማቴዎስ ስላስጠነቀቀን እኛም ሌሎቹ መነኩሴዎች እነዳደረጉት ሁሉ እጁን ሳምነው፤ ነገር ግን አንድ ዳኛ እንጂ አቡን አለመሆኑን በኋላ ተረዳን። በማዕርጉ ከዚህ ሰው በላይ የሆነ በገዳሙ የነበረ መሆኑን አወቅን። የገዳሙ መነኩሴዎች ከሲታዎች እንደእንጨት የደረቁና የሸመገሉም ስለነበሩ መጀመርያ ላያቸው ሰው የቅዱሳንን መልክ ያስታውሳሉ። በገዳሙ አቅራቢያ ባሉት ተራራዎች ጫካዎች የሚገኙትን ምድሮች የሚያርሱት ገበሬዎች ለገዳሙ የሚከፍሉትን ግብርና መነኩሴዎቹ ራሳቸው የሚዘሩትን እህል ለመሰብሰብ በየእርሻው ይዞራሉ። መነኩሴዎቹ ጫማ አያደርጉም፤ ልብሳቸውም ወይባ የተነከረ አሮጌ የጥጥ ጨርቅ ነው። ካረፍንበት ቦታ እሩብ ሌግዋ ያህል ወደፊት እልፍ እንዳልን እኛና ማቴዎስ ፍሬመስቀልና መነኩሴዎቹ ከነጓዛችን አንድ ዛፍ አጠገብ እንደደረስን ከመነኩሴዎቹ አንዱ ማቴዎስ አቡን ነው ሲል ያስተዋወቀን ሽማግሌ መነኩሴ አንድ ፍሪዳ አዞልን ያን አርደን እራታችንን በላን። ከእራት በኋላ የምንሄድበትን ስላላወቅን ሁላችንም ማለት አምባሳደሮቹ፤ መነኩሴዎቹና ፍሬመስቀልም በተባለው ቦታ አደርን።

ምዕራፍ ዘጠኝ፤ በዚህ ቦታ አስቀደስን፤ ፍሬመስቀል ከኛ ተለየ፤ ወደአንድ ገዳም ሄደን በዚያ እንደደረስን የኛ ሰዎች ታመሙብን።

በማግሥቱ የቅድስት መስቀል ዘግንቦት በዓል የሚከበርበት ቀን ስለነበር ባንድ ዛፍ ሥር ሆነን ለቅድስት መስቀል ክብር ቅዳሴ በማቅረብ አምላካችን ለቅድስት ሐና መንገዱን እንደከፈተላት ሁሉ ዙርያው ገደል ለሆነብን ለኛም የደህንነታችንን መንገድ እንዲከፍትልን በመለመን የኛ ፖርቱጌዞች ሁሉ እንዲጸልዩ ለመንናቸው። ከቅዳሴው በኋላ ምሳ በላንና ማቴዎስ ጓዙን በሰው አሸክሞ በቅዱስ ሚካኤል ስም በምትጠራው ወደዲቤ ገዳም ሄደ። መንገዱ መጥፎ ስለነበር የአምባሳደሩ ጸሐፊ ሊቅ ዮሐንስና እኔ ዕቃውን የተሸከሙትን ሰዎች ተከትለን በእግራችን ወደገዳሙ ሄድን፤ የሄድንበት ምክንያት ወደፊት ለመሄድ ወይም ወደኋላ መመለስ ያስፈልገን እንደሆነ አጣረቶ ለማወቅ ነበር። በዚህ ጊዜ ፍሬመስቀል ተሰናብቶን ከኛ ተለየ። ያን ገደልና ዳገት መንገድ ሙቀቱንም በመከራ አልፈን በገዳሙ በደረስን ጊዜ ጸሐፊውና እኔ ከድካማችን ብዛት ከሞት አፋፍ ደርሰን ነበር።

ጥቂት ካረፍንና ገዳሙን ካየን በኋላ በዚያ ቦታ ለጓዛችንና ለኛ ማረፊያ ቦታ ስለነበር ጓደኞቻችንን ለመጥራት ጸሐፊው ወደ ኋላ ሲመለስ እኔ ግን በዚያው ቀርቼ በመጠበቅ ቆየሁ።

በማግሥቱ ግንቦት 4 ቀን ጓደኞቻችንና ጓዛችንም በሙሉ በሰው ሸክም ሆኖ እኔ ወደአደርሁት ቦታ መጡ። በዚያ ቦታ ባደር ንባት ሌሊት አምባሳደሩ ንጉሣችንንና እግዚአብሔርን ለማገልገል ለራሳችንም ደህንነትና ክብር የሚያደርገውን ተግባር የሚቃወም አምባጓሮ በመካከላችን ተነሣ፤ወዲያውኑ ከሰዎቻችን አንዱ ብድግ ብሎ «በመካከላችን የግል ሃሳባቸውን እንጂ ተስማሚ የሆነውን ሃሳብ ሊከተሉ የማይፈቅዱ ሰዎች አሉ» ሲል እንዳበቃ ጦር መወራወር ተጀመረ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን አንድም ሰው አል ቆሰለም። በዚህ ጊዜ እኔ በጉዳዩ ገብቼ አምባሳደሩ አለቃችን መሆኑን

አሳስቤ፤ ለእግዚአብሔርና ለንጉሣችን አገልግሎት የተደረገ ነገር ሁሉ ለራሳችን ጥቅም መሆኑን አስገነዘብሁ፤ እንዲሁም ለወደፊቱ ማናቸውም ነገር በደንብ ሳይመከርበት እንዳይፈጸም አስጠንቅቄ ጥለኞቹን አስታረቅሁዋቸው።

በቅዱስ ሚካኤል ገዳም እንደደረስነ አንድ መልካም ቤት ተሰጥቶን ማቴዎስ በነገረን መሠረት ከሰባት ወይም ከስምንት ቀኖች በኋለ እንድንሄድ ተስፋ በማድረግ መልካም ምግብ እየተ ሰጠን በዚያች ቤት አረፍን። በዚያ እንደነበርን ማቴዎስ ወደኛ መጥቶ ለቤተ መንግሥቱና ለእቴጌ እሌኒ ለአቡኑም በቅሎ በመለመን ደብዳቤ የጻፈ መሆኑን ገልጾልን መልሱም እስኪመጣ ድረስ በትንሹ አርባ ቀን መጠበቅ አስፈላጊ ነው ሲል ነገረን። ከዚህም በላይ የክረምቱ ወራት ስለተቃረበ ለሶስት ወር ክረምት በቂ ስንቅ ሳንይዝ ልንጓዝ የማይቻል መሆኑን ገለጸልን። ከዚህም ሌላ አስፈላጊውን እርዳታ ሊሰጠን የሚችለው የገዳሙ አቡን ስለሆነ እርሱ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ የሚገባን መሆኑን አስታወቀን፤ ይህ አቡን የሚለው ሰው የገዳሙ ሃላፊ መነኩሴ እንጂ በእውነቱ አቡን አልነበረም።

ስለገዳሙ ሃላፊ መምጣትና በክረምቱ ወራት ማለት በሰኔ፤ ሐምሌ፤ ነሐሴና መስከረም አጋማሽ ካንድ ቦታ ወደሌላው መንቀሳቀስ የማይቻል መሆኑን ማቴዎስ የገለጸልንን የገዳሙ መነኩሴዎችም አረጋገጡልን፤ የገዳሙም ሃላፊ ሳይዘገይ ደረሰ። በዚያ ቦታ ደርሰን ጥቂት ቀኖች እንደቆየን የኛ ሰዎች ማለት ፖርቱጌዞቹና አገልጋዮ ቻችንም በደም ተቅማጥ ደዌ ክፉኛ ታመውብን አንዳንዶቹም ሲደክሙ ልሎቹም በጎ መሆን ሲጀምሩ ሐኪማችን መምሕር ዮሐንስም ይህንኑ በመሰለ ደዌ ስለታመመብን ሕክምናው ተቋረጠብን።ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ሁልጊዜ ከኛ ጋር ስለነበር፤ ያላንዳች ሕክምና ሰዎቻችን ሁሉ ድነው በመካከላችን ጤና ነግሦ ሳለ በፊታችን የነበሩት ሌሎች ሰዎች መታመም ጀመሩ፤ ከነርሱም አንዱ አምባ ሳደር ማቴዎስ ነበር። አስፈላጊው መድኃኒት ከተደረገለት በኋላ ማቴዎስም በጎ ሆኖ ተነሣና ጓዙን አሸክሞ በሚካኤልና በቢዘን

ገዳሞች መካከል በደምትገኘው የቢዘን መነኩሴዎች ከብቶቻቸውን በሚያሰማሩባት ብዙ ጥሩ ቤቶች ወደሚገኙባት ገንጋርጋራ[1] ወደምትባል መንደር ሄደ።ማናቸውንም ሃብቱን ወደዚያች ቦታ እንዳስወሰደ ሕመሙ ስላገረሸበት ከሁለት ቀን በኋላ ወደኛ መልእክተኛ ልኮ መምሕር ዮሐንስ መጥቶ እንዲያክመው ጠየቀ፤ ይህም ሌሎቹን በሽተኞች ሁሉ ትቶ ወደ ማቴዎስ ከመሄዱ በላይ፤ አምባሳደር ሩድሪጉና እኔም አብረን ሄደን በሽተኛው በእውነት መታመሙን ተረዳን። አምባሳደር ሩድሪጉ ወደኛ ሰዎች ሲመለስ እኔ በሽተኛውን ለማናዘዝና ለማቁረብ ሶስት ቀን በዚያ ቆየሁ፤ማቴዎስ በኑዛዜ አባቱ በመምሕር ፍራንሲሽኩ አማካይነት ኑዛዜውን በፖርቱጌዝ ቋንቋና በአገሩም ቋንቋ ከገዳሙ መነኩሴዎች ላንዱ ከሰጠ በኋላ ግንቦት 23 ቀን 1520 ዓም አረፈ።የመሞቱ ወሬ እንደተሰማ በቶሎ አምባሳደሩና ጊዮርጊስ ዲ አብሬው የአምባሳደሩ ጸሐፊ ሊቅ ዮሐንስም እንዲሁም ብዙዎች የገዳሙ መነኩሴዎችም ወደዚያ መጥተው የቀብሩን ስነሥርዐት ለማስፈጸም አስከሬኑን ተከትለን ደብረቢዘን ገዳም ከሄድን በኋላ የፍትሃቱ ሥርዐት በኛና በአገሩ ወግ ተፈጽሞ በዚያው በክብር ተቀበረ።

ማቴዎስ በሞተበት ሌሊት የአምባሳደሩ ጸሐፊ ፕሬይራም ሞተ። የማቴዎስ ቀብር ከተፈጸመ በኋላ አምባሳደር ሩድሪጉና ጊዮርጊስ ዲአብሬው የአምባሳደሩ ጸሐፊ ሊቅ ዮሐንስም እንዲሁም አንዳንድ የገዳሙ መነኩሴዎች በፍራንሲሽኩ ማቴዎስ እጅ የሚገኘውን የሙዋቹን ሃብት ዝርዝር ለማውጣት ማቴዎስ ወደሞተባት ወደዚያች መንደር ተመለሱ፤ ፍራንሲሽኩ ማቴዎስ በፖርቱጋል ንጉሥ መልካም ፈቃድ አርነት ከመውጣቱና ለማቴዎስ ከመሰጠቱ በፊት በባርነት የሚኖር ባርያ ነበር።ሃብቱን ለመካፈል ተስፋ ያደርጉ የነበሩት መነኩሴዎችና ፍራንሲሽኩ ማቴዎስም ዝርዝር እንዳይወጣ መቃወማቸውን በማየት አምባሳደር ሩድሪጉ ወደኛ ሰዎች ተመለሰ፤ ከዚህ በኋላ ፍራንሲስኩና መነኩሴዎቹ የሙዋቹን ሃብት በሙሉ አስይዘው ወደ ገዳሙ ሄደው ከዚያም በሙዋቹ ኑዛዜ መሠረት ዕቃውን ለእቴጌ እሌኒ ለማስረከብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሄዱ።

ምዕራፍ አሥር፤ ዶም ሩድሪጉ ለጉዞው የሚያስፈልገውን እርዳታ በመጠየቅ ለባሕር ነጋሹ መልእክት ላከ።

በዚህ ቦታ ያላንዳች ተስፋ አንድ ወር ሙሉ በመቆየታችንና ማቴዎስም በመሞቱ ስለጉዞዋችን ምን ማድረግ እንደሚገባን ለማወቅ ስላልተቻለ በዚያ ቦታ ተረስተን እንዳንቀር ለጉዞአችን የሚያስፈልገውን እርዳታ እንዲሰጠን በመጠየቅ ባሕርነጋሹን ልንልክበት ስንሰናዳ የገዳሙ መነኩሴዎች ይህን ውሳኔ ሰምተው በጣም በማዘናቸው ወደ ዶም ሩድሪጉ መጥተው የተባለውን መልእክት ወደባሕርነጋሹ እንዳይልክ ለመኑት። የገዳሙ ሃላፊ መነኩሴም ከአሥር ቀን በኋላ የሚመጣ መሆኑን ሲያረጋግጡ፤ ነገር ግን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልመጣም አስፈላጊውን እርዳታ እነርሱ የሚሰጡን መሆናቸውን ገለጹለት።ምንም እንኳ አምባሳደሩ ቃሉን ቢሰጣቸውም መነኩሴዎቹ በጣም ተጠራጣሪዎች ስለነበሩ ሊያምኑት አልቻሉም ነበር፤ ስለዚህ አሥር ቀን የምንቆይ መሆናችንን ለማረጋገጥ መስቀል አስይዘው እያንዳንዳችንን አስማሉን።እነርሱም ከአሥር ቀን በላይ የማያቆዩን መሆናቸውን ቃላቸውን በመሃላና በመስቀል ምልክት አጸደቁልን።

ምንም እንኳ መነኩሴዎቹ ይህን ተስፋ ቢሰጡንም ከሁለት ያጡ ሆነን በከንቱ እንዳንቀር የሚበጀውን ነገር አሁኑኑ መምረጥ በጎ ነገር መሆኑን በመገንዘብ፤ ባሕርነጋሹ ከእንደራሴው ጋር በሐርኪኮ አቅራቢያ ተገናኝቶ የፖርቱጋልን ንጉሥ ንብረትና ዜጎች ሁሉ በማናቸውም ቦታ የሚጠብቅ መሆኑን በማረጋገጥ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ለጉዞአችን አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያደርግልን በመለመን ዮሐንስ ጎንሳልቭሽ የተባለውን አስተርጓሚና የንብረት ሹሙን አማኑኤል ድማርሽን ሌሎችንም ሁለት ፖርቱጌዞች አምባሳደሩ ላከ።መልእክተኞቹ ከሄዱ ከአሥር ቀን በኋላ ባሕርነጋሹ ለጓዛችን ማጓጓዣ በሮችና ለኛም በቅሎዎች ሊያዝልን የሚመጣ መሆኑን በመግለጽ የንብረት ሹሙ አብረውት ከተጓዙት ፖርቱጌዞች አንዱንና ሌላም አንድ የባሕር ነጋሹን ጭፍራ ላከብን።

ምዕራፍ አስራ አንድ፤ የገዳሞቹ ዓይነት ሁኔታና አቀማመጥ፤ የቅዱስ ሚካኤል ገዳም።

ገዳሞቹ ሁሉ የተቆረቆሩት በኮረብታ ወይም በጎድጓዳ ቦታ ነው። የቅዱስ ሚካኤል ገዳም የተቆረቆረው ባንድ ትልቅ ቁሊልታ ግርጌ ባለ ሊወጣበት በማይቻል ባንድ የሚያስፈራ ታላቅ ቋጥኝ ላይ ነው። ይህ የድንጋይ ክምር በፖርቱጋል ወደብ ላይ የሚገኘውን ድንጋይ ይመስላል። በዚህ ቋጥኝ አካባቢ የሚገኘው ቦታ በውስጡ ጣር የበቀለበት የወይራና የልዩልዩ ዛፎች ጫካ ነው። በዚህ ጫካ ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ዛፎች ከዚህ በፊት አይተናቸው የማናውቅና ፍሬም የሌላቸው ናቸው። የገዳሞቹ እርሻዎች በሚገኙባቸው ጠባብ ሽለቆዎች ውስጥ ብርቱካን፤ ሎሚ፤ ትርንጎ፤ ቱፋ፤ በለስና ኮክ፤ እንዲሁም በፖርቱጋልና በሕንድ እንዳየነው ሁሉ ጭብጥ ጎመን፤ የመድኃኒት ቅጠላቅጠሎችና ሌሎችም ልዩልዩ እጽዋት አሉ፤ ምንም እንኳ መሬቱ የዘሩበትንና የተከሉበትንም ሁሉ የሚያበቅል ቢሆንም ምድሩ የሚሰጠው ሃብት በሚገባ በጥቅም አልዋለም።በደንብ ቢሠራ ኖሮ በይበልጥ ሊሰጥ ይችል ነበር።

የገዳሙ ቤተ ክርስቲያን በአሠራሩ የኛን ቤተ ክርስቲያን ይመስላል፤ ልክ እንደኛዎቹ እንዚህም ማህሌትና አንድ ዋና ሁለት አቋራጭ በጠቅላላው ሶስት በሮች አሉዋቸው። ቤተ ክርስቲያኖች የተከደኑት በሰንበሌጥ ነው፤ ይህ ክዳን ሳያፈስ ያንድ ሰው ዕድሜ ይቆያል። ጣርያዎቹ በሚገባ የተሠሩና ቅስቶቹም በደንብ የተሸፈኑ ስለሆኑ ልክ የኛን ቤተ ክርስቲያኖች ጣርያዎች ይመስላሉ፤ሁሉም በቅስት የተደገፉ ይመስላሉ። የታቦቱ መንበር ያለበት ቦታ ከዳር እስከዳር በመጋረጃ ተሸፍኖአል፤በግራና ቀኝ የሚገኙ በሮቹም ፊትለፊት በሐር መጋረጃ ተጋርደዋል።እነዚህ መጋረጃዎች በመካከልና በግድግ ዳዎቹ ጥግ እያንዳንዳቸው ሶስት መካፈቻ አላቸው። በየመካፈቻዎቹ ላይ ከመጋረጃው ገመድ ላይ ትንንሽ ቃጭሎች ተንጠልጥለዋል፤ ስለዚህ ሰው በገባና በወጣ ቁጥር የነዚህ ቃጭሎች ድምጽ ይሰማ። በቤተ ክርስቲያኖቹ ቅድስተ ቅድስታት ውስጥ አንድ መሠውያ አለ፤ ይህ መሠውያ ቅዱስ መንበሩ በሚያርፍባቸው አራት አውታሮች ድረስ ይደርሳል። ታቦቱ የሚቀመጥበት ይህ መንበር ለብቻው ጣርያ ተሠርቶለታል፤ ከታቦቱ ዘንድ ጥቂቅ ጎድጎድ ያለ አንድ ትልቅ የነሃስ ጻሕል አለ። ይህ ጻሕልም በአራት በኩል በሚገኙት በወንበሩ አውታሮች ይደርሳል። በዚህ በትልቅ ጻሕል ውስጥ ሌላ ትንንሽ ጻሕል ተቀምጦአል። ይህ መንበርና መሠውያም ከፊትለፊት ብቻ ግልጽ ሲሆን በግራና ቀኝ በስተኋላም በሚንዘረፈፍ መጋረጎ ተጋረዶአል። በመሠውያው ዙርያ ለመሄድ ይቻላል።

ደወሎቹ ከድንጋይ የተሠሩ ናቸው፤ ቀጭን ረጅም ድንጋይ በገመድ አስረው ያንጠለጥሉና ከዚሁ በተሠራ የቡና ዘነዘና በመሰለ እንጨት ሲመቱት የሰባራ ደወል ጩኸት የመሰለ ከሩቅ የሚሰማ ድምጽ ይሰጣል። በአውድ ዓመት ቀን የመቅደሱን ጻሕል ያወጡና በትንሽ እንጨት በመምታት የዋናውን ደወል ድምጽ እንዲያግዝ ያደር ጋሉ። ከዚህም በላይ የብረት ደወል አላቸው፤ ይህ ደወል በግራና ቀኝ የቆመ ሁለት ብረት ሲሆን አንድ ሌላ ብረት በመካከሉ አግብተው ወዲያ ወዲህ ሲያጋጩት ጠጣር ምድር በአካፋ ሲቆፈር የሚሰጠውን ድምጽ ይመስለል። ቀሳውስቱ ታቦቱን ይዘው ሲጓዙ በዓመት በዓልም ቀን በእጃቸው ይዘው የሚመቱት በአሠራሩ መልከቢስ የሆነ ምርዋ አላቸው፤ በተራው ቀን የሚደውሉት የእንጭቱንና የብረቱን ደዎሎች ነው።ከጥዋት ጸሎት ማድረሻ ጊዜ ሁለት ሰዓት ቀደም ብለው የየቤተ ክርስቲያኖችና የየገዳሞቹ ሁሉ ደወሎች ይደወሉና ካህናቱ ጸሎት ለማድረግ ይነሣሉ፤በመብራት ወይም በኩራዝ ካልሆነ በስተቀር ጸሎታቸውን በጨለማው ውስጥ ሆነው በቃል ነው የሚያደርሱት። የመብራት ቅብአኑግ ስለሌላቸው በዚህ ፈንታ በኩራዛቸው ቅቤ ጨምረው ያነዳሉ፤ ጸሎታቸውን የሚያደርሱትና የሚቀድሱትም በከ ፍተኛና ጣዕም በሌለው ድምጽ ነው።በመካከሉም ቅኔ አያነቡም፤ ቅዳሴአቸው አንድ ዘርፍ ወይም ግጥም ያለው ሁሉም ባንድነት የሚከተሉት ነው። በተራው ቀን ለጸሎታቸው ዳዊት ይደግማሉ፤ በዓመት በዓል ቀን ግን ከዳወት ሌላ በተለይ ለበዓሉ የሚስማማ ስድ ንባብ በቃል ያነባሉ። ጸሎታቸውን በቤተ ክርስቲያኑ ቁመው ያደርሳሉ።ቅዳሴውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከቅዱሳት መጻሕፍት

ጥቅስ የሚያነቡት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አንድ ቄስ ወይም መነኩሴ ከዋናው በር ፊትለፊት በችኮላና በሚያነበንብ ከፍ ባለ ድምጽ ያነባል።ቅዳሜና እሁድ ወይም በበዓል ቀን ከንባቡ በኋላ ቀሳውስቱ አራት ወይም አምስት የናዝራዊ መስቀሎችን እስይዘው ከቤተ ክርስቲያኑ ውጭ ይወጣሉ፤ መስቀል ያዦችም መስቀላቸውን በግራ እጃቸው እንደ ምርኩዝ ይዘው በቀኝ እጃቸው ጽና ስለሚይዙ የመስቀሎቹና የጽናዎቹ ቁጥር ሁልጊዜ እኩል ነው። ቀሳውስቱ በአገልግሎት ላይ እንዳሉ የሚለብሱት የክህነት ልብስ ከመናኛ ሐር የተሠራ ካባ ነው። የዚህ ካባ ጨርቅ ስፋት ከዱማስ ወይም ከሌላ ሐር ጨርቅ ሳይበልጥ ከላይ እስከታች ባንድ ስፋት ይወርዳል። ከካባው ጨርቅ ከማይመሳሰሉ ከሌሎች ጨርቆች የተቆረጡ መስቀሎች ከካባው ደረትና በግራና በቀኝም ተሰፍተዋል። ከካባው ጨርቅ አንድ ኮቫዶ ርዝመት ያለው ክፍል በመሬት ይንዘረፈፋል። ስነሥርዓቱን የሚፈጽሙት በማህሌቱ ውስጥ ነው። ይህን ካደረጉ በኋላ ቅዳሜና እሁድ በዓመት በዓልም ቀን ሰሞነኛው ቄስ ከሁለት ሌሎች ካህናት ጋር ከመቅደሱ ውስጥ ገብቶ በጥንታዊ ጌጥ በተቀረጸ ኮርኒስ ውስጥ የሚገኘውን የምስለ ፍቁር ወልዳን ስዕል ያመጣል፤ የእመቤታችን ስዕል በየገዳሞቹና በየቤተ ክርስቲያኖቹ ሁሉ ይገኛል።

ቅዳሴውን የሚጀምረው ቄስ ፊቱን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዋና በር መልሶ በመተላለፊያው መስቀልኛ ቦታ በመስቀል ያገዙ አጠገብ ቁሞ የእመቤታችንን ስዕል በደረቱ ላይ ይዞ ዜማውን ይጀምራል፤ በጎኑ የሚቆሙት ሌሎች ካህናት የጥዋፍ መብራት ይይዛሉ። ከዚህ በኋላ ካህናቱ ሁሉ ሽኮታ[1] የሚጨፍሩ ይመስል ባንድነት እየወረቡና እያሸበሸቡ ያልፋሉ። በእመቤታችን ስዕል ዙርያ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲዞሩ በሚያዜሙበት ጊዜ ምርዋና ከበሮ ይመታል።

በእመቤታችን ስዕል አጠገብ ባለፉ ቁጥር እየተሳለሙ ይሄዳሉ፤ ይህ ተግባር ለአምላክ የተደረግ ስለሆነ በእውነተኛው መልካምና በጎም ነገር ነው። በዚሁም ቀን መስቀልና ጽናም ይዘው ይጓዛሉ። ይህ ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ስነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ስዕሉን ያኖሩና በወንጌሉ በኩል ማለት በስተሰሜን በኩል በሚገኝ

የቁርባኑ ሕብስት በሚዘጋጅበት በቤተልሄሙ ይገባሉ። በዚያኑ ጊዜ የተዘጋጀውን የነጭ ስንዴ ሕብስት አስይዘው መስቀል ይዘው ምርዋ እየመቱ ከቤተልሄሙ ይወጣሉ፤ በገዳሙ ውስጥ ያሉት ሰዎች ቁጥር ጥቂት ስለሆነ ሥጋ ወደሙን የሚያዘጋጁት በልኩ ነው።በሌሎች ቤተ ክርስቲያኖችና ገዳሞች ብዙ ሰዎች ስላሉና ቤተ ክርስቲያን ሳሚዎቹ በሙሉ ስለሚቆርቡ ሥጋ ወደሙ በርከት ብሎ ነው የሚዘጋጀው፤ ሕብስቱ ሰፋ ብሎ የተጋገረ ሲሆን ውፍረቱም በአንድ ወይም በሁለት የጣት እንጓ ወይም ከዚህ በላይ የሚገመት ነው። ይህን ማቁረቢያ በመሠውያው ላይ ከተቀመጡት በአንዱ ሳህን ላይ አኑረው በጨርቅ በመሸፈን ምርዋ እየመቱና መስቀልም ይዘው ይመጣሉ።

በቤተ ክርስቲያኑ መቅደስ ውስጥ ለመግባት የተፈቀደላቸው ሥልጣን ያላቸው ቄሶች ብቻ ሲሆኑ ምዕመናኑ በዋናው በር አጠገብ ባለው በቅኔ ማህሌቱ ይገባሉ። ይህንየ መሰለው አከመፈል በቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ ይገኛል። በቅኔ ማህሌቱ ውስጥ ማንም ሊገባ ይፈቀድለታል። ቄሶቹ ሥጋ ወደሙን ይዘው ምርዋ እየመቱ በምእመናኑ ፊት በሚያልፉበት ጊዜ በዚያ የሚገኙት ሰዎች ሁሉ የምርዋው ድምጽ እስኪያበቃ ድረስ በጉልበታቸው ላይ ሆነው ግንባራቸውን በምድር ላይ ያሳርፋሉ። የምርዋው ድምጽ የሚያበቃው ሥጋ ወደሙ የመጣበት ሳህን በታላቁ ሳህን ውስጥ ተቀምጦ በጥቁር ጭርቅ ተሸፍኖ በመሠውያው ላይ ከተቀመጠ በኋላ ነው። በዚህ ገዳምና በሌሎች ሃብታም ቤተ ክርስቲያኖች የብር ጽዋ ይገኛል፤ እንዲያውም አንዳንዶቹ ከወርቅ የተሠራ አላቸው፤ «የባለጌ» ቤተ ክርስቲያኖች በሚባሉ የገበሬዎች ቤተ ክርስቲያኖች ግን ጽዋቸው ከመዳብ የተሠራ ሲሆን ሳህኖቻቸውም መልክና ቅጥ የሌላቸው ትልልቅ ነገሮች ናቸው። ቆራቢዎቹ ሥጋውን በሚበሉበት ጊዜ ደሙን መጠጣት ስላለባቸው በርከት ብሎ የተዘጋጀ የወይን ጭማቂ በጽዋ ይቀርባል። ቅዳሴውን የሚጀምረው ቄስ እጅግ ከፍ ባለ ድምጽ ሃሌሉያ እያለ ሲያዜም ሌሎቹ ይቀበሉታል። አቁራቢው ግን ቆራቢዎቹን በመስቀል እያሳለመ ይባርካል እንጂ ከሌሎች ጋር አይቀድስም። በማህሌቱና በመቅደሱ ውስጥ ያሉት ቄሶች ጥቂት ጊዜ ያህል እየተቀ

ባበሉ ከቀደሱ ባኋላ እመሠውያው አጠገብ ካሉት ካህናት አንዱ ወደ ዋናው በር አጠገብ ቀርቦ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አንብቦ ሲጨርስ እርሱ ራሱ ማውረድ ይጀምርና በመሠውያው አጠገብ ያሉትና በማህሌቱ ውስጥ ያሉት እየተቀበሉት ይቀድሳሉ። ከዚህ በኋላ አቁራቢው ቄሰ ከመሠውያው ላይ አንድ መጽሐፍ አንስቶ ለወንጌል አንባቢው ይሰጠውና በረከት ለመቀበል ጎንበስ ይላል። በረከቱን ከተቀበለ በኋላ ከአንድ መስቀልና ጽና ያዥና ከአንድ ምርዋ መች ጋር ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስ ወደተነበበበት ቦታ ይሄዳል።በዚህ ቦታ ከወንጌልና ከሐዋርያት መልእክት በሚያነበንብ እጅግ ከፍ ባለ ድምጽ ይነበባል፤አንባቢው ወደ መቅደሱ ሲመለስ ሌላ ዜማ ይጀመርና ሌሎቹ እየተቀበሉ ይቀጥላሉ። ወደ መሠውያው ከተመለሰ በኋላ ሰሞነኛውን ቄስ አሳልመውት መጽሐፉን በቦታው ያኖሩታል። በመሠውያው አጠገብ መጽሐፍ አይነበብም። ከዚህ በኋላ ሰሞነኛው ቄስ ጽናውን ወስዶ ወይም በእጁ ሲሰጡት እየዞረ መሠውያውን ያጥናል። ከእጥነቱ በኋላ ወደ መሠውያው ይመለስና በመስቀሉ ብዙ ቡራኬ ይሰጣል፤ ከዚያህ በኋላ ተሸፍኖ የተቀመጠውን ሥጋ ወደሙን ይገልጥና ሕብስቱን በመጀመርያ በሁለት እጆቹ ከዚያም በቀኝ እጁ አሳልፎ በመጨረሻም በግራ እጁ ብቻ ይይዝና ይህንኑ ሕብስት በቀኝ እጁ አውራ ጣት በአምስት ቦታ ማለት፤ በራስጌ በመካከል በግርጌ በግራና በቀኝ ጎድጎድ ያሉ ምልክቶችን በመተው በቋንቋቸውና በኛም ቃላት እየተናገረ ይባርከዋል።ከባረከው በኋላ ሕብስቱን ከፍ አያደርገውም። ቋንቋው ልዩ ቢሆንም ስነሥርዓቱ ከኛ ቅዳሴ ወግ ጋር አንድ ነው። ጽዋውንም በዚሁ ዓይነት ባርኮ ሲጨርስ እንደነበረው ሸፍኖ ያኖረውና ከዚያ በኋላ ሕብስቱን ከመሳካሉ ከሁለት ይከፍለዋል። በግራ እጁ ከሚቀረው ቁራሽ ላይ ጥቂት ሸርፎ ከቀመሰለት በኋላ ሁለቱን ክፍሎች አነባብሮ ያኖራቸዋል። ቄሱ ያችን ሽራፊ ወደአፉ በማድረንግና ከጽዋውም በመቅመስ ሥጋ ወደሙን ይቀበላል። ቀጥሎም ወንጌሉንና የሐዋርያት መልእክትን የሚያነቡትን ያቆርባቸዋል። ከዚህ በኋላ ሥጋ ወደሙን አንድ ዲያቆን በቀኝ እጁ እንዲይዘው አድርጎ በዚያ ያሉትን ካህናት ከሕብስቱ በጥቂቱ እየሸረፈ ያቆርባቸዋል።ቄሱን ተከትሎ የሚሄደው ዲያቆን ሥጋውን ለበሉት ሁሉ ቤተ ክርስቲያኑ

እንደአቅሙ ሊኖረው በሚችለው በወርቅ በብር ወይም መዳብ እርፈ መስቀል በጥቂቱ እየለካ ከደሙ ያቀምሳቸዋል።ቅዳሴ ጠበሉን በማንቆርቆርያ ይዞ የቀረበው ሌላው ቄስ በቆራቢዎቹ እጅ ላይ ከጠበሉ ጥቂት ሲያንቆረቁርላቸው እነርሱም በዚሁ አፋቸውን ተጉመጥምጠው ይውጡታል። ከዚህ በኋላ ሁሉም ባንድነት ሆነው ሥጋ ወደሙን ይዘው ወደመሠውያው ሄደው ከመጀመርያው መጋረጃ ፊት ይቀርባሉ።

በዚህ ዓይነት በዚያና በሌላውም መጋረጃ አጠገብ እንዲሁም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለቁርባን የመጡትን ሴቶችና ወንዶች ምዕመናን ሁሉ ያቆርባሉ። ቁርባኑ በሚሰጥበትና በቅዳሴውም ጊዜ ሁሉም ይቆማሉ።

የገዳሞቹ ሁሉ ቄሶች ቅዳሴ ከመግባታቸው በፊት እጃቸውን ይታበሉ። የቁርባኑ ስነሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ አቁራቢው ሰሞነኛው ቄስና ሌሎቹም ወደ መሠውያው ይቀርቡና ሥጋ ወደሙ የቀረበበትን ሳህን በቅዳሴ ጠበሉ ጭላጭ ያጥቡታል። ሳህኑ የታጠበበትን ውኃ ከጽዋው ውስጥ ይገለብጡትና አቁራቢው ቄስ በመጨረሻ ይጨልጠዋል። ይህ ከተፈጸመ በኋላ በመቅደሱ ካሉት ቄሶች አንዱ መስቀልና ምርዋ ይዞ አንድ አጭር ዜማ ይጀምርና ወንጌሉና መልእክቱ ወደተነበበበት ወደ ዋናው በር ይቀርባል። የቁርባኑ ስነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ምዕመናኑ እንደበፊቱ ምድሩን ይሳለሙና ወደየቤታቸው መሄድ ይጀምራሉ። በረከት ከመሰጠቱ በፊት የሚሄድ ሰው የለም። ቅዳሜና እሁድ በበዓልም ቀን ለምዕመናኑ ጸዲቅ ይታደላል። ከ 20-25 መነኩሴዎች በላይ ባሉበት በዚህ ገዳም የሚከተሉት ስነ ሥርዓት በሌሎች ታናናሽና ታላላቅ ገዳሞች የሚከተሉትን ስነ ሥርዓት የመሰለ ነው። የጉዞው ስነ ሥርዓት ሳይቆጠር ቅዳሴው ብቻ የሚፈጀው ጊዜ ጥቂት ነው። በአዘቦቱ ቀን የሚደረገው ቅዳሴ በጣም አጭር ነው።

ምዕራፍ አስራ ሁለት፤ የማቁረቢያ ሕብስት እንዴትና በየት እንደሚዘጋጅ፤ ካህናቱ ስላደረጉት አንድ ጉዞ፤ የቅዳሴ ስነ ሥርዓትና ከጉዞው መልስ ወደ ቤተ ክርስቲያን በንዴት ያለ ሁኔታ እንደገቡ።

ሕብስቱ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ይዘጋጃል። ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ሁሉ ቤተልሄሙ የሚገኘው ከቤተ ክርስቲያኑ ውጭ ነገር ግን ከገረገራው ግቢ ከመሠውያው በስተቀኝ በኩል ባለው ክፍል ነው። ቤተ ክርስቲያኖቹና ገዳሞቹ ሁሉ ቤተ ልሄም ያላቸው ሲሆኑ በነዚህም አስፈላጊ ከሆነ ዕቃ ማለት የስንዴ መፈተጊያ ሙቀጫና ወፍጮ በስተቀር ሌላ ነገር አይገኝም። የሕብስቱን ስንዴ ሴቶች ያዘጋጁት ዘንድ ስለማይፈቀድ እጅግ ንጹህ በሆነ አኳኋን የሚፈትጉትና የሚፈጩትም መነኩሴዎቹ ራሳቸው ናቸው። ዱቄቱን የሚለውሱበት ልዩ የገበቴ ማቡኪያ አለቸው። ቡኮዋቸው ከኛው ጥቂት ወፈር ብሎ ይዘጋጃል።ከዚያም በኋላ የቤተ ክርስቲያኑ አቅም በሚፈቅደው መጠን የሸክላ የብረት ወይም የመዳብ ምጣዱን በምድጃው ላይ ከጣዱ በኋላ በደንብ ሲሰማ ሰፊፍ በተን አድርገው እያሰሱ ያጸዱትና ቡኮውን በሚፈልጉት መጠን በእንጨት ማንኪያ እየዛቁ በምጣዱ ላይ በክብ ያሰፉታል። ይህ በደንብ ከበሰለ በኋላ በዚሁ መልክ ሌላ ያሰፉና የበፊቱን አነባብረውት ይገለብጡታል፤ እነባበሮው በምጣዱ ላይ እንዳለ በደንብ ክብ ያልሆነውን ጠርዙን ያስተካክሉትና እያገላበጡ በደንብ እሳት ካስመቱት በኋላ አውጥተውት በዚሁ መልክ እንዳስፈላጊነቱ መጠን ሌላ ይጋግራሉ። ደሙ የሚዘጋጅበት ዘቢብና መጭመቂያውም የሚገኘው እንዲሁም ቅዳሜና እሁድ የሚታደለው ጸዲቅም የሚጋገረው በዚሁ ቤት ውስጥ ነው። በዓመት በዓል ቀን ማለት በልደትና በትንሳኤ በዓላት ወይም በነሃሴ ኪዳነ ምሕረት ታቦቱ በሚወጣበት ቀን ሥጋውን በግምጃ ጥለ ሥር ሆነው በምርዋ ድምጽና በመስቀል በማጀብ በታላቅ ክብር ይይዙታል። በመቅደሱ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ይህንኑ እንደያዙ በቅኔ ማህሌቱ አንድ ጊዜ ይዞራሉ። በተራው ቀን ግን ይህን የመሰለ ስነሥርዓት አይፈጸምም።

ከእርገት በዓል በፊት በአንድ ቅዳሜ ካህናቱ ቀጥሎ በምናትተው አኳኋን አንድ ጉዞ አደረጉ፤ እኛ ለአገሩ እንግዶች በመሆናችን ሁሉም ነገር አዲስ ስለሆነብን ይህ ስነ ሥርዓት በጣም አስደስቶን ነበር። ግምጃ የተሸፈነውን ታቦቱን የአገልግሎት ልብስ የለበሰ አንድ ቄስ በጭንቅላቱ ተሸክሞ መጽሐፎች ቅዳሴ ጠበልና መስቀል ተይዞ ምርዋ እየተመታ አካባቢው እየታጠነ ሕዝቡ ቅዱሳንን በማሞገስና በመጨፈር ተከትሎ ወደ አንድ እርሻ ቦታ ከሄዱ በኋላ ስነሥርዓቱ ሲያበቃ በዚሁ አኳኋን ታቦቱ ወደ ገዳሙ ተመለሰ። በዚሁ ስነ ሥርዓት ላይ ያ ቦታ ጠበል ተረጨ፤ እኛም ይህን የመሰለ ነገር የሚደረገው በምን ምክንያት መሆኑን ብንጠይቅ ሰብላቸውን ተምች ስላጠፋባቸው ይህን ተባይ እግዚአብሔር እንዲያጠፋላቸው መሆኑን ገለጹልን።

በዚህ አገር ቄሶቹና ዲያቆኖቹ ቅዳሴ ሲገቡ የሚለብሱት ልብስ አንድ ዓይነት ሲሆን ጥቂት የሚለያዩት ቄሶቹ ራስ ለማስገባት ያህል ከመካከሉ የተሰነጠቀ ከፊትና ከኋላ መሬት የሚነካ ተደራቢ ልብስ ያጠልቃሉ።

ቅዳሴ የሚገቡት መነኩሴዎች ጠጉራቸውን አይላጩም፤ ቄሶቹ ጥምጥም ያስራሉ፤ ዲያቆኖቹ ግን ይላጩታል። መነኩሴዎችም ሆኑ ቄሶች በቅዳሴ በገቡ ጊዜ መጫሚያቸውን ማውለቅ አለባቸው፤ ማንም ሰው ቢሆን ከነመጫሚያው በቤተ ክርስቲያን ለመግባት አይፈቀድለትም። ይህ የተደረገበት ምክንያት እግዚአብሔር አምላክ ሙሴን «መጫሚያህን አውልቅ የቆምህባት ምድር ቅድስት ናትና» ሲል ባዘዘው መሠረት ነው።

ምዕራፍ አስራ ሶስት፤ በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በቀን ከአንድ ጊዜ በላይ ቅዳሴ ስላለመኖሩ፤ ማቴዎስ ስለተቀበረበት የቢዘን ገዳም ቦታና ስለዐቢይ ጾም።

ባረፍንበት በቅዱስ ሚካኤል ገዳም ቤተ ክርስቲያን ታዛ ሥር እኛ በየቀኑ ቅዳሴአችንን እናደርስ ነበር፤ በዚህ አገር በየቤተ ክርስቲያኑና ገዳሞቹ ሁሉ በቀን ከአንድ ጊዜ በላይ አይቀደስም። የኛን ቅዳሴ ካህናቱ ወደኛ ዘንድ እየመጡ ስነ ሥርዓቱን በታላቅ ብጽዕና ይመለከቱ ነበር። ያለ እጣን መቀደስ የማይገባ ነገር አድርገው ስለሚቆጥሩትና እኛም እጣንና ጽና የሌለን መሆናችንን በመረዳት ይህንኑ ከቤተ ክርስቲያኑ አመጡልን። በነርሱ ወግ የቅዳሴውን አገልግሎት የሚያከናውኑት ሶስት አምስት ወይም ሰባት ሆነው ስለነበር በኛ ደንብ ግን በአንድ ቄስ ብቻ በመሆኑ ቅር ተሰኙ። ይልቁንም እኛ ከነመጫሚያችን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በመግባታችን በዚያም በመትፋታችን በጣም ተደነቁ። በዚህ አኳኋን እስከ ሥላሴ እሁድ ድረስ በየቀኑ ቅዳሴ እናደርስ ነበር። በሚቀጥለው ሰኞ ቅዳሴ ለማድረግ ስንሰናዳ ምክንያቱ ሳይገለጽልን እንዳትቀድሱ የሚል ትእዛዝ በድንገት ስለደረሰን ከልብ አዘንን፤ እንዲያውም በመጥፎ ነገር የተጠረጠርን ነበር የመሰለን። ነገር ግን የዚህ አገር ክርስቲያኖች ከሕገ ክርስትና ጋር አንዳንድ የኦሪት ሕጎችን አጣምረው ስለሚያከብሩ በዚሁ መሠረት የዐቢይ ጾምን የሚጀምሩት ከኛ ጾም መግቢያ አስር ቀን ቀደም ብለው ስለሆነ የጾሙ ቀን አርባ ቀን መሆኑ ቀርቶ ሃምሳ ቀን ነው። እነዚህን አስር ቀኖች መቀጠላቸው የማይጾምባቸውን እሁዶች ለማሙዋላት ነው ይባለል።

እስከ ቀትር ድረስ ይጾሙና ከዚያ በኋላ ይመገባሉ፤ ጾዋሚዎች ሁሉ መቁረብ ስላለባቸው ቅዳሴ የሚገቡት ከቀትር በኋላ ነው። የሃምሳው ቀን ጾም ሲያልቅ ከማናቸውም ዓይነት ጾም ነፃ የሆኑ ሃምሳ ቀኖች ከትንሳኤው በዓል በኋላ ይከተላሉ። በዚህ ጊዜ ቄሶቹ ቅዳሴ የሚገቡት ጠዋት ነው። የዚህ የመጨረሻው የሃምሳ ቀን ምስጢር ከቶ አልገባንም ወይም የሚያስረዳን ሰው አላገኘንም። ይህ ጊዜ

ካለቀ በኋላ ቅዳሴ የሚያደርሱት ከቀትር በኋላ ብቻ ነው። እኛም እንዳንቀድስ እንከለከላለን። ያላንዳች ምክንያት ቅዳሴአችንን እንዳናደርስ በመከልከላችን በእውነተኛው አዘንን። ይህ ከጾም ነፃ የሆነው ጊዜ ሲያልቅ ከሥላሴ በዓል በኋላ ቄሶችና መነኩሴዎች ሁሉ ከእሁድና ከቅዳሜ በስተቀር ማናቸውንም ቀን እንዲጾሙ ግዴታ አለባቸው። ይህ ጾም የሚፈታው በልደት በዓል ነው፤ በነዚህ ወራት ሁሉም ጾመኞች በመሆናቸው ቅዳሴ የሚገቡት ሌሊት ነው። በጾሙ ወራት ቅዳሴ በሌሊት የሚገቡበት ምክንያት ክርስቶስ የመጨረሻውን እራት የጋበዘበትና እውነተኛ አካሉን የባረከው በጾም ጊዜ ስለሆነና ጊዜው ምሽት ስለነበረ ነው ይላሉ። ተራው ሕዝብ ከሥላሴ በዓል ጀምሮ ከልደት በፊት እስከሚገኙት ሳምንታት ድረስ ከዚያም በኋላ እስከ ልደት ሳምንት ድረስ ባለው ጊዜ ከረቡእና አርብ በስተቀር ከማናቸውም ጾም ነፃ ነው። የንጻት በዓልን የሚከተሉት ሶስቱ ቀኖች ቅዳሜ ወይም እሁድ የሚውልባቸው ካልሆኑ በስተቀር ምዕመናንና ካህናት በሙሉ አንድ ጊዜ ብቻ በመመገብ በጥብቅ የሚጾሙባቸው ናቸው፤ እነዚህን ሶስት ቀኖች የነነዌ ጾም ይሉዋቸዋል። ከሥላሴ በኋላ እንዳደረጉት ሁሉ ከነዚህ ሶስት ቀኖች መጨረሻ እስከ አቢይ ጾም ድረስ ይጾማሉ። የልደትንና የዓቢይ ጾሞችን ካህናትም ሆኑ ተራው ሕዝብ ወንዶችም ሴቶችም ልጆችና አዋቂዎች ጤነኞችና በሽተኞች በሙሉ መጾም አለባቸው። ስለዚህ ከትንሳኤ እስከ ሥላሴ በዓልና ከዚያም ከልደት እስከ ንጽዐት በዓል ድርስ ጾም ስለሌለ ካህናት ቅዳሴ የሚገቡት በማለዳ ሲሆን፤ በጾሙ ጊዜ ግን በሌሊት ነው።

ማቴዎስን ያስቀበርንበት እጅግ የተከበረው የቢዘን ገዳም ቤተ ክርስቲያን በየሱስ ስም ይታወቃል። እኛ ከሠፈርንበት ገዳም እስከ ቢዘን ድረስ ያለው ርቀት በግምት አንድ ሌግዋ የሚሆን ገደላም ምድር ነው። የደብረ ቢዘን ገዳም ባንድ ኮረብታ ጫፍ ላይ የተቆረቆረ ሲሆን ከዚህ ቦታ ላይ ሆኖ አካባቢውን ሲመለከቱት የገሃነምን አዘቅት ያሳስባል። የገዳሙ ቤት በስፋቱም ሆነ በቁመቱ በጣም ታላቅና ገቢውም ከፍ ያለ በቂ አገልጋዮች ያሉት ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ባማረ አኳኋን የተሠሩ ሶስት ተካባቢ ክፍሎች

ሲገኙበት እያንዳንዱ ክፍል ለየብቻው ምሰሶና ጣርያ አለው። ጣርያው በሚያስደንቅ አኳኋን ቀለም ስለተቀባ እንጨት ይሁን ድንጋይ ለይቶ ለማወቅ አይቻልም። ከቤተ ክርስቲያኑ አካል ዙርያ ሁለት ዙር ግድግዳዎች አሉ። እነዚህ ግድግዳዎች በደንብ የተለሰኑና በልዩ ልዩ ስዕሎች ማለት በሐዋርያትና በፓትርያርኮች በነቢያትና በቅዱስ ጊዮርጊስ ስዕልና ከአሪት ከተወሰዱ ልዩ ልዩ ጥቅሶች ያጌጠ ነው። በዚህ ገዳም የክርስቶስ ስቅለትና የእመቤታችን መልክ እንዲሁም የሐዋርያትና ሌሎችም ምስሎች ፓትርያርኮችና ነቢያት የተሳሉበት በያንዳንዱም ግርጌ የላቲን ስያሜው የተጻፈበት ታላቅ የጨርቅ ስዕል ይገኛል። ይህ በጥሩ ሰዓሊዎች ያልተሳለ መሆኑ ግልጽ ነው። ከዚህም ሌላ አንድ የማዕድ ቤትና አንድ የግብር ቤት አለ። በግብር ቤቱ ለሶስት ሰዎች አንድ ገበታ ይቀርባል፤ በዚህ ቤት የሚበላው ምግብ በጣም መናኛ ነው። እንጀራው የማሽላና የስንዴ የጥቁር ጤፍም ነው። ለያንዳንዱ መነኩሴ በቀን ሶስት እንጀራ ለአዲስ ገብ ተማሪዎች ግን ለሁለት ሶስት ይሰጣቸዋል። ይህን ምግብ ብቻ እየበሉ እንዴት አድርገው ለመኖር መቻላቸው እጅግ የሚያስገርም ነው። ከእንጀራው ጋር ጨውና ዘይት ያልገባበት ጎመን ይሰጣል፤ ወደግብር ቤቱ መምጣት ለማይችሉት ሽማግሌዎች ከዚሁ ምግብ ይላክላቸዋል። ይህን ልመለከት የቻልሁት ማቴዎስን ልናስቀብር በመጣንበት ዕለት ብቻ ሳይሆን የሠፈርንበት ቦታ ቅርብ ስለነበር አንዳንድ ጊዜ በተለይም በዓመት በዓል ቀን ወደዚያ እንሄድ ስለነበር ነው። ስለዚህ ከመነኩሴዎቹ ጋር በመነጋገር ስለባሕላቸው ስለሃብታቸውና ስለገቢያቸው ላውቅ ችያለሁ። በዚህ ገዳም በኔ አገማመት አንድመቶ የሚሆኑ መነኩሴዎች ይገኛሉ። ከነርሱም ውስጥ ብዘዎቹ በጣም ያረጁና እንደ እንጨት የደረቁ ሲሆኑ አንዳንድ ጎልማሶችም ይገኙባቸው ነበር። ገዳሙ ዙርያውን ታጥሮ በሁለት መዝጊያዎች ሁል ጊዜ ይዘጋል።

ምዕራፍ አስራ አራት፤ የደብረ ቢዘን ገዳም የስድስት ሌሎች ገዳሞች አስተዳዳሪ ስለመሆኑ፤ የመነኩሴዎች ቁጥርና ጌጣጌጦች፤ ፊልጶስን እንደ ቅዱስ በመቁጠር የሚያደርጉለት ስግደት።

ይህ ገዳም በዚያ አካባቢ በየተራሮቹ የሚገኙትን ስድስት ገዳሞች የሚያስተዳድርና የሚመራ ነው፤ ከስድስቱ ገዳሞች አንዱ ሶስት ሌግዋ ያህል ርቆ ይገኛል፤ እያንዳንዱ ገዳም «ዳኛ» በሚያሰኝ መጠርያ በሚታወቅ ሰው ይተዳደራል፤ ይህን ሰው የሚሾመው የደብረ ቢዘን ገዳም አለቃ ነው። የደብረ ቢዘን ሃላፊም በበኩሉ ዳኛ ሲሆን በማዕርጉ ግን ከአቡኑ ተከታይ ነው። በደብረ ቢዘን ሶስት ሺ የሚሆኑ መነኩኬዎች ይገኛሉ ማለትን ወሬ በጣም እጠራጠር ስለነበርሁ ይህንኑ ለማጣራት ስል የነሃሴ ኪዳነ ምሕረት በዓል በሚከበርበት ዕለት እገዳሙ ድረስ ሄጄ እስኪሰበሰቡ ድረስ ጠበቅሁ። የገዳሙን ሃብትና የታቦቱንም የንግሥ ስነ ሥርዓት በመመልከቴ ተደሰትሁ። በኔ አገማመት የመነኩሴዎቹ ቁጥር ከሶስት መቶ አይበልጥም፤ ከነዚህም ውስጥ ይበልጡ ሽማግሌዎች ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትን የገዳሙን ቤተ ክርስቲያን ሁለቱን ዙሮች የሚከብ ክፍት የሆነ አንድ ግድግዳ አየሁ። ይህ ግድግዳ ተቀጣጥለው በተሰፉ በወርቅና በሐር ጨርቆች ዙርያውን ተሸፍኖአል። ካህናቱ ቅዱ ደስ የማያሰኝ ነገር ግን በወርቀዘቦ የተንቆጠቆጠ የከፈይ ካባ ለብሰው በተጋረደው ታዛ ውስጥ አለፉ። በአሠራራቸው የማያምሩ ሃምሳ ትንንሽ የብር መስቀሎችና ቁጥራቸው በዚሁ የሚገመት የመዳብ ጽናዎች ይዘው ቅዳሴ በገቡ ጊዜ ቁርባን የሚሰጡበት የወርቅ ዋንጫና እርፈ መስቀል ይዘው አይቻለሁ፤ ወደገዳሙ ከመጡት ሶስት መቶ ካህናት ውስጥ የዚያው መሆናቸውን እኔ የማውቃቸው ጥቂት ብቻ ነበሩ። አንዳንድ ወዳጆቼ የሆኑ ሰዎችን አግኝቼ በዚህ ገዳም ብዙ መነኩሴዎች አሉ ይባላል፤ ነገር ግን ለምንድን ነው በበዓሉ አለመገኘታቸው ብዬ ብጠይቃቸው የመነኩሴዎቹ ቁጥር ከሚገመተው በላይ መሆኑ የማይካድ ነው ዳሩ

ግን በኀልማሳነታቸው ጊዜ በዚህ ገዳም ምንም እርዳታ ስለማይ ደረግላቸው ራሳቸውን ለማስተዳደር ሲሉ በየገዳሙና በየቤተ ክርስቲያኑ በየገበያውም ተሰራጭተው ይገኛሉ፤ ወደዚህ ገዳም የሚመጡም ካረጁና መራመድ ካቃታቸው በኋላ ለመሞት ብቻ ነው ሲሉ ገለጹልኝ። በዚያን ዕለት አሥራ ሰባት ወጣቶች የክህነት ማዕርግ ሲቀበሉ አየሁ።

በዚህ ገዳም ውስጥ አባ ፊልጶስ የተባለ የገዳሙ ሃላፊ የነበረ ሰው መቃብር ይገኛል፤ አንድ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቅዳሜን ማክበር አያስፈልግም ሲል አውጆ ስለነበር ይህንኑ የንጉሣዊ ትዕዛዝ ለማሻር ሲል ካህናቱን አስከትሎ መጽሐፉንም አሸክሞ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቀርቦ ሰንበት ይከበር ዘንድ እግዚአብሔር ማዘዙንና ያላከበረም ሰው በድንጋይ ተወግሮ መሞት አለበት የሚለውን ጥቅስ አንዳንድ የኢትዮጵያ ሊቃውንት በተገኙበት አሳይቶ ትዕዛዙን ያስሻረ በመሆኑ የቅዱስነት ማዕርግ ሰጥተውት ያከብሩታል። ስለዚህ ቅዳሜ እንዲከበር ያደረገ እርሱ በመሆኑ ቅዱስ እየተባለ በየዓመቱ በሐምሌ ወር ተዝካር እየተዘጋጀለት ያከብሩታል። ስለዚህ የገዳሙ መነኩሴዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የኦሪትን ሕግ በበለጠ አጥብቀው የሚያከብሩ ናቸው። በዚህ ተዝካር ላይ ሁለት ጊዜ ስገኝ በክብር ተቀብለውኛል፤ መጀመርያ በተገኘሁበት ዓመት ሰላሳ በሁለተኛውም ሃያ ፍሪዳ አረዱ፤ በያንዳንዱ ዓመት ከታረደው ፍሪዳ የሰባው ተመርጦ ግማሽ ጎኑ ለኔ ይሰጥ ነበረ። ይህ ሥጋ እየተቆረጠ በተዝካሩ ላይ ለተገኙት ሰዎች ይታደላል፤ መነኩሴዎቹ ግን ሥጋ ስለማይበሉ ለራሳቸው ምንም አያስቀሩም። ፍሪዳዎቹ በግዛቱ ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች ለአባ ፊልጶስ እየተሳሉ የሚያበረክቱዋቸው ናቸው።

በዚህ ገዳምና በሌሎችም ጥገኛ ገዳሞች አንስታይ የሆኑ ሁሉ ማለት፤ ሴቶች ላሞች፤ ሴት ዶሮች፤ በቅሎዎችም ወይም ማናቸውም የዚህ ጾታ ወገን የሆኑ ሁሉ መግባት አይፈቀድላቸውም። ለምሳሌ ለፊልጶስ ተዝካር ድግስ የምትታረድ መሲና ከገረገራው ራቅ ብላ ነው የምትጣል። እኔ ወደገዳሙ በመጣሁ ጊዜ ከቦታው ለመድረስ

ያንድ ወንጭፍ ውርወራ ርቀት ያህል ሲቀረኝ አንድ ሰው መጥቶ በቅሎዬን ተቀብሎኝ ማቴዎስ በሞተበት ዣንጋርጋራ በተባለ ቦታ ወስዶ አሰራት።

ምዕራፍ አሥራ አምስት፤ የዚህ ቀበሌ እርሻ፤ ሕዝቡ እንዴት አድርጎ ራሱን ከአውሬ እንደሚጠብቅና የገዳሙም ገቢ።

የገዳሙ መነኩሴዎች ሊያርሱና ዛፍና ወይንም ሊተክሉ አትክልት ሊያዘጋጁና ልዩ ልዩ ጎመናጎመንም ሊያለሙ ይችሉ ነበር፤ ነገር ግን ምንም አይሠሩም፤ ባልታረሰው ምድር ላይ በቅሎ የሚታየው ሰብል እንደሚያስረዳው መሬቱ ለምለም ስለሆነ የዘሩበትን ሁሉ ያበቅላል፤ ነገር ግን አዘውትረው የሚሠሩት ማሽላ መዝራትና ቀፎ መስቀል ነው።

መነኩሴዎቹም ሆኑ ሌሎችም ሰዎች አውሬዎችን በመፍራት በሌሊት ወደውጭ አይወጡም። ሰብላቸውን በዱር ሆነው የሚጠብቁት ሰዎችም ይህንኑ በመፍራት ከታላላቅ ዛፍ ላይ ማማ ሠርተው በዚያ ላይ ተኝተው ያድራሉ። በዚህ ገዳም ግዛት ባሉ ሸለቆዎች ውስጥ የአረብ[1] እረኞች የሚጠብቋቸው ብዙ የቀንድ ከብት መንጋዎች ይገኛሉ። በያንዳንዱ መንጋ ከአርባ እስከ ሃምሳ የሚሆኑ አረቦች ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ሆነው በዘላንነት ይኖራሉ። የሚጠብቋቸው ከብቶች በባሕር ነጋሹ ግዛት የሚገኙ የክርስትያን መሳፍንት ስለሆኑ ከአረቦቹ በላይ ሆነው የሚያዙት ሹማምንት ክርስቲያን ናቸው። እነዚህ አረቦች ከላሞቹ የሚያገኙትን ወተትና ቅቤ ብቻ ራሳቸውን ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውንም እንዲመግቡበት ይፈቀድላቸዋል እንጂ ለድካማቸው ዋጋ ሌላ ምንም አይሰጣቸውም። ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ በመንገድ ላይ ከነዚህ እረኞች ጋር ባደርን ጊዜ ከብት ለመግዛት ፈልገን ያሻንን ያህል መርጠን በርካሽ ዋጋ ሊሸጡልን ፈቃደኛ መሆናቸውን ገለጹልን።

እነዚህ አረቦችና አለቆቻቸው ክርስቲያኖቹም የከብቶቹ ባለቤቶች እምነት የጣሉባቸው ቢሆኑም ወስላቶች ናቸው ይላሉ፤ ስለዚህ ከነጋዴ ጋር ካልሆኑ በስተቀር ብቻ ሆኖ ለማለፍ ያስፈራል።

የዚህ ገዳም ሃብት በጣም ሰፊ ነው፤ ዋና ሃብቱ እኔ ያየሁትና ሲያወሩ የሰማሁት አስር ሌግዋ ስፋት ያለው ገዳሙ የተቆረቆረበት ተራራ ነው። በዚሁ ቦታ ማሽላና ልዩ ልዩ የብዕር እህል የዘራል፤ በዚያ የሚገኙት ገበሬዎች ሁሉ ከሰብላቸውና በከብቶቻቸው ቁጥር ለገዳሙ ግብር ይከፍላሉ። በተራራው ጥግ የሚገኙት መንደሮች አብዛኞቹ የገዳሙ ናቸው። ከዚህም በላይ ያንድ ወይም የሁለት ቀን መንገድ ከተጓዙ በኋላ በአገራችን በፖርቱጋል ኮቱሽ ወይም ሳለይሩሽ የምንላቸውን የመሰሉ ሰፊ የሆነ የገዳሙ ጉልት አለ።

አምባሳደር ዶም ሩድሪጉና እኔ ባንድነት ሆነን ወደ ቤተ መንግሥቱ የሚወስደውን መንገድ ተከትለን የአምስት ቀን ጎዳና ከሄድን በኋላ ከሃያ ቤቶች በላይ በሚገኙባት ባንዲት መንደር ደርሰን ቅዳሜንና እሁድን በዚያ ዋልን፤ በዚያች ቦታ የሚገኙት መንደረተኞችም በገዳሙ ጉልት ላይ ያሉ መሆናቸውን ነገሩን እኛ ያረፍንባት መንደር ከሌሎች መቶ የሚሆኑ በገዳሙ ሃብት ላይ ከሚገኙት ልዩ ልዩ መንደሮች አንዷዋ ናት። በዚያ አካባቢ የሚገኙትን ብዙ ቦታዎች አሳይተውን እያንዳንዱ መንደር በየሶስት ዓመት አንድ ፈረስ ለገዳሙ የሚገብር መሆኑን ነገሩን፤ ስለዚህ በዓመት በግብር ስም ለገዳሙ የሚከፈሉት ፈረሶች ሰላሳ ሶስት መሆናቸው ነው።

መንደረተኞቹ የሰጡን ይህ መረጃ እውነተኛ መሆኑን ለማጣራት ስል አሊቃሺውን ጠይቄ አረጋገጠልኝ። የገዳሙ መነኩሴዎች በፈረስ የማይሄዱ መሆናቸውን ስለማውቅ ገዳሙ ለምንድርን ይሆን ፈረሶችን የሚፈልገው ብዬ ደግሜ ብጠይቀው እነዚህ ቦታዎች የገዳሙ ጉልት ከመሆናቸው በፊት የንጉሠ ነገሥቱ ሃብት ስለነበሩ በዚያን ጊዜ የሚከፈለው ግብር በመንደር አንድ ፈረስ ነበር፤ ዳሩ ግን ይህን ሃብት ንጉሠ ነገሥቱ ለገዳሙ ከሰጠው በኋላ ጉልተኞቹና ገዳሙ ስምምነት አድርገው ግብሩ በፈረስ መከፈሉ ቀርቶ በከብት

እንዲከፈል ተደርጓል ሲል አስረዳኝ። ከከብቶቹ ሌላ በተጨማሪ በፍራፍሬ ላይ ቀረጥ ይከፈላል። ከገዳሙ የአስራ አምስት ቀን መንገድ ከተጓዙ በኋላ በትግሬ መኮንን[2] ግዛት ውስጥ የሚገኘው እዴት የሚባለው ስፋቱ የአንድ መስፍን ግዛት የሚያህል ቦታም የገዳሙ ጉልት ነው። ይህ ግዛት ለገዳሙ በየዓመቱ ሰላሳ ፈረስና ሌላ ልዩ ልዩ ግብርና ቀረጥም ይከፍላል።

በዚህ ቦታ ገዳሙ በበለጠ ስለሚከበርና ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችም ስለሚገኙ ከሺ የሚበልጡ መነኩሴዎች በዚሁ ይኖራሉ። ከነዚህ መነኩሴዎች አንዳንዶቹ በጣም መልካሞችና የተከበሩ ለእግዚአብሔር የተገዙ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ቅን ያልሆኑ አሉ። በዚህ ግዛት የንጉሠ ነገሥቱ ንብረት የሆኑ ቦታዎች ሰላሉ ግብራቸውን በፈረስ ይከፍላሉ፤ ከተባሉት ቦታዎች አንዳንዶቹ የግብጽና የአረብያ ግዛቶች ድንበረተኛ የሆኑት ያገራቸውን ፈረሶች በግብር ስም ያበረክታሉ፤ ይሁን እንጂ የግብጽ ፈረሶች በዓይነታቸው በጣም የተሻሉ ናቸው።

ምዕራፍ አስራ ስድስት፤ እንዳንሄድ መነኩሴዎቹ እነቅፍት ስለሆኑብን።

ባረፍንበት በሚካኤል ገዳም እንደነበርን ዕቃችንን ለመውሰድ አጋሰሶች የያዘ ሰው ባሕርነጋሹ ሰኔ አራት ቀን ላከልን፤ ከዚሁ ሰው ጋር ሁለት የኛ ፖርቱጊዞች ነበሩ። የተባለው ሰው በተራራው ጥግ ወደሚገኙት መንደሮች ሄዶ በተጨማሪ አጋሰሶችና ሰዎች አምጥቶ ዕቃችን ከተጫኔና እኛም መንገድ ለመግባት ከተዘጋጀን በኋላ መነኩሴዎቹ ተሰብስበው በማናውቀው ቋንቋ ብዙ ከተነጋገሩ በኋላ ጉዞው እንዲሰረዝ ስላደረጉብን አምባሳደሩ መምሕር ዮሐንስንና መልእክተኛውን ወደባሕርነጋሹ ልኳቸው መልእክቱን አድርሰው ከስድስት ቀን በኋላ ተመለሰ። እነዚህ ሰዎች ባመጡት መልእክት መሠረት መነኩሴዎቹ እኛን እንዲሸኙንና ዕቃችንንም እንዲያስጭኑ

ልን ባስፈለገን መጠን በቅሎዎችና አጋሰሶችም እንዲሰጡን ታዘዘ። ይህም ሆኖ መነኩሴዎቹ ክፉ ያሰቡ ይመስል መንገዳችንን ለማስታጎል በብርቱ ሞክረው ነበር። ሐምሌ 15 ቀን ከሚካኤል ገዳም ተነሣን። አጋሰሶቹ የመጡት ቀስበቀስ በመንጠባጠብ በመሆኑና ዕቃችንን መጫኑም ጊዜ ስለፈጀ በዚሁ ምክንያት ዘግይተን ተነሣን፤ በቂ በቅሎዎች ስላልነበሩ ግማሾቹ ሰዎች በእግራቸው ሄዱ፤ የምንሄድበት መንገድ ለጭነት ከብት የማይመች በመሆኑ ዕቃውን በሸክም የሚወስዱት ሰዎች ቁጥር ጥቂት ስለነበር አለሎ መወርወርያው መኪናና አራት በርሜል ባሩድ በዚያ ቀረ። ከገዳሙ ጥቂት እልፍ ብለን እጅግ ቢበዛ ግማሽ ሌግዋ እንደተጓዝን አምባሳደሩና አብረውትም የነበሩት ወደኛ ከመጡ በኋላ ዕቃችን በሙሉ ተራግፎ አገኘነው። ይህ የተደረገበት ምክንያት ስላልገባን ዕቃችን እንደገና እንዲጫን አዘን ከዚያ ቦታ ልንሄድ ስንነሳ በመንገድ አድፍጠው ዕቃችንን ሊቀሙን የሚፈልጉ ሌቦች አሉ ማለትን አንዳንድ ሰዎች የሚያወሩ መሆናቸውን ጭምጭምታ ሰማን። ይሁን እንጂ ይህ ወሬ ምንም ዓይነት ድንጋጤ ሳያስከትልብን መንገዱ ጠባብ ስለነበር ዕቃችንን አስጭነን በየጥሻው እያቋረጥን ጉዞአችንን ወደፊት ቀጠልን። አምባሰደሩና አብረውትም የነበሩት ሁሉ በንጉሡ ሃብት ላይ መሞትን ቆረጡ። ከአስር እስከ አስራሁለት የምንሆን ሰዎች በነዚያ ታላላቅ ተራሮች ጥግ አሉ የተባሉትን ብዙ ሌቦች ሳንፈራ በድፍረት ወደፊት ገፋን። ይህ የድፍረት ተግባር ክልብ ነበር እቃችንን የተሸከሙልንን ሰዎች ያስደነቃቸው። ስለዚህ አጋሰሶቻችንንና ተሸካሚዎቻችንን ከፊታችን አስቀድመን በጓድ ተከፋፍለን ወደፊት ገፋን።

መንገዳችንን ወደፊት በመቀጠል ብዙ ዳገትና ቁልቁለትን ታላላቅ ተራሮችንና ኮረኮንች መንገዶች እያለፍን ተጓዝን። በነዚህ ተራሮች ላይ ታላላቅ ዛፎች በቅለውባቸው የሚገኙት ቦተዎች በደንብ ቢሠሩ ኖሮ ዘይት የሚሰጥ ወይራ ሊተክልባቸው ይቻል ነበር። እነዚያን ተራሮች ከዞርን በኋላ በክረምቱ ወራት ጎርፍ በሚተላለፍባቸው ደረቅ ወንዞች ደረስን። ከነዚህ ደረቅ ወንዞች ግራና ቀኝ አልፈናቸው የመጣነውን የሚመስሉ ታላላቅ ተራሮች

አሉ። በወንዞቹ ውስጥ ከዚህ በፊት አይተናቸው የማናውቅ ልዩ ልዩ ዕፅዋትና ዘንባባዎች አሉ። በዚያ ዕለት ጥቂት ውኃ በነበረበት ባንዱ ወንዝ አጠገብ አደርን።

ምዕራፍ አስራ ሰባት፤ ብዙ ዝንጀሮች የነበሩበትን አንድ ተራራ አለፍን፤ ቅዳሜና እሁድ ጸሎት በተባለ ባንድ ቦታ ቅዳሴ አደረስን።

በማግሥቱ መንገዳችንን ቀጥለን በበቅሎም ሆነ በእግር ሊታለፍበት በማይቻል ባንድ ትልቅ ተራራ ደረስን። በዚህ ተራራ ላይ ዓይነታቸው የበዛ ልዩ ልዩ አራዊትና በየገደሉና በየቋጥኙ ፉካ ውስጥ እየተንጠላጠሉ በመንጋ የሚሄዱ ዝንጀሮች ነበሩ። ባንድ መንጋ የሚገኙት ዝንጀሮች ቁጥር ከሁለት ወይም ከሶስት መቶ በላይ ነበር። እነዚህ ዝንጀሮዎች በገደሎቹ አፋፍ አንዳንድ ሜዳ ቦታዎች ያገኙ እንደሆነ በዚያ እየተዝናኑ የሚያገኙዋቸውን ድንጋዮች ሁሉ እየገለበጡ ቦታውን ይቆፍሩና ልክ በሰው የታረሰ ያስመስሉታል። ትልቅነታቸው ከደህና በግ ጋር የሚመዛዘን ሲሆን ከትከሻቸው ጀምሮ ወደፊት እንደ አንበሳ በጎፈር የተሸፈኑ ናቸው።

ተራራውን ከዞርን በኋላ ጸሎት በሚባል ባንድ ቦታ አጠገብ ደረስን። ይህ ቦታ ከተነሣንበት ከገዳሙ አራት ወይም አምስት ሌግዋ ርቆ የሚገኝ ነው። ንጹህ ውኃ በሚገኝበት ባንድ ወንዝ አጠገብ ደርሰን ከነዕቃችን በዚሁ ካረፍን በኋላ የዚያች መንደር ሃላፊ የሆነ በጣም የተከበረ ሽማግሌ ወደሚገኝበት ቦታ ሄድን። በዚያ እንደደረስን ይህ ሰው በክብር ተቀብሎን የዶሮ ወጥና ጠጅ የጋበዘን ከመሆኑ በላይ አረፍንበት ቦታ ድረስ አንድ ድልብ ፍሪዳ ላከልን። ማግሥቱን እሁድ ስለነበር በዚህ ቦታ በሚገኝ በሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስቀደስን፤ ይህ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎቹ ሲመዛዘን በጌጡና በመልኩ በጣም ምስኪን ነው። በዚህ ቤተ ክርስቲያን

ትዳር የያዙ ሶስት ቄሶችና ሶስት ዲያቆኖች አሉ። እነዚህ ካህናት ሁሉም ለቤተ ክርስቲያኑ አገልሎት ጠቃሚ እንደመሆናቸው መጠን ቁጥራቸው ከዚያ ያነስ እንደሆነ ቅዳሴው ሊታጎል ይችላል። የመንደሩ ሹም የነበረው ያ ሰው ሃብቱንና ልጆቹን ሁሉ ትቶ ከመነኮሰ በኋላ በደብረቢዘን ገዳም ከአዲስ ገብ መነኩሴዎች ጋር ሆኖ ቁርባን ሲቀበልና ከቅዳሴውም በኋላ በክብር ከገዳሙ አለቃ ጋር ሲነጋገር አይቼዋለሁ።

ይመሩን የነበሩት ያገሩ ሰዎች ከዚህ እንድንሄድ ስለፈለጉ የዚያኑ ዕለት እሁድ ከቀትር በኋላ ተነሣን። በሰፊ ሜዳ ላይ ጉዞአችንን ወደፊት ቀጥለን በፖርቱጋል ያሉ ቀበሌዎችን በመሰለ በእዳሪና በታረሰ በመካከሉም የወይራ ዛፎች ብቻ በበቀሉበት ምድር አልፈን ሄድን። ከጉዞአችን በኋላ መልካም ቤቶች ባሉባቸው መንደሮች አጠገብ ደርሰን በዚያ በምትገኝ ወንዝ አጠገብ ላዳራችን ሠፈርን።

ምዕራፍ አስራ ስምንት፤ ባርዋ ከተማ ስለመድረሳችን፤ አምባሳደሩ ባሕር ነጋሹን ፍለጋ ስለመሄዱና ስለባሕር ነጋሹም ሁኔታ።

ከጸሎት ሶስት ሌግዋ ርቆ በሚገኝ ባርዋ በሚባል ቦታ ሰኔ 28 ቀን ደረስን። ይህ ቦታ የባሕር ነጋሹ ግዛት ዋና ከተማ ስለሆነ ዋና ዋኖቹ ቤተ ንጉሦች የሚገኙት በዚሁ ነው። ባሕር ነጋሹ ልክ እኛ በደረስንበት ቀን ሰራዌ በተባለ አውራጃ ከተማ ወደ ባራ ሄዶ ነበር። እኛ በደረስንበት ቀን መሄዱ ሊቀበለን ባለመፍቀዱ መስሎን ነበር፤ ሌሎች ሰዎች ግን የሄደበት ምክንያት ዓይኑን ስለታመመ ነው አሉን። በዚህ ቦታ ዝርግ ጣራ ባለው ባንድ ትልቅ ቤት ውስጥ ዐረፍን። ከሶስት ቀን በኋላ አምባሳደር ዶም ሩድሪጉ ድሊማ ባሕር ነጋሹ ወደሚገኝበት ቦታ እንድንሄድ ወስኖ ከርሱ ጋር አምስት ሰዎች በበቅሎ ሆነን ስንጓዝ ከዋልን በኋላ በተባለው ቦታ ወደ ማታ ደረስን። ከተነሣንበት እስከዚህ ቦታ ድረስ ያለው ርቀት ከሶስት

ተኩል እስከ አራት ሌግዋ ይሆናል፤ ካንዲት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሚገኘው ከቤተ ንጉሡ በር ድረስ እስክንደርስ ከበቅሎቻችን ወርደን በእግር ሄደን ከቤተ ክርስቲያኑ ስንደርስ ጸሎት አደረስን። ከዚህ በኋላ ወደቤተ ንጉሡ ሄደን ከባሕር ነጋሹ ልንገናኝ ስናስብ ሰዎች መጥተው እርሱ ተኝቶአልና ለመግባት አይቻልም ሲሉ ከለከሉን። ብዙ ከጠበቅን በኋላ ለመገናኘት በፍጹም የማይቻል ስለሆነብን ሁላችንም ባንድነት በፍየል ጉሮኖ ውስጥ ታፍገን ተኛን። ለመኝታችን ምንጣፍ ሁለት የበሬ አንጋሬ ለእራታችንም በአገሩ በብዛት የሚገኘውን እንጀራና ጠላ እንዲሁም አንድ በግ ሰጡን። በማግሥቱም ለመገናኘት ብዙ ከጠበቅን በኋላ እንድንገባ ተፈቀደልን፤ በመጀመርያው በር ላይ በእጃቸው አለንጋ የያዙ ሶስት በረኞች በርበሬ ካልሰጣችሁን እና ስገባም ብለው በበሩ ላይ ብዙ አቆሙን። ይህን በር አልፈን በሁለተኛው ላይ እንደደረስን ሌሎች ሶስት በረኞች አገኘን፤ እነዚህ በረኞች ከበፊተኞቹ የተሻሉና ማዕርጋቸውም ከፍ ያለ ይመስላል፤ በዚህም ቦታ እንደገና ግማሽ ሰዐት ያህል ገለባ በተጎዘጎዘበት ቦታ በብረቱ ውቀት ላይ አቁመውን ደጅ ጥናቱ ስለበዛብንና በእውነተኛው ስለተመረርን ሊቀበሉን ይፈቅዱ እንደሆነ ያስጠሩን ያለዚያ ወዳረፍንበት መሄዳችን ነው ሲል አምባሳደሩ ለባሕር ነጋሹ ላከበት። መልእክቱን አንድ ከፍ ያለ አጋፋሪ ተቀብሎ ሄዶ ይግቡ የሚል ትዕዛዝ ይዞ ተመለሰ። ባሕር ነጋሹ በዚያ አገር በብዛት በማይገኝ ፎቅ ባልሆነ ትልቅ ቤት በመናኛ መጋረጃ በተሸፈነ ባንድ አልጋ ላይ ሆኖ ዐይኑን ታሞ ባለቤቱ በራስጌው ተቀምጣ ደረስን።

ቀርበን እጅ ከነሣን በኋላ አምባሳደሩ ሐኪም ሊያዝ ፈቃደኛ መሆኑን ቢገልጽም ባሕር ነጋሹ ግን ለጊዜው ሐኪም አያስፈልገኝም በማለት ምስጋና እንኳ ሳያቀርብ በቀጥታ እምቢ አለ። በዚህን ጊዜ አምባሳደሩ ባሕር ነጋሹን በንጉሠ ነገሥቱ ስም እርዳታ በመጠየቅ ለመንገዳችን የሚያስፈልገንን ማናቸውንም ነገር ለምኖ ምንም እንኳ ይህ እርዳታ በቀጥታ ለኛ ቢደረግም ለፖርቱጋል ንጉሥ እንደተደረገ ያህል ስለሚቆጠር ወሮታውን ጠቅላይ ገዥውም የሚከፍሉት መሆናቸውን ከማረጋገጡ በላይ ከንጉሠ ነገሥቱም የሚገባውን ክብር

ለማግኘት እንዲችል ጉዳዩን የሚያቀርብ መሆኑን ጨምሮ ገለጸለት። ባሕር ነጋሹ የሚያስፈልገንን ነገር እንድንነግረው ስለጠየቀን ባስቸኳይ የሚያስፈልጉን አጋሰሶችና በቅሎዎች መሆናቸውን አምባሳደሩ ገለጸ፤ ነገር ግን ባሕር ነጋሹ ሊረዳን ስላልፈቀደ በቅሎ ልሰጣችሁ አልችልም፤ በቅሎ ከፈለጋችሁ በገንዘባችሁ መግዛት አለባችሁ፤ ሌላውን የሚያስፈልጋችሁን አዝላችኋለሁ፤ ከልጆቼ አንዱ ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲሄድ አዛለሁ ብሎ በዚሁ ብቻ አሰናበተን።

ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ፤ በባሕር ነጋሹ ቤተንጉሥ ስለመጋበዛችን፤ በዚህ አገር ርቀትን በሌግዋ ስላለመለካታቸው።

ባሕር ነጋሹ ከነበረበት ቤት ራቅ ብላ በምትገኝ ባንዲት ቤት አዳራሽ ውስጥ ሳጣራ በተነጠፈበት ምድር ላይ ካስቀመጡን ባኋላ ለምግባችን አንድ ገበቴ በሶና ጠጅም በቀንድ አቀረቡልን። ይህን የመሰለ ምግብ ከዚህ በፊት አይተን ስለማናውቅ ልንበላ አልፈቀድንም፤ ነገር ግን አገሩን ከለመድነው በኋላ ያለችግር እንበላ ጀመርን። ስለዚህ ይህን ምግብ ምንም ሳንቀምስለት እኩለ ቀን ሊሆን ሁለት ሰዓት ሲቀረው ተነሥተን ወደ አረፍንበት ቦታ ሄድን። ግማሽ ሌግዋ ወይም ከዚህ በላይ እልፍ እንዳልን አንድ ሰው እየሮጠ ከኋላችን መጥቶ እንድንጠብቀው ለምኖን የባሕር ነጋሹ እናት ሌላ ምግብ ያዘዘችልን መሆንዋን ከመግለጹ በላይ በአገር ወግ መሠረት የሚቀርበውን ምግብ ሳይበሉ መሄድ ቅር የሚያሰኝ ነገር መሆኑንም አሳሰበን። ስለዚህ ለመመገብ ወደኋላ ተመልሰን በቤት ከገባን በኋላ አምስት የስንዴ እንጀራና አንድ ቀንድ ጠጅ እንደገና ቀረበልን። የበሬ ቀንድ ዋንጫ ተሠርቶ በልዩ ልዩ መኳንንትና በንጉሡ ነገሥቱ ቤትም መጠጥ ስለሚሰጥበት ጠጅ በቀንድ መቅረቡ አንባቢውን ሊያስደንቀው አይገባም፤ አንዳንዱ ትልልቅ ቀንድ አምስትና ስድስት ከናዳዎች[1] ይይዛል። የባሕር ነጋሹ እናት በሶው

እንደገና እንዲቀርብ አዛልን በለን። በሶሞቅ ባለ ውኃ ተበስብሶ የሚቀርብ የተቆላ ስንዴ ዱቄት ነው።

ምግቡን በልተን ገበታ ዝቅ ካለ በኋላ ዕቃችንና ጓዛችን ወደ ሚገኝበት ወደባርዋ ከተማ ሄድን። በኢትዮጵያ ውስጥ የርቀት መለኪያ ሌግዋ የለም፤ ለምሳሌ ከዚህ እስከዚያ ቦታ ድረስ ያለው ርቀት ምን ያህል ይሆናል ሲሉ አንዱን ሰው ቢጠይቁት ጠዋት ጸሐይ ስትወጣ ብትነሱ ጸሐይ ከፍ ስትል ወይም በቀትር ወይም ጸሐይ ስትዘቀዘቅ በተባለው ቦታ ትደርሳላችሁ፤ ነገር ግን ቀስ ብላችሁ ከሄዳችሁ ከብት ሲገባ ትደርሳላችሁ በሚል አኳኋን መልስ ይሰጣል። ብዙ መንገድ ከሆነ አንድ ሰንበት ይፈጃል ይላሉ እነጂ ቀዋሚ በሆነ መስፈርያ ሊገልጹ አይችሉም። ለምሳሌ ከፍ ብዬ እንደገለጽሁት ከባርዋ እስከ ባራ ያለው ርቀት ከሶስት ተኩል እስከ አራት ሌግዋ አይበልጥም ስል የኛን አገማመት ገልጫለሁ፤ እኛ ይህን ርቀት ካንድ ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ የምንሄደው ከመሆናችን በላይ ካንዱ ወዳንዱ ቦታ በቀላሉ እየተዘዋወርን ምሳ እየበላንና ሌላም ጉዳያችንን እያከናወንን እንዲያውም ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት ውሎ ገባ ደርሰን እንመለስ ነበር። ነገር ግን የአገሩ ተወላጆች ቀስ ብለው ስለሚሄዱ ይህን ያንድ ቀን መንገድ አድርገው ይገምቱታል።

በሁለቱ ቦታዎች መካከል ልዩ ልዩ ሰብል ማለት ስንዴና ገብስ በቆሎ፤ ሽንብራና ምስር፤ ልዩ ልዩ ዓይነት አትክልትና ከዚህ በፊት አይተናቸው የማናውቃቸው አዝርዕት የበቀሉባቸው እርሻዎች አሉ። በጎዳናው ላይ ሆኖ በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለውን ቦታ ሲመለከቱት ከፍ ባለ ቦታ ላይ የተቆረቆሩ ከሃምሳ በላይ የሆኑ መንደሮች ይታያሉ። በዚህ ሰፊ ሜዳ አገርና በታረሰውም ምድር ላይ በአርባና ሃምሳ እየተከፋፈሉ የሚሄዱ ብዙ አውሬ የቀንድ ከብት መንጋዎች ይገኛሉ፤ አደን ፖርቱጊዞችን ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው፤ ነገር ግን ያገሩ ሕዝብ ያደንን ሞያ እምብዛም የማያውቅ ስለመሆኑ አውሬ ሰብሉን ሲያጠፋበት ይታያል።

ምዕራፍ ሃያ፤ ስለባርዋ፤ በውስጡም ስለሚገኙት ሴቶችና ሕዝብ፤ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ስለሚደረግ ጋብቻ።

መጀመርያ ባረፍንበትና በኋላም ተመልሰን ስንመጣ ብዙ ጊዜ የኖርንበት ባርዋ የተባለው ከተማ በግምት ከሶስት መቶ በላይ የሚሆኑ ቤተ ሰቦች የሚገኙበት ሲሆን ከነዚሁ ውስጥ ይበልጡ ሴቶች ናቸው፤ ይህ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት ቀጥሎ እንገልጻለን፤ አንደኛ ይህ ቦታ የንጉሥ ጭፍሮች መኖርያ በመሆኑ በዚህ ከሚኖሩት ጭፍሮች በጨዋነት የሚቀመጡ ጥቂት ናቸው። ሁለተኛም ይህ ከተማ የባሕር ነጋሹ መኖርያ ስለሆነ እርሱን ለማጀብ በየቀኑ ከሶስት መቶ በላይ የሚሆኑ ፈረሰኞች ወደቤቱ ሲመጡ ደግሞም በነርሱ ልክ ለሌላ ሥራ ወደዚያ ከሚመጡት ውስጥ በጨዋነት የሚቀመጡ ጥቂት ስለሆኑ በዚህ ቦታ ኮረዶች ሊኖሩ ቻሉ፤ እነዚህ ኮረዶች ካረጁ በኋላ ወይም በወጣትነታቸው ጊዜ በከተማው በየሳምንቱ ማክሰኞ ሶስት ወይም አራት መቶ ሰዎች በሚገኙበት ገበያ ላይ ሚዛናቸውን እየያዙ እየሄዱ የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት ስንዴና ጨው ይመዝናሉ፤ ከዚህም በላይ በዚያ የሚያድሩትን ሰዎች ያስተናግዳሉ፤ እንዲሁም ሳይሸጥላቸው የቀረው ሰዎችን ዕቃም እስከሚከተለው የገበያ ቀን ድረስ ያስቀምጡላቸዋል። በዚህ ቦታ ጋለሞቶች የበዙበት ሌላው ምክንያት ደግሞ በቂ ምግብ ያላቸው ወንዶች ሁሉ ሁለት ወይም ሶስት ሴቶች ይዘው መቀመጥን ስለሚወዱ ነው። ይህን አሳፋሪ ተግባር የሚገስጽ ንጉሥ ነገሥቱ ወይም ፍርድ ቤቶቹ ሳይሆኑ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት። ሁለት ወይም ብዙ ሚስቶች ያለው ወንድ በቤተ ክርስቲያን እንዳይገባና ቁርባን እንዳይቀበል ከመከልከሉ በላይ በተጨማሪ ይገዘታል።

እኅት የምሆነው አንድ ዘመዴና እኔ አባቢታይ በተባለ ባንድ ሰው ቤት አንድ ዓመት ተኩል ተቀምጠን ስለነበርን ይህ ሰው እኛ በመልካም በቅርብ የምናውቃቸው በሕይወታቸው ያሉ ሶስት ሚስቶች እንደነበሩት እናውቅ ነበር። እንዲያውም ሰባት ሚስቶች አግብቶ ከነዚህ ሚስቶች የተወለዱ በጠቅላላው ሰላሳ ልጆች ነበሩት

እየተባለ መወራቱን ሰምተናል። ስለዚህ እላይ እንደተገለጸው ይህን ነውር ተግባር የሚፈጽሙትን ሰዎች የቁርባንን በረከት በመከልከል የምትገስጻቸው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት። ስሙን ከዚህ በፊት የጠቀስነው ያ ሰው ይህን ተግሳጽ በመስማት እኛ ከዚያ ከመሄዳችን በፊት በመጨረሻ ካገባት ወጣት ሚስቱ ጋር ብቻ ለመኖር ወስኖ ሌሎቹን ሁለቱን ፈታቸው። ከዚህ በኋላ መብቱ ተመልሶለት ካንድ ሚስት በላይ እንደሌላቸው ምዕመናን ተቆጥሮ በቤተ ክርስቲያን ይገባና ቁርባን ይቀበል ጀመረ። ስለዚህ በዚህ ቦታ ጋለሞታዎች የበረከቱበት ምክንያት ወንዶቹ ባንድ ጊዜ ሁለት ሶስት ወይም የፈቀዱትን ያህል ለማግባት የሚያስችላቸው ሃብት ስላላቸው ነው።

በዚህ አገር ጋብቻ የጸና ነገር ስለይደለ በሁለቱ መካከል አንዳች አለመገባባት ሲፈጠር ብዙውን ጊዜ ፍች ይደርሳሉ። ከዕለታት አንድ ቀን ባንድ የሰማንያ ጋብቻ ስነሥርዓት ላይ ተገኝቼ ከጥሎ በተመለከተው አኳኋን ሲፈጸም አይቻለሁ፤ ከጥቂት ቤቶች ፊት ለፊት በሚገኝ ባንድ አደባባይ ላይ አንድ ድንክ አልጋ ተዘርግቶ በዚያ አልጋ ላይ ሙሽሮቹ እንደተቀመጡ ሶስት ቄሶች ሃሌሉያ እያሉ በማዜም አልጋውን ሶስት ጊዜ ዞሩት። ይህ ከተፈጸመ በኋላ ከሙሽሮቹ ላይ ጥቂት ጠጉር ቆርጠው ወስደው ይህን ጠጉር በጠጅ ካራሱት በኋላ የሙሽራውን በሙሽራይቱ የሙሽራይቱን በሙሽራው ራስ ላይ ጠጉሩ ከተቆረጠበት ቦታ አኑረው ቅዳሴ ጠበል ካፈሰሱበት በኋላ የድግሱ መብልና የሠርጉም ጨዋታ ተጀመረ። ከመሸም በኋላ ሙሽሮቹ በጫጉላ ይገቡና አንድ ወር ሙሉ በመከባከብ ሲቀመጡ ከነርሱ ጋር ከሚገኘው ከሚዜአቸው በስተቀር ከማንም ጋር አይገናኙም። ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ሚዜአቸው ይሄዳል። ሙሽራይቱ የሃብታም ልጅ ከሆነች ግን በጫጉላ አምስት ስድስት ወር ትቆያለች። በፊቱዋ ላይ ያለውን ጥቁር ዓይነርግብም በዚሁ ጊዜ ውስጥ አትገፍም። ነፍሰ ጡር ከሆነች ቀደም ብላ፤ የተወሰነው ጊዜ ካለፈ ግን ነፍሰ ጡር ባትሆንም መግፈፍ አለባት።

ምዕራፍ ሃያ አንድ፤ ስለጋብቻና ስለበረከት፤ ስለሰማንያና ስለፍችም።

የአገሩ አጠራር «ጳጳስ» የሚላቸው አቡነ ማርቆስ ከዕለታት አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያኑ በር ፊት ለፊት ተቀምጠው ለነበሩት አንድ ሙሽራና ሙሽሪት ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን በረከት ሲሰጡ አይቻለሁ። ሙሽሮቹ በአልጋ ላይ እንደተቀመጡ አቡኑ መስቀልና ጽና ይዘው በዙሪያቸው ከዞሩ በኋላ እጃቸውን በሙሽሬቹ አናት ላይ አሳርፈው «እግዚአብሔር በወንጌሉ ላይ ያዘዘውን አክብሩ፤ ከዛሬ ጀምሮ ባንድ ሥጋ የተቆራኛችሁ ሁለት ሰዎች ናችሁ እንጂ የተለያያችሁ አይደላችሁም፤ ልባችሁና ፈቃዳችሁ መተባበር አለባቸው» ብለዋቸው ካቆረቡዋቸው በኋላ ሙሽሮቹ አሳርገው ሄዱ። ይህ ስነሥርዓት ሲፈጸም ያየሁት በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በሚገኝ ደራ በተባለ ቦታ ነው። ከዚህም ሌላ በባሕር ነጋሹ ግዛት ውስጥ ሸከት በተባለ ቦታ ውስጥ የሰማንያ ጋብቻ ሲፈጸም አይቻለሁ፤ የሰማንያው ድርድር ባጭሩ «ብተውሽ ወይም ብትተይኝ ይህን ያህል መቀጫ እከፍላለሁ» የሚል ነው። መቀጫ የሚባለው የሰውዬውን ወይም የሴትዮዋን አቅም በመገመት እንደመሆኑ መጠን በወርቅ፤ በብር፤ በበቅሎች፤ በልብስ፤ በከብቶች፤ በፍየሎች ወይም በቁና በሚወሰን እህል እንዲከፈል ይወሰናል። ፍችውን ፈላጊው ክፍል መቀጫ ሊያስጥሉበት የማይችሉትን ጥቃቅን ምክንያቶች በማሳበብ ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ እንዳሻቸው ጋብቻውን ያፈርሳሉ። ጋብቻን አክብረው የሚኖሩ አንዳንድ ሰዎችም ቢኖሩም ሚስቶቻቸውን በፍጹም ሊፈቱ የማይችሉ ቄሶችና ገበሬዎች ናቸው፤ በመጨረሻ የተጠቀሱት ወደውም ሆነ በግዴታ ጋብቻቸውን በማክበር ሚስቶቻቸውን ወደው የሚኖሩበት ሴቶች ባሎቻቸውን እየተከተሉ በግብርናው ሥራ በአረምም ስለሚረዱ ገበሬዎቹም የዕለት ሥራቸውን አከናውነው ማታ ወደቤታቸው ሲመለሱ ሃሳባቸውን ጥለው ጥቂት ለማረፍ ስለሚችሉና ልጆቻቸውንም ለማሳደግ ስለሚረዱዋቸው ነው። ለምሳሌ ዶሪ የተባለው መጀመርያ ያወቅነው ባሕር ነጋሽ ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሲያገባ ለቀድሞይቱ ሚስቱካሣ አንድ መቶ ወቄት ወርቅ ከፈላት፤ ይህች የተፈታችው ሴት የባሕር ነጋሹ (ማለት የቀድሞ ባልዋ) ወንድም የነበረውን አሮን የተባለ አንድ መስፍን አገባች። ይህች ሴት ከሁለቱ ወንድማማቾች እኛ በደንብ የምናውቃቸው ልጆች ወልዳላቸዋለች። እንድዋን ሴት ያገቡ እነዚህ ሁለቱ ወንድማማቾች የንገሥ ነገሥቱ ሚስት ወንድሞች ናቸው። ወደቤተ መንግሥቱ የሄድን ሁሉ ያየናት የንጉሠ ነገሥቱ እህት የሆነች ወይዘሮ ሮማነ ወርቅ የተባለች ሴት ወይዘሮ የመሳፍንት ዘር የሆነ አንድ ወጣት የጨዋ ልጅ አግብታ ትኖር ነበር፤ ነገር ግን እኛ እዚያ በነበርንበት ጊዜ ይህን ሰው ፈትታ ከአርባ ዓመት በላይ ዕድሜ የነበረውን አቡሄር በሚያስኝ ማዕርግ የሚጠራ የዓቃቤ ሰዓት ልጅ አገባች። ዓቃቤ ሰዓት በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ከፍተኛውን ማዕርግ ይዞ የሚገኝ ነው። ስለዚህ ይህን የመሰሉ ብዙ ፍችዎች አይቻለሁ፤ እነዚህን ምሳሌዎች መጥቀሴ ሰዎቹ የታወቁ በመሆናቸው ብቻ ነው። አሮን የወንድሙን ሚስት አገባ ስል ከላይ የጠቀስሁትን የሚያነብ እምብዛም ማድነቅ አይገባውም፤ ምክንያቱም በአገሩ ባሕል መሠረት ወንድም የወንድሙን ሚስት ቢደፍር እንደነውር የሚቆጠር ነገር አይደለም። አሮን የወንድሙን ሚስት አግብቶ ልጆች ከወለደችለት በኋላ ፈቶአት ለሁለተኛ ጊዜ አግብቶ አሁን ካዲሲቱ ሚስቱ ጋር ይገኛል።

ምዕራፍ ሃያ ሁለት፤ የሕጻናት ጥምቀት፤ ግዝረትና የቀብር ስነሥርዐት።

ግዝረትን እግዚአብሔር በኦሪት ያዘዘው ሕግ መሆኑን መሠረት በማድረግ ይህን ተግባር የሚፈጽመው ሰው ያላንዳች ስነሥርዐት ያከናውነዋል። በኦሪት ሕግ የማይገኝ ሕግን በመከተል ሴቶችን እንደወንዶች ይገርዛሉ ስንል የምንገልጸውን የሚያነብ ሰው ሊደነቅ አይገባውም። ወንዶች ከተወለዱ ከአርባ ቀን በኋላ ሴቶች ደግሞ በሰልሳ ቀን ዕድሜአቸው ይጠመቃሉ፤ ከዚህ ቀን በፊት የሞቱ እንደሆነ ሳይጠመቁ ይቀበራሉ ማለት ነው። ስለዚህ ሕፃናት እንደተወለዱ አለማጥመቅ ስህተት መሆኑንና ይልቁንም «ከሥጋ የተወለደ

ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው፤» የሚለውን የወንጌል ቃል በቀጥታ የሚቃረን መሆኑን ደጋግሜ ለብዙ ሰዎች እንደሚ ስረዳቱ መጠን የእናቶቹ እምነትና ሴቶቹ በነፍሰጡርነታቸው ጊዜ የሚቀበሉት ቁርባን ለሕፃናቱ ክርስትና በቂ ሊሆን ይችላል ሲሉ ደጋግመው መልሰውልኛል። ሕፃናቱ የሚጠመቁት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ነው። የሚጠመቁት በውኃ ስለሆነ ከጥምቀቱ በፊት ውኃውን በማብረጃ ወይም በቅምጫና አኑረው ይባርኩታል። ከዚህ በኋላ ሕፃናቱን እናታቸውን ደረታቸውንና ትከሻቸውን በቅበአ ቅዱስ ያብሱዋቸዋል። ክሪዝማ ወይም የቅበአት ዘይት ስለሌላቸው በዚህ አይገለገሉም። የጥምቀቱ ስነሥርዐት የሚፈጀው ጊዜ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ስነሥርዐት ጋር ትክክል ነው፤ ሕፃኑን የማጥመቁ ደንብ ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው የሚፈጸም፤ የሕፃኑ ክርስትና አባት የሆነው ሰው ሕፃኑን ከእናቱ እጅ ተቀብሎ በብብቱ ሥር ሲያ ቅፈው ቄሱ በዚያኑ ጊዜ ባንድ እጁ ውኃውን እያንቆረቆረ «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ» እያለ በሌላው እጁ ሕፃኑን ያጥበዋል። ሕፃናት የሚጠመቁት ቅዳሜና እሁድ ስለሆነ ቁርባን ለመቀበል እንዲደርሱ በማለት የሚጠመቁት በማለዳ ነው። የሚቀርቡት ሕፃናት ሁሉ መቁረብ አለባቸው፤ ለስላሳ ያልሆነ ነገርን ለመዋጥ ምንም እንኳ ዕድሜአቸው ባይፈቅድላቸውም ሥጋ ወደሙን እንዳቅማቸው በውኃ እየጋቱ እንዲውጡ ያደርጓቸዋል። ሕፃናቱ ቁርባን እንዲወስዱ ማድረግ አስጊና የማያስፈልግም ነገር መሆኑን ጨምሬ ገለጽሁላቸው።

ሕፃናቱ እናታቸው በቅበአ ቅዱስ ይታበሳል ስል ስለገለጽሁት ከዚህ በታች አትታለሁ። ለጥምቀት የሚመጡት ሕፃናት ሁሉ የተላጩና አፍንጫቸውንም የተበጡ ናቸው፤ ይህን የሚያደርጉት በእሳት በመተኮስ ወይም አንዳች የክርስትና ሕግን በመከተል ሳይሆን ለጌጥ ሲሉ በቀዝቃዛ ብረት በመብጣት ነገር ነው። ይህን የሚያ ከናውኑት በተለይ በሥራቸው ቅልጥፍናና በሞያቸው የታወቁ ሴቶች ሲሆኑ ሥራቸውን ቀጥሎ በተመለከተው መንገድ ይፈጽማሉ። የነጭ ሽንኩርት ቅጠል አምጥተው የሕፃኑን ዓይን ማዕዘን ከሸፈኑት በኋላ በቅጠሉ ዙርያ በስለቱ ይበጡታል፤ ከዚያን በኋላ ብጡን በጣታቸው

እየገፉ ያሰፉትና በስንጥቁ ላይ በመጀመርያ ሰም በሰሙም ላይ ሊጥ ያኖሩበትና በጨርቅ ሸፍነው ካሳደሩት በኋላ ይፈቱታል፤ ቁስሉ ከዳነ በኋላ ጠባሳው በጥቁር ቆዳቸው ላይ ሁል ጊዜ እሳት እንደመሰለ ይቀራል።

አንድ ሰው ሲሞት ብዛታቸው ከልክ ያለፈ አዋቂዎችና ወጣቶች ለቀብር ይወጣሉ፤ የቀብሩ ስነሥርዐት ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ይፈጸማል። አስከሬኑን ተሸክመው ሲጓዙ ጥዋፍ እያበሩ አይከ ተሉም፤ ነገር ግን ጽና ይዞ እያጠኑ መሄድ የተለመደ ነገር ነው። አስከሬኑ ተከፍኖና ተሸፍኖ በቃሬዛ ላይ አኑረው ያጉዙታል፤ ሙዋቹ ሃብታም ሰው ከነበረ ግን አስከሬኑ በጠፍር አልጋ ላይ ሆኖ በከፈኑ ላይ ነት ተደርቦ ነው የሚጓዝ። አስከሬኑ ከመውጣቱ በፊት ካህና ቱ እቤት ድረስ መጥተው ጥቂት ከጸለዩ በኋላ መስቀልና ጽና የቅዳሴ ጸበልም ይዘው አስፈላጊውን የጉዞ ፍትሃት ስነሥርዐት እያስፈጸሙ ይሄዳሉ። በጉዞው ላይ ካህናቱ በፍጥነት ስለሚሄዱ የሚደርስባቸው ሰው የለም። በመቃብሩ አጠገብ እንደደረሱ አስከሬኑን በዚያው አቅራቢያ ያኖሩታል እንጂ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አያስገቡትም። ፍትሃቱ በኛ ሥርዐት በተለመደው አኳኋን አይደለም የሚፈጸመው፤ ከመዝሙረ ዳዊት ወይም ከመጽሐፈ ኢዮብ ጥቅስ አያነቡም። በፍትሃቱ ስነሥርዐት ላይ የሚነበበው ምን እንደነበረ ለማወቅ ጠይቄ የዮሐንስ ወንጌል በሙሉ መሆኑን ገልጸውልኛል።

ከዚህ በኋላ መቃብሩን አጥነውና ጠበል ረጭተው ከባረኩት በኋላ አስከሬኑን ይቀብሩታል፤ ለሙዋች ነፍስ ወይም በሕይወት ላለ ሰው መጸለይ የተለመደ ነገር አይደለም፤ በያንዳንዱ ቤተ ክርስ ቲያን በቀን ካንድ ጊዜ በላይ ቅዳሴ የለም። ወደቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት ሁሉ ቁርባን ይቀበላሉ።

ምዕራፍ ሃያ ሶስት፤ ስለባሕር ነጋሹ ግዛት ዋና ከተማ ባርዋ፤ ባቅራቢያዋም ስለሚገኙ የዱር አራዊትና ስለአደን።

ባርዋ ባንድ ወንዝ ዳር በሚገኝ በትልቅ የአለት ገደል ጫፍ ላይ የተሠራች እጅግ ያማረች ከተማ ናት፤ በዚሁ ገደል ጫፍ ላይ የባሕር ነጋሹ ቤተ ንጉሦችም ይገኛሉ። እነዚህ ቤተ ንጉሦች ከገደሉ አፋፍ ላይ ባማረ አኳኋን የተሠሩ ምሽጎችን ይመስላሉ። ቤተ ንገሡ የተሠራበት ቦታ ለጥ ያለ ሜዳ ሲሆን ከሜዳው ድንበሮች ላይ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ቤቶች የሚገኙባቸው መንደሮች አሉ። ልዩ ልዩ ከብቶች ማለት ላሞችና በሮች ፍየሎችና በጎች ልዩ ልዩ የአደን አውሬዎችም አሉ። በየወንዞቹ ውስጥ አሣና ዓይነታቸው የበዛ ዳክዬዎች በየብሱም ላይ የሜዳ ከብቶችና ሌሎች ብዙ ዓይነት አራዊት፤ በየመስኩም ብዙ ጥንቸሎች ይገኛሉ። በየቀኑ ጥዋት ያለ ውሻ እርዳታ በወጥመድ ብቻ ሃያና ሰላሳ ጥንቸሎች እንይዝ ነበር። በታላቅነታቸውና በእግራቸው ቀለም ብቻ ልዩ ሲሆኑ በሌላው ረገድ በኛው አገር የሚገኙትን የሚመስሉ ሶስት ዓይነት ቆቆች አይተናል። በእግራቸውና በአፋቸው ብጫነት ብቻ ሲለያዩ በሌላው ሁኔታቸው በኛው አገር የሚገኙትን የሚመስሉ ብዙ አሉ፤ ከነዚህም ሌላ በትልቅነታቸው ዶሮችን የሚተካከሉ እንደኛው አገሮቹ አፋቸውና እግራቸው ቀይ የሆነ ሌሎችም አሉ። በአፋቸውና በእግራቸው አመድማ መልክነት ብቻ ሲለዩ በትልቅነታቸው በቀለማቸውና በማናቸውም ረገድ ከኛዎቹ የማይለዩ ሌሎችም አሉ። ቆቆቹ እንደቀለማቸው ማማር ሥጋቸውም ቃናው ማለፊያ ነው። በብዙ አእላፋት የሚቆጠሩ ድርጭቶች ቆቆችና ኾግራዎች እነዚሁኑ የመሳሰሉ ሌሎች ሥጋቸው የሚበላ ወፎችም ምድሩን ሸፍነውት ይታያሉ። የሚናገር ወፍና ሌሎችም ከዚህ በፊት አይተናቸው የማናውቅ ወፎች በብዛት ይገኛሉ። ንስር፤ ጆፌ አሞራ፤ ጭልፊት፤ ቁራና ሾለቅ ሌሎችም ሥጋበል አሞራዎች በብዛት በያለበት ይገኛሉ። በየተራሮቹ ላይ ከርከሮዎች፤ አጋዘኖች፤ ድኩላዎችና ሌላም እነዚህን የመሳሰሉ ሥጋቸው የሚበላ የዱር አራዊት አሉ። አገሩ እንደዚያ

ሕዝብ የበዛበት ሲሆን የዱር አራዊትና አሦች እንዴት በብዛት ሊገኙ ቻሉ በማለት በማድነቅ የሚያስጠይቅ ነው።

የዱር አራዊት በብርካቴ መገኘታቸው አገሬው ስለማያድንና አሣም ስለማያጸምድ፤ ወይም ለዚሁ አገልግሎት የሚውል መሣርያና ዘዴም ስለሌለው ይልቁንም የአደን ምኞት ያላቸው ሰዎች ባለመኖራቸው ምክንያት ይመስለኛል። አንበሳና ነብር፤ ተሁላና ግስላ፤ ጅብና ቀበሮ ሌሎችም ከዚያ በፊት የማናውቃቸው ዓይነታቸው የበዛ ሥጋ በል አራዊት አሉ። ሕዝቡ ምንም እንኳ በጣም ቢፈራም የዱር አራዊት ብዙ አደጋን ጣሉ ማለትን አልሰማሁም። ይሁን እንጂ ከባርዋ ግማሽ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ካማርዋ በተባለ ቦታ ላይ አንድ አደጋ መድረሱን ሰምቻለሁ፤ አንድ ሰው ከልጁ ጋር ሆኖ መንጋውን በመጠበቅ ሌሊት ከአጥሩ በር አጠገብ እንደተኛ በድንገት አንበሳ መጥቶ ማንም ሳይሰማ ልጁን ትቶ ሰውዬውን ገድሎ አፍንጫውን ቦጭቆ ደረቱን ሰንጥቆ ልቡን አወጣው። አንበሳው የሰውን ሥጋ ጣእም ለምድዋልና ለወደፊት አደጋ መጣሉ አይቀርም በማለት የአገሩ ሕዝብ በጣም ይፈራ ነበር። አንዳች አደጋ ይደርስብን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስላልነበር በዚያ ቦታ አቅራቢያ ለአደን ስንሄድ ነብርና ግስላ እንጂ አንበሳን ከቶ አላጋጠመንም፤ እኛ ልነገድላቸው ስላልፈለግን አልተተናኮሉንም።

ምዕራፍ ሃያ አራት፤ የባሕር ነጋሹ ግዛት፤ ከርሱ ትዕዛዝና ሥልጣን በታች ስላሉት መሳፍትና አገረገዥዎች፤ ስለሚከፍሉትም ግብር።

የባሕር ነጋሹ አገር አከፋፈል ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው። የማዕርግ ስሙ ትርጉም እንደሚያመለክተው ባሕር ነጋሽ ማለት የባሕር አዋሳኝ ግዛት ንጉሥ ማለት ነው። ይህ የንጉሥነት ማዕርግ ሲሰጠው ራስ ወርቅ ይጭናል፤ ይሁን እንጂ ይህ ራስ ወርቅ ንጉሠ ነገሥቱ ከፈቀደበት ጊዜ በላይ ከባሕር ነጋሹ ዘንድ ሊቆይ አይ

ችልም። እኛ በዚያ አገር በቆየንበት የስድስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አራት ባሕር ነጋሾች ተለዋውጠዋል፤ ከነዚህም ውስጥ እኛ በደረስን ጊዜ የነበረው ባሕር ነጋሽ ዶሪ የተባለ ሰው ነበር። ይህ ሲሞት በንጉሡ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ማዕርጉ ቡላ ለተባለው ዕድሜው አስር ወይም አስራ ሁለት ለሆነ ለሙዋቹ ልጅ ተላለፈ። ይህ ልጅ ነግሦ ጥቂት እንደቆየ ወደንጉሡ ነገሥቱ ዘንድ ተጠርቶ ሄደና ማዕርጉ ተወስዶበት ራስ ነቢያት ለተባለ ለአንድ መስፍን ተሰጠ። ራስ ነቢያት በዚሁ ማዕርግ ሁለት ዓመት ካገለገለ በኋላ እርሱም ወደ ቤተ መንግሥቱ ተጠርቶ የቢትወደድነት ማዕርግ ተሰጥቶት ባሕር ነጋሽነቱ አዲቢ ለተባለ ለአንድ ሌላ ሰው ተስጥቶ አሁን በዚሁ ቦታ ላይ ይገኛል። ከባሕር ነጋሹ በታች ሹም በሚያሰኝ የማዕርግ ስም የሚታወቁ ብዙ መሳፍንት አሉ። ከነዚሁም ውስጥ ሽሬ የተባለውን ታላቅ አውራጃ የሚገዛ «ሹም ሽሬ» የተባለው ነው፤ ይህ ሰው የንጉሡ ነገሥቱ እህት ባል ነው። ይህ ግዛት ከመ ንገዳችን እጅግ የራቀ በመሆኑ አልሄድንበትም። እኛ የጎበኘነው ሌላ የሹም ግዛት ሰራዌ ይባላል፤ የዚህ አውራጃ ሹም ጋሻና ጦር ቀስትም የያዙ አስራ አምስት ሺ ወታደሮች አሉት ይባላል። ከነዚህ ሌላ ጻምአና ቡር የተባሉ ሌሎች የሹም ግዛቶች አሉ። በመጨረሻ የተጠቀሱት እነዚህ ሁለት ቦታዎች ከዚህ በፊት ተጠቃለው ባንድ አውራጃነት ይተዳደሩ ነበር፤ ነገር ግን አውራጃው ትልቅ ስለነበር በባሕር ነጋሹ ላይ ያምጻል ብሎ በመስጋት ንጉሠ ነግሥቱ ራሱ በሁለት እንዲከፈል አደረገው፤ ይሁን እንጂ እንዲሁም ሆኖ እያን ዳንዱ ግዛት አሁንም ታላቅ ነው። አሁን በሁለት ተከፍሎ የሚገኝ ይህ ግዛት ጥንት የንግሥተ ሕንደኬ አገር ነበር ይባላል። በአገሩ ውስጥ የክርስትናን ሃይማኖት ለመጀመርያ ጊዜ የተቀበለችና ጌታችን የሱስም ኃይለኛይቱ ያላት ይህችኑ ንግሥት ሕንደኬን ነው። ከግብጽ ጋር የሚዋሰኑት ደፍላና ከንፌላ የተባሉ ባለሥል ጣኖች የሚገዙዋቸው ሌሎች የሹም ግዛቶች አሉ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አውራጃዎች ሁሉ ነጋሪት እንዲ ኖራቸው የተፈቀደላቸው ታላላቅ መሳፍንት ያሉባቸው ናቸው፤ እነዚህ መሳፍት ባሕር ነጋሹ በሄደበት ቦታ ሁሉና በጠየቃቸውም

ጊዜ በጦርነት ይረዱትል። ከመሳፍንቱ ሌላ ከባሕር ነጋሹ ሥልጣን ሥር ያሉ ብዙ ራሶች አሉ። ከነዚህ አንዱ እኛ የምናውቀው በአገሩ አጠራር «ጨዋ» የተባሉ አስራ አምስት ሺ ባለመሣርያ ወታደሮች የነበሩት ራስ አደራው ነበር። ራስ አደራውን ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ደጅ ሲጠና አይቼው ነበር፤ ከወገቡ በታች በጣም ያማረ የሐር ጨርቅ አሸርጦ ከላይ ግን ሸሚዝ ሳይለብስ የአንበሳ ጎፈር ደርቦ በቀኝ እጁ ጦር በግራ እጁ ጋሻ ይዞ ነበር። ይህ ሰው በንደዚህ አኳኋን ለብሶ መሄዱን በማድነቅ ምክንያቱን ብጠይቅ የጨዋዎች ወይም የባለ መሣርያ ሠራዊት አለቃ በመ ሆኑ እንደዚህ መልበሱ ትልቅ ክብር ያለው ሰው ለመሆኑ ምልክት ነው አሉኝ። ይህ ሰው ጋሻና ጦር የያዙ ሃያ ወይም ሰላሳ ሰዎች አስከትሎ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲሄድ ባለ ጉዳዮችን አስከትሎ የሚሄድ ዳኛ ይመስል ነበር። ከዚህም ሌላ ራስ ተክሌና ራስ ያዕቆብ የተባሉ ታላላቅ አውራጃዎችን የሚገዙ ነገር ግን ማዕርግ የሌላቸውን አገረ ገዥዎች ተዋውቂ ነበር።

ከላይ የጠቀስናቸው ታላላቅ ገዥዎች ሁሉ የባሕር ነጋሹ ጭፍሮች ሲሆኑ ባሕር ነጋሹ ብዙ ጭፍሮች ያሉት ትልቅ አገርን የሚያስተዳድር ከፍ ያለ ክብር ያለው ሰው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፤ ይሁን እንጂ ባሕር ነጋሹም ሆነ ጭፍሮቹ የንጉሠ ነገሥቱ ዜጎች በመሆናቸው እንዳስፈለገው የሚሾማቸውና የሚሽራቸው ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ነው፤ ግብርም የሚከፍሉት ለርሱው ነው። እነዚህ መሳፍንት የሚገዙዋቸው አውራጃዎች የሚገኙት ማለፊያ ፈረሶችና የወርቀ ዘቦ የሐርም ጨርቅ ከሚገኝባቸው ከግብጽና ከአረብ አገሮች ድንበር በመሆናቸው ግብራቸውን የሚከፍሉት በዚሁ ሃብት ነው። ይህንኑ ለባሕር ነጋሹ ያስረክቡና እርሱም በየዓመቱ የራሱንና የጭፍሮቹን ድርሻ ለንጉሠ ነገሥቱ አንድ መቶ ሃምሳ ፈረሶች ይከፍላል። የሐሩንና የወርቀዘቦውን ልክ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፤ ይሁን እንጂ መጠኑ እጅግ የበዛ መሆኑን ሰምቻለሁ፤ እንዲሁም በሐርኪኮ ወደብ በቀረጥ የሚከፈለውን የአቡጀዲድ ጨርቅ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚልኩ መሆናቸውን ሰምቻለሁ።

ምዕራፍ ሃያ አምስት፤ እረኝነት፤ የዱር አራዊት፤ በዚህ አገር ሁለት ክረምት ስለመኖሩና በባርዋ ስለሚገኙ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች።

በባርዋና ባጠገቡም ባሉ ቦታዎች የሚገኙት መኖርያዎች በመንደሮች ተከፋፍለው እያንዳንዱ መንደር ከአስር እስከ አስራ አምስት ቤቶች ያሉበት ሲሆን ዙርያውን በአጥር ተከቦ አንድ በር ብቻ አለው። በአጥሩ ግቢ ውስጥ ወተትና ቅቤ የሚሰጡዋቸውን የቀንድ ከብቶች በጎችንና ፍየሎችን እንዲሁም የጋማ ከብቶችን የሳድራሉ። ጠባቂዎች የአጥሩን በር በደንብ ይዘጉና እሳት እያነደዱ በእርሻውና በየመንደሩ ሲዞሩ የሚያድሩት አውሬዎች ከብቶቻቸውን እንዳይበሉባቸው ሲጠብቁ ያድራሉ፤ ይህን የመሰለው ጥንቃቄ ባይደረግ ኖሮ በእውነተኛው አንድም ከብት አይተርፍም ነበር።

በደብረ ቢዘን ተራሮች ማሽላ የሚዘሩት ሰዎች በዚህ ቦታና በአካባቢው የሚኖሩት ናቸው። ወደዚያ እየሄዱ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው። ቀደም ብዬ እንደ ገለጽሁት በዚህ ቦታ ማናቸውም ዓይነት እህል ይበቅላል። ቦታውም ከባሕር ጠረፍ በመሆኑ ወደ አረብ አገር፤ ሜካ፤ ጅዳ፤ ዘቢድና ቶር [1] ወደ ሌሎችም ቦታዎች ለመላክ ወደ ጠረፉ እየወሰዱ ሰብላቸውን ይሸጣሉ። የዚህ አገር ክረምት ባንድ ወቅት መጥቶ አገሩን በሙሉ የሚያዳርስ ሳይሆን በዓመት ሁለት ጊዜ መጥቶ ባንደኛው ጊዜ ባንድ ቦታ በሁለተኛው ጊዜ በሌላ ቦታ ዝናም ይጥላል። ስለዚህ እህልም የሚዘራው ይህንኑ የክረምት አመጣጥ በመከተል ስለሆነ ለምሳሌ በደብረ ቢዘን የክረምቱ ወራት በየካቲት መጋቢትና ሚያዚያ በመሆኑ እህል የሚዘራው በዚሁ ጊዜ ነው። ከደብረ ቢዘን የስምንት ቀን መንገድ በሚያስሄድ በባሕር ነጋሹ ግዛት ውስጥ በሚገኝ ካማ [2] በተባለ ባንድ ተራራ ላይና ከዚያም አንድ ወር ያህል በሚያስሄድ ዶባ በተባለ ቦታ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ወቅት ዝናም ይጥላል። የማሽላው አዝመራ ዝናም ስለሚወድና የክረምቱም ጊዜ

የሚመጣው ዘግይቶ በመሆኑ ሕዝቡ ዝናም ወደሚጥልበት ቦታ እየተዘዋወረ እህሉን በመዝራት በአንድ ዓመት በሁለት ክረምት ይጠቀማል።

በባርዋ ብዙ ቄሶች የሚገኙባቸው ለሴቶችና ለወንዶች ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች አሉ። የወንዶቹ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሚካኤል የሴቶቹም የሐዋርያት ጴጥሮስ ወጳውሎስ ይባላል። የወንዶቹን ቤተ ክርስቲያን ያሠራው በዘመኑ የኖረ አንድ ባሕር ነጋሽ እንደሆነና ይህም ሰው ከባለቤቱና በቁርባን ጊዜ ከምትከተላት ከደንገጡርዋ በስተቀር ማንም ሴት እንዳትገባ ትዕዛዝ መስጠቱ ይተረካል። የርሱም ሚስት ብትሆን ምዕመናኑ በሚቆሙበት በቅኔ ማህሌቱ ውስጥ ሆና መቁረብ እንጂ ከዚያ አልፋ እንድትገባ አልተፈቀደላትም። ከዚህ ሰው በኋላ የኖሩ ባሕር ነጋሾች ሚስቶች በተሰጣቸው ልዩ መብት መሠረት ደንገጡሮቻቸውን እያስከተሉ በወንዶች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሄዱ በመቁረብ ፈንታ ከሌሎች ምዕመናን ጋር እየተቀላቀሉ በሴቶች ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ ሲቆርቡ አይቻለሁ።

ሁለቱም ቤተ ክርስቲያኖች ባንድ ረዥም አጥር ውስጥ ናቸው፤ የሁለቱም ሥጋ ወደሙ የሚዘጋጀው ባንድነት ባንድ ቤት ውስጥ ነው። ቄሶቹም በሶስት ተከፍለው ሁለቱ ክፍል በወንዶች አንዱ ክፍል በሴቶች ቤተ ክርስቲያን ባንድ ጊዜ ቅዳሴ ይገባሉ። እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች አሥራት አይከፍሉም፤ ነገር ግን ካህናቱ ብዙ ርስት ስላላቸው ይህንኑ መልካም አድርገው በመሥራት በሚያገኙት ገቢ ይተዳደራሉ፤ ለቤተ ክርስቲያኑ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ዕቃዎች ማለት ጌጣጌጦች ሰም፤ ቅቤ፤ እጣንና ሌሎችንም ባሕር ነጋሹ ይሰጣል። በነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ሃያ ቄሶችና ሃያ ሁለት መነኩሴዎች ሁልጊዜ ይገኛሉ። መነኩሴዎች የማይገኙበት ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ቄሶች የማይገኙበት ገዳም ከቶ አላየሁም፤ መነኩሴዎቹ ከብዛታቸው የተነሣ ዓለምን ያለብሳሉ። በየገዳሞቹ፤ በየቤተ ክርስቲያኑ፤ በየመንገዱ፤ በየገበያውና በያለበትም በብዛት ይገኛሉ።

ምዕራፍ ሃያ ስድስት፤ ስለቄሶች ሁኔታ፤ ስለክህነት፤ ቤተ ክርስቲያኖችና ለአጥቢያ ደብሮች ስላላቸው ክብር።

ቄሶች ሚስት ያገቡ ዘንድ የተፈቀደላቸው ስለሆኑ ማናቸውም ቄስ አግብቶ ባንድ ሚስት ረግቶ ይቀመጣል። በዚህ አኳኋን ቄሶች ሥልጣን ከሌላቸው ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የጋብቻን ሕግ ያከብራሉ። ስለዚህ ቄሶች ትዳር ይዘው ልጆች ወልደው ይኖራሉ፤ ይሁን እንጂ ሚስቲቱ ብትሞት ቄሱ ለሁለተኛ ጊዜ ለማግባት አይፈቀድለትም፤ ወይም ቄሱ ቢሞት ሴቲቱ ሌላ ለማግባት አይፈቀድላትም። እርሱዋ ከፈለገች መንኩሳ ትኖራለች፤ ያለዚያ ግን የሙት ሚስት ሆና መቅረት አለባት። አንድ ቄስ ሚስቱ በሕይወትዋ ሳለች አልፎ ሌላ ሴት የደፈረ እንደሆነ ሥልጣኑ ተወስዶበት ለሁለተኛ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን እንዳይገባና በቤተ ክርስቲያኑም ሃብት እንዳይጠቀም ፈጽሞ ይከለከላል። በሚስቱ ላይ ሌላ ሴት ሲደፍር የተገኘ ቄስ ተከሶ በአቡኑ ፊት ቀርቦ ጥፋተኛነቱን ካመነ በኋላ ይህ ሰው ለወደፊቱ በእጁ መስቀል እንዳይዝ፤ በቤተ ክርስቲያንም እንዳይገባ፤ በዚያም የነበረው መብትና ሥልጣን ተወስዶበት ተራ ሰው እንዲሆን አቡኑ ሲፈርዱበት አይቻለሁ። ሚስቱ የሞተችበት ቄስ ለሁለተኛ ጊዜ ያገባ እንደሆነ ሥልጣኑ ይወሰድበታል፤ ለምሳሌ ከዚህ በፊት ስሙን የጠቀስሁት የንጉሠ ነገሥቱን እህት ወይዘሮ ሮማነ ወርቅን ያገባ አቡኬር የተባለ ሰው በፊት ቄስ አጼ የነበረ የተከበረ ካህን ነበር፤ እርስዋን ካገባ በኋላ ግን ሥልጣኑ ተወስዶበት በመቅደስ እንዳይገባ ተከልክሎ እንደተራው ሰው ከሴቶች ጋር እየተቀላቀለ ይቆርብ ነበር። ቄስ የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ የቄስ ልጆች ናቸው፤ ይህም የሚሆንበት ምክንያት በዚያ አገር ትምህርት ቤቶችና መምህራን ባለመኖራቸው ቄሶቹ ያችኑ የሚያውቋትን ለልጆቻቸው ያስተምሩና ተማሪዎቹ አስፈላጊ የሆነ ተጨማሪ ሕግ ሳይቀበሉ በቄስ ልጅነታቸው ብቻ ተክነው ሥልጣን ይቀበላሉ።

በመላ ኢትዮጵያ ክህነት የሚሰጡት አንዱ አቡነ ማርቆስ ብቻ ናቸው፤ ወደፊት እንደምገልጸው ክህነት የሚሰጠው ሁለት ጊዜ ነው፤ ክህነት ሲሰጥ እኔ ራሴ ብዙ ጊዜ በዓይኔ አይቻለሁ።

የሙታኑን አስከሬን አውሬዎች ከመቃብር አውጥተው እንዳይበሉዋቸው በማለት የዚያ አገር ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ ዙርያቸውን በረዥም አጥር ታጥረዋል። ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያን ያለው አክብሮት በጣም ከፍ ያለ ነው፤ ለምሳሌ አንድ መንገደኛ በቅሎ ተቀምጦ በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ሲያልፍ ምንም እንኳ በችኮላ ላይ ቢሆን ከበቅሎው ወርዶ በእግሩ ብዙ ሄዶ ቤተ ክርስቲያኑንና ገረገራውን በደንብ ካለፈ በኋላ ነው እንደገና በበቅሎው የሚቀመጥ።

ምዕራፍ ሃያ ሰባት፤ ከባርዋ ስለመውጣታችንና ባራ እስክንደርስ በመንገድ ስለደረሰብን ችግር።

ለጉዞአችን የሚያስፈልገን እርዳታ እስኪሰጠን በመጠበቅ በመጀመርያ ጊዜ በባርዋ አስራ አንድ ቀን ቆይተን ነበር። ከዚህ ቦታ ለመሄድ ሰኔ 28 ቀን 1520 ዓም በተነሣን ጊዜ ደስ አለን። ዕቃችንን የተሸከሙልን ሰዎች ግማሽ ሌግዋ ያህል ከተጓዙ በኋላ ከአገራችን ድንበር ስለደረስን ከንግዲህ ወዲያ ወደፊት ለመሄድ አንችልም ብለው ባንድ ቦታ ላይ ትተውን ተመለሱ። ይህ የሆነው በሰኔ ወር በክረምቱ መጀመርያ ሲሆን ያረፍነውም ባንድ ትልቅ ሜዳ ላይ ስለነበር ዕቃችንንና እኛንም ትልቅ ዝናም ወረደብን። ዕቃችንን የኤምባሲው የንብረት ሹምና ጸሐፊው ከሌሎቹ ፖርቱጌዞች ጋር ሆነው እንዲጠብቁ ትተናቸው አምባሳደሩና እኔ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር ባሕር ነጋሹ ወደሚገኝበት ወደ ባራ ተመለስን። በባሕር ነጋሹ መኖርያ እንደደረስን ልንነግረው ያሰብነው የርሱ ሰዎች በአጉል ቦታ ላይ ትተውን የሄዱ መሆናቸውን ነበር፤ ነገር ግን በዚያን ዕለት ከርሱ ጋር አልተገናኘንም ነበር። በማግሥቱ በማለዳ

ተነሥተን ባሕር ነጋሹን አግኝተን ጉዳያችንን አቅርበንለት ዕቃችሁ ወደሚገኝበት ቦታ ሰው እልካለሁ ሲል ተስፋ ሰጥቶን ወዲያውኑ ሰዎች ልኮ ዕቃችንን አንድ ሌግዋ ተኩል ማለት ሶስት ድንበሮች አሳልፈው ከሸኙን በኋላ እንደገና ትተውን ስለተመለሱ በዝናምና በነጎድጓድ ውስጥ አራት ቀን ቆየን።

ስለዚህ አንድ ጊዜ ዕቃችን ወደሚገኝበት በሌላ ጊዜ ወደማደርያችን በሌላም ጊዜ ወደ ባሕር ነጋሹ ቤት በመመላለስ ትዕግሥታችንን ስለጨረስን ዝም ማለት አልቻልንም ነበር፤ ወደ ባሕር ነግሹ ዘንድ ሄደን ይህ ዕቃ የፖርቱጋል ንጉሥ ንብረት ሲሆን የተላከው ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በመሆኑ አስፈላጊውን ተሸካሚዎች እንዲያዝልን፤ ያለበለዚያም ፈቃደኛ አለመሆኑን እንዲገልጽልንና ይህን ካወቅን በኋላ ዕቃውን አቃጥለነው ያለችግር ጉዞአችንን አቋርጠን ወደመጣንበት የምንመለስ መሆናችንን ገለጽንለት። የባሕር ነጋሹ ተስፋ ሁልጊዜ አጥጋቢ ነበር፤ ነገር ግን ፍጻሜው ሁል ጊዜ አያምርም። ከአራት ቀን በኋላ ተሸካሚዎች አዘዘልን።

ምዕራፍ ሃያ ስምንት፤ ዕቃችን በባራ ስለመድረሱና ባሕር ነጋሹ ለኛ እርዳታ ስለመንሳቱ።

ጉዞአችንን ለመቀጠል ተሰናድተን ስንጠባበቅ በነበርንበት በባራ ከተማ ዕቃችን ሰኔ 3 ቀን 1520 ዓም እንደደረስን ወደባሕር ነጋሹ ሄደን እንዲያሰናብተን ጠይቀነው ደስ የሚያሰኝ ተስፋ ሰጠን። በማግሥቱ ከንጉሠ ነገሥቱ የተላከ አንድ ትልቅ ሰው ስለመጣ ባሕር ነጋሹ በትልቅ ክብርና ግብዣ ተቀበለው፤ በዚሁ ጊዜ የኛ ጉዳይ ተረሳ። እንግዳው ከመድረሱ በፊት ባሕር ነጋሹ ብዙ ሰው አስከትሎ ከቤቱ እልፍ ብላ ወደምትገኝ ወደአንዲት ኮረብታ ሄዶ ተቀበለው፤ ከወገቡ በላይ ራቁቱን የነበረው እንግዳው እዚያ በተዘጋጀው ልኡላዊ ቦታ ላይ ተቀምጦ ንጉሠ ነገሥቱ ሰላምታቸውን ልከውላችኋል ሲል በተናገረ ጊዜ በአገሩ የአክብሮት ደንብ መሠረት በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ምድሩን በእጃቸው ነኩ። እንግዳው መልእክቱን ለሕዝቡ አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ማለፊያ ልብስ ለብሶ የነበረው ባሕር ነጋሹ ወደ ቤቱ ወሰደው። በአገሩ ወግ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ የሚልከውን መልእክት ከቤት ውጭ ሆኖ መስማት ደንብ ነው። ሰሚው መልእክቱ እስኪሰጥ ድረስ ከወገቡ በላይ ራቂቱን መሆን አለበት፤ መልእክቱ የንጉሠ ነገሥቱን ደስታ የሚገልጽ ከሆነ ተሰጥቶ እንዳለቀ ይለብሳል፤ ነገር ግን እንዲህ መሆኑ ቀርቶ የንጉሠ ነገሥቱን ቅሬታ ወይም አለመደሰት የሚገልጽ ከሆነ ሲሰማ በነበረበት ሁኔታ ራቂቱን ይቆያል።

ባሕር ነጋሹ የንጉሠ ነገሥቱ እናት ወንድም ነው። አምባሳደሩም እኛም ሆነን ጉዳያችንን ለማቅረብ እንደገና ወደ ባሕር ነጋሹ ብንሄድ እባካችሁ ስለ እግዚአብሔር ዝም በሉኝ፤ አሞኛልና አታስቸግሩኝ፤ ሲል አሰናበተን። እኛም ተስፋ ባለመቁረጥ ጉዳያችንን ለማቅረብ ቆይተን ተመልሰን ብንሄድ ተኝቷዋልና ለመግባት አይቻልም ሲሉ መለሱን። ከብዙ ጊዜ በኋላ አንድ ቀን አምባሳደሩ ወደ ባሕር ነጋሹ ሄዶ ለራሱና (ማለት ለአምባሳደሩ) ለጭፍሮቹ ለጉዞአቸው አስፈላጊውን እርዳታ እሰጣለሁ ሲል ለፖርቱጋል ንጉሥ የባሕር ኃይል አዛዥ በመሃላ በማጽናት የሰጠውን ተስፋ ያልፈጸመ መሆኑንና የፖርቱጋልን ንጉሥ ንብረት ወይም ዜጎች ባለመከባከቡ ሁለቱ ክፍሎች የተማማሉበትን ወዳጅነት ያላከበረ መሆኑን አሳሰበው። ምንም እንኳ ይህን ማሳሰቢያ ብንሰጠውም በእንግዳው መምጣትና በርሱም ሕመም በማመካኘት ምንም አልረዳንም።

ለንጉሠ ነገሥቱና ለባሕር ነጋሹ ግብር ለመክፈል ሰባት ወይም ስምንት በማለፊያ ዕቃ ያጌጡ ፈረሶች የተቀመጡ ከሌላ አውራጃ ታላላቅ እስላሞች ሰኔ 6 ቀን በመጡ ጊዜ የነዚህ ሰዎች መምጣት ለርሱ ሁል ጊዜ ሃብት የሚያስከትልለት ስለነበር ለራሱም ሕመም ወይም ለእንግዳው ሳያስብ እነዚህን ሰዎች ፈጥኖ ተቀበላቸው።

ባሕር ነጋሹ ለነዚህ እስላሞች ያደረገው ከፍ ያለ አቀባበልና ያሳያቸውም ክብር ለኛ ትልቅ ችግር አስከተለብን፤ አስራ ሁለት በቅሎዎች ስለሚያስፈልጉን እነዚሁ በውሰት እንዲሰጡን አምባ ሳደሩ ቢጠይቅ ከፈለጋቻሁ መግዛት አለባችሁ እንጂ በውሰት ለመስጠት አይቻልም ሲል ባሕር ነጋሹ እምቢ ስላለ የተባሉትን በቅሎዎች ልንገዛ ስንዘጋጅ ሳለን አሽከሮቹ ወደ ሻጮቹ መጥተው ለኛ እንዳይሸጡልን፤ የሸጡም እንደሆነ መቀጫ በወርቅ የሚከፍሉ መሆናቸውን በመግለጽ አስፈራሩዋቸው፤ (መቀጫ በወርቅ እንዲከፍሉ የሚደረገው በአገሩ የመገበያያ ገንዘብ ባለመኖሩ ነው።) ወሬው በግዛቱ በሙሉ ከመነዛቱ የተነሣ የሚያገኙን ሁሉ ሻጮቹስ ባሕር ነጋሹን ባይፈሩ ኖሮ በቅሎቹን ሊሸጡላችሁ ይፈቅዱ ነበር፤ ነገር ግን ባሕር ነጋሹ የራሱን በቅሎዎች ሊሸጥ ስለሚፈልግ የሌሎች ሰዎች እንዳይሸጡ መከልከሉ በዚህ ምክንያት ነው፤ እያሉ ይነግሩን ነበር።

በመላ ኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ ስለሌለ በገንዘብ ፈንታ የሚሠራበት ወርቅ ነው፤ ወርቅ የሚለካው በወቄት ነው። ባሕር ነጋሹ በግዛቱ ውስጥ በርሱ መመዘኛ እንጂ በሌላ እንዳይሠራ ከመ ከልከሉም በላይ ወርቅ በተሸጠ ወይም በተነዛ ጊዜ መመዘኛውን ከርሱ ወይም ከወኪሎቹ መጠየቅ አስፈላጊ ነበር፤ ስለዚህ ውስጥ አዋቂ የሆኑ ሰዎች በሚያወሩት መሠረት በዚህ ዓይነት አጠባበቅ በአገሩ ውስጥ ያለውን የወርቅ ልክ ባሕር ነጋሹ ስለሚያውቀው ባስፈለገው ጊዜ ሊወስደው ይችላል ይባላል።

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ፤ ስለባራ ቤተ ክርስቲያንና ስለጌጡ፤ በዚሁ ከተማ ስለሚውለው ገበያና ሸቀጥ፤ ስለመነኩሴዎች መነኩሲቶችና ቄሶች አለባበስ።

በባራ ከተማ ማለፊያ ሆኖ የተሠራ ውስጡም በወርቀዘቦና በከፈይ፤ መልኩ ብጫ በሆነ በግመል ሱፍ ጨርቅ ያጌጠ አንድ የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን አለ። በቤተ ክርስቲያኑ የሚከናወነው

የቅዳሴ ስነሥርዐት ልክ እንደባርዋ ቤተ ክርስቲያን ነው። ይሁን እንጂ ባሕር ነጋሹ የሚኖረው በዚህ ቦታ በመሆኑና ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ካህናትና መነኩሴዎች ስለሚገኙ በባራ ቤተ ክርስቲያን የቅዳሴው ጊዜ የበዛ ነው።

ቤተ ክርስቲያኑ የሚመራው በቄሶቹ ነው። ባንድ የንግሥ ቀን ቄሶችና መነኩሴዎች፤ ወንዶችና ሴቶችም ከገረገራው ግቢ በብዛት ተሰብስበው የንግሡን ስነሥርዐት ሲያስፈጽሙ አይቻለሁ። በዚሁ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለመቁረብ ይችላሉ። ከፍ ብዬ የጠቀስኳቸውን ጌጣጌጦች በጉዞው ላይ ይዘው አይቻለሁ። በስነሥርዐቱ ላይ ቄሶቹ በእመቤታችን ስዕል ፊትና በእሁድ ቀን ከበሮ እየመቱ ሥርዐቱን እንደሚፈጽሙት ሁሉ አጊጠ በመልበስ ቅዳሴ ማርያምን እያዜሙ ከበሮና ነጋሪት እየመቱ በቤተ ክርስቲያኑም ሰላሳ ጊዜ ዞሩ፤ በበዓል ቀን ቁርባን ሲሰጡም ይህንኑ የመሰለ ስነሥርዓት ይፈጽማሉ። ይህ ጉዞ የተደረገበት ምክንያት እግዚአብሔር በሰብሉ ላይ ዝናም እንዲያወርድ ለመለመን ነበር። የዚህም ቤተ ክርስቲያን ደወል እንሌሎቹ ከድንጋይ የተሠራ ነው፤ ምርዋውም መናኛ ዓይነት ነው።

በባርዋና በሌሎችም አውራጃዎች ከተማዎች እንዳለው ሁሉ በባራም በየሳምንቱ የሚውል ገበያ አለ፤ በገበያው በመሸጥና በመ ግዛት ፋንታ ዕቃ በዕቃ ይለዋወጣሉ፤ ማለት አህያን በላም ይለ ውጡና ግምቱ አነስ ያለውን ከብት የሰጠው ክፍል በተጨማሪ ሁለት ወይም ሶስት እንጀራ ይከፍልና በእንጀራው ጨርቅ፤ በጨርቁ በቅሎና ላም ወይም ሌላ አስፈላጊ ነገር፤ ደግሞም በጨው፤ በእጣን፤ በከርቤ፤ በድኝ በሌሎችም ልዩ ልዩ ሸቀጦች ይለዋወጣሉ። ዶሮችና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በዚሁ ዓይነት ግብይት ውገበያበ ይገ ኛሉ። በዚህ ገበያ ማናቸውም ነገር የሚገዛና የሚሸጠው በለውጥ በመሆኑ ገንዘብ በፍጹም የለም። በገበያው የሚታዩት ዋናዋናቹ ነጋዴዎች መነኩሴዎችና መነኩሲቶች ናቸው። መነኩሴዎቹ መሬት እየጠረገ የሚሄድ ወይባ የተነከረ ረዥምና ወፍራም የጥጥ ጨርቅ ልብስ ይለብሳሉ። አንዳንዶቹም ስፌ ሱሪ የመሰለ ብጫ የተነከረ የለፋ የፍየል ቆዳ ይታጠቃሉ። መነኩሲቶቹም ብጫ ልብስ ለብሰው

ይታያሉ፤ ወንዶቹም የቅዱስ ዶሚኒክ ማህበርን ከቶሊካውያን ቄሶችን ይመስል ብጫ ንክር ቆብ ይደፋሉ። መነኩሲቶቹ ግን ቆብ ሳይደፉ ራሳቸውን ተላጭተው በራሳቸው ዙርያ ቀጭን ጠፍር ሸብ ያደርጋሉ። መነኩሴዎቹ በዕድሜ ሲገፉ የተላጨውን ራሳቸውን ከብርድ ለመከልከል ሲሉ ቆብ ይደፋሉ። መነኩሲቶቹ በየመንደርና በየገዳም እየተዘዋወሩ ይኖራሉ እንጂ ባንድ ገዳም ውስጥ ተዘግተው አይቀመጡም።

መነኩሴዎችና መነኩሲቶች ሁሉ ያንድ ማህበር አባሎች ሲሆኑ የሚያዛቸው ልብስ የሚሰጣቸው ገዳሙ ነው። መነኩሲቶቹ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ከሌሎች ሴቶች ጋር ተቀላቅለው በሴት በር መግባት አለባቸው። የመነኩሲቶች ቁጥር እንደመነኩሴዎቹ የበዛ ነው። ከነዚሁ ውስጥ አንዳንድ ብፅዕታት ይገኙባቸዋል ይባላል። ቄሶች የሚለብሱት እንደተራው ሕዝብ ንጹህ የሆነ አንድ ዓይነት ጨርቅ ሲሆን ባለባበሳቸው ያለው ልዩነት ጥቂት ነው። ይሁን እንጂ ቄሶቹ ራሳቸውን ተላጭተው በእጃቸውም መስቀል መያዛቸው ተራው ሕዝብ ግን ጠጉሩን አጎፍሮ መሄዱ መለያ ሊሆን ይችላል። በቄሶችና በተራው ሕዝብ መካከል ያለው ሌላው መለያ ቄሶቹ ጢማቸውን እንዳለ ሲትውት ተራው ሕዝብ ግን ሲለሚላጨው ነው። በመንበረ ጸባዓቶች ውስጥ የሚያገለግሉ ደብተራዎች ግን ሁል ጊዜ በደንብ የሚለብኑ ሲሆኑ በየገበያው አይሄዱም።

ምዕራፍ ሰላሳ፤ የባሕር ነጋሹ ሁኔታና የቤቱ ስነሥርዐት፤ በኑብያ ላይ ለመዝመት ስለማሳወጁና ስለፍርድ ሁኔታ።

ምንም እንኳ የባሕር ነጋሹ ማዕርግ ከፍ ያለ ቢሆንና ንጉሥ የሚያሰኝ ማዕርግ ቢኖረውም በኑዋኑዋሩ በጣም የደኸየ ነው፤ ጉዳያችንን ለማስፈጸም ወደ ቤቱ በሄድን ቁጥር የምናገኘው ብዝት ደርቦ ጨርቅ በተሸፈነች ባንዲት ድንክ አልጋ ላይ ተቀምጦ ነው፤

የአገሬው ሕዝብ ብዝት የሚለው ይህ የጥጥ ልብስለአገሩ አየር ተስማሚና ማለፊያ ነገር ነው፤ ማለፊያውን ዓይነት ይህን ጨርቅ ለመግዛት ብዙ ዋጋ ይጠይቃል። ከአልጋው በስተኋላ ባለው ግድግዳ ላይ አራት ሰይፎችና በማህደር ውስጥ የነበሩ መጽሐፎች በችካል ላይ ተንጠልጥለው ነበር። እንግዶች ሲመጡ የሚቀመጡበት ከአልጋው ፊት ስሌን ተነጥፎአል፤ ቤቱ የሚጠረገው አንዳንድ ጊዜ ነው፤ ባለቤቲቱ በራስጌ በኩል ባንድ ሰሌን ላይ ሁልጊዜ ትቀመጣለች። ከባሕር ነጋሹ ፊት ሁልጊዜ ብዙ ሰው አይጠፋም፤ ታላላቆቹ በሰሌኑ ላይ በምድር ይቀመጣሉ። ከአልጋው አጠገብ ሆነው የሚታዩ አራት ፈረሶች በደጅ ይቆማሉ፤ ከነዚህ ፈረሶች አንደኛው ተጭኖ ሁልጊዜ ዝግጁ ሆኖ የሚገኝ ሲሆን ሌሎቹ ሶስቱ ግን ሌጣቸውን ናቸው። የባሕር ነጋሹ ቤት በሁለት አጥር የተከበበ ሲሆን በያንዳንዱ አጥር በር ላይ ከውስጥና ከግቢ ቆመው የሚገኙ አለንጋ የያዙ አጋፋሪዎች አሉ፤ በውስጠኛው አጥር በር ላይ የሚቆሙት አጋፋሪዎች በአለባበሳቸውና በሁኔታቸው ሻል ያሉ ናቸው፤ ማዕርጉ ከነዚህ አጋፋሪዎች ከፍ ያለ አቤቱታ እየሰማ አስፈላጊውን ፍርድ የሚሰጥ አሊቃሺ [1] የተባለ ማዕርግ ያለው ባለሥልጣን አለ፤ ይህ ሰው ከርሱ ሥልጣን በላይ የሆነ ጉዳይ ያጋጠመው እንደሆነ በበኩሉ ጉዳዮን አጥንቶ ከራሱ አስተያየት ጋር ለባሕር ነጋሹ አቅርቦ ፍርድን ባሕር ነጋሹ ይሰጣል። ነገር ግን ጉዳዩ አነስተኛ ከሆነና ባለጉዳዮቹም ከተስማሙ ፍርድን የሚሰጠው አሊቃሺው ነው። ይሁን እንጂ አሊቃሺውም ሆነ ባሕር ነጋሹ ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ የሆነ በታዛቢነት በዚያ የሚቀመጥ መልከኛ የተባለ ባለሥልጣን መገኘት አለበት፤ ፍርድ ጎደ ሎበት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ችሎት ይግባኝ የሚል ሰው ሁሉ አስ ቀድሞ የዚያን ባለሥልጣን ምስክርነት ማግኘት አለበት። በየአ ውራጃው በቀጥታ በንጉሠ ነገሥቱ የተሾሙ አንዳንድ አሊቃሽና መልከኛ ይገኛሉ፤ እንዲሁም ከባሕር ነጋሹና ከሌሎችም ታላላቅ ገዥዎች ሥር በሚገኙት ግዛቶች ሁሉ እነዚሁ ሁለት ባለሥልጣኖች ይገኛሉ።

እጅ ለመንሳት ወይም ለሌላ ጉዳይ ወደ ባሕር ነጋሹ ቤት የሚመጡ መኳንንት ሁሉ ቀጥሎ በተመለከተው ስነ ሥርዓት ነው፤

አንድ መኮንን በበቅሎ ተቀምጦ ሰባት ስምንት ወይም አስር ሰዎች ያስከትልና ከበሕር ነጋሹ አጥር በር ሲደርስ ከበቅሎው ይወርዳል፤ መኮንኑ ሃብታም ከሆነ ሰባት ስምንት አስር፤ ድሃ ከሆነ ግን ከዚህ ያነሱ በቅሎዎች ይከተሉታል። መኳንንት በዚህ ዓይነት መጥተው በመጀመርያው በር ላይ ሲደርሱ ከበቅሎዎቻቸው ወርደው ከዚያ በኋላ በእግራቸው እስከ ሁለተኛው በር ድረስ ሄደው ወዲያውኑ እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው ይገባሉ፤ ካልተፈቀደላቸው ግን ለጊዜ ማሳለፊያ እንኳ ምንም ሳያደርጉ ባንድነት ተሰብስበው በጸሐይ ላይ በመንቃቃት ደጅ ይጠናሉ።

ወደ ባሕር ነጋሹ ቤት የሚመጡ መኳንንት ሁሉ እያንዳንዳቸው በትከሻቸው ላይ የበግ ለምድ ይደርባሉ፤ ከነርሱም ውስጥ እጅግ የተከበሩት የአንበሳ፤ የነብር፤ ወይም የግስላ ለምድ ይደርባሉ፤ እኛ በባለሥልጣን ፊት ስንደርስ ባርኔጣችንን እንደምናወልቀው ሁሉ እነዚያም መኳንንት በባሕር ነጋሹ ፊት ሲቀርቡ ለምዳቸው ያወልቃሉ።

አንድ ቀን በባራ ገበያ ላይ ሳለን አርማና ጦር የያዙ ሰዎች ባሕር ነጋሹ በኑብያ ላይ ሊዘምት ነው እያሉ የክተት አዋጅ እየለፈፉ ሲሄዱ አየን። ኑብያ ከዚህ በፊት ከጠቀስናቸው ዳፍላና ከንፊላ ከተባሉ የድንበር ግዛቶች የስድ ስት ቀን መንገድ ርቆ የሚገኝ በግብጽ አጠገብ ያለ አገር ነው። ኑበያውያን አስቀድሞ ክርስቲያን ነበሩ የሚባሉ አሁን ግን እስላሞች አይሁዶች ወይም ክርስቲያኖች ያልሆኑ አሕዛብ ናቸው፤ አገራቸውም ጥሩ ዓይነት ወርቅ የሚገኝበት ነው ይባላል። ባሕር ነጋሹ በኑብያውያን ላይ ሊዘምት የተነሣበት ምክንያት ከዚያ ጊዜ በፊት ልጁን ስለገደሉበት ይህንኑ ለመበቀል ነበር ይባላል። ኑብያውያን ኃይለኛ ጦረኞችና በአገራቸውም ላይ የናይል ወንዝ ስለሚያልፍ ምድሩ ለምለም ከመሆኑ የተነሣ በምግብ በኩል ምንም ችግር የሌለባቸው ከመሆናቸው በላይ በአገራቸው ወሰን ላይ አራት ወይም አምስት መቶ የሚሆኑ ፈረሰኞች አሰልፈው የሚመጣባቸውን ለመመከት ተዘጋጅተው ነበር እየተባለ ሲወራ ሰምቻለሁ። የባሕር ነጋሹ ሠራዊት ከአምስት ቀን በኋላ የሚሄድ

መሆኑን አዋጅ ነጋሪው አስታወቀ፤ ነገር ግን ሌላ ምንም ዓይነት ንቅናቄ ወይም ክተት አልተደረገም ነበር። ይህ የሆነበት ብዙ የጦር መሣርያ ባለመኖሩ ሳይሆን አይቀርም፤ ጋሻና ጦር ቀስትም ካላቸው ከጨዋዎች በስተቀር በአገሩ ውስጥ የጦር መሣርያ ያላቸው ብዙ ሰዎች የሉም። ከነዚህ ጨዋዎች አንዳንዶቹ ሰይፍና የጦር መከላከያ ልብስ ያላቸው አሉ።

ይህችን ትንሽ አመጽ ለመደምሰስ በተነሣ ጊዜ ባሕር ነጋሹ አምባሰደሩን ጉራዴዎች ለመነው። አምባሳደሩ ይዞት ከመጣው ጉራዴዎች ውስጥ አንዱን አንስቶ ቢሰጥም ባሕር ነጋሹ የግል ጉራዴውን እንዲሰጠው በጥብቅ ለምኖ ነበር። ነገር ግን የተጠየቀውን ለመፈጸም ፈቃደኛ ስላልነበር አምባሳደሩ ባለወርቅ ጫማ የከፈይ አፎት የነበረው ሌላ ጉራዴ ከጓደኞቹ ገዝቶ አበረከተ። ዕቃችንን ካኖርንባትና የኛም ሰዎች ተኝተውባት ከነበረች በር የሌለባት ቤት ውስጥ ሁለት ጉራዴና አንድ የብረት ባርኔጣ ተሠረቀብን። ይህ ስርቆት ሊደርስ የቻለው በጦርነቱ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

ምዕራፍ ሰላሳ አንድ፤ ከባራ ወደ ቴሜይ ስላደራግነው ጉዞና ስለከተማውም ሁኔታ።

በገዛናቸው በቅሎዎችና በሕር ነጋሹም በሰጠን ሶስት ግመሎች ዕቃችንን ጭነን ከዚህ ቦታ ባቃራቢ ግምት ከሰኔ አስራ አምስት እስከ መስከረም አስራ አምስት ድረስ በሚቆየው ዝናምና ነጎድጓድ በሚጥልበት የክረምት ጊዜ ውስጥ ጉዞአችንን ጀመርን። ክረምቱ ባንድ ወር ሲበረታ በሌላው ወር ይቀላል። የአገሩ ሕዝብ እንኳ ወዲያ ወዲህ በማይንቀሳቀስበት በዚህ የክረምት ወራት ውስጥ የገሩን ባሕል ሳናውቅ ወይም ሊደርስብን የሚችለውን አደጋ ሳንገምት መንገዳችንን አፋጠንን። ግማሽ ዕቃችንን ጭነን ግማሹንም

በተባለው ከተማ ለንብረት ሹማችን አደራ ትተን ጉዞአችንን ጀመርን። ከተነሣንበት ከባራ ከተማ አራት ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ በማይ ጸዐዳ ቀበሌ ቴሜይ በተባለ ከተማ ሠፈርን። የያዝነው ዕቃ እስኪበላሽ ድረስ በጣለው ዝናም ምክንያት ያ ቅርብ መንገድ ሶስት ቀን ፈጀብን።

በዚያ ከተማ የሚኖር የማይ ጸዐዳ ወረዳ ገዥ የነበረ የንጉሠ ነገሥቱ እናት ወንድም የሆነ እጅግ የተከበረ ሹም አገኘን። ይህ ሰው እኛን በሚገባ አኳኋን ተቀብሎ አከበረን። እርሱ የሚያስተዳድራት ይህች ቀበሌ ከባሕር ነጋሹ ግዛት ወረዳዎች ሁሉ እጅግ ያነሰች በመሆንዋ በውስጥዋ የሚተዳደሩት ከተማዎች ሃያ ብቻ ናቸው።

ዙርያውን ለርሻ በሚያመች ምድርና በሸለቆዎች በተሰመሩ መስኮች ባጌጠ ተራራ ላይ በተቆረቆረው ቴምያ በተባለው ከተማ ላይ ሆኖ አስራ አራትና አስራ አምስት ሌግዋ ድረስ ያለው ምድር በሶስት በኩል ያለ አንዳች ችግር ይታያል። በአራተኛው ጎን ግን አንድ ሌግዋ ያህል እልፍ ሲሉ ወደ አንድ ወንዝ የሚወርድ አንድ ትልቅ ገደል ይጀምራል፤ በወንዙ አጠገብ ከመቶ በላይ የሚገመቱ ታላላቅ መንደሮች ይገኛሉ፤ በሰው መተፋፈግ፤ በእህል፤ በከብት፤ በወፎችና በአራዊት ብዛት ይህን ቦታ የሚተካከል ሌላ ቦታ ከቶ በዓለም ላይ የሚገኝ አይመስለኝም። ከነብርና ከተሁላ ከቀበሮና ከጅብ በስተቀር ሌላ አይታይም። ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት የአገሩ ሕዝብ ቆቅን ብቻ በወስፈንጥር ሲያድን የሌሎች የዱር አራዊት ሥጋን ግን ስለማይበላ ወይም የአደን ዘዴና መሣርያም ባለመኖሩ ስለማይታደኑ አራዊት እየበረከቱ መሄዳቸው በዚህ ምክንያት በመሆኑ ሕዝብ በበዛበት ሜዳ ቦታ እንዴት አድርገው አራዊት ሊበዙ ቻሉ ሲል አንባቢ ሊገረም አይገባውም። ስለዚህ አራዊት ስለማይታደኑ ለማዳ ሆነው በብዛት ይገኛሉ፤ ለምሳሌ አንድ ቀን በውሻ እንኳ ሳንረዳ ባንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሃያ ጥንቸሎች ገደልን። እንዲሁም በዚሁ ቁጥር የሚገመቱ ቆቆች በወጥመድ ያዝን። በዚያ ቦታ ማደን ፍየሎችን ወደ ጉሮኖ ወይም ዶሮችን ወደ ቆጥ የመንዳት ያህል ቀላል ነው።

ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት፤ የአንበጣ ብዛትን በሰብልም ላይ የሚጥለው ጉዳት።

በዚህ ቦታና በሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶች በሰብል ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚጥል አንበጣ በብዛት ይገኛል። ምድሩን የሚሸፍነውን በአየም ሲበር የጸሐዩን ብርሃን የሚጋርደውን የአንበጣ መንጋ ከብዛቱ የተነሣ ለኛ ላየነው ሰዎች እንኳ ለማመን አስቸጋሪ ሲሆንብን ያላየ ሰውማ እንዴት ሊያምን ይችላል? እርግጥ ነው፤ አንበጣ በየጊዜው እየመጣ በአገሩ መሙሉ አደጋ አይጥልም፤ እንዲህ ቢሆንማ ኖሮ አግሩ ባድማ ይሆን ነበር፤ ነገር ግን በየዓመቱ ከአውራጃ ወደ አውራጃ አደጋውን ይጥላል። የአንበጣውን ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር አብራርቶ ለማስረዳት የስፓኝንና የፖርቱጋልን ጠቅላይ ግዛቶች ምሳሌ በማድረግ እንቀጥላለን።

አንድ ዓመት በጋሊዛ፤ በሚቀጥለው ዓመት በዶሮና በሚኙ በትራዙሽ ሞንትሽ፤ በሚቀጥለው ዓመት በቤይራ፤ በሚቀጥለው በኤስትራማዱራ፤ በሚቀጥለው በአንዳሉዚያ፤ በሚቀጥለው በካስቴላ አቬልያ፤ በሚቀጥለው በአራጎን አንዳንድ ጊዜም ባንድ አውራጃ ውስጥ የሚገኙትን ሁለት ወይም ሶስት ቦታዎች ባንድ ጊዜ በመውራር ጥፋቱን ያስከትላል ማለት ነው።

አንበጣው ያረፈበት ምድር በእሳት የተጋየ ይመስላል። አንበጣ ትልቅ ፌንጣ የሚመስል ብጫ ክንፍ ያለው ነገር ሲሆን፤ ከመታየቱ በፊት ያንድ ቀን መንገድ ሲቀረው ሕዝቡ መምጣቱን ያውቀዋል። መምጣቱን በቅድሚያ ሊናገሩ መቻላቸው አይተውት ሳይሆን የጸሐዩ ብርሃን በምድሩ ላይ ብጫ ሆኖ ስለሚታይ ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሕዝቡ በፍጹም ተስፋ በመቁረጥ «ወይኛ፤ አንበጣ መጣብን እንግዲህ ምን ይበጀን ይሆን» ይላሉ። የአንበጣን ወረራ ያየሁት ሶስት ጊዜ ሲሆን የመጀመርያው በባርዋ ነበር። እዚህ አገር ከመጣን ሶስት ዓመት ሲሆነን አንበጣ በዚህ ቦታ አደጋ ጣለ፤ በዚያ ቦታ ከፍ ያለ ጉዳት አስከተለ ሲባል ደጋግመን እንሰማ

ነበር። አንድ ቀን ጸሐዩና ጥላውም አቡዋራ ሲመስል ሕዝቡ የአንበጣ ምልክት አድርጎ የሚቀበለው ነው እንዳልነው ሁሉ ይህ ምልክት ከታየበት ማግሥት፤ በኋላ እንተረዳነው፤ ስምንት ሌግዋ ያህል ያለውን ምድር አልብሶት አየን። የአንበጣው ወረራ እንደተቃረበ የከተማው ቄሶች ወደኔ መጥተው መድኃኒት እንድሰጣቸው ቢጠይቁኝ እግዚአብሔር አንበጣውን ከአገር እንዲያስወጣው ባንድነት ሆኖ መጸለይ ነው እንጂ ሌላ የሚያዋጣ መድኃኒት አላውቅም ስል መለስሁላቸው። ይህንኑ ጉዳይ ለአምባሳደሩ በማቅረብ እኛም ከሕዝቡ ጋር ሆነን የጉዞ ጸሎት ብናደርግ እግዚአብሔር ይሰማናል ስል አማከሬው በሃሳቡ ተስማማበት፤ በማግሥቱ እኛም መሠውያችንንና መስቀላችንን ይዘን የከተማውም ሕዝብ መስቀልና ታቦት የያዙትን ቄሶች ተከትሎ ጉዞ ተጀመረ። በጉዞው ላይ ዝም ብሎ መሄድ አይገባም እንደኛው እየጸለያችሁ መሄድ አለባችሁ ስል ሃሳብ ሰጥቻቸው «እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ» የሚለው ጸሎት ተጀመረ። በዚህ አኳኋን የጸሎቱ ስነሥርዓት እየተፈጸወ ጥቂት ከተጓዝን በኋላ ባንድ የስንዴ እርሻ ውስጥ ሲሶ ሌግዋ ያህል ሄደን በዚያ በምትገኝ ባንዲት ጉብታ ላይ ወጥተን እኔ ባለፈው ማታ በጽሑፍ ያዘጋጀሁትን የመወገዣ ቃል ሰማን፤ አንበጣው በሶስት ሰዓት ውስጥ ከዚያ ቦታ ተነሥቶ ለክርስቲያኖች ሊጠቅም ወደማይችል ወደ እስላሞች አገር ወይም ወደ ባሕሩና ወደተራሮቹ እንዲሄድ በማዘዝ፤ ያልሄደም እንደሆነ የሰማይ አእዋ ፋትና የምድር አራዊት እንዲበሉት በረዶና ወጨፎም ተነሥቶ እንዲያጠፋው ተገዘተ። ቃሉ ከመነበቡ በፊት ጥቂት አንበጣዎች እንዲያዙ አዝዤ እነሱ ባሉበት የመወገዣው ቃል ተሰጠ። ስነሥርዐቱ ከተፈጸመ በኋላ የተያዙት አንበጦች እንዲለቀቁ አዘዝሁ።

እግዚአብሔር አምላክ የኛን የኀጢአተኞችን ጸሎት ሰማን። አንበጣው ወደመጣበት ወደ ባሕር በኩል ሲያመራ በላያችን እየበረረ ኩሱን እየጣለብን ሲሄድ ከብዛቱ የተነሣ ጎድናችንን ለማድቀቅ ወይም ራሳችንን ለመፈንከት የድንጋይ እሩምታ የወረደብን ይመስል ነበር። በሠፈራችን ስንደርስ በአንበጣው መሄድ ምክንያት በየቤቱ ጣርያ ላይ ሠፍረው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ የነበሩት ወንዶችና

ሴቶች ሕፃናትም ባንድነት ተሰብስበው አገኘናቸው፤ ከኋላችን ብዙ ሰዎች ተከትለውን ነበር። ወዲያውኑ ከባሕሩ የሚነፍስ ኃይለኛ ዝናምና በረዶ ተነሥቶ ሶስት ሰዓት ያህል ጥሎ ወንዞቹ ሁሉ በጎርፍ ተመሉ። ዝናሙ ካበቃ በኋላ እልቆ መሳፍርት የሌለውን የአንበጣ ሬሣ ማየት በእውነት የሚያስደንቅ ነገር ነበር። በየወንዙና በየጎርፍ ማለፊያው ላይ ተረፍርፎ የሚገኘው ቁልል በግምት ሁለት ክንድ ጥልቀት ነበረው።

በማግሥቱ ጥዋት በመላው አገር ውስጥ አንድ ተባራሪ አንበጣ እንኳ ከቶ አይታይም ነበር። የአንበጣው ወረራ ባጠቃው ቦታ የሚገኙ ሰዎች የተፈጸመውን ተአምር ለማየት መጠተው አንዳንዶቹ እነዚህ ፖርቱጊዞች ቅዱሳን ናቸው እግዚአብሔርን በመለመን አንበጣውን ከዚህ አስወገዱልን አሉ፤ አንዳንዶቹም (የሌላ ቦታ መነኩሴዎችና ቄሶች) እነዚህ ሰዎች አስማተኞች ናቸው፤ አንበጣ ውን ሊያስወግዱ መቻላቸው በዚሁ ሞያ ነው፤ በአስማተኛነታቸው ምክንያት አንበሶችንና ሌሎችንም የዱር አራዊትን አይፈራም አሉን።

ይህ ከሆነ ከአስራ ስድስት ቀን በኋላ ኮርባርያ የተባለ ቦታ ሹም የነበረ አንድ ሰው ከአሽከሮቹ ከመነኩሴዎችና ከቄሶች ጋር ሆኖ እኛ ወደነበርንበት ቦታ መጥቶ እባካችሁ ስለእግዚአብሔር ስትሉ መጥታችሁ ከኛ ዘንድ አንበጣውን አባሩልን ሲል ለመነን። የመጡበት ቦታ ከባሕር ዳር ያለ ከባርዋም ርቀቱ ከስምንት ሌግዋ በላይ ስለነበር ሲጓዙ ውለው ከኛ ዘንድ የደረሱት ከመሸ በኋላ ነው። የዚያኑ ዕለት ማታ አምስት ፖርቱጊዞች ሆነን ወደተባለው ቦታ ስንጓዝ አድረን ጸሐይ ከወጣ ከአንድ በዓት በኋላ ደረስን። በዚያ እንደደረስን የአንበጣው ወረራ የደረሰባቸው የከተማው ነዋሪዎች ባንድ ቦታ ተሰብስበው አገኘናቸው። አንበጣው ከወረራቸው ከሌሎች ቦታዎች የመጡ በዚያ የነበሩ ሰዎች ደግሞ ስለእግዚአብሔር ስትሉ እባካችሁ ወደኛ ዘንድ እንድትመጡልን ሲሉ ለመኑን።

ይህ ከተማ ባንድ ኮረብታ ላይ ስለነበር የተቆረቆረው በዚያ ሆኖ የሚታየው አንበጣው የሠፈረበት ቦታና የከተማው ክፍል

አቡዋራ የተነፋበት ይመስል ነበር። ከዚያ በፊት እንደምናደርገው ሁሉ በከተማው ጥግ በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ጸልየን በዚያ አጠገብ የሚገኙትን አራት ቦታዎች ጎብኝተን አንበጣዎቹን ይዘን ወገዝናቸው። ከውግዘቱ በኋላ ለቀናቸው ስነሥርዓቱን ስናበቃ ምሳችንን ለመብላት ሄድን። ከምሳ በኋላ ወደውጭ ብቅ ብለን ስንመለከት ለምልክት ያህል እንኳ በዚያ አንድም አንበጣ አይታይም ነበር፤ ያገሩ ሕዝብ ይህንን በመመልከት ልዩ ልዩ ቦታዎችን እየዞርን እንድንጎበኝለት በመጠየቅ ከዚያ እንዳንሄድበት ለምኖን በሚገባ የሚከባከበን መሆኑን ገለጸልን። አንበጣው ጨርሶ ስለጠፋ ወደየቦታው መሄድ አስፈላጊ ስላልነበር ሕዝቡን በረከት ስጥተነው እንዲሄድ አሰናበትነው፤ እኛም በማግሥቱ ተነሥተን ወደሠፈራችን ሄድን። በዚያ የነበሩ ሰዎች ለእግዚአብሔር መገዛትና ለርሱም መጸለይ አንበጣውን የሚያባርረው መሆኑን አመኑ።

ምዕራፍ ሰላሳ ሶስት፤ አንበጣው በሌሎች ሁለት ቦታዎች የጣለውን አደጋ አየን።

በአንጎት ግዛት ውስጥ በሚገኝ ንጉሠ ነገሥቱ ስንቅ እንዲሰጠን ባዘዘልን ቡግና በተባለ ወረዳ ውስጥ በሌላ ጊዜ የአንበጣ ወረራ አይተናል። ይህ ቦታ ከዚህ በፊት ከነበርንበት ከባርዋ ከተማ የሰላሳ ቀን መንገድ ርቆ የሚገኝ ነው። ከፖርቱጋል የመጣው አምባሳደርና እኔ እንዲሁም ከኛ ጋር አምስት ጄኖቫውያን ሆነን ወደ አገው ሄድን። ወና በሆነ ምድር በጣም ትልልቆች የሆኑ የበቆሎ አገዳዎች በሚታዩባቸው እርሻዎችን እያለፍን አምስት ቀን ሙሉ ተጓዝን፤ የበቆሎዎቹ አገዳዎች በታላቅነታቸው ለወይን ዛፍ መደገፊያ እንዲሆን የሚሠራውን ቆጥ አጠና ይመስላሉ። ያ ሁሉ ተሰባብሮ ቅጠሉም ተመልምሎ ሲታይ አህያ የተለቀቀበት እርሻ ይመስላል እንጂ በእውነቱስ አንበጣ ነው ያጠፋው ብሎ ለማመን ያስቸግራል። የስንዴ የገብስና የጤፍ ሰብል ማርም ፈጽሞ ተበልቶ ዛፎችም

ከቅጠላቸው ተመልምለው ገሬንጫቸው ቁሞ ይታዩ ነበር። ለበቅሎቻችን ገብስ ለኛም አስፈላጊውን ስንቅ ጭነን ባንነሣ ኖሮ እኛም ከብቶቻችንም በረሃብ እናልቅ ነበር።

ያ የተጓዝንበት ምድር ሁሉ በኩብኩባ ተሸፍኖ ይታይ ነበር። በአገሩ ለጊዜው ይገኙ የነበሩትን አንበጣዎች የቀፈቀፈው ኩብኩባው ነው ይባላል፤ ክንፍ አውጥተው መብረር እንደጀመሩ በቶሎ አገራቸውን ፍለጋ ይጀምራሉ ይላሉ። ኩብኩባው ከብዛቱ የተነሣ ምንም ዓይነት ግምት ሊሰጠው የማይቻል ስለሆነ የብዛቱን ነገር ሳላነሣ ሌላውን ሃተታ ብቻ አስከትላላሁ። ወንዶችና ሴቶች ሕፃናትም በፍርሃት ተውጠው ባንድነት ተሰብስበው በኩብኩባው መካከል ተቀምጠው አይቻለሁ።

ሕዝቡ በአንበጣ መሰቃየቱን በማየት እነዚህን አንበጣዎች በመግደል የቀፈቀፏቸውን ኩብኩባዎች ለምንድር ነው የማትበቀሉ? እርሱን እንኳ መበቀል ባትችሉ እነዚህን በመግደል ብቻ ትልቅ ጉዳት ልታስወግዱ ትችላላችሁ፤ ብላቸው በኃጢአታችን ምክንያት ሊቀጣን እግዚአብሔር የላከብንን መቀጫ አንቀበልም ስንል ለመከላከል አንችልም ሲሉ መለሱልኝ።

በዚያ ቦታ በነበረው ሕዝብ ላይ አንበጣው ጉዳት ስለጣለበት ረሃብ ወዳላጠቃው ቦታ ለመሄድ ወንዶችና ሴቶች ሕፃናትም ጓዛቸውን በጭንቅላታቸው ተሸክመው ሲሄዱ ማየት በእውነተኛው የሚያሳዝን ትርኢት ነበር።

በቡግና ቀበሌ በምትገኝ አቋት በምትባል ቦታ እንደነበርን ትልቅ የአንበጣ ወረራ ደርሶ ከቀኑ ከሶስት ሰዓት ጀምሮ ሌሊቱን ሙሉ ወደዚያች ቦታ እየመጣ ያርፍ ነበር። በማግሥቱ ጠዋት ከዚያ ተነሥቶ መሄድ ጀምሮ በእኩለ ቀን ላይ በሙሉ ቦታውን ለቆ ሲሄድ በዛፎቹ ላይ ለምልክት እንኳ አንድ ቅጠል አልተረፈም ነበር። ወዲያውኑ ሌላ ጓድ መጥቶ ተተክቶ እንደፊተኛው በዚያ ቆይቶ በማግሥቱ ሲሄድ ሊበላ የቻለውን ነገር ሁሉ ጥርግርግ አድርጎ ሄደ።

ተከታትለው የመጡት እነዚህ ጓዶች አንዱ ሌላውን በመፈለግ ነው ይባላል። ቀድመው የበረሩት ኩብኩባዎቹን መንገድ ይመሩዋቸዋል ይባላል። አንበጣው ያጠፋው ምድር ርዝመት ሶስት ሌግዋ ያህል ስለሆነ የጓዱ ብዛት የቱን እንደሚያህል ግምት ሊሰጠን ይችላል። ባረፈበት ቦታ የዛፍ ቅርፍት እንኳ ሳይቀር በፍጹም ከመብላቱ ይልቅ ያረፈበት ምድር ሣር ከዳር እስከ ዳር ተግጦ በመድረቁ ምክንያት በረዶ የተኛበት ምድር ይመስል ነበር። በሰብል ላይ ጉዳት ይደርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስላልነበር አንበጣው የመጣው እህሉ ተወቅቶ ከተከተተ በኋላ ነበር። አንበጣው የመጣው ባሕር ነክ ከሆነው ጠረኞቹ ደንከሎች እስላሞች ከሚኖሩበት ግዛት መሆኑን ብቻ ስናውቅ ወረራውን ካበቃ በኋላ ግን ወዴት እንደሚሄድ ለማወቅ አይቻልም ነበር።

ምዕራፍ ሰላሳ አራት፤ ቴሜይ ስለመድረሳችን፤ አምባሳደሩ ትግሬ መኮንኑን ፍለጋ ስለመሄዱና እኛንም ስለማስጠራቱ።

ጉዞአችንን ቀጥለን በዚህ ቴሜይ በተባለ ቦታ ደርሰን ሁለት ቀን ከቆየን በኋላ በባርዋ ላይ ትተነው የመጣነው ዕቃችችን ከመድረሱ በፊት አምባሳደር ሩድሪጉ ስድስት ፈረሰኞችን አስከትሎ ብዙ አገረ ገዥዎችንና ሠራዊትን እያዘዘ በጠቅላይነት አንድ ሰፊ ግዛት የሚያስተዳድር ትግሬ መኮንን በሚያሰኝ ማዕርግ የሚታወቀውን ሰው አግኝቶ በርሱ ግዛት ብዙ ስለቆየን ስንቅ እንዲያዝልን ለመጠየቅ ሲል ሄደ።

መምህር ዮሐንስ፤ እኔና ሌሎችም ሁለት ፖርቱጌዞች ቴሜይ በተባለው በዚያ ቦታ ቆየን። በባርዋ ትተነው የመጣነውን ዕቃችንን እንዲጠብቅልን የተውነው ሰው ጓዛችንን በሙሉ አስይዞ እኛ በነበርንበት ቦታ ደርሶ ሁላችንም ባንድነት ሆንን። የባሕር ነጋሹ ወንድም የነበረው የዚህ ከተማ ሹም በሚገባ አከባክቦ አስተ

ናገደን። ተከትለውት ከሄዱት ፖርቱጌዞች ጋር ካረፈበት ከትግሬ መኮንኑ ቤት ድረስ ጓዙን አስይዘን እንድንሄድ በማዘዝ አምባሳደሩ ባንድ ሹም በኩል የላከብን መልእክት ሐምሌ 28 ቀን 1520 ዓም ደረሰን። ተሸካሚ በመፈለግ ሁለት ቀን ከቆየን በኋላ አንድ ሹም መጥቶ የሚያስፈልገንን ሰጥቶን ወደ አምባሳደሩ ጉዞአችንን ጀመርን። ጊዜው ክረምት ነበር። አንድ ሌግዋ ያህል ስፋት ያለውን ሜዳ ከሄድን በኋላ ቁልቁለትና ጥሻ በሆነ ገደላም መንገድ በተጨማሪ አንድ ሌግዋ ተጉዘን ሲመሽ ነብር እንዳይበላን በመፍራትና ከነጎድጓድ ለመሸሽ ስንል ባንድ ቤተ ክርስቲያን ገረገራ ውስጥ ገብተን አደርን። በማግሥቱ ተነሥተን ብዙ ተራሮችንና ገደሎችን ፍሬ የሌላቸው ዛፎች ጫካዎችን እያለፍን ብዙ ከተጓዝን በኋላ በዝናሙ ብዛት ምክንያት በጉርፍ መልቶ አላሻግር ባለን ባንድ ትልቅ ወንዝ ደረስን። ይህ ወንዝ በባርዋ አጠገብ የሚያልፈውና ከናይል ወንዝ የሚቀላቀለው ነው። የባሕር ነጋሹንና የትግሬ መኮንኑን ግዛቶች ድንበር ሆኖ የሚያዋስናቸው ይኸው ወንዝ ነው። ያ ያደርንበት ከተማ ከዚህ ወንዝ በግምት ሁለት ሌግዋ ያህል ርቆ ይገኛል። አገሩ ምንም እንኳ ተራራማና ጫካም ቢሆን ሰው በብዛት ይገኝበታል።

ምዕራፍ ሰላሳ አምስት፤ ትግሬ መኮንኑ ዕቃችንን ለማስፈለግ አንድ መኮንን ስለመላኩና በመጀመርያው ቦታ ስላየናቸው ቤቶች ሁኔታ።

ዕቃችንን ይዘውልን የመጡት ሰዎች ጓዙን እንዳሳረፉ ከወንዙ ወዲህ ማዶ ትተናቸው ልንሻገር ስንል የነጋሪት ድምጽና የሰው ጫጫታ ሰምተን ምን መሆኑን ብንጠይቃቸው ትግሬ መኮንኑ የሚቀበሉን ሰዎች የላከልን መሆኑን ነገሩን፤ እኛም ያን የመላ ወንዝ በታላቅ ችግር ከተሻገርን በኋላ በሚገባ አኳኋን የለበሱ አምስትና ስድስት መቶ የሚሆኑ እኛን ለመቀበልና ዕቃችንንም ሊሸከሙልን የመጡ ሰዎች አገኘን። በነዚህ ሰዎችና ዕቃችንን ተሸከመው በመጡት በባሕር ነጋሹ ሰዎችና በትግሬ መኩንኑ

ጭፍሮች መካከል ፉክክር ተነሥቶ የወዲህ ማዶዎቹ ዕቃሙ ወዲህ ማዶ ካልደረሰልን ከቶ አንሸከምም ሲሉ የወዲያ ማዶዎቹ፤ ማለት የባሕር ነጋሹ፤ በግዛታችን ድንበር ስላደረስን ከንግዲህ ወዲያ የኛ ፈንታ አይደለም በማለት በታላቅ አተካራ ላይ ደረሱ። ይሁን እንጂ ወዲያውኑ በመካከላቸው የመገባባት መንፈስ ተፈጥሮ ሁለቱም ወገኖች በመተባበር ዕቃችንን አሻገሩልን።

የትግሬ መኮንኑ ሰዎች ዕቃችንን ተሸክመው እኛም በበቅሎ ሆነን እኩል ስንገሰግስ በፊት ያጋጠሙንን የመሰሉ ተራሮችን በማለፍ የዚያኑ ዕለት ብዙ መንገድ ተጓዝን። በመንገዳችን ላይ ብዙ አሳማዎች አንዳንዶቹም በሃምሳ ጓድ ሆነው ሲሄዱ እናይ ነበር። ቆቆችና ሌሎች ወፎችም ምድሩንና ዛፎቹን አልብሰዋቸው ይታዩ ነበር፤ በዚያ ቦታ ማናቸውም ዓይነት እንስሳ ይገኛል ይባላል፤ የተራሮቹን ብዛትና የቦታውን የተፈጥሮ ባሕል ሲመለከቱት በእውነትም የእንስሶቹን መገኘት ለመካድ አይቻልም። የዚያን ዕለት ማታ ባንድ ሜዳ ላይ ሠፍረን አውሬ እንዳይተናኮለን በማለት ዙርያችንን እሳት አያይዘን ስናነድ አደርን። ከዚያ ጀምሮ ወደፊት ያለው የተፈጥሮ ሁኔታ፤ የሕዝቡ አለባበስና ዕዕዋቱም በፊት ካየነው ልዩ እየሆነ ሄደ። ተጠጋግተው ባንድነት የሚገኙት ቀጥ ያሉ ተራሮች አጠገብ ደረስን። ተራሮቹ ተንዘራፍጠው የሚገኙበት ምድር በጣም ሰፊ አይደለም፤እነዚሁኑ የመሳሰሉ ያለማቋረጥ በአገሩ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ። በተራሮቹ ጫፍ ለመድረስ ምንም እንኳ አደገኛ ቢሆንም የፈለገ ሰው እላይ ድረስ ወጥቶ በዚያ የሚገኙትን አብዛኞቹ በእመቤታችን ስም የሚጠሩትን ቤተ ክርስቲያኖች ለማየት ይችላል። በብዙዎቹ ሌሎች ተራሮች ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች አይተናል፤ ነገር ግን እንዴት አድርጎ በዚያ ለመድረስ እንደሚቻል ለማወቅ ያስቸግር ነበር።

የዚያን ዕለት ማታ አባ አፍጼ በተባለ ተራራ ጫፍ መካከል በሚገኝ ከተማ አደርን። በዚያ ከተማ ባማረ ሁኔታ በተሠራና የመካከላቸው መተላለፊያ ከፍ ያለ የተጌጠ ጣርያ ያለው አንድ የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን አለ። መስኮቶቹ ማለፊያ ሆነው

የተሠሩና ጣርያውም የተጌጠ ነው። በዚያ መልክ የተሠራ ሌላ ቤተ ክርስቲያን በአገሩ ውስጥ አላየንም። በአሠራራቸው ይህን የሚመስሉ በፖርቱጋል በዶሩና በሚኙ መካከል በሚገኘው ግዛት ቀበሌዎች ይገኛሉ። ቁመትና ስፋት ያለው አሠራሩ ማለፊያ የሆነ አንድ ግድግዳ በዚያ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ አለ። ምንም እንኳ ከጊዜ ብዛት ያ ከጥርብ ድንጋይ የተሠራ ሕንጻ ወደመውደቅ ቢደርስም ቤቱን ያሠሩት ነገሥታት መሆናቸው በግልጽ ይታወቃል። ይህን የመሰለ ሕንጻ በአገሩ ውስጥ ከቶ አላየንም። በሕንጻው ዙርያ ግድግዳቸው ያማረና ጣርያቸውም ሜዳ የሆነ የታላላቅ መሳፍንት መኖርያ የሚመስሉ ብዙ ቤቶች አሉ። እነዚህ ሕንጻዎች የንግሥት ሕንደኬ ነበሩ የሚል ወሬ ሰምተናል። ይህች ሴት የክርስትናን ሃይማኖት በተቀበለችበት ጊዜ ትኖርበት የነበረው ቤት ከዚህ ቦታ ጥቂት እልፍ ብሎ የሚገኝ ስለሆነ ወሬው እውነት ሊሆን ይችላል። ይህ ቦታና ቤተ ክርስቲያን ዙርያውን በተራራ የተከበበ ባንድ መልካም መስክ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ ከተራራው ጫፍ የሚፈሰው ውኃ በመስኖ ተዘጋጅቶ በዚያው መካከል ያልፋል። በመስኖው ምድር ላይ ገብስና ስንዴ፤ ባቄላና ሽንብራ አተርም ይዘራል፤ ነጭና ቀይ ሽንኩርት ልዩ ልዩ ጎመናጎመኖች በብዛት ይተከላሉ።

በዚህ ቦታ በደንብ የለበሱና መልካም ሰዎች የሚመስሉ ብዙ ካህናት ነበሩ፤ የክርስትና ሃይማኖት ለመጀመርያ ጊዜ በኢትዮጵያ በገባ ጊዜ በዚህ ቦታ ሰባት ቤተ ክርስቲያኖች ተሠርተው ነበር፤ ያ እነርሱ የሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ከነዚያ አንዱ ነው ሲሉ እነዚሁ ካህናት ነገሩን፤ የክርስትና ሃይማኖት ለመጀመርያ ጊዜ በኢትዮጵያ የተሰበከው ከዚያ ቦታ ጥቂት እልፍ ብሎ በሚገኘው አክሱም በተባለው ቦታ ስለሆነ ያ የሰማነው ወሬ ምናልባት እውነት ሳይሆን አይቀርም።

ምዕራፍ ሰላሳ ስድስት፤ ከአባ እፍጼ ተነሥተን የቅዱስ ሚካኤል ቤቶች ወደተባለው ከተማ[1] ስለመሄዳችን።

እኛና ዕቃችንን የተሸከሙልን ሰዎችም ከዚያ ቦታ ተነሥተን በመጣንበት አኳኋን ጉዞአችንን ቀጠልን፤ ቅዱስ ሚካኤል በተባለ ባንድ ከተማ አደርን። ዕቃውን የመሸከሙን ተግባር ሕልፈት[2] ይሉታል። በዚያ ከተማ ማደር ክልክል ስለነበር ማደርያ አልተሰ ጠንም፤ ስለዚህ በዝናሙ ውስጥ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄደን ከገረገራው ውስጥ ከሚገኘው ረጃጅም ሣር ውስጥ በቅሎቻችንን አስገብተን እኛም በቤተ ክርስቲያኑ ታዛ ሥር አደርን። በዚህ ቦታና በመላ ኢትዮጵያ ምግብ የሚሰጠው በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። እኛ በዚያ የደረስነው በምሽት ስለነበር፤ ምንም ምግብ ሳይሰጠን ሁላችንም ተርበን ቁጭ እንዳልን የንብረት ሹማችን ድንገት «አባ እንብላ» የሚል ድምጽ አሰማኝ። እኔም በነገሩ ተገርሜ «ምንድን ነው የምን በላው ልጄ» ብዬ ብጠይቀው የሁለት ዶሮች ሥጋ አብስዬ ይዣለሁና እንብላ ሲል ጋበዘን። እኔና ጻሐፊአችን የዶሮ ሥጋ ያለ እንጀራ በመበላቱ በመደነቅ ሁላችንም ባንድነት ሆነን የቀረበልንን በላን።

ከዚያን ጊዜ በኋላ ሥጋን ያለ እንጀራ እንጀራንም ያለ ሥጋ ወይም ያለ ጨው ብዙ ጊዜ መብላት ብዙ ጊዜ ግድ ስለሆነብን አድናቆታችን ሁሉ ቀረ። በዚያ ቦታ ሕዝቡ የሚበላው ምግብ ከውኃ ብቻ የተዘጋጀ ፍትፍት ነው።

በታዛው ሥር እንደተኛን ሌሊት ምግብ ልከውልን ጥቂት ጽዳት ወዳለው ቦታ ለመጠጋት ስንል ሥጋ ወደሙ ወደሚቀመጥበት ወይም ወደሚሰጥበት ቦታ ተጠግተን መብራት እያበራን ቁጭ እንዳልን በጣርያው ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ርግቦች ሲንቀሳቀሱ አየን። ወዲያውኑ ብድግ ብለን እንዳያመልጡን በሩን ዘግተን በሙሉ ከነጫጭቶቻቸው ይዘናቸው በከረጢታችን ውስጥ መላናቸው። በሌላ ጊዜ በዚህ ቦታ ስናልፍ ምንም እንኳ ከተማው የተከለከለ ቢሆንም ለማደር ተፈቅዶልን ነበረ። ነገር ግን እንደገና ረብተው ይገኙ የነበሩትን

የቤተ ክርስቲያኑን ርግቦች እንዳንገድል አስጠነቀቁን። በዚህ አገር ነዋሪዎችና በባሕር ነጋሹ ግዛት ሕዝብ መካከል ያለው ልዩነት አለባበስ ነው። ወንዶቹ እንደኛው አገር ሴቶች ልብስ የተሰሩ ጨርቅ ወይም ቆዳ ያሸርጣሉ። ይህ ሽርጥ ከሁለት ስንዝር የበለጠ ርዝመት ስለሌለው ለብሰውት ሲሄዱ ነውራቸውን ለመሸፈን በቂ ነው፤ ነገር ግን ጎንበስ ሲሉ ሲቀመጡ ወይም ነፋስ ሲነፍስ ይጋለጣሉ። ልጃገረዶቹ ለነውራቸው መሸፈኛ ያህል የሚበቃ አጭር ልብስ ሲለብሱ ያገቡት ደግሞ ጥቂት ሻል ያለ ይለብሳሉ። ሌሎች ሴቶች በአንገታቸው ላይ የሚያደርጉትን ጌጥ የዚህ አገር ሴቶች በወገባቸው ላይ ያስሩታል። በሰውነታቸው ላይ ቃጭል ያንጠለጥላሉ። ከሴቶቹ አዳንዶቹ ከአንገታቸው ላይ ብቻ ሸብ ተደርጎ ቁልቁል በመንዘርፈፍ የሰውነታቸውን አንድ ክፍል ብቻ የሚሸፍን የበግ ለምድ ይለብሳሉ። ቆዳውን በአንገታቸው ላይ የሚያስሩት የበጉን የፊትና የኋላ እግር አብሮ በማያያዝ ነው።

እኛ በነበርንበት በዚያ ቦታ ለመድረስ ከግብጽና ከሱዋኪን ወይም ከቀይ ባሕር የሚመጣውን መንገድ ተከትሎ ከበደበጅ በሮች እስኪደርሱ በቀጥታ ወደደቡብ መጓዝ ነው። ከዚህ ቦታ ጥቂት እልፍ ብሎ የሚገኘውን ንጉሠ ነገሥቱ የሠፈረበትን ከተማ እየጠየቁ ወደ ምሥራቅ ሌላም ጊዜ ወደ ምዕራብ ወይም በቀጥታ መጓዝ ነው። የበደበጅ በሮች ያማራንና የሸዋን ግዛቶች የሚያዋስኑ ናቸው። እኛ መንገድ እየተሳሳትን አንዳንድ ጊዜ በመንገድ ስንገባ አንዳንድ ጊዜም ስንወጣ በአገሩ በመመላለስ ስድስት ዓመት አሳልፈናል።

ምዕራፍ ሰላሳ ሰባት፤ ስለአክሱም፤ ንግሥተ ሳባ ለንጉሥ ሰሎሞን ስለወሰደችው ወርቅ ከርሱም ስለወለደችው ልጅ።

እስካሁን ድረስ ከምንገኝበት ከዚህ አምባ በስተምዕራብ በኩል በጣም ታላላቅ የሆኑ ግዛቶች አሉ። ከነዚሁም አንዱ ከቅዱስ ሚካኤል ከተማ የሁለት ቀን መንገድ ርቆ የሚገኘው አክሱም የተባለው ከተማ

ነው። በንጉሡ ነገሥቱ ትዕዛዝ በዚህ ከተማ ስምንት ወር ተቀምጠናል። አክሱም የንግሥት ሳባ መናገሻ ከተማና መኖርያዋም ነበር፤ ንጉሥ ሰሎሞን የየሩሳሌምን መቅደስ በሚያሠራበት ጊዜ ይህች ንግሥት ወርቅ አስጭና የሄደችው ከዚሁ ቦታ ነው ይባላል። በዚያ እንደደረስን እጅግ ያማረ ቤተ ክርስቲያን አገኘን፤ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መጀመርያ በእብራይስጥ በኋላም በግሪክ ከዚያም ወደ ከልዳይስጥ[1] የተተረጎመ አንድ ትልቅ ዜና መዋእል አገኘን። ይህ ዜና መዋእል እንዲህ በሚል ቃል ይጀምራል። «ንግሥተ ሳባ ንጉሥ ሰሎሞን በየሩሳሌም የጀመረውን ግዙፍ ሥራ ለማየት ወደዚያው ለመሄድ አስባ ለሥራው መርጃ የሚሆን ወርቅ በግመሎች አስጭና ሄደች። በከተማው አጠገብ በሚገኝ የእንጨት መሸጋገርያ በተጣለበት ባንድ ኩሬ አጠገብ ስትደርስ ከተቀመጠችበት ከብት ወርዳ ለተጋደመው እንጨት ሰግዳ አምላክ ሆይ የዓለም መድኃኒት የሚሰቀልበትን እንጨት እግሮቼ ይረግጡ ዘንድ አትፍቀድ ብላ ዞራ በማለፍ ሰሎሞን ወደነበረበት ሄዳ ያን እንጨት ከዚያ እንዲያስነሣ አደረገች። ከአገርዋ ይዛ የመጣችውን ገጸ በረከት ሰጠችና ቀጥሎ የተመለከተውን አድናቆት ገለጸች። የዚህ መቅደስ ታላቅነትና ጌጠኛነት ተዋዳዳሪ ስለሌው ያዩት ሰዎች ከዚህ በፊት ከነገሩኝ እጅግ የሚበልጥና በሰው ልሳን በተሙዋላ አኳኋን ሊገለጽ የማይቻል ነው። ይዤው የመጣሁት ገጸ በረከት በጣም ትንሽ በመሆኑ በጣም አዝናለሁ፤ ይሁን እንጂ ወደ አገሬ ስመለስ ሥራው የሚጠይቀውን ያህል ወርቅና ለመቅደሱም ሕንጻ የሚያስፈልገውን ጥቁር እንጨት እልካለሁ ብላ ለንጉሡ አገለጸችለት።»

ንግሥቲቱ በየሩሳሌም በቆየችበት ጊዜ ከንጉሥ ሰሎሞን አንድ ወንድ ልጅ ወልዳ ጉዞዋን ለመጀመር ስትችል ወደ አገርዋ ለመመለስ ተነሣች፤ ከአገርዋ እንደደረሰች ብዙ ወርቅና ለመቅደሱም ማጌጫ ጥቁር እንጨት ለንጉሡ ላከችለት። ይህ ልጅ አስራ ሰባት ዓመት እስኪሆነው ድረስ ከንጉሥ ሰሎሞን ሌሎቹ ልጆች ጋር አብሮ አደገ። በሰውነቱ መጠንከርና በግዙፍነቱ ከሌሎቹ ልጆች በጣም ይበልጥ ስለነበር መላውን የእስራኤልን ሕዝብና የይሁዳን ምድር ያስፈራ ነበር። እስራኤላውያን ወደሰሎሞን እየቀረቡ ንጉሥ ሆይ ልጆችህ

ሁሉ አንድ ቀን ነገሥታት የሚሆኑ ቢሆኑም ሁሉንም አንግሠን ለመቀበል አንችልም፤ ይልቁንም ከአንተ የበለጠ ታላቅነት ካላት ከንግሥተ ሳባ የወለድኸው ልጅህን ወደዚያው ወደናቱ አገር ላክልን፤ እኛ እርሱን አንችለውም አሉት። ከዚህ በኋላ ሰሎሞን ለአንድ ንጉሥ የሚያስፈልገውን አጀብ አዞለትና በግብጽ አገር ድበር ያለውን ጋዛ የተባለውን ቦታ እንዲያርፍበት ሰጥቶት ከብዙ ታላላቅ ሰዎች ጋር ወደ እናቱ አገር ላከው። በዜና መዋእሉ መሠረት ከባሕር እስከ ባሕር እንደገዛና በሕንድ ውቅያኖስም ሰላሳ መርከቦች እንደነበሩት ይተረካል። የዜና መዋእሉ መጽሐፍ በጣም ትልቅ ነው፤ እኔ የገለበጥሁት የመጀመርያውን ብቻ ነው።

ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት፤ ቅዱስ ፊልጶስ ለንግሥተ ሕንደኬ ግንደረባ የኢሳኢያስን ትንቢት እንደገለጸለት፤ በዚሁ ጃንደረባ አማካይነት እርስዋና ሕዝብዋም የክርስትናን ሃይማኖት ስለመቀበላቸውና ስለ አክሱም ከተማ ሕንጻዎች።

በኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ለመግባቱ መጀመርያ የነበረችው ንግሥት ሕንደኬ የኖረችው በአክሱም ከተማ ነበር። ከአገሩ ሕዝብ እንደሰማነው ይህች ንግሥት የተወለደች ከአክሱም ግማሽ ሌግዋ ርቆ በሚገኘው አሁን የባለእጆች መኖርያ በሆነው በኢትዮጵያ ለመጀመርያ የክርስትና ሃይማኖት በተሰበከበት መንደር ነው። በመጽሐፉቸው በተጻፈው መሠረት መልአኩ ወደ ፊልጶስ መጥቶ ተነሣና ከየሩሳሌም ወደጋዛ የሚወስደውን ምድረ በዳ መንገድ ተከትለህ ወደ ደቡብ ተጓዝ አለው።

ፊልጶስም መንገዱን ይዞ ከተጓዘ በኋላ የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ የሃብትዋ ሁሉ ሹም የነበረውን ጃንደረበ አገኘ። ይህ ሰው የንግሥቲቱን ሃብት ሁሉ የሚያስተዳድር ታላቅ ሰው እንደመሆኑ

መጠን በሠረገላ ወደ ኢየሩሳሌም ደርሶ ሲመለስ ወዳገሩ ለመሄድ ንጉሥ ሰሎሞን ለልጁ በሰጠው ጋዛ በተባለ ቦታ ደርሶ ነበር። የነቢዩ የኢሳኢያስን ትንቢት እያዜመ ሲሄድ ፊልጶስ አግኝቶት የምታዜመው ቃል ይገባሃልን ብሎ ቢጠይቀው የሚገልጽልኝ ሰው ሳይኖረኝ እንዴት ሊገባኝ ይችላል ሲል መለሰለት። ወዲያውኑ ቅዱስ ፊልጶስ በሠረገላው ላይ ወጥቶ ያን ትንቢት እየገለጸለት ሄዶ ዣንደረውን አጥምቆ በክርስትና ሃይማኖት አስገባው። ወዲያውኑ ፊልጶስን መንፈስ ስለነጠቀው ዣንደረባው ደህና አድርጎ ተምሮ ብቻውን ቀረ። ፊልጶስ ይህን ሰው አግኝቶ ማጥመቁ ንጉሥ ዳዊት«ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ሐበ እግዚአብሔር» ሲል ለሰጠው ትንቢት ፍጻሜ ነው ይላሉ። ስለዚህ በዚሁ ግንኙነት ምክንያት በዓለም ላይ ለመጀ መርያ ጊዜ የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበልን እኛ ኢትዮጵያውያን ነን ይላሉ።

ጀንደረባው በደስታ ተምልቶ ወዲያውኑ የእመቤቱ መኖርያ ወደሚገኝበት ወደኢትዮጵያ ሄዶ የሰማውን ዜና በመንገር ብቻ ንግሥቲቱንና ቤተሰብዋን ከማጥመቁ በላይ የቡርን ግዛት ሕዝብ በሙሉ እንዲያጠምቅ አዘዘች። ይህ ቡር የተባለ ግዛት ከባሕር ነጋሹ ግዛት ከሚገኝ ከአከሱም በስተምዕራብ ያለ አሁን በሁለት ተከፍሎ የሚገኝ ነው። የክርስትናን ሃይማኖት በተቀበለችበት በአክ ሱም ከተማ ቅድስት ማርያም ዘጽን የተባለ ቤተ ክርስቲያን አሠራች ይባላል።[1] ቤተ ክርስቲያኑ በጽዮን ስም መጠራቱ የታቦቱ ጽላት ከጽዮን ተራራ ስለመጣ ነው ይባላል። በተነገረን መሠረት በያንዳንዱ ታቦት ላይ ያንዳንድ ቅዱሳን ስም ተጽፎ ስለሚገኝ ቤተ ክርስቲያኑ በዚያው ስም ይጠራል አሉን። የዚህን ታቦት ጽላት ሐዋርያት ናቸው ከደብረ ጽዮን የላኩልን የሚል እምነት አላቸው።

ቤተ ክርስቲያኑ ረዣዥምና ሰፋፊ የሆኑ አምስት ቅስቶች አለው፤ ጣርያውና ግድግዳው በደንብ ቀለም ተቀብቶአል፤ የቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ ጥሩ ሆኖ በጥርብ ድንጋይ ታንጾአል፤ ጀርባቸውን ወደምስራቅ ያዞሩ መሠውያቸው በደንብ ያጌጡ ሶስት ቅድስተ ቅድስታት በሕንጻው ውስጥ አሉ።

በኛ ቤተ ክርስቲያን እንደተለመደው ዓይነት የመዘምራን ክፍል አላቸው፤ ይሁን እንጂ ጣራው በጣም ቅርብ ስለሆነ ሲቆሙ በራሳቸው ይነኩታል። ከቅድስቱም በላይ የመዘምራን ክፍል አለ፤ ነገር ግን ይህን እምብዛም አይጠቀሙበትም፤ በቤተ ክርስቲያኑ ዙርያ በሰፋፊ ጥርብ ድንጋይ የተሠራ ረዥም ግድግዳ አለ፤ ይህ ግድግዳ እንደሌሎቹ ቤተ ክርስቲያኖች በጣርያ አልተከደነም። ይህ ቤተ ክርስቲያን አንድ ትልቅ ከተማ ይመስል ዙርያውን በሁለት አጥር ተከቦአል። ከውጭ በኩል ባለው በመጀመርያው አጥር ግቢ ውስጥ ውኃ የሚተፉ በአንበሳና በውሻ መልክ የተሠሩ የድንጋይ መስረበ ማዮች አሉ። በታላቁ አጥር ግቢ አንደኛው በስተቀኝ ሌላውም በስተግራ በኩል የሚገኙ ከቤተ ክርስቲያኑ ሊቀ ካህናት ሁለት ቤቶች አሉ፤ በዚያው ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ቤቶች የደብ ተራዎችና የመነኩሴዎች መኖርያዎች ናቸው። ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ባለው በታላቁ አጥር በር ላይ አሁን ፈርሶ የሚገኝ አራት መዓዘን ሆኖ በየመዓዘኑም የጥርብ ድንጋይ የነበረበት አንድ ፍራሽ አለ። ይህ ቤት የአንበሳ ቤት ይባላል፤ ይህን ስያሜ ያገኘበት ምክንያት የታሠሩ አንበሶች ስለሚኖሩበት ነበር ይባላል። የታሠሩ አንበሶች አሁንም በዚሁ ቦታ ይገኛሉ፤ በንጉሠ ነገሥቱም ፊት የታሠሩ አራት አንበሶች ሁል ጊዜ ከፊት ቀድመው ይሄዳሉ። ከትልቁ በር ፊትለፊት የተተከለ የፈረዖን በለስ የተባለ አንድ ዛፍ አለ፤ በዛፉ ግራና ቀኝ አዲስ የታነጸ የድንጋይ ንጣፍ አለ፤ በበለሱ ዛፍ ጥግ የሚገኙትን የድንጋዩን ክፍሎች ሥሩ ቢፈነቅላቸውም ሌሎቹ ግን በመልካም ሁኔታ ይገኛሉ። ከድንጋዩቹ ላይ እያንዳንዳቸው ካንዳንድ ድንጋይ ተጠርበው እንጨት መስለው የተሠሩ የእግር ማሳረፊያ ያላቸው ወንበሮች አሉ፤ እነዚህ ወንበሮች በቤተ መንግሥቱ ለሚያገለግሉ አስራ ሁለት ዳኞች የተሠሩ ናቸው ይባላል። ከቤተ ክርስቲያኑ ዙርያ በኢትዮጵያ መሰል የሌላቸው ማለፊያ ሕንጻዎች የሚገኙበት አንድ ትልቅ ከተማ አለ፤ የከተማው ሕዝብ ውኃ የሚ ቀዳው በድንጋይ አምረው ከተሠራ ጥሩ የውኃ ጉድጓዶች ነው። ብዙ ሕንጻዎች ከዚህ በፊት እንደገለጽነው በአንበሳ በውሻና በዎፎችም መልክ የተቀረጹ መስረበ ማዮች ይታዩባቸዋል። ከቤተ ክርስቲያኑ በስተኋላ በኩል በሚገኝ ማለፊያ ሆኖ በተሠራ ባንድ የውኃ ማጠራ

6

ቀሚያ ዙርያ ባሉ ደረጃዎች ላይ ብዛታቸው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያሉትን የሚያህል የድንጋይ ወንበሮች ተደርድረው ይገኛሉ።[2] ይህ ከተማ የተቆረቆረው ባንድ ሜዳ ዳርቻ በሁለት ተራሮች ጫፍ አጠገብ ነው፤ የድንጋይ ወንበሮችና ጽሁፍ የተቀረጸባቸው አምዶች በየመካከላቸው የሚገኝባቸው ቤቶች ሜደውን በሙሉ ሸፍነውታል።

ከከተማው በለይ በደንብ አምሮ ከተጠረበ ድንጋይ የተሠሩ ማለፊያ ሐውልቶች ተተክለው ግማሾቹም በምድር ላይ ትጋድመው ይታያሉ። ከሐውልቶቹ አንደኛው እጅግ ግዙፍ የሆነና የመሰውያ ድንጋይ መስሎ በተሠራ በሌላ ድንጋይ ላይ የተሠራ ነው። ይህ ግዙፍ ሐውልት ቁመቱ ሰለሳ አራት፤ ስፋቱ ስድስት፤ ጎኑም ሶስት ኮቫዱ[3] ነው። ቀጥ ብሎ የሚወጣው ይህ ሐውልት ከላይ እስከ ታች ማገር በሚመስል ጌጥ እያጌጠ ይወጣና ጫፉ ግማሽ ጨረቃ በሚመስል ጌጥ ይደመደማል። በጫፉ ላይ ያሉ በመበስበሳቸው ምክንያት በደንብ የማይታዩ አምስት ምስማሮች አሉ፤ እነዚህ ምስማሮች ባቀማመጣቸው ኪናሽ[4] ይመስላሉ። ይህን ረዥም ሐውልት እንዴት አድርጎ ለመለካት ተቻለ ሲል አንባቢ ሳይጠይቅ አይቀርም ይሆናል፤ ነገር ግን ከፍ ብለን እንደገለጽነው ማገር የሚመስሉትን ጌጦች እስከግማሽ ጨረቃው ድረስ እየወጡ ይሄዳሉ ስላልን ሁሉም ትልቅ ነታቸው እኩል በመሆኑ አንዱን በመለካት ብቻ የሐውልቱን ታላቅነት ለማወቅ ይቻላል።

ስለዚህ እነዚያን ማገር መሰል ጌጦች እስከምንደርስበት ድረስ ለከተን ቁመቱን ካገኘን በኋላ የእናቱን ጌጥ እጅግ ቢያንስ አራት ኮቫዱ ገመትነው። ሐውልቱ ምስማሮቹ በሚታዩበት በኩል በምዕራብ ባለው ክፍሉ ባንድ ሰው ቁመት ልክ የተሠራ መዝጊያ መሰል ጌጥ አለው። በሩ የተዘጋ ይመስል የመቀርቀርያና የቁልፍ ምስል ይታይበታል። ሐውልቱ የተተከለበት ድንጋይ አምሮ የተጠረበ አንድ ኮቫዱ ውፍረት ያለው ነው። ይህም ድንጋይ በሌሎች ታናናሽ ድንጋዮች ላይ ተቀምጦአል፤ የላይኛው ድንጋይ የቱን ያህል ጠልቆ በትንንሾቹ ላይ እንደተተከለ ወይም እስከምድር ድርስ ይጠልቅ እንደሆነ ለማወቅ አይቻልም። ከዚህም በስተቀር ሌሎች በምድር ላይ

ተተክለው የሚገኙ ቁመታቸው በሰላሳና በአርባ ኮቫዱ መካከል የሆነ ብዛታቸውም ከሰላሳ የማያንስ አሉ። ከነዚህ ሐውልቶች አንዳንዶቹ በትልልቁ የተቀረጹ ጽሑፎች ይታዩባቸዋል፤ ይህን ጽሑፍ የአገሩ ሕዝብ ወይም እኛ ልናነበው አልቻልንም፤ ይሁን እንጂ የእብራይስጥ ጽሑፍ ሳይሆን አይቀርም።[5] ሁለቱ ታላላቆቹና ልዩልዩ ጌጥ ተቀርጸውባቸው የነበሩት ሐውልቶች አሁን ወድቀው ይገኛሉ፤ አንደኛው በሶስት ቦታ ተሰባብሮአል። እነዚህ ሐውልቶች እያንዳ ንዳቸው ቁመታቸው ስፋታቸውም ከአስር ኮቫዱ በላይ ይሆናል። ሐውልቶቹ ከመውደቃቸው በፊት በቆሙባቸው ቦታዎች ላይ በደንብ የተጠረቡና ብዙ ቀዳዶች የሚታዩባቸው ድንጋዮች በዙርያው ይገኛሉ።

ምዕራፍ ሰላሳ ዘጠኝ፤ በአክሱም ዙርያ ስላሉት ሕንጻዎችና በውስጣቸውም ስለሚገኘው ወርቅ፤ በዚያም ስላለው ቤተ ክርስቲያን።

ከአክሱም ሲሶ ሌግዋ ርቆ በሚገኝ ብዙ ቦታዎችን በሚያዋስን አንድ ኮረብታ አጠገብ ከመሬት ውስጥ ተቆፍረው የተሠሩ ያለ መብራት የማይገባባቸው ሁለት ቤቶች አሉ።[1] የቤቶቹ ጣርያዎች ሳይቀሰቱ ግድግዳና ጣርያቸው በጠፍጣፋ ድንጋይ ለብሶአል፤ ምሰሶዎቹ በውጭ በኩል ነፃ ናቸው። ግድግዳዎቹ አስራ ሁለት ኮቫዱ ርዝመት አላቸው፤ ምሰሶዎቹ ከግድግዳው ተጠጋግተው ስለሚገኙ አንድ ትልቅ ድንጋይ ይመስላሉ። ባንደኛው ክፍል ውስጥ ብዙ ክፍሎችና ጎተራዎች አሉ፤ በደፉ ላይ የበሩ መሰኪያ ቀዳዳ ይታያል። ከነዚህ ክፍሎች ባንዱ የያንዳንዳቸው ርዝመት አራት ኮቫዱ ውፍረታቸውም አንድ ኮቫዱ ተኩል የሆነ ሁለት ትልልቅ ሣጥኖች አሉ። የውስጣቸው የላይኛ ክፍል ለመክደኛ እንዲመች ታስቦ የተሠራ ይመስል ቀዳዶች ይታዩበት ነበር። (ንግሥተ ሳባ ሃብቱዋን የምታከማቸው በነዚህ ሣጥኖች ውስጥ ነበር ይባላል።) ጥቂት ሰፋ ያለው ቤት አንድ ክፍልና አንድ ታዛ ብቻ ነው ያለው። ካንዱ በር እስከ ሌላው ያለው ርቀት ያንድ «መልያው» ጭዋታ ያህላል።[2] ከቱርክ እስረኝነት አምልጠው

የመጡ ከኛ ጋር የነበሩ ትሮያንና በግብጽ የሚገኘውን የዮሴፍን ኅተራ [3] የኀበኙ የካታሉንያና የጄኖቫ ሰዎች ምንም እንኳ ያዩዋቸው ሕንጻዎች ታላቅነት የማይካድ ቢሆንም ነገር ግን በታላቅነት በአክሱም ያዩዋቸውን በፍጹም የማይተካከሉ መሆናቸውን በመግለጽ ቃላቸውን በመሃላ አረጋግጠዋል። እነዚህን ሕንጻዎች እንድንመለከት ንጉሠ ነገሥቱ በተለይ ወደዚያ ያስመራን ነበር የመሰለን፤ ታላቅነታቸውንና አስገራሚነታቸውን በጽሑፍ ልገልጸው ከሞከርሁት በላይ የሆኑትን እነዚህን ሕንጻዎች በማየታችን በጣም ተደሰትን። በክረምቱ ወራት ልዩልዩ ዓይነት እህል ተዘርቶባቸው በሚገኙት በአክሱም አካባቢ ባሉት ቀበሌዎችና በከተማው ዝናም በጣለ ቁጥር ወንዶችና ሴቶች ሕጻናትም በሙሉ ከቤታቸው ወጥተው በየእርሻውና ጎርፍ በሚያልፍበት ቦታ ሁሉ ወርቅ ለመፈለግ መጫርያ እንጨት ይዘው ይወጣሉ። ዝናም በጣለ ጊዜ ጎርፍ የተሠወረውን ፈልፍሎ ወደውጭ ስለሚያወጣው ወርቅ በብዛት ይገኛል ይባላል። ስለዚህ በከተማውም ሆነ በየእርሻው ወርቅ እንደልብ ይገኛል እየተባለ ሲወራ በመስማት በፎሸ ዲ አሮካና በፖንት ሙስላው (ፖርቱጋል) ያየሁትን የመሰለ አፈሩን ማጠቢያ ሳንቃ ሠራሁና እንደሕዝቡ ፍለጋ ገባሁ፤ ነገር ግን ወርቁን በፍጹም ላገኝ አልቻልሁም። ማጠቡን ባለማወቄ ወይም ካጠብሁት በኋላ ላየው ባለመቻሌ ወይም ወርቅ ባለመገኘቱ መሆኑን አላወቅሁም፤ ይሁን እንጂ ብዙ ወርቅ መኖሩ ይወራል።

በኢትዮጵያ ምድር ላይ በመጀመርያ ተሠራ የሚሉት የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በዚሁ ምክንያት ከሁሉ የበለጠ የተከበረ በመሆኑ በውስጡ የሚፈጸመው የቅዳሴ ስነሥርዓት በሚገባና በተሙዋላ አኳኋን ነው። በቤተ ክርስቲያኑ አንድ መቶ ሃምሳ ደብተራዎችና በዚሁ የሚገመቱ መነኩሴዎች አሉ። አንደኛው የደብተራዎቹ ሌላው የመነኩሴዎቹ አለቃ የሆኑ ንብረ እድ በተባለ የማዕርግ ስም የሚታወቁ ሁለት ባለሥልጣኖች የቤተ ክርስቲያኑን ሥራ በበላይነት ይመራሉ። የሁለቱም ንብረ እዶች መኖርያዎች በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ ሲገኙ የደብተራዎቹ ንብረ እዱ ከሌላው የበለጠ ሥልጣን ስላለውና በይበልጥ የተከበረ በመሆኑ በስተቀኝ በኩል በሚገኘው መኖርያ ውስጥ ይቀመጣል። ይህ ንብረ እድ ደብተራዎቹን ብቻ ሳይሆን

የአክሱምንም ከተማ ሕዝብ ይዳኛል። የመነኩሴዎቹ ንብረ እድ ግን የሚመራውና የሚዳኘው መነኩሴዎቹን ብቻ ነው፤ ሁለቱም ንብረ እዶች ነጋሪትና እምቢልታ አላቸው።

ቤተ ክርስቲያኑን የሚያገለግሉ እነዚህ ሰዎች ከሚያገኙት ደህና ገቢ በላይ በየጥዋቱ ከቅዳሴ ሲወጡ ማሕበር የሚሉት የእንጀራና የጠላ ድርጎ አላቸው። ይህ ድርጎ ለሁለቱም ማለት ለደብተራዎቹም ለመነኩሴዎቹም በጋራ የሚሰጥ ሲሆን መነኩሴዎቹ ከዚህ ምግብ በስተቀር ሌላ የሚበሉት አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው። አርብ የጾም ቀን በመሆኑ ከዚህ ዕለት በስተቀር ድርጎው ከቶ አይጓደልም። ደብተራዎቹ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሆነው አይደለም ማሕበሩን የሚበሉት፤ እንዲያውም ባንዳንድ በተወሰነ ቀን ብቻ እንጂ በቤተ ክርስቲያኑ ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ አይገኙም፤ ንብረ እዱም አንዳንድ ጊዜ ባለ ጉዳዮችን ለመስማት እንጂ ሁልጊዜ አይገኝም። ይህ የሚሆንበት ደብተራዎቹ ትዳር ይዘው ከቤተ ክርስቲያኑ ውጪ ስለሚኖሩ ነው። ተራው ምዕመናን ማለት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ለስግደትም ሆነ ለቁርባን በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ለመግባት አይፈቀድላቸውም። ስለዚህ ደብተራዎቹ ማሕበርን በቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ለመጋበዝ የማይፈቅዱበት ሚስቶቻቸው ወደዚያ ለመግባት ስለማይችሉ ወደየቤታቸው ሄደው ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር አብረው መብላትን ስለሚፈልጉ ነው።

ምዕራፍ አርባ፤ የሁለት ቅዱሳን አጽም የሚገኝባቸው በአክሱም አጠገብ በደብር ላይ የተቆረቆሩ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች።

በአክሱም አቅራቢያ አንደኛው በምስራቅ ሌላው በምዕራብ ሆነው የሚነጻጸሩ ሁለት ደብሮች (ተራሮች) አሉ። ዳገታም የሆነው በስተምዕራብ በኩል በሚገኘው ደብር በጫፉ ላይ ከወጡ በኋላ ስፋቱ በግማሽ ሌግዋ የሚገመት በቆጥ የተደገፈ የወይን

ተክል የሚታይበት መልካም መስክ ይገኛል። ከአክሱም ሆኖ ፊትለፊት በሚታየው በደብሩ ክፍል በጥሩ ድንጋይ የተሠራ ነገር ግን አሁን ይበልጡ ክፍል የፈረሰ አንድ ሰገነት አለ። የአክሱም ምዕመናን ቅዳሜና እሁድ ቊርባን ለመቀበል የሚሄዱበት የቅዱስ ሚካኤል ቤት ክርስቲያን የተሠራው ከዚህ ሰገነት ድንጋይ ነው። በስተምስራቅ በኩል ባለው ደብር ላይ የአባ ሊቃኖስ ቤት ክርስቲያን ይገኛል። ቤት ክርስቲያኑ በርሱ ስም የተጠራው የንግሥት ሕንደኬ የኑዛዜ አባት ነበር የሚባለው የጻድቁ አጽም በዚሁ ቤት ክርስቲያን ይገኛል።

ይህን ቤት ክርስቲያን የሚያስተዳድር የአክሱም ጽዮን ቤት ክርስቲያን ስለሆነ የቅዳሴውን አገልግሎት የሚያከናውኑት ካህናት የሚመጡት ከዚያው ነው። የአባ ሊቃኖስ ቤት ክርስቲያንና ቤት በምዕመናን ዘንድ እጅግ የተከበረ በመሆኑ ለማስቀደስና ቊርባን ለመቀበል ብዙ ሰዎች ይመጣሉ። ከደብሩ በስተግርጌ ብዙ ሕዝብ ከትሞ የሚኖርበት የቤት ክርስቲያን ጉልት አለ።

ከዚህ ቤት ክርስቲያን በግምት ሲሶ ሴግዋ ያህል ወደላይ ከፍ ሲሉ በጣም ቀጥ ያለ ወደጫፉም የሚያወጡ ሶስት መቶ ደረጃዎች የተሠሩበት እንድ ቁሊልታ አለ። በቁሊልታው ጫፍ ላይ በጣም የተከበረ የሰቀላ ቤት መልክ ያለው አንድ ቤት ክርስቲያን አለ። በዚሁ ዙርያ ቁመቱ ባንድ ሰው ደረት ልክ የሆነ የካብ አጥር ተሠር ቶአል። ከዚህ ሆኖ ቁልቁል ሲመለከቱ ስለሚያስፈራ ለማየት የሚደፍር ሰው የለም። ከአጥሩ እስከ ቤት ክርስቲያኑ ድረስ ያለውን ስፋት ሶስት ሰዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው በተራ ቢቆሙ ሊሞሉት ይችላሉ። ስለዚህ በቦታ ማነስ ምክንያት ቤት ክርስቲያኑ ታዛ እንኳ በሰፊው አልተሠራለትም።

ቤት ክርስቲያኑ በስሙ የሚታወቀው የአባ ጰንጠሌዎን አጽም በዚሁ ይገኛል። ምንም እንኳ ቤት ክርስቲያኑ አነስተኛ ቢሆንም ገቢው ከፍ ያለ በመሆኑ ሃምሳ ደብተራዎችና እንደ አክሱም ጽዮን የራሱ ንብረ እድ አለው። እንደ አክሱሙ ይህም በኢትዮጵያ ለመጀ

መርያ ጊዜ የክርስትና ሃይማኖት በተሰበከበተ ጊዜ የተቋቋመ ነው። እንደ ብራጋ (ፖርቱጋል) ገዳም ይህም ከድንጋይ የተሠሩ መቃ ብሮች በዙርያው ይገኙበታል።

<u>ምዕራፍ አርባ አንድ፤ የሃሌሉያ ገዳም የሚገኝበት በአክሱም በስተ ምዕራብና በስተሰሜን ስላለው ቦታና በስተምስራቅ በኩል ስለሚገኙ ሌሎች ሁለት ገዳሞች።</u>

ከአክሱም ወደምዕራብ ወይም ወደናይል አግጣጫ በኩል ታላላቅ ግዛቶች አሉ። ንግሥተ ሳባ የምትጠራበት ሳባ የተባለው ቦታ የሚገኘው በዚህ ነበር፤ ወይም ይህ ቦታ የሳባ ክፍል ነበር ይባላል። ለዚሁም ማስረጃ ሊሆን የሚችለው ለንጉሥ ሰሎሞን መቅደስ ማነጫ እንዲሆን ንግሥቲቱ የላከችው ጥቁር እንጨት በዚህ ስለሚገኝ ነው። ይህ ጥሩና ታላቅ ቦታ የንጉሠ ነገሥቱ አማች በሆነ ባንድ ትልቅ መኰንን እየተገዛ ከትግሬ መኰንኑ ግዛት ሥር ተጠቃሎ ይተዳደራል። በስተሰሜን በኩል አራት ሴግዋ ያህል ርቆ የሚገኝ በጣም ተራራማ የሆነ ቶራቱ የተባለ ግዛት አለ። በዚያ ቦታ በሚገኝ ከግርጌ እስከ ጫፉ ግማሽ ሴግዋ ርቀት ባለው በታላላቅ ዛፎች ባሸበረቀ አንድ ረጅም ተራራ ላይ ብዙ ገቢ ያለው ሃሌሉያ የተባለ ገዳም አለ። በአገሩ ውስጥ የክርስትና ሃይማኖት ለመጀመርያ ጊዜ ሲሰበክ የአክሱም ጽዮን ቤት ክርስቲያን ሲሠራ ወዲያውኑ ቀጥሎ የተሠራው ይህ ቤት ክርስቲያን እንደዚህ ያለውን መጠርያ ያገኘበት ምክንያት ቀጥሎ በተመለከተው ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው።

ቤት ክርስቲያኑ እንደተሠራ ምን ዓይነት ቅዳሴ እንደሚደረግ ወይም እንዴት እንደሚጸለይ ካህናቱ አያውቁም ነበር ይባላል። ስለዚህ በዚያው ሆኖ ሌሊቱን በሙሉ ከአምላክ ጋር ይማለል የነበረ አንድ ብጹዕ ሰው መላእክት በአርያም ሃሌሉያ እያሉ ሲዘምሩ አይቻለሁ

ሲል ስለተናገረ ይህንኑ በመከተል ማናቸውም ጸሎት በዚሁ ቃል እንዲጀመር ታዞ ቤተ ክርስቲያኑም ሃሌሉያ ተብሎ ተሰየመ ይባላል። ምንም እንኳ ቦታው በዚያን ጊዜ ያን ሰው የመሰለ ጻድቅ የኖረበት ቢሆንም አሁን ግን የሚኖሩበት ሰዎች በወስላታነታቸው የታወቁ ናቸው።

ይህ ገዳም የተቆረቆረበት ሁለት ወይም ሶስት ሌግዋ ስፋት ያለው ያ ደብር ዙርያውን በደረቅ ወንዞች የተከበበ ነው። በዚያው በቶራቴ ግዛት ውስጥ በሚገኝ ባንድ ሌላ ተራራ ላይ ከሃሌሉያ አነስ የሚል አንድ ሌላ ገዳም አለ። በውስጡ የሚኖሩ መነኩሴዎች በጣም መልካም ሰዎች ስለሆኑ እነዚያን ወስላቶቹን እይወዱዋቸውም ይባላል ። በመንገዳችን ላይ ከአክሱም ሶስት ሌግዋ ያህል እልፍ ሲሉ በአንድ ሌላ ተራራ ላይ የቅዱስ ዮሐንስ ገዳም ይገኛል።

ከዚያ ሁለት ሌግዋ ያህል እልፍ ሲሉ የአባ ገሪማ ገዳም አለ። አባ ገሪማ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በጸሎትና በቅድስና ኖሮ ከመሞቱ በፊት የግሪክ ንጉሥ ነበር ይባላል። ከመቃብሩ በስተኋላ በኩል የሚገኝ ለመማለያ የሚመች ዋሻ ውስጥ ሁልጊዜ ይጸልይ ነበር፤ የሞተውም በዚያው ነው ይላሉ። አባ ገሪማ ብዙ ተአምራት ያሳያል ይባላል፤ ስለዚህ በዓሉ በሚከበርበት ቀን ከገዳሙ ድረስ ሄደን ከሶስት ሺ በላይ የሚገመቱ ዕውራንና ለምጻሞች ልዩ ልዩ ድውይ ያለባቸውም ሰዎች በዚያው ተሰብስበው አየናቸው። ገዳሙ የተቆረቆረው በሶስት ተራራዎች መካከል ባንድ ቁልቁለት ምድር ላይ ነው፤ ጻድቁ የጸለየበት ዋሻ ተንዶ ሊወድቅ ደርሶአል። ወደዚያ ዋሻ በመሰላል ይወርዱና አሸዋና ጠጠር ድብልቅ የሚመስል አፈር ወይም ለስላሳ ድንጋይ አውጥተው በድውያኑ አንገት ላይ ያኖሩባቸዋል። (በዚህ አኳኋን ተፈወስን የሚሉ አንዳንድ ድውያን አሉ።) የዚህ ገዳም ገቢ የቱን ያህል መሆኑን ጠይቄ በዓመት አስራ ስድስት ፈረስና ከዚሁም በላይ ለመነኩሴዎቹ ሕዝቡ ምግብ የሚሰጥ መሆኑን ገለጹልኝ። ገዳሙ ትንሽ በመሆኑ እንዲሁም የመነኩሴዎቹ ቁጥርና ገቢውም ጥቂት በመሆኑ ለመተዳደርያቸው ማገገ እንዲሆን

ከቦታው በስተግርጌ በኩል ብዙ ሽንኩርትና ወይን እየተከሉ ዘቢብ ያዘጋጃሉ። ወይኑ በጥር ወር ይደርስና በመጋቢት ወር ያልቃል።

ምዕራፍ አርባ ሁለት፤ ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንና መንደር ወጥተን አምባ ሰናይት ወደተባለ ቦታ ሄድን፤ ከዚያም ወደማሉሽ ቀጠልን፤ ያሉትን ገዳሞች ጎበኘን።

ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተነሥተን ዕቃችን በተሸከሙልን ያገሩ ሰዎች እየተመራን ስንጓዝ ከዋልን በኋላ አንገባ[1] በተባለ ከተማ ስንደርስ መሽቶብን ባንድ ቤተንጉሥ ውስጥ ገብተን አደርን። ከዚህ በፊትም በየመንገዳችን በሚገኙ መሰል ቤቶች ውስጥ እየገባን አድረናል። ቤተንጉሦቹን የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴዎች የሆኑ መሳፍንት አንዳንድ ጊዜ ያርፉባቸዋል እንጂ ለማንም ክፍት አይደሉም። መሳፍንቱ ከሌሉ በነዚህ ቤቶች ውስጥ መግባት ለማንም አይፈቀድም። በራቸው ሁልጊዜ ክፍት ሆኖ አልጋ ተነጥፎ ምድጃ ተዘጋጅቶ ይጠብቃል። ዕቃችንን አሸክመን ከዚያ ቦታ ሶስት ወይም አራት ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ አምባ ሰናይት የሚባል ትልቅ ወንዝ ባጠገቡ በሚገኝበት ባንድ ኮረብታ ላይ አደርን። የግዛቱም ስም አምባሰናይት ይባላል። የዚህ ቦታ ገዥ የንጉሠ ነገሥቱ ሴት አያት ናት ይባላል። ሴትዮዋ ለግዛቱ አትስማማም ተብሎ ማዕርጓ በተወሰደባት ጊዜ እኛ በዚያ ነበርን። አምባሰናይት በትግሬ መኮንኑ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ብዙ ሕዝብ የሚገኝበት ወንዞችና ተራሮችም ያሉበት ለምለም ቦታ ነው። ከሕዝቡ ላይ ማናቸውንም ነገር እየነጠቁ የሚወስዱትን ወንበዴዎች በመፍራት ቤቶቹ የተሠሩት በየተራራው ጫፍ ከመንገድ ወጣ ባሉ ቦታዎች ነው። አውሬ እንዳይተናኮለን በማለት መሪዎቻችን በኛና በከብቶቻችን ዙርያ የእሾህ አጥር አጠሩልን፤ ነገር ግን ምንም ሳንሰማ ወይም ሳናይ አደርን። ከአምባሰናይት ተነሥተን በግምት ሁለት ሌግዋ ያህል በመጓዝ ማሉሽ

በተባለ ከተማ አደርን። በማሎሽ አካባቢ ከዚህ በፊት ካየናቸው ሁሉ እጅግ የሚያምሩ የስንዴና የገብስ የበቆሎ እርሻዎች አየን።

በዚህ ከተማ አጠገብ ምንም ዓይነት እጽዋት ያልበቀለበት ግድግዳ የሚመስል ስፋቱ ከላይ እስከ ታች አንድ የሆነ ቀጥ ብሎ የቆመ ተራራ አለ። ይህ ተራራ በሶስት ቁሊልታዎች ይከፈልና ከነዚሁ ሁለቱ ጫፋቸው በጣም ሹል ሲሆን የመካከለኛው ግን ደራ ያለ ነው። ከሹሎቹ ባንደኛው ላይ አባ ማታ የተባለ በእመቤታችን ስም የሚጠራ ገዳም አለ። በገዳሙ የሚኖሩት ሰዎች እውነተኛውን የምንኩስና ኑሮ የሚኖሩ ናቸው ይባላል። በመላ ኢትዮጵያ የካህርት ማህበር አንድ ነው። ሁሉም የቅዱስ እንጦንዮስ ማህበር ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ እስጢፋኖስ የተባለ አንድ ማህበር አለ። የመጀመርያዎቹ በመካከለቸው የሚገኙትን መስቀልን የማያከብሩትን ከሃድያንን ያቃጥላሉ ሲሉ የመጨረሻዎቹ የጠልዋቸዋል። ካህናቱ ሁሉ በእጃቸው የሚይዙትን ተራውም ሕዝብ በአንገቱ የሚያንጠለጥለውን መስቀል የሚጠርቡት እነዚህ ከሃድያን የሚሉዋቸው መነኩሴዎች ናቸው፤ መስቀልን የማይስሙበት ወይም የማይሰግዱበት ምክያት ክብርና ስግደት የሚገባው ያ የሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ብቻ እንጂ ሌሎቹ መስቀሎች ግን ሰው የሠራቸው ምሳሌ ነገሮች ስለሆኑ ሊሰገድላቸው አይገባም የማለት አስተያየት ስላላቸው ነው። ከዚህም ሌላ ልዩ ልዩ ከንቱ እምነት አላቸው።

ገዳሙ የነበረበት ቦታ ርቀቱ በግምት አንድ ሌግዋ ያህል ብቻ ስለሚመስል ወደዚያ ልሄድ አሰቤ መንገድ ብጠይቅ ምንም እንኳ ቅርብ መስሎ ቢታይም የአንድ ቀን መንገድ የሚፈጅ ዳገታም በመሆኑ በእጅ ምናምን እየያዙ በጥንቃቄ መሄድ ያስፈልጋል ስላሉኝ ሳልሄድ ቀረሁ።

በመካከል በሚገኘው የጠረጴዛ መልክ ባላው ቁሊልታ ላይ በያመቱ ለንግሥ ብዙ ሰዎች የሚሄዱበት የእመቤታችን ቤተ ክርስ ቲያን አለ። ከዚህ አንድ ተኩል ወይም ሁለት ሌግዋ ርቆ ባለው በሌላው ቁሊልታ ላይ የቅድስት መስቀል ቤት ይገኛል።

የአባ ማታ ገዳም ያለበትን ቁሊልታ በሚመስል በሌላ ላይ የአባ ዮሐንስ ገዳም አለ። ይህ ቦታ ከገዳሙና ከመነኩሴዎቹ መኖርያ በስተቀር ሌላ ምንም ቤት አይገኝበትም። እጽዋትም የሌለበት ደረቅ ቦታ ነው። የገዳሙ አገልጋዮች የሚኖሩት በስተግሮጌ በሚገኝ ባንድ ለምለም ቦታ ነው። ስለዚህ የሚያስፈልገውን ምግብና ማናቸ ውንም ነገር በላይ ለሚኖሩት ሰዎች ከዚያ ይልኩላቸዋል። ወደኋላ ትተነው በመጣነው ምድርና በዚህ መካከል ብዙ ልዩነት እናይ ጀመር።

በባሕር ነጋሹና በትግሬ መኮንኑ ግዛቶች ድንበር ላይ ድውያንና ዓይነሥውሮች ለማኞችም በብዛት ሲገኙ በዚህ ቦት ግን እምብዛም የሉም። ወንዶቹ የመለያ ልብስ ይለብሳሉ፤ ያገቡ ወይም ከወንዶች ጋር የሚኖሩ ሴቶች ባለጠርዝ የጥቁር ሱፍ ቀሚስ ይለብሳሉ፤ እንደ ባሕር ነጋሹ ግዛት ሴቶች በራሳቸው ላይ ጌጥ አያደርጉም። በሃያና በሃያ አምስት ዓመት ዕድሜ መካከል የሆኑት ልጃገረዶች ከወገባቸው በታች አሽርጠው ጌጣጌጥ አንጠልጥለው ሰውነታቸውን ገልጸው ራቁታቸውን ይሄዳሉ። በዕድሜአቸውና በቁመታቸው ከፍ ያሉት አንዳንዶቹ ደግሞ በአንገታቸው ዙርያ የበግ ለምድ ሽብ አድርገው ከላይ እስከ ታች ሰውነታቸውን በአንድ በኩል ሸፍነው በሌላው በኩል እርቃናቸውን ይሄዳሉ። በፖርቱጋልና በእስፓኝ ወንዶች የሚያገቡት ሴቲቱ መልኳ ደስ የሚያሰኝ የሆነ እንደሆነ ወይም የሚወዱዋት ሲሆን ነው፤ በዚህ አገር ግን ከመልኳና ፍቅርዋ ሌላ አካላትዋን በማየት ጭምር ሊሆን ይችላል።

ምዕራፍ አርባ ሶስት፤ በዚህ ቀበሌ ስለሚገኙት የዱር አራዊት፤ አምባሳደራችን ወደነበረበት ቦታ ወደኋላ ስለመመለሳችን።

በዚህ ቦታ በሌሊት በበረትና በግርግም እየገቡ ከብቶችንና አህዮችን የሚበሉ ነብርና ሌሎችም የዱር አራዊት በብዛት ይገኛሉ፤ በባሕርነጋሹ አገር ግን ይህን ያህል አይተናኩሉም። በትግሬ መኮንኑ

ግዛት አምባሳደሩ ወደሚገኝበት ቦታ ለመሄድ ነሃሴ ስድስት ቀን 1520 ዓም ተነሣን። በባሕር ነጋሹ ግዛት በሚገኝ ቴሚይ ከሚባል ቦታ አስከትሎአቸው ከሄደው ፖርቱጊዞች ጋር ሆኖ በዚያ ከተማ በደስታ አርፎ ይቀመጥ ነበር። በትግሬ መኮንኑ ልዩ ትዕዛዝ የአምባሳደሩ ባልደረባ ሆኖ ጸጥታውን የሚጠብቅለትና የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የሚያሰጥ በዚያ ቦታ አንድ ትልቅ መኮንን ነበር። ሌሎችም ብዙ ታላላቅ ሰዎችና የትግሬ መኮንኑ ጭፍሮች ባካባቢው ይገኙ ነበር። አምባሳደሩ ትግሬ መኮንኑ ከሚኖርበት ቤተንጉሥ አንድ ሌግዋ ርቆ በሚገኝ ቦታ ነበር ያረፈው።

እኛ በዚያ ቦታ በደረስንበት ቀን ትግሬ መኮንኑ አምባሳደሩን አስጠርቶ እኛም ከርሱ ጋር ሆነን ወደ ቤተንጉሡ ሄድን። በቤተ ንጉሡ እንደደረስን ከነባለቤቱ ቁርባን ለመቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዱን ገለጸልን፤ ጊዜው የጾም ወራት ስለነበር ቅዳሴ የሚገቡበት ሰዓት ጸሐይ ከመጥለቁ አንድ ሰዓት በፊት ነበር። እኛም ከርሱ ጋር ለመገናኘት አስበን የቤተ ክርስቲያኑን መንገድ ይዘን ስንሄድ በበቅሎ ተቀምጦ ብዙ መኳንንትና ጭፍሮች በበቅሎና በእግር ሆነው አጅበውት ሲመጣ በመንገድ አገኘነው።

ትግሬ መኮንኑ መልካምና በጣም የተከበረ ሽማግሌ ነው። ባለቤቱ ፊትዋንና ሰውነትዋን በሙሉ በሰማያዊ ጨርቅ ሸፍና በበቅሎ ላይ ተቀምጣ ትሄድ ስለነበር ፊትዋን አላየነውም። ባጠገባችን እንደደረሰ እኔ በእጄ መስቀል መያዜን አይቶ እንዳሳልመው ጠይቆኝ እርሱ ከተሳለመ በኋላ ባለቤቱም እንደተሸፈነች እንድት ሳለም አዘዘ። ከዚህ በኋላ ሁላችንንም በታላቅ ክብር ተቀበለን።

የትግሬ መኮንኑ ቤት በጣም ትልቅና ብዙ አሽከሮችና ገረዶች ጭፍሮችም የሚገኙበት በጣም የተከበረ ከባሕር ነጋሹ ቤት የሚበልጥ ነው። ይህ ሰው ስንቅና ማናቸውንም የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ከመስጠቱ በላይ ለኛ ሰዎች ልዩ ክብርና መስተናግዶ ያደረገላቸው መሆኑን አምባሳደሩና አብረውት የነበሩት ፖርቱጊዞቻ ሁሉ ነገሩን።

ትግሬ መኮንኑ ይህን ሥልጣን የተቀበለው ከቅርብ ጊዜ በፊት ስለነበር ከበታቹ የሚተዳደሩትን ልዩ ልዩ ሹማምንትና የንጉሥነት ማዕርግ ያላቸው መሳፍንት የሚገዙዋቸውን አውራጃዎች ሁሉ ገና ጎብኝቶ አልጨረሰም ነበር። ማናቸውንም ጠቅላይ ገዥና ከበታቹ ያሉትን ገዥዎች ሁሉ በምክንያት ወይም ያለምክንያት እንዳሰኘው የሚሾምና የሚሽር ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ነው። ስለዚህ ገዥዎቹ ይህን በመሰለው ንጉሣዊ ውሳኔ ቅር ቢሰኙም ቅሬታቸውን የሚገልጹት በምስጢር ነው። እዚያ በነበርንበት ጊዜ ብዙ ሹማምንት ተሽረው በቦታቸው አዲስ ባለሥልጣኖች ተሹመው ሁለቱም በወዳጅነት ሲኖሩ አይተናል (የልባቸውን ግን እግዚብሔር የወቅ)። የዚህ ቦታ ነዋሪዎች የሚደርስባቸውንና የሚደርስላቸውን ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሆነ ነው ሲሉ ይቀበሉታል።

በትግሬ መኮንኑ ግዛት የሚገኙ መሳፍንት ሁሉ ለንጉሠ ነገሥቱ በያመቱ ግብር በፈረስ፤ በባሕር ነጋሹ ያሉት ደግሞ በወርቀዘቦ በሐርና በጥጥ ጨርቅ ይከፍላሉ። ከትግሬ ግዛት ጀምሮ ወደመካከል ኢትዮጵያ የሚገኙት በወርቅና በሐር በበቅሎና በፍሪዳ በጥምድ በሮች በሌሎችም ሃብቶች ግብር ይከፍላሉ ይባላል። ከመሳፍንቱ በታች ያሉት ታናናሾቹ ሹማምንት ምንም እንኳ የተሾሙት በንጉሠ ነገሥቱ ቢሆንም ድርሻቸውን ለመሳፍንቱ ይገብሩና እነዚህ አጠቃለው ለንጉሠ ነገሥቱ ይከፍላሉ። አገሩ ብዙ ሕዝብ የሚኖርበት ስለሆነ ከግብር የሚገኘው ጥቅም ከፍ ያለ መሆኑ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ምንም እንኳ ጥቅሙ ከፍ ያለ ቢሆንም ተጠቃሚዎቹ ይህን የሚያገኙት ድሃውን ሕዝብ እያሰቃዩ መሆኑ አይካድም።

ምዕራፍ አርባ አራት፤ አምባሳደሩ ትግሬ መኮንኑን በመንገድ አግኝቶት ለመሄድ ስንብት ጠየቀው፤ ስንቅና ሌላም አስፈላጊ እርዳታ ተደርጎልን መንገዳችንን ቀጥለን መነኩሴዎች ለእግዚአብሔር ምስጋና ሲያቀርቡበት በነበር ባንድ ገዳም ደረስን።

ትግሬ መኮንኑ ወደሌላ አገር ሲሄድ በመንገድ አግኝተነው ስንሰናበተው አጋሰስ እንዲያዝልን ብንጠይቀው ለንጉሠ ነገሥቱ የያዛችሁትን ዕቃ እኔ አሸከምላችኋለሁ፤ የናንተን ጓዝ ግን ራሳችሁ ማሸከም አለባችሁ ብሎን ተሰነባብተን ተለያየን።

የኛ ጓዝ ከባድ ሸክም ስለነበር ተሸካሚ እንዲታዘዝልን ለመለመን ለሁለተኛ ጊዜ በትግሬ መኮንኑ ፊት ለመቅረብ አሰበን ጊዮርጊስ ዲ አብሬውንና መምሕር ዮሐንስን በወርቅ ያጌጠ አንድ ሳንጃና የከፈይ አፎት የነበረው አንድ ባለ ወርቅ ጫሚ ጎራዴ ገጸ በረከት አስይዘን ላክናቸው። ትግሬ መኮንኑም መልካም ፈቃዱ ሆኖ የአገሩ ሕዝብ ዕቃችንን እንዲሸከምልንና በደረስንበትም ቦታ ሁሉ መብልና መጠጥ ሥጋም እንዲሰጠን ትእዛዝ ሰጠልን። ይህ ትእዛዝ እንደደረሰን የዚያኑ ዕለት ማለት ነሃሴ ዘጠኝ ቀን መንገዳችንን ቀጠልን።

ቀኑን ስንጓዝ ውለን ሲመሽ ከዚህ በፊት ያየናቸውን የሚመስሉ ነብርን በመፍራት በታጠሩ መንደሮች ውስጥ ገብተን አደርን። የዚያን ዕለት ከምሽቱ በግምት ሁለት ሰዓት ሲሆን ሁለት ሰዎች በመንገድ ሲሄዱ ነብር አግኝቶአቸው አንደኛውን እግሩን ክፉኛ አቆሰለው፤ ያ ሰው ዕድለኛ ስለነበር እኛን እግዚአብሔር ስላዘዘለት በቶሎ ደርሰን ባናስጥለው ኖሮ ይህ ክፉ አውሬ አያስተ ርፈውም ነበር።

በዚያ ቦታ ከክርስቲያኖች መንደሮች አጠገብ የተሠሩ የእስላሞች መንደሮች አይተናል፤ በነዚህ መንደሮች የሚገኙ እስላሞች ሁሉ ለክርስቲያኑ ባለ እርስቶች በወርቅና በሐር ግብር ይከፍላሉ ይባላል። እንደ ክርስቲያኑ ልዩ ልዩ ዓይነት ሥራ አይሠሩም፤ መስጊድ እንዲሠሩም አይፈቀድላቸውም።

በዚያ አካባቢ የሚገኝ ምድር በፊት እንዳየነው ብዙ ሣር የሚገኝበት እርሻና ተራራም በብዛት የሚታይበት ነው፤ ተራሮቹ ግን እንደበፊተኞቹ ታላላቅ አይደሉም። ከነዚህ ታናናሽ መንደሮች ተነሥተን አራት ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ ባንድ ትንሽ መንደር ደርሰን በዚያው አደርን። በመንገዳችን ላይ በስተግራ በኩል ብዙ ዛፎችና ሣር ባለበት ባንድ ተራራ ጫፍ አንድ ገዳም አይተናል። ያ ገዳም በቅዱስ ዮሐንስ ስም የሚጠራ መሆኑንና በውስጡም ብዙ መነኩሴዎች የሚኖሩበት የተከበር መሆኑን ነገሩን። ባደርንበት መንደር አጠገብ የሕንፃው ሥራ የኛን አገር ቤተ ክርስቲያኖች የሚመስል ቅስት ጣርያ ያለው ማለፍያ ሆነው በተሳሉ በሐዋርያት፤ በአበውና በነቢያት በኤልያስና በሄኖክ ስዕሎች ያጌጠ አንድ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አለ። ቤተ ክርስቲያኑን የሚያገለግሉት አስር ቄሶችና መነኩሴዎች ናቸው።

መነኩሴዎቹ የማይገኙበት ቤተ ክርስቲያን ወይም ቄሶች የማይገኙበት ገዳም እስካሁን ድረስ አላጋጠመንም። ካህናቱ ምንም እንኳ በጣም የተከበሩ ቢሆኑም ባለባበሳቸው እንደመነኩሴዎቹ ሳይጠነቀቁ እንደ ተራው ሕዝብ ለብሰው የሚሄዱ ናቸው። በገበያ ቀን ግን መነኩሴዎቹም ሆኑ ካህናቱ ከገበያተኛው ጋር ተቀላቅለው ሲገዙና ሲሸጡ ይታያሉ።

ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በስተ ምስራቅ በኩል አንድ ሌግዋ ርቆ በሚገኝ ባንድ ተራራ አጠገብ ባንድ ወንዝ ዳር የተሠራ ሃያ ወይም ሃያ አምስት መነኩሴዎች የሚገኙበት ጰራቅሊጦስ የተባለ ገዳም አለ። ገዳሙም መነኩሴዎቹም በብጽእና የተሞሉ ይመስላሉ። እኛን ባዩን ጊዜ ከዚያ በፊት የማያውቁትን ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ከሌላ አገር የመጡ ክርስቲያንን ላሳያቸው አምላክ ምስጋና ከማቅረባቸው በላይ እኛን ተቀብለው ገዳሙንና ንብረታቸውን ሁሉ አስጎበኙን።

የገዳሙ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ ትንሽ ቢሆንም ጣርያው በቅስት የተሠራና በሚያምሩ ስዕሎች ያሸበረቀ ማህሌቱና መና።

ዠዎቹም ማለፊያ ሆነው የተሠሩ ከዚህ በፊት ካየናቸው ሕንፃዎች ሁሉ በይበልጥ የሚያምር ነው። በዚህ ቦታ ከሚገኙት የሚያምሩና በምቹ ካደጉ አትክልት ውስጥ ለምሳሌ ኀመን፤ ነጭ ሽንኩርት፤ ቀይ ሽንኩርት፤ ልዩ ልዩ ቅጠላቅጠል ምግቦች፤ እንዲሁም ሎሚ፤ ትርንጎ፤ ኮክ፤ ወይን፤ በለስና ሌሎችም ልዩ ልዩ ፍራፍሬና ዛፎችም ይገኛሉ።

ቀኑ ቅዳሜ ስለነበር በነርሱ ልምድ ምንም ነገር እንዳይሠራና ፍሬም እንዳይቆረጥ ስለሚከለከል ይህንኑ ምክንያት በማድረግ ከአታ ክልቱ ፍሬ ወስደን ልንጋብዛችሁ ስላልቻልን ይቅርታ አድርጉልን ሲሉ ጉዳዩን ገልጸውልን ወደቤታቸው ከተመለስን በኋላ ደረቅ ነጭ ሽንኩርትና ሎሚ ሰጡን። በመጨረሻም ወደ ግብር ቤታቸው ወስደውን ተቀቅሎ ያደረ ነጭ ሽንኩርት ጣል ጣል ተደርጎ ጨው የገባበት ኀመናን ሁለት እንጀራ (አንዱ የስንዴ ሌላው የገብስ) አንድ ገምቦ ጠላም አቀረቡልን፤ እነዚህ መነኩሴዎች ያን ምግብ ያቀረቡልን በጎ ፈቃድ በተመላ መንፈስ ስለነበር እነርሱ እንዳደረጉት ሁሉ ለአምላክ ምስጋ አቅርበን የተሰጠንን ተቀበልን።

ካረፍንበት ቦታ ሁለት ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ብዙ ጊዜ የተስተናገድንበት የትግሬ መኮንኑ ቤተ ንጉሥ በሚገኝበት ወቅሮ በተባለ ቦታ ላይ ጣራና ግድግዳው ምሰሶውም ካንድ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ባለ ሶስት ቅስት የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን አለ። መቅደሱና መሰውያው ዋናው በርና ምሰሶዎቹም ካንድ ቋጥኝ ተፈልፍለው የተሠሩ ናቸው፤ ለየብቻቸው ተጠርበው በተጋጠሙ ድንጋዮች እንኳ ቢሠሩ ኖሮ ይህን ያህል ሊያምሩ አይችሉም ነበር። ውበቱና በውስጡም ሆነው ሲነጋገሩ ወይም ሲዘምሩ ድምጽን በማስተጋባት የሚደርሰውን የዜማ ቃና መስማት በእውነተኛው ልብን የሚማርክ ነው።

በዚህ ቤተ ክርስቲያን ማናቸውም ነገር ለምሳሌ ነጋሪት፤ ከበሮና ሌሎችም መሰል ዕቃዎች ሁሉ ከድንጋይ የተሠሩ መሆን ስላለባቸው ደወል የለም።

ምዕራፍ አርባ አምስት፤ አጉላና ብለት ወደተባሉ ቦታዎች ሄድን፤ ባልጋዳ ሮቤል የተባለ ሰው ሊጎበኘን ስለመምጣቱ፤ በዚህ አገር ስለሚገኝ ጨው።

በጠቀስነው ቦታ ቅዳሜና እሁድን ከዋልን በኋላ ነሃሴ 13 ቀን ጉዞአችንን ቀጠልን፤ የዚያኑ ዕለት አጉላ በተባለ ከተማ ደረስን። በዚህ ከተማ ጣርያው በጥርብ ድንጋይ ምሰሶ የተደገፈ እጅግ ያማረ የቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ከተማው ሰንድ ወንዝ ዳር የተሠራ የደስ ደስ ያለው ነው። በቅሎ የተቀመጡ ሰዎች እንጂ ፈረሰኞች በዚያ እንዳይገቡ የሚከለክል ከተማው ልዩ መብት አለው። ከዚያ ቦታ ተነሥተን ከተጓዝን በኋላ በመንገዳችን ላይ በነበሩ ቆሻሻ መንደሮች ደርሰን እራት ሳንበላ በዚያው ተጣበን አደርን።

በማግሥቱ ጥዋት ከዚያ ተነሥተን የትግሬ መኮንኑ ቤተ ንጉሥ በነበረበት ብለት በተባለ ቦታ አደርን። በዚያ እንዳረፍን አንድ ትልቅ መኮንን ሊጎበኘን መጣ፤ ይህ ሰው ስሙ ሮቤል የግዛቱም ስም ባልጋዳ ሲሆን በተለምዶ ባልጋዳ ሮቤል በሚያሰኝ መጠርያ ይታወቃል[1]። ባለ በቅሎዎች ፈረሰኞችና ነጋሪት መችዎችም ይህን መኮንን አጅበውት ነበር። ከዚህ በፊት እንደገለጽነው ትግሬ መኮንኑ ከሌለ በቤተ ንጉሡ ውስጥ ማንም ሰው እንዳይገባ በጥብቅ በመከልከሉ ሕጉን ጥሶ የገባውን ሰው በንጉሡ ነገሥቱ ስም አገሩን የሚገዛው ትግሬ መኮንነ ይሙት በቃ ሊፈርድበት ስለሚችል ይህንኑ በመፍራት መኮንኑ ከቤተ ንጉሡ አጥር በር ሲደርስ መልእክተኛ ወደ አምባሳደሩ ላከበት። አምባሳደሩም መልእክተኛውን ተቀብሎ እኔ አምስት ሺ ሌግዋ አቋርጩ የመጣሁ ሰው ስለሆንሁ ክቡርነትዎ ሊያገኙኝ ከፈለገ ወደቤት ሊገባ ይችላል እንጂ እኔ ከክፍሌ ወደውጭ ልወጣ አልችልም ሲል መልእክተኛውን መለሰው። ወዲያውኑ አንድ ቶፋ ነጭ ማርና አንድ ፍሪዳ ልኮ የአምባሳደሩን መምጣት በመስማት ለመተዋወቅ ሲል እዚያ ድረስ መምጣቱንና በቤተ ንጉሡም የውጭ አገር ክርስቲያኖች ስላሉ በነርሱ ምክንያት ወደውስጥ ቢገባ ምንም ቅጣት የማይደርስበት መሆኑን በመረዳት ሊገባ ዝግጁ መሆኑን ገለጸ፤

በደጃፉ ሲደርስ ከባድ ዝናም ስለጣለ ወደውስጥ ገብቶ ከአምባሳደሩና ከኛም ጋር ስፊ ንግግር ጀምሮ ስለኑሮአችን፤ ስለ ክርስትና ሃይማኖት አገሮችና ስለኛም አገር ጠየቀን። እርሱም የበኩሉን ታሪክ ማውራት ጀምሮ ከእስላሞች ጋር ስላደረገው ጦርነትና በባሕር ጠረፍ ያለው የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት እንዴት በነርሱ እንደተወሰደ እርሱም በበኩሉ አርበኝነቱን ያላቋረጠ መሆኑን ነገረን። ባንዲት መልካም በቅሎ አንድ ጎራዴ ለወጠ፤ አምባሳደሩም አንድ የጦር መመከቻ ባርኔጣ ሸለመው።

ከንጉሠ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት ከደረስን በኋላ ይህን መኮንን ደጋግመን በዚያ ያየነው ከመሆናችን በላይ በጉበዝናውና በጀብድ ተግባሩ እጅግ የታወቀ ሰው መሆኑን በዚያው የነበሩ ሰዎች አረጋገጡልን። እርሱ የሚገዛው ይህ ትልቅ አውራጃ እኛ የመጣንበትን መንገድ ይዞ ወደደቡብ የሚገኝ ነው። በስተ ምስራቅ በኩል በቀይ ባሕር ሲደርስ ሌላው ክፍል ደግሞ የተጓዝንበትን ጎዳና ይነካል።

በኢትዮጵያ እጅግ የተወደደው የመገበያያ ገንዘብ በእስላሞችና በአሕዛብ አውራጃዎች እንዲያውም እንደሚወራው እስከ ሜኒኮንጎ ድረስ የሚሠራበት የአሞሌ ጨው ማዕድን በዚያ መኮንን ግዛት ውስጥ ይገኛል። አሞሌው እየተፈለጠ ቁመቱ አንድ ስንዝር ተኩል፤ ጎኑ የአራት ጣት ስፋት፤ ግርጌው የሶስት ጣት ስፋት ሆኖ በግንብ መሥሪያ ሸክላ መልክ የተጠረበ በአጭሩ እንደተጎራረደ እንጨት በደንብ ታስሮ በአጋሰስ ይጫናል።[2]

በማዕድኑ አጠገብ መቶ ሃያ ወይም መቶ ሰላሳ አሞሌ አንድ ድራክም ያወጣል፤ አንድ ድራክም ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት የሶስት መቶ ሪያይሽ እኩያ ነው። ከማዕድኑ የአንድ ቀን መንገድ ርቆ በሚገኝ አዲ ቆርቆራ በተባለ ከተማ ገበያ ያንድ ድራክም ዋጋ ከበፊቱ አምስት ወይም ስድስት አሞሌ ይነቀሳል፤ ስለዚህ ከማዕድኑ እየራቁ ወደ መካከል አገር እየገቡ ሲሄዱ የአሞሌው ግምት ከፍ እያለ ይሄድና በቤተ መንግሥቱ ሲደርስ ያንድ ድራክም ዋጋ ስድስት

ወይም ሰባት አሞሌ ብቻ ይሆናል። በክረምቱ ወራት አንድ ድራክም በአምስት አሞሌ ብቻ ሲመነዘር እኔ ራሴ አይቻለሁ። ስለዚህ በመንገዱ ርቀት ምክንያት አሞሌው በሚወጣበት ቦታ ሲረክስ በቤተ መንግሥቱ አጠገብ ሲደርስ ውድ ይሆናል። ይህም ሊሆን የሚችልበት ካንድ ቦታ ወደ ሌላው ማዘዋወሩ ቀላል ባለመሆኑ ነው።

ዳሞት[3] በተባለ ቦታ ሲደርሱ በሶስት ወይም በአራት አሞሌ አንድ ደህና ባርያ ለመግዛት ይቻላል ይባላል፤ እንዲያውም በባሮች አገር ከገቡ በአንድ አሞሌ አንድ ባርያ ደግሞም ባንድ አሞሌ ክብደት ላይ ጥቂት ጨምሮ የዚያኑ ክብደት እኩያ ወርቅ ለማግኘት ይቻላል ይባላል።

ሶስት ወይም አራት መቶ የሚሆኑ አጋሰሶች አሞሌ ተጭነው ባንድነት ሲሄዱ ሌሎችም ለማምጣት ሌጣቸውን ሲሄዱ በመንገድ እናይ ነበር። እነዚህ የአጋሰሶች ጭነቶች መኳንንቱ በያመቱ በቤተ መንግሥቱ በደጅ ጥናታቸው ጊዜ የሚተዳደሩባቸው ናቸው ይባላል። ባንዳንድ ቦታ ሃያ ወይም ሰላሳ አጋሰሶች የሚነዱ ሰዎች ይገኛሉ፤ ባንዳንድ ቦታም ወደድ ወደሚልበት ቦታ ወስዶ ትርፍ አግኝቶ በለውጥ የሚየሻውን ሁሉ ለማግኘት ሰዎች አሞሌውን በጭን ቅላታቸው ተሸክመው ረጅም መንገድ ሲሄዱ ይታዩ ነበር።

ምዕራፍ አርባ ስድስት፤ ዕቃችንን አስቀድመን ጉዞአችንን ቀጠልን፤ የትግሬ መኮንኑን ባለ ሥልጣን እኛን ፍለጋ የመጣ አንድ መነኩሴ መታው።

ከዚህ ቤተ ንጉሥ ተነሥተን ስንጓዝ ከዋልን በኋላ በናቤል[1] በተባላ ተራራ በነበሩ መንደሮች ደርሰን በዚያው አደርን። በማግሥቱም ስንጓዝ ውለን ሲመሽ በፊታችን የነበሩ ጓዛችንን የያዙልን ሰዎች ብዙ ውኃ ይገኝበት በነበረ ባንድ መስክ መካከል አርፈው

አገኘናቸው። ዕቃችን በንደዚህ ያለ ሁኔታ በሜዳ ላይ ሆኖ ስናየው በጣም አዘንን፤ በዚያ እርፈን እንደነበርን አራት ወይም አምስት የሚሆኑ ሰዎች በበቅሎ፤ አስር ወይም አስራ ሁለት የሚሆኑ ሌሎች ሰዎች ደግሞ በእግራቸው በተባለው ቦታ ደረሱ፤ ከነዚህም ውስጥ አንድ መነኩሴ ነበር። ይህ መነኩሴ በዚያ እንደደረሰ ዕቃችንን አሸክሞ ይመራን የነበረውን የትግሬ መኮንኑን ባለ ሥልጣን ተንደ ርድሮ ሲመታው በማየት ለመገላገልና ምክንያቱንም ለማጣራት ሁላችንም ሮጠን ሄድን። የተመታው ሰው መድማቱን በማየት አምባሳደሩ መነኩሴውን በደረቱ ላይ ጨቡዶ ሊመታው ነበር፤ እንዲያውም ሳይመታው አልቀረም። እኔና ከአምባሳደሩ ጋር የመጡት ሌሎቹ ሰዎች መሣርያችንን አዘጋጅተን በመነኩሴው ደረት ላይ ደገንንበት። ነገር ግን ኢጣሊያንኛ ጥቂት ያውቅ ስለነበር ይህንኑ ቋንቋ በመጠኑ ያስተውል ከነበረው ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር ባይነጋገርና እኔም በራሱ ላይ የነበረውን ቆብ በማየት መነኩሴ መሆኑን ባላረጋግጥለት ኖሮ ያች ቀን የሕይወቱ መጨረሻ ትሆን ነበር።

ሁለቱን ሰዎች አስማምተን እርቅ ከወረደ በኋላ መነኩሴው ይህን ያደረገበትን ምክንያት በመግለጽ ከንጉሡ ነገሥቱ ዘንድ ተልኮ ዕቃችንን ሊያስወስድልን የመጣ መሆኑንና የትግሬ መኮንኑ ባለሥልጣን ባደረገው ተግባር ከመገረሙ ይልቅ ለኛ የሚገባው እርዳታ ስላልተደረገልን የተቆጣ መሆኑን አስረዳን። ይሁን እንጂ በዚያ ሕገ ወጥ ተግባር አምባሳደሩ በፍጹም ቅር ተሰኝቶ ስለነበር፤ ያ በትር በሰውዬው ላይ ሳይሆን በኔ ላይ እንደተሰነዘረ አድርጌ ነው የምቆጥረው፤ ይልቁንም በኔ ፊት ያን የመሰለ የድፍረት ተግባር ስለመፈጸሙ በእውነተኛው ቅር ተሰኝቻለሁ ሲል መለሰለት። ነገሩ ከበረደ በኋላ ከዚያ ቦታ የግማሽ ቀን መንገድ ርቆ በሚገኝ ቦታ ባለው ቤተ ንጉሥ ገብተን እንድንጠብቀው በመጠየቅ ወደኋላ ተመልሶ ከባልጋዳ ሮቤል ቤት አጋሰሶችና ግመሎች የሚያመጣ መሆኑን ነገረን። (ወደፊት እንደምንረዳው የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖ ወደፖርቱጋል የተላከው አባ ፀጋ ዘአብ የተባለው መነኩሴ ይህ ነው)።

መንገዳችንን ስንገፋ ከዋልን በኋላ ሲመሽ የቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በነበረበት ባንድ መንደር ገብተን አደርን፤ በዚያ ቦታ ነብር ይገኛል ማለትን ስለሰማን ሌሊቱን ተጠንቅቀን ነበር ያደርን። በማግሥቱ ከግማሽ ሌግዋ ጥቂት በለጥ የሚል ርቀት ከተጓዝን በኋላ የተባለው ቤተ ንጉሥና ቤቶች ቤተ ክርስቲያኖችም ይገኙበት በነበረው አዲ ቆርቆራ ከተማ ደረስን። መነኩሴውን እየጠበቅን ሶስት ቀን ማለት ቅዳሜና እሁድን ሰኞን በዚያ ዋልን። ከአዲ ቆርቆራ በስተምስራቅ በኩል ብዙ መነኩሴዎች የሚገኙበት ናዝሬት የተባለ አንድ ትልቅ ገዳም አለ ይባላል። በዚያ ገዳም ወይንና ኮክ ሌሎችም ልዩ ልዩ ዓይነት ፍራፍሬዎች በብዛት ስለሚገኙ ሰዎች ከዚያው ፍሬ አምጥተው አበረከቱን። በስተ ምዕራብ በኩል ማለት በአባይ አግጣጫ ዘዴ በማጣት አውጥተው ያልተጠቀሙበት ብዙ የብር ማዕድን ይገኛል ይባላል።

<u>ምዕራፍ አርባ ሰባት፤ ከቆርቆራ ከተማ ተነሥተን ወደፊት ስንጓዝ በመንገድ ተጠፋፋን፤ በመንገዳችን ላይ ነብር አጋጠመን።</u>

መነኩሴውን ሶስት ቀን ጠብቀነው ስላልመጣ ማክሰኞ ዕለት በጥዋት ተነሥተን ባንድ ወንዝ ሸቅበ ሁለት ሌግዋ ያህል ተጓዝን። በወንዙ ግራና ቀኝ ትልልቅ ዛፎችና ሌሌችም ቅጠላቅጠል ይታዩ ነበር። በሸለቆው በሁለት በኩል በሚገኙ ታላላቅ ተራራዎች ግርጌ በጥንቃቄ ታርሶ የተዘራ የገብስና የስንዴ ሰብል ይታያል፤ ገበሬዎች እዳሪ መሬት ለማቅናት ሲሉ ጫካውን ሲመነጥሩ በየጉቶው ላይ የሚያቆጠቁጠው የወይራና ለሌሎችም ዛፎች ቁጥቋጦ አዲስ ተተክ ለው የፋፉ ዛፎችን ይመስላሉ።

በዚያ ሸለቆ ውስጥ በጣም ወፍራምና ረጅም በሆኑ በጥድ ዛፎች የተከበበ ባጠገቡም የቄሶች ቤቶች የሚታዩበት አንድ የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ከደጀሰላሙ አጠገብ ንጹህ ውኃ የሚያ

ፈልቅ አንድ ምንጭ አለ። ከቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ያለው ምድር በመስኖ ዘዴ ውኃ እየጠጣ ልዩ ልዩ የሆኑትን በአገሩ የሚገኙትን እህሎች ለምሳሌ ገብስ፤ ስንዴ፤ ማሽላ፤ ሽንብራ፤ ምስር፤ አተር፤ ባቄላ፤ ጤፍ ዳጉሳና ልዩ ልዩ ዓይነት ጎመናጎመኖች አብቅሎ ይታያል። እዚህ ያለው ምድር አዲስ የተዘራ ነው፤ እዚያ ያለው ቡቃያ ነው፤ እልፍ ብሎ ያለው የሸተ ነው፤ ከዚያ አልፎ ያለው ታጭዶ ተከምሮአል፤ በመጨረሻ ያለው ተወቅቶ በጎተራ ገብቶአል። ከዚያ ሸለቆ በስተግርጌ በኩል በሚገኝ ባንድ ደረቅ ትራራ ጫፍ ጥግ ባጠገቡ የቄሶች መኖርያዎች ብቻ እንጂ ሌሎች ቤቶች የማይገኙበት አንድ ቤተ ክርስቲያን አለ። በዚያ ተራራ ጫፍ በጥንት ጊዜ ያን መተላለፊያ የሚጠብቁበት መሆኑን የሚያስረዳ በር የሚመስሉ[1] የሚታዩበት አንድ አሮጌ የግንብ ግድግዳ ይታያል፤ ያገሩ ሰው እንደሚያወራው ስፋቱ ሃያ ሴግዋ ለሆነው በዚያ አካባቢ ለሚገኘው ቦታ ሌላ መተላለፊያ የለም። በዚያ መተላለፊያ የሚሰበሰበው ሕዝብ ብዛት የሰማነውን ወሬ ሊያረጋግጥልን ችሎአል።

ከዚያ ተራራ ወርደን በፊት እንዳየነው ሁሉ ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት እህል የተዘራበት ሰፊ የመስኖ እርሻና ከብቶች የሚሰማሩበት የሣር ቦታ ያለበት አንድ ትልቅ ሜዳ ደረስን። በዚያ ሜዳ መግቢያ ላይ ዙርያውን የቄሶች መኖርያ ቤቶች የነበሩበት የቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን አለ፤ ከዚያም እልፍ ሲሉ ካንድ ጉብታ ላይ የተሠራ አንድ ቤተ ንጉሥና አንድ ከተማም አሉ። ይህ ግራና ቀኙ ተራራ የሆነ በሸለቆው ውስጥ የሚገኝ ሜዳ በግምት ቁመቱ ሁለት ሴግዋ ስፋቱም ግማሽ ሴግዋ ይሆናል። በየተራሮቹ ግርጌ በግራና ቀኝ ብዙ ትንንሽ ቤተ ክርስቲያኖችና ሁለት ገዳሞች አንደኛው የቅዱስ መስቀል ሌላውም የቅዱስ ዮሐንስ ይገኛሉ። እነዚህ ገዳሞች በያንዳንዳቸው ከአስርና ከአስራ ሁለት የማይበልጡ መነኩሴዎች የሚገኙባቸው ታናናሾች ናቸው።

ከዚያ ሜዳ ጀምሮ ወደፊት ያለው የተፈጥሮ ሁኔታ እየተለወጠ ሄደ። የዚያን ዕለት ሌሊቱን ተጠፍፍተን ግማሽ ሌሊት ስንፈላለግ ነበር ያደርነው። አምባሳደሩ በሄደበት በኩል አራትስ ዎች፤ በሌላ

በኩል ደግሞ ሁለት ሰዎች ሄዱ፤ እኔ ከአምባሳደሩ ጋር ነበርሁ። ዕቃችን ከአንድ ሰው ጋር በዚያ ገደላም ቦታ ቀረ። ከአምባሳደሩ ጋር ከሄድነው ሰዎች ፊት ከሸለቆው ማዶ አንድ ትልቅ እሳት ወለል ብሎ ይታይ ነበር። እሳቱ እኛ ከነበርንበት ቦታ ምንም እንኳ ሁለት ሴግዋ ያህል ርቆ ቢገኝም ጊዜው ሌሊት ስለነበር ልክ ከአጠገባችን የሚነድ ይመስል ነበር። ነገሩን ለማጣራት ወደፊት ስንሄድ ብዙ ነብሮች ተከትለውን ባንድ ጥሻ ስንደርስ በጦር ጨበጣ ሊወጉዎቸው እስኪቻል ድረስ ቀረቡን። ከኛ ሰዎች ውስጥ ጦር የያዘ አንድ ሰው ብቻ ነበር፤ የተቀሩት ግን ጎራዴ ብቻ ነበር የያዙት፤ እኔ ባዶ እጄን የሆንሁት በነርሱ መካከል ነበርሁ። እሳቱን ተከትለን ወደፊት ስንሄድ አንድ ጥሻ አጠገብ ደርሰን ወደጥሻው ውስጥ የገባን እንደሆነ የነብሮቹ ምግብ መሆናችንን በመገንዘብ የምንሄድበትን ስላላወቅነው ባንድ እርሻ ውስጥ ገብተን እንድናድር ተስማማን። በእርሻው ውስጥ ንጹህ የሆነውን ቦታ መርጠን በቅሎቻችንን ባንድነት አስረን ጎራዴ የያዙት ሰዎች በከብቶቹ ዙርያ ተቀመጡ። እነርሱም የተባረኩ ሰዎች ስለነበሩ «አባ እርስዎ ይተኙ እኛ ባለጎራዴዎቹ እንጠብቃለን» ብለውኝ ሲጠብቁ አደሩ።

በማግሥቱ ከቀኑ በስምንት ሰዓት እኛና አምባሳደሩ የተቀሩትም ሰዎች ካደርንበት ቦታ ሁለት ሴግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ማናዴሌ በተባለ ከተማ ተገናኘን። ያን ከተማ በሙሉ ይዘው የሚገኙ ለንጉሡ ነገሥቱ የሚገብሩ አንድ ሺ የሚሆኑ እስላሞች ናቸው። በከተማው ባንድ በኩል ፈንጠር ብለው የሚኖሩ ጠቅላላ ቁጥራቸው ከሰላሳ የማይበልጥ ክርስቲያኖች በከተማው ከሚያልፈው መንገደኛ የኬላ ቀረጥ እየተቀበሉ ይኖራሉ። ከፍ ብሎ እንደተመለከተው የአየሩ ሁኔታ እየተለዋወጠ ሄደ ብያለሁ፤ ጉዞአችንን የጀመርነው በክረምቱ ወራት መጀመርያ ላይ ሲሆን ሁለት ወር ብቻ እንደተጓዝን በዚህ ቦታ ስንደርስ ዝናም ፈጽሞ አልነበረም፤ እንዲያውም ፍጹም በና ነበር።

ከዚህ በላይ በምዕራፍ ሃያ አምስት እንደገለጽሁት የዝናሙ ወራት በየካቲት በመጋቢትና በሚያዚያ ከሆነባቸው ቦታዎች ይህ ዶባ የተባለው አንዱ ነው። የክረምታቸው ወራት የተለዋወጠ

ቦታዎች ሁሉ ታላላቆቹን ተራራዎች መከላከያ አድርገው በየጎድጓዳው ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ዶባ በእስላሞች አገር ድረስ ስለሚገባ በውስጡ አልፌ የጎኑን ስፋት ለማወቅ አልቻልሁም፤ ነገር ግን ቁመቱ የአምስት ቀን መንገድ መሆኑን ተረድቼአለሁ። በዚህ ቦታ ቁጥራቸው እጅግ የበዛና ጥሩ የሆኑ በዓለም ከሚገኙት ሁሉ የበለጡ ከብቶች አሉ።

ማናዶሌይ ከመድረሳችን በፊት ባንድ ተራራ ላይ ብዙ ሰዎች በሕብር ድምጽ «እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ» እያሉ ለእግዚብሔር ሲጮሁ ሰምተን ምክንያቱ ምን መሆኑን ለመረዳት ወደቦታው ሄደን በቦናው መጠንከር ምክንያት ከብት ስላለቀባቸውና እህልም መዝራት ስላልቻሉ እግዚአብሔር ዝናሙን እንዲያወርድላቸው በመለመን የሚጸልዩ መሆናቸውን አስረዱን። ማናዶሌይ እንደ አንድ መናገሻ ከተማ ወይም ወደብ ከፍተኛ ግምት ያለው ከተማ ስለመሆኑ የልዩ ልዩ አገር ሸቀጥ የሚገኝበት ትልቅ የንግድ ከተማ ነው። የልዩ ልዩ አገር ነጋዴዎች በዓለም ላይ የሚገኘውን ሸቀጥ ሲገዙና ሲሸጡ ይታያሉ። እንዲሁም የብዙ አገር እስላሞች ማለት የቱኒስ አረቦች፤ ቱርኮች፤ የግሪክ ሩሚዎች፤ የሕንድ እስላሞች፤ የፋርስና የግብጽ ቋንቋዎች ይሰሙ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ነጋዴዎቹ ሳይፈቅዱ አንድ ሺ ወቄት ወርቅ አበድሮአቸው በዓመት ያንኑ ያህል ወለድ ስለሚጠይቃቸው እዚያ በነበርንበት ጊዜ ነጋዴዎች በጣም ያጉረመርሙ ነበር። ያገሩ ተወላጅና ነዋሪዎች በዚህ ቦታ መኖራችን ለከብቶቻችን ስንል እንጅ ለቀነው እንሄድ ነበር ይላሉ። (ይህ ጉዳይ የውጭ አገር ሰዎችን አያገባቸውም)። ንጉሠ ነገሥቱ ከሚጠይቃቸው ግብር ሌላ የቦታው ገዥ የሆነው ትግሬ መኮንኑም በበኩሉ የራሱን ድርሻ ቀረጥ ይጠይቀናል ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ። ስለዚህ ነጋዴዎቹ ለመኖር አልቻልንም እያሉ ያማርሩ ነበር።

የማናዶሌይ ገበያ የሚውለው በየሳምንቱ ማክሰኞ ሲሆን በዚሁ ዕለት ከአካባቢው ግዛቶች የሚመጡ እልቆ መሳፍርት የሌላቸው ሰዎችና ማናቸውም ዓይነት ሸቀጦች ይገኛሉ። ነጋዴዎቹ ግን በየቀኑ በገበያው አደባባይ ላይ ተሰብስበው ይውላሉ።

ምዕራፍ አርባ ስምንት፤ አባ ፀጋ ዘአብ በመናዶሌይ ደርሶብን ከዚያ ተነሥተን ድፈርፎ ስለመሄዳችን፤ ስለድፈርፎ ሕዝብ ምግብና መጠጥ።

የመነኩሴውን ወሬ ሳንሰማ ብዙ ቀኖች በቆየንበት በማናዶሌይ እንደነበርን አንድ ቀን መነኩሴው አባ ፀጋ ዘአብ ዕቃችንን ማስጫኛ አጋሰሶችና ግመሎች እያስነዳ መምጣቱን የሚያስታውቅ አንድ መልእክተኛ መጣ። ይህንኑ በመስማት በመጀመርያ ስናገኘው የተፈጸመውን ሁሉ ረስተነው ከኛ ሰዎች ጥቂቶቹ መንገድ ድረስ ሄደው በደስታ ተቀበሉት፤ እንደደረሰ ወዲያውኑ መንገዳችንን ቀጥለን አንድ ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ በተራራ ላይ በሚገኝ ባንድ ቤተ ንጉሥ ውስጥ ገብተን አደርን።

በማግሥቱ ከቤተ ንጉሡ ተነሥተን ሁለት ሌግዋ ያህል ተጉዘን አንድ ሺ የሚሆኑ ክርስቲያኖች በሚኖሩበት ድፈርፎ በተባለ ከተማ አደርን። የከተማው ቤተ ክርስቲያን አንድ መቶ ቄሶችና መነኩሴዎች እንዲሁም በዚሁ ቁጥር የሚገመቱ መነኩሲቶች አሉበት። ቤተ ክርስቲያኑ ገዳም ባለመሆኑ መነኩሲቶቹ እንደተራው ሴቶች በከተማው ይኖራሉ። መነኩሴዎቹ በሁለት አጥራም መንደሮች ውስጥ ይኖራሉ። የካህናቱ የመነኩሴዎቹና የመነኩሲቶቹም ቁጥር እጅግ የበዛ በመሆኑ ሌሎቹ የከተማው ነዋሪዎች ተጣበው ነው የሚኖሩት። በሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ቁርባን የሚሰጠው ከቤተ ክርስቲያኑ በር ፊት ለፊት ነው፤ እዚህ ግን ከውጭ ተተክሎ በሚገኝ የሐር ድንኳን ውስጥ ነው። የቁርባኑ ስነሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ ጽናጽልና ከበሮ እየተመታ ዜማው ይቀጥላል። እዚያ ባደርንበት ሁለት ሌሊት መነኩሲቶቹ እግራችንን እያጠቡን እጣቢውን በመፈንጠቅ ፊንታ ይጠጡትና ፊታቸውንም ይታጠቡበት ነበር። ይህን ያደረጉበት እኛን ከየሩሳሌም የመጣን ጻድቃን ክርስቲያኖች ናቸው ብለው በመገመት ነበር።

በዚህ ከተማ አጠገብ ልዩ ልዩ ዓይነት ሰብል ተዘርቶባቸው የሚገኙ ታላላቅ እርሻዎች አሉ። በየእርሻዎቹ መካከል ስንዴና

ኑግ ሌሎችንም የዘይት እህሎች የሚወቁባቸው አውድማዎች አየን። በዚህ ቦታ የመጣነው ሁለት ጊዜ ስለሆነ በመጀመርያ በመጣንበት ጊዜ ገበሬዎቹ ያመረቱት እህል እጅግ ያለመጠን የበዛ እንደነበርና ነቀዝ ባይበላውማ ኖሮ እስከ አስር ዓመት ድረስ ሕዝቡን ለመመገብ ይችል ነበር ሲሉ ያገሩ ሰዎች ስለነገሩን በነገሩ ተገረምሁ። የኔን መገረም በማየት አንዱ ሰው ወደኔ ቀርቦ እንዲህ አለኝ። «የተከበሩ እንግዳችን ሆይ አይገረሙ፤ በያመቱ የምናመርተው እህል እጅግ ያነሰ እንደሆነ ለሶስት ዓመት የሚበቃ ነው፤ አንበጣውና በረዶው ባያጠፋብንማ ኖሮ በያመቱ በምንዘራው ዘር ግማሽ ብቻ ይህን ያህል ለማምረት እንችል ነበር። ይህ ምድር የሚሰጠው የስንዴ፤ የገብስ፤ የምስር የሽንብራና የሌላም እህል ሰብል ብዛት ለማመን ያስቸግራል። በያመቱ ስንዘራ በእህላችን ላይ የሚደርስበትን አደጋ በመገመት ነው፤ ስለዚህ ከአደጋው ተርፎ ወቅተን የምናስገባው ችግራችንን አሸንፎ ይተርፋል፤ አዝመራችን በሙሉ ቢበለሽ እንኳ ባለፈው ዓመት ባከማቸነው ለመኖር እንችላለን»።

ድፋርፎ በራስጌው ሁለት ተራሮች የሚገኙበት በሸለቆው ውስጥ የተቆረቆረ ነው። በዚህ ከተማ ሁለት ቀን ማለት ቅዳሜና እሁድን ዋልን። በየተራሮቹ ጥግና በየሸንተረራቸው ውስጥ ተስማርተው የሚገኙት እነዚያ የደስደስ ያላቸው የቀንድ ከብቶች ብዛት ከፍ ያለ በመሆኑ ለማመን ያስቸግራል።

የዚህ አውራጃ ሕዝብ ቋንቋ ከዚህ በፊት ያየነው ሕዝብ ከሚናገረው የተለየ አንጎትኛ የተባለ ነው። ይህ ቋንቋ የሚነገርበትን አንጎትንና የትንሬ መኮንኑን ግዛት የሚያዋስናቸው የእሳላሞች መኖርያ የሆነው ዶባ የተባለው ግዛት ነው።

ወደፊት የሚገኘው ግዛት የእስላሞች መኖርያ ስለሆነ ከላይ እንደገለጽሁት የመንገደኛውን ጸጥታ ለመጠበቅ በድንበሩ ላይ የሚገኙ ሁለት ተራሮች ላይ ሆነው ቁልቁል የሚመለከቱ ሰዎች መኖራቸውን በዚያ ሁለት ጊዜ ስናልፍ አይቻለሁ። ከኮረብታዎቹ አልፈው ሲሄዱ ሁለት ሌግዋ ያህል ስፋት ያለው ጫካ አለ። ከዚያም በኋላ እስላሞቹ

ከትመው የሚኖሩባቸው ተራኖች ይከተላሉ። አንድ ቀን እስላሞች በብዛት መምጣታቸውን በመመልከት ጠባቂዎቹ ምሽጋቸውን ትተው ሸሹ፤ ስለዚህ እስላሞቹ ከዚያ ቦታ ያገኙትንና ያሻቸውን ዘርፈው ሄዱ።

ይህ የእስላሞች ድል ለክርስቲያኖች ትልቅ ሐፍረት ስለሆነ ባቸው እነዚያ ምሽግ ጠባቂዎች በየቀበሌውና በየግዛቱ እየሄዱ እስላሞቹን ለሁለተኛ ጊዜ ልንገጥማቸው እንፈልጋለንና እርዱን፤ መምጣታቸውን ስታዩ ቀደም አድርጋችሁ ምልክት ስጡን እያሉ አገሬውን ለመኑት። እንደተለመነው አገሬው ብዙ ሰው መልምሎ ወደተባለው ቦታ ላከና እስላሞቹም ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጡ ምልክት ሰጥቶ ውጊያው ተጀመረ፤ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ቀኑን የክርስ ቲያኖች አደረገው፤ ከእስላሞቹ በኩል ስምንት መቶ ሰዎች ከክርስ ቲያኑ በኩል ግን አምስት ሰዎች ብቻ ሞተው እስላሞች ፍጹም ድል ተነሥተው ከዚያ ቦታ ጠፉ። ክርስቲያኖቹ የእስላሞቹን አንገት እየቀሉ ከዚያ ቦታ ግማሽ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ብዙ መንገደኛ በሚተላለፍበት አውራ ጉዳና ላይ ጭንቅላታቸውን ሰቀሉት፤ የሞቱትን እስላሞች ጦርና ጋሻ በሙሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ላኩ፤ እኛ በዚያን ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ስለነበርን የምርኮውን ርክክብ አይተናል። ከቤተ መንግሥቱ ስንመለስ በዚያ አውራ ጉዳና ደርሰን ጭንቅላቶች ተንጠልጥለው በማየታችን በነርሱ ሥር ለማለፍ ትልቅ ጽያፌና ፍርሐትም አደረብን።

የዚያ አውራጃ ሕዝብ የሚበላው እንጀራ እንደሌላው ቦታ ሕዝብ ከአንድ ዓይነት እህል ብቻ ሳይሆን ከልዩ ልዩ እህሎች ማለት ከስንዴ፤ ከገብስ፤ ከማሽላ፤ ከሽንብራ፤ ከአተር፤ ከምስር፤ ከአደንጓሬ፤ ከባቄላ፤ ከጤፍ፤ ከዳጉሳና ከሌሎችም እህሎች የተዘጋጀ ነው፤ የዚህ ቦታ ጠጅ ከሌላው ሁሉ የበለጠ ነው። አብሮን በነበረው መነኩሴ አማካ ይነት በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ የአገሩ ሕዝብ ባረፍንበት ቦታ ሁሉ ምግብ እንዲሰጠን ስለታዘዘ ከላይ የጠቀስሁትን ከልዩ ልዩ እህል የተሠራውን እንጀራ ያመጣልን ነበር። እኛ የስንዴ እንጀራ እንጂ ሌላውን ዓይነት ገና ባለመልመዳችን አንበላም ነበር፤ ይህንኑም

የማንፈቅደውን ምግብ የሚያመጡልን የማዕድ ሰዓት በጣም ካለፈ በኋላ ነበር፤ ይህም የሚሆንበት ምክንያት በአገሩ ደንብ ምግብ የሚበላው በቀን አንድ ጊዜ ማለት እራት ብቻ በመሆኑ ነው። አዘውትረው የሚበሉት ምግብ በእበት[1] እየተለወሰ የሚበላው ብርንዶ ነው። እኛ ግን ብርንዶውን አልቀመስነውም፤ እንጀ ራውም ከስንዴ ወይም ከሽንብራ ካልተሠራ አንበላውም ነበር። አገሬው ከሚያመጣልን ጥሬ ሥጋ ዕቃችንን የተሸከሙልን ሰዎች ሌላ ዓይነት ምግብ እንዲያዘጋጁልን አዘዝርቸው። መነኩሴው የኛን ባሕልና ልምድ እየለመደው ስለሄደ አሽከሮቹ ዶሮ እየሠሩ የበግ ወይም የበሬ ሥጋ እየጠበሱ ወይም እየቀቀሉ እንዲያቀርቡልን አዘዘ።

ምዕራፍ አርባ ዘጠኝ፤ የእስላም መኖርያ ግዛቶችን ለማለፍ በደንብ ስለመዘጋጀታችን።

ከድፋርፎ ተነሥተን አገዳው ትልልቅ የሆነ ማሽላ በተዘራበት እረሻ ውስጥ አቋርጠን ስንጓዝ ውለን ሲመሽ ባንድ ተራራ ጥግ በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ አደርን። እላይ እንደገለጽሁት አገሬው ምግባችንን እንዲሰጠን ስለታዘዘ ይህ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ ለሕዝቡ እንድንቀርበው በማለት ከአውራ ጎዳና እየወጣን በመንደሮች አጠገብ ማደር ጀመርን። ከፊታችን የነበረው ቦታ የጦረኞች እስላሞች መኖርያ ስለነበር እንድንጠነቀቅና መሣርያ ችንንም በእጃችን ይዘን በአንድነት ሆነን እንድንሄድ መነኩሴው መከረን። አሁን ከምንጓዝበት ከባሕሩ ገጽ ለገጽ ካለው ጎዳና ጀምሮ ወደደቡብ የሚገኘው ቦታ ዶባ የተባሉ እስላሞች የሚኖሩበት ቀበሌ ነው፤ ይህ ስም የወረዳው እንጂ የጠቅላይ ግዛቱ ስም አይደለም። እስላሞቹ የሚገኙበት ክፍል ሃያ አራት ወረዳዎች ይገኙበታል ይባላል፤ የአስራ ሁለቱ ወረዳዎች እስላሞች በሰላም ሲቀመጡ ለሌሎቹ አስራ ሁለቱ ግን ሁልጊዜ እንደተዋጉ ነው የሚኖሩት

ይባላል። እኛ በዚያ በነበርንበት ጊዜ ሁለቱም ክፍሎች ሲዋጉ ነበሩ። አንዳንድ ጊዜ በሰላም የሚኖሩት ባላባቶች ከንጉሠ ነገሥቱ ይቅርታ ለመጠየቅና ታማኝነታቸውንም ለመግለጽ ወደ ንጉሣዊው ከተማ መጥተው አይተናቸዋል። እያንዳንዱ ባላባት በጭንቅላቱ ላይ ድንጋይ ተሸክሞ በድንጋዩም ላይ ሁለት እጆቹን ጭኖ ይታይ ነበር። የዚህ ተግባር ምስጢሩ ምን መሆኑን ለመረዳት ፈልገን የሚያውቅ ሰው ብንጠይቅ ድንጋይ የተሸከመው ሰው ሰላም ፈልጎ ምሕረት መጠየቱ ነው አሉን። ለገጸ በረከት በቅሎዎችና ፈረሶች አስይዘው ከመቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎችን አስከትለው የመጡትን እነዚህን በጭንቅ ላታቸው ድንጋይ የተሸከሙትን ባላባቶች ንጉሠ ነገሥቱ በክብር ተቀበላቸው። በደጅ ጥናት ከቤተ መንግሥቱ ከሁለት ወር በላይ በቆዩበት ጊዜ በየቀኑ አንዳንድ ፍሪዳ በጎች ማርና ቀቤ ድርጎ ይሰጣቸው ነበር።

ባላባቶቹ እንደጠየቁት ንጉሠ ነገሥቱ ምሕረት አደረገላቸው። ይሁን እንጂ ለወደፊቱ ጸጥታ እንዳይነሱ በማለት ጓዛቸውንና ሰዋቸውን በሙሉ ይዘው ከዶባ እንዲለቁና አንድ መቶ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ዳሞት በተባለ ቦታ ሠፍርው በዚያ በጥብቅ እንዲኖሩ አዘዘ።

ነገር ግን ባላባቶቹ ከአገራቸው እንዲሰደዱ የተፈረደባቸው መሆኑ እንደተሰማ እስላሞቹ ሌሎች ባላባቶች ሹመው ወዲያውኑ በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ላይ አመጹ። ይህ እንደሆነ በዚያ መንገድ በምናልፍበት ጊዜ አርብ ዕለት የዋለውን የጥምቀትን በዓል ጾም ለመጾምና ከዚያም በኋላ ቅዳሜንና እሁድን ለመዋል በዚያ ቆየን።

ባመጹት እስላሞች ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ያዘመተባቸው ብዙ ሰዎችና ታላላቅ የጦር መኮንኖች የሚገኙበት እኛ ከሠፈርንበት ጥቂት እልፍ ሲሉ በሚገኘው ተራራ ላይ ድንኳን ጥለን ሠፍረን ስለነበር ጭስ ሲጨስ አየን። በዚያ የሠፈሩትን መኳንንት አይተው ጉዳዩን አጣርተው ወሬ እንዲያጡለት አምባሳደሩ ወደ ቦታው ሁለት ፖርቱ ጌዞች ላከ። መልእክተኞቹ ሲመለሱ መኳንንቱ የላኩልንን ስድስት

ፍሪዳ አምጥተውልን ከአስራ አምስት ሺ ሰው በላይ የሆነው በታላላቅ መኳንንት የሚመራው ሠራዊት በዚያ ሠፍሮ መቀመጡን ነገሩን፤ ከሠፈሩ ጥቂት እልፍ ሲሉ ውኃ ይገኝ ነበር፤ ነገር ግን እስላሞቹ በዚያ እያደፈጡ የሚያገኙትን ሰው ሁሉ ስለሚገድሉ የንጉሠ ነገሥቱ ሰዎች በርከት እያሉ ድሄዳሉ እንጂ በቅሎቻቸውንና ፈረሶ ቻቸውን ውኃ ለማጠጣት ወይም ውኃ ለመቅዳት አንድ በአንድ አይሄዱም ሲሉ ፖርቱጊዞቹ ነገሩን፤ ቅዳሜና እሁድ ክርስቲያኖቹ የማይዋጉባቸው ቀኖች መሆናቸውን በማወቅ እስላሞቹ በነዚሁ ቀኖች አደጋ ይጥሉ ነበር ሲሉ እነዚሁ ሰዎች ጨምረው ገለጹልን።

የአገሩ ሕዝብ እንደሚያወራው የእስላሞች ጦርነት ከመቼውም ይልቅ አሁን በሥልጣን ላይ ባለው ንጉሠ ነገሥት ዳዊት ዘመነ መንግሥት የተፋፋመበት ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ ያባቶቹን ልምድ ባለማክበሩ ነው ይባላል። ከአጼ ዳዊት አባት ጀምሮ ወደኋላ ያሉት ንጉሠ ነገሥታት ሁሉ አምስት ወይም ስድስት ሚስቶች ያገቡ ነበር፤ ሚስቶቻቸውም የእስላምና የአሕዛብ ባላባት ልጆች ነበሩ፤ ከነዚህ እስላሞች ባላባቶች ንጉሠ ነገሥቶቹ እንዳስፈለጋቸው አንድ ወይም ሁለት፤ ከደንከል፤ ከአዳል፤ ወይም ከሐድያ መርጠው ያገቡ ነበር። ለአጼ ዳዊት የመጀመርያ ሚስቱ እንድትሆን የተዳረችለት የሃድያ ባላባት ልጅ ነበረች፤ ዳሩ ግን የፊት ጥርሶችዋ በጣም ትልልቅ ስለነበሩ ንጉሠ ነገሥቱ ጠላት። ይሁን እንጂ ልጅቱ በክርስትና ሃይማኖት ተጠምቃ ስለነበረች ንጉሠ ነገሥቱ ወዳባትዋ ሊመልሳት ስላልቻለ ላንድ መስፍን ዳራት። ከዚያ ጊዜ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ የእስላምን ወይም የአሕዛብን ባላባት ልጆች አላገባም ብሎ ቆርጦ አንዲት የክርስቲያን ልጅ አግብቶ በወንጌል ሕግ መሠረት በዚያች ሴት ብቻ ረጋ። ንጉሠ ነገሥቱ ይህን የመሰለውን ተግባር መፈጸሙ እስላሞቹን ስላስቆጣቸው ከጥንት ጀምሮ የሚከፍሉትን ግብር ከማስቀ ረታቸው በላይ በዚሁ ምክንያት ብቻ ያለማቋረጥ መዋጋት ጀመሩ። የዶባ እስላሞች እልኸኞችና ጦረኞች ናቸው፤ ይህ እልኸኛነት ሳይ በርድ የሚኖርበት ምክንያት አንድ ወጣት አስራ ሁለት ክርስቲያን ገድሎ የግዳዩን ምልክት ካላበረከተ ሚስት እንዲያገባ በሚከለክለው ያገር ልምድ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በእስላሞቹ አገር ከነጋዴ ጋር ካልሆኑ በስተቀር ለብቻ ለማለፍ አይቻልም፤ ነጋዴዎቹ በያንዳንዱ ክፍል ከአንድ ሺ ሰው በላይ እየሆኑ በነጋድራሳቸው እየተጠበቁ በሳምንት ሁለት ጊዜ ይተላለፋሉ። ከሁለት ቦታ የሚነሱት እነዚህ ሁለት ክፍል ነጋዴዎች እያንዳንዳቸው የራሳቸው ነጋድራስ አላቸው። ነጋዴዎቹ የሚነሡባቸው ከማናዴሌይና በአንጎት ግዛት ከሚገኘው ከቆርቆራ ገበያ ነው። ምንም እንኳ በርከት ብለውና በነጋድራሳቸውም እየተጠበቁ ቢሄዱም እስላሞቹ ከነርሱ ውስጥ ብዙ ጊዜ ሰው ይገድላሉ። ይህን ላውቅ የቻልሁት በንጉሣችን ቤት አሽከር የነበረ እኔ አጎት የምሆነው አምባሳደር ዶም ሩድሪጉን የሚያገለግል አንድ ወጣትና አንድ ሌላ ፖርቱጊዝ ከነጋዴዎች ጋር ተቀላቅለው የእስላሞችን አገር አልፈው ስለነበር ነው። እነዚህ ሰዎች በነገሩኝ መሠረት እስላሞቹ በስተኋላ በኩል በድንገት ደርሰው ክርስቲያኖቹ ዘንጋ ማለታቸውን በማየት አስራ ሁለት ሰዎች ገድለውባቸው ሸሹ። ያን መጥፎ መንገድ በበለጠ አደገኛ የሚያደርጉት የሁለት ቀን መንገድ የሚፈጅ ስፋቱና ሜዳነቱ እንዲሁም አልፎ አልፎ የሚገኝ የታላላቅ ዛፎች ጫካው ከመሆናቸው በላይ ጉዞውንም ያለቅጥ ረጅም የሚያደርገው እስላሞች ጫካውን በማቃ ጠል መንገዱን ስለሚዘጉት ያን እየዞሩ መሄዱ ነው። ጫካውን እሳት ሲለቁበት ታካኪዎቹ ዛፎች ተለብልበው ሲቆሙ ጥሻና ቅጠላቅጠል በሙሉ ይቃጠላል። ከአውራ ጉዳናው ጀምሮ የእስላሞቹ መንደሮች ድረስ ያለው ቦታ በሙሉ ለጥ ያለ ሜዳና ጫካ ብቻ ነው። በነዚህ ተራሮችም በፊት ያየናቸውን ተራሮች ይመስል ብዙ ዝሆኖችና የዱር አራዊት ይገኛሉ።

ምዕራፍ ሃምሳ፤ የጃናሞራ ሕዝብና የእስላሞቹ ጦርነት፤ በመነገድ እንዳለን መብረቅ ስለመጣሉ።

ከዶባ እስላሞች ጋር ሁል ጊዜ ይዋጋ የነበር ሹም ጃናሞራ የተባለ አንድ መኮንን ነው። ሹም ጃናሞራ ማለት የጃናሞራ አውራጃ ገዥ ማለት ነው። የጃናሞራ ሕዝብ ጎበዝና ጦረኛ ነው ይባላል፤

እኔም እንደተገነዘብሁት ሕዝቡ ጠንቃቃ በመሆኑ እንደሚወራው ጎበዝ ሳይሆን አይቀርም። እስላሞቹ እዚህ ቦታ ድረስ እየመጡ ቤቶችንና ቤተ ክርስቲያኖችን እያቃጠሉ እበረት እየገቡ ከብት እየዘረፉ የሄዱሉ።

አንድ ቄስ መርዝ የተቀባ ቀስት ይዞ ስላየሁት አንተ ቄስ በመሆንህ መሣርያ ልትይዝ አይገባህም ስል ገሠጽሁት። እርሱም መለሰና እዚያ ማዶ የተቃጠለውን ቤተ ክርስቲያን ይመልከቱ፤ ከዚያ ቦታ ሃምሳ ከብቶች ዘርፈው የሃብቴ ምንጭ የሆኑትን ብዙ ቀፎዎች አቃጥለውብኛል፤ ስለዚህ ይህን መሣርያ መያዜ ጠላቴን ለመግደል ነው ሲል መለሰልኝ። በልቡ ውስጥ የነበረው ሃዘን በፊቱ ላይ ግልጽ ሆኖ ይታይ ስለነበር ምንም መልስ ልሰጠው አልቻልሁም ነበር።

ከዚህ ካረፍንበት ቦታ ተነሥተን የጃናሞራ ክርስቲያኖች በሚኖሩበት ተራራ በኩል አድርገን ያን ሜዳ ተከትለን መንገዳችንን ወደፊት ቀጠልን፤ ከተራሮቹ እየፈለቁ ቁልቁል የሚፈሱትን ወንዞች እየተሻገርን ስንሄድ አርፍደን ትልልቅ ዛፎች ባሉበት ባንድ ደረቅ ወንዝ ዕረፍት አደረግን። ጊዜው ሙቀት ነበር፤ በተራራው ላይ ምንም ደመና አይታይም ነበር፤ አካባቢው በሙሉ ነፍስ ያለው ፍጡር የማይኖርበት ይመስል ርጭ ብሎ ነበር። እኛ በሁለቶ ቦታ ተከፍለን ከወንዙ ማዶና ማዶ ሆነን እያወጋን ተቀምጠን ነበር። ወዲያኑ የነጎድጓድ ድምጽ ከሩቅ ቦታ ይሰማ ጀመር፤ ይህን የመሰለው ነጎድጓድ በሕንድ አገርም አንዳንድ ጊዜ ይደርሳል እያልን እናወራ ነበር።

እኛ በነበርንበት ቦታ እንኳን ዝናም ቀርቶ የዝናምም ምልክት ከቶ አይታይም ነበር፤ ስለዚህ ያ ከሩቅ ይሰማ የነበረው የነጎድጓድ ድምጽ እንዳቆመ እኛም ዕረፍታችንን ጨርሰን መንገዳችንን ለመቀጠል ዕቃችንን ማዘጋጀትና ድንኳናችንን መንቀል ጀመርን። ከኛ ሰዎች አንዱ ወንዙን ተከትሎ ወደላይ ሄዶ የነበረው መምሕር ዮሐንስ ወዲያውኑ እየሮጠ ወደኛ መጥቶ በታላቅ ድምጽ «ተጠንቀቁ፤ ተጠንቀቁ፤» እያለ ሲጮህ ሰምተነው ነገሩን ለማጣራት ቀና ብለን ስንመለከት ያለጥርጥር ካንድ ጦር ቁመት በላይ የሚዘል ጎርፍ

ደርሶብን አየን። እንኳን ዕቃችንን ለማንሣት ቀርቶ ነፍሳችንንም ለማዳን ጊዜ አልነበረንም፤ እጃችን ያረፈበትን ብቻ እየያዝን ወደዳር ሮጥን። ያረፍንበት ድንኳን የተተከለው ራቅ ብሎ ስለነበር በውስጡ የነበሩት ሰዎችና ዕቃችን ሲተፉ ሌላውን ዕቃችንን ወሰደብን። ከግል ዕቃዬ ሌላ ከኔም አንድ የጸሎት መጽሐፍና ለቁርባን መስጫ የያዝሁትን አንድ ጠርሙስ የወይን ጠጅ ወሰደብኝ። ከያንዳንዳችን ላይ አንዳንድ ነገር፤ ለምሳሌ ካባ፤ ጉራዴ፤ ባርኔጣ ወሰደብን። አንዱ ጓደኛችን ሲሸሽ ክፉኛ ስለወደቀ ግማሻችን ስናዝን ግማሻችን ደግሞ ወዶ ያደረገው ይመስል እንስቅበት ነበር። የደሙን ማቅመሻ የብር ዋንጫውን በፍየል ቆዳ ማህደር ውስጥ አድርጌ ለዕረፍት ስንቀመጥ በዛፍ ላይ አንጠልጥዬው ነበር። ይህ ዕቃ ይጠፋ ዘንድ እግዚአብሔር ስላልፈቀደ አንድ ኢትዮጵያዊ ራሱን ለማዳን ሲል በዛፉ ላይ ወጥቶ ስለነበር ዋንጫውን ይዞ ውኃው እስኪጎድል ድረስ በዛፉ ላይ ቆየ። ይህ ወንዝ በተራራው ላይ የሚጥለው ዝናም ሁሉ ጎርፍ የሚተላለፍበት ነው።

ጎርፉ ከተራራው ላይ እያግበሰበሰ ታላላቅ ግንድና አዋሽ በርሜልን የሚያህሉ ብዙ ድንጋዮች እየተላጉ የሚያስከትሉት ድምጽ ከትልቅነቱ የተነሣ ምድር የተናወጸና ሰማይም ተሰብሮ የወደቀ ይመስል ነበር። የዚህን ድምጽ ታላቅነት በእውነተኛው ለማመን ያስቸግራል። ጎርፉ በፍጥነት እንደመምጣቱ በፍጥነት አለፈ። ከመምጣቱ በፊት በዚያ የነበረው ድንጋይ በሙሉ ተነሥቶ ሌላ ብዙ ድንጋይ መጥቶ ተተካበት። ከዚያ እልፍ ብለን ባንድ ምስኪን መንደር ስንደርስ ነዋሪዎቹ ድንጋይ እየወረወሩ ከዚያ ቦታ ሊያባርሩን ሞከሩ። የሆነ ሆኖ ምንም ምግብ ሳናገኝ ሌሊቱንም ዝናም እየዘነመብን በዚያችው መንደር አደርን።

ምዕራፍ ሃምሳ አንድ፤ ከዚያ ምስኪን ቦታ ተነሥተን ሰባሌቴ በተባለ ወንዝ አጠገብ አረፍን።

ያ ያረፍንበት ቦታ ምንም ምግብ የማይገኝበት ደረቅ ቦታ ስለነበር ሁላችንም ተነሥተን ወደፊት ሄድን፤ ዕቃችንን የሚሸከሙልን ሰዎች ስላልነበሩ በሙሉ ከመነኩሴው ጋር ትተነው ወደፊት ቀጠልን። ወደፊት ባለው መንገድ ላይ እስላሞች የሚገኙ ከመሆናቸው በላይ በመንገድ እያደፈጡ መንገደኛውን እየገደሉ የሚዘርፉ ወንበዴዎች በብዛት ይገኛሉ ስላሉን ከበፊቱ የበለጠ ፍርሃት አሳደሩብን። ስለዚህ ከአደጋ ለመዳን ከፈለግን ሁላችንም ሳንለያይ ባነድነት መሣርያችንን አዘጋጅተን መሄድ እንደሚገባን በተጨማሪ ገለጹልን።

በዚያን ዕለት የተጓዝንበት መንገድ ከኋላችን ትተነው እንደ መጣነው ለጥ ያለና ሰፊ ጥሻ የሚገኝበት ነበር። እንደበፊቱ ተራራውን እየተጠጋን ስለነበር የምንጓዘው ከእስላሞቹ አገር እየራቅን ሄድን። ለወንበዴዎች ማድፈጫ ምቹ የሆኑ ጥሻዎችና ፉካዎች በብዛት የሚገኙት በዚህ ቦታ ስለሆነ አደገኛ መሆኑን አስረዱን። አገሩ ልዩ ልዩ ዓይነት በሽታ ይገኝበታል ይባላል፤ ስለዚህ በየጎድጓዳ ቦታ እንዳትተኙ፤ በውኃ ዳርም እንዳታርፉ፤ በተቻለ መጠን ከፍ ያለ ቦታ እየፈለጋችሁ ማደር አለባችሁ እያሉ አስፈራሩን።

ጓዛችንን ወደኋላ ትተነው በዚህ አኳኋን ወደፊት ስንሄድ ከዋልን በኋላ ሰባሌቴ በተባለ ወንዝ አጠገብ ስንደርስ መሸቶብን በዚያው አደርን። የሰባሌቴ ወንዝ የትግሬ ጠቅላይ ግዛትንና አንጎትን የሚያዋስን ነው። ወንዙ ከሚነሣበት በስተምዕራብ በኩል ባንድ ተራራ ላይ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አለ። የአንጎት ግዛት ዋና ከተማ ይህ ቤተ ክርስቲያን በተቆረቆረበት ቦታ ነው ያለው። የዚህ ጠቅላይ ግዛት ገዢዎች ሲሾሙ ሥልጣናቸውን የሚረካከቡት በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ይባላል። ከነበርንበት መንገድ ሁለት ወይም ሶስት ሌግዋ ርቆ በስተምስራቅ በኩል በሚገኝ ባንድ ከፍተኛ ተራራ ላይ በጣም ትልቅ የሆነ ብዙ መነኩሴዎች የሚገኙበት አንድ ገዳም አለ ይባላል፤ (ይህ ቦታ የእስላሞች መሆኑ ቀርቶአል።) ነገር ግን አጋጣሚ ጊዜ ስላላገኘን በዙርያው የነበሩትን ዛፎች ከሩቁ አየን እንጂ ሄደን አልጎበኘነውም። በዚያ ወንዝ ዳር ቅዳሜንና እሁድን ውለን እሁድ ሌሊት እንደተለመደው በዙርያችን እሳት አንድደን እንደተኛን ነብር መጣብን። ምንም እንኳን እሳት መንደዱ ነብሩን ሊያስፈራራው ስላልቻለ አንድ በቅሎና አንድ አህያ አስደንብሮብን ወዴት እንደደረሱ ስላላወቅን ተበልተዋል በማለት ተስፋ ቆረጥን። በማግሥቱ ጥዋት በዚያ አቅራቢያ ባለ መንደር የሚኖሩ ሰዎች ወደዚያ መጥተው ትናንት ማታ ሁለት ከብቶች ሸሽተው ከኛ መንደር ገብተዋል ስላሉን እንዲያመጡልን አዘዝ ናቸው።

ሰኞ ጥቅምት 3 ቀን 1520 ዓ መንገዳችንን እንደገና ጀምረን በዚያ ሜዳ ላይ ሁለት ሌግዋ ያህል እንደተጓዝን በአጉል ቦታ ያደርን እንደሆነ በሽታ ይይዘናል በማለት ዕቃችንን አስይዞ ከኛ ጋር ተቀላቅሎ የነበረው ያ መነኩሴ ገደልና ድንጋይ በበዛበት ባንድ መንገድ መርቶ ለአዳር ወደ አንድ ተራራ ጫፍ ወሰደን። በመንገዱ መጥፎነት ምክንያት ዕቃችን ወደላይ መውጣት ስላልቻለ በአውራ ጎዳናው ላይ ቀረ። የዚያን ዕለት ማታ በመነኩሴው ላይ ሁላችንም አጉረ ምርመንበት እኛ በሽታ አንፈራምና ለወደፊቱ በንደዚህ ያለ ቦታ እንዳትመራን፤ ወይም ከሕዝቡ ምግባችንን ለመቀበል እንዲመቸን በማለት እንደሆነ ከአውራ ጎዳናው የምታወጣን ምግቡ ይቅርብን፤ ምክንያቱም የፖርቱጋል ንጉሥ የሰጠን በቂ ስንቅ ስላለን ለራሳችንም ሆነ ለአንተ ይበቃል አልነው። እርሱም እኛ ያልነውን ለመፈጸም ለወደፊቱ ከአውራ ጎዳና አላወጣችሁም እናንተ በሄዳችሁበት እከተ ላለሁ ስላለን ተደሰትን።

በማግሥቱ ማክሰኞ ጥዋት ካደርንበት ተራራ ቁልቁል ስንጓዝ ካረፈድን በኋላ በአውራ ጎዳናው አቅራቢያ በነበረው በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በተቀመጠው ዕቃችን ዘንድ ደርሰን የእኩለ ቀን ዕረፍት አደረግን። ያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ካህናትና መነኩሴዎች መነኩሲቶችም የሚገኙበት ሲሆን የሚመራው በካህናቱ ነው። ቤተ

ክርስቲያኑ ያለበት ቦታ ቆርቆራ ዘአንጎት ይባላል። በዚሁ ስም የሚጠራ በየሳምንቱ ረቡዕ ገበያ የሚውልበት ሌላ ከተማ በትግሬ ጠቅላይ ግዛት አለ።

ወደተራራው ጫፍ የሚወስደው መንገድ ለከብት በፍጹም የማይመች ስለነበር ከብዙ ጓዛችን ጋር ግመሎቻችንን ከፍ ብለን በጠቀስነው ቤተ ክርስቲያን ትተናቸው ሄድን። የዚያን ዕለት ከቀትር በኋላ አብዛኛውን ጊዜ በእግራችን እየሄድን አንዳንድ ጊዜም እንደድመት እየቡዋጠጥን ከብዙ ድካም በኋላ አንድ ተራራ ለመዞር ቻልን። በየተራሮቹ መካከል ሰፋፊ ሸለቆዎች አገኘን። ባንደኛው ውስጥ ወንዝ ስላለ ልዩ ልዩ ሰብል ተዘርቶበት የሚታይ ብዙ እርሻ አለ። በዚህ መንገድ ያለፍነው ብዙ ጊዜ ስለሆነ መሬቱ ዓመቱን በሙሉ የዘሩበትን ሁሉ የሚያበቅል መሆኑን ተረድተናል። አንዳንዱ እርሻ አዲስ የተዘራ ነው፤ እልፍ ሲሉ ያለው ቡቃያ ነው፤ እልፍ ሲሉ በደንብ የበቀለና ለመታረም የደረሰ ነው፤ እልፍ ሲሉ የሸተው ይታያል፤ እልፍ ሲሉ በስሎ ማጭድ የሚጠብቅ ነው፤ እልፍ ሲሉ ታጭዶ የተከመረ ወይም የተወቃ ነው። ስንዴውም ገብሱም አተሩም ሌላውም እህል እንደዘሩት ይበቅላል። መሬቱ ዓመቱን ሁሉ ረግረግ ሆኖ ስለሚቆይ እህል ሲዘራ ጊዜ አይጠበቅም። ስለዚህ መሬቱ ይህን የመሰለ ምቾት ስለሚሰጥ አንዱ አዝመራ ሲታጨድ ሌላው ይዘራል።

በተጓዝንበት መንገድ በግራና በቀኝ በሚገኙት ተራራዎች ጥግ ማዶና ማዶ እያንዳንዳቸው ጥሩ ሆነው የተሠሩ የራሳቸው ቤተ ክርስቲያኖች ያላቸው ብዙ መንደሮች ይታያሉ። በቤተ ክርስቲያኖቹ ዙርያ ታላላቅ ዛፎች ሁልጊዜ ስለሚገኙ ወደዚያ መሄድ ሳያስፈልግ በዛፎቹ ምልክት ብቻ ቤተ ክርስቲያኖቹ የት እንደሚገኙ ለመረዳት ይቻላል [1]።

<u>ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት፤ ስለአንኮና ቤተ ክርስቲያን፤ በአንጎት ግዛት የመገበያያው ገንዘብ ብረትና ጨው ስለመሆኑ፤ በዋሻ ውስጥ ስለ ሚገኝ አንድ ገዳም።</u>

በዚያው ሳምንት ውስጥ ረቡእ መንገዳችንን ቀጥለን ብዙ የማሽላና የባቄላ እርሻ በሚታይበት አንድ ትልቅ ሸለቆ ደረስን። ይህ ሸለቆ አንኮና ይባላል። ሸለቆውን ከተሻገሩ በኋላ በአንድ ተራራ ላይ የአንኮና ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። በቤተ ክርስ ቲያኑ ብዙ ሊቀ ካህናት፤ መነኩሴዎችና መነኩሲቶች አሉት። ከዚህ ወደፊት ያገኘናቸው ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ የነገሥታት ቤተ ክርስቲያኖች እየተባሉ ይጠራሉ፤ በውስጣቸውም ደብተራዎችና ሊቀ ካህት በብዛት ይገኛሉ። አሠራራቸው ደስ የሚያሰኝ ሁለት ደወሎች በዚያ አሉ፤ እነዚህ ደወሎች የተሰቀሉት በጣም ወደምድር ዝቅ ብለው ነው። ከዚህ በፊት ካየናቸው ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ እነዚህን የመሰሉ ከቶ አላየንም። በዚህ ከተማ በየሳምንቱ ሐሙስ የሚውል ገበያ ስለነበር በተባለው ዕለት በዚያ ቦታ ቆየን።

በአንኮናና በመላው በአንጎት ግዛት እንደ ገንዘብ ተቆጥሮ የሚገበያዩበት በአካፋ መልክ የተሠራ ብረት ነው። ይህ ብረት ተጨፍልቆ ሌላ ዕቃ መሥርያ ካልሆነ በስተቀር ምንም አይጠቅምም። ከኛ አገር ገንዘብ ጋር ሲመዛዘን አንድ ድራክም አስር፤ አስራ አንድ፤ አንዳንድ ጊዜም አስራ ሁለት ብረት ይመነዘራል። በሕንድ አገር ግን እኩል በኩል ይመነዘራል፤ ማለት አንድ ክሩዘይሩ በአንድ ብረት ይመነዘራል ማለት ነው። አሞሌ በመላ ኢትዮጵያ እንደገንዘብ የሚሠራበት ነው እንዳልነው ሁሉ በዚህ ግዛትም ይሠራበታል፤ ይሁን እንጂ የአሞሌው ግምት ከብረቱ በጣም ያነሰ ነው። (አንድ ብረት በስድስት ወይም በሰባት አሞሌ ይመነዘራል)።

ከነበርንበት ቦታ ቀጥታ ሲሄዱ በስተምዕራብ በኩል በጣም ትልቅ የሆነ ብዙ ኤስፓርቶ አለበት በሚባል ቡግና በተባለ ብርዳምና ተራራማ አገር አለ። ከዚያ ኤስፓርቶ ለዓይነት ያህል ጥቂት አምጥቼ

ከኛ ጋር ይሄዱ ለነበሩት የጄኖቫ ሰዎች ባሳያቸው በመገረም ይህ በአሊካንቴ (እስፓኝ) ከሚገኘው የበለጠ ነው፤ ይህን የመሰለ ከዚህ በፊት አይተን አናውቅም ሲሉ መሰከሩ። በየተራሮቹ ጫፍ ገብስ በየሸለቆዎቹ ጥሩ ዓይነት ስንዴ ይበቅላል። ላሞች፤ ፍየሎቹና በጎቹ በፖርቱጋል በዶሩና በሚኙ አውራጃዎች መካከል ማያ በተባለው ቀበሌ እንዳሉት ከብቶች በጣም ትንንሾች ናቸው። ይህ አቢሚራስ የተባለ ቦታ በአንጎት ግዛት አንጎትራስ ከተባለ ቀበሌ በስተግርጌ በኩል የሚገኝ ስፍራ ነው። ቡግና ርዝመቱ የስድስት ቀን ስፋቱም የሶስት ቀን መንገድ ነው። ከአክሱምና ከዙርያው ግዛቶች ቀጥሎ የክርስቲያን አውራጃ የሆነ ይህ ቦታ ነው ይባላል።

ምንም እንኳ ይህ አውራጃ በመጀመርያ ሲመለከቱት የደረቅነትና የምስኪንነት መልክ ቢታይበትም በአውራጃው የኖሩ ነገሥታት እንደ አክሱም ነገሥታት በዚሁ ቤተ መንግሥት ነበራቸው ይባላል። እኔ ራሴ ያየኋቸው አንዳንድ ጥሩ ሕንፃዎች ይገኛሉ። ከሁሉ አስቀ ድመን ያየነው አከቴ በተባለ ቦታ ላይ በሚገኝ ባንድ ትልክ ተራራ ላይ ባለ ዋሻ ውስጥ የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ያለበት አንድ እጅግ የሚያምር ገዳም አለ። ይህ ገዳም የይኩኖ አምላክ ገዳም ይባላል።

ቤቱ የውበቱን ያህል ትልቅ አይደለም፤ እንደሌሎቹም ገዳሞች ገቢ የለውም፤ ይሁን እንጂ ብዙ መነኩሲቶችና መነኩሴዎች ይገኙበታል። መነኩሴዎቹ የሚኖሩት ከዋሻው ላይ በሚገኝ ዙርያውን በአጥር በተከበበ መውጫውና መግቢያው አንድ ብቻ በሆነ በአንድ ተራራ ላይ ነው። መነኩሲቶቹ ደግሞ ከዋሻው በታች ባለ አጥር በሌለው በአንድ ገደል ላይ በሚገኝ ቦታ ነው የሚኖሩት። ከላይ እንደገለጽሁት ገዳሙ ገቢ የሌለው በመሆኑ መነኩሴዎቹና መነኩ ሲቶቹ ምድሩን ሲቆፍሩና ልዩ ልዩ የግብና ሥራ ሲያከናውኑ ይታያሉ። እንዲሠሩ በዚያም እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ለገዳሙ ያላቸው ፍቅር ብቻ ነው። ይህ በዋሻ ውስጥ ያለ ገዳም ዙርያውን ሊያስሄድ በሚያስችል በመስቀል መልክ የተሠራ ነው። ከገዳሙ በር አምስት ብራሳ ርቆ የተሠራ ቁመቱ ከአስር እስከ አስራ ሁለት ብራሳ የሆነ

ቁመቱ ከዋሻው ቁመት የሚተካከል አንድ ግድግዳ አለ። መነኩሲቶቹ ቁመው የሚያስቀድሱበትና ቁርባን የሚቀበሉበት በውስጥ በኩል በዚያ ግድግዳ ጥግ ነው። የመነኩሲቶቹ ቦታ በስተደቡብ በኩል ነው። ቤተ ክርስቲያኑ በስተምስራቅና በስተምዕራብ በኩል ስለሆነ ቦታው በስተ ደቡብ በኩል ሆነ። ከዋሻው በላይ ከሚገኝ ከአንድ ተራራ እየፈለቀ ዓመቱን በሙሉ ሳይደርቅ ከገዳሙ በስተቀኝ በኩል ወደመነኩሲቶቹ መኖርያ የሚፈስ አንድ ወንዝ አለ። በፊት እንዳየናቸው ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ የዚህ ገዳም ቤተ ክርስቲያኖችም በሜዳ ላይ የተሠሩ ይመስል ሶስት በሮች (ማለት አንድ ዋና ሁለት የጎን) አሉት።

ይህ በመስቀል መልክ ነው የተሠራው ያልሁት ገዳም ባሠራሩና በስፋቱ በብራጋ ከተማ በፖርቱጋል ከሚገኘው ከቅዱስ ፍሩትዎዙ ገዳም ይመሳሰላል።

ምዕራፍ ሃምሳ ሶስት፤ አንድ ንጉሠ ነገሥትና አንድ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የተቀበሩት በዚሁ ግዛት ውስጥ ስለሚገኝ ስለ አንድ ሌላ የዋሻ ቤተ ክርስቲያን።

ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ይህ ገዳም ወደ ምዕራብ በኩል የሁለት ቀን መንገድ ርቆ የሚገኝ በሌላ ዋሻ ውስጥ የተሠራ አንድ ትልቅና ጌጠኛ ቤተ ክርስቲያን አለው። በኔ አገማመት ሶስት ትልልቅ መርከቦች ከነወጋግራቸው ባንድነት ቢገቡ ዋሻው ይችላቸዋል። ወደዚያ የሚያስገባው መንገድ ሁለት ሠረገላዎች ጎን ለጎን ቢነዱበት ሊያሳልፋቸው ይችላል። ወደዋሻው የሚወስደው ሁለት ሌግዋ የሚሆነውን ዳገት መውጣት በእውነተኛው አድካሚ ነው። እኔ ዳገቱን ወደላይ ስወጣ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ብርዳም ባያደርገው ኖሮ በእውነተኛው እሞት ነበር። አንድ ኃይለኛ ሰው ወገቤን በገመድ አሥሮ እየሳበኝ እኔም በእግሬ እያገዝሁት እንደምንም በብርቱ

ድካም ልወጣ ቻልሁ። በቅሎቹ ቀድመው የሄዱ እንደሆነ ምናልባት ተንከባለው ይወድቁበኛል በማለት ስለሰጋሁ አንድ ሰው ከኋላ ሆኖ ይነዳቸው ነበር። ተራራውን መውጣት የጀመርነው በማለዳ ጸሐይ ከመውጣቱ በፊት ነበር፤ ነገር ግን በዳገቱ ምክንያት ገና መንገዱን ሳንጨርስ እኩለቀን ሆነ።

በዋሻው ውስጥ ያለ ያ ቤተ ክርስቲያን በጣም ትልቅና በደንብ የተከደነ ቅስቶቹም ጥሩ ሆነው ከተጠረቡ ድንጋዮች የተሠሩ ሲሆኑ፤ መሠውያዎቹ በደንብ የተጌጡ ሶስት ማለፊያ ቅድስተ ቅድስታት አሉበት። የዋሻው ዋና በር በምስራቅ በኩል ሲሆን የቅድስተ ቅድስ ታቱም ጀርባ በዚያው በኩል ነው። የጥዋት ጸሎት በሚደረግበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ የገባ ሰው ያለ መብራት ምንም ሊያይ አይች ልም። ስለዚህ በቅዳሴ ጊዜ ጥዋፍ እያበሩ ነው የሚያገለግሉ። ይህ ብዙ ገቢ ያለው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን በመሆኑ ብዙ አገልጋዮች አሉት። ሰው እንደሚያወራው እኔም ብዛታቸውን እንዳየሁት ሁለት መቶ ደብተራዎች አሉ ይባላል። መነኩሴዎችም መኖራቸውን አይ ቻለሁ እነዚህን ሁሉ ከበላይ ሆኖ የሚያስተዳድራቸው አንድ ሊቀ ካህናት ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን ይምርሃነ ክርስቶስ ይባላል፤ የክርስቶስ መንገድ ማለት ነው።

በዋሻው በኩል ሲገቡ ፊት ለፊት ያለው ቅድስተ ቅድስታቱ ነው፤ ሲገቡ በስተቀኝ በኩል ሁለት በስዕል ያጌጡ ክፍሎች አሉ፤ እነዚህ ክፍሎች ያን ቤተ ክርስቲያን ያሠራውና መኖርያውንም በዚያ ዋሻ ውስጥ ያደረገ ያንድ ንጉሠ ነገሥት መኖርያ ነበሩ ይላሉ። በመሠውያው በስተቀኝ በኩል በጣም የተከበሩ ሶስት መቃብሮች አሉ። እነዚህን የመሰሉ መቃብሮች በመላ ኢትዮጵያ ገና አላየንም፤ ከመቃብሮቹ አንዱ ከፍ ብሎ ስለሆነ የሚገኘው ወደላይ የሚወስዱ አምስት ደረጃዎች በዙርያው አሉ። ይህ መቃብር በወርቀዘቦና በከፈይ ተሸፍኖአል፤ ከዚያም በላይ አንድ ጨርቅ ደርበውበት ይህ ጨርቅ መቃብሩን አልብሶ በመሬት ላይ ተንዘርፍፎአል። መቃብሩ እንደዚህ ያጌጠበት ምክንያት የሙዋቹ ዓመት የሚከበርበት ቀን ስለነበር ነው። በዚያ የተቀበረው አብርሃም የተባለ ንጉሠ ነሥት

ነው ይባላል። ሌሎቹ ሁለቱ በዋሻው ውስጥ የሚገኙት መቃብሮች በአሠራራቸው ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ አንደኛው አራት ሌላውም ሶስት ደረጃዎች አላቸው። ሶስቱም መቃብሮች የሚገኙት ከዋሻው መካከል ነው። ከሁለቱ መቃብሮች አንዱ የዚያን ንጉሠ ነገሥት ብጽእና በመስማት አንድ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሊጎበኘው መጥቶ በዚያው ስለሞተ የተቀበረበት ነው ይባላል። በጣም ትንሹ ዝቅ ብሎ የሚገኘው የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ የተቀበረችበት ነው ይባላል።

አብርሃም የተባለው ነጉሠ ነገሥት በየቀኑ በቅዳሴ እያገለገለ አርባ ዓመት ሙሉ ሠርቱዋል ይባላል። የንጉሠ ነገሥትነቱን ሥልጣን ከተወ በኋላ በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ በየቀኑ ያገለግል ነበር ይባላል። ይህ ሁሉ ሃተታ በገድሉ ተጽፎ ይገኛል፤ እኔ ሌላ ሥራ ሳልሠራ በዚያ በቆየሁበት ሁለት ቀን ያን ገድል እያነበቡ ስልገ ለጹልኝ ታሪኩን በከፊል ልረዳው ችያለሁ።

እንደሚወራውና ገድሉም እንደተነበበልኝ ለዚያ ንጉሠ ነገሥት ከተፈጸሙለት ተአምራት አንዱ በአርባ ዓመት የብጽዕና ጊዜው ምዕመናንን በሚያቆርብበት ቁጥር መላእክት ነበሩ ሥጋ ወደሙን የሚያቀብሉት ይባላል። በዚያ መጽሐፍ መጀመርያ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ በመሠውያው ፊት ቆሞ የሰሞነኛ ቄስ ልብስ ለብሶ እንደነበረ የሚያሳይ ስዕል ተስሎአል። በዚያ ስዕል ላይ በአንድ መስኮት ውስጥ ሥጋወደሙን የሚያቀብል ይመስል አንድ እጅ ቅዱስ ጻሕልና ሕብስት እንደያዘ ብቅ ብሎ ይታያል። በመቅደሱ ውስጥም ይህንኑ የመሰለ ስዕል ይታያል። ካህናቱ እንደነገሩኝ የቤተ ክርስቲያኑ የውጭው ክፍል የተሠራበት ድንጋይ ከየሩሳሌም ነው የመጣው፤ በሁኔታውም እንደየሩሳሌም ድንጋይ ጥቁርና ጥሩ ዓይነት ነው። እኔን እንዲረዳና እንዲያገለግል የታዘዘው ሰው እየመራኝ አንድ ቀን ከዚያ ተራራ ጫፍ ወጣሁና የድንጋይ ሽርፍራፊዎችና ቋጥኝ ይታይበት በነበረ ጥንት ድንጋይ በሚፈለጥበት አንድ ጎድጓዳ ቦታ ደረስሁ። ያን ሽርፍራፊ በጄ ይዤ ሰብሬው ደህና አድርጌ ከመረመርሁት በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ ከተሠራበት ድንጋይ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ስላረ ጋገጥሁ የታነጸው ከዚህ ድንጋይ እንጂ በእውነቱስ እንደነገሩኝ

ከየሩሳሌም በመጣ ድንጋይ አለመሆኑን ተረዳሁ። ያ ንጉሠ ነገሥት ከገባሮቹ ላይ ግብር የማይቀበል መሆኑንና አንዳንዶችም የሚያመጡለትን ግብር ለድሆች የሚያከፋፍል መሆኑን፤ ራሱም የሚተዳደረው ከግል ሁዳዱ ከሚመጣለት ሐብት መሆኑን የሚገልጽ በገድሉ ላይ ተጽፎ ይገኛል። ከዚህም በላይ ከመጽሐፉ እንደተነበበልኝ ወደፊትም እንደምገልጸው ወራሽህ ከሆነው ከበክር ልጅህ በስተቀር ዘመዶችህን ሁሉ በግዞት ማኖር አለብህ የሚል ራእይ የተገለጸለት መሆኑ ተጽፎአል።

ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ዝና ብዙ ሰምቼ ስለነበር የሰማሁትን በዓይኔ ለማየት ስል አንድ በዓል በሚከበርበት እሁድ ዕለት ነበር የሄድሁት። በዚያኑ ዕለት ሃያ የሚሆኑ ምዕመናን ለቁርባን መጥተው ነበር። ከላይ እንደገለጽሁት ቀኑ እሁድ ስለነበር ሊነጋ ሲቃረብ ቅዳሴ ገብተው ወዲያውኑ በሶስቱ በሮች ላይ ሆነው ቀኑን በሙሉ ሲያቆርቡ ውለው ከመሸ በኋላ ጨረሱ። ይህ ሁሉ ሲፈጸም ምሳዬን ለመብላት አንድ ጊዜ ወጣሁ እንጂ ከዚያ አልተለየሁም ነበር።

ምዕራፍ ሃምሳ አራት፤ በቡግና አውራጃ ላሊበለ ስለሠራቸው ቤተ ክርስቲያንና ስለጎልጎታም ቤተ ክርስቲያን።

ከይምረሃነ ቤተ ክርስቲያን ያንድ ቀን መንገድ ከሄዱ በኋላ ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍለው የተሠሩ (እነርሱን የሚመስል በዓለም ውስጥ ከቶ ሌላ ሕንፃ የማይገኝ) ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ፤ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤ ቤተ አማኑኤል፤ ቤተ መድኃኔ ዓለም፤ ቤተ ማርያም፤ ቤተ መስቀል፤ ቤተ ጊዮርጊስ፤ ቤተ ጎልጎታ፤ ቤተ ልሄም፤ ቤተ መርቆርዮስና ቤተ ደናግል። ከሁሉም የሚበልጠው የላሊበላ ቤተ ክርስቲያን ነው። ላሊበላ ከዚህ በፊት ከጠቀስነው አብርሃም ከተባለ ንጉሠ ነገሥት በፊት የነገሠና ሰማንያ ዓመት ያለማቋረጥ አገሩን የገዛ

ነበር ይባላል። እነዚህን ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ ያሠራው ይኸው አጼ ላሊበላ የተባለው ንጉሠ ነገሥት ነው ይላሉ። የላሊበላ አጽም የሚገኘው በስሙ በሚጠራው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጎልጎታ በተባለው ከዚያ ከሚገኙት ሁሉ በአነስተኛው ውስጥ ነው፤አሠራሩም ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው፤ ሕንፃው ቁመቱ አንድ መቶ ሃያ፤ ስፋቱም ሰባ ሁለት ስንዝር ከሆነ ካንድ ቋጥኝ ተጠርቦ የተሠራ ነው። ጣርያው በአምስት ምሰሶዎች የተደገፈ ሲሆን አንደኛው በመካከል ሁለቱ በግራ ሌሎቹ ሁለቱ በቀኝ ቁመው የኪናሽ መልክ አላቸው። ጣርያውም እንደወለሉ ሜዳ ነው። ግድግዳዎቹ መስኮቶቹና መዝጊያዎቹ በሐረግ አምረው አጊጠዋል፤ ይህ ጌጥ በጣም ቆንጆ በመሆኑ አንጥረኛም በወርቅ ወይም ሻማ ሠሪም በሰም ይህን የመሰለ ሐረግና ጥልፍልፍ ነገር ለመሥራት የሚችል አይመስለኝም። የንጉሠ ነገሥቱ መቃብር በጋሊሴያ ጠቅላይ ግዛት (ስፓኝ) ዋና ከተማ በካምፖስቴላ በቅዱስ ያዕቆብ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን መቃብር ይመስላል፤ አሠራሩም ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው፤ የቅኔ ማህሌቱ ወለል ከመቅደሱ ዝቅ ያለ ነው። ከመቅደሱ ወደዚሁ የሚያወርድ በር አለ። ከቅኔ ማህሌቱ ግድግዳ ከፍ የሚል ነገር ግን ከመቅደሱ የሚተካከሉ ሶስት መስኮቶች አሉ። የመስኮቶቹ ፉካ ርዝመት ከቤተ ክርስቲያኑ ወለል እኩል ነው። ከነዚህ መስኮቶች በአንዱ ውስጥ ወደጸሐይ ሲመለከቱ መቃብሩ ከታላቁ መሠውያ በስተቀኝ በኩል ይታያል። ከመቅደሱ ወለል መካከል ወደምድር ቤት የሚያወርድ የሚመስል አንድ ትልቅ በር አለ። ይህ በር ጽላት በሚመስል ልክክ አድርጎ በሚዘጋ ድንጋይ ተገጥሞአል። ያ በር ወደ ምድር ቤት መውረጃ ቢሆንም በዚያ መግባት ለማንም አይፈቀድም። እንዲያውም ያን በር ወይም ድንጋይ ለመክፈት የሚቻል አይመስልም። ያ ድንጋይ ከመካከሉ ከላይ እስከታች ቀዳዳ ስላለው ያን ቀዳዳ በመለካት የድንጋዩ ውፍረት ሶስት ስንዝር መሆኑን ተረድቻለሁ። ምዕመናኑ በዚያ ብዙ ሊይዝ በማይችል ቀዳዳ ውስጥ እጃቸውን ያገባሉ፤ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ብዙ ተአምራት ይፈጸማል ስለሚባል ነው፤ ከምስራቁ በር ወደፊት ሲሄዱ በስተግራ በኩል ቤተ ክርስቲያኑ ከታነፀበት ድንጋይ የታነፀ አንድ መቃብር አለ፤ ይህ መቃብር በአስተናነፁ የክርስቶስን መቃብር መስሎ ነው የተሠራው

ይባላል። ስለዚህ እንደዚያ እንደሚያከብሩትና እንደሚያስታውሱት እንደ ክርስቶስ መቃብር አድርገው በመገመት ይህንንም የሚገባውን ፍርሃትና ክብር ይሰጡታል።

በሌላ በኩል በሕንፃው ድንጋይ ላይ የተቀረጹ ሁለት ታላላቅ ምስሎች አሉ። እነዚህን ምስሎች በማየት የምንደነቅ መስሎ ዋቸው አስጎበኙን። ለነዚህ ምስሎች (አንዱ የቅዱስ ጴጥሮስ ሌላው የቅዱስ ዮሐንስ) ሕዝቡ ያለው ክብር ከፍ ያለ ነው።

ይህ ቤተ ክርስቲያን ስድስት ምሰሶዎች ማለት ሶስት በግራ ሶስት በቀኝ የደገፉት ማለፊያ ሆኖ የተሠራ ባለቅስት ጣርያና የራሱ ታላቅ ቅድስተ ቅድስታት አለው። መቅደሱ በደንብ የታነፀና የመካከሉም ቅስት ከፍ ብሎ በሚገባ የኳኋን የተሠራ ነው። መስኮቶቹና በሮቹ (ማለት ዋናውና አንድ የጎን በር) በጌጥ አሸብርቀው የተሠሩ ናቸው። ሌላው በር ግን ለቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ አገልግሎት ውሎአል። ስፋቱና ርዝመቱ እኩል የሆነው ይህ መቅደስ ከዳር እስከዳር ያለው ስፋት ሃምሳ ሁለት ስንዝር ይሆናል። ከዚሁ መቅደስ በላይ በሕንፃው ጫፍ በቁመቱ ልክ የሆኑ ብዙ መስኮቶች ያሉበት የደወል ቤት የሚመስል በተጨማሪ አንድ ሌላ መቅደስ አለ። የመስኮቶቹ ስፋትና ርዝመት እኩል ስለሆነ የያንዳንዳቸው ስፋት አስራ ሁለት ስንዝር ነው።

የዚያ ቤት ክርስቲያን መቅደሶች፤ መሠውያዎች፤ አጎበርና ምሰሶዎች ሳይቀሩ ባንድ ድንጋይ ተጠርበው የተሠሩ ናቸው። ከቤተ ክርስቲያኑ ዙርያ ቁመቱ ከሕንፃው እኩል የሆነ ከቋጥኝ ተፈልፍሎ የወጣ አራት ማዕዘን መልክ ያለው አጥር አለ። የአጥሩ ግድግዳዎች በሙሉ የገበቴ አፍ የሚያህሉ ቀዳዳዎች አሉባቸው።

እነዚህ በትንንሽ ድንጋይ የተገጠሙ ቀዳዳዎች መቃብሮች ናቸው ይባላል፤ አንዳንዶቹ ቀደም ብለው ሌሎቹም በቅርቡ የተደፈኑ ስለሆኑ በእውነቱ መቃብር ይመስላሉ። በአጥሩ ግቢ የሚያስገባ በቋጥኙ ውስጥ ለውስጥ ከሥር ወደላይ ተሰርስሮ የተሠራ ርዝመቱ አስራ

ሶስት ስንዝር የሆነ አንድ አዘቅት መተላለፊያ አለ። ያ ቋጥኝ በፖርቱ (ፖርቱጋል) አጠገብ እንደሚገኘው አለት ጠንካራና ትልቅ ቢሆንም መተላለፊያው በሙሉ ተጠርቦ የተሠራ ነው እንጂ የተቆፈረ አይደለም።

ምዕራፍ ሃምሳ አምስት፤ ስለመድኃኔ ዓለምና ስለጎረቤት ቤተ ክርስቲያኖች፤ ስለአጼ ላሊበላ ልደትና ከአገሩም ስለሚሰበሰበው ቀረጥ።

የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ብቻውን የሚገኝ ከገደል ተጠርቦ የወጣ ቤተ ክርስቲያን ነው። ርዝመቱ ሁለት መቶ ስንዝር ስፋቱም አንድ መቶ ሃያ ስንዝር ነው። ሕንፃው አምስት ቅስቶች አሉት፤ እያንዳንዱ ቅስት በረድፍ የቆሙ ሰባት አራት ማዕዘን ምሰሶዎች አሉበት፤ እያንዳንዱ ምሰሶ አራት ስንዝር ስፋት አለው፤ የግድግዳውም ውፍረት ከዚሁ እኩል ነው። ምሰሶዎቹና ከጣርያው አንድ ስንዝር ያህል ዝቅ ብለው የሚገኙት ቅስቶችም እንዲሁም እጅግ ከፍ ብለው የተሠሩት ቅስት ጣርያዎች ማለፊያ ሆነው የተሠሩ ናቸው፤ በተለይም ከመካከለኛው ቅኔ ማህሌት በለይ የሚገኘው በግራና ቀኙ ካሉት ሁለቱ ከፍ ብሎ የተሠራው ጣርያ በጣም ውበት አለው። ቁመቱም ደስ የሚያሰኝ ነው። ይህ ጣርያ መስተዋትና ቁልፍ፤ ጽጌ ረዳና ሌላም ልዩ ልዩ ነገሮች መሰለው ተጠርበው የወጡ በሐረግ ያጌጡ ምስሎች ይታዩበታል። በግራና በቀኝ ያሉ በሐረግ ጌጥ አሸብር ቀው የሚያምሩ ረዥምና ጠባብ የሆኑ መስኮቶች አሉ። እነዚህ መስኮቶቾ ከግቢና ከውጭ ሰፊ ሆነው ከመካከል ጠባብ ስለሆኑ በምሽግ ላይ የተሠሩ የቀስት ማሾለኪያ ቀዳዳዎችን ይመስላሉ። የቤተ ክርስቲያኑ የምስራቁ ክፍል በጣም ከፍ ያለ ነው፤ በአራት እግር ተደግፎ ከሚገኘው መሠውያ በላይ ያለው አጎበር እንዲሁ ከፍ ብሎ ነው የተሠራው። በሌሎቹ ቤተ ክርስቲያኖች ቅድስተ ቅድስታቱና መሠውያው በመጋረጃ አይሸፈኑም። ዋናው መግቢያ በግራና በቀኝ በጣም ትልልቅ ድጋፎች አሉት። በአሠራራቸው

እንደሌሎቹ የሆኑ እየጠበቡ የሚሄዱ ቅስቶች ያሉበትን አንድ በር ተከትለው ሲሄዱ ቁመቱ ዘጠኝ ስንዝር ስፋቱም አራት ስንዝር ተኩል ብቻ በሆነ መዝጊያ ይደረሳል። ሌሎቹ አቋራጭ በሮች ግን እንደዋናው በር እየጠበቡ የሚሄዱ አይደሉም።

ከቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ አስራ ሁለት ስንዝር ርቀው የሚገኙ በግማሽ ጨረቃ መስል ረድፍ የቆሙ ሰባት ምሰሶች አሉ፤ በየምሰሶዎቹ መካከል ቅስት ተሠርቶ ከቤተ ክርስቲያኑ ጫፍ ወደነዚህ ቅስቶች የሚደፉ ጣርያ ተሠርቶአል። ይህ በቅስት የተሠራ ጣርያ በአሠራሩ አስደናቂ በመሆኑ በለስላሳ ጥርብ ድንጋይ እንኳ ከዚህ የበለጠ ሊያምር አይችልም። በውጭ በኩል ያሉት ቅስቶች ቁመት የሁለት ጦር ቁመት ያህላል። ይህ ቤተ ክርስቲያን በታነፀበት ቋጥኝ አንድም ባዕድ መልክ አይታይም፤ በጠቅላላው ከአንድ እብነበረድ የተሠራ ይመስላል። ገረገራው እንኳ ሳይቀር ከዚያ ከአንድ ድንጋይ ተጠርቦ የወጣ ነው፤ የገረገራው የዳር እስከዳር ስፋት ስልሳ ስንዝር ሲሆን ከዋናው በር ፊት ለፊት ያለው ስፋት ደግሞ አንድመቶ ስንዝር ነው። በዚያ ቤተ ክርስቲያን አናት ጣርያው ሊያርፍበት በሚገባው ቦታ ላይ እንደሌሎቹ ቤተ ክርስቲያኖች በዳር በሚገኙት መቃብሮች ላይ የሚደፉ በያንዳንዱ በኩል ዘጠኝ ቅስቶች ስላሉ ከበታቻቸው ታዛ ሠርተዋል። ወደቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚያስገባው መንገድ በድንጋዩ ውስጥ ለውስጥ ተሠርሥሮ የተሠራ ነው። የዚህ መንገድ ርዝመት ከደጀ ሰላሙ እስከ ቤተ ክርስቲያኑ ሰማንያ እርምጃ፤ ስፋቱም አስር ሰው ጎንለጎን የሚያስሄድ ቁመቱም ካንድ ጦር ቁመት እኩል ነው። ለመንገዱ ብርሃን የሚሰጡ አራት ቀዳዳዎች በላይ በኩል አሉ። ከቤተ ክርስቲያኑ ዙርያ ካለ ከዚህ ቋጥኝ እልፍ ሲሉ ዙርያውን ብዙ መንደሮችና የገብስ እርሻዎች አሉ።

ቤተ ማርያም ምንም እንኳ የቤተ መድኃኔ ዓለምን ያህል ትልቅ ባይሆንም በአሠራሩ በጣም የሚያምር ነው። ከሶስቱ ቅኔ ማህሌቶች የመካከለኛው በጣም ከፍ ያለና ከቋጥኙ ተጠርበው የወጡ ልዩ ልዩ ሐረግና የጽጌረዳ ምስሎች አሉበት።

በያንዳንዱ ቅኔ ማህሌት ዳርቻ አምስት ምሰሶዎች አሉ፤ በምሰሶዎቹ ላይ ጌጠኛ ሆነው የተሠሩትን ጣርያዎች የሚደግፉት ቅስቶች ያርፉባቸዋል። በቅኔ ማህሌቱና በቅድስተ ቅድስታቱ መካከል በሚገኘው በጣም ትልቅ በሆነ ምሰሶ ላይ በሐረግ ያጌጠ አንድ አኀበር አለ፤ ይህ የሐረግ ጌጥ ቁልጭ በማለቱና በማማሩ አንጥረኛ በሰም ላይ አፍስሶ የሠራው እንጂ በእውነተኛውስ ከድንጋይ ተጠርቦ የወጣ አይመስልም። እንደ ቤተ መድኃኔ ዓለም በዚህም በያንዳንዱ ቅኔ ማህሌት መጨረሻ አንዳንድ ቅድስተ ቅድስታት አሉ። የነዚህ አቀማመጣቸው በያንዳንዱ በር ላይ ቢሆንም በአሠራራቸውና በስፋታቸው ከመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያኖቹ ተመሳሳይ ናቸው፤ በውጭ በኩል ስድስት ምሰሶዎች አሉ፤ ከነዚህ ሁለቱ ከግድግዳው ጋር የተያያዙ ሲሆኑ አራቱ ግን ተራርቀው ቆመው በድንጋይ ጣርያ ተከድነው ለቤተ ክርስቲያኑ በር በረንዳ ሆነውታል። በምሰሶዎቹ ላይ አርፎ የሚገኘው ያ የድንጋይ ጣርያ አስራ አምስት ስንዝር ርዝመት ይህንኑ የሚያህል ስፋት አለው። ቁመቱ ከቤተ ክርስቲያኑ እኩል የሆነ ከድንጋዩ ተጠርቦ የወጣ ዙርያውን አጥር አለው። ቤተ ክርስቲያኑ ሰማንያ ስንዝሩ ርዝመትና ይህንኑ ያህል ስፋት አለው። ከደጀሰላሙ ፊትለፊት ለነዳያን ምግብ የሚሰጥበት ከቋጥኙ ተጠርቦ የተሠራ ቤት አለ፤ በደጀ ሳላሙ ላይ ያልሁበት ምክንያት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚወስደው ከድንጋዩ ውስጥ ለውስጥ ተሰርስሮ የወጣው መንገድ በር ያለው በዚሁ ቤት ውስጥ በመሆኑ ነው። ከቤተ ክርስቲያኑ በግራና በቀኝ በኩል ባሉት ሁለት በሮች ፊት ለፊት ሌሎች ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች አሉ። በዚያ አካባቢ የሚገኙትን ሁሉ የሚያስተዳድር የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ነው። ሁሉም ብዙ ካህናት ይገኙባቸዋል፤ ከቤተ ማርያም በስተደቡብ በኩል የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን በቁመቱና በስፋቱ ከዚሁ ከቤተ ማርያም የሚወዳደር ነው። ሶስት ቅኔ ማህሌቶች አሉበት፤ እያንዳንዱ በደንብ የተጠረቡ ሶስት ማሰሶዎች በረድፍ አሉበት። ቤተ ክርስቲያኑ እንደ ሌሎቹ ሳይሆን አንድ ቅድስተ ቅድስታትና መሠውያ ብቻ ነው ያለው። ማለፊያ ሆኖ የተሠራው ዋናው በር ወደፊት የሚመራ መንገድ የለውም። በዚህ ፈንታ ወደእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን የሚመራ በቋጥኙ ውስጥ ለውስጥ የሚያልፍ በረንዳ አለው። ይህ

በረንዳ ወይም ፉካ ውስጡን ብዙ የሚያስሄድና ጨለማም ነው። መግቢያው ከመሬቱ ከፍ ብሎ ስለሚገኝ ወደዚያው የሚያስወጡ ከቋጥኙ ተጠርበው የተሠሩ አምስት ደረጃዎች አሉ። ወደ እመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በኩል ባለው ጎኑ አንድ መልካም በርና ሁለት መስኮቶች ሲኖረው በስተጓሮውና በሌላው ጎኑ ግን ከቋጥኙ ጋር እንደተያያዘ ይገኛል።

ይህ ከዚህ በላይ ያተትነው ቤተ ደናግል ነው። ከእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በስተ ሰሜን በኩል የሚገኘው ደግሞ ቤተ መስቀል ነው። ርዝመቱ ሰላሳ ስምንት ስንዝር ብቻ የሆነ በቅኔ ማህሌቶች ፊንታ አንድ ሰፊ ክፍል ብቻ ያለው ሕንፃ ነው። ልሙጥ የሆኑውን ጣርያ የሚደግፉትን ቅስቶች የተሸከሙ ሶስት ምሰሶዎች በመካከል ቁመዋል። በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በኩል ባለው ጎኑ አንድ ማለፊያ የኋላ በርና ጥሩ ሆነው የተሠሩ መስኮቶች አለው፤ እንደ ሌሎቹ ቤተ ክርስቲያኖች አንድ መሠውያ ብቻ ነው ያለው፤ ዋና በሩም ማለፊያ ሆኖ ነው የተሠራው። ከዚህ በር ወደውጭ የሚመራ መንገድ ወይም ትርፍ ቦታ ባለመኖሩ መውጫው እንደበረንዳው ሆኖ ከተሠራው መንገድ ጀምሮ በድንጋዩ ውስጥ ለውስጥ ተጠርቦ የተሠራ ጨለማ ፉካ ነው።

ቤተ አማኑኤል ከውጭም ሆነ ከግቢ አምሮ የተሠራ አርባ ሁለት ስንዝር ርዝመት ሃያ ስንዝር ስፋት ያለው ትንሽ ሕንፃ ነው። ሶስት ቅኔ ማህሌቶች ያለው ሲሆን የመካከለኛው ከፍ ያለና ጣርያው በቅስት የተደገፈ ነው፤ በግራና በቀኝ የሚገኙት ግን ቅስት የላቸውም። በቅኔ ማህሌቶቹ ድንበሮች በያንዳንዳቸው ላይ የሚገኙት አምስት ምሰሶዎች ሲሆኑ ያንዱ ምሰሶ ጎን ስፋት አራት ስንዝር ይሆናል። ከነዚህም ሌላ ከሕንፃው ጋር ተያይዘው የሚገኙ አራት ምሰሶ ዎች አሉ። ይህ የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ጥሩ ሆነው የተሠሩ ዋና በርና የኋላ በሮች አሉት፤ የበሮቹ ሁሉ ስፋት እኩል ነው፤ (ማለት ቁመታቸው ዘጠኝ ስንዝር፤ ስፋታቸው አራት ስንዝር።) ቤተ ክርስቲያኑ ሶስት ደረጃዎች ባሉበት አጥር ዙርያውን ተከቦአል። በሮቹ ግን ከየፊታቸው ሰፊ ሜዳ ሲኖራቸው ከነዚህ ደረጃዎች

በላይ እያንዳንዳቸው አምስት ደረጃዎች ከፍ ብለው ተሠርተዋል። እነዚህ ደረጃዎች ሁሉ ከአንድ ድንጋይ ተጠርበው የወጡ ናቸው። በሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች የሌለ በዚህ ብቻ የሚገኝ ከቅኔ ማህሌቱ በላይ ያለ በጠምዛዛ መሰላል የሚያስወጣ አንድ የመዘምራን ክፍል አለ። ይህ ክፍል ያለበት ፎቅ ቅርብ በመሆኑ በጣም ረጅም የሆነ ሰው በጭንቅላቱ ጣርያውን ሊነካው ይችላል። የዚህ ክፍል ጣርያ እንደቤተ ክርስቲያኑ ወለል ልሙጥና ሜዳ ነው። ከክፍሉ ዙርያ ትንንሽ ፉካዎች አሉ፤ እነዚህ ፉካዎች ካንዱ ወዳንዱ እንዲሁም ወደመዘምራን ክፍሉ የሚያገናኙ በሮች አሉዋቸው። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ይህ ክፍል በተለይ የተሠራው ለመዘምራን ቢሆንም ለጊዜው የቤተ ክርስቲያኑ አልባስና ጌጣጌጥ የሚቀመጥባቸው ሣጥኖች ማኖርያ አድርገውታል። ሣጥኖቹ በክፍሉ ውስጥ የተሠሩ ይሆናሉ እንጂ በትልልቅነታቸው ምክንያት ከውጭ ተሠርተው ወላልቀው ቢገቡ እንኳ በሩ ሊያስገባቸው አይችልም። የቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ በሌሎች ላይ የማይታይ በውጭ በኩል ልዩ ልዩ ጌጥ አለው፤ ይኸውም ዙርያውን የሚገኘው ደረጃ የሚመስለው ጌጥ ነው። እነዚህ ደረጃ መሰል ጌጦች የሁለት ጣት ርዝመት ያህል ወደውጭ ወጥተዋል። ወጣ ብሎ የሚታየው ድንጋይ ሁለት ስንዝር፤ ወደውስጥ የገባው ደግሞ አንድ ስንዝር ስፋት አላቸው። ስለዚህ የነዚህን ወጣ ገባ ድንጋዮች ስፋት በመለካት የግድግዳው ቁመት ሃምሳ ሁለት ስንዝር መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። ቤተ ክርስቲያኑ ዙርያውን ከድንጋዩ ተጠርቦ በወጣ አጥር ተከቦአል። የታጠረ ከተማ ወይም መንደር ይመስል ጥሩ ሆነው የተሠሩ ሶስት ትንንሽ በሮች አሉበት።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎቹ በታች የሚገኝ በፊት እንዳየናቸው ሁሉ ከአንድ ድንጋይ ተጠርቦ የወጣ ለብቻው ባንድ ቦታ ላይ ያለ ነው፤ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ወስጥ የሚገባው ከድንጋዩ ውስጥ ለውስጥ ስምንት ደረጃ ወጥቶ ባለው መንገድ ውስጥ ሲሆን ይህን መንገድ ሲጨርሱ ዙርያውን ለሰው መቀመጫ ድንጋይ ባለበት ቤት ውስጥ ይገባል። በድንጋዩ ላይ ተቀምጠው የሚገኙት ነደያን ምጽዋት የሚሰጣው በዚህ ቤት ውስጥ ነው። ከጠቀስነው ቤት ቀጥሎ የሚገኘው ከአንድ ድንጋይ ተጠርቦ የወጣው

የቤተ ክርስቲያኑ አጥር ነው። አጥሩ የመስቀል መልክ አለው። ቤተ ክርስቲያኑም ይህንኑ መልክ ስለሚከተል ከዋናው በር እስከ መሰውያው ድረስ ያለው ርቀት ከዳርና ዳር ከሚገኙት በሮች መካከል ካለው ርቀት እኩል ነው። የውጭው መዝጊያዎች ጌጠኞች ናቸው፤ እኔ እዚያ በደረስሁ ጊዜ ተዘግቶ ስለነበር ወደውስጥ ልገባ አልቻልሁም። ከውጭ ሲገቡ በስተቀኝ በኩል ከቤተ ክርስቲያኑ ገረገራ ውስጥ ያንድ ሰው ቁመት ያህል ከፍ ብሎ በሚገኝ ገንዳ ውስጥ የተጠራቀመ ውኃ አለ። ወደውኃው የሚወስድ ደረጃ ባጠገቡ ተሠርቶአል። ይህ ውኃ ምንጭ ነው አሉኝ፤ ነገር ግን ሲፈስ አላየሁም። ውኃው ጸበል ነው ስለሚባል ለበሽተኞች እየቀዱ ደወስዱላቸዋል። እንደሌሎቹ ቤተ ክርስቲያኖች በዚህም ገረገራ ውስጥ መቃብሮች በብዛት ይገኛሉ። በዚህ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ጣርያ ላይ አንደኛው ጎድጓዳ ሆኖ የተሠራ ሌላውም በጎድጓዳው ላይ የተቀመጠ ሁለት መልክ ያለው መስቀል አለ። ይህ መስቀል ማህበረ ክርስቶስ የሚባሉትን ካቶሊካውያን መስቀል ይመስላል።

በዙርያው የሚገኘው ቋጥኝ ከቤተ ክርስቲያኑ ከፍ ያለ ነው። ከቋጥኙ ዳር በሚገኘው ምድር ላይ ትልልቅ የወይራና የጥድ ዛፎች አሉ። እነዚህን ሕንፃዎች እያየሁ ስለነርሱ ማተቱ በእውነተኛው አደከመኝ፤ ከዚህ በላይ በተጨማሪ ባትት ሊያምነኝ የሚችል ሰው ሊኖራ አይችልም፤ የተጻፈውንም ሐሰት ነው ሲሉ ይነቅፉኝ ይሆናል፤ ስለዚህ የጻፍሁት ሁሉ እውነት መሆኑን በሥልጣኑ ሥር ባለሁት በእግዚአብሔር ስም በመማል አረጋግጣለሁ። ያልተጻፈው ከተጻፈው የበለጠ ነበር፤ ነገር ግን ሐሰተኛ ተብዬ እንዳልነቀፍ በማለት አልፌዋለሁ። ይህንንም ያደረግሁበት ምክንያት የሕንፃውን ዝና በመስማት ሁለት ጊዜ የሄድሁት ብቻዬን እንጂ ሌላ ፖርቱጌዝ ስላልተከተለኝ ነው። ይህ ቦታ ባንድ ተራራ ወገብ ላይ ያለ ሲሆን ከዚህ እስከ ተራራው ጫፍ ድረስ ያንድ ቀን ተኩል መንገድ ነው። ከላይ ወደታች ሲወርዱ ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራበት ያ ቁልቁለት ቦታ የሌላ ተራራ ቁልቁለት ይመስላል፤ ነገር ግን የዚሁ ተራራ ክፍል ነው። አራት ወይም አምስት ሌግዋ ያህል የሚያስሄደው ቁልቁለት ሲያልቅ ሰፊ ሜዳ ይገኛል። ከቤተ ክርስቲያኑ እስከዚያ

ድረስ ያለው ርቀት ሁለት ቀን ያስሄዳል ይባላል። እኔ እንደገመትሁት ግን ከአንድ ቀን በላይ የሚያስሄድ አይመስልም። በዚያ ሜዳ ቦታ የድንጋይ ወንበር ያላቸው የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያንንና ሌሎችንም የሚመስሉ ሕንፃዎች ይገኛሉ ይባላል፤ ወደአባይ አቅጣጫ በሚገኘው በዚያ ቦታ ባንድ ክፍል በጥንት ጊዜ የነገሥታትና የንግሥታት መኖርያ ነበር ይባላል። እኔ ወደታች ወርጄ ሁሉንም ባልጎበኝም ሲወራ የሰማሁትን አስደናቂ ነገር አገልጻለሁ። እነዚህ ከድንጋይ ተጠርበው የተሠሩ ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ በሃያ አራት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተሠርተው መከናወናቸውን የሚገልጽ ጽሑፍ መኖሩንና ያገሩ ሰዎች መልካም ሥራ ሊሠሩ ስለማይችሉ ቤተ ክርስቲያኑን ያነፁት ግብጻውያን መሆናቸውን ነገሩኝ። ሕንፃዎቹን ያሠራው አጼ ላሊበላ የተባለው ንጉሥ ነው ይባላል፤ ላሊበላ ትርጓሚው ተአምር ማለት ነው።

ይህን ስም መምረጡ ወይም ሕዝቡ ይህን ስያሜ የሰጠው በተወለደ ጊዜ ንቦች ሙሉ ሰውነቱን ሸፍነውት አንዳች ጉዳት ሳይጥሉበት ትተውት ስለበረሩ ነው ይባላል። ላሊበላ የንጉሠ ነገሥት እህት ልጅ እንጂ ልጅ አልነበረም ይባላል። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ወራሽ ሳይተው ስለሞተ ላሊበላ ያጎቱን ዙፋን ወረሰ ይባላል። ላሊበላ ብዙ ተአምራት ያሳየ ቅዱስ ነበር ስለሚባል ብዙ ምዕመናን በየዓመቱ ለስግደት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ይሄዳሉ።

ከኢትዮጵያ ከመሄዳችን በፊት ነጉሠ ነገሥቱ የቡግናን ግዛት ወደ ፖርቱጋል ለላከው አምባሳደሩ ሰጠው። ከፍ ብዬ እንደገለጽሁት እነዚያን ቤተ ክርስቲያኖችና ሕንፃዎች ሁለት ጊዜ ነው የጎበኘኋቸው ብያለሁ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ልጎበኛቸው መቻሌ አምባሳደሩ ያን የተመረቀለትን ግዛት ሊረከብ ሲሄድ አብሬው በመሄዴ ነው። ስለዚህ እኛ በመንገድ በነበርንበት ጊዜ ሁለት የንጉሠ ነገሥቱ ቀላጤዎች መጥተው ንጉሣዊውን ቃል ያረጋገጡልን ከመሆናቸው በላይ ከርሱ በፊት የነበረው አገረ ገዥ ያልከፈለውን ውዝፍ ግብር አምባሳደሩ እንዲልክ የታዘዘ መሆኑን ጨምረው ነገሩን። የበፊቱ ገዥ የነበረበት ዕዳ ቀጥሎ የተመለከተው ነው፤ አንድ መቶ ሃምሳ

የርሻ በሮች፤ ሰላሳ ውሾች፤ ሰላሳ ጋሻና ሰላሳ ጦር ነበር። ይህ አዲስ ገዥ በቀድሞው ባለሥልጣን መሬት ላይ የሚገኘውን ሕብት ግምት ካወቀ በኋላ ከዚያ ሐብት ላይ ዕዳውን የሚከፍል መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጠ። በዚህና በሌሎች ግዛቶች ግብር የሚከፈለው በዚህ አኳኋን ነው። ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት በግብጽና በአረቢያ የሚገኙት ግዛቶች ግብራ ቸውን የሚከፍሉት በፈረስና በሐር ጨርቅ ነው ብያለሁ፤ ስለዚህ ግብር የሚከፈለው እያንዳንዱ ግዛት ባለው ሐብት እንጂ ባንድ ቋሚ መገበያያ አይደም።

ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት፤ ከአንኮና ወደይንጋበሉ ስለመሄዳችን፤ ዕቃችንን ፍለጋ ወደኋላ ስለመሄዳችን።

ከአንኮና ቤተ ክርስቲያን ተነሥተን ሶስት ሌግዋ ከተጓዝን በኋላ ዕቃችንን በሙሉ አስይዘን አንድ መንደር ደረስን፤ ያ መንደር የንጉሠ ነገሥቱ እናት እርስት ስለነበር መንደረተኞቹ ከርስዋ ልዩ ትዕዛዝ ካልመጣ በስተቀር ዕቃችሁን አንሸከምም ብለው አሻፈረን ከማለታቸው በላይ የሚመራንን መነኩሴ ሊመቱት ፈልገው ነበር፤ እንዲያውም ከሰዎቹ አንዱን ደበደቡበት። ስለዚህ ዕቃችንን በዚያ ቦታ ትተን ይንጋበሉ በተባለ ጥሩ ቤቶች በነበሩበት ትልቅ ከተማ አደርን። ይንጋበሉ የሚገኘው በትልልቅ ተራራዎች በተከበበ ባንድ የርሻ ቦታ ላይ ባለ ኮረብታ ጫፍ ነው። በነዚህ ትልልቅ ተራራ ዎች ጥግ ከዚህ በፊት ካየናቸው ሁሉ የሚበልጡ ብዛታቸውም ከመቶ በላይ የሆነ መንደሮች አሉ። ከዚህም በላይ ከተማው በግራና በቀኝ የሚፈሱ ሁለት ወንዞች አሉት። በዚህ ቦታ አንድ የሚያምር የግንብ ቤተ ክርስቲያን በመሠራት ላይ ነበር። ከይንጋበሉ ሆኖ እንዴት አድርጎ እነዚያን መንደሮች ሁሉ ለማየት ተቻለ ብሎ እንዳያጠራጥር መንደሮቹን በሙሉ ለማየት የቻልነው በተራሮቹ በኩል ስላለፍን ነው። ከከተማው እጅግ ርቀው የሚገኙት ቦታዎች ከአንድ ሌግዋ ተኩል በላይ ርቀት የላቸውም።

በዚህ ከተማ ተቆጥረው የማይዘለቁ ዶሮች አየን፤ ጥቂት በርበሬ ሰጥቶ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ዶሮች ለመግዛት ይቻላል። ከዚህም በላይ ብዙ ሎሚና ትርንጎ ይገኛል፤ በዚህ ቦታ ቅዳሜንና እሁድን ዋልን።

እሁድ ሌሊት ነብሮች ባንድ ቤት ውስጥ ገብተው አንድ ልጅ ይዘው ከሄዱ በኋላ እንደገና ከዚያ ወጥተው እኛ ካረፍንበት ቤት ግቢ ውስጥ ገብተው ከብቶች አስደነበሩብን። ከዚህ በፊት በሳቤሌቴ ወንዝ አጠገብ ደንብረው ጠፍተውብን የነበሩት አንድ በቅሎና አንድ አህያ አሁንም ደንብረው ወደውጭ ሲሮጡ በቅሎው ዘሎ በአንድ በረት ገብቶ ከላሞች መካከል ነፍሱን ሲያድን አህያውን ግን በሉት።

ሰኞ ጥዋት መስከረም 11 ቀን ከዚያ ቦታ ተነሥተን ጓዛችን ወደቀረበት ቦታ ስንመለስ በመንገድ ላይ ብዙ ሰዎች አየን፤ ከነዚህ ሰዎች ግማሾቹ (ዕቃችንን አልቀበል ያሉን) ዱላ የያዙና ጾብ ፈላጊ ዎች ሲሆኑ የተቀሩት ግን ሰላማዊ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን እኛን በደንብ ተቀብለው አስተናገዱን እኛም እንዲሁ አከበርናቸው። ከዚህ በፊት ያሳዩንን መጥፎ ተግባር ለመሻር ደህና ምግብ አዘጋጅተው በመንደራቸው አሳደሩን። በማግሥቱ በጥዋት ተነሥተን ሁለት ወይም ሶስት ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ ባንድ ቦታ ስናድር ገና ዕቃችንን አላገኘነውም ነበር። ሐሙስ ጓዛችንን ለመፈለግ ወደኋላ ተመልሰን ካገኘነው በኋላ ወደ ቀኝ ተጠምዝዘን ከዚህ በፊት የተጓ ዝንበት በሚመስል ተራራማና ሸለቆ ቦታ እያለፍን ሶስት ሌግዋ የሚሆን መንገድ ተጓዝን። የተጓዝንበት መንገድ አንድ ትልቅ ተራራ ይመስላል።

ይህ የአንጎት ግዛት ከዳር እስከ ዳር አንድ ዓይነት የተፈጥሮ ሁኔታ ነው ያለው፤ ማለት ግዛቱ በሙሉ ሸለቆዎችና ተራራዎች የበዙበት ነው። መሬቱ ገብስና ስንዴ በብዛት አይለማበትም፤ ነገር ግን ብዙ ማሽላ፤ ጤፍ፤ ዳጉሣ፤ ሽንብራ፤ አተር፤ ምስር፤ ባቄላ እንዲሁም ብዙ የበለስ ፍሬ፤ ነጭና ቀይ ሽንኩርት ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት የአትክልት ምግብ በብዛት ያፈራል። ከላይ እንደተገጸው የዚህ አገር ሕዝብ የሚገበያየው በብረት ነው።

ምዕራፍ ሃምሳ ሰባት፤ አምባሳደሩ ከመነኩሴው ተለይቶ ለብቻው ሄደ፤ ከመነኩሴው ጋር የቀረነው በድንጋይ ስለመደብደባችን፤ ከአምባሰደሩ ጋር ሁላችንም ወደአንጎትራሱ ቤት ስለመሄዳችን።

መስከረም 14 ቀን ሐሙስ አንጎትራሱ (የአንጎት ጠቅላይ ገዥ) ከሚኖርበት አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ በአንድ ደረቅ ወንዝ ዕቃችን ደረሰ። ቦታው ደረቅ በመሆኑና አምባሳደሩም ከአንጎትራሱ ጋር ለመገናኘት ምክንያት ስላልነበረው ጥቂት ሰዎች አስከትሎ ዕቃው ከነበረበት ቦታ አንድ ሌግዋ ተኩል ያህል ወደፊት ሲሄድ ግማሾቻችን ከመነኩሴውና ከጓዙ ጋር በዚያ ቀረን፤ ከአውራ ጎዳናው አንድ ሌግዋ ያህል ወጥቶ ወደሚገኘው መንደር ሄደን በዚያው እንድናድርና ዕቃችንንም በሰው አሸከሞ ጥቂት እልፍ ካደረገልን በኋላ አገሬው እንዲጠብቅልን አደራ የሚልልን መሆኑን መነኩሴው ገለጸልን። አገሬው ተጠራርቶ በሶስት ክፍል ሆኖ ሲመጣ በእውነተኛው ሊረዳን የመጣ መሰሎን ነበር፤ ነገር ግን አመጣጣቸው ለተንኮል ነበር። በያንዳንዱ ክፍል ከመቶ ሰዎች በላይ ሆነው እነዚያ ሰዎች በወንጭፍና በእጅ ውርወራ የድንጋይ እሩምታ አወረዱብን። ከመነኩሴው ጋር የነበርነው ሰዎች በጠቅላላው አርባ ሰዎች ስንሆን ከመካከላችን ድንጋይ ያላረፈበት ሰው አንድም አልነበረም። ከኛ ጋር የነበረ ክፉኤ የተባለ አንድ በሽተኛ ልጅና እኔ ብቻ አመለጥን። ስድስት የመነኩሴው ሰዎች፤ አንድ የአንጎትራሱ ባለሥልጣንና ከኛም ሰዎች መምሕር ዮሐንስ ራሳቸውን ተፈንክተው አገኘናቸው። የተደበደብነውና የቆሰልነው አልበቃ ብሎአቸው ሊይዙዋቸው የቻሉትን በጣም የተጎዱትን አሰሩዋቸው፤ ግማሾቻችን ሸሽተን በማምለጥ ዕቃችን ወደነበረበት ወደኋላ ተመልሰን እራታችንን ሳንበላ አደርን። ከኔና ከበሽተኛው ልጅ በስተቀር ራሳቸውን የተፈነከቱት ወይኔ ራሴን እያሉ በመሰቃየት አደሩ። በማግሥቱ አርብ በማለዳ ተነስቼ አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ አምባሳደሩ ወደነበረበት ቦታ ሄድሁ።

ወዲያው እንዳገኘሁት የደረሰብንን ሁሉ በሙሉ እንደነገርሁት በቅሎውን አስጭኖ ለፖርቱጊዞች መሞት አለብኝ ሲል በግሥጋሴ ዕቃችን ወደ ነበረበት ቦታ አብረን ሄድን። በዚያ እንደደረስን አንጎትራሱ በርከት ካሉ ሰዎች ጋር ሆኖ አገኘነው። መነኩሴውም በዚያው ነበር። አምባሳደሩም በአስተርጓሚ ለአንጎትራሱ እንዲህ አለው፤ እኔ ወደዚህ መምጣቴ እርስዎን ወይም መነኩሴውን ለማግኘት ሳይሆን በርስዎ ግዛት የጠፉብኝን ፖረቱጊዞች ለመፈለግ ነው።

የዚያ አደጋ ሁኔታ ሲወራ መምሕር ዮሐንስ ክፉኛ ራሱን ተፈንክቶ በደም ተበክሎ ከእስር ቤት አምልጦ እኛ በነበርንበት ቦታ ድንገት መጣ። የአምባሳደሩ የአንጎትራሱና የመነኩሴውም ክርክር ካለቀ በኋላ ቅዳሜና እሁድን እርስዎና ፖርቱጊዞቹ በኔ ቤት እንድትውሉ ጋብዣችኋለሁ ሲል አምባሳደሩን አንጎትራሱ ጥሪ አቀረበለት። አምባሳደሩም ጉዳዮን ከኛ ጋር ካጠናው በኋላ ግብዣውን ተቀበለ። ከዚህ ቦታ አንድ ሌግዋ ተኩል ያህል ርቆ በሚገኘው በአንጎትራሱ ቤት ሄደን በደንብ ተቀብሎ አስተናገደን። የርሱ እንግዶች ሆነን በዚያ እሁድንና ቅዳሜን ዋልን። በደረስንበት ዕለት ማለት ቅዳሜ ልክ የአንድ ተራ ሰው ቤት ይመስል ያለ አንዳች ችግር አስገቡን። በቤት እንደገባን አንጎትራሱ ከባለቤቱና ከጥቂት ሰዎች ጋር ተቀምጦ አገኘነው። የተቀመጠው በመደብ ላይ ነበር። በማዕርግ ተቀብለው ወደቤት ካስገቡን በኋላ በአዳራሹ ውስጥ ተቀምጦ ከነበረው አራት ገንቦ ጠጅ በብርሌ እየቀዱ ይሰጡን ጀመር፤ የአንጎትራሱ ባለቤትና አብረዋት የነበሩት ሁለት ሴት ወይዛዝርት በአገር ልምድ መሠረት ጠጡ ተጋበዙ የገንቦውን ጠጅ መጨረስ አለባችሁ እያሉ ያን አስጨርሰውን ሌላ ሊያመጡ ሲሰናዱ ወደጓሮ መዞር አለብን ብለን ምክንያት በመስጠታችን ብቻ ሊለቁን ቻሉ። እያንዳንድ ገንቦ ስድስት ወይም ሰባት ከናዳዎች ይይዛል።

በማግሥቱ እሁድ ወደቤተ ክርስቲያን ሄደን በዚያው አንጎትራሱን አግኝተነው በክብር ተቀብሎ አነጋገረን። ወዲያውኑ ከኔ ጋር ስለኛ ሃይማኖት ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ ጀምረን ንግግሩን ለመቀጠል በጣም ፍላጎት ስላደረበት ከኛ ጋር ይጓዝ የነበረውን

መነኩሴና ሁለት ሌሎች ቄሶች እንዲሁም እኔና የኛም አስተርጓሚም ሆነን ለብቻችን ወደአንድ ቦታ ሄደን በሰፊው ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ ጀመርን። ብዙ ተራ ጥያቄዎች አቀረቡልኝ፤ ጥያቄዎቹም ቀጥሎ የተመለከቱት ነበሩ፤ የሱስ ክርስቶስ በየት ነበር የተወለደው? ማርያምና ዮሴፍ በየት በኩል ነበር የሱስን ወደምድረ ግብጽ የወሰዱት? በምድረ ግብጽ ስንት ዓመት ቆየ? በዚያን ጊዜ ዕድሜው ስንት ነበር? ወደ የሩሳሌም የገባው በምን ላይ ተቀምጦ ነበር? መቼ ነበር የሱስ ክርስቶስ ጠፍቶ እናቱ እመቤታችን ማርያም በመቅደስ ውስጥ ያገኘችው? ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የለወጠው በየት ነበር፤ በዚያስ ማን ነበር? በየሩሳሌም ሲደርስ በማን ቤት ነበር እራት የበላ? በየሩሳሌም ቤት ነበረውን? እግሩን ማን ነበር ያጠበው? ጴጥሮስ ማለት ትርጓሜው ምንድር ነው? ጳውሎስስ?

የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስለነበር የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁሉ በሚገባ መለስሁላቸው። እኛን ይመራን የነበረው ያ መነኩሴ ይህ ሰው በጣም አዋቂ ነው እያለ ስለኔ ለሌሎቹ የነገራቸው መሆኑን አስተርጓሚው ገለጸልኝ። ይህ መነኩሴ በነገራቸው መሠረት ሁሉም ብድግ ብለው በግድ ጫማዬን ሳሙኝ፤ እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው። ቄሶቹ ማናቸውንም ነገር ለአንጎትራሱ ነግረውት እርሱም ጉንጩን ሳመኝ። ይህ ሰው ምንም እንኳ አሁን አገረገዥ ቢሆንም በኢትዮጵያ ካሉ መልካም ቄሶች አንዱ ነው። እኛ ከኢትዮጵያ በሄድንበት ጊዜ የባሕር ነጋሽነቱን ማዕርግ ከመያዙ በላይ በቤተ ክርስቲያን እየገባ የሚቀድስ ካህን ነበር። ከቅዳሴው በኋላ ወደቤት ሄደን ምሳ እንድንበላ ጋብዞን ግብዣውን ተቀበልን። ነገር ግን የነርሱ ምግብ ቅቤ የበዛበት የዶሮ ወጥና የሰባ ሥጋ የገባበት ጎመን በመሆኑ ለኛ የማይስማማ ስለነበር የራሳችንን ምግብ ይዘን እንድንሄድ አምባሳደሩ አዘዘ።

ግብዣው የተፈጸመው ቀጥሎ በተመለከተው ስነ ሥርዐት ነበር። በቤተ ንጉሡ ውስጥ በሚገኝ ወለል በሌለው ባንድ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ገባን፤ አንጎትራሱ ተቀምጦበት በነበረው አልጋ ፊትለፊት በምድሩ ላይ ብዙ ኬሻ ተነጥፎ ነበር፤ አንጎትራሱም ከአልጋው

ወርዶ በምድር ላይ ተቀመጠ። በኬሻው ላይ ጥቋቁር ድብዳቦች አንጥፈው በድብዳቦቹ ላይ ሁለት የሚያምሩ ገበታዎች አቀረቡ። የነዚህ ገበታዎች ከንፈር ከሁለት ጣት አይበልጥም፤ ገበታዎቹን ዙርያቸውን ሲለኩዋቸው ትልቁ አስራ ስድስት ስንዝር ትንሹ ደግሞ አስራ አራት ስንዝር ይሆናል። እነዚህ ገበታዎች ትልልቅ እንግዳዎች በመጡ ጊዜ የሚቀርቡ ናቸው። አንጎትራሱና እኛም በዙርያው ከበን ተቀመጥን። የጣት ውኃ ቀርቦ ሁላችንም ታጠብን፤ ነገር ግን ታጥቦ እጅ ማድረቂያ ፎጣ የለም። ልዩ ልዩ ዓይነት እንጀራ ማለት የስንዴ፤ የገብስ፤ የማሽላ፤ የሽንብራና የጤፍ ቀረበ። መብላት ከመጀመራችን በፊት አንጎትራሱ ከጋሬው እየቆረሰ በፊቱ እንዲያኖሩለት አዘ፤ በያንዳንዱ ቁራሽ ላይ ብርንዶ እየቆረጠ አስቀምጦበት በውጭ ቆመው ይጠብቁ ለነበሩት ነደያን እንዲሰጡለት አዘዘ። ከዚህ በኋላ በኛ ወግ ገበታውን ባረክንና መብል ተጀመረ። አንጎትራሱ የኛን የገበታ ጸሎት በመስማቱ በጣም ተደሰተ። ሶስት ዓይነት ወጥ ከነድስቱ ቀረበ፤ ወጡ ከምን እንደተሠራ አላውቅም፤ ይሁን እንጂ ነጭ ሽንኩርት የነበረበት መሆኑን በጣዕሙ አውቄዋለሁ። ከቀረበውም ምግብ አንደኛው ዓይነት የከብት እበትና[3] ሃሞት ቅልቅል ነበር። ይህን ምግብ የሚበሉት ታላላቅ ሰዎች ብቻ ናቸው ይባላል። ወጡ የሚቀርበው ማለፊያ ሆኖ በተሠራ ወጭት ሲሆን እንጀራውን እየቆረሱ ይፈተፍቱትና በገበታው ላይ ያወጡታል። ነገር ግን ከዚህ ምግብ ልንበላ ስላልፈቀድን በደንብ ተዘጋጅቶ የነበረውን የኛን ምግብ አቅርበን መብላት ጀመርን። ጠጁ በገፍ ነበር የቀረበው። የአንጎትራሱ ባለቤት በኛ አጠገብ በመጋረጃ ውስጥ ሆና የራስዋን ምግብ ትበላ ነበር። ከኛም ምግብ አቅርበውላት ነበር፤ ነገር ግን በመጋረጃ ውስጥ ስለነበረች መብላትዋን ወይም አለመብላትዋን ላረጋግጥ አልቻልሁም። የቀረበልንን መጠጥ ደህና አድርገን ተጋበዝን። ከምግቡ በኋላ የፍርንባ ቁርጥ ቀረበ፤ እኛ ግን አልቀመስነውም። አንጎትራሱና ሌሎቹ ሰዎች ግን ከምግብ በኋላ እንደሚበላ ጣፋጭ ወይም ብስኩት ይመስል ያን ሥጋ እያቀላጠፉ ይበሉት ነበር። በዚህ አኳኋን የምሳው ስነ ሥርዐት ተፈጽሞ ወደማረፊያችን ሄድን።

ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት፤ አምባሳደሩ አንጎትራሱንና መነኩሴውን ተሰናብቶ ሄደ፤ ግማሾቻችን አደጋ ወደተጣለብን ቦታ ተመለስን፤ ከዚያም ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ወደሚገኙበት አንድ ለምለም ቦታ ሄድን።

ሰኞ ጥዋት ሁላችንም ባንድነት ሆነን አንጎትራሱን ስንሰናበት መነኩሴው አግኝቶን የመምሕር ዮሐንስን በቅሎና አደጋ በተጣለብን ቦታ የተዘረፈብንን አንድ አህያ ከነጭነቱ ጠብቃችሁ ይዛችሁ መሄድ አለባችሁ ስላለ እንድንቆይ አደረገ። አምባሳደሩ ግን ከዚህ በፊት ተከትለውት ከነበሩት ሰዎች ጋር ሲሄድ እኛ ከመነኩሴው ጋር በዚያ ቀረን።

የዚያኑ ዕለት ወደማታ በቅሎውና አህያው ስለመጡ አምባሳደሩን እንድንደርስበት በማለት ተነሥተን መንገዳችንን እንድንቀጥል መነኩሴው አዘዘ። እኛም ይህ የሚሆን መስሎን ትዕዛዙን በመቀበል ወደፊት ቀጥለን ባንድ ጫካ መንገድ እየመራን ሄደን ከዚህ በፊት አደጋ በተጣለብን ቦታ ደረስን። አደጋ የጣሉብንን መንደረተኞች ሊበቀል ስለፈለገ ስምንት በቅሎኞችና አስራ አምስት እግረኞች አስከትሎ ነበር። ከመሸ በኋላ በመንደረተኞቹ ቤት ውስጥ ለማደር ገብተን በዚህ ቤትና በመንደሩ በሙሉ ሰዎች አላገኘንም ነበር። መንደረተኞቹ በሙሉ ከሠፈራቸው በላይ ወደሚገኝ ወደ አንድ ተራራ ሄደው ነበር። ለኛና ለከብቶቻችን ምግብ እንደልብ አገኘን።

ነገር ግን በዚያ እንደደረስን ተከትውን የነበሩት ሰዎች ትተውን ስለሄዱ በእውነተኛው ፍርሐት አደረብን። እንዲያውም መነኩሴው ከአውራ ጎዳናው አውጥቶ ወደዚህ ያመጣን ሊያስገድለን ነው በማለት ክፉኛ ተጠራጠርነው። ወደዚህ ቦታ የመጣንበት ሕዝቡን በፍርድ ለመቅጣት ነውና ነገ ጥዋት እንሄዳለን አለን። በማግሥቱ ጥዋት የምንሄድ መስሎን እንነሣ ብንለው አሁን እንቆይና በእኩለ

ቀን እንሄዳለን አለን። ልክ እኩለ ቀን ድረስ ቆይተን እንሂድ ብንለው ዛሬን አድረን ነገ በጥዋት እንሄዳለን ስላለን በከንቱ ጊዜ ማጥፋት መሆኑን ተረድተን እርሱን በዚያው ትተነው ዕቃችንን አስይዘን ወደፊት ሄድን፤ በዚያኑ ዕለት ጓዛችን በነበረበት ቦታ ደረስን።

ነገር ግን በነዚያ ሰዎች መካከል ብቻውን ሊያድር ባለመድፈሩ መነኩሴው የዚያኑ ዕለት ሌሊት ደረሰብን። መንደረኞቹ አደጋ ስለጣሉብን የደም ዋጋ ሁለት በቅሎችና አንድ ላም ስምንት ልብሶችም ተቀብሎ መጣ። የሕዝቡን ሐብት መውሰድ መነኩሴው በፍርድ መቅጣት የሚለው ነው። በድንጋይ የተደበደብንባቸው ቦታዎች አንደኛው አንጓ ሌላውም መስተኞ ይባላሉ፤ ሁለቱም የአቡነ ማርቆስ ርስቶች ናቸው ይባላል።

በየተራሮቹም ጥግ ብዙ ሕዝብ የሚኖርበትና አያሌ ቤተ ክርስቲያኖች በነበሩበት አንድ የሚያምር ተራራማ ቦታ ደረስን። ይህ ቦታ ልዩ ልዩ ዓይነት እህል የተዘሩ እርሻዎች ይገኙበታል። በለስ፤ ሎሚ፤ ብርቱካን፤ ትርንጎ እንዲሁም የከብቶች መሠማርያ የሣር ቦታዎች አሉበት። አሁን አምባሳደር እየተባላ ከሚጠራው መነኩሴ ጋር በዚህ ቦታ ለሁለተኛ ጊዜ ስመለስ ቅዳሜና እሁድን ባንድ ደብተራ ቤት ቆየን። ሁለቱንም ቀኖች አብረነው ወደቤተ ክርስቲያን ሄደን በዚያ ብዙ ደብተራዎች ስላየን ቁጥራቸውን ብጠይቀው ስምንት መቶ ነው አለኝ። የቁጥራቸውን መበርከት በመመልከት ለነዚህ ሁሉ ማስተዳደርያ የሚሆን በቂ ገቢ አላችሁ ወይ ብለን ብንጠይቀው መጀመርያ የደብተራዎቹ ቁጥር እንደዚህ ሳይበረክት ገቢው በቂ ነበር፤ ነገር ግን ልጆቻቸው ያባቶቻቸውን ምሳሌ እየተከተሉ ደብተራዎች ስለሚሆኑ ቁጥራቸው እየበረከተ በመሄዱ ገቢው የማይበቃ ሆነ ሲል ገለጸልን።

ካህናቱ ልጆቻቸውን እያስተማሩና እያስካኑ ቁጥራቸውን እያበረከቱ መሄዳቸውን በማየት አዲስ ቤተ ክርስቲያን በተሠራ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ካህናት የሚያስወስደው ከዚህ ቦታ ነበር። ለምሳሌ የመካነ

ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተሠራ ጊዜ ከዚህ ቤተ ክርስቲያን ሁለት መቶ ካህናት ተወስደው ነበር፤ በዚያ ሸለቆ ውስጥ ስምንት ደብሮች ሲገኙ ብውስጣቸው ያሉ በአራት ሺ የሚገመቱ ካህናት ሁሉ ከዚያ ቤተ ክርስቲያን የመጡ ናቸው። ከዚህም በላይ ንጉሠ ነገሥቱ ለቤተ መንግሥቱ ቤት ክርስቲያኖች ካህናት የሚያስወስድ ከዚሁ ነው፤ በዚህ አኳኋን ኑሮዋቸው እንዲሻሻል ባያደረግ ኖሮ በብዛታው ምክንያት እርስ በርሳቸው ተፋጅተው ያልቁ ነበር።

ምዕራፍ ሃምሳ ዘጠኝ፤ የንጉሠ ነገሥቱ ልጆች በግዞት ስለሚቀመጡበት ምሽግና በዚያም ቦታ አጠገብ ያለው ሕዝብ እኛን በድንጋይ ስለመደብደቡ።

ከፍ ብለን የጠቀስነው ሸለቆ የንጉሠ ነገሥቱ ልጆች በግዞት ከሚቀመጡበት አምባ ጋር የሚዋሰን ነው። ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት አርባ ዓመት ሙሉ በዋሻ ይኖር የነበረው አብርሃም የተባለው ንጉሥ ከበኩር ልጁ በስተቀር ወንድ ልጆቹን ሁሉ በግዞት እንዲያኖር ራዕይ ተገልጾለት ነበር ማለትን ተረድተናል፤ ስለዚህ ከዚህ ንጉሠ ነገሥት በኋላ የነገሡ ሁሉ ልጆቻቸውን በግዞት በአምባ ውስጥ ያኖሩዋቸው ነበር። ይህ የሚደረግበት ምክንያት ልጆቹ ሕዝቡን አሳድመው አገሩን በመበጥበጥ ሕጋዊውን ወራሽ እንዳያጠፉት በማለት ነው። አብርሃም በተገለጸለት ራዕይ በመገረም ይህ አምባ የት ይሆን የሚገኘው እያለ ሲያስበ ለሁለተኛ ጊዜ ራዕይ ተገልጾለት «በአገርህ በመላ አንድ ትልቅ የሆነ ተራራ አስፈልግ፤ ያ ተራራ ሊወድቁ የደረሱ የሚመስሉ ብዙ የሜዳ ፍየሎች ይታዩበታል፤ ይህን የመሰለ ተራራ ባገኘህ ጊዜ እነሆ የልጆችህ ማሠርያ» ሲል አመለከተው። በራዕዩ መሠረት ተራራውን ሲያስፈልግ ይህን ከሸለቆው በላይ የሚገኘውን አምባ አገኘ። አምባው በዙርያው የሁለት ቀን መንገድ ያስሄዳል። ከአምባው ዙርያ ባለው ገደል ጥግ ሆኖ ወደላይ ሲመለከቱ ቀጥ

ብሎ በመቆሙ ምክንያት ሰማዩ የተከደነበት ይመስላል። ወደ አምበው የሚያስወጡት መንገዶች ሶስት ብቻ ናቸው ይባላል፤ ከነዚህም አንዱን ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን በድንገት ልናየው ችለናል።

አገሩን ደህና አድርጎ የማያውቀው የንጉሠ ነገሥቱ ቀላጤ የነበረ አንድ ወጣት እየመራን ወደቤተ መንግሥቱ ስንጓዝ መሸቶብን ሕዝቡ ሊቀበለን ባልፈለገበት ባንድ ቦታ እንድናድር ወደዚያ መርቶ ወሰደን፤ ይህ ቦታ የንጉሠ ነገሥቱ እህት ርስት ነበር። ምሽቱ ገና ለዓይን ስላልያዘ የምታድሩበት ቦታ እዲሰጣችሁ አደርጋለሁና ተከተሉኝ እያለ በበቅሎ ተቀምጦ ባቋራጭ መንገድ ከፊታችን ይሄድ ነበር። ሎፔ ደ ጋማ የተባላ የኛ ሰው ወጣቱን እያየ እንዲከተል እኔም እርሱን እያየሁ እንድሄድ አምባሳደሩና ሌሎቹም ሰዎች እኔን እየተመለከቱ እንዲከተሉ አድርገን ጥቂት እንደተጓዝን በጣም ጨልሞ ለመተያየት አልተቻለም ነበር፤ ከአውራ ጉዳናው አንድ ሌግዋ ያህል ርቀን ከልዑላኑ አምባ አጠገብ ስንደርስ ያከባቢው መንደር ነዋሪዎች ሊገድሉን ፈልገው በድንገት የድንጋይ እሩምታ አውርደውብን በሶስት ወይም በአራት ክፍል በታተኑን። አምባሳደሩ በስተኋላ በኩል ስለነበር ወደኋላው ተመለሰ፤ በመካከል የነበሩት ደግሞ እየዘለሉ ሸሹ። በበቅሎ ላይ የነበረ አንድ ሰው ደግሞ በቶሎ ከበቅሎው ላይ ወርዶ አንዲት ከረጢት በእጁ አንጠልጥሎ ሩጫውን ጀመረ። ሎፔ ደ ጋማና እኔ ደግሞ ወደኋላ ለመመለስ ስላልቻልን ወደሌላ መንደር ሸሸን። ነገር ግን በዚህ መንደር የሚኖሩት ሰዎች ጫጫታውን በመስማት በደንብ ተዘጋጅተው ይጠብቁ ስለነበር እነዚህም እንደገና በድንጋይ ጠመዱን። እንደዝናም ከሚወርድብን ድንጋይ ሌላ በጨለማው ምክንያት ዓይን ቢወጉ አይታይም ነበር፤ ስለዚህ የበቅሎዬን ኮቴ በመስማት ወርውረው እንዳይመቱኝ በማለት ከበቅሎ ወረድሁና አሽከሬ እየሳበ እንዲሄድ ሰጠሁት። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ወዲያውኑ አንድ የተከበረ ሰው መጥቶ ማነህ አንተ ብሎ ጠየቀኝ፤ እኔም መለስሁና ጋሻ ንጉሥ (ወይም የንጉሥ እንግዳ) ነኝ ስል መለስሁለት። ይህን እንደሰማ ወዲያውኑ ጠጋ ብሎኝ ደግፎ እየመራኝ «አትፍራ፤ አትፍራ» እያለኝ አሽከሬንና በቅሎዬን እያስ

ከተልን ወደፊት ቀጠልን። በመካከሉ ጎጆ መስሎ ብዙ አጠና በተከ መረበት በቤቱ አጠገብ ባለ አንድ የአትክልት ቦታ ስንደርስ በዚያ ገብቼ እንዳርፍ ነገረኝ። በአጣናው ውስጥ ሰው የምታስገባ ንጹህ ጎጆ ስለነበረች የሚያሰጋ ነገር የለም ብዬ በዚያ ገብቼ ዐረፍ ለማለት ጥዋፍ እንዲበራ አዘዝሁ። የጥዋፉን ብርሃን በመመልከት ወዲያውኑ በጎጆው ላይ የድንጋይ በረዶ መጣል ስለጀመሩ በቶሎ መብራቱን ሳጠፋው ድንጋዩ ቆመ።

ያ ሰው በዚያ ቦታ እንዳደረሰኝ ወዲያውኑ ወደኋላ ተመልሶ ድንጋይ በሚወራወሩበት ቦታ ደርሶ ሲመለስ አንድ ሰዓት ያህል ቆየ። በዚያን ጊዜ ሎፑ ደ ጋማ ከነበርሁበት ቦታ ድምጽ ሰምቶ በዳበሳ ጥሻ እየጣሰ መጣ። ሎፑ እንደደረሰ ያ ሰውዬም ደርሶ፤ አትነጋገሩ አይዞአችሁ ምንም አይነካችሁም አለን። ወድያውኑ ጥዋፉን አብርቶ ሁለት ዶሮች አሳርዶ እንጀራና ጠላ አቅርቦልን በደንብ አስተናገደን።

በማግሥቱ ጥዋት አስተናጋጃችን እጄን ይዞኝ ከቤቱ እልፍ ብሎ ጥቅጥቅ ብሎ ወደታጠረ አንድ ቦታ ወሰደኝ። በአጥሩ ላይ ያለችውን አንድ ትንሽ በር ከፍቶ ወደዳገቱ ላይ የሚወጣውን መንገድ አሳየኝ። እንዲህ ሲልም አስጠነቀቀኝ «ይህን መንገድ ታየዋለህ? ከናንተ አንዱ ይህን አልፎ በዚያ መንገድ ቢገባ እጅና እንሩ ተቆርጦ ዓይኑም ወጥቶ ይጣላል፤ ይህን የመሰለ ቅጣት ተጣለብን ብላችሁ ልታማርሩ አትችሉም ወይም ይህን የመሰለ ቅጣት እንዲደርስባችሁ ማድረጋችሁ ጥፋቱ የናንተ አይደለም፤ ጥፋቱስ እዚህ መርቶ ያመ ጣችሁ ሰው ነው። እኛ ጠባቂዎቹ ይህን የመሰለውን ቅጣት ከልፈ ጸምን ይሙት በቃ ይፈረድብናል» ሲል ነገረኝ።

ሎፑ ደ ጋማ እኔና ያ ይመራን የነበረው ወጣት በቅሎቻችንን ተቀምጠን ከነበርንበት ተራራ ብዙ ሌግዋ ርቆ ወደሚገኘው ወደ አውራ ጎዳናው ሄደን የኛን ሰዎች ግማሾቹን በዚያው አገኘናቸው።

ምዕራፍ ስልሳ፤ የንጉሠ ነገሥቱ ልጆች መታሠሪያ ምሽግ ታላቅነት።

በኢትዮጵያ በነበርንበት ጊዜ አልጋውን ይዞ እስከነበረው እስከ አጼ ዳዊት ድረስ የነገሡት ነገሥታት ሁሉ እያንዳንዳቸው አምስት ወይም ስድስት ሚስቶች ስለነበሩዋቸው ከያንዳንዳቸው ወይም ከሁሉም ልጆች ይወልዳሉ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ሲሞት አልጋውን የሚወርሰው የመጀመርያው ወንድ ልጁ ነው፤ አንዳንድ ሰዎች እንደሚያወሩት አልጋውን የሚወርሰው ልጅ አባቱ ችሎታ ያለውና አስተዋይ ሆኖ ያገኘው ብቻ ነው ይላሉ፤ ሌሎች እንደሚያወሩት ደግሞ አንድ ልጅ ለወራሽነት የሚመረጠው በቂ ደጋፊዎች ያሉት እንደሆነ ብቻ ነው ይላሉ። እኔም ሲወራ የሰማሁትን አስከትላለሁ፤

የዳዊት አጎት አጼ እስክንድር ወራሽ ሳይተው በመሞቱ ወንድሙን ናኦድን ከአምባው አምጥተው አነገሡት ይባላል። ናኦድ በግዞት በሚኖርበት ጊዜ ሚስት አግብቶ ከዚች ሚስት በአመሉ ጥቂት ኃይለኛ የነበረ ነገር ግን በመኰንንነቱና በጨዋነቱ የተመሰገነ አንድ ልጅ ተወለደለት። ናኦድ ከአምባው አርነት ወጥቶ የወን ድሙን አልጋ ከወረሰ በኋላ ሌሎች ሚስቶች አግብቶ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ተወለዱለት። እርሱ በሞተ ጊዜ ያን በግዞት የተወለ ደውን ልጁን ሊያነግሡ ፈለጉ፤ አንዳንድ ሰዎች ግን የልጁን ኃይለኛነት በማወቅ የነገሠ እንደሆነ ሕዝቡን ያጠቃል በማለት ተቃወሙ። ሌሎች ደግሞ ምንም እንኳ የመጀመርያ ወንድ ልጁ ቢሆንም የተወለደው አባቱ ከመንገሡ በፊት በግዞት ስለሆነ አልጋ ለመውረስ ሕግ አይፈቅድለትም ሲሉ ተቃወሙ። የሆነ ሆኖ የናኦድ አልጋ አስራ አንድ ዓመት ዕድሜ ለነበረው ለልጁ ለዳዊት ተላለፈ። አቡነ ማርቆስና እቴጌ እሊኒ መኳንንቱ ሁሉ በእጃቸው ስለነበሩ ልጁን ያነገሡት እነርሱ መሆናቸውን አቡኑ ራሳቸው ነገሩኝ። ስለዚህ ከብኩርናው ሌላ ደጋፊዎችም እንዲኖሩ የሚያስፈልግ ይመስ ለኛል።

ገና ወጣት የነበሩት ሌሎቹ የናኦድ ልጆች ከአባቱ ጋር ከመጣው ከትልቁ ልጅ ዘንድ ከቆዩ በኋላ ወደ አምባው መለሱዋቸው፤ ይህ አድራጎት ከንጉሥ አብርሃም ጀምሮ በነገሥታቱ ልጆች ላይ ሲፈጸም የቆየ ልምድ ነው።

ይህ አምባ ብርዳምና ትልቅ ነው ይባላል፤ ጫፉ ክብ የሆነ ዙርያውም የአስራ አምስት ቀን መንገድ የሚፈጅ ነው ይላሉ። መንገዳችንን በወዲህ በኩል ጀምረን ጥጉን በመጓዝ ሁለት ቀን ስለፈጀብን እንደሚባለውም አስራ አምስት ቀን ሳይፈጅ አይቀርም። በዚህ አኳኋን አምባው ከነበርንበት ብዙ ርቆ እስካለው በአባይ ድንበር እስከሚገኘው እስከ በጌምድር አማራ ግዛት ይደርሳል። ከዚሁ አምባ ጫፍ በመካከላቸው ሸለቆዎች የሚገኙባቸው እጅግ ከፍ ያሉ ሌሎች ተራራዎች አሉ ይባላል። ሸለቆው በሁለት በር ስለሚዘጋ ከገቡ በኋላ በምንም አኳኋን ለመውጣት አይቻልም። ለጥቂት ጊዜ በዚያ በሚቆዩበት በጥብቅ እንዲጠበቁ የንጉሠ ነገሥቱን ዘመዶች በዚያ ያኖሩዋቸዋል ይባላል። የልጅ ልጆችና ራቅ ያሉ ወደመረሳት የደረሱ ዘመዶች ግን በጥብቅ አይጠበቁም። የሆነ ሆኖ አምባው በብዙ ሠራዊትና መኮንኖች የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህም በላይ ከቤተ መንግሥቱ ሠራዊት እሩቡ በዚሁ ሥራ ይረዳል።

በቤተ መንግሥቱ ያሉት የአምባው ጠባቂዎችና ሠራዊት መኮንኖችም ከማንም ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው ብቻቸውን ፈንጠር ብለው ይኖራሉ። ይህ መደረጉ የአምባው ምስጢር እንዳይገለጥ በማለት ነው። ለንጉሠ ነገሥቱ መልእክት ይዘው ወይም ለመነጋገር በደጁ በደረሱ ጊዜ በዚያ የሚገኙ ሁሉ ገለል ማለት አለባቸው። እነዚህ ሰዎች ጉዳያቸውን በሚነጋገሩበት ጊዜ ማናቸውም ተግባር ይቆማል።

ምዕራፍ ስልሳ አንድ፤ በአምባው ከሚኖሩ ልዑላን መልእክት ባመጣ ባንድ መነኩሴና በጠባቂዎች ላይ የተጣለባቸው መቀጫ፤ የንጉሠ ነገሥቱ ወንድምና እኅት ከአምባው አምልጠው ስለመሄዳቸውና ተይዘውም ስለመቀጣታቸው።

ስለነዚህ ልዑላን ጉዳይ ቀጥሎ የተመለከተውን አትታለሁ፤ ሰላሳ ዓመት ያህል ዕድሜ የነበረውን አንድ መነኩሴና ከርሱም ጋር የአምባው ጠባቂዎች የነበሩትን በሁለት መቶ የሚገመቱትን ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥቱ አመጡዋቸው። መነኩሴው በአምባው ላይ ከነበሩት ልዑላን ደብዳቤ አመጣ ስለተባለ እርሱንና አብረውት የነበሩትንም በሁለት ከፍለው በጅራፍ ይገርፉዋቸው ነበር። መነኩሴውን በየሁለት ቀን ሲገርፉት ከጠባቂዎቹም ግማሾቹን ከርሱ ጋር አብረው ይገርፉዋቸው ነበር። ግርፋን የሚጀምሩት ሁልጊዜ ከመነኩሴው ሲሆን ከዚያን በኋላ እርስ በርሳቸው እየተያዩ የሚጠብቁትን ያስከትሉዋቸዋል። መነኩሴውን በየጊዜው ይህን ደብዳቤ የሰጠህ ማነው? ለማንስ ነው ያመጣኸው? ሌላ ደብዳቤ አምጥተሃልን? ከየትኛው ገዳም ነው የመጣኸው? በየት ነው የመነኮስኸው? የቅስናስ ሥልጣን የተቀበልኸው በየት ነው? እያሉ ይመረምሩት ነበር። ይህ የፈረደበት መነኩሴ ደብዳቤውን የሰጡኝ ከአምባው እንደወጣሁ ከአስራ ስድስት ዓመት በፊት ነበር፤ ከዚያ በኋላ በፍጹም ወደዚያ አልተመለስሁም፤ ዛሬ ኃጢአቴ ሲያጋልጠኝ ይህን ደብዳቤ ከእጄ አወጣሁት እንጂ ከዚህ በፊት ለማንም ልሰጥ አልደፈርሁም ይል ነበር። (በዚህ አገር በደብዳቤ ላይ ቀን ወር ወይም ዓመት መጻፍ ያልተለመደ ነገር ስለሆነ የተናገረው እውነት ሊሆን ይችላል።) ጠባቂዎቹ መነኩሴውን እንዴት እንደለቀቁት ይጠይቋቸው ነበር እንጂ ሌላ ምርመራ አያደርጉላቸውም ነበር።

መነኩሴውን በሆዱ አጋድመው ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ይገርፉት ነበር፤ ሁለት እጆቹንና እግሮቹን አጣምረው ያሥሩና እጆቹን ከእንጨት ጋር አያይዘው እግሮቹን ደግሞ በገመድ እንደታሠሩ

ሁለት ሰዎች ወደኋላ ወጥረው ይስባሉ፤ ከዚህ በኋላ በግራና በቀኝ የሚገኙት ገራፊዎች እየተፈራረቁ ጅራፉን ያሳርፉበታል። አንዳንድ ጊዜም ሰውዬውን በመግረፍ ፈንታ መሬቱን ይመታሉ። ጅራፉ ኃይለኛ በመሆኑ ሰውዬውን በደንብ ቢገርፉት ኖሮ እዚያው ይሞት ነበር። በዚህ አኳኋን አንድ ጊዜ አንድ ሰው ተገርፎ ሲያበቃ ልብስ ከመልበሱ በፊት በዚያው ሲሞት እኔ ራሴ አይቻለሁ። ጥፋተኞች ቅጣታቸውን የሚቀበሉት በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ፊት ለፊት ስለሆነ የሰውዬውን ሞት ወዲያውኑ ገልጸውለት ሙዋቹ ወደተገረፈበት ቦታ እንዲመለስና ከዚያም በኋላ የሚገረፉት ሰዎች የሙቱን እግሮች እንዲሳለሙ ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ።

መነኩሴውና አብረውት የነበሩት ሰዎች ከእሁድና ከቅዳሜ በስተቀር ሁለት ሳምንት ሙሉ እላይ በገለጽሁት አኳኋን ሲቀጡ ቆዩ። ይህ መነኩሴ የተገኘበት ደብዳቤ በአምባው ላይ የሚገኙት ልዑላን ፖርቱጌዞች ከዚያ እንዲያወጡዋቸው በመለመን ለነርሱ የተጻፈ ነው የሚል ወሬ በቤተ መንግሥቱ በስፊው ተነዝቶ ነበር። እኛ በንደዚህ ያለ ጉዳይ ውስጥ በፍጹም አልገባንም፤ መነኩሴውም እንደኛው መሆኑን አምናለሁ።

ነገር ግን እኛ በዚያ በነበርንበት ጊዜ እንደሚባለው የአስራ ስድስት ዓመት ዕድሜ የነበረው አንድ የንጉሠ ነገሥቱ ወንድም ከአምባው አምልጦ ወደ እናቱ ቤት ሄደ፤ ይሁን እንጂ ከአምባው አምልጠው የሚወጡትን ልዑላን መጠጊያ የሰጠ ሰው ይሙት በቃ ይፈረድበታል የሚል አዋጅ ስለነበር እቴጌይቱ ልጅዋን አስራ ለንጉሠ ነገሥቱ አሳልፋ ሰጠችው። ንጉሠ ነገሥቱም በምን ምክንያት ነው የሸሸኸው ብሎ ወንድሙን ቢጠይቀው ረሃብ ስለጸናብኝ ወደዚህ መምጣቴ የሚላከኝ ሰው ስላጣሁ ነው ሲል መለሰለት ይባላል። ንጉሠ ነገሥቱም ወዲያውኑ መልካም ልብስ አልብሶት ወርቅና የሐር ጨርቅም ሸልሞት ወደአምባው መለሰው ይላሉ። በቤተ መንግሥቱ የሚገኙት ብዙዎች ሰዎች እንደሚያወሩት ደግሞ ልጁ ከአምባው የሸሸበት ምክንያት ከፖርቱጌዞች ተቀላቅሎ ለማምለጥ ፈልጎ ነው ይላሉ።

እኛና ወደፖርቱጋል የሚሄደው የኢትዮጵያ አምባሳደር ንጉሠ ነገሥቱ የሰጠውን የቡግናን ግዛት ለመረካከብ ሲሄድ በላሊበላ በነበርንበት ጊዜ ካመለጠበት ተይዞ ወደአምባው የተወሰደውን ይህን የንጉሠ ነገሥቱን ወንድም ብዙ ሰዎችና አንድ ቀላጤ ከበውት በዚያ በኩል አለፉ፤ እስረኛውና የተቀመጠባትም በቅሎ ዓይኖችዋና ጆሮዎችዋ ብቻ ሲቀሩ በሙሉ በጥቁር ጨርቅ ተሸፍነው ነበር። በእግር የሚሄዱት ሰዎች እንደሚያወሩት ይህ ልጅ የመነኩሴ ልብስ ለብሶ ከአንድ መነኩሴ ጋር ሲሄድ ከንጉሠ ነገሥቱ ግዛት በሚወጡበት ቀን በዚያኑ ዕለት መነኩሴው ማን መሆኑን ስላወቀው አሣሥሮ ይዞት መጣ ይላሉ። ከበቅሎይቱ ግራና ቀኝ ሆነው ደግፈውት ከሚሄዱት ሰዎች በስተቀር ማንም እንዲያነጋግረው ወይም እንዲጠጋው አልተፈቀደም ነበር። ብዙዎች ሰዎች ይሞታል ወይም ዓይኑን ያፈሱታል እያሉ ያወሩ ነበር፤ መጨረሻው ምን እንደነበር አላውቅም።

አሁን በሕይወቱ ያለ አንድ ሰው ከአምባው አምልጦ በቅጠላቅጠል ውስጥ ገብቶ እንደተቀመጠ ድንገት ቅጠሉ ስለተወዛወዘ በዚያው አጠገብ ያርሱ የነበሩ ገበሬዎች ተጠግተው ሰውዬውን ስላገኙት ይዘው አሠሩት፤ ጠባቂዎቹም ያን ሰው በእጃቸው እንዳስገቡት ወዲያውኑ ዓይኑን አፈሰሱት ይባላል። ይህ ሰው የንጉሠ ነገሥቱ አጎት ነበር ይላሉ።

በአምባው ላይ ብዙ ሰዎች አሉ ይባላል፤ ሁሉም ዘመዳሞች ስለሆኑ ኢፍላቂታ [1] ወይም የእስራኤል ልጆች፤ ወይም እንደ ንጉሠ ነገሥቱ የዳዊት ልጆች ይባላሉ። በዚህ አውራጃ በዙ ቤተ ክርስቲያኖችና ገዳሞች ቄሶችና መነኩሴዎችም ይገኛሉ ይባላል።

ምዕራፍ ስልሳ ሁለት፤ የንጉሠ ነገሥቱ ዘመዶች፤ አጼ ዳዊትና ልጆቹ፤ በአምባው ላይ ለሚኖሩ እስረኞች የተፈቀደላቸው መተዳደርያ።

በዚህ አገር ንጉሠ ነገሥቱ ዘመድ እንደሌለው ሰው ሆኖ ነው የሚቆጠር፤ ምክንያቱም በእናቱ በኩል ያሉት እንደ ዘመድ አይታዩም። በአባቱ በኩል ያሉትም በግዞት ስለሚያዙ እንደሞቱ ያህል ነው የሚገመቱ። ምንም እንኳ በግዞት እንዳሉ ቢጋቡና እንደሚባለውም ብዙ ልጆችም ቢኖራቸውም ከዚህ በላይ እንደጠቀስሁት ንጉሠ ነገሥቱ ወራሽ ሳይተው የሞተ እንደሆነ ችሎታ ያለውን ተስማሚ የሆነ ቅርብ ዘመድ ይነግሥ ዘንድ ከመካከላቸው ይወሰዳል እንጂ በሌላ አኳኋን በፍጹም አይወጡም። አንዳንድ ሴቶች ለመዳር ከአምባው ውጭ ይወጣሉ ይባላል፤ ምንም እንዚህ ሴቶች የንጉሥ ቤተ ሰብነት የማይካድ ቢሆንም እንደ ንጉሠ ነገሥት እህቶች ወይም ልጆች አይቆጠሩም። የሚከበሩት አባታቸው ወይም ወንድማቸው በሕይወቱ እስካለ ድረስ ሲሆን እነዚህ ከሞቱ በኋላ ግን እንደ አንድ ተራ ሴት ነው የሚቆጠሩት ይባላል። የንጉሠ ነገሥቱ የአጎት ልጅ የነበረች አንዲት ሴት ምንም እንኳ ጃንጥላ እየያዘች ብትሄድም በጣም ያንገዋለልዋት መሆንዋን እኔና ጓደኞቼ በቤተ መንግሥቱ በነበርንበት ጊዜ አይተናል። የዚችው ሴትዮ ልጅ ልክ ተራ አሽከር መስሎ ተጎሳቁሎ አይተነዋል፤ ስለዚህ ዘመዱ ማለት ንጉሠ ነገሥቱ ሲሞት የንጉሥ ዘርነቱ ይረሳል።

አሁን አልጋውን ይዞ የሚገኘው አጼ ዳዊት እኛ ከዚያ ሳንነሳ ሁለት ወንዶች ልጆች ተወልደውለት ነበር። ለነዚህ ልጆች ሰፋፊ ርስት ሰጥቶ ተከላቸው። ያንደኛው ልጅ ሰፊ ርስት የሚገኝበትን ቦታ እኔ ራሴ አይቼዋለሁ። የሆነ ሆኖ አባትዬው ሲሞት ከሁለቱ አንዱ ስለሚነግሥ ሌሎቹን ሃብት ሳያስከትሉ ወደ ግሸን አምባ ይወስዱዋቸዋል ይባላል። ከንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላላ ወጭ ሲሶው ለነዚህ ልዑላንና ኢፍላቂታዎች የሚወጣ መሆኑንና ንጉሠ ነገሥቱም ግዞተኞቹን ከርሱ በፊት የነገሡት ነገሥት ካደረጉት አብልጠ

እስረኞቹን አከባክቦ ይዞአቸዋል ማለትን ሰምቻለሁ። ከተፈቀደላቸው ግብር በላይ ብዙ ወርቅና ሐር ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት ጨርቅ እንዲሁም እንደወርቅ ተቆጥሮ በአገሩ በመላ የሚገበይበትን አሞሌ ጨውም ይልክላቸዋል ይባላል። እኛ በዚያ እንደደረስን ካበረከትንለት በርበሬ ግማሹን ለዘመዶቹ ወደአምባው የላከላቸው መሆኑን ሰምተናል። ከዚህም በላይ አባቴ የፖርቱጋል ንጉሥ ሰው ልከው ስላስጎበኙኝና ይህንንም በርበሬ ስለላኩልኝ በጣም ደስ ብሎኛል ሲል ጨምሮ ልኳል። በኛ አገር ነገሥታቱ እንዳላቸው የቤተ ርስት ሃብት ዓይነት ንጉሠ ነገሥቱም በአገሩ ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታዎች ሰፋፊ እርሻዎች ያሉት መሆኑን በማየታችን አረጋግጠን ለማወቅ ችለናል።

እነዚህ እርሻዎች ወይም የቤተ ርስት ምድሮች የሚታረሱትና የሚዘሩት በንጉሠ ነገሥቱ አሽከሮችና በሬዎች ነው። አሽከሮቹን ስንቅና ልብስ የሚሰጣቸው ንጉሠ ነገሥቱ ነው። እነዚህ እየተጋቡ ከማንም ይልቅ የበለጠ ነፃነት አግኝተው የሚኖሩ ሰዎች የጥንት ባሮች ዘሮች ናቸው ይባላል። በአምባው አጠገብ ካሉት እርሻዎች የሚገኘው ሰብል አብዛኛው በአምባው ውስጥ ላሉት እሥረኞች ይላካል። የተረፈውም ለገዳሞችና ቤተ ክርስቲያኖች እንዲሁም በፊት ርስት ለነበራቸው አሁን ደህይተው ለሚገኙ መኳንንት ይሰጣል። ለኛ ለፖርቱጊዞቹም ከዚሁ ሰብል ሁለት ጊዜ ማለት በአክሱም እንደነበርን አምስት መቶ ጭነት፤ በአቋት እንደነበርን ሌላ አምስት መቶ ጭነት ተልኮልን ነበር። ስለዚህ ከመሬቱ የሚገኘው ከላይ በተመለከተው አኳኋን ተከፋፍሎ ያልቃል እንጂ ለንጉሠ ነገሥቱ ገቢ የሚሆን ወይም የሚሸመት አይተርፍም።

ምዕራፍ ስልሳ ሶስት፤ ከአንጎት ወጥተን በአማራ ግዛት ስለመጣባታችን፤ አንድ ቀላይና በውስጡም ስለሚገኙ ደሴቶች፤ ወደ አሰል ያደረግነው ጉዞ፤ መነኩሴው አምባሳደሩን ወደ አንድ ተራራ ሊመራው ስለመፈለጉ።

ጉዞአችንንና መንገዳችንን እንደገና በመቀጠል አንድ ደረቅ ወንዝ ተከትለን በተራራው ጥግ ወደላይ ወጣን። ይህ የምንጓዝበት ቦታ በጣም የሚያምርና ማሽላና ልዩ ልዩ የአገሩ እህሎች በቅለውበት የሚገኙበት ነው፤ ስንዴ ግን አላየንም። በወንዙ ግራና ቀኝ በሚገኘው ዳገት ላይ ብዙ ሰዎች የሚኖሩባቸው መንደሮች አሉ። ሸለቆው ካለቀ በኋላ ከወንዙ ወጥተን ጥሻና ድንጋያም ቦታ እንዲሁም የገብስና የስንዴ በአገሩ የሚገኙ የልዩ ልዩ አትክልት እርሻዎችም ደረስን። ይህ ቦታ የአንጎትና የአማራ ግዛቶች ድንበር ነው። ከዚህ ቦታ እልፍ ሲሉ በአማራ ግዛት ውስጥ በስተ ምስራቅ በኩል የሚገኝ ባጠገቡ ያረፍንበት ርዝመቱ ሶስት ሌግዋ ያህል ስፋቱም ከአንድ ሌግዋ የሚበልጥ አንድ ቀላይ አለ።[1] በቀላዩ መካከል ባለች ደሴት ውስጥ የቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኝባት አንዲት ደሴት አለች። በገዳሙ ውስጥ ብዙ ሎሚ፤ ብርቱካንና ትርንጎ ይገኛል።

ጀልባ መሥራት ስለማያውቁ ሸንበቆ ባንድነት አስረው አራት ትልልቅ ቅሎች አስረውበት በዚሁ ነው ሰውን የሚያሸጋግሩ። ይህ መቃ በፖርቱጋል የሳጣራ ንጣፍ የሚሠራበት ነው። ጀልባው ወይም መሸጋገሪያው ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው የተሠራው፤ አስቀድመው አራት እንጨት ያጋድሙና በእንጨቱ ላይ አጠጋግተው መቃ ያኖሩበታል፤ በመቃው ላይ ሌላ አራት እንጨት አምጥተው እንደማገር ከሥር ካሉት ጋር ያነባብሩትና በዳርና ዳር የወጡትን ጫፎች ባንድነት አጥብቀው ያሥሩዋቸዋል። በያንዳንዱ ማዕዘን ላይ ትልቅ ቅል ያሥሩበትና ከተዘጋጀ በኋላ ይሸጋገሩበታል። ይህ ቀላይ በክረምቱ ጎርፍ ብዛታ ምክንያት ስለሚሞላ በሁለት በኩል ውኃ ወደውጭ ያፈሳል ይባላል። በቀላዩ ውስጥ ልዮ ልዮ ዓይነት አሣዎችና ጉማሬ ይገኛሉ፤ በተለይም ጭንቅላቱ በጣም አስቀያሚ

ገላው ለስላሳ የሆነ በዓለም ከሚገኙት አሣዎች ሁሉ ሥጋው የሰባና ጣእም ያለው አንድ ልዩ አሣ አለ። እስከ ቀላዩ ድረስ የሚመጡ በዙርያው የሚገኙ ብዙ መንደሮች አሉ። በቀላዩ አካባቢ ባለ ከሁለት ወይም ሶስት ሌግዋ በማይበልጥ ቦታ ውስጥ የአሥራ አምስት ሹሞች ግዛት አለ ይባላል። በዚህ አገር ካየኋቸው ቀላዮች ሁሉ ትልቁ ይህ ሐይቅ የተባለ ቀላይ ነው።

ከዚህ ተነሥተን በጥሻውና በረግረግ ምድር ማሽላ በተዘራበት ውኃማ ምድር አድርገን አራት ሌግዋ ተጓዝን። ስንጓዝ ውለን ሁላችንም በድከም ላይ እንደነበርን ወደ ማታ ሲሆን መነኩሴው ለአዳር ወደ አንድ ትልቅ ተራራ ሊወስደን ፈለገ። የዚህን ጊዜ አምባሳደሩ እኔ ቀጥተኛ መንገድ ይገቼ ለመጓዝ እንጂ ከአገር ወደ አገር ልጓዝ አልመጣሁም፤ ለምግብም እንደሆነ ዕድሜ ለፖርቱጋል ንጉሥ፤ ዋና አዛዡ የሰጠን ወርቅና ብር፤ በርበሬና ጨርቅም ይዘን መጥተናልና በዚሁ እየገዛን ለመመገብ እንችላለን፤ ያገሩ ሰዎች ምግብ ሲያመጡልን አንተ በቅሚያ ባትወስድባቸው ኖሮ ከየመንገዶቹ ራቅ ብለን እስከ ሠፈርንበት ቦታ ድረስ እንኳ ቢሆን ያመጡልን ነበር፤ ነገር ግን አንተን በመፍራት አያመጡልንም አለው። እኛ በአውራ ጎዳናው አጠገብ ባንድ ሜዳ ላይ አረፍን። መነኩሴው ሰዎቹን አስከትሎ ወደ ተራራው ሄዶ እኩለ ሌሊት ሲሆን ምግብና ጠጅ ላከልን። ከዚያ ካደርንበት ቦታ አርብ ዕለት ተነሥተን ስንሄድ መነኩሴው ግን አልመጣም፤ ወይም መልእክተኛ አላኩብንም። ዕቃችንን የሚሸከሙልንም ሰዎች አልመጡም ነበር።

አንድ ሌግዋ ያህል እንደተጓዝን አንድ የመነኩሴው አሽከር መጥቶ ቅዳሜና እሁድን ለማሳለፊያ ተስማሚ የነበረውን የመጀ መርያውን ከተማ እንዳናልፍ ጠይቆን እኛም በሃሳቡ በመስማማት በዚህ ቦታ እንደደረስን ደስ የሚያሰኝ ሆኖ ስላገኘነው ልናልፍ አልፈቀድንም። ይህ ዙርያውን ሜዳ በሆነ በሁለት ወንዞች መካከል በሚገኝ ኮረብታ ላይ የተቆረቆረ ከተማ አሰል[2] ይባላል። በሜዳው ላይ ብዙ የማሽላ እርሻ፤ ልዩ ልዩ እህሎችና ስንዴም የተዘራባቸው ምድሮች አሉ።

ይህ አሰል የተባለ ከተማ ገበያ የሚውልበት ጥሩ ቦታ ነው። ከአንደኛው ወንዝ ማዶ በባርያ ንግድ የከበረ ሐርና ሌላ ልዩ ልዩ ሸቀጥም የሚገኝበት ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት በትግሬ መኮንኑ ግዛት ድንበር እንደሚገኘው ማናደሌይ እንደተባለው ከተማ ዓይነት የእስላሞች ከተማ ይገኛል። እንደሌሎቹ ሁሉ በዚህ ቦታም የሚገኙት እስላሞችም ለንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ግብር ይከፍላሉ ይባላል። ክርስቲያኖች ወንዶችና ሴቶች ለእስላሞቹ ውኃ እየቀዱላቸው ልብሳቸውንም ስለሚያጥቡላቸው በዚህ ቦታ በክርስቲያኖችና በእስላሞች መካከል የተቀራረበ ግንኙነት አለ። ክርስቲያኖቹ ሴቶች ፈንጠር ብሎ በሚገኘው በእስለሞቹ ከተማ ይሄዳሉ፤ ይህም አድራጎት ሴቶቹን በአጉል ተግባር እንድንጠረጥራቸው አስገደደን። ከመንደሩ አጠገብ በሚገኝ ባንድ ሜዳ ላይ ቅዳሜና እሁድን በቆየንበት ጊዜ ሌሊቱን ነብር ስለመጣብን የኛ ሰዎች በጦር ሲከላከሉ ስላደሩ እኛም ከብቶቹም ዕረፍት አጥተን ነበር ያደርነው። በዚሁ ቦታ ባንዲት ትንሽ ምክንያት አምባሳደሩና ጊዮርጊስ ዲ አብሬው ተጣሉ።

ብዙ ሕዝብ በሚኖርባቸው ተራሮች መካከል ባለ እህል በሚገኝበት ሰፊ ሜዳ አልፈን ሰኞ ዕለት ሁለት ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ ገደልና ድንጋይ ወይም ጥሻ በሌለበት በሙሉ ታርሶ የተዘራ አንድ ትልቅ ተራራ ላይ ወጥተን የቀትር ዕረፍት አደረግን። ይሁን እንጂ አሰል በነበርንበት ጊዜ በመካከላችን በተነሣው አለመግባባት ምክንያት ተኮራርፈን ስለነበርን ለየብቻችን ተቀምጠን ነበር ያረፍነው። በዚህ አጠገብ ካለ ትንሽ ቁጥቋጦ ዘንድ ሆኖ ሰፋፊ እርሻዎች ይታያሉ። አስር ወይም አስራ ሁለት የሚሆኑ ታላላቅ አገሬዎች አጠገቤ መጥተው ተቀምጠው ያረፍንበትን ተራራ ርዝመትና ከጫፉም ሆኖ ብዙ ተራራዎች የሚታዩ መሆናቸውን ባስተርጓሚ እርዳታ ማውራት ጀመርን። ከዚህ በፊት የጠቀስሁትን ከነበርንበት ቦታ ሶስት ወይም አራት ሌግዋ ያህል ርቆ የሚገኘውን ልዑላኑ የሚታሠሩበትን አምባም አሳዩኝ። ከዚያ በፊት ያየነውን ቋቋኝ የሚመስለው በዚያ ምሽግ ላይ ያለው የድንጋይ ግድግዳ ወደ አባይ ስለሚያቆለቁል የሚያልቅበትን ቦታ ለማየት አይቻልም። ይህ አሁን ያለንበት ተራራ በጣም ከፍ ያለ ስለነበር ያ የልዑላን መታሠርያ ምሽግ ከግርጌአችን

ያለ መስሎ ይታይ ነበር። ልዑላኑ በንዴት ያለ የግዞት ሁኔታ እንደሚያዙና በብዙም ሰዎች የሚጠበቁ መሆናቸውን ምግብና ልብስም በገፍ የሚሰጣቸው መሆኑን እነዚህ ሰዎች በዝርዝር ገለጹልኝ። ከዚያ ጀምሮ የዓይን አንጻር ሊያርፍበት እስከሚችለው ድረስ ያለው በስተምዕራብ በኩል የሚገኘው ግዛት ምን እንደሚባልና የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት መሆኑን ለማረጋገጥ ብጠይቃቸው፤ ከነበርንበት ጀምሮ አንድ ወር መንገድ የሚያስሄደው የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ሲሆን ቀጥለው የሚገኙት ተራሮችና ምድረ በዳ ናቸው፤ ከዚያ በኋላ ግን በጣም ክፉዎች የሆኑ ጥቁር ሰዎች የሚኖሩበት ነው አሉኝ[1]። ይህን በነገረኝ ሰው አገማመት የአሥራ አምስት ቀን መንገድ ስፋት ያለውን የነዚህን ነገዶች አገር ካለፉ በኋላ ከቱኒዚያ የመጡ ነጭ እስላሞች በሚኖሩበት ቦታ ይደረሳል። (ከቱኒዚያ እስከ ካይሮ ከዚያም ኢትዮጵያ ድረስ ነጋዴዎች ሁልጊዜ ስለሚመላለሱ በዚህ አልተደነቅሁም።) እነዚህ ነጋዴዎች መናኛ በርኖስና ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት ሸቀጥ ያመጣሉ። የነበርንበት ይህ ቦታ የማሽላና የስንዴ አውራጃዎች ድንበር ላይ የሚገኝ በመሆኑ ወደፊት በመንገዳችን ላይ የምናየው እህል ስንዴና ገብስ ብቻ መሆኑን ነገሩን።

ምዕራፍ ስልሳ አራት፤ ወደ አንድ ሌላ ቀላይ ሄድን፤ የመካነ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ልንጎበኝ ሄደን እንዳንገባ ስለመከልከላችን።

በዚህ ተራራ ቁመት ስንዴና ገብስ በተዘራበት መሬት አድርገን ሶስት ሌግዋ ያህል ተጉዘን በፊት ካየነው ቀላይ የሚያንስ በግምት ቁመቱ አንድ ሌግዋ ስፋቱም ግማሽ ሌግዋ የሚሆን አንድ ሌላ ቀላይ አገኘን[1]። ከዚህ ጥልቅ ከሚመስል ዙርያውን በመቃ ከተከበበ ቀላይ የሚነሣ አንድ ወንዝ አለ። በክረምቱ ወራት ከተራሮቹ ላይ ከሚመጣው ጎርፍ በስተቀር ወደ ቀላዩ የሚፈስ ወንዝ የለም። አንድ ጨፌ ቦታ ላይ ለማዳር ሄደን ሌሊቱን ትንኞች ሲነክሱን ስላደሩ ልንተኛ አልቻልንም ነበር።

በተራራው አጠገብ የተጠራቀመውን ውኃ ሕዝቡ እየቆፈረ ወደ ውጭ በማሸራሸር መሬቱን ለጥቅም ማዋል ስለማያውቅ፤ ያ ስፈረግረግ ቦታ ለከብት ማሰማርያ ሆኖ ቀርቶአል። ብዙ ታላላቅ ከተማዎችና ሰፋፊ የገብስና የስንዴ እርሻዎች አይተናል። ከዚህ ቦታ ወደፊት በመቀጠል በትልልቅ ሸለቆዎች አድርገን ወደፊት ስንሄድ በጣም ቅጭጭ ያለ የስንዴና የገብስ ሰብል አየን። ባንዳንዱ እርሻ ላይ ያለው ሰብል ውኃ ተኝቶበት ያበላሸው ይመስል ብጫ ሆኖ ይታያል። ሌሎችም በውኃ እጦት ደርቀው በማየታችን እህሉ በምን ምክንያት ሊበላሽ መቻሉ አልገባንም።

ከዚህ በኋላ ቀኑ ብዙ በሚሞቅበት ሌሊቱም በሚበርድበት ባንድ አውራጃ መግባት ጀመርን። በዚህ አውራጃ ድኃው ወንድ አጭር ቆዳ ያገለድማል። ሻል ያሉ ሰዎች የሚገኙ በጥቂት ብቻ ስለሆነ ሰዉ በመላ ድኃ ነው ለማለት ይቻላል። ሴቶቹ ወንዶቹ ከሚያሸርጡት ቆዳ ጥቂት ረዘም በሚል ጨርቅ እግዚአብሔር የፈጠረላቸውን ሲሸፍኑ ሌላው ሰውነታቸው ግን ይራቆታል። ጠጉራቸውን በሁለት ይከፍሉትና አንደኛው ክፍል በትከሻቸው ላይ ሲወድቅ ሌላው ደግሞ በዚሁ ላይ ያልፍና በጆሮ ግንዳቸው ላይ ይንጠለጠላል። እነዚህ ቦታዎች ለንጉሠ ነገሥቱ ጥሩንባ ነፊዎች የተሰጡ ናቸው። ከመንገዱ ጥቂት ወጥቶ ወደ ቀኝ በኩል ሲሄዱ በተራራው አጠገብ አንድ ትልቅ ጫካ ይታያል፤ በጫካው አጠገብ አንድ ንጉሥ ያሠራውና የተቀበረበት ብዙ ደብተራዎች የሚገኙበት አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አለ። የዚያኑ ዕለት ብዙ ተራራዎችን አልፈን ስንጓዝ ከዋልን በኋላ ከተራሮቹ ርቆ በሚገኝ ስፊ ሜዳ መግቢያ ላይ ደርሰን በዚያው አደርን።

መስከረም 26 ቀን ጠዋት በዚያ ሜዳ አንድ ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ መካነ ሥላሴ [2] በተባለ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ደረስን። ንጉሠ ነገሥቱ የአባቱን አጽም በዚህ ቤተ ክርስቲያን ባዛወረበት ጊዜ ከርሱ ጋር ወደዚያ ሄደናል። ይህ ቤተ ክርስቲያን አንደኛው ከድንጋይ ሌላውም ከጠርብ የተሠሩ ሁለት አጥሮች አሉት።

ጠርቡ አጥር ዙርያውን ርዝመቱ አንድ ሌግዋ ይሆናል፤ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ መነኩሴው ብዙ አውርቶልን ስለነበር በዚያው አጠገብ አድረን ለመጎብኘት ስንሄድ ካህናቱ አላስገባ አሉን። እኛ ከቤተ ክርስቲያኑ አጥር የአንድ ወንጭፍ ውርወራ ያህል ርቀን በምንገኝበት ጊዜ አንድ ሰው እየሮጠ መጥቶ ከበቅሎቻችን እንድንወርድ ጠየቀን፤ ይህን የመሰለ ተግባር ያገር ልምድ መሆኑን በማወቅና በተለይም ለዚህ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ልዩ አክብሮት ሲባል ከሌሎች ይልቅ ከሩቅ ከበቅሎ የሚወረድ መስሎን እንደተጠየቅነው አደረግን። በእግራችን ወደፊት ቀጥለን ከደጀሰላሙ ስንደርስ በዚያ ተሰብስበው የነበሩ ሰዎች እንዳንገባ ከለከሉን። እኛን ብቻ ሳይሆን እዚያ ድረስ መርቶ ያመጣንንም መነኩሴ ጭምር እጃቸውን በደረታችን ላይ አድርገው እንዳንገባ ከለከሉን። ከጭቅጭቁ ብዛት ወደ ጸብ ደርሰን ስለነበር ክርስቲያኖች ነን ብለን ማስረዳታችን ብቻ በቂ አልሆነንም ነበር። ከዚህ ቦታ በመሄድ ወደፊት ጥቂት እልፍ ካልን በኋላ ሰዎች ከኋላችን እየሮጡ መጥተው ለማስገባት ፈቃድ ተሰጥቶናልና ተመለሱ አሉን፤ ነገር ግን እኛ ወደኋላ ለመመለስ ስላልፈቀድን የቤተ ክርስቲያኑንና የሕንፃውን ሁኔታ አልጎበኘንም። ይህ ቤተ ክርስቲያን የተቀረቀረበት ቦታና አቀማመጡም እንደሚከተለው ነው፤ አጥሩ የተሠራው ላዮ ሜዳ በሆነ ኮረብታ ላይ ሲሆን የኮረብታው ዙርያም ሜዳ ነው። ከኮረብታው በላይ ባለው ክፍል አንድ ሌግዋ፤ በሌላው በኩል ሁለት ሌግዋ ደግሞ በሌላው በኩል ሶስት ሌግዋ በስተግርጌ ማለት በስተደቡብ በኩል አራት ወይም አምስት ሌግዋ ስፋት አለው። ያ ግሩም የሆነ ምድር አንድ ስንዝር ያህል እንኳ ሳይቀር በሙሉ ታርሶ ከማሽላ በስተቀር ልዩ ልዩ ዓይነት እህል ተዘርቶበት ይታያል። ይህ ሜዳ ዓመቱን በሙሉ ቡቃያ አለበት፤ አንዱ ሲታጨድ አንዱ ይዘራል። ከቤተ ክርስቲያኑ በስተኋላ በኩል ለጥ ባለ ሜዳ ላይ የሚያልፍ አንድ ወንዝ ስላለ የዚያን ሜዳ አብዛኛውን ክፍል በመስኖ ወኃ የሚያጠጡት በዚሁ ወንዝ ውኃ ነው። ከተራራው የሚፈልቁ ሌሎች ጅረቶች ስላሉ እርሻዎቹ በሙሉ ውኃ ያገኛሉ። በዚህ ሜዳ ላይ ለየብቻቸው ተሠርተው የሚገኙ አንዳንድ ቤቶች ይታያሉ። ቤተ ክርስቲያኖች ያሉባቸው ታናናሽ መንደሮችም አሉ፤ ምንም እንኳ የንጉሠ ነገሥታት ቤተ ክርስቲያኖች ቢኖሩም ገበሬዎቹ እነዚህን ቤተ ክርስትያኖች እንዳይስሙ አይከለከሉም።

ምዕራፍ ስልሳ አምስት፤ ንጉሠ ነገሥታቱ በነዚህ አውራጃዎች ስላሠሩዋቸው ቤተ ክርስቲያኖች፤ የአብራን[1] መንደር ጎብኝተን ከዚያም በትልልቅ ደረቅ ወንዞች ስለመጉብኘታችን።

ከዚህ በላይ በጠቀስሁት ሜዳ ከተጓዝን በኋላ በሌላ ታለቅ ሜዳ ገባን፤ ነገር ግን ይህ ሜዳ ረግረጋም ስለሚመስል በደንብ ታርሶ አልተዘራበትም። ሰፋፊ የሣር ቦታዎችና ሐይቆች ይገኛሉ፤ መሬቱን ረግረግ የሚያደርገው ከሐይቁ የሚፈሰው ውኃ ነው። ቁጥራቸው በጣም የበዛ ላሞችና በሬዎች በጎችም ነበሩ፤ (ፍየሎች ግን አልነበሩም።) ከአውራ ጎዳናው ራቅ ያሉ በያንዳንዳቸውም ቤተ ክርስ ቲያን የሚገኝባቸው ብዙ መንደሮች አሉ። በዚህ ቦታ አስር ወይም አስራ ሁለት ሌግዋ ያህል ወደ ምስራቅ ከተጓዝን በኋላ የንጉሠ ነገሥቱ አያት አጽም የሚገኝበትን የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን አሳዩን። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ወደፊት አትታለሁ።

የትግሬ መኰንኑና የባሕር ነጋሹ ግዛቶች ነገሥታት ግዛታቸውን በነዚህ በአሕዛብ አገሮች ላይ እያስፋፉ ከአንጎት ወደዚህ ወደ አማራ አውራጃ እየመጡ ብዙ ጊዜ ይቀመጡ ስለነበር ለመቀበር ያቸው ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ጥለው መተዳደርያም ሰጥተዋቸው ነበር ሲሉ ነገሩኝ። አሁን ያለው ንጉሠ ነገሥት አባት አጼ ናአድ ሲሞት ለዚያ ላስጀመረው ለመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያንና ለሌሎችም መተዳደርያ እንዲሆን ይህን አውራጃ አንድ ስንዝር እንኳ ሳይቀር በሙሉ ተናዞ ስለሞተ ልጁ ያባቱን ፈቃድ በመፈጸም እንዲሰጥ አደረገ።

የነዚህ የነገሥታት ቤተ ክርስቲያኖች መኖር በብዛት ለሚገኙት ለተራው ሕዝብ ቤተ ክርስቲያኖች እንቅፋት ሊሆኑ አልቻሉም ነበር። የአስራ አምስት ቀን መንገድ በሚፈጀው በመካነ ሥላሴ ምድር ስንጓዝ ከዚህ በፊት በጎበኘናቸው አገሮች ካየናቸው በስተቀር አንድ ገዳም እንኳ አላየንም ወይም አለ ማለትን አልሰማንም፤ የምናያቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያኖች የደብተራዎች ናቸው፤ የገበሬዎቹ ግን የቄሶች ናቸው።

ይህ አውራጃ ለጊዜው ገዥ አልነበረውም፤ በዚህ አውራጃ ላይ ለገዥነት የሚሾው ሁሉ «አማራ ጣፊላ»[2] የሚያሰኝ ማዕርግ ይሰጣቸዋል፤ ትርጓሜውም የአማራ ንጉሥ ማለት ነው። እንዲሁም የሸዋ ንጉሥ «ሸዋ ጣፊላ» በሚያሰኝ ስም ይጠራል። የአጼ ናአድ አጽም እስከተዛወረበት ይህ አውራጃ ራሱን ችሎ በዚያ ይገኝ ነበር።

እኛ ፖርቱጊዞቹ ለጎበኘነው ለመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተፈቀደው የአማራ ጣፊላው ግዛት ከንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ላይ ተወስዶ በሙሉ አባትዬው እንደተናዘዘው ለቤተ ክርስቲያኑ ተሰጠ። በዚህ ቦታና በማናቸውም ግዛት የሚገኙቱ ቤተ ክርስቲያኖች፤ ደብተራዎችና ካህናት ሁሉ ከጦርነት በስተቀር በማናቸውም ነገር ንጉሠ ነገሥቱን ያገለግላሉ። ለደብተራዎቹም ሆነ ለካህናቱ ወይም ለመነኩሴዎቹ ሕጉ እኩል ነው። በዚሁ መሠረት እኛን ይመራን የነበረው መነኩሴ ዕቃችንን ሲያሸክምልን ሕዝቡ የታዘዘው ከመሆኑ በላይ ካህናትንና መነኩሴዎችን ለመግረፍ ሥልጣን ነበረው።

በዚህ ሰፊ ሜዳ አገር ስንሄድ ዓይን የሚያርፍበት አንድም ነገር ስለማይታይ በእውነቱ ከተራሮቹ ርቀን በባሕር ላይ የምንሄድ ነበር የሚመስለው። ቅዳሜንና በመስከረም ወር መጨረሻ ላይ የዋለውን እሁድን የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በሚገኝበት ባንድ ምስኪን ቆሻሻ መንደር ነበረ። በስተምስራቅ በኩል በዚህ ቤተ ክርስ ቲያን አጠገብ ሲያዮዋቸው የሚያስፈሩ ተራሮችና ገደሎች ይጀምራሉ። የነዚህ ገደሎች ጥልቀት የሰው ልጅ ከዚህ በፊት ካያቸው ሁሉ የበለጠ ነው። የተራሮቹም ጫፍ እስራኤላውያን እንደሚኖሩበት አንባ ላያቸው ተጠርቦ የተስተካከለ ይመስላል። የተራሮቹ ግርጌ በጣም ሰፊ ነው፤ በኛ አገማመት አንዳንዶቹ አራት ሌሎቹም አምስት ደግሞ ሌሎቹም ሶስት ሌግዋ ስፋት አላቸው።

ይህ ገደል ከዚህ ብዙ ርቆ እስከሚገኘው እስከ አባይ ወንዝ ይደርሳል ይባላል፤ በላይ በኩል ደግሞ እስከ እስላሞች አገር እንደ ሚደርስ እናውቃለን። በእስላሞቹ አገር የሚገኘው ክፍል እንደ ዚህኛው በጣም የሚያስፈራ አይደለም ይባላል፤ በዚህ ገደል ግርጌ

ብዙ መንደሮች ይገኛሉ። ቁጥራቸው በጣም የበዛ ከወገባቸውም በላይ የአንበሳን ጉፈር የመሰለ ጠጉር ያላቸው ብዙ ዝንጀሮዎች ይገኛሉ።

<u>ምዕራፍ ስልሳ ስድስት፤ የሸዋ ግዛት በሚጀመርበት ባንድ የተፈጥሮ በር ደረስን።</u>

ሰኞ ጥቅምት 1 ቀን 1520 ዓም ሐይቆችና የከብቶች መሠማርያ ባሉበት ባንድ ሰፊ ሜዳ አድርገን ገደሉን በመከተል ሶስት ወይም አራት ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ ወንዙን በምንሻገርበት አጠገብ አደርን። ማክሰኞ ጠዋት መንገዳችንን ጀምረን ግማሽ ሌግዋ ያህል እንደተጓዝን በግራ ቀኝ የሚገኙ ሁለት ገደሎችን የሚለያይ ባንድ ትልቅ የተፈጥሮ በር ደረስን። ይህ በር እጅግ ጠባብ ከመሆኑ የተነሣ ከአንድ ሠረገላ በስተቀር ሌላ ሊያስገባ አይችልም። መዝጊያው በተዘጋ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር ቦታውን በሙሉ ይገጥመዋል። ይህን በር አልፎ በአንድ ጥልቅ ሸለቆ ውስጥ ሲገቡ ያንድ ጦር ቁመት ያለው የኀራዴ ስለት የመሰለ ድንጋይ በሸለቆው በግራና ቀኝ ቁሞ ይታያል። በዳርና ዳር የሚገኙት ድንጋዮች ቁመት ሁለት ጉጉሽድ መልያው[1] የሆነ በጣም ጠባብ ነገር በመሆኑ አንድ ሰው በፈረስ ላይ ተቀምጦ ሊያልፍበት አይችልም። በቅሎዎቹ በዚያ ሲያልፉ እርካባቸው ግድግዳውን ይነካል፤ ይህ ቁልቁለት ሰው የሠራው ይመስል በጣም ቀጥ ያለ ስለሆነ ወደ ታች ሲወርዱ በእጅ እየተመረኮዙ መሄድ ያስፈልጋል። ከዚህ በር አልፈን ጥቂት እንደተጓዝን አራት ስንዝር ያህል ስፋት ባለው ባንድ ትልቅ ቦይ ደረስን፤ ከቦዩ ግራና ቀኝ ከትልቅነቱ ብዛት ለማመን የማይቻል አለት አለ፤ እኔ ራሴ እንኳ ባላየው ኖሮ ታላቅነቱን ቢነግሩኝ ላምነው አልችልም ነበር። በቅሎቻችንና ሰዎቻችን ሲያልፉበት ባላይ ኖሮ ፍየል እንኳ ያለ ሥጋት ታልፍበታለች ብዬ ለማመን አልችልም ነበር። ከብቶቹን

ወደ አደጋ ቦታ የሚመራ ሰው ይመስል ሌላ መንገድ ባለመኖሩ በቅሎቻችንን በገደሉ ቁልቁል መርተናቸው እኛም በእጃችን እየተመረኮዝንና እየቡዋጠጥን ተከተልናቸው። ይህ ገደላም መንገድ ያንድ ወንጭፍ ውርወራ ርቀት አለው፤ ስሙም አህያ ፈጅ ይባላል። በዚህ ቦታ ቀረጥ መክፈል ግዴታ ነው።

በዚህ በር ባለፍንበት ቁጥር ከገደል ላይ ተንከባለው የወደቁ ወይም ወደላይ ሲመጡ አንሸራትቶአቸው ቁልቁል ተገለባብጠው የሞቱ ከብቶች ሬሣ እናይ ነበር። ይህን ቦታ ካለፉ በኋላ ሁለት ሌግዋ ያህል ርቀት ያለው ጎድጓዳና ድንጋያም አስቸጋሪም የሆነ መንገድ አለ። በቁልቁለቱ መንገድ መካከል ከላዩ ውኃ የሚፈስበት አንድ የድንጋይ ዋሻ አለ። በዚህ ዋሻ ሁልጊዜ ለማኞች አይጠፉም። ሁለት ሌግዋ ያህል ከተጓዝን በኋላ ብዙና ትልልቅ አሦች በሚገኙበት ወንጭት በተባለ ወንዝ ደረስን። ካንድ ሌግዋ የማያንስ ዳገታም መንገድ ከተጓዝን በኋላ ከአፋፉ ላይ ሆኖ ሌላ ወንዝ[2] በሚታይበት ባንድ ሌላ ሸለቆ ደረስን። በዚያ ለጊዜው የማይሠራባቸው በሮች አሉ። ሸለቆውን ከዳር እስከዳር ባንድ ቀን ለመሻገር ስለማይቻል መንገደኞች በዚህ ቦታ ያድራሉ። መሪያችን መነኩሴው በዚህ ባረፍንበት ቦታ ክርስቲያን ሊያደርገው የማይገባ ወይም በእስላም ላይ የተፈጸመ ይመስል አንድ አስቃቂ የሆነ የጭካኔ ተግባር ፈጸመ። እኛ ካረፍንበት ቦታ በስተራስጌ በኩል የሚገኙት መንደሮች ሹም ከመንደረተኞቹ ጋር ሆኖ ሊቀበለን ስላልመጣ የርሱን ሰዎችና ዕቃችንንም የተሸከሙልንም ሰዎች ወደቦታው ልኮ በመንደሩ አጠገብ የተዘራውን የባቄላ አዝመራ እንዲያጠፉበት አዘዘ። የተላኩት ሰዎች መንደረተኞቹ የሚመገቡትን ከአንድ ሞዩ[3] በላይ የሆነ ባቄላ ዘርፈው አመጡ፤ በዚያ ሸለቆ ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች ከባቄላና ከማሽላ በስተቀር ሌላ እህል አያመርቱም። ያን አዝመራ ሲበላሽ ማየት በእውነተኛው የሚያሳዝን ነገር ነበር። ይህን በማድረጉ ተቃውመነው ነበር፤ ነገር ግን በአገሩ የተለመደ ፍርድ ነው ሲል መልስ ሰጠን፤ ዕቃችንን ያልተሸከሙልንን ሰዎች ሁሉ በየቀኑ ከማስገረፉም በላይ የማይታዘዝ ሁሉ መቀጣት አለበት እያለ በቅሎቻቸውን ላሞቻቸውንና ጥንድ በሬዎቻቸውን ሁሉ ይወስድባቸው ነበር።

ማክሰኞ ጥቅምት 2 ቀን ከዚህ በፊት ያየነውን የመሰለ ለማመን የሚያስቸግር ድንጋያም ጠባብና አደገኛም በግራና ቀኝ ትልልቅ አለት ያለበትን መንገድ አልፈን ብዙ ሌግዋ ከተጓዝን በኋላ አሣ በሚገኝበት ጀማ በተባለ ወንዝ ደረስን። ይህ ወንዝና ወንጭት ይገናኙና ከአባይ ጋር ይቀላቀላሉ ይባላል። ባለፈው ቀን ቁልቁለቱን ስንወርድ አሁን ግን በትልቅ ዳገት እየተጓዝን መንገዳችንን ቀጠልን። ሁለት ሌግዋ ያህል ባንድ ቁልቁለት መንገድ ከተጓዝን በኋላ ከዚህ በፊት በእህያ ፈጅ ላይ ያለፍነውን በመሰለ በሌላ ኬላ ደረስን። ይህ ኬላ ሁልጊዜ እንደተዘጋ ነው፤ በላይም ሆነ በታች ሌላ መተላለፊያ ስለሌለ በዚያ የሚያልፉ ሁሉ ቀረጥ መክፈል አለባቸው።

ከኬላው ግማሽ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ባንድ ሜዳ አደርን። እዚያ ቦታ ከደረስን በኋላ ያለፍነውን ሽለቆ አለትና ድንጋይ የመሰለ ሁለተኛ አይታይም ነበር። እንዲያውም በመካከሉ ምንም የማይ ታይበት ለጥ ያለ ሜዳ መስሎ ይታይ ነበር። ካንዱ በር እስከ ሌላው ያለው ርቀት አምስት ሌግዋ ይሆናል። ያማራንና የሸዋን ግዛቶች የሚያዋስኑ እነዚህ በሮችና ሸለቆዎች ናቸው። በሮቹ በደበጅ ይባላሉ፤ ተርጓሚውም አዲስ አገር ማለት ነው። በነዚህ ሸለቆዎችና ገደሎች ውስጥ ብዙ አእላፋት ወፎች ይገኛሉ። ገደሉ ከልክ ያለፈ ትልቅና ቀጥ ያለ ስለሆነ እነዚያ ወፎች እንዴት አድርገው ጫጩቶቻቸውን በዚያ እንደሚያሳድጉና እንዴትስ ተንከባለው እንደማይወድቁ ተገረምን።

ምዕራፍ ስልሳ ሰባት፤ የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ዮሐንስ ሞትና በርሳቸው ፈንታ ሌላ እጨጌ ስለመመረጡ።

ጥቅምት ሶስት ቀን ከገደሉና አለቱ እምብዛም ርቆ በማይገኝ ሜዳ በኩል አድርገን ስንጓዝ ከዋልን በኋላ በደብረ ሊባኖስ ገዳም በስተቀኝ በኩል በሚገኝ በንድ ትልቅ ተራራ ላይ ወጥተን አደርን።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ገዳሙ ሶስት ጊዜ ሲሄድ አይቻለሁ። ለመጀመርያ ጊዜ ያየሁት ዮሐንስ የተባሉ የገዳሙ ሃላፊ በሞቱ ጊዜ ሊያስቀብር ሲሄድ ነው። የገዳሙ ሃላፊ እጨጌ በሚያሰኝ መጠርያ ይታወቃሉ። ከሁሉ በላይ ከሆኑት ከአቡነ ማርቆስ ቀጥሎ በአገሩ በሙሉ ከፍተኛ ማዕርግ ያላቸው የዚህ ገዳም እጨጌ ናቸው። ንጉሠ ነገሥቱ የእጨጌው ተዝካር በወጣበት ወር ለሁለተኛ ጊዜ እንዲሁም ከእጨጌው ሞት አርባ ቀን በኋላ ሌላ እጨጌ ለመምረጥ ለሶስተኛ ጊዜ ሄዶ ነበር። ሙዋቹ ልዩ ልዩ ተአምራት የፈጸሙ ቅዱስ ሰው ነበሩ ስለሚባል ንጉሠ ነገሥቱ በቀብሩና በተዝካሩ የተገኘው በዚህ ምክንያት ነው። ከኛ ጋር ይጓዝ የነበር የትውልድ አገሩ ሊዝቦን የሆነ አልአዛር ዲ አንድራድ የተባለ የታወረ አንድ ፖርቱጊዝ ሰዓሊ ነበር። ይህ ከሙዋቹ መቃብር አጠገብ ሄዶ በሙሉ እምነት ቢታጠብ ሊፈወስ የሚችል መሆኑን በመግለጽ ወደዚያ እንዲሄድ ንጉሠ ነገሥቱ አዞት ሄዶም ነበር፤ ነገር ግን በነበረበት ሁኔታ ተመለሰ።

አዲስ የተመረጠውም እጨጌ በቅድስና የሚኖር ሰው ነበር። ይህ ሰው በፊት እስላም ነበር። የግል ወዳጄ ስለነበር ታሪኩን ቀጥሎ እንደ ተመለከተው ገለጸልኝ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ራዕይ ተገልጾልኝ እንዲህ የሚል ድምጽ ሰማሁ፤ የምትሄድበት መንገድ መልካም አይደለም፤ የኢትዮጵያ ካህናት ሃላፊ ወደሆነው ወደ አቡነ ማርቆስ ሂድ እርሱም ሌላ መንገድ ያሳይሃል። ከዚያም በኋላ ወደ አቡነ ማርቆስ ሄጄ የሰማሁትን ነግሬአቸው አጥምቀውኝ የክርስትና አባት ሆኑኝ አሉኝ። ስለዚህ ከተጠመቀ በኋላ ያዕቆብ የተባለውን ይህን ሰው የገዳሙ ሃላፊ እንዲሆን ንጉሠ ነገሥቱ ሾመው። ያዕቆብ ወዳጄ ስለነበር ሁል ጊዜ ከኔ አይለይም ነበር። ፖርቱጋልኛም በደንብ አጥንቶ ስለነበር ያለችግር ሃሳብ እንለዋወጥ ነበር። በአገሩ ፊደል ቅዳሴ ጸጋን፤ ጸሎተ ሃይማኖትን፤ የጌታችንን ጸሎት፤ ውዳሴ ማርያምን፤ የሐዋርያት እምነትንና ሳልቬ ሬጂናን ራሱ ጽፎ በላቲንኛ ከኔው እኩል ያውቃቸው ነበር። የዮሐንስን ወንጌልም ገልብጦ በደንብ በሐረግ አጊጦ ይዞ ነበር። ያዕቆብ መኖርያውን በገዳሙ አደረገ። እጨጌ ማለት የገዳም ሃላፊ ማለት ነው። በትግሬ መኮንኑና በባሕር ነጋሹ ግዛቶች ቋንቋ በትግርኛ ግን እንደዚህ ያለ ሥልጣን ያለውን

ሰው አባ ይሉታል። አለቃውና ከርሱም ቀጥሎ ያለው አባ ይባላሉ። ከዋናው ቀጥሎ ያለው ባለሥልጣን በዚህ ቋንቋ ገበዝ ይባላል ሲሉ ሰምቻለሁ። ይህ የተፈጸመው በምንጓዝበት ጊዜ ሳይሆን ንጉሠ ነገሥቱ ከነአጀቡ መጥቶ ከገዳሙ አንድ ሌግዋ ተኩል ርቆ በሚገኝ ትልቅ ሜዳ ላይ ባረፈበት በሌላ ጊዜ ነው። ገዳሙ የሚገኘው ካለፍነው ኬላ ከሚጀምር ባንድ ገደል ውስጥ ነው።

መንገዳችንን እንደገና ጀምረን ከዚያ ገደል እጅግ ርቆ በማይገኝ አንድ ሜዳ ላይ ሐሙስንና አርብን ተጉዘን ስናበቃ ከመሬት ውስጥ ተቆፍረው የተሠሩ የሚመስሉ መንደሮች በሚገኙበት በንድ ቦታ ደረስን። ቤቶቹ በንደዚህ ያለ አኳኋን የሚሠሩበት ምክንያት መንደሩ በአውላላ ሜዳ ላይ ስለሚገኝ ነፋሱን በመፍራት ነው። ከብቶቹም ከነፋሱ እንዲድኑ በማለት ከመሬቱ ውስጥ ተቆፍሮ በተሠራ በረት ውስጥ ነው የሚኖሩት። በዚህ ቦታ የሚኖሩት ሰዎች ወሰካሞችና ቡቱቶ ለባሾች ሲሆኑ ብዙ ከብቶች ማለት የቀንድ ከብቶች፣ ፈረሶችና በቅሎዎች ያረባሉ። ከመንደሮቹ ዙርያ ከዚህ በፊት ካየነው ሁሉ በይበልጥ የፋፋ ትንሽ የገብስ አዝመራ አየን። ባንድ እርሻ ላይ ሶስት ወይም አራት አልኬይርሽ[1] የሚሆን ዘር ይዘሩበትና ከዚህም ያንድ ወንጭፍ ውርወራ እልፍ ካሉ በኋላ ይህንኑ የሚያህል በሌላ እርሻ ይዘራሉ። መሬቱ የተከፋፈለ ስለሆነ እያንዳንዱ መንደር የራሱን እርሻ ዘርቶ ይታያል። ምንም እንኳ መሬቱ በጣም ጥሩ ቢሆንም በደንብ ስላልተሠራ እያንዳንዱ ገበሬ ወይም ነዋሪ ስድስት አልኬይርሽ አያመርትም። በሜዳው ላይ ቀላዮች ስላሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ወፎች ይገኛሉ። ሕዝቡ ወፎችን ማጥመድ አያውቅም። አውራጃው ወግዳ ይባላል።

<u>ምዕራፍ ስልሳ ስምንት፤ ሶስት ቀን በሜዳ ላይ ተጓዝን፤ የበሽተኞች መፈወስና የሰዎች መታየት።</u>

ሰኞ ጥቅምት 9 ቀን መንገዳችንን ጀምረን በለምለምነቱና በአዝመራው ከዚህ በፊት ያለፍነውን የሚመስል ሜዳ ስንጓዝ ውለን እንዳ በተባለ መንደር ደርሰን በዚያው አደርን። ለእራት የበላነው ምግብ በጣም መጥፎ ሆኖ የተዘጋጀ የገብስ እንጀራ ነበር። በማግሥቱ ማለት ማክሰኞ ዕለት መንገዳችንን ቀጥለን በሜዳው ላይ ስንጓዝ ውልን ጥቂት ቤቶች በሚገኙበት ባንድ መንደር አደርን። ረቡዕ የመስኖ ገብስና ስንዴ በተዘራበት ደህና ምድር ደረስን። ይህ አሁን የደረስንበት ቦታ ብዙ ሕዝብ የሚኖርበትና ብዙ ከብቶችም የሚገኙበት ተጉለት ይባላል።

በዚህ ቦታ ትኩሳት ያደረበቸው ብዙ በሽተኞች አሉ፤ በሽተኞቹን በሙሉ ምንም ዓይነት ሕክምና ሳያደርጉ እንዲያው ይተዋቸዋል። ይሁን እንጂ ራስ ምታት ያደረበትን በሽተኛ ዋግምት ያደርጉለታል። ሆድ ቁርጠት የወገብና የትከሻ ሕመም ያደረበትንም ሰው በእሳት ይተኩሱታል። ትኩሳት የያዘውን ሰው ምንም መድኃኒት አያደርጉለትም።

በዚሁ ቀን የንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን የተጣለበትን ቦታ በሩቁ አየን፤ እኛም እንደተለመደው ከመንገዳችን ወጥተን ባንድ ቦታ አደርን። ሐሙስና አርብ ብዙ አልተጓዝንም፤ ቅዳሜና እሁድ ባንድ ቦታ ለማረፍ ፈልገን ገና ሥዕል ያልተሳለበት አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚገኝበት ባንድ መንደር ደርሰን በዚያው ቆየን፤ ቤተ ክርስቲያኖቹ ሁሉ ምንም እንኳ መናኛ ዓይነት ቢሆኑም ሥዕል ይገኝባቸዋል። ይህ ቤተ ክርስቲያን ስሙ በሐዋርያት የሚታወቅ ሲሆን በተለይ ለነገሥታት የተሠራ ነው ይባለል። ቤተ ክርስቲያኑ ንጉሠ ነገሥቱ ባረፈበት ቦታ ሶስት ወይም አራት ሌግዋ ያህል፤ አቡነ ማርቆስ ተቀምጠውበት ከነበሩበት ቦታ አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ ይገኛል። ቅዳሜና እሁድን በዚህ ቦታ ባረፍንበት ጊዜ በምጽዋ ላይ ሲደርሱ

ከኛ መርከቦች ወጥተው የጠፉ ሶስት መርከበኞች ወደኛ መጡ። ያ መነኩሴ የነዚህን ሰዎች ወደኛ መምጠት በማወቅ ወደ አገሩ የሚመጡ እንግዶች ሁሉ ከንጉሠ ነገሥቱ ከመገናኘታቸው በፊት ከሌላ ሰው ጋር መነጋገር ያገር ልምድ አይደለም ሲል ተቆጥቶ ወዳረፈበት ቦታ ተመለሰ። የዚያኑ ዕለት ማለት ቅዳሜ መነኩሴው አቡነ ማርቆስ ዘንድ ሄዶ ሲመለስ አንድ ቅርጫት ዘቢብና አንድ ማድጋ የወይን ጠጅ አመጣልን። በማግሥቱ እሁድ ከመርከበኞቹ አንዱ ለሁለተኛ ጊዜ ሊጎበኘን መጣ፤ ነገር ግን አምባሳደሩ የመነ ኩሴውን ቅር መሰኘት በማወቅ መርከበኛው ወደ መነኩሴው እንዲ ሄድና የማጣበት ምክንያት ከኛ ጋር ስለነበረው ታላቅ ወዳጅነት እንጂ ለሌላ መጥፎ ምክንያት ያለመሆኑን እንዲገልጽለት አዘዘው። ይህን ሰው መነኩሴው ባየው ጊዜ ተይዞ እንዲታሠር አዘዘ። እኛ ደርሰን በቁጣ ቃል ተናግረን ባናስጥለውማ ኖሮ በእግር ብረት ሊታሠር ነበር። መነኩሴውም በማማረር የውጭ ሰው ሲመጣ መጀመርያ ንጉሠ ነገሥቱን መገናኘት ስላለበት እናንተ አስቀድ ማችሁ ከርሱ ጋር መነጋገር የለባችሁም አለን።

ምዕራፍ ስልሳ ዘጠኝ፤ አንድ መኮንን ባልደረባ ተሰጥቶን ድንኳን እንዲጣልልን ስለማዘዙ።

ንጉሠ ነገሥቱ ከነአጀቡ ከሠፈረበት ከተማ አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ ከሚገኘው ከዚያ ካደርንበት ቦታ ጥቅምት 17 ቀን ተነሥተን የዚያኑ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ በሠፈረበት ለመድረስ ተጓዝን። በማግሥቱ ጠዋት ከዚያ የሚወስዱን መስሎን ስንጠብቅ ሳለን ሕዱግ ራስ በሚ ያሰኝ የማዕርግ ስም የሚጠራ አንድ መኮንን ወደኛ መጥቶ እናንተን ለመከተልና የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ለመስጠት ነው የመጣሁት አለን። ወዲያውኑ በቅሎቻችንን እንድንቀመጥና እንድንከተለው አዘዘን። እኛም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ የሚወስዱን መስሎን የታዘዝነውን ፈጸምን። ነገር ግን ይህ መሆኑ ቀርቶ እርሱ እየመራን

ወደኋላ ተመልሰን ኮረብቶች እያዞርን አንድ ሌግዋ ያህል ተጓዝን። ንጉሠ ነገሥቱም በዚሁ መንገድ ይመጣሉና ቅር አይበላችሁ አለን። ከፊታችን ስድስት ፈረሰኞች በጥሩ ፈረሶች ሆነው ጉግስ እየተጫወቱ ብዙዎችም በበቅሎ ሆነው ይሄዱ ነበር።

ከኮረብቶች በስተኋላ በኩል ሠፍረን ያ መኮንን በራሱ ድንኳን ውስጥ ሲያርፍ እኛም ይዘነው የመጣነውን ያንኑ ደሳሳ ድንኳናችንን በርሱው አጠገብ አስተክለን ዐረፍን። የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ እንዲሰጠን አዘዘልን። ይህ ያረፍንበት ቦታ ከመንገዱ በጣም ውጭ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም እኛ ባለንበት ዘንድ ከተመ። ረቡዕ ጠዋት አንድ ትልቅና ክብ ድንኳን አመጡልንና ይህን ድንኳን የመሰለ ከንጉሠ ነገሥቱና ከቤተ ክርስቲያኖች በስተቀር ሌላ ሰው የሌለው መሆኑን ገልጸውልን እርሱ በጉዞው ላይ ባለ ጊዜ የሚያርፍበት የግል ድንኳኑ መሆኑንና ከርሱም ዘንድ የተላከልን መሆኑንም ጨምረው ነገሩን። ምን ማድረግ እንደሚገባን ሳናውቅ በዚህ አኳኋን እስከ አርብ ድርስ ቆየን። ባልደረባችን የሆነው መኮንንና መነኩሴው ወደኛ መጥተው በዚህ አገር ብዙ ሌቦች አሉና ተጠንቀቁ አሉን፤ ይህንኑ ቃል ባገሩ ውስጥ የሚገኙ ፈረንጆችም አረጋገጡልን። ከዚህም በላይ ለሠረቁት ሃብት ግብር የሚከፍሉ ደንበኛ ድርጅትና ጭፍሮች ያሉዋቸው ሌቦች ያሉ መሆናቸውን ጨምረው አስረዱን።

ምዕራፍ ሰባ፤ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ስለመቅረባችን፤ ስለአቀራረባችን ሁኔታና ስለንጉሠ ነገሥቱም።

አርብ ጥቅምት 20 ቀን የሶስት ሰዓት ጸሎት በሚደረግበት ጊዜ መነኩሴው ወደኛ ሲሮጥ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ በፊታቸው እንድትቀርቡ ስለፈቀዱ ያመጣችሁትን ዕቃ ይዛችሁ እንድትቀርቡ፤ ሌላውንም ዕቃችሁን ለማየት ስለሚፈልጉ ይዛችሁ እንድትቀርቡ ብለዋል አለን። ነገር ግን የባሕር ኃይል አዛዡ ከላከው ገጸ በረከት

በስተቀር ሌላ ዕቃ እንዳይሄድ አምባሳደሩ አዞ የተባለው ገጸ በረከት ብቻ ተጫነ። እግዚአብሔር ይመስገን እኛም በደንብ ለብሰን እንደ ተሰናዳን የሚያጅቡን ብዙ ሰዎች መጡ። በዚህ አኳኋን ሄደን ባንድ ትልቅ በር ስንደርስ ንጉሠ ነገሥቱ ከትሞ የተቀመጠበት ቦታ ይታይ ጀመር። በዚያ ከሚታዩት አንዳንድ ነጫጭ ድንኳኖች ፊት ለፊት አንድ ቀይ ድንኳን ተተክሎ ነበር። ይህ ድንኳን የሚተከለው ድግስ በተደገሰ ጊዜ ወይም ትልቅ እንግዳ በመጣ ጊዜ ነው ይባላል። ከተተ ከሉት ድንኳኖች ፊት ለፊት አንድ በቀይ ሌላውም በነጭ ጨርቅ የተጠቀለሉ ሁለት ረድፍ ቅስቶች ነበሩ። ቅስቶቹ የመስቀል መያገ እንጨት ይመስል በጨርቆቹ ተጠቅልለዋል። በዚህ አኳኋን ቅስቶቹ እስከ ዳር ድርስ ይሄዳሉ። በያንዳንዱ ተራ በግምት ሃያ ቅስቶች አሉ። በስፋቱና በቁመቱ ትንሽ የቤተ ክርስቲያን ቅስት ይመስላል። አንዱ የቅስት ተራ ከሌላው አንድ ጦር ድ መልያው ይርቃል። በዚህ ቦታ ከሃያ ሺ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በያንዳንድ በኩል በደንብ ተሠልፈው ቁመው ይታያሉ። በደንብ የለበሱት ሰዎች ከቅስቱ ተጠግተው ቁመዋል። በደንብ ከለበሱት ውስጥ የቀይ ሐርና ሌላም ዓይነት ቀብ የደፉ ደብተራዎችና ቄሶች ሌሎችም ሰዎች ይገኙባ ቸዋል። ጥሩ ከለበሱት ከነዚህ ሰዎች ፊት ለፊት ባማረ ኮርቻና ግላስ ተጭነው በወርቀ ዘቦ ጨርቅ የተሸፈኑ አራት ፈረሶች ማለት ሁለቱ በግራ ሁለቱ በስተቀኝ በኩል ቁመው ነበር። በነዚህ ፈረሶች ላይ የተጫነው መጣርያ ወይም ስለት ነገር ምን መሆኑን አላውቅም። የፈረሶቹ መጣብር በፊርጥ ያጌጠና በዘርፍ የሚያልቅ ነው። እነዚህ ፈረሶች ከቆሙበት ቦታ በታች የነበሩ ነገር ግን እንደነዚህ ያላጌጡ የተጫኑ ሌሎች ብዙ ፈረሶች ይታያሉ። እነዚህ በተራ ተሠልፈው ከሰዎቹ ጋር ወደረኛ መስመር ገብተው ነበር፤ ከፈረሶቹ በስተኋላ በኩል በጣም የተከበሩ ከወገባቸው በታች ነጭ ስስ ጨርቅ ያሸረጡ ሰዎች ከነርሱም በኋላ ተራው ሕዝብ ተደርበ ቆሞአል።

ከንጉሠ ነገሥቱና ከመኳንንቱ ፊት ልምጭና ጅራፍ ይዘው የሚቆሙ አጋፋሪዎች ሁልጊዜ ይገኛሉ፤ አጋፋሪዎቹ ጅራፉን ሲያጮሁት ሕዝቡ ገለል ይላል። ከኛ ፊት አንድ መቶ የሚሆኑ አጋፋሪዎች ጅራፋቸውን እያጮሁ ይሄዱ ስለነበር በጅራፉ ጩኸት ምክንያት

የሕዝቡ ድምጽ አይሰማም ነበር። እኛን አጅበው የመጡት ሰዎች ከመድረሳችን በፊት ራቅ ብለው ከፈረሶቻቸውና ከበቅሎቻቸው ሲወርዱ እኛ ግን ሳንወርድ ከድንኳኑ ለመድረስ ያንድ ወንጭፍ ውርወራ ርቀት ሲቀረን ወረድን። ያጀቡን ሰዎች እጅ ነስተውን እኛም እንደተማርነው ቀኝ እጃችን መሬት እስኪነካ ድረስ እጅ ነሳን። በፊታችን ባለው ያንድ ወንጭፍ ውርወራ ርቀት መንገድ ስልሳ የሚሆኑ መልእክተኞች ወደኛ ሲሮጡ መጡ፤ የሚሮ ጡበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱን መልእክት በሚያድርሱበት ጊዜ ሁልጊዜ መሮጥ ልምዳቸው ስለሆነ ነው። እነዚህ ሰዎች ማለፊያ የሐር እጀጠባብ ለብሰው በትከሻቸው ላይ የአንበሳ ጉፈር ደርበዋል። የለበሱት ጎፈር ከሳድ በወርቅና መናኛ ሆኖ በተሠራ ሙካሽ አጊጦ፤ በአንገታቸውም ላይ ልዩ ልዩ ዓይነት የከበረ ድንጋይ አንጠልጥ ለዋል። በቀለሙና በስፋቱ የፈረስን የሚመስል ባለቀለም የሐር ቀበቶ ታጥቀዋል። በብዙ አኳኋን ይህ ቀበቶ የፈረስ ሲመስል የሚለ ይበት ረጅምና ጫፉም መሬት የሚነካ ስለሆነ ነው። እነዚህ ሰዎች ከሁለት በኩል መጥተው አጅበውን እስከ መጀመርያው ቅስት ድረስ ወሰዱን። ከቅስቱ ከመድረሳችን በፊት በመንገዳችን ላይ አራት አንበሶች በወፍራም ሰንሰለት ታሥረው ነበር።

በሜዳው መካከል በሚገኙት በመጀመርያዎቹ ቅስቶች ጥላ ሥር አራት መኳንንቶች ነበሩ። ከነርሱም ውስጥ አንደኛው በአገሩ ውስጥ ከሚገኙት ከፍተኛ ማዕርግ ካላቸው ቢትወደዶች አንደኛው ነበር። እነዚህ ሁለት ቢትወደዶች በንጉሠ ነገሥቱ ግራና ቀኝ የሚቆሙ ናቸው። የቀኝ ቢትወደዱ እስለሞችን ለመዋጋት በጦርነት ላይ ይገኛል አሉን። አሁን በዚያ ይገኝ የነበረው የግራ ቢትወደዱ ነበር። ከርሱ ጋር የነበሩት ሶስቱ መኳንንትም በጣም የተከበሩ ታላላቅ ሰዎች ናቸው። በነዚህ መኳንንት ፊት ስንደርስ እነዚያ እኛን ያመጡት ሰዎች እንዳደረጉት አደረግን። በዚያው እነርሱ ከኛ ጋር እኛም ከነርሱ ጋር ስንነጋገር ረጅም ጊዜ ቆመን ሳለን እንደ በርኖስ ሆኖ የተሰፋ የከች ካባ ደርቦ ለብቻቸው የቆሙት ቄሶች የጫኑትን የሚመስል ትልቅ የሐር ቆብ የጫነ የንጉሠ ነገሥቱ መምህርና ዘመድም ነው የሚሉት አንድ ሽማግሌ ቄስ ወደኛ መጣ።

ይህ ሰው ዐቃቤ ሰዓት በሚያሰኝ የማዕርግ ስም የሚጠራ በአገሩ ውስጥ ያለ ሁለተኛው ታላቅ ሰው ነው። ቄሱ ከቅስቱ ሁለት ግርግድ መልያው ርቆ ከሚገኘው ድንኳን ወጣ። በቅስቱ ዘንድ ከኛ ጋር ቆመው ከነበሩት መኳንንት ሶስቱ ከግማሽ መንገዱ ሊቀበሉት ሲሄዱ ከነዚህ ማዕርጉ ከፍ የሚለው ቢትወደዱ ከኛው ዘንድ ቆየ። ዓቃቤ ሰዓቱና ሌሎቹም ሲመጡ ቢትወደዱ ሶስት እርምጃ ያህል ወደፊት ሄዶ ከነርሱ ጋር ተቀብሎ አምስቱም ባንድነት ሆነው እኛ ወደነበርንበት መጡ። ባጠገባችን እንደደረሱ አምባሳደሩ ምን ፍለጋ እንደመጣና ከወዴትስ እንደመጣ አቃቤ ሰዓቱ ጠየቀው፤ አምባሳደሩም መልሶ የፖርቱጋል ንጉሥ እንደራሴ ሆኖ ሕንድን ከሚያስተዳድረው ጠቅላይ ገዥ በመልእክተኛነት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የመጣሁ ነኝ ሲል መልስ ሰጠ። ይህን ከጠየቀ በኋላ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሄዶ በፊት በመጣበት አኳኋን ሶስት ጊዜ ወደኛ መጣ። ሁለት ጊዜ መጥቶ ጥያቄ ሲያቀርብ አምባሳደሩም አንድ መልስ ሲሰጠው በሶስተኛው ጊዜ ግን ምን መልስ ልሰጥ እንደሚገባኝ አላውቅም አለ። ዓቃቤ ሰዓቱም መልሶ ለንጉሠ ነገሥቱ ልታቀርብ የምትፈልገውን ጉዳይ ለኔ ንገረኝና እኔ አቀርብላቸዋለሁ አለው። በዚሁ ጊዜ አምባሳደሩ መልሶ መልእክቱን ለንጉሠ ነገሥቱ እንጂ ለሌላ ሰው ልነግር አልችልም አለ። ከዚሁም በላይ የመጣንበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱን እጅ እንድንስም፤ እግዚአብሔር ክርስቲያንን ከክርስቲያን ስላገናኘ ለዚሁ ደስታችንን እንድንገልጽ ታዘን መሆናችንንና እኛም የመጀመርያዎቹ በመሆናችን መደሰታችንን አምባሳደሩ ገለጸ። ዓቃቤ ሰዓቱም ይህንኑ መልእክት አድርሶ እንደገና በበፊቱ አኳኋን በክብር ተመልሶ ጠቅላይ ገዥው የላከለት ገጸ በረከት እንዲቀርብለት ንጉሠ ነገሥቱ የጠየቀ መሆኑን ነገረን። በዚህ ጊዜ አምባሳደሩ ወደኛ መለስ ብሎ የያንዳንዳችንን ሃሳብ ጠየቀ። እኛም ገጸ በረከቱን እንዲልክ መክረነው ያመጣነውን ዕቃ አንድ በአንድ አውጥቶ ከዚህም በላይ ለኛ ስንቅ ከያዝነው አራት ጭነት በርበሬ አስረከበ። ገጸ በረከቱ በሙሉ ወደድንኳኑ ቀርቦ ከዚያም እንደገና እኛ ወደነበርንበት ቦታ መጥተው የሰጠናቸውን መጋረጃና ሌላውንም ማናቸውንም ነገር በቅስቱ ላይ ሰቀሉት። ማናቸውም አኳኋን በዚያ ከተዘረጋ በኋላ አፈ ንጉሡ ብድግ ብሎ

የሕዝቡን ጸጥታ ጠይቆ ጠቅላይ ገዥው ለንጉሠ ነገሥቱ የላከውን ገጸ በረከት አንድ በአንድ በከፍተኛ ድምጽ ከገለጸ በኋላ ክርስቲያንን ከክርስቲያን ላገናኘው አምላክ ሕዝቡ ምስጋና እንዲያቀርብ አዘዘ፤ ይህ አድራጎት ያሳዘነው ሰው ቢኖር ሊያለቅስ መቻሉን ያስደሰተውም ቢኖር ሊዘፍን መቻሉን ጨምሮ ገለጸ። በዚያ የነበረው ሕዝብ በከፍተኛ ድምጽ በመጮህ ረጅም ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋና ካቀረበ በኋላ አሰናብተውን ሄድን። ከንጉሣዊው ድንኳን ያንድ ጥይት ርቀት እልፍ ብሎ በሚገኝ ቦታ ተተክሎ ዕቃችን በሚገኝበት ወደድንኳናችን ሄድን።

ምዕራፍ ሰባ አንድ፤ ዕቃችን በተዛወረበት ጊዜ አንዳንድ ነገር ተሠረቀብን፤ ንጉሠ ነገሥቱ ስንቅ አዘዘልን፤ ከመነኩሴው ጋር ንግግር አደረግን።

ዕቃችን በመጣበት ጊዜ ከሌባ እንድንጠነቀቅ የነገሩን ደረሰ። ከኛ ጋር ሆኖ ሲያገለግለን የነበር አንድ አሽከር ዕቃ ይዞ በመንገድ ሲሄድ ወንበዴዎች አራት የመዳብና ሁለት የሸክላ ዕቃዎችና ሌሎችም የማዕድ ቤት መሣርያዎች ቀሙት፤ ይህ አሽከር ዕቃውን ለማስጣል ሲሞክር ደብድበውት አንድ እግሩን ከፉኛ አቆሰሉት። ሰውዬው አስፈላጊው ጥንቃቄ እንዲደረግለት አምባሳደሩ አዘዘ፤ ዕቃችን ግን እንደተሠረቀ ቀረ።

በዚያ እንዳረፍን ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሶስት[1] ነጭ እንጀራና ብዙ ገምቦ ጠጅ አንድ ፍሪዳም ተላከልን። ይህን ምግብ ያዘዘልን ንጉሠ ነገሥቱ መሆኑን ከዚህም በላይ ሃምሳ ፍሪዳዎችና ብዙ ጠጅም ያዘዘልን መሆኑን መልእክተኞቹ ነገሩን። በማግሥቱ ቅዳሜ ጥቅምት 21 ቀን በደንብ ሆኖ የተዘጋጀ ልዩ ልዩ ዓይነት ሥጋና እንጀራም መጣልን። እሁድም በዚሁ አኳኋን አስተናገዱን። ከተላከልን ምግብ

አንደኛው ዓይነት በደንብ ሆኖ የተዘጋጀ ያንድ ጊደር ሥጋ በሙሉ ነበር። በተለይም ይህ ምግብ በጣም ጣፍጦ ስለነበር የተሠራው ሳንጠግብ አለቀ።

በማግሥቱ ሰኞ መነኩሴው ወደኛ መጥቶ ለአንተና ለሰዎችህ እስከ ምጽዋ ድረስ አስፈላጊው ምግብ እንዲታዘዝላችሁ ከፈለጋችሁ የያዝኸውን ሁሉ በርበሬ ለንጉሠ ነገሥቱ ማስረከብ አለብህ ሲል ለአምባሳደሩ ነገረው። የታዘዙልን ሃምሳ ፍሪዳዎችና ጠጅም ብቻ ሳይሆን ማናቸውም ምግብ ተቋረጠብን። በአገሩ ውስጥ ይገኙ የነበሩት ፈረንጆች ሁሉ ከኛ ጋር አንዳች ግንኙነት እንዳይኖራቸው ተከለከሉ። ወዳገሩ የሚገቡ እንግዶች ሁሉ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ከመቅረባቸው በፊት ከድንኳናቸው መውጣት ያልተለመደ ነገር በመሆኑ እኛም እንዲሁ ከድንኳናችን እንዳንወጣ ተከለከልን። ካርኔሩ በሚያሰኝ የቁልምጫ ስም የሚጠራ በመንገድ አግኝቶ ያነጋገረን ፖርቱጌዝና አንድ ሌላ ፈረንጅም የቤተ መንግሥቱን ምስጢር ያወጣሉ ተብለው መታሠራቸውን እናውቃለን። ካርኔሩ በብረት እንደታሠረ ከሚጠብቀው ጃንደረባ አምልጦ ከነብረቱ እኛ ወደነበርንበት መጥቶ አደረ፤ በማግሥቱ ጥዋት ሰዎች ሊወስዱት መጥተው ነበር፤ ነገር ግን አምባሳደሩ ምንም ቢሆን አሳልፌ አልሰጠውም በማለት አሻፈረኝ ከማለቱ በላይ የንብረት ሹሙና አስተርጓሚው ወደ ቢትወደዱ ሄደው የፖርቱጋል ዜጎች በምን ምክንያት በብረት እንደሚታሠሩና ባርያ ጃንደረቦች እንዲያጉላሉዋቸው መደረጉን እንዲጠይቁለት ላካቸው። ቢትወደዱም ወደዚህ አገር እንድንመጣ ማን እንደጋበዘን በመጠየቅ ወደ ፖርቱጋል ሄዶ የነበረው ማቴዎስ ከንጉሠ ነገሥቱ ወይም ከእቴጌ እሌኒ ያልተላከ መሆኑን በመግለጽ ላከብን። ከዚህም በላይ መልእክቱን በመቀጠል ጃንደረባው ፖርቱጌዙን በብረት ማሠሩ እርግጥ ነው፤ ነገር ግን በአገሩ ሕግ መሠረት ፖርቱጌዙ ጃንደረባውን መልሶ በብረት ማሠር ነበረበት ሲል ገለጸልን።

<u>ምዕራፍ ሰባ ሁለት፤ ንጉሠ ነገሥቱ ከተማውን ለወጠ፤ አምባሳደሩ ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የሚችል መሆኑን መነኩሴው ነገረው፤ አምባሳደሩ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሄደ።</u>

ማስሰኞ ጥቅምት 24 ቀን ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ያቀርቡናል ብለን ስንጠብቅ አጀቡን አስከትሎ በመሄድ ሁለት ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ቦታ ከትሞ መቀመጡን ተረዳን። መነኩሴው ወደኛ ዘንድ መጥቶ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ከተማ መሄድ ከፈለግን ለዕቃችን ማስጫኛ አጋሰስ ልንገዛ እንደምንችል ነገረን፤ ወደ አምባሳደሩም ሄዶ መግዛትና መሸጥ ከፈለገ እንዲሁ ሊያደርግ የሚችል መሆኑን ገለጸለት። አምባሳደሩ መልሶ እኛ የመጣነው እግዚአብሔርንና ነገሥታትን ለማገልገልና ክርስቲያንን ከክርስቲያን ለማገናኘት እንጂ ለመነገድ አልመጣንም አለው። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን እርሱ ራሱ መነገድ መጥፎ ነገር መሆኑን ይናገር ነበር። ይህን የመሰለውን ነገር ያቀረቡበት ምክንያት የኛ ሰዎች ሃሳብ ምን እንደሆነ ለማቅ ሲሉ ነው።

ሐሙስ ዕለት ማለት ከሁለት ቀን በኋላ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ከተማ ሄደን ለዓቃቤ ሰዓቱና ለቢትወደዱ መልእክት እንድናደርስለት አምባሳደሩ እኔንና አስተርጓሚውን ዮሐንስ ጎንሳልቬሽን ላከን። እንድናደርስ የታዘዝነው ተግባር መነኩሴው የነገረውን ጉዳይ ነበር። መነኩሴውም ከኛው ጋር ሆኖ ወደከተማው ሄድን። ጉዳዩን ለቢትወደዱ በማቅረብ መነኩሴው ወደ አምባሳደሩ ሄዶ ለመሸጥና ለመግዛት ከፈለግህ ፈቅጄልሃለሁ ስላለው አምባሳደሩ በጉዳዩ በጣም የተገረመ መሆኑን በመጀመርያ ገለጽንለት። አምባሳደሩ በእናቱም ሆነ በአባቱ ወይም በአያቶቹ በኩል ንግድ የሚባል ሥራን ፈጽሞ የማያውቅ መሆኑንና ከርሱም ጋር የመጡት ሰዎች ይህን የመሰለ ልምድ የሌለባቸው መሆናቸውን ገለጽንለት። አምባሳደሩና ጭፍሮቹ በፖርቱጋል ንጉሥ ቤተ መንግሥት ያደጉና በተከበረ ሥራ ላይ የቆዩ እንዲሁም ለነገሥታታቸው ክብር በጦርነት ላይ በመዋጋት እንጂ በንግድ የማያገለግሉ መሆናቸውን ነገርነው። ከዚህም በላይ እዚህ አገር

በምንቆይበት ጊዜ ከተነሣንበት ከምጽዋ እስከንደርስ ድረስ አስፈላጊው ስንቅ እንዲሰጠን ከፈለግን የያዝነውን በርበሬ ሁሉ ለንጉሠ ነገሥቱ መስጠት ያለብን መሆኑን መነኩሴው ለአምባሳደሩ መንገሩን ጨምረን አስረዳነው። ፖርቱጌዞች ወርቅና ብር እየከፈሉ መመገብ እንጂ ምስኪኖችና ችግረኞች ሰዎች የለፉበትን በነፃ መብላትና መጠጣት ልምዳቸው ያለመሆኑን በማስገንዘብ፤ ይልቁንም በአገሩ ውስጥ የመገበያያ ገንዘብ አለመኖሩን በመረዳት ጠቅላይ አዛዡ ለመንገዳችን ከወርቅና ብር በላይ ብዙ በርበሬና ጨርቅ የሰጠን መሆኑንና ከዚሁም የግል በርበሬአችን አምባሳደሩ አራት ጭነት ለንጉሠ ነገሥቱ ማበርከቱን የተረፈውን እላይ ለተገለጸው ጉዳይ የምናውለው መሆናችንን ለቢትወደዱ ገለጽንለት። ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ከተማ መሄድ ከፈለጋችሁ አጋሰስ መግዛት ያስፈልጋችኋል ሲል መነኩሴው ያስታወቀን መሆኑንም ጨምረን ነገርነው። ከዚህም በላይ አምባሳደሩ ካለበት ቦታ ለመሄድ ፈቃዱ አለመሆኑንና ካገሩ በሚወጣበት ጊዜ ይገዛል እንጂ አሁን አጋሰሶች የማያስፈልጉት መሆናቸውን ጨምረን ነገርነው። የዚህን ጊዜ ቢትወደዱ አስር አጋሰሶች ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ተልከውላችኋል አልደረሱዋችሁምን ሲል ጠየቀን። በጉዞአችን ላይ በነበርንበት ጊዜ መነኩሴው ከሰጠን ሶስት ከደከሙ አጋሰሶችና ከሶስት ሰዎች በስተቀር የተባሉት አጋሰሶች ያልደረሱን መሆናቸውን ነገርነው። ለጠየቅነው ጉዳይ መልስ በመስጠት ፈንታ ከጉዳዩ ውጭ የሆኑ ለምሳሌ፤ የፖርቱጋል ንጉሥ አግብቶአልን፤ ስንት ሚስቶች አሉት፤ በሕንድ አገር ስንት ግንብ አሠርቶአል የሚልና እንዲሁም ይህን የመሳሰሉ ነገሮች ይጠይቀን ጀመረ። ከዚህም በላይ ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሩ ያመጣውን መልእክት መስማት የሚፈልግ ከሆነ ጉዳዩን በቀጥታ ለርሱ የሚያቀርብ መሆኑን፤ ካልፈለገ ግን በጽሑፍ እንጂ በሶስተኛ ሰው አማካይነት ሊነግረው የማይችል መሆኑንን ጨምሮ እንዲገልጽለት አምባሳደሩ ቢትወደዱን መጠየቁን ነገርነው።

የመጨረሻውን መልእክት በነገርነው ጊዜ ትንሽ ጠብቁ መልስ ይሰጣችኋል ብሎን ምንም የተጨበጠ ነገር ሳንይዝ ተመለስን። እስከዚያ ጊዜ ድረስ በቤተ መንግሥቱ ይታዩ የነበሩ አንዳንድ

ፈረንጆች ከኛ ጋር እንዳይቀላቀሉ ተከልክለው ነበር። አልፎ አልፎ ቢመጡም በድብቅ ነበር። መነኩሴው እንደጠባቂያችን ሆኖ ከኛ ጋር ነበር የሚኖረው።

ምዕራፍ ሰባ ሶስት፤ በኢትዮጵያ ስለሚኖሩ ፈረንጆች፤ ወደዚህ አገር አመጣጣቸው ታሪክ፤ ያመጣነውን በርበሬና ዕቃም እንድንሰጥ እኛን ስለመምከራቸው።

ከዚህ በላይ በመደጋገም ስለፈረንጆች ስላተትሁ ስለነርሱ ጥቂት ልገልጽ እፈቅዳለሁ። የሕንድ ጠቅላይ ገዥ የነበረው ሎፑ ስዋርሽ ብዙ መርከቦች አሰልፎ ወደጅዳ በመጣ ጊዜ (እኔም አብሬ መጥቼ ነበር) በዚሁ ስም በምትጠራው ደሴት ውስጥ የልዩ ልዩ አገር ዜጋ የሆኑ ቱርኮች የማረኩዋቸው ሰላሳ ወንዶች ክርስቲያኖች አገኘን። በቤተ መንግሥቱ ያገኘናቸው እንደነገሩኝ በኛ መርከቦች ውስጥ ዘሎ ለመግባት ቆርጠው እግዚአብሔር መልካም ፈቃዱ ሆኖ ፖርቱጌዞችን እንዲያመጣላቸው ይጠብቁ ነበር። ነገር ግን የሎፑ ስዋርሽ መርከብ ከየብሱ ባለመድረሱ መቅረት ግድ ሆነባቸው። ወዲያውኑ ከጥቂት ቀኖች በኋላ ከነዚያ ፈረንጆች አስራ ስድስቱና ብዛታቸውም ይህንኑ የሚያህል ኢትዮጵያውያን እሥረኞች ሁለት ጀልባ ሰርቀው የኛን መርከቦች ፍለጋ አመለጡ። ነገር ግን መርከቦቹ በነበሩበት በካማራን ደሴት መድረስ ስላልቻሉ በሐርኪኮ አጠገብ በሚገኘው በኢትዮጵያ ወደብ በምጽዋ ደረሱ። ጀልባቸውን በምጽዋ ላይ ትተው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሄደው እርሱም በሚገባ አከባክቦ እንዲያውም ከኛ አብልጦ በክብር ተቀብሎአቸው በገባር መሬት ላይ ተከላቸው። ከነዚህ ፈረንጆች አብዛኞቹ ጄኖቫውያን ሲሆኑ ሁለት ካታሎናውያን፤ አንድ ቂዎሳዊ (ጽርእ)፤ አንድ ባስካዊና አንድ ጀርመን ናቸው። እነዚህ ፈረንጆች ወደዚህ ከመምጣ

ታቸው በፊት በፖርቱጋል ስለነበሩ ፖርቱጋልኛንና ካስቲልኛን (ማለት ዛሬ እስፓንኛ የሚባለውን) ደህና አድርገው ይናገሩ ነበር። ይህ ፈረንጅ የሚባለው ቃል እኛ ብቻ ሳንሆን ማናቸውም ቀዳው ነጭ ሕዝብ ማለት ሶርያውያንና ከለዳውያን የየሩሳሌምም ሕዝብ የሚጠሩበት ነው። የካይሮን ሰዎች ግን ግብጾች ይሉዋቸዋል።

እኛ የያዝነው በርበሬና ጨርቅ በሙሉ ጠቅላይ ገዥው ለንጉሠ ነገሥቱ የሰጠው ነው እንጂ የኛ አይደለም እየተባለ በቤተ መንግሥቱ ይወራብን ስለነበር ይህንኑ በመስማትና ለኛም ለማሰማት ሁለት ፈረንጆች ጥቅምት 29 ቀን እሁድ ወደኛ መጡ። ስለዚህ ይህንን ዕቃ ካልሰጠን የንጉሠ ነገሥቱን በጎ ፈቃድ የማናገኝ መሆናችንን በማስገንዘብ የያዝነውን በርበሬና ልብስ በሙሉ እንድንሰጥ መከሩን፤ ይህን ካልፈጸምን በአገሩ ደንብ መሠረት አንድ የውጭ አገር ሰው ሲመጣ እንዳይሄድ መከልከል ደንብ ስለሆነ ዕቃውን መስጠቱ የተሻለ ነገር መሆኑን አስገነዘቡን፤ በነርሱ አስተያየት ነገሥታቱ ከከተሞችና አገሮች ይልቅ ትርኪምርኪ ነገሮችን በቅድሚያ ለማግኘት የሚወዱ ናቸው። በጉዳዩ አምባሳደሩና እኛ ሁላችንም ተመካከርንበት፤ ለራሳችን ወጭ ከያዝነው አምስት ጭነት በርበሬ ውስጥ አንዱን ብቻ በማስቀረት ለንጉሠ ነገሥቱ ለመስጠት ተስማማን። ከዚህም በላይ እርሱን የሚያስደስተውን ለኛም በጎ አስተያየት የሚያስከትልልን መስሎን ልብስ ያመጣንባቸውን በቆዳ የተለጎሙ አራት ሣጥኖች ልንሰጠው ወሰንን። በማግሥቱ ጥቅምት 30 ቀን ሰኞ በማለዳ ፈረንጆቹ ብዙ አጋሰሶችንና አሽከሮቻቸውንም አስከትለው ዕቃችንን ሊያስጭኑልን መጡ። አምባሳደሩ ከሌሎች ሰዎች ጋር ረፈድ ካለ በኋላ ሊሄድ በመወሰን እኔና የንብረት ሹሙ ገጸ በረከቱን አስጭነን እንድንቀድም አዞን በርበሬውንና ሣጥኖቹን አስጭነን ሄድን። በመንገድ ላይ እንዳለን አንድ መልእክተኛ በበቅሎ ተቀምጦ ሲመጣ አገኘን። በአገሩ ልምድ መሠረት የንገሥ ነገሥቱን መልእክት በበቅሎ ላይ ሆኖ መስማት ወይም ማሰማት የማይገባ ነገር በመሆኑ መልእክተኛውም እኛም ከበቅሎቻችን ወርደን ቆምን። ይህ ሰው ያመጣልን መልእክት በንጉሣዊው ከተማ እንድንመጣ ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዘን መሆኑን ነበር።

አምባሳደሩ ወደዚያ ለመምጣት ከኋላችን ስለነበር የመልእክ ተኛው ወደፊት መሄድ አስፈላጊ አለመሆኑን አስረድተነው ይልቁንም የያዝነውን ዕቃ በእንዴት ያለ አኳኋን ለግርማዊነታቸው ለማበርከት እንደምንችል ይረዳን ዘንድ ተመልሶ ከኛ ጋር እንዲሄድ ጠይቀነው ተስማማ። ይሁን እንጂ ሕዝቡ ሁልጊዜ መለመን ልምዱ ስለሆነ ታዲያስ ምን ትሰጡኛላችሁ አለን። ነገር ግን ምንም የማንሰጠው መሆናችንን በዘዴ አስታውቀነው በቃል ብቻ አስደሰትነው።

ይህ ሰው ንጉሠ ነገሥቱ አንዳንድ ጊዜ ይኖርበታል በሚለው አንድ ትልቅ ሳር ክዳን ሰቀላ ቤትና በዙርያው ብዙ ድንኳኖች ተተክለው በሚገኙበት ባንድ ጆኅል አጠገብ ወሰደን፤ እርሱም የሚኖረው በዚሁ ነበር። ከጆኅሉ መግቢያ ፊት ለፊት ብዙ ሰዎች ይገኙ ነበር ማለትን ሰማን። ለመድረስ ጥቂት ሲቀረን እንደተለመደው ከበቅሎቻችን ወርደን ለግርማዊነታቸው የምናበረክተው ዕቃ ይዘናል ስንል መልእክተኛ ላክን። ወዲያውኑ አንድ ትልቅ ሰው ወደኛ መጥቶ ለምንድር ነው አምባሳደሩ ያልመጣው ሲል በቁጣ ቃል ጠየቀን። አምባሳደሩ ያልመጣበት ለዕቃው ማስጫኛ አጋሰሶችና ረዳት ሰዎችም ስላልታዘዙልን መሆኑን እርሱም በመምጣት ላይ ያለ መሆኑን ገልጸን፤ አሁንም ሊመጣ መቻሉ በፈረንጆቹ እርዳታ ምክንያት መሆኑን በማስታወቅ መልሰንለት የያዝነውን በርበሬና ሣጥኖች በንዴት ያለ አኳኋን ለጃንሆይ ለማቅረብ ይረዳን ዘንድ ለመንነው። እርሱም መልሶ ለጊዜው ስለዚህ ጉዳይ ምንም ልታስቡ አይገባችሁም፤ ለማናቸውም ነገር አምባሳደሩ መምጣት አለበት፤ እርሱ ሲመጣ እንዲቀርብ ሲፈቀድለት ገጸ በረከቱን ይዞ ሊገባ ይችላል አለን። አምባሳደሩ ሲመጣ ድንኳናችን የሚተከልበትን ቦታ አሳዩን፤ አምባሳደሩም በዚያኑ ጊዜ ደረሰ።

ምዕራፍ ሰባ አራት፤ አምባሳደሩ ካገር እንዳይወጣ ያገሩ መኳንንት ንጉሠ ነገሥቱን ያማከሩት መሆናቸውን ሰማን፤ ድንኳኑን እንዲያዛውር ታዘዘ፤ ንጉሠ ነገሥቱ አንድ መስቀል እንድንሰጠው ጠየቀን፤ አምባሳደሩ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንዲቀርብ ስለመጠራቱ።

የዚያን ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ በጀጎሉ ውስጥ ወይም በዚያው በሚገኘው ሰቀላ ቤት ውስጥ ወይም በድንኳኖቹ ውስጥ ያልነበረ መሆኑን ተረዳን። የነበረበትስ ቦታ ከዚያ ቦታ ግማሽ ሌግዋ ያህል እልፍ ብሎ የሚታይ ባንድ ኮረብታ ላይ በተተከሉ ድንኳኖች ውስጥ ነበር። በዚሁ ቀን ምንም ሳንሠራ ከጀጎሉ በስተቀኝ በኩል ጥቂት እልፍ ብሎ በሚገኝ በተወሰነልን ቦታ ድንኳናችንን ተክለን ተቀመጥን። ያ እኛን ይመራን የነበረው መነኩሴ እነዚህ ሰዎች አገሪቱን ሰድበ ዋልና እንዲወጡ የተፈቀደላቸው እንደሆነ በበለጠ ስማችንን የሚያ ጠፉን ይሆናሉ እያለ የቤተ መንግሥቱን መኳንንት መጥፎ ስሜት የሚቀሰቅስብን መሆኑን በዚያ የሚገኙ ፈረንጆች ወደኛ መጥተው ነገሩን። ወደአገሪቱ የሚመጡ የውጭ አገር ሰዎች እንዳይመለሱ መከልከል ያገሩ ልምድ መሆኑንም ጨምረው ገለጹልን። እነዚህ ሰዎች ይህን ነገር ከነገሩን በኋላ በእውነተኛው ጥርጣሬ ገባን፤ ምክንያቱም ከዚህ በፊት ትሪስታው ደ ኩኛ ዮሐንስ ጎምሽ የተባለ አንድ የፖርቱጌዝ ቄስና እንዲሁም አንድ እስላም ወደዚህ ልኮ ነበር፤ ፖርቱጌዞቹን ካገር እንዳይወጡ በሞት በማስፈራራት የከለ ከሉዋቸው መሆናቸውን፤ እስላሙም እስከዛሬ ድረስ በማናዴሌይ ከተማ የሚገኝ መሆኑን እናውቅ ነበር። እግዚአብሔር ነፍሱን ይማርና የፖርቱጋል ንጉሥ ዶም ዮሐንስ ልኮት ከፖርቱጋል ከአርባ ዓመት በፊት የወጣው ፔሮ ድኩቪሊያንም በዚህ አገር ከመጣ ከሰላሳ ዓመት በላይ መሆኑን እንውቃለን። አሁን መርቆርዮስ በሚባል ስም የሚጠራው የቀድሞው ስሙ ኒኮላዎ ብራንካ ሌዎኔ የነበረ አንድ የቬኔዚያ ተወላጅ ሰላሳ ሶስት ዓመት ሙሉ በዚሁ ይገኛል። ቶማስ ግራዳኒ የተባለ ሌላ ሰውም በዚህ አገር ከመጣ አስራ አምስት ዓመት ሆኖታል።

እነዚህ ሰዎች የቁም እስረኞች ሆነው በቤተ መንግሥቱ ወዲያ ወዲህ ይዞራሉ። አንዳንዶቹም በዚሁ ሁኔታ እንዳሉ ሞተዋል። ለዚህም አድራጎት የሚያቀርቡት ምክንያት ሊሹን የመጡትን ሰዎች ሁሉ ስለምንፈልጋቸው መሄድ አይገባቸውም እኛም ልንለቃቸው አይገባም የሚል ነው። ፔሮ ድ ኩቪሊያን በመንገዳችን ላይ አልፈነው በመጣነው በተፈጥሮ በሩ አጠገብ በሚገኘው ቤቱ ስለነበር የሚገኝ ለጊዜው በቤተ መንግሥቱ አልነበረም።

በጥቅምት ወር መጨረሻ ዕለት ማክሰኞ ንጉሠ ነገሥቱ ከነበረበት ከላይኛው ድንኳን ሰቀላውና ሌሎቹም ድንኳኖች ወደሚገኙበት ወደ ጀጎሉ መጣ። ከንጉሣዊው ድንኳን እጅግ ርቆ የማይገኘውን የኛን ድንኳን ንጉሠ ነገሥቱ ሲያልፍ ስላየ ወዲያውኑ ወደአምባሳደሩ መልእክተኛ ልኮ ያለህበት ቦታ በሽታ ያለበት ነውና ድንኳንህን በቶሎ እንድታስነቅል ሲል አዘዘው። ይህ የነበርንበት ቦታ በዚያ እንደደ ረስን የተሰጠን ነበር። አምባሳደሩም ድንኳኑን የሚነቅልልኝና ዕቃዬንም ለማጓጓዝ የሚረዳኝ ሰው የለኝምና ግርማዊነትዎ ወደሚወስንልኝ ቦታ ለመሄድ እንድችል ሰው እንዲያዙልኝ እለምናለሁ ሲል መልእክተኛ ላከ። የዚያኑ ዕለት ማታ አንድ መልእክተኛ መጥቶ ከአምባሳደሩ ወይም ከሰዎቹ ካንዱ ዘንድ የወርቅ ወይም የብር መስቀል ይገኝ እንደሆነ ለማየት ስለሚፈልግ እንዲላክለት ንጉሠ ነገሥቱ ጠይቋል አለን። የተፈለገው መስቀል የሌለን መሆኑን አምባሳደሩ ገልጾ የነበረውን አንዱን መስቀሉን ለባሕር ነጋሹ የሰጠው መሆኑን በማስታወቅ ብላቴናውን መልሶ ላከው። መልእ ክተኛው እንደገና መጥቶ ግድ የለም ማናቸውም ዓይነት መስቀል ቢሆን ካላችሁ ላኩልኝ ብሎአል ስላለን በዚህ አገር በምንጓዝበት ጊዜ ሁሉ በአገሩ ካህናት ልምድ በእጁ ይዤው የነበረውን የክርስቶስ ስቅለት የተሳለበትን የኔን መስቀል ላክንለት። ወዲያውኑ ያንኑ ብላቴና መልሶ በመላክ ክርስቲያኖች በመሆናችሁ በጣም ደስ ብሎኛል ሲል ገለጸልን። አምባሳደሩ በዚሁ መልእክተኛ አማካይነት ለራሳችን ወጭ እንዲሆን የያዝሁት በርበሬና እንዲሁም ለልብስ መያዣ የሚሆኑ አራት ሣጥኖች ይዣለሁና ለግርማዊነትዎ መቼ ላቀርብልዎ እችላለሁ ሲል በመጠየቅ ላከበት። ንጉሠ ነገሥቱም

በርበሬውንም ሆነ ሣጥኖቹን የማይፈልግና ከዚሁም በፊት ያበርከትንለትን ልብስ ለቤተ ክርስቲያኖች ከበርበሬውም አብዛኛውን ለድሆች ያከፋፈለ መሆኑን ነገረን። የሕንድ ጠቅላይ ገዥ ይህን የፖርቱጋል ንጉሥ የላከልኝን ልብስ ለቤተ ክርቲያኖች ያከፋፈለብኝ መሆኑን ሰምቻለሁ ሲል መልእክተኛውን መልሶ ላከው። አምባሳደሩም መልሶ ይህን ነገር ለግርማዊነታቸው የነገራቸው ሰው ሃሰተኛ ነው፤ እነዚያ ልብሶች በሙሉ በመጡበት አኳኋን ተጠቅለው ይገኛሉ፤ ለቤተ ክርስቲያን ተሰጥተዋል ሲሉ የተናገሩት የማቴዎስ አሽከሮች መሆን አለባቸው አለ።

ይሁን እንጂ የፖርቱጋል ንጉሥ ለግርማዊነታቸው ስለላከው ስለነዚያ ልብሶች እኔ የማውቀው አንድ ነገር ስለነበር መልስ በመስጠት እርግጥ ነው እነዚያ ልብሶች በሣጥን ተጣጥፈው ተቀምጠው ነበር፤ ነገር ግን እንዳይበላሹና እግዚአብሔርንም እንዲያገለግሉ በማለት በአንድ በክብረ በዓል ዕለት በኮቺን (በሕንድ) የምትገኘው በቅድስት መስቀል ቤተ ክርስቲያን ጋርደናቸው ነበር፤ በዓሉ ካለፈ በኋላ ግን በሚገባ አጣጥፈን አኖርናቸው፤ ይህ የተደረገበት ምክንያት እግዚአብሔርን ለማገልገልና በዓሉንም ለማክበር እንዲሁም ጨርቁ ሳይናፈስ ብዙ የተቀመጠ እንደሆነ ብል የሚበላው መሆኑን በማወቅ ነው። ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን ተዳርጓል ሲሉ ያወሩት ይህን ምክንያት በማድረግ ቢሆንም እውነት ሊሆን አይችልም ስል ገለጽሁ። ይህ መልእከተኛ ከተመለሰ በኋላ አምባሳደሩንና እኛን በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ለማቅረብ ከምሽቱ በግምት ሶስት ሰዓት ያህል ሲሆን አንድ ሌላ መልእክተኛ ወደኛ መጣ። በደተጠራንበት ቦታ ለመሄድ ሁላችንም ወዲያውኑ የክት ልብሳችንን መልበስ ጀመርን።

ለብሰን ከተዘጋጀን በኋላ አንድ ሌላ መልእክተኛ ወደኛ መጥቶ ዛሬ ለመቅረብ አልተቻለም አለን። የቱርክ ዶሮ [1] ጅራቱን ሲያቆም ደስ ይለዋል፤ እንኑን ሲመለከት ግን ይከፋዋል፤ የኛም ሁኔታ ከዚሁ የሚመሳሰል ነበር።

ምዕራፍ ሰባ አምስት፤ ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሩን አስጠርቶ በሶስተኛ ሰው አማካይነት አነጋገረው።

ረቡዕ ሕዳር 1 ቀን በግምት ከምሽቱ አንድ ወይም ሁለት ሰዓት ሲሆን በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሊያቀርበን አንድ ብላቴና መጣ። እኛም ወዲያውኑ ተከትለነው ሄድን። በጀነሉ የመጀመርያ በር እንደደረስን አጋፋሪው አላስገባ ብሎን በብርድና ደረቅ ነፋስ ውስጥ በትንሹ አንድ ሰዓት ያህል ቆመን ደጅ ጠናን። ከነበርንበት ቀጥሎ የሚገኘውን የኋላ በር አልፎ ብዙ ሰዎች በእጃቸው መብራት ይዘው ቆመው አየን። አላስገባ ብለውን ደጅ እየጠናን ብዙ በቆምንበት ጊዜ የኛ ሰዎች ሁለት ጥይት ተኮሱ። ወዲያውኑ ከንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ መጥቶ ለምንድር ነው ከባሕር ማዶ ብዙ ጠበንጃ ያላመጣችሁት ሲል ጠየቀን። አምባሳደሩ ለዚህ ጥያቄ መልስ በመስጠት እኛ ወደዚህ አገር የመጣነው ለጦርነት ስላይደለ ጠበንጃ ይዘን አልመጣንም፤ የኛ ሰዎች ይዘዋቸው የመጡት ሁለት ወይም ሶስት ጠበንጃዎች የራሳቸው መደሰቻዎች ናቸው አለ። በደጅ ጥናታችን ላይ እንደነበርን አምስት መኳንንት ወደኛ መጡ፤ ከነዚህም ውስጥ አንደኛው ከዚህ በፊት ባልደረባ የተሰጠንና ወደኋላ የመለሰን ሕዱግ ራሱ ነበር። ይህን መልእክት ይዘውልን ሲመጡ በተለመደው አኳኋን እጅ ተነሣሣን። አምስት ወይም ስድስት እርምጃ ያህል ወደፊት ሄደን ተቀራረብን። እነዚህ አምስት መልእክተኞች ጎን ለጎን ተራ ገብተው ከነርሱም ግራና ቀኝ ሁለት ሰዎች በእጃቸው መብራት ይዘው እየመሩን ከፊታችን ይሄዱ ነበር። እነዚህ እኛን የመሩን ሰዎች እያንዳንዳቸው በተራ አስር ጊዜ «እነሆ ያዘዙት አቤቶ» [1] አሉ። እነዚህ እንዳበቁ በበለጠ ከፍ ባለ በማህበር ድምጽ ከውስጥ ያሉት ሰዎች «አስገቡአቸው» አሉ። ወደፊት እልፍ ብለን እነርሱም እኛም ጸጥ ብለን እንደቆምን የበፊቱን ቃል ደግመው ሲያሰሙ በውስጥም ያሉት በዚያው አኳኋን መለሱ። ከመጀመርያው በር እስከ ሁለተኛው ድረስ በትንሹ አስር ጊዜ ያህል አቆሙን። በውስጥ ያሉት ሰዎች ይግቡ እያሉ የንጉሠ ነገሥቱን ፈቃድ ባሰሙን ጊዜ መሪዎቻችንና እኛ እጃችን መሬት እስኪነካ ድርስ እጅ እንነሳ

ነበር። ሁለተኛውን በር ካለፍን በኋላ የሚመሩን ሰዎች «እነሆ እንዲቀርቡ ያዘዙት ፈረንጆች አቤቶ»[1] ሲሉ የበፊቱን ያህል ደጋግመው አሰሙ። ከውስጥ ያሉት በተለመደው አኳኋን መልስ እስኪሰጡ ጠበቁ። በዚህ አኳኋን በያለበት እየቆምን አንድ መደብ አጠገብ ደረስን። ከዚህ መደብ ፊት ለፊት በመጀመርያው በር ላይ ሆነን ያየናቸውን በግምት ሰማንያ የሚሆኑ መብራቶች አየን። መብራቶቹን የያዙት ሰዎች በተርታ መስመር ገብተው ቆመው ነበር። መስመራቸውን ሳይሰብሩ ወይም ወጣ ገባ ሆነው እንዳይቆሙ በማለት እስከ ደረታቸው የሚደርስ አገዳ በእጃቸው ይዘው ነበር። የተባለው መደብ የሚገኘው ከዚህ በፊት በጠቀስነው አዳራሽ ፊት ለፊት ነው። ቤቱ በትልልቅ የጥድ ምሰሶዎች ተደግፎአል። ከምሰሶው ላይ ባረፈው ሳንቃ ተዋቅረው ከግራና ቀኙ እስከ ድምድማቱ ድረስ ወጣ ገባ እየሆኑ የሚወርዱ ማዕዘኖች አሉ። አሠራሩ በጠቅላላው ደስ አያሰኝም፤ ጣርያው በሰንበሌጥ ተከድኖአል፤ ይህ የሰንበሌጥ ክዳን ያንድ ሰው ዕድሜ ልክ ሊኖር ይችላል ይባላል። በቤቱ መጨረሻ በሚገኘው በመግቢያው ላይ አራት መጋረጃዎች ተጋርደዋል፤ ከነዚህም መጋረጃዎች በመከከል የሚገኘው የወርቀ ዘቦ ሲሆን የተቀሩት ግን ከጥሩ ዓይነት ሐር የተሠሩ ናቸው። ከመጋረጃው በስተኋላ ጥሩ ዓይነት ምንጣፍ ተነጥፎአል። ሁለት ሰፋፊ ብዝቶችም በዚያው ነበሩ። ከዚህም ሌላ ወለሉ በሳጣራ ምንጣፍ ተነጥፎአል። ቤቱ ከዳር እስከ ዳር በመብራት ደምቋል።

ቁመን ስንጠብቅ ሳለን አንድ ሰው ከመጋረጃው ውስጥ ወጥቶ ለንግግር መግቢያ የሚሆን አንዳች ነገር እንኳ ሳይናገር ማቴዎስን ወደፖርቱጋል እንዲሄድ የላክሁት እኔ አይደለሁም፤ ይሁን እንጂ ምንም እንኳ እኔ ባልከውም የፖርቱጋል ንጉሥ በዚሁ ሰው በኩል ብዙ ስጦታ ልኮልኛል፤ ወዴት አደረሳችሁት? ለምንድርንስ ነው ንጉሡ በላከልኝ ሁኔታ ያላመጣችሁልኝ? ጠቅላይ ገዥው የላከውን ገጸ በረከቶች አከፋፍለን ጨርሰናቸዋል ብሎአል ንጉሠ ነገሥቱ አለን። አምባሳደሩም ንጉሠ ነገሥቱ እንዲሰማው ለምኖ ቅር ለተሰኘበት ነገር ሁሉ ምክንያቱን የሚገልጽ መሆኑን አስረድቶ ጠቅላይ ገዥው የላከውንና ከዚህም በላይ ለስንቃችን ከያዝነው ከፍለን

የሰጠን መሆናችንን አስገንዝቦ ንጉሠ ነገሥቱ ስለጠቀሰው ስጦታ የሆነውን ነገር ሁሉ አንድ በአንድ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ አተተ።

የፖርቱጋል ንጉሥ ለግርማዊነታቸው ገጸ በረከት መላኩ እርግጥ ነው። ነገር ግን ተልኮ የመጣው አምባሳደር ድዋርት ጋልቫው በካማራን ደሴት ላይ ስለመሞቱና እንዲሁም ከኛ ሰዎች ሶስቱን ማለት ወኪሉን አስተርጓሚውንና የንብረት ሹሙን በዳህላክ ላይ ሰዎች ስለገደሉዋቸው፤ እንዲሁም የባሕሩ ነፋስ ወደ መርከቦቹ ይነፍስ ስለነበርና መርከቦቹም በምጽዋ መድረስ ስላልቻሉ ወደሕንድ መመለስ ግድ ሆነባቸው። በዚያን ጊዜ ጠቅላይ ገዥው ወደፖር ቱጋል ተመልሶ ስለነበር ሁለቱ አምባሳደሮች ማለት ድዋርት ጋልቫውና ማቴዎስ በኢትዮጵያ ደርሰዋል ሲል የፖርቱጋል ንጉሥ በመገመት፤ ከቀይ ባሕር ላይ እስላሞችን ለማስወገድና ስለተባላውም አምባሳደር ወሬ ለማምጣት ብቻ መርከቦች ተላኩ። ስለዚህ መርከቦቹ ከዚህ በፊት ምጽዋ ለመድረስ ሞክረው አቅቶዋቸው ስለነበር በቀጥታ ወደጅዳ በመሄዳቸው የፖርቱጋል ንጉሥ የላከውን ስጦታ አላመጡም። ስጦታዎቹ ባንድነት ተከማችተው በሕንድ አገር ይገኛሉ። መርከቦቹ ማቴዎስን ይዘው የመጡት ምናልባት በእግዚአብሔር ቸርነት በኢትዮጵያ ጠረፍ ለመድረስ የቻሉ እንደሆነ እርሱን በዚያው ትቶ ለመሄድና በመጀመርያው አምባሳደር እጅ የተላኩትን ገጸ በረከቶች እዚያው ድርስ ለማምጣት ነበር። ለጊዜው በእስላሞች ሥልጣን ሥር በሚገኘው በኢትዮጵያ ወደብ በምጽዋ እንደደረስን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስለነበር እነዚያን ያበረከትኋቸውን ገጸ በረከቶች ይዤ ከማቴዎስ ጋር ወደዚህ እንድመጣ እኔን ሩድሪጉ ድ ሊማን ወደዚህ የላከኝ ጠቅላይ ገዥው ነው። እኔ ወደዚህ የመጣሁበት ዓይነተኛ ምክንያት ለጉብኝትና ወደፊት ከፖርቱጋል ንጉሥ አምባሳደር ተልኮ ሲመጣ እንዳይቸገር መንገዱን ለማጥናት ነው። ማቴዎስ በደብረ ቢዘን ገዳም ሞተ።

አምባሳደሩ ይህን መልስ ከሰጠ በኋላ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ እንደገና መልእክተኛ መጥቶ ሶስቱ ሰዎች በዳህላክ ላይ ሲገደሉ ማቴዎስ በንዴት ያለ አኳኋን ሊያመልጥ እንደቻለ አስጠየቀን።

ማቴዎስ ሊያመልጥ የቻለው ወደጠረፈ ሳይሄድ በመርከቡ ውስጥ ዐርፎ በመቀመጡ ምክንያት መሆኑ ተገለጸለት። ማናቸውንም ነገር ንጉሠ ነገሥቱ እንዲሰማው አምባሳደሩ በጥብቅ ለምኖ ጠቅላይ ገዥው ከደብዳቤው ሌላ በቃል እንዲናገር ያዘዘውን መልእክት አስፈላጊ ከሆነ በጽሑፍ የሚያቀርብ መሆኑን አስታወቀ፤ ስለዚህ በሁለቱ አማካይነት የፖርቱጋል ንጉሥ አምባሳደር መላኩ እርግጥ መሆኑንና ጠቅላይ ገዥውም ለጉብኝት መምጣቱን ጭምር ሊረዳ የሚችል መሆኑን ገለጸ።

በዚህ አኳኋን አንዳች የተጨበጠ ነገር ሳይከተል መልእክተኛ በመለዋወጥ ብቻ ጊዜውን አሳልፈን በማግሥቱ አሰናበቱን። እንጀራና ጠጅ ሥጋም ተልኮልን ከኛ ዘንድ ሆነው የሚያስፈልገንን ሁሉ እያቀረቡ የሚያገለግሉን ሁለት አሽከሮች ታዘዙልን። ምንም እንኳ ይህን የመሰለ ትዕዛዝ ቢሰጥም ትዕዛዙ ስለተዘነጋ ጥቂት ቀኖች ምግባችን ተቋርጦብን ነበር።

ምዕራፍ ሰባ ስድስት፤ አምባሳደሩ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲቀርብ ተጠርቶ ደብዳቤውን ይዞ ስለመቅረቡ፤ በኛ ሥርዐት ለመቀደስ ይፈቀድልን ዘንድ ስለመለመናችን።

ቅዳሜ ማታ ሕዳር 3 ቀን ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶን ቀርበን ደርሰን ጥቂት እንደቆምን መልእክተኛ መጥቶ ጠበንጃ እንድንተኩስ አዘዘን። እንዲሁም አንዳች ተንኮል ነገር እንዳንሠራ በማለት ጠበንጃችንን እንዳናጎርስ ተከለከልን። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንድንገባ ተፈቅዶልን ልክ እንደበፊቱ በያለበት እየቆምን ከዚህ በፊት በነበርንበት በበሮቹና በመጋረጃቹ መካከል ደረስን። ከመጋረጃው በስተኋላ የነበረው መደብ ከዳር እስከ ዳር ተሸፍኖ ከፊት

ለፊትም በወርቀ ዘቦ አጊጦአል። ደማቅ ልብስ የለበሱ ሰዎች ጉራዴአቸውን መዘው እርስ በርሳቸው ለመጨፋጨፍ የተዘጋጁ ይመስል በአዳራሹ ግራና ቀኝ ተሠልፈው ነበር። ከዚህ በፊት በመጣን ጊዜ እንዳየነው ሁሉ ዛሬም በያንዳንዱ በኩል ሁለት መቶ የጥዋፍ መብራቶች በርተው ይታያሉ። እኛ በዚያ እንደደረስን ዓቃቤ ሰዓቱና አብዲናጎ የተባለው የብላቴናዎች ሹም መልእክት ማመላለስ ጀመሩ። ይህ በመጨረሻ የተጠቀሰው መልእክቱን ይዞ ሲመጣ ጉራዴ መዞ በእጁ ይዞ ነበር። የመጀመርያው ጥያቄ ቀጥሎ የተመለከተው ነው።

ጥያቄ፤ ስንት ናችሁ፤ ስንት ጠበንጃስ ይዛችኋል፤ ለእስላሞች ጠበንጃና ነፍጥ[1] መሥራት ያስተማራቸው ማነው፤ ለምሳሌ እስላሞች በፖርቱጌዞች ላይ ቢተኩሱ ፖርቱጌዞቹም መልሰው ቢትኩሱ ከሁለቱ ወገኖች ማንኛው ክፍል ኖሮአል በጣም የሚፈራ፤ እስላሞች ናቸው ወይስ ፖርቱጌዞቹ?

መልስ፤ (እነዚህን ጥያቄዎች አንድ በአንድ መልስ ሰጠን፤ ስለ ፍርሐቱ ጉዳይ ቀጥሎ የተመለከተውን መለስን።) እኛ ፖርቱጌዞች በየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት የጸናን ስለሆንን እስላምን አንፈራም፤ እስላምን የምንፈራ ብንሆን ኖሮ በእውነተኛው ያላንዳች ሌላ ምክንያት እናንተን ለማግኘት ብቻ ያን ሁሉ ረጅም መንገድ አቋርጠን ለመምጣት እንደፍር ኖሮአል? ስለእስላሞች መሣርያ መሥራት መቻል ስለጠየቃችሁን ደግሞ እስላሞችም ሰዎች ስለመሆናቸው እንደማናቸውም ሕዝብ እውቀትና መሣርያ አላቸው።

ጥያቄ፤ ቱርኮችስ ጥሩ ነፍጥ አላቸውን? መልስ፤ የቱርኮች ነፍጥ ጥሩና ከኛም መሣርያ ጋር የሚመሳሰል ነው፤ ይሁን እንጂ እኛ የምንዋጋው ስለየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት እነርሱ ግን እርሱዋን ለማጥፋት ስለሆነ በፍጹም አንፈራቸውም። ጥያቄ፤ ለቱርኮች መሣርያ መሥራትን ያስተማራቸው ማነው? መልስ፤ ቱርኮችም ሰዎች ናቸው፤ አንድ የሚጎድላቸው ነገር የክርስትና ሃይማኖት ብቻ ነው። መሣርያና ሰብአዊ ዕውቀት በማናቸውም ረገድ በተሙዋላ አኳኋን አላቸው።

ከዚህ ጥያቄና መልስ በኋላ የጎራዴና የጦር ጨዋታ እንድናሳይ ተጠየቅን። አምባሳደሩም ከሰዎቹ ሁለቱን ለዚሁ ጨዋታ አዘዘ። እነዚህ ሰዎች በመጠነኛ አኳኋን ጨዋታውን አሳይተው ነበር፤ ነገር ግን ይህ ጨዋታ የፖርቱጌዞች የሆኑ ነገሮች ሁሉ ሊከናወኑ በሚገባቸው አኳኋን ባለመፈጸሙ አምባሳደሩ ቅር ተሰኝቶ ነበር። ወዲያውኑ ለሁለተኛ ጊዜ መጥተው እንዲጫወቱ ንጉሠ ነገሥቱ ስለጠየቀ ሁለቱም እንዲቀርቡ አምባሳደሩ ጊዮርጊስ ዴ አብሬውን አዘዘው። እነዚህ ሰዎች በጦር መሣርያ አያያዝ የሠለጠኑና የቀለጠፉ ስለሆኑ እንደሚገመተው ሁሉ ጨዋታውን በሚያስገርም አኳኋን አሳዩ።

ከጨዋታው በኋላ አምባሳደሩ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮ፤ የፖርቱጋል ንጉሥ ታዛዥ ስለሆንሁ እርሱ ጌታዬ ካላዘዘኝ በስተቀር ሃምሳ ሺ ክሩዛዶ እንኳ ቢሰጡኝ ይህን የመሰለ ጨዋታ በዓለም ላይ ባለ በማንም ንጉሥ ፊት አላደርገውም። ግርማዊነትዎ የፖርቱጋል ንጉሥ እንደራሴ የላከውን ለማወቅ እንዲችል መልእክቱን እንዲሰማኝ እለምናለሁ፤ እዚህ ሆኜ በከንቱ ስንቅ ሳልጨርስ መርከቦቹ ሲመጡ በጊዜ ተሳፍሬ ለመሄድ እንድችል እንዲያሰናብቱኝ እለምናለሁ። በዚያን ጊዜ እንዲህ የሚል ቃል መጣ። የመጣችሁት ከቅርብ ጊዜ በፊት ስለሆነ አገሩን ገና ሲሶውን እንኳ አላያችሁትምና ጥቂት ቆዩ፤ ጠቅላይ ገዥው ወደምጽዋ ሲመጣ መልእክተኛ እልክበትና የዚያን ጊዜ ትሄዳላችሁ፤ ሩሚዎች (እስላሞች) ከናንተ በብዛት ስለሚበልጡ እናንተ በምጽዋ፤ በሱዋኪንና በዘይላ ላይ ምሽግ ብትሠሩ እኔ ደግሞ የሚያስፈልገውን ስንቅ እችላለሁ። ከዚህም በላይ በቀይ ባሕር ላይ ምሽጎች ቢሠሩ ያለ ሥጋት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ይቻላል። አምባሳደሩም ንጉሠ ነገሥቱ ያቀረበው ሃሳብ የፖርቱጋል ንጉሥ ምኞት መሆኑን ገልጾ መልእክቱን እንዲሰማው እንደገና ለመነ። እንዲሁም ጠቅላይ ገዥው የላከለትን ደብዳቤ እንዲቀበለው ወይም ለመቀበል ካልፈለገ ጉዳዮን በጽሑፍ ለማስታወቅ እንዲፈቀድለት ጠየቀ። ከዚህ ልመና በኋላ ጉዳዩ በራሱ ቋንቋና ፊደል ተጽፎ እንዲቀርብለት ንጉሠ ነገሥቱ ስላዘዘ አምባሳደሩ ማናቸውንም ነገር በጽሑፍ አቅርቦ መልእክቱን በሙሉ ሰምቶ እንዲያሰናብተው ለመነ።

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ፖርቱጌዞቹ ማኅኮርዲያ እንዲመቱና እንዲጨፍሩ አዞ እንዲሁ አደረጉ። ከጭፈራውም በኋላ ክርስቲያኖች በማሆናችን በሮም ቤተ ክርስቲያን መሠረት እንቀድስ ዘንድ እንዲፈቀድልን ለመንን። ወዲያውኑ አንድ መልክተኛ ተልኮ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ ክርስቲያን መሆናችሁን ያውቃሉ፤ እንዲያውም እነዚያ መጥፎዎችና እርኩሶች እስላሞች እንኳ በፊሊጣቸው ጸሎት ሲያደርጉ እናንተ ለምንድን ነው በልምዳችሁ የማትጸልዩ ብለዋል አለን። ስለዚህ የሚያስፈልገንን ማናቸውንም ነገር ሁሉ የሚሰጠን መሆኑን ገልጾልን ወደማረፊያችን እንድንሄድ አዘዘን። በማረፊያችን እንደደረስን አንድ ሰው ሶስት መቶ እንጀራና ሃያ አራት ገንቦ ጠጅ አስይዞ መጣ። ለኛ የተላከልን ጠጅ ሰላሳ ገንቦ ነበር፤ ነገር ግን የተሸከሙት ሰዎች ስድስቱን የቀነሱት መሆናቸውን ይኸው ሰው ነገረን።

ምዕራፍ ሰባ ሰባት፤ በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ለአምባሳደሩ የቀረቡት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች፤ አምባሳደሩ ለአንድ ብላቴና ልብስ ሸለመ፤ የቅዱስ ቁርባን መስጫ ዕቃችንን አሳየን።

በማግሥቱ እሁድ ከንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ጥያቄዎች ዐረፍንበት ቦታ ድረስ ተላከልን፤ እነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ የፖርቱጋል ንጉሥ ስለላከው የጦር መሣርያና እነዚም መሣርያዎች ወደሕንድ ተልከዋልን የሚሉ ነበሩ። አምባሳደሩም መልሶ የፖርቱጋል ንጉሥ የላኩዋቸውን የጦር መሣርያዎችና ማናቸውንም ሌሎች ነገሮች ሁሉ ጠቅላይ ገዥው በሚቀጥለው ዓመት ይዞ ይመጣል ወይም እንዲላክ ያደርጋል፤ ይህንንም በማሳሳብ ደብዳቤ እጽፍለታለሁ ሲል መልስ ሰጠ። የዚያኑ ዕለት ማቁረቢያ ይዘን እንደሆነ እንድናሳየው በመጠየቅ ሰው ልኮብን ስለነበር፤ የክርስቶስ ስቅለት የተሳለባቸውን በደንብ የተሠሩ እርፌ መስቀሎች ይገፍ እኔ ቀረብሁ። እርፌ መስቀሎቹን በቶሎ አይቶ እንዲመለሱ ስላዘዘ እኔም በቶሎ ተመለስሁ። ጠቅላይ ገዥው የላከለትን

የብረት ልብስ እንዴት እንደሚሠራበት እንድናሳየው ጠይቆ የኛ ሰዎች በዚያ ሄደው አሳዩ። እንዲሁም በኛ ሰዎች እጅ የሚገኘውን ጎራዴና የደረት ጋሻ እንድንልክለት ጠይቆ አምባሳደሩም የተጠየቀውን ሁሉ ከመላኩ በላይ እነዚህን የመሳሰሉና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑትን መሣርያዎች ሁሉ የፖርቱጋል ንጉሥ የሚልክለት መሆኑን ጨምሮ ገለጸ። የዚያኑ ዕለት ከቀተር በኋላ የበፊቱን የሚያህል እንጀራና ጠጅ ተልኮልን፤ በጣም ከመሸ በኋላ አንድ ብላቴና አምባሳደሩን ለመጥራት ወደኛ መጣ። አምባሳደሩም ይህን ብላቴና በፖርቱጊዝ አለባበስ ማለት አንገትጌው በወርቅ የተጠለፈ ሸሚዝ ፐሎት ድ ኡስቴዳ[1] የወርቅ ነጥቦች ያለበት ቆብ፤ የሐር ሱሪ ስርቪሊያሽ[2]፤ ቡርዝጊሽ[3] ጫማ ሸልሞት እርሱንና አብረውት የመጡትን አስደትቶ ላካቸው። በማግሥቱ ጠዋት ብላቴናው ያን ጥልፍ ልብስ ብቻ ይዞ መጥቶ ይህን ልብስ ከናንተ በመቀበሌ ንጉሠ ነገሥቱ ተቆጡኝ አለን፤ ይህን ካለን በኋላ ከብረት ልብስ ውስጥ የሚውል ከፖርቱጊዞች ጨርቅ የተሠራ አንድ ኮት እንዲላክላቸው ንጉሠ ነገሥቱ ጠይቀዋል አለን። አምባሳደሩም የተጠየቀውን ሰጠ። ስለተጠለፈው ልብስ ግን ፖርቱጊዞች የሰጡትን መንሣት ልምዳቸው አለመሆኑን አምባሳደሩ ነግሮት ብላቴናውም ያን ልብስ ይዞ ሄደ፤ ዳግመኛም አልተመለሰም።

ምዕራፍ ሰባ ስምንት፤ የቅዱስ ቁርባን ዕቃና የቅዳሴ ልብሳችንን እንድናሳይ ንጉሠ ነገሥቱ እኔን ቄሱን ፍራንሲሽኩ አልቫርሽን አስጠራኝ፤ አንዳንድ ጥያቄም አቀረበልኝ።

ነጉሠ ነገሥቱ የቅዱሰ ቁርባን መስጫውን ዕቃ ለማየት ስለፈለገ ሰኞ ጥዋት ይዤ እንድቀርብ እኔን ፍራንሲሽኩ አልቫርሽን አስጠራኝ። እኔም በደንብ የተሠሩ አስራ አንድ ሀብስቶች በሐር በተሸፈነ ባንድ ጥሩ ሸክላ ውስጥ አስቀምጬ ወሰድሁ። ቂጣ መስለው ለተሠሩት ለራሳቸው ሀብስቶች ያላቸውን ክብር ስለማውቅ የክር

ስቶስ ስቅለት ስዕል ያለበትን ይህን የኛውን በሣጥን አልወሰድሁትም። እንደነገሩኝ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን በማየቱ እጅግ ደስ ብሎት ስለነበር በጥንቃቄ ለመመልከት ይችል ዘንድ ስቅለተ ክርስቶስ የተሠራበትን የሀብስቱን መጋገርያ እንድናቀርብለት ጠየቀ። እንዲሁም ቅዳሴ ስንገባ የምንገለገልባቸው ቅዱሳን ዕቃዎች ሁሉ እንዲቀርቡለት ጠየቀ። እኔም ማናቸውንም ዕቃ አቅርቤለት አንድ በአንድ ከተመለከተ በኋላ በንፁህ ጨርቅ ተሸፍኖ ተቀምጦ የነበረውን ጽላት በከፊል ተርትሬ እንዳሳየው ጠይቆ እንዲሁ አድርጌ መልሼ ሸፈንሁት። (ያሳየሁትም ሙሉ አልባሱን ጽዋውን መሸፈኛውን ጽላቱንና ብርሌዎቹን ነበር።)

ካሰየሁት ዕቃዎች አንዱ የመሠውያው ጽላት ከላይ አራት ማዕዘን ሆኖ በደንብ ለስልሶ የተሠራ በታች በኩል ግን እንደ ድንጋዩ ዓይነትና የተፈጥሮ ሁኔታ ተስተካክሎ በአራት ማዕዘን መልክ አልተሠራም ነበር። ድንጋዩን አይተው ከመለሱልኝ በኋላ ይህን የመሰለ መልካም ሥራ የሚያከናውኑ ሠራተኞች በፖርቱጋል ስላሉ ለምንድን ነው ጽላቱን አራት ማዕዘን አድርገው ያልሠሩት ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም መልሼ ይህ ድንጋይ ከላይ በኩል ለስላሳ አራት ማዕዘን ሆኖ በደንብ የተሠራ ሲሆን በግርጌ በኩል ደግሞ እንደዚያ ሆኖ መሠራቱ በደንብ መሬት ይዞ እንዲቀመጥ በማለት ነው ስል ነግሬአቸው ነበር፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሃብቶች የሆኑ ሁሉ ጉድለት የሌለባቸው መሆን ይገባቸዋል ሲሉ መለሱልኝ።

ከመሸ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ከነበረበት ቦታ አምስት ክንድ ያህል እልፍ ብሎ በሚገኘው ሥጋጃ ከዳር እስከዳር በተነጠፈበት ባንድ ድንኳን ውስጥ አስገብተው በመካከል እንድቀመጥ አዘዙን። ቅዳሴ የምገባ ይመስል የአገልግሎት ልብሴን እንድለብስ ንጉሠ ነገሥቱ አዞኝ በርሱው ፊት ለበስሁ። ከለበስሁ በኋላ ይህን ልብስ የሰጣችሁ ማን ነው፤ ሐዋርያት ናቸው ወይስ ሌሎች ቅዱሳት? ሲሉ ጠየቁኝ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ከየሱስ ሕማማት የወረሰችው ነው ስል መለስሁ። ልብሶቹ አንድ በአንድ ምን ምሳሌ እንዳላቸው ጠይቀውኝ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን መልስ ሰጠኋቸው። ከውስጥ የሚውለው

ቀሚስ ቄሶች ሁሉ የሚለብሱት ልብስ ነው። ከሱ በላይ የሚውለው የየሱስ ክርስቶስን ፊት የሸፈኑበት ጨርቅ ምሳሌ ነው። ከዚያ በላይ የሚለበሰው ነጭ ጨርቅ እመቤታችን ለልጅዋ የሰፋችለትን የጲላጦስ መኳንንት እጣ የተጣጣሉበትን ልብስ የሚያስታውስ ነው። መቀነቱ ደግሞ የንጽሕና ኑሮ ምሳሌ ነው፤ ገመዱ የየሱስ ክርስቶስን እጅ ያሰሩበትን ትንሽ ገመድ የሚያስታውስ ነው አልሁ። የዚህን ጊዜ በአስተርጓሚ አማካይነት ንጉሠ ነገሥቱ ራሱ ተናግሮ የክርስቶስን ሕማማት በዚህ አኳኋን ታስታውሳላችሁና እውነተኛ ክርስቲያኖች ናችሁ አለኝ። እኔም ሃተታዬን በመቀጠል ማተቡ የክርስቶስን አንገት አሥረው ወዲያና ወዲህ ያንገላቱበትን ገመድ የሚያስታውስ መሆኑን እንዲሁም ካባው አይሁዶች በክርስቶስ ላይ በማላገጥ ላለበሱት ካባ ምሳሌ መሆኑን አስረዳሁ። ንጉሠ ነገሥቱ በአስተርጓሚዎቹ አማካይነት ሃሳቡን በመግለጽ ሕማማቱን በንደዚህ አኳኋን ስለምታስታውሱ እውነተኛ ክርስቲያኖች ናችሁ ሲል ለሁለተኛ ጊዜ አረጋገጠልኝ። የአገልግሎት ልብሴን እንዳወልቅና አንድ በአንድ ምሳሌውን እንዳስረዳ አዘዘኝ። ካባውን አውልቄ ቀሚሱ ብቻ ሲቀረኝ እንደገና እንድለብስና ምሳሌውን እንድገልጽ ታዘዝሁ። እንደታዘዝሁት ከቀሚሱ በላይ ከሚውለው ልብስ ጀምሬ በካባው በመጨረስ ምሳሌውን አንድ በአንድ ገለጽሁ። በዚህ ጊዜ በከፍተኛ ድምጽ በመናገር ሕማማቱን በሙሉ ታስታውሳላችሁና ክርስቲያኖች ናችሁ ሲል ካረጋገጠልኝ በኋላ እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበልኝ። ቤተ ክርስቲያን ይህን የወረሰችው ከየሱስ ክርስቶስ ሕማማት ነው ብልሃል፤ ነገር ግን በክርስቲያን ዓለም ውስጥ ሁለት ቤተ ክርስርያኖች ማለት በግሪክ አገር በቁስጥንጥንያና በሮም ስላሉ የትኛውን ማለትህ ነው ሲል ጠየቀኝ። እኔም መልስ በመስጠት ምንም እንኳ ቁስጥንጥንያ በመጀመርያ የክርስትና መንበር የነበረች መሆንዋ የማይካድ ቢሆንም አሁን ግን ይህ መሆኑ ቀርቶአል። ምክንያቱም አንተ ኬፋ (ትርጓሜው ጴጥሮስ) ነህና ቤተ ክርስቲያን ባንተ ላይ ትታነጻለች ሲል ክርስቶስ ለጴጥሮስ ነግሮታልና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው ጴጥሮስ በነበረባት ቦታ ነው፤ ቅዱስ ጴጥሮስ አንጾክያ በነበረበት ጊዜ የቀድስት ቤተ ክርስቲያን መንበር በዚያ ነበር፤ ነገር ግን ወደሮም ከመጣ በኋላ መንበሩም ወደሮም ተዛወረ፤ ለሁልጊዜም በዚያው ይሆናል።

ይህች ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ በመመራት አስፈላጊው ቅዳሴ እንዲቀርብ አዛለች። ከዚህም በላይ ሐዋርያት ያዘጋጁትን ወይም ያስተማሩትን ጸሎተ ሃይማኖትን ሲያደርስ ሐዋርያ ስምኦን «በቅድስት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ» ሲል የጸለየ መሆኑን ጨምሬ ገለጽሁ። እንዲሁም የአርዮስን ክህደት ለመቃወም ሲባል በኒቂያ ላይ በተደረገው በሶስት መቶ አሥራ ስምንት አበው ጉባኤ በተዘጋጀው ትልቁ እምነት ላይ አንዲት ቅድስት ካቶሊካዊትና የሐዋያት ቤተ ክርስቲያን የሚል ቃል አለ። በጸሎተ ሃይማኖት ላይ «በሐዋርያት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ» ብቻ እንጂ «በቤተ ክርስቲያን አምናለሁ» የሚል ቃል የለም። ይህች ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጴጥሮስ የሚገኝባትና በላይዋም እግዚአብሔር ራሱ እንደተናገረው ቤተ ክርስቲያኑን ያነጻባት የሮም ቤተ ክርስቲያን ናት። ቅዱስ ጳውሎስም የአሕዛብ መምሕር እንዲሆን ተመረጥ።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስና ለሌሎቹም ሐዋርያት ለማሠርና ለመፍታት የሰጣቸው ሥልጣን ሁሉ ስለሚገኝባት ይህች ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊትና የሐዋርያት ተብላለች። የኔን ሃተታ ከሰሙ በኋላ መልስ በመስጠት ስለሮም ቤተ ክርስቲያን የሰጠኸው መግለጫ መሠረት ያለው ነው፤ ነገር ግን የቁስጥንጥንያ ቤተ ክርስትያን የቅዱስ ማርቆስ የግሪክ ቤተ ክርስቲያንም የእስክንድርው ፓትርያርክ የቅዱስ ዮሐንስ ናት አሉኝ። እኔም መልስ በመስጠት ይህ ያቀረባችሁት አስተያየት ሃሳቤን የሚደግፍ ነው፤ ምክንያቱም ቅዱስ ጴጥሮስ የቅዱስ ማርቆስ የክርስትና አባትና መምህር ስለነበር ወደዚያ የላከው እርሱ ነው፤ ማርቆስም ሆነ ዮሐንስ በላካቸው ስም ካልሆነ በስተቀር በራሳቸው ሥልጣን ቤት ሊሠሩ አይችሉም። ስለዚህ እነርሱ የሠሩዋቸው ቤቶች ሁሉ ሙሉ ሥልጣን የተሰጣት የዚያች የላከቻቸውና ከበላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን አባሎች ናቸው። ከዚህም በላይ ከጥቂት ዓመታት በፊት ቅዱስ የሮኒሞስና ሌሎችም ብዙዎች ቅዱሳን በብትህና መኖርን ከመምረጣቸው በላይ የብትህናን ኑሮ አስተማሩ፤ ይህን ትምህርት በሮም ከምትገኘው ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ሳይቀበሉ አላስተማሩም፤ ወይም ፈቃድ ሳይቀበሉ

ባላስተማሩም ነበር። ከጌታችን የሱስ ክርስቶስ ካልሆነ በስተቀር ታላቅዋን ቤተ ክርስቲያን በመጉዳት እንዴት አድርጎ ሰው ሌላ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራትና ለማነጽ ይችላል?

ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ከሰማ በኋላ በጣም የተደሰተ መሆኑን አስተርጓሚዎቹ ገለጹልኝ። ወዲያውኑ ጥያቄአቸውን በማስከተል የፖርቱጋል ቄሶች ያገባሉን ሲሉ ጠየቁኝ፤ የማያገቡ መሆቸውን ገለጽሁ። ወዲያው በማስከተል በኒቂያ ላይ የተደረገውን የጳጳስ ሌዎንን ጉባኤ ትቀበላላችሁን ብለው ጠየቁኝ። ሃይማኖተ አበው የተዘጋጀው በዚያ መሆኑን ከዚህ በፊት መግለጼን በማስገንዘብ ጉባኤውን የምንቀበል መሆናችንን አስረዳሁ። በዚያ ጉባኤ ላይ የተገኙት አበዎች ስንት መሆናቸውን ጠየቁኝ፤ ሶትት መቶ አስራ ስምንት ናቸው ስል ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት ሁሉ አሁንም መለስሁ። በጉባኤው ላይ ቄሶች እንዲያገቡ ተወስኖአል፤ የጉባኤው ቃል በመሐላ የጸና ሲሆን በምን ምክንያት ነው ቄሶች እንዳያገቡ የተደረገበት ሲሉ ጠየቁኝ። በዚህ ጉባኤ ላይ ሃይማኖተ አበው መዘጋጀቱን እመቤታችንም የአምላክ እናት እንድትባል መወሰኑን እንጂ ሌላ ነገር አላውቅም አልኳቸው። በዚያ ጉባኤ ላይ ተወስነው በመሐላ የጸኑትን ብዙ አንቀጾች ጳጳስ ሌዎን አፍርሶዋቸዋልና እነዚህ ያፈረሳቸው አንቀጾች የትኞቹ መሆናቸውን ጠየቁን። የቶቹ መሆናቸውን ለይቼ ልነግራቸው የማልችል መሆኔን ገለጽሁላቸው፤ ይሁን እንጂ አስተያየቴን በመስጠት አንዳንድ የጣሳቸው ቃላት ቢኖሩም የዚያን ጊዜ ክህደት የበዛበት ጊዜ ስለነበር ይህንኑ ጉዳይ ብቻ የሚመለከቱትን ሊሆን ይችላል፤ ቅዱስ ተብሎ በመንበር ላይ መቀመጡ ይህን እንዲያደርግ አይደለምን አልኳቸው። ለሁለተኛ ጊዜ ወደቄሶች ጋብቻ ጉዳይ ተመልሰን ሐዋርያት አግብተዋል ሲሉ ገለጹልኝ። ሐዋርያት የሱስ ክርስቶስን ለመከተል ከተነሡ በኋላ ሚስቶች የነበራቸው መሆናቸውን ወይም ማግባታቸውን ከመጽሐፍ አላነበብሁም ወይም ሲወራ አልሰማሁም፤ ምንም እንኳ ቅዱስ ጴጥሮስ ልጅ የነበረችው መሆኑ ቢታወቅም ይህች ልጅ የየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ከመሆኑ በፊት ከነበረችው ሚስቱ የተወ ለደች ናት ስል ገለጽሁላቸው። ሃተታዬንም በመቀጠል እመቤታችንና

የሱስ ክርስቶስ በተገኙበት በቃና ዘገሊላ ላይ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌ ላዊም ተገኝቶ ነበር፤ ነገር ግን በድንግልናው የሱስ ክርስቶስን ተከትሎ መሄዱን አንብቤአለሁ ሲወራም ሰምቻለሁ፤ ከየሱስ ሞት በኋላ ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት የየሱስን ሃይማኖት እስከ ጊዜ ሞታቸው ድረስ ያስተማሩት ያላገቡ ከመሆናቸው በላይ የንጽህና ኑሮን አስተምረዋል። ስለዚህ እውነት የመሠረታት ሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ይህን በመከተል ቄሶች የሕሊና ዕረፍት እንዲኖቸውና ጊዜአቸውንም ስለሚስቶች፤ ስለልጆች፤ ስለከብቶች ስለእርሻና ሃብት በማሰብ እንዳያሳልፉት በማለት እንዳያገቡ ከልክላለች ስል በሙሉ አስረድቻቸው ነበር፤ ነገር ግን የነርሱ መጽሐፍት ጋብቻን የሚፈ ቅዱና ቅዱስ ጳውሎስም ይህን የሚደግፍ መሆኑን መልስ ሰጡኝ።

የአገልግሎት ልብሴን ለብሼ እንዳለሁ ብዙ ልዩ ልዩ ጥያቄ አቅርበውልኝ ከነዚሁም አንዱ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ መላእክት «ምስጋና ይሁን ለእግዚአብሔር በአርያም» ሲሉ የዘመሩት መዝሙር በናንተ ዘንድ የታወቀ ነውን ሲሉ ጠየቁኝ፤ የታወቀ መሆኑን መለስ ሁላቸውና በዜማ እንዳሰማቸው ጠይቀውኝ ሁለቱን ቄጥሮች ዘመር ሁላቸው። ከዚያም በኋላ እንደገና ጥያቄ አቅርበውልኝ ጸሎተ ሃይማ ኖትን አውቅ እንደሆነ ጠይቀውኝ ከዚህ በፊት የጠቀስሁ መሆኔን አሳስብኳቸው። ሌላ አንድ ጸሎት በዜማና በንባብ እንዳሰማቸው ጠይቀውኝ ሌሎች ሁለት ቄጥሮች አዚሜ «ምስጋና» እና «አአምን» በሚሉ ቃሎች የሚጀምሩትን ሁለት ጸሎቶች አነበብሁላቸው። አንድ አስተርጓሚና በመንገዳችን ላይ ሲመራን የነበረ መነኩሴ በዚያ ነበሩ፤ ይህ መነኩሴ ኢጣሊያን አገር ሄዶ ስለነበር ላቲን በመጠኑ ስለሚያውቅ ንጉሠ ነገሥቱ ቋንቋውን ታስተውለዋለህን ሲል ጠይቆት እርሱም «አዎ ጌታዬ ምንም እንኳ ይህ መዝሙር የተዘመረው በልዩ ቋንቋ ቢሆንም ከኛው ቅዳሴ ጋር አንድ ነው» ሲል መልስ ሰጠ። ለጠየቀኝ ጥያቄ ሁሉ በተለይም ስለአለባበሱ ምሳሌ መልስ በሰጠሁ ቄጥር ክርስቲያኖች መሆናችንን የሚጠራጠር ሰው ይመስል ሕማማቱን የሚያስታውስ ማናቸውም ነገር አላቸውና ክርስቲያኖች ናቸው ማለቱን አስተርጓሚው በሙሉ ነገረኝ። እንደገና ንጉሠ ነገሥቱ ጥያቄ በማቅረብ ለምንድን ነው በናንተ ስርዐት በዚህ የማትቀድሱ

አለኝ፤ ይህን ያላደረግንበት ድንኳን ስለሌለን ነው አልሁት። ስለዚህ በየቀኑ ቅዳሴ ለማድረስ እንችል ዘንድ በማግሥቱ ድንኳን የሚያዝልን መሆኑን ተስፋ ሰጠኝ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ለብሼው የነበረውን ያገልግሎት ልብሴን የያንዳንዱን ልብስ ምሳሌ እንደገና እንዳስረዳው አዞኝ እንዲሁ አደረግሁ። ከዚህ በኋላ ምሽቱን ያላንዳች ዕረፍት በዚህ አኳኋን ካለፍን በኋላ ከእኩለ ሌሊት በላይ ሲሆን አሰናብቶን ሄድን።

ምዕራፍ ሰባ ዘጠኝ፤ የዕቃችን መሠረቅና ንጉሠ ነገሥቱ ለኛ ድንኳን ስለመላኩ።

ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በቤተ መንግሥቱ በነበርሁበት ማታ ከመንፈቀ ሌሊት በኋላ በድንኳናችን ውስጥ ሌቦች ገብተው የአምባሳደሩን ሁለት ካባዎች ሁለት ጥልፍ ልብስ «ፕሎት» ሰባት ሸሚዞች አንድ ባርኔጣና ብዙ ማለፊያ ዕቃዎችም ሌሎች ጥቃቅን ነገሮችንም ሣጥን በሚያህል ባንድ ትልቅ የቆዳ ቦርሳ ውስጥ ባንድነት እንዳኖራቸው ከነቦርሳው ወሰዱበት። የአማኑኤል ድሞራይሽንም ሃብት በቦርሳ ውስጥ እንዳኖረው በሙሉ ወሰዱበት። በዚያ ካገኘናቸው ፈረንጆች አንዱ እንድናኖርለት ትናንትናውን ከኛ ዘንድ የተዋቸው ሰባት ልብሶችም ተሰረቁ። በዚያ ሌሊት የተሰረቀውን ሃብት በሙሉ በሁለት መቶ ክሩዛዱ ገመቱት። በማግሥቱ ጥዋት የተሰረቀብንን ሃብት ለንጉሠ ነገሥቱ አመልክተን ፍርድ እንዲሰጠን አቤት እንል ዘንድ አምባሳደሩ እኔንና የንብረት ሹሙን ጸሐፊውንም ላከን። የዚያን ዕለት ማታ አምባሳደሩ ከሌቦቹ አንዱን ይዞ ባሰረበት ጊዜና እኛም አቤቱታችንን ለማቅረብና ፍርድ ለመጠየቅ ከብላቴናዎቹ ጋር ሆነን በንጉሣዊው ድንኳን ደጃፍ ደጅ በምንጠናበት ጊዜ አንድ ሴት እየጮኸች መጥታ «የፖርቱጋል አምባሳደርና ሰዎቹ የአገሩን ቋንቋ በሚያውቅ በአንድ አረብ አስተርጓሚነት ትናንት ማታ ወደ ቤቴ መጥተው ሴት ልጄን ነጥቀው ወደ ድንኳናቸው ወስደው ተዳፈ

ሩዋት፤ ወንዱ ልጄ በእህቱ መደፈር ተበሳጭቶ ለአቤቱታ ሲሄድ አግኝተውት ሌባ ነው ብለው ልጅቱዋን አታሎ ከወሰዳት ከዚያ አረብ ጋር አሰሩት» ስትል አቤቱታዋን አቀረበች። ስለዚህ እኛ የተዘረፍነውና ሴትዮዋ ባንድነት ቀርበን ከተነጣጠርን በኋላ በዚያ የነበሩት ሁሉ ባንድ ቃል ፍርድ ይሰጥ ካሉ በኋላ ከሳሾችንና ተከሳሾችን አሰናብተውን ወደየቦታችን ሄድን።

በንጉሠ ነገሥቱ ፊት በቀረብሁ ጊዜ በዚያው የነበረው ያመነኩሴ አቤቱታችንን ባቀረብንበት ማታ አንድ ማለፊያ ዓይነት ግን ጥቂት የተሠራበት ድንኳን አምጥቶልን የቅዳሴ ሥነ ሥርዐታችንን እንድንፈጽምበት ንጉሠ ነገሥቱ የላከልን መሆኑን ነገረን። ከዚህም በላይ በማግሥቱ የሊቀ መላእክት የቅዱስ ሩፋኤል በዓል የሚከበርበት ቀን ስለነበረ ድንኳኑን በቶሎ እንድንተክልና ለበዓሉ ክብር እንድ ናስቀድስ እንዲሁም በየቀኑ ለእርሱ ጤንነት እንድንጸልይለት ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዘ መሆኑን ገለጸልን። ይህ ድንኳን በወርቀዘቦና በከፋይ የተሠራ ሲሆን በውስጥ በኩል ደግሞ በጣም ስስ የሆነ የሻውል[1] ካባ ገበር አለው። ድንኳኑ ባሁኑ ሁኔታው እንኳ በጣም ጥሩ ስለሆነ ባዲስነቱ ግን በጣም ግሩም ዕቃ የነበረ መሆኑን ለመገመት ይቻላል። ይህን ድንኳን ንጉሠ ነገሥቱ የዘይላና የበርበራ ባላባት ከነበረው አንድ አዳል የወሰደው ነው ይባላል። ይህ የሆነው ከአራት ዓመት በፊት ነው ይላሉ። በዚህ ድንኳን ውስጥ ከመቀደሳችን በፊት ምናልባት አንድ እስላም በውስጡ ኃጢአት ሳይሠራበት አልቀረምና እንድንባርከው ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዘ መሆኑን መልእክተኛው አስታወቀን። ድንኳኑን የዚያኑ ዕለት ተክልነው፤ በማግሥቱ ጥዋት ቀደስንበት፤ በዚህ አገር ከአርባ ዓመት በፊት ጀምሮ የሚኖሩት ፈረንጆችና አንዳንድም ያገሩ ሰዎች በዚያ ተገኝተው አስቀደሱ።

ምዕራፍ ሰማንያ፤ ንጉሡ ነገሥቱ አምባሳደሩን ጠርቶ አንዳንድ ጥያቄ አቀረበለት፤ አንዳንድ ዕቃዎችም ለመነው።

ሐሙስ ህደር ስምንት ቀን ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶን ወዲያው ሄድን። አምባሳደሩ ከዚህ በፊት ሊያበረክት የነበረውን በርበሬና ማጥን አስይዞ ለመቅረብ ወሰነ። በጀጎሉ የመጀመርያ በር እንደደረስን በዚያ አቁመው በሉብነት ተጠርጥረው ስለታሠሩት ሰዎች ጉዳይ የማይረባ ጥያቄ አቀረቡልን፤ እንዲያውም ከንግግራቸውና ከጥያቄ አቸው ይልቅ ስለተሠረቀብን ዕቃ ጉዳይ አንዳች ውሳኔ ሳይሰጡን ወይም ምን ማድረግ እንደሚበጅ ሳይነግሩን የታሠሩትን ሰዎች እንድንለቅ አዘዙን። የሆነ ሆኖ ሶስት መቶ እንጀራና ሰላሳ ገንቦ ጠጅ አዘውልን እንዲሁም እነርሱ ከሚበሉት ማለፊያ ምግብ ተልኮልን ወደ ድንኳናችን ተመለስን።

ለሁለኛ ጊዜ አስጠርተውን ከሄድን በኋላ ለአምባሳደሩ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች አቀረቡለት፤ ከነዚህም ጥያቄዎች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፤ ወደዚህ እንድትመጣ የሾመህ የፖርቱጋል ንጉሥ ነው ወይስ ጠቅላይ ገዥው? ጠቅላይ ገዥው ወደ ምጽዋ ወደብ በመጣ ጊዜ እስላሞቹን ሁሉ ገድሎአልን ወይስ የዚያኑ ጊዜ አንዳንዳቹ ወደከተማው ተመልሰዋል? ዳሞት ከባሕሩ ቅርብ ስለሆነ ለምንድን ነው ከባሕሩ በቀጥታ ወደዚያ ያልሄዳችሁት? የፖርቱጋል ንጉሥ አሽከሮች ከሆናችሁ ለምንድር ነው ቀኝ ትከሻችሁን በመስቀል ያልተተኮሳችሁት? (ይህን ጥያቄ ያቀረቡበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱ አሽከሮችና እንዲሁም ታናናሾችና ታላላቆች መኳንንት ሁሉ በቀኝ ትከሻቸው ላይ የመስቀል ትኩሳት እንዲኖራቸው ልምድ ስለሆነ ነው።) ይህን በርበሬ ለንጉሠ ነገሥቱ ከሰጣችሁ እናንተስ ለስንቃችሁ ምን ይተርፋችኋል? አምባሳደሩም ለቀረቡለት ጥያቄዎች ሁሉ በተለይም በመጨረሻ ለተጠቀሰው ጥያቄ መልስ በመስጠት «የፖርቱጋል ንጉሥ ያዘዘልን ብዙ ወርቅና ብር ጨርቅም ስላለን እሱን እየበላን እንሄዳለን» አለ። እንዲሁም ተመልሰን ለመሄድ እንድንችል ፈቃድ ጠየቀ። አምባሳደሩ በመጨረሻ ያቀረበውን ጥያቄ

መልስ በመስጠት አይዞአችሁ ትሄዳላችሁ አሉን። አምባሳደሩም መልሶ በግርማዊነትዎ ፊትና በቤተ መንግሥትዎ ይልቁንም ክርስቲያኖች በሚኖሩበት በግዛትዎ ባለንበት ጊዜ ከቶ ሥጋት አያድርብንም ሲል መለሰ። ከዚህ በኋላ አሰናብተውን ወደ ድንኳናችን ሄድን።

በማግሥቱ አርብ ንጉሠ ነገሥቱ በዚያ የነበሩትን ጉራዴዎች ላከ[1]። አምባሳደሩም ጉራዴዎቹን ለንጉሠ ነገሥቱ ከመላኩ በላይ ደስ ካሉት ሊያስቀራቸው እንደሚችልና እነዚህንም መሣርያዎች ቢገለገልባቸው እንደውለታ አድርጎ የሚቆጥረው መሆኑንም ጨምሮ አስታወቀ። ንጉሠ ነገሥቱም መልእክተኛውን መልሶ በመላክ እነዚያን ጉራዴዎች የወሰድሁ እንደሆነ የፖርቱጋል ንጉሥ ለሠራዊቱ በጣም የሚያስፈልገውን መሣርያ ወሰድባቸው አይለኝምን? ሲል ጠየቀን። በዚህ ጊዜ አምባሳደሩ እንደገና በመልእክተኛው አማካይነት መልስ በመስጠት ከወደዱዋቸው ሊያስቀሩዋቸው ይችላሉ፤ በሕንድ በሚገኙት በንጉሣችን ግንቦችና በግምጃ ቤቶቹም ውስጥ ሌሎች ብዙዎች አሉና ስለዚህ እርስዎ እነዚህን መሣርያዎች ወስደው በኛ በአሽከሮቹ መሣርያዎች ቢገለገሉ የፖርቱጋልን ንጉሥ ያስደስተዋል አለ። ይህ መልእክት እንደተላከ ወዲያውኑ ሱሪ በመለመን ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ላከ። አምባሳደሩም የራሱንና የሎፑ ደ ጋማን ሱሪ ልኮ በአምባሳደሩና በጓደኞቹ እጅ ሱሪዎች ልዩ ልዩ ልብሶችና ጉራዴዎች እንዲሁም ያያቸውንና መኖራቸውንም የሚያውቀውን ማናቸውንም ዕቃዎች ከወደዳቸው በሙሉ ሊወስዳቸው የሚችል መሆኑን ከመግለጹም በላይ ይልቁንም ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ዕቃ ስለተገለገለበት የፖርቱጋል ንጉሥና ጠቅላይ ገዥውም እርሱንና (ማለት አምባሳደሩንና) ሰዎቹን የሚከሱ መሆናቸውን ጨምሮ ተናገረ። የዚያን ዕለት ብዙ ጥያቄዎች ቀርበው በሙሉ መልስ ተሰጡ፤ እነዚህን ጥያቄዎችና መልሶች በዚህ ላይ መጻፍ ብዙ ሃተታ ማብዛት ይሆናል በማለት አልፌአቸዋለሁ።

ምዕራፍ ሰማንያ አንድ፤ ጉግስ እንድንጫወት በመጠየቅ ንጉሠ ነገሥቱ ለአምባሳደሩ ፈረሶች ስለመላኩ፤ አንድ የብር ጽዋም ስለማበርከቱ፤ ለአምባሳደሩ ስለቀረቡለት አዲስ ጥያቄዎች፤ የተሠረቁት ዕቃዎች ጉዳይ ስለመቅረቡ።

አምባሳደሩና ሌሎች የኛ አራት ሰዎች ሆነው በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ፊትለፊት ጉግስ እንዲያሳዩ በመጠየቅ ንጉሠ ነገሥቱ ሕዳር 12 ቀን ማክሰኞ ከድንኳናችን ድረስ አምስት ትልልቅና መልካም ጥርኞች ላከልን። ጊዜው በጣም መሽቶ ነበር። አምባሳደሩም ይህን ጨዋታ ስለማያውቅ ለመሄድ አልተደሰተም ነበር። የኛ ሰዎች ግን ባንድነት ተያይዘው «እንዲህ አድርጉ አሁን ደግሞ ይህን አድርጉ» እያሉዋቸው ጨዋታውን ካሳዩ በኋላ ወደ ድንኳናችን ሄደን ሶስት ገንቦ ጠጅ ተላከልን።

በማግሥቱ አንድ ጠንካራና ጥሩ ሆኖ በኛ ዓይነት በብር ተሠርቶ ወርቅ የተነከረ እግራም የብር ጽዋ ንጉሠ ነገሥቱ ለአምባሳደሩ ላከለት። ይህ ጽዋ በእግሩ ላይ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ምስል ሲኖረው በወገቡም ላይ በጥሩ ፊደሎች በላቲንኛ «ይህ የአዲስ ኪዳን ጽዋ ነው» የሚል ቃል ተቀርጾበታል። ይህ የተላከው አምባሳደሩ እንዲጠጣበት ነበር። እርፈ መስቀል አልነበረበትም፤ ወይም የጽሑፉን ትርጉም አላስተዋሉትም ነበር፤ በአሠራሩም የነርሱን አይመስልም። የነርሱ ጽዋ ከወጭት ጥቂት አነስ ብሎ የተሠራና ይዘቱ ጥልቅና ጎድጓዳ ስለሆነ ማቁረቢያውን ደም የሚያወጡት ከዚሁ በማንኪያ በመጨለፍ ነው።

በዚህ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ጥያቄዎችን አቀረበ፤ ሌላም ብዙ ነገሮች ተናገረ። ከነዚህም አንዱ ዘይላን ለመያዝ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል የሚል ነበር። ንግግሩንም በመቀጠል እርሱ ራሱ ወደ ዘይላ በምድር ለመሄድ የሚፈልግ መሆኑንና ሠራዊቱ ከፖርቱጋል ንጉሥ ሠራዊት ጋር የሚገናኙና የሚተያዩ መሆናቸውን ገለጸ፤ ይሁን እንጂ ውኃ የማይገኝበት የሁለት ቀን መንገድ መኖሩን እንድ

ንገነዘብ አስጠንቅቆ፤ ለዚሁም ሁኔታ ማሸነፊያ ምን ማድረግ እንደሚበጅ ምክር ጠየቀን። እኛም መልስ በመስጠት አምስት ስድስት ወር የሚፈጀውን መንገድ አቋርጠን ስንመጣ በመንገድ ውኃ የማይገኝ መሆኑን በማወቅ በርከት አድርገን ይዘን መጥተን ስለነበር በመንገድ ስለውኃ ሳናስብ እዚያ መድረሳችንን ገለጽን። ስለዚህ በአገሩ ብዙ ግመሎች ስለሚገኙ በነሱ ውኃ ቢጫን ያን ደረቅ የሁለት ቀን መንገድ ያለሥጋት ለማለፍ የሚቻል መሆኑን አስታወቅን።

በማግሥቱ ሕዳር 14 ቀን ንጉሠ ነገሥቱ እምብዛም ግምት የሌላቸው ሁለት ዕቃዎች፤ ማለት ለጸሎት ቤታችን መሠውያ በወርቅ ቀለም የተቀባ አንድ የመጽሐፍ ማኖርያ አንድ ጠረጴዛና ለእጃችን መታጠቢያ እንዲሆን ከእንጨት የተሠራ ገበቴ ላከልን። የዚያኑ ዕለት የሁላችንም ስም በጽሑፍ እንዲላክለት ጠይቆ ዝርዝሩ ተላከለት። መልእክተኛው ወዲያው ተመልሶ አምባሳደሩን «ሩድሪጉ ማለት ትርጉሙ ምንድን ነው? ሊማስ? የሌሎቹስ ሰዎች ስሞች ትርጉሙ ምንድር ነው?» ሲል ጠየቀው። ትርጉሙ እንደተጠየቀው በጽሑፍ ተገልጾ ተላከለት።

በማግሥቱ ኅሕ ከመቅደዱ በፊት እንዳለፈው ጊዜ ከአምባሳደሩ ድንኳን ውስጥ ሌላ ዕቃ ተሰረቀ። ስድስት ወይም ሰባት የሚሆኑ ሰዎች ከድንኳኑ ውስጥ ገብተው ጊዮርጊስ ዲ አብሬው ተንተርሶት የተኛውን በአርባ ክሩዛዱ የገዛውን ካባ ወሰዱበት፤ እንዲሁም ከዕቃችን ውስጥ ሁለት ጥቅል የጥጥ ጨርቅ ወሰዱ። ስለተሰረቀብን ዕቃ ምንም ዓይነት ዕርዳታ አልተደረገልንም። የሌቦች ሹም አለ የሚባላው እርግጥ ነው ይላሉ። የሌቦቹ አለቃና የጭፍሮቹም[1] ሥራ ንጉሠ ነገሥቱ በሄደበት ቦታ ሁሉ እየሄዱ ድንኳን መትከል ነው ይባላል፤ ለዚህ አገልግሎታቸው ምንም ዋጋ ስለማይከፈላቸው እየሰረቁ በሚያገኙት ሃብት ብቻ ይተዳደራሉ።

የዚያኑ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ በቀይ ፈርጥ ያጌጠ አንድ የፈረስ ኮርቻ ላከልን፤ ይህ ኮርቻ በጣም ከባድ ከመሆኑም በላይ በአሠራሩም ደስ የማያሰኝና ውራጅም ነበር። ወዲያውኑ መልእክተኛ መጥቶ

በዚህ አገር የፖርቱጋልን ንጉሥ በይበልጥ ደስ ሊያሰኘው የሚችል ነገር ምንድን ነው? ጃንደረባ ወይም ሌላ ነገር ነውን? ሲሉ አምባሳደሩን ጠየቁው። አምባሳደሩም መልስ በመስጠት ነገሥታትና መሳፍንት ከራሳቸው ሃብት ይልቅ ሌሎች ነገሥታት የሚልኩላቸውን ዕቃዎች በጣም የሚወዱበት ምክንያት በግምታቸው ታላቅነት ሳይሆን ስጦታ በመሆናቸው ብቻ ነው ሲል መለሰ።

ምዕራፍ ሰማንያ ሁለት፤ አምባሳደሩን አንድ ፈረስ እንዲያሳዩት ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ፤ የቤተ መንግሥቱ መኳንንት በኛ ጸሎት ቤት መጥተው እንዲያስቀድሱ ታዘዙ፤ ንጉሠ ነገሥቱ እኔን አስጠርቶኝ ብዙ ጥያቄ አስጠየቀኝ።

በማግሥቱ ጥዋት በወሩ በአስራ አምስተኛው ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ተሸፍኖ የነበረ አንድ ፈረስ አምባሳደሩ እንዲጎበኝ አዞ ከጉብኝቱ በኋላ ይህን የመሰለ በፖርቱጋል ይገኛልን ሲል ጠየቀው። አምባሳደሩም መልሶ የፖርቱጋል ንጉሥ ቁጥራቸው የበዛ የጦር መሣርያዎች ከነዚህም ውስጥ ከብረት የተሠሩ የፈረስ መሸፈኛዎች በዱዋርት ጋልቫው እጅ (ለንጉሠ ነገሥቱ) ተልከውለት አሁን በሕንድ የሚገኙ መሆናቸውን እንዲሁም የፈለገውን ያህል የፖርቱጋል ንጉሥ የሚልክለት መሆኑን ነገረው።

በማግሥቱ ማለት ቅዳሜ በቤተ መንግሥቱ የሚገኙት መኳንንት በጸሎት ቤታችን ተገኝተው እንዲያስቀድሱ ታዘዙ፤ በማግሥቱ እሁድም ቅዳሜ ዕለት ከመጡት የበለጡ ብዙ ሰዎች ተገኝው አስቀድሰው ስናጠምቅም አዩ። በሁኔታቸው እንደተመለከትነውና በአገሩም የሚገኙት ፈረንጆች እንደነገሩን እንዲሁም ከኛ ጋር የነበሩት አስተርጓሚዎች ባረጋገጡልን መሠረት በቅዳሴው ላይ የተገኙት ሰዎች በጣም የተደነቁና የቅዳሴ ሥርዐታችንንም በጣም የወደዱት መሆና

ቸውን ተረድተናል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳ ሌላውን ነገር ሁሉ ቢወዱትም በቅዳሴው ላይ የተገኙትን ሰዎች ሁሉና የተጠመቁትን ባለማቁረባችን ቅር የተሰኙ መሆናቸውን ተረዳን። የክርክራቸውም መሠረት ያደረጉት እኛ ቁርባን የምንሰጠው በአንዳንድ በዓል ቀን ብቻ ሲሆን ይኸውም የሚሰጠው ለተናዘዙት ሰዎች ብቻ መሆኑን፤ የተጠመቁት ሰዎች በጥምቀቱ ጊዜ ንጹህ መሆናቸው የማይካድ ቢሆንም የአምላክን ሥጋ ወደሙ በንዴት ያለ ክብር ሊቀበሉት እንደሚገባ ስለማያውቁ አካለ መጠን እስኪደርሱ ሥጋ ወደሙ እንዳይቀበሉ መከልከሉ አግባብ ነገር ነው ሲሉ መለሱ። ነገር ግን በነርሱ ደንብ መሠረት ቅዳሴ የገቡት ቄሶችና ዲያቆኖች ያስቀደሱትም ምዕመናንም ሁሉ፤ የተጠመቁ ሕጻናት ታላላቅ ሆኑ ታናናሽ በሙሉ መቁረብ አለባቸው አሉ። ይህን አስተያየት የገለጹ አዛውንትና የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች መልስ በመስጠት ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከተገኙት ምዕመናን ውስጥ አንዳንድ ወይም አንዳንዶች ኃጢአተኞች ስለማይጠፉ የሱስ ክርስቶስ ሥጋዬን በከንቱ የበላውን እኮንነዋለሁ ያለ መሆኑን አሳሰብናቸው። ስለጥምቀትም ጉዳይ ጌታችን ራሱ ያመነ የተጠመቀ ይድናል የማያምን ይፈረድበታል ሲል ያስተማረ መሆኑን ከዚህም በላይ የማያውቁ ሰዎችና በሃይማኖቱ ያላደጉ ሁሉ ትንሽ እምነት የሚኖራቸው መሆኑን፤ ሕጻናትም አለማወቃቸው በቂ መሆኑን በማስረዳት የነርሱ ልምድ ትክክል ያልመሰለኝ መሆኔን ገለጽሁላቸው። ሕጻናት በሃይማኖት ሳያድጉ ወይም ሳያጠኑና ያን ትልቅ ምስጢር ለማስተዋል የሚያበቃ ዕድሜና ችሎታ ሳይኖራቸው ሥጋ ወደሙ እንዲቀበሉ ማድረጉ መልካም ነገር አለመሆኑን ጨምሬ አስረድቻቸው በዚያ የነበሩት ሁሉ ይህን ከማመስገናቸው በላይ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ለመስማት የሚደሰት መሆኑን ነገሩኝ።

በወሩ አስራ ስምንተኛው ቀን ሰኞ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶ ብዙ ጥያቄዎች አቅርቦልኝ ላንዳንዶቹ «እንደዚህ መሆኑ እርግጥ ነው» ለሌሎቹም «ይህን መሆኑን አላውቅም» ስል በእግዚአብሔር እርዳታ መልስ ሰጧቸው። የመጀመርያው ጥያቄ የሚከተለው ነበር። የክርስቶስን መምጣት የተነበዩት ነቢያት ስንት ነበሩ?

በኔ አገማመት ሁሉም የተነቡ መሆናቸውን ገለጽሁ፤ አንዱ ስለመ ምጣቱ፤ ሌሎቹ ሥጋ ስለመልበሱ፤ ሌሎቹ ስለሕይወቱ፤ ሌሎቹ ስለሕማማቱና ሞቱ፤ ሌሎቹም ስለትንሳኤው እንዲሁም በጠቅላላው ትንቢቶቹ ሁሉ ስለክርስቶስ የሚናገሩ ናቸው። ሁለተኛ ጥያቄ፤ የነቢያት ቁጥር ስንት ነው? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት አልቻ ልሁም አልኳቸው። ሶስተኛ ጥያቄ፤ እያንዳንዱ ነቢይ ስንት መጽሐፍ ደርሶአል? እያንዳንዱ ነቢይ ለምሳሌ ኤርምያስ ወይም ዳንኤል ወይም ማናቸውም ሌላ ነቢይ የጻፈውን ትንቢት የምናነበው አንደኛ፤ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መጽሐፍ በማለት ሳይሆን በውስጡ በሚገኙት ብዙ መቶ ክፍሎች መጠን ስለሆነ እያንዳንዱ ነቢይ በምዕራፍ የተከፈሉ አንዳንድ መጽሐፍ ጽፎአል። አራተኛ ጥያቄ፤ ጳውሎስ የጻፋቸው መጽሐፍ ቁጥር ስንት ነው? ምንም እንኳ የጻፈው ለብዙ ሕዝቦች ለምሳሌ ለሮሜ ሰዎች ለቆርንጦስ ሰዎች ለኤፌሶን ሰዎች ለዕብራውያንና ለሌሎችም በመለየት ቢሆንም፤ አጻጻፉም የነቢያትን ቢመስልም መጽሐፉ አንድ ብቻ ነው። አምስተኛ ጥያቄ፤ ወንጌላውያን ስንት መጽሐፍ ነው የጻፉት? ለዚህም ጥያቄ መልስ በመስጠት ከዮሐንስ በስተቀር እያንዳንዱ ወንጌላዊ በምዕራፍ የተከፋፈሉ አንዳንድ መጽሐፍ ደርሶአል። ዮሐንስ ግን የዮሐንስ ራዕይን በተጨ ማሪ ስለጻፈ ሁለት መጽሐፍ ጽፎአል። ወዲያውኑ ሌላ ጥያቄ ተከትሎ በአዲስና በብሉይ ኪዳኖች የሚገኙትን የነቢያትን የሐዋርያትንና የወንጌላውያንን መጽሐፍ በጠቅላላው እንድዘረዝር ተጠየቅሁ። የቅድ ስት መጽሐፍት ቁጥር ሰማንያ አንድ ነው ሲሉ የሚያምኑ መሆናቸውን አስቀድሜ ሰምቼ ስለነበር ይህንኑ መልስ ሰጠኋቸው። ይሁን እንጂ ይህን ጥያቄና ሌሎቹንም ባቀረቡልኝ ጊዜ በመርከብ ሆኜ ስድስት ዓመት ሙሉ ወዲያ ወዲህ እዞዋወር ስለነበርሁ መጽሐፍ ይዤ ባለመምጣቴ በቃል የያዝሁት ጠፍቶብኛል በማለት ቁርጥ ያለ መልስ አልሰጠኋቸውም። እነርሱም ወዲያውኑ መልሰው ምንም እንኳ መልስህን «በኔ አስተያየት» እያልህ ብትሰጥም እውነተኛ ነገር በመሆኑ ነገር የማትዘነጋ ሰው ነህ አሉኝ።

ምዕራፍ ሰማንያ ሶስት፤ አምባሳደሩ ተጠርቶ ገብቶ ይዞ የመጣውን ደብዳቤ ለንጉሠ ነገሥቱ ስለማቅረቡ፤ ስለንጉሠ ነገሥቱ ዕድሜና ሁኔታ።

ማክሰኞ ዕለት አምባሳደሩና አብረነው የነበርነው ሁሉ ተጠርተን ቀረብን። ማታ በኃይለኛ ብርድ ውስጥ ሶስት ሰዓት ያህል ከጠበቅን በኋላ እንደበፊቱ የጀነሉን በሮች አልፈን ገባን። ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ስንገባ ካየናቸው የበለጡና መሣርያ የያዙ እጅግ ሰዎች አየን። ከበሩም ፊትለፊት ከመቼውም የበለጡ ጥዋፎች በርተው ነበሩ። በዚህኛው በር ላይ ብዙ ሳያቆሙን ወዲያውኑ ከአምባሳደሩ ጋር ቁጥራችን ዘጠኝ የሆነውን እኛን ፖርቱጊዞቹን ከመጀመርያው መጋረጃ ውስጥ አስገቡን፤ ከነዚህ ከመጀመርያዎቹ መጋረጃዎች አልፎ የሚገኙ እጅግ ያጌጡ ሌሎች መጋረጃዎች ስለነበሩ እነሱን አልፈን እንድ ንሄድ አዘዙን። ከነዚህ ከመጨረሻዎቹ በኋላ ሰፋፊ ስጋጃ የተነጠ ፈባቸው ትልልቅና ጌጠኞች መደቦች አየን። ከመደቦቹ ፊት ለፊት እጅግ ያጌጡ መጋረጃዎች ይታዩ ነበር። እኛ እዚህ በቆምንበት ጊዜ መጋረጃዎቹን ወደ ግራና ቀኝ ሸምጥጠዋቸው ንጉሠ ነገሥቱ እጅግ የተጌጡ ስድስት ደረጃዎች ባላው ትልቅ መደብ ላይ ተቀምጠ አየነው። ከወገቡ በላይ በወርቅ ከዚያም በታች በብር ኮርቶ የተሠራ ዘውድ ጭኖ በእጁም የብር መስቀል ይዞ አፉንና አገጩን ባንድ ሰማያዊ ሻሽ ሸፍኖ ይታይ ነበር። ሻሹን አንዳንድ ጊዜ እየገለጡ ስለሚሸፍኑት ፊቱ በሙሉ ይታይ ነበር።

በቀኙ በኩል አንድ ብላቴና ጠፍጣፋ የብር መስቀል ይዞ ቆሞ ነበር። በመስቀሉ ላይ የተቀረጸው ነገር ምን መሆኑን ከነበር ንበት ቦታ ሆኖ ለይቶ ለማወቅ አይቻልም ነበር። ነገር ግን በኋላ ጠጋ ብዬ ስላየሁት ምን መሆኑን ለማወቅ ችያለሁ። ንጉሠ ነገሥቱ ፕሎት የሚመስሉ እጅጌአቸው ሰፊፋ የሆነ የሐር ሸሚዞች ለብሶ ካባ ደርቦ ነበር። ከጉልበቱ በታች የአቡን ሽርጥ በሚመስል ልብስ ተሸፍኖ በግድግዳ ላይ የተሳለ የእግዚአብሔር አብን ስዕል መስሎ ጉብ ብሎ ነበር። መስቀል ይዞ ከቆመው ብላቴና ሌላ በእጃቸው

ጎራዴ ይዘው በግራና ቀኝ የቆሙ ሁለት ሰዎች ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ መካከለኛ ሰውነት ያለው መልከመልካም ጠይም ጎልማሳ ነው። ዕድሜው ሃያ ሶስት ዓመት ነበር ይባላል። ፊቱም ክብ ዓይኖቹም ትልልቅ አፍንጫው ሰንዳዳ ጢም ለማብቀል የጀመረ ነው። በአስተያየትና በሁኔታው ትልቅ ሰው መሆኑ ይታወቅ ነበር። እኛ እርሱ ከነበረበት ቦታ የሁለት ጦር ርቀት ካለው ቦታ ላይ እንገኝ ነበር።

በኛና በንጉሠ ነገሥቱ መካከል እንደተለመደው አቃቤ ሰዓቱ መልእክት ያመላልስ ነበር። ከንጉሣዊው መደብ ግራና ቀኝ መብራት ይዘው የቆሙ በያንዳንድ በኩል አራት ብላቴኖች ነበሩ። የመልእክት መለዋወጡ ስነሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ በአገሩ ፊደልና ቋንቋ የተተረጎመውን የጠቅላይ ገዥውን ደብዳቤና መልእክት በአቃቤ ሰዓቱ አማካይነት አምባሳደሩ አቀረበለት። ደብዳቤውን ወዲያው አንብቦ «እነዚህ ደብዳቤዎች ከጠቅላይ ገዥው እንደሆነ የመጡት በምን ምክንያት ነው ስለ ፖርቱጋል ንጉሥ የሚናገሩት?» ሲል ጠየቀ። አምባሳደሩም መልሶ ጠቅላይ ገዥው ስለጌታው ስለንጉሡ ሆኖ ሕንድን የሚገዛ ሲሆን ስለርሱ ማለት ስለንጉሡ ሳይናገር እንዴት አድርጎ ለመጻፍ ይችል ኖሮአል? አለ። ከዚህ በኋላ ጥያቄውን ትቶ አባቶቹ ያላዩትንና እርሱም ሊያየው የማይችለውን ነገር ስላየ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚያቀርብ ከመሆኑ በላይ፤ የጋራ ጠላቶቻችን (ሩሚዎች) በምጽዋና በሱዋኪን ላይ ይቋቋማሉ እየተባለ ይፈራ ስለነበር፤ የፖርቱጋል ንጉሥ በተባሉት ቦታዎች ላይ ምሽግ እንዲሠራ ቢያዝ ኖሮ የሚደሰት መሆኑን ገልጾ፤ እስላሞች በነዚህ ቦታዎች የተቋቋሙ እንደሆነ እርሱንና እኛን ፖርቱጊዞችንም ድል የሚነሱን መሆናቸውን አሳስቦ ለተባሉት ቦታዎች መጠበቂያ የሚያስፈልገውን ስንቅና ሰው የሚችል መሆኑን ነገረን። ነገር ግን የዘይላ ወደብ ለአደን፤ ለጅዳና፤ ለሜካ፤ እስከ ቶሮና ካይሮ ድረስ ለመላው የአረብ አገር የሚላከው ምግብ የሚያልፍበት ስለሆነ ብዙ ምግብ ስለሚገኝበት ከሁሉ በፊት ዘይላን መያዝ አስፈላጊ ነገር መሆኑን አስገነዘበን። በዚህ ጊዜ መልስ በመስጠት የፖርቱጋል ንጉሥ መርከቦች ባለፉበት ቦታ የሚኖሩ ሁሉ በፍርሃት ከተማቸውን እየጣሉ ስለሚሸሹ ዘይላንም ሆነ ሌሎቹንም ቦታዎች መያዝ አስቸጋሪ

አይደለም፤ ዳሩ ግን ዘይላ ከባብ ኤል መንደብ ወሽመጥ ውጭ ሲሆን ሌሎቹ ሁለቱ ግን በግቢ በኩል ስለሚገኙ በነዚህ ላይ ምሽግ ቢሠራ ጅዳንና ሜካን ለመያዝ እንዲያውም እስከ ካይሮ ድረስ የሚገኙትን ማናቸውንም ቦታዎች በሙሉ ለመያዝ የሚቻል መሆኑንና በዘቢድ ላይ የሚገኘውን የቱርኮችንና የሩሚዎችን የባሕር ኃይል ለመከላከል የሚያመች መሆኑን ገለጽን። ለዚህና ለባሕር ኃይሉም ስንቅ ማናቸውንም አስፈላጊ ነገር የሚሰጥ መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ አረጋገጠ። ይህን ስንቅ ማን እንደሚሰጥና ከየትስ እንደሚወሰድ ንጉሠ ነገሥቱ ያዝ ዘንድ አምባሳደሩ ለመነው።

ንጉሠ ነገሥቱም መልሶ ስንቅ የሚሰጥ ሰው የሚሾም መሆኑን ተስፋ ሰጥቶ አምባሳደሩም የምሽጉ ሹም እንዲሆን አዘዘው። አምባሳደሩም መልሶ ይህ ምሽግ ያለአንዳች አዛዥ ሊቆይ ስለማይገባው ግርማዊነትዎን ለማገልገል የምችል ሆኜ ካገኙኝ የምሽጉ አዛዥ ሆኜ በዚህ እንድቀር ጠቅላይ ገዥው ፈቃድ እንዲሰጠኝ እጠይቀዋለሁ አለ። በዚህ እኳኋን መልካም ቃል ስንለዋወጥ ከቆየን በኋላ በጉብኝታችን ተደስተን ተለያየን።

ምዕራፍ ሰማንያ አራት፤ እኔ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተጠርቼ ስለቅዱስ የሮኒሞስ፤ ቅዱስ ዶሚንጎስና ቅዱስ ፍራንሲስኮ ጥያቄ ቀረበልኝ።

በማግሥቱ ሕዳር ሃያ ቀን ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶኝ ገብቼ ብዙ ጥያቄ ቀረበልኝ። ከነዚህም ጥያቄዎች የቅዱስ የሮኒሞስ ቅዱስ ዶሚንጎስና ቅዱስ ፍራንሲስኮ ትውልድ አገራቸው የት መሆኑን፤ እንዲሁም ጠቅላይ ገዥው በጻፈው ደብዳቤ ላይ በመደጋገም በማንሣት የፖርቱጋል ንጉሥ ባቀናቸው አገሮች ሁሉ ለምሳሌ በሜኒ ኮንጎና በቤኒን በሕንድም በነዚህ ቅዱሳን ስም ቤተ ክርስቲያኖች አሠርቶአል ማለቱ በምን ምክንያት መሆኑን በሙሉ እንድ ገልጽ ታዘዝሁ። ጥያቄውን በማቋረጥ ቅዱስ የሮኒሞስ በየሩሳሌም

የነበር ፓትርያርክ ሲሆን ትውልድ አገሩ በግሪክ ወይም በኤስክላቮንያ[1] ነበር፤ ቅዱስ ዶሚንጎስ ትውልድ አገሩ በአስማ ኤጲስቆጶሳዊ ቀበሌ በእስፓኝ ነበር፤ ቅዱስ ፍራንሲስኮ ከኢጣሊያ ነው ስል አስረዳሁ። እኔ በማውቀወና ገድላቸው ተጽፎባቸው የሚገኙትን መጽሐፍ ባነበበሁት መሠረት ስለነዚህ ቅዱሳን ብዙ አተትሁላቸው። እንዲሁም በነዚህ በተባረኩ ቅዱሳን ስም በፈረንሳይ አገር[2] ታላላቅ ቤተ ክርስቲያኖች የተሠሩ መሆናቸውን ከመግለጼ በላይ በነዚህ ሰዎች የተቀደሰ ኑሮ ምሳሌነት ብዙ ሌሎች ቅዱሳን የወጡ መሆናቸውን ጨምሬ አስረዳሁ። ወዲያውኑ ባስተርጓሚው አማካይነት የነዚህን ቅዱሳን ገድል አውቃለሁ ብለሃልና ስለነርሱ አፍታተህ አትት አለኝ። የታዘዝሁትን ከመፈጸሜ በፊት ቀጥሎ የተመለከተው ሌላ ጥያቄ ቀረበ። «እናንተም እኛም ክርስቲያኖች ስንሆን እናንተ ቤተ ክርስቲያኖችን ማለት የአንጾክያን የቁስጥንጥንያንና የሮምን ቤተ ክርስቲያን በምትጠራጠሩት መካከል እንዴት ልዩነት ሊኖር ቻለ? እያንዳንዱም ቤተ ክርስቲያን የራሱን መንገድ መከተሉ፤ ሶስት መቶ አስራ ስምንት አበው የተገኙበት የጳጳስ ሌዎን ጉባኤ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ የክርስትና መንበር በአንጾክያ መሆኑ ለምንድን ነው?» ሲሉ ጠየቁኝ። ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ይህ ጥያቄ ቀርቦልኝ መልስ የሰጠሁ ብሆንም ቀጥሎ በተመለከተው ዓይነት መለስሁላቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ በአንጾክያ (በግሪክ) አምስት ዓመት አቡን ስለነበር ይህች ከተማ የክርስትና መንበር የነበረባት መሆኑዋ የማይካድ ነው፤ ከዚያ በኋላ ግን ጴጥሮስ በሮም በአቡንነት ሃያ አምስት ዓመት ቆይቶ እርሱም ቅዱስ ጳውሎስም በዚያው ተሰቃይተው ስለሞቱ የሱስ ክርስቶስ «ጴጥሮስ ቤተ ክርስ ቲያኔን ባንተ ላይ አንጻለሁ» ያለው ትንቢት ስለተፈጸመ እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን አጽማቸው በሚገኝበት ቦታ ላይ ተሠራች። ስለዚህ ጉዳይ መልስ አልሰጡኝም። ይህ ካለቀ በኋላ የሮም ጳጳሱ የሚያዘውን ሁሉ ትፈጽማላችሁን ሲሉ ጠየቁኝ። ለዚህም መልስ በመስጠት «ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን» ስንል በምንናዘዝባት በቅድስት ሃይማኖታችን ማለት በካቶሊክ ሃይማኖት ጳጳሱ የሚለውን ቃል እንድንፈጽም ታዘናል። ቅድስት ቤተ ክርስ ቲያን የተባለው ጳጳሱ ራሱ ነው። እርሱ ያሠረው የታሠረ ይሆናል

እርሱም የፈታው የተፈታ ይሆናል፤ ይህ ሥልጣን በሕያዋን ላይ ብቻ ሳይወሰን በቅጣት ላይ የሚገኙትን ሙታንንም የሚጨምር ነው። ለዚህም መልስ በመስጠት ጳጳሱ ሐዋርያት ያልጻፉትን ነገር እንድንፈጽም ቢያዘን ትዕዛዙን እንጥሰው ነበር፤ እንዲሁም አቡናችን ይህን የመሰለ ቃል ቢሰጡን ትዕዛዙን እናቃዋለው ነበር አሉኝ።

ጳጳሱ የቤተ ክርስቲያን ሃላፊ መሆኑንና የማዕርግ መጠርያውም ቅዱስ አባት የሚያሰኝ በመሆኑ እርሱ የሚያዘውን ሁሉ መፈጸም አለብን። እርሱ ቅዱስ በመሆኑ ሐዋርያት እየጠቀሱ በጻፉዋቸው በነቢያት መጻሕፍትና በአራቱ ወንጌሎች መሠረት ቅዱስ ትዕዛዝ ይሰጣል እንጂ ሌላ ነገር አያዝም። ከነዚህ ሌላ ጳጳሱ ትዕዛዙን የሚመሠርትባቸው ተበታትነው የሚገኙት ማናቸውም ምስጢሮች በሚገኙባቸው በእመ አብያተ ክርስቲያናት መጽሐፍ ነው። መንፈስ ቅዱስ ብሩሃን ያደረጋቸው ጳጳሱና መሑራኑ ሆነው እነዚህን ምስጢሮች ካላስተማሩና ካልገለጹ በስተቀር ሰው ሊያስተውላቸው አይችልም። ብጹእ ጳጳሱ ብቻ ሳይሆን ካርዲናሎቹም ሊቀ አቡኖቹም አቡኖቹም ፓትርያርኮቹም እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኖችም ሃላፊዎችም ሁሉ የቅድስቲቱ ሃይማኖት ሰባኪዎችና አዋጅ ነጋሪዎች ናቸው። ይህች ቅድስት ሃይማኖት ለግርማዊነትዎ አገር በጣም አስፈላጊ ናት። ምክንያቱም ምንም እንኳ በዚህ አገር አንዳንድ የተማሩ ሰዎች ቢኖሩም ትምህርታቸው ለራሳቸው ነው እንጂ ሃይማኖቲቱን ለማወጅ ወይም ሌሎችን ለማስተማር አይደለም። ስለማናቸውም ጉዳይ በመጽሐፍት ውስጥ የሚገኘው ምስጢር ሁሉ የተሰጠው በምሳሌ መሆኑን ግርማዊነትዎ ሊያውቀው ይገባል። ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ በሃያ አራተኛው ምዕራፍ የሱስ ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱ ፊት ልዩ ልዩ ተአምራት አድርጓል፤ እነዚህም በመጽሐፍ አልተጻፉም ብሎአል።»

ምንም እንኳ ይህን ሃተታ ብሰጣቸውም፤ በሙሉ የሐዋርያት በነበረው በኒቂያ ጉባኤ ላይ የተወሰነውን እንጂ ጳጳሱ የሚያዘውን ለመፈጸም ግዴታ የለባችሁም አሉኝ። ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት ሁሉ በጉባኤው ላይ እመቤታችን የአምላክ እናት እንድትባል

መወሰኑንና ታላቁ እምነት መዘጋጀቱን አውቃለሁ፤ ነገር ግን የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ ላንተ እሰጣለሁ ሲል ክርስቶስ ሥልጣን የሰጠው ቅዱስ ጴጥሮስ ሃላፊዋ በሆናት በርሱም መንበር ላይ በተቀመጡት ወራሾቹ በምትመራዋ ባንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማለት በካቶሊክ ሃይማኖት እንድናምን ሐዋርያት ያስተማሩን መሆናቸውን እንጂ ሌላ ነገር መታዘዙን አላውቅም አልኋቸው። ምንም እንኳ ለጥቂት ጊዜ ቁስጥንጥንያ የክርስትና ሃይማኖት መንበር የነበረባት መሆንዋ የማይካድ ቢሆንም እውነተኛይቱ ቦታ ሮም ስለሆነች መንበሩ ወደዚያ ተዛውሮአል።

በዲያውኑ መልእክተኛ መጥቶ የኔን መልስ ንጉሠ ነገሥቱ የሚስማማበት መሆኑን ገልጾልኝ፤ እንደገናም ጥያቄውን ቀጥሎ በኢትዮጵያ ወይም በነርሱ አገርና ግዛቶች ሁሉ እንደ ኢጣሊያ እንደ ጀርመንና እንደ ግሪክ አገሮች በዙ ቅዱሶችና ቅድስቶች አለመኖራቸው በምን ምክንያት ነው ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም አስተያየቴን በመግለጽ በነዚያ አገሮች ብዙ አሕዛብ ነገሥታትና መኰንኖች በጭካኔ አገሮቹን ሲገዙ የክርስቶስን ሃይማኖት የመረጡት ግን በሃይማኖታቸው የጸኑ በመሆናቸው ጣዖትን ከመስገድና አጉል ሃይማኖትን ከመከተል ይልቅ ለክርስቶስ መሞትን ስለመረጡ በነዚህ አገሮች ብዙ ሰማዕታትና ተናዛዦች ደናግልም ሊበዙ ቻሉ፤ ስለዚህ በነዚህ ሰዎች ጽናትና ብርታት በመመራት እንዲሁም ከየሱስ ክርስቶስ ዕርገት ጀምሮ ያለማቋረጥ በፈረንጅ አገር የሚደረገውን ስብከት በመስማት የነዚህ አገሮች ሰዎች ሁልጊዜ እውነተኛይቱን ሃይማኖት ይከተላሉ፤ ስለዚህ ቅዱሶችና ቅድስታት መኖራቸው በዚህ ምክንያት ነው ስል አስረዳኋቸው። ይህን ተናግሬ እንዳበቃሁ ንጉሠ ነገሥቱ እኔ በሰጠሁት መልስ የተስማማና ይህን ግልጽ አስተያየት በመስማቱ የተደሰተ መሆኑን የሚገልጽ መልስ ሰጥተውኝ ወዲያውኑ ይህ የኢትዮጵያ ምድር የክርስቲያን አገር ከሆነ ስንት ጊዜ ያለው ይመስልሃል? ሲል አሰጠየቀኝ። ለዚህም የሚከተለውን መልስ ሰጠሁ፤ ትክክለኛውን ጊዜ አጣርቼ አላውቅም፤ ነገር ግን የክርስትና ሃይማኖት ወደዚህ አገር የመጣው ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ነው፤ ክርስትናን ወደዚህ አገር ያመጣው ሐዋርያው

ቅዱስ ፊሊጶስ ያስተማረውና ያጠመቀው የንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ነው፤ እንደዚሁም ወደዚህ አገር ክፍል ሐዋርያ ቅዱስ ማቴዎስ መጥቶአል፤ ነገር ግን ይህ አገር እንደገና ወደ አሕዛብ አገርነቱ ተመልሶ እንደሆነ ወይም የሌላ ሕዝብ መኖርያ ሆኖ እንደሆነ አላውቅም አልኋቸው። እኔ የሰጠሁትን መልስ በማተት በጃንደረባው ስብከት የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበለው የትግሬ አውራጃ ብቻ ሲሆን በዚያ አልፎ በሚገኙት አውራጃዎች ግን ክርስትና የደረሰው በጦር መሣርያ አስገዳጅነት ነው አሉኝ። ንግሥት ሕንደኬ የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበለችው ክርስቶስ ከሞተ ከአሰር ዓመት በኋላ ስለሆነ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ ኢትዮጵያ በክርስቲያን ነገሥታት ትገዛለች። በዚሁ ምክንያት ሰማዕታት አልነበሩም፤ የሰማዕታትም መሞት አስፈላጊ አልነበረም፤ በአገራችን ብዙ ወንዶችና ሴቶች የቅድስናን ኑሮ በመኖር ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ በዚያው ሞተዋል አሉኝ። በማግሥቱ ጥዋት የቅዱስ የሮኒሞስን የቅዱስ ፍራንሲስኮንና የቅዱስ ዶሚንጎስን የቅዱስ ቂርቆስንና የጳጳስ ሌዎንን ገድል እንዳሰማው ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዙኝ መሆኑን ነግረውኝ ተለያየን።

ምዕራፍ ሰማንያ አምስት፤ የተጠቀሱት ቅዱሳን ገድል ለንጉሠ ነገሥቱ መተርጎም፤ የኛን ቅዳሴ ስለመውደዳቸው፤ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበን ስለመሸለማችን።

በማግሥቱ ሐሙስ በወሩ 21ኛ ቀን ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮ እላይ የተጠቀሱትን ቅዱሳን ገድል ምልክት በማድረግ «ፍሎስ ሳንቶሩም» የተባለውን መጽሐፌን እንድልክለት ጠየቀ። የቅዱሳኑን ገድል ምልክት በማድረግ መጽሐፉን ልኬላቸው ወዲያውኑ ይህንኑ ይዘው ሁለት መነኩሴዎች መጡ። በያንዳንዱ ስዕል ራስጌ የያንዳንዱን ቅዱስ ስም በቋንቋቸው እንዲጽፉለትና የክርስቶስ ሕማማት በየትና በንዴት ያለ አኳኋን እንደተፈጸመ እንዲጻፍለት ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዘ መሆኑን መነኩሴዎቹ ነገሩን። መነኩሴዎቹ

መጽሐፉን ከወሰዱት በኋላ እንደገና መልሰውት መጥተው በፍሎስ ሳንቶሩሙ ላይ የሚገኙት ቅዱሳን ሁሉ ከየት እንደነበሩና በየት እንደተሰቃዩ ምን ዓይነት ኑሮም እንደኖሩ በመግለጽ ገድላቸውን በሙሉ እንድጽፍለት ያዘዘ መሆኑን ነግረውኝ ስለቅዱሳኑ የታዘዘውን በመፈጸም ከየት እንደነበሩና በየት እንደተወለዱ በየት እንደሞቱና ሌላም ሃተታ ጭምር አወጣን።

ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ቅዱሳን ገድል አስተዋጽኦ እንድናዘጋጅ በማግሥቱ አርብ የተባሉት መነኩሴዎች መጽሐፉን ይዘው መጡ። ከኛ ቋንቋ ወደነርሱ መተርጎሙ በጣም አስቸጋሪ ነገር በመሆኑ ይህን አስተዋጽኦ ማዘጋጀቱ ብዙ ቀን ፈጀብን። የኛን ፍሎስ ሳንቶሩም በመሰለ የቅዱሳን ዝርዝር ይዞ በሚገኘው በነርሱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ሌሎቹን ቅዱሳን ገድልም አመዛዘንን። በነርሱ መጽሐፍት ከሚገኙት ቅዱሳን ውስጥ የቅዱስ ሰባስጥያኖስን፤ የቅዱስ እንጦንዮስንና የቅዱስ በረላምን ገድል አመዛዘንን። በመጽሐፋቸው ላይ የዚህ በመጨረሻ የተጠቀሰው ጻድቅ ገድል ቢገኝም የሚከበርበትን ቀን ስለማያውቁት ይህንኑ እንድነግራቸው አጥብቀው ለመኑኝ። የተጠየቀውን ማስረጃ በማናቸውም የቀን መቁጠርያ ስላላገኘሁት አዝኜ ነበር፤ ነገር ግን ወዲያው ባንድ የስንክሳር መጽሐፍ ውስጥ ስላገኘሁት ነገርኳቸው። እነርሱም በቶሎ ጽፈውት እንዲከበር አዘዙ። ያንዳንድ ጻድቃን ቀን የሚከበርበትን ስለሚጠይቁኝና ለጥያቄአቸውም በቶሎ መልስ እንድሰጣቸው ይፈልጉ ስለነበር የቀን መቁጠርያ መጽሐፉን ሳልይዝ መሄድ አልደፍርም ነበር።

ቅዳሜና እሁድ በበዓልም ቀን በዜማ የምናደርሰውን ቅዳሴ ይሰሙ ዘንድ አንዳንድ ደብተራዎችና በቤተ መንግሥቱም የሚገኙ ቄሶች የቅድስት ከተሪና በዓል በሚከበርበት እሁድ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ ላካቸው። ቅዳሴው ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ በዚያ ሆነው ያስቀደሱት እነዚህ ካህናት በጣም ከመደሰታቸው የተነሣ ይህ የሰማነው ቅዳሴ የመላእክት ቅዳሴ እንጂ የሰውስ አይደለም ሲሉ አድናቆታቸውን የገለጹ መሆናቸውን አስተርጓሚው ነገረን። ከነዚህ ሰዎች ሌላ በዚያ ተገኝቶ ያስቀደሰ በአገሩ ከአርባ ዓመት በለይ

የኖረ የሕዝቡን ቋንቋ አቀላጥፎ የሚያውቅ የትውልድ አገሩ ቬኔዚያ የነበረ ብራንካ ሌዎኔ የተባለ ሰአሊ ነበር። ምንም እንኳ ሰአሊ ቢሆንም እጅግ የተከበረና ትልቅ ሰው ነበር። ይህ ሰው ለካህናቱ የኛን ቅዳሴ (ማለት ክሪዎሽን፤ ግሎርያን፤ ዶሚኖስ ቮቢስኩምን) ይተረጉምላቸው ነበር። በነርሱም ቋንቋ ሲተረጎም «ሰላም ለኩልክሙ» ይሆናል። እንዲሁም ከሐዋርያት መልክትና ከወንጌሎቹም የተነበበውን ጥቅስና ማናቸውንም ነገር ተረጎመላቸው። ብራንካ ሌዎኔ ወደዚህ አገር ከመምጣቱ በፊት መነኩሴ ነበር ይባላል። እነዚህ ካህናት ቅዳሴውን በጣም ስለወደዱት እንደዚህ ደስ የሚያሰኝ ይሆናል ስንል ተስፋ አለደረግንም ነበር እያሉ ወሬውን በከተማው ውስጥ በሰፊው ይነዙት ነበር፤ ይሁን እንጂ የቅዳሴው ስነ ሥርዐት ባንድ ቄስ ብቻ መከናወኑንና በዚያም ለነበሩት ምዕመናን ሁሉ ቁርባን አለመስጠቱን መንቀፋቸውን አልተውም። እኔም ከዚህ በፊት በሌላ ምዕራፍ ላይ የሰጠሁን መልስ ሰጥቼ በመልሱ የተደሰቱ መስሎኛል፤ ከዚህ ጊዜ በኋላ ብዙ ሰዎች ወደኛ ቅዳሴ ይመጡ ነበር።

የዚያኑ ዕለት እሁድ ንጉሠ ነገሥቱ ለአምባሳደሩ አንድ መልካም ፈረስ ላከለት፤ ከኛ ሰዎችም አንዳንዶቹ ቅር የተሰኙ ይመስል አጉረመረሙ። እንዲሁም የዚያኑ እሁድ ዕለት ማታ ከተኛን በኋላ መልዕክተኛ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ ጠርቶአችኋል አለን። ከዚህ በፊት የገለጽሁትን ስነ ሥርዐት ፈጽመን በቤተ መንግሥቱ ገብተን በመጀመርያው መጋረጃ አጠገብ እንደደረስን እጅግ የተጌጡ ልብሶች ሸለሙን። አምባሳደሩን በተለይ ከመጋረጃው ውስጥ እንዲገባ ጠይቀውት ለርሱም ልብስ ሰጡት። በዚህ አኳኋን ሁላችንም ከለበስን በኋላ በፊት ባየነው አኳኋን በመደብ ላይ ተቀምጦ በነበረው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት አቀረቡን። በዚያን ጊዜና ቦታ ብዙ ውሳኔዎች ተሰጡ፤ ከነዚሁም አንዱ ሌሎቹ ፈረንጆች ሁሉ አምባሳደሩና ጭፍሮቹም ወዳገራቸው ሊመለሱ መቻላቸው ተፈቅዶ በአገሩ ውስጥ ይገኙ ከነበሩት ፈረንጆች አንዱ ኒኮላዎ ሙትዛ የተባለሙ ብቻ እንዲቀር መወሰኑ ነው። ይህ ሰው እንዲቀር የተወሰነበት ምክንያት አንድ ደብዳቤ በወርቅ ቀለም እንዲጽፍ ስለሆነ ጽሕፈቱ ብዙ ጊዜ ስለሚፈጅ አምባሳደሩ መንገዱን እንዲቀጥልና ደብዳቤዎቹን የተባለው ፈረንጅ

እመንገድ ድረስ የሚያመጣለት መሆኑ ተነገረን። አምባሳደሩም ደብዳቤውን ሳይዝ የሄደ እንደሆነ ስለንጉሠ ነገሥቱ መልካም ዜና ሊሰጥ የማይችል መሆኑን በማስረዳት ግርማዊነትዎ እስከፈቀደበት ጊዜ ድረስ ቆይቼ ደብዳቤውን ይዤ ለመሄድ እመርጣለሁ፤ የሆነ ሆኖ ጠቅላይ ገዥውን ይዘው የሚመጡት መርከቦች በምጽዋ ላይ እንዳሉ ሳያመልጡኝ ላገኛቸው እንድችል በቶሎ እንዲያሰናብቱኝ እለምናለሁ ሲል መለሰ። ንጉሠ ነገሥቱም በራሱ ቃል መልስ በመስጠት የተደሰተ መሆኑን ገልጾ አምባሳደሩ በአዛዥነት በምጽዋ ለመቆየት ይፈቅድ እንደሆነ ጠየቀው። አምባሳደሩም መልሶ ምንም እንኳ ዋናው ምኞቴ ጌታዬን የፖርቱጋልን ንጉሥ ማየት ቢሆንም ግርማዊነትዎ የሚያዘውን ማናቸውንም ነገር መፈጸምን ንጉሡና ጠቅላይ ገዥው ለነርሱ የተደረገ አገልግሎት አድርገው ስለሚቀጥሩት እርስዎ የሚያዙኝን በደስታ እፈጽማለሁ አለ። ከዚህ በኋላ ተሰናብተን ወደ ድንኳናችን ሄድን።

ምዕራፍ ሰማንያ ስድስት፤ ንጉሠ ነገሥቱ በድንገት ወደሌላ ቦታ ስለመሄዱ፤ ስለአምባሳደሩ ዕቃ አነሣሥ፤ በመካከላችን ስለተነሣ አለመግባባት፤ ንጉሠ ነገሥቱ ስለላከው ጎብኝ።

ሰኞ ጥዋት በወሩ 25ኛ ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ከከተማው የሄደ መሆኑን ነገሩን። ሁለት ብላቴኖች ብቻ አስከትሎ በፈረስ ተቀምጦ በኛ ድንኳን አጠገብ አለፈ። ይህ መሆኑ በታወቀ ጊዜ «ንጉሡ ሄዱ፤ ንጉሡ ሄዱ» የሚል ድምጽ በከተማው በመላ ተሰምቶ እያንዳንዱ ሰው በተቻለ ፍጥነት ለመከተል ወጣ። ንጉሠ ነገሥቱ ከመሄዱ በፊት ዱቄትና ጠጅ የምንጭንባቸው ሃምሳ አጋሰሶች አዞልን ነበር፤ ነገር ግን ለዚህ አገልግሎት ስላሳ አምስት አጋሰሶች ብቻ ሰጥተውን ከነዚህም ውስጥ አስራ አምስቱ ለዕቃችን ማጓጓዣ ነበሩ። ከአስራ አምስቱ አጋሰሶችና እንዲያግዙን ከታዘዙልን ሰዎች አምባሳደሩ ሁሉም የኔ ናቸው ሲል የሚያስፈ

ልገውን ያህል ወሰደ። አዛዥ ሩፋኤል የተባለ አንድ የተከበረ ቄስና አንድ ሌላ ባለሥልጣን ባልደረቦቻችን እንዲሆኑን ታዘዙልን። በየቀኑ ሁለት ፍሪዳ የታዘዘልን መሆኑን ነገሩን።

ማክሰኞ ዕለት ጉዞአችንን ጀምረን ንጉሠ ነገሥቱ የሄደበትን ተከትለን አራት ሌግዋ ያህል የሚሆን መንገድ ከተጓዝን በኋላም ንጉሠ ነገሥቱን ልንደርስበት አልቻልንም። ረቡእ ዕለትም ከተጓዝን በኋላ በቤተ መንግሥቱ ደርሰን የንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ከተተከለበት ግማሽ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ባንድ ወንዝ አጠገብ በነበረ በንድ ትልቅ ሜዳ ላይ ሠፈርን። እኛ ወዳረፍንበት ቦታ ከቤተ መንግሥቱ ሁለቱ ካህናት አንዱ የነበረው እጅግ የተከበረውና የቤተ ክርስቲያን ጸሐፊች አለቃ የሆነው የአክሱም ንብረ እድ መጣ። ይህ ሰው የንጉሠ ነገሥቱን ጥያቄ ይዞ በመምጣት ወደዚህ ቦታ እንዴት እንደመጣን እንዴትስ እንደምንሄድ እንዲሁም ያዘዘልን ሁሉ ደርሶን እንደሆን ጠየቀን። አምባሳደሩም መልስ በመስጠት ግርማዊነታቸው ሰው ልከው ስላስጎበኙን እጃቸውን እስማለሁ፤ ከታዘዘልንም አንድ ነገረ እንኳ ሳይጎድልብን በሙሉ ደርሶናል አለና ለንብረ እዱ ገለጸለት። የዚያን ጊዜ ከኛ ሰዎች አንዱ ጊዮርጊስ ዲ አብሬው በድንገት መልስ በመስጠት «ይህን መልእክት እንዳያደርሱ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዙልንን አጋሰሶች በሙሉ በመስጠት ፈንታ ጥቂቶቹን ማለት የተጎሳቆሉና የታወሩትን መርጠው ከማይረቡ የሸመገሉ ረዳት ሰዎች ጋር አድርገው ነው የሰጡን። እነዚህንም ለሌላ ሰው አንድ እንኳ ሳይተው አምባሳደሩ በሙሉ ራሱ ወሰዳቸው» ሲል ለንብረ እዱ ነገረው። አምባሳደሩም የመጀመርያውን ቃሉን በማጥበቅ አጋሰሶቹም ሆኑ ረዳቶቹም ምንም ጉድለት አልነበረባቸውም በማለት ንብረ እዱ ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲነግረው ለመነው። የዚህን ጊዜ ጊዮርጊስ ዲ አብሬው ወደ አምባሳደሩ ዞር ብሎ «በእውነት አንተ እንዳልከው ምንም ጉድለት የሌለባቸው አጋሰሶችና ረዳቶችም ተሰጥተውን እንደሆነ ላንተ ብቻ ይሆናል እንጂ ለኛ ግን እንደዚህ ያለ ነገር ከቶ አልደረሰንም። ስለዚህ ይህን የመሰለ ጉዳይ ለወደፊቱ መቀጠል የለበትም።» ሲል ገላመጠው። ጊዮርጊስ ዲ አብሬው ይህን የመሰለ የዘለፋ ቃል የሚያወርደው በንብረ እዱ ፊት ሲሆን አምባሳደሩ ነገሩን በትዕግሥት ከማሳለፉ

በላይ ጊዩርጊስ ዲ አብሬውን እንዲህ አለው። «ጊዩርጊስ፤ እባክህ ስለእግዚአብሔር ስትል ይህን ሰው ማስቸገራችንን እንተውና ጉዞአችንን ለመቀጠል እንዘጋጅ፤ በቂ በቅሎዎች አሉን፤ ጥቂት ተሰጥተውናል፤ የሚያንሱንም ከሆኑ ይጨመሩልናል»። ምንም እንኳ አምባሳደሩ ይህን ልመና ቢያቀርብም አተካራው እየተፋፋመ ሄዶ ጦርና ጎራዴ ተማዘው ግብ ግብ ሲገጥሙ እኔም ሁኔታው አጉል ነገር ስለመሰለኝ በመካከላቸው ጥልቅ ብዬ መቋሚያዬን ወዲያና ወዲህ በማወዛወዝ መገላገል ጀምርሁ። ምንም እንኳ እንዳጀማመራቸው መዋጋትና መማታት ባይቀርም ጊዩርጊስ ዲ አብሬው ብቻ ሲቆስል ከሁለቱም ወገን ሌላ የተጎዳ ሰው አልነበረም። ጊዩርጊስ ዲ አብሬውና ሎፑ ደ ጋማ ወጥተው ሲሄዱ የተቀሩት በዚያው ቀሩ።

ምዕራፍ ሰማንያ ሰባት፤ የፖርቱጌዞቹን መጣላት በመስማት ይታረቁ ዘንድ ንጉሠ ነገሥቱ ስለመለመኑ፤ በከተማው የትግል ውድድር ስለመደረጉ፤ በዚያ ቦታ ስለማጥመቃችንና ስለሌሎችም ጉዳዮች።

በሁለቱ ሰዎች መካከል ተነሥቶ የነበረውን ጸብ አይቶ የነበረው ንብረ እዱ ጉዳዩን ለንጉሠ ነገሥቱ ነግሮት ስለነበር አርብ ጥዋት መልእክት መጥቶ ቀጥሎ የተመለከተውን ንጉሣዊ መልእክት ነገረን። ዕቃችሁን ያነሡላችሁ ዘንድ ያዘዝሁላችሁ አጋሰሶችና ሰዎች እንዲመራችሁ ለታዘዘው ለአንድ አዝማች እንጂ በቀጥታ ለናንተ እንዲሰጡ አላዘዝሁም፤ ይህ ሰው የታዘዘውስ ከብቶቹንና ሰዎቹን በሃላፊነት ተቀብሎ ጓዙን እንዲያስጭን ነበር። እናንተም ነጋዴ ይመስል ዕቃ መጫንና ማራገፍ መሸከምና ማሸከም የማይገባችሁ መሆኑን አውቃለሁ፤ ለታዘዘው ሰው ከብቶቹና ሰዎቹ እንደደረሱ እናንተ መጓዝ ብቻ ነው ያለባችሁ። አዝማቹ ማናቸውንም ነገር ያከናውናል። ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዘውን አጋሰሶችና ሰዎች በቶሎ አምጥተው ለአዝማቹ አስረከቡት።

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶን ወዲያውኑ ቀርበን በመልእክተኛ አማካይነት ከእልፍኝ የመጣልን የመጀመርያው ጥያቄ ለምንድን ነው የተጣላችሁት የሚል ነበር። ከጥያቄም ጋር እንድንታረቅ በመለመን ላከብን። አምባሳደሩም መልሶ እነዚህ ሁለት ሰዎች ማለት ሎፑ ደ ጋማና ጊዩርጊስ ዲ አብሬው እርሱንና የተላኩበትን የፖርቱጋል ንጉሥ ሥራንም መቃወማቸው ይህ የመጀመርያ ጊዜ ስላይደለ ከድንኳኑና ከጭፍሮቹም እንዲርቁለት ንጉሠ ነገሥቱ ያዝለት ዘንድ ለመነው። ይህም መልእክት ከደረሰ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ መልሶ ሊያስታርቅ ቢሞክርም አምባሳደሩ ከዚህ በፊት ያልገለጻቸውን ጉዳዮች ሁሉ በመዘርዘር በፍጹም ለመታረቅ የማይፈልግ መሆኑን ለመልእክተኛው ነገረው። ይህን መልእክት በምንለዋወጥበት ጊዜ ለምለም ሣር መስክ ላይ እንድንቀመጥ ታዘዝን። በዚያ ቦታ ከአስር ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ድረስ ተቀምጠን ስለነበርን በሙቀት ተቀምጠን በብርድ ተነሣን። ጊዮርጊስ ዲ አብሬውና ሎፑ ደ ጋማም ወደዚያው ቦታ ተጠርተው መጡ።

በዚያ እንደተቀመጥንም መልእክት መለዋወጥ ጀመርን። የተቀመጥነው ተራርቀን ስለነበርን የተለዋወጥናቸው ቃላት ምን እንደሆኑ አላወቅሁም። ሳንበላ በዚያ ቦታ ቀንና ማታ በብርድ ውስጥ መቀመጥ ከባድ ነገር በመሆኑ ለመሄድ እንዲፈቀድልን አምባሳደሩ መልእክት ላከ። ከዚህ በኋላ ተፈቅዶልን እኛም ወደድንኳናችን ስንሄድ ጊዮርጊስ ዲ አብሬውና ሎፑ ደ ጋማ ወደታላቁ ቢትወደድ ቤት እንዲሄዱ ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ወዲያውኑ መልእክተኛ መጥቶ ሁለቱን ወገኖች ለማስማማት ሲል በዚያ ቦታ ያቆያቸው ቅር ለማሰኘት ሳይሆን ለማስደሰትና በሰላም ሊልከው በመፈለግ በመሆኑ አምባሳደሩ እንዳይቀየም በመጠየቅ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ላከ። እንዲሁም የትግል ውድድር ለማድረግ ፈልጎ ለዚሁ ተካፋዮች የሚሆኑ ሰዎች ከኛ ዘንድ ጠየቀ። ነገር ግን መሽቶ ስለነበር አምባሳደሩ ይቅርታ ጠይቆ ቀረ። እድንኳናችን ድረስ ብዙ እንጀራና ጠጅ ተልኮልን በዚያ መስክ ላይ ብዙ ጊዜ በመቆየታችን ቅር እንዳይለን በተጨማሪ ለመኑን።

እሁድ ታህሣሥ 2 ቀን 1520 ዓም ከቀትር በኋላ የትግሉ ውድድር ተጀምሮ ከኛ ሰዎች አንዱ አልአዛር ዲ አንድራድ የተበለው ሰአሊ በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን አጠገብ ይገኝ ስለነበር በትግሉ እንዲገባ ተጠየቀ። ትግሉን እንደጀመሩ አፍታ እንኳን ሳያቆዩ ቅልጥሙን ሰብረው ለቀቁት። ከዚህ በኋላ የወርቅዘቦ ልብስ ሸልመውት አራት ሰዎች ተሸክመውት ወደኛ ድንኳን አመጡት።

በማግሥቱ ሰኞ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አምባሳደሩ መልእክተኛ ልከ ሌሎች ታጋዮች እንዲላኩ ጠየቀ። ስለዚህ አምባሳደሩ የተሰበረውን የአልአዛር ዲ አንድራድን ቂጭት ለመወጣት ሲል ሁለት ምርጥ ታጋዮች ማለት እስጢፋኖስ ፓልያርት የተባለውን አሽከሩንና አይርሽ የተባለ የኤምባሲውን ጸሐፊ እንዲታገሉ ላካቸው። ሁለቱም ወደ ትግሉ ሄደው መጀመርያ አይርሽ ገጠመ፤ ነገር ግን እርሱንም አፍታ ሳያቆዩ ክንዱን ቀልጥመው ስለጣሉት ክንዱን አንከርፍፎ ወደ ድንኳኑ መጣ። የጓደኛውን መሰበር የተመለከተው እስጢፋኖስ ፓልያርትም ሁኔታው የሚያሰጋ ስለሆነበት ሳይገጥም ፈርቶ ተወው። የኛን ሰዎች ክንድና ቅልጥም የሰበረ ታጋይ በፊት እስላም የነበረ ገብረ ማርያም የተባለ ሰፊ ትከሻ የነበረው ጡንቸኛ የንጉሠ ነገሥቱ አሽከር ነው። አሁን በቤተ መንግሥቱ በወርቅ ሠሪነትና በጠላፊነት ያገለግላል።

በጦርነት ላይ ከሚገኘው ቢትወደድ የዚያን ዕለት መልእክት መጥቶ ጠላት ፍጹም ድል የተነሣ መሆኑንና ብዙ ምርኮ ማለት ወርቅና ባርያ እንዲሁም ከጠላት በኩል የተገደሉትን ታላላቅ ሰዎች ጭንቅላት ቢትወደዱ የላከ መሆኑን ገለጸ።

እኛ በዚያ ከተማ በቆየንበት ጊዜ እዚያ ካገኘናቸው ፈረንጆች ውስጥ አንዱ ጴጥሮስ ኮርዲዬሩ የተባለው የጄኖቫ ተወላጅ ሚስቱ ወልዳ ሕጻኑ ስምንት ቀን ሆኖት ስለነበር እንዳጠምቅለት ለመነኝ፤ ነገር ግን ሕፃኑ የተወለደው በዚህ አገርና በቤተ መንግሥቱ ስለሆነ ይልቁንም ወንድ ልጅ አርባ ቀን ሳይሞላው ማጥመቅ የተለመደ ስላይደለ ከንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ሳላገኝ ሕፃኑን ላጠምቀው አልፈ

ቀድሁም። ከዚህ በፊት ያጠመቅሁ መሆኔ የታወቀ ቢሆንም ያጠመቅሁት ያስርና ያስራ አንድ ዓመት ዕድሜ የነበራቸውን የኛን አሽከሮች ነበር። ስለዚህ ጉዳዩን ለንጉሠ ነገሥቱ ለማቅረብ እኔው ራሴ ሄጄ በኛ ስነ ሥርዐት እንዳጠምቅ ስልተጠየቅሁ መልከም ፈቃድዎ ሆኖ እንዲፈቅዱልኝ እለምናለሁ ስል መልእክተኛ ላክሁበት። ወዲያውኑ መልእክተኛው መጥቶ እንዳጠምቅና ቁርባንም በፈረንጅ አገርና ልክ በሮም ቤተክርስቲያን ሥርዐት እንዳከናውን የተፈቀደልኝ መሆኑንና ከዚም በላይ በጥምቀቱ ሊገኙ የሚሹትን ሰዎች ሁሉ እንድፈቅድላቸው የታዘዝሁ መሆኔንም ገለጸለኝ። ቅበአኑግም እንዲሰጠኝ ታዘዘልኝ። ሕፃኑ በተጠመቀበት ቀን ማለት ታህሣሥ 10 ቀን በቤተ መንግሥቱ ከሚገኙት ታላላቅ መኳንንት ብዙዎቹ ተገኝተው ነበር። ሕፃኑ በተጠመቀ ጊዜ በአገሩ ልምድ መስቀል ተይዞ ጥምቀቱንም በተቻለ መጠን በቀስታ አደረግሁት። በዚያ የነበሩት አስተርጓሚዎችና ፈረንጆችም እንደነገሩን እኛም በሁኔታቸው በተረዳነው መሠረት ከቤተ መንግሥቱ የመጡ መኳንንት በጣም ከመገረማቸው በላይ ይህን የመሰለውን የቁርባን ስነ ሥርዐት እግዚአብሔር ራሱ ያዘዘው ነው ሲሉ ስሜታቸውን ገልጸው መልካም ምግብ የበሉ ይመስል ተደስተው ሄዱ። የኛ የቅዳሴ ስነ ሥርዐትና ጥምቀት የተከናወነው በዝግታ በመሆኑ በጣም ወደውት ከነርሱ ስነ ሥርዐት ይልቅ የኛ የተሙዋላ መሆኑን መሰከሩ።

ምዕራፍ ሰማንያ ስምንት፤ ንጉሠ ነገሥቱን የሚያጅቡት ፈረሰኞችና እግረኞች

ከዚህ ቦታ ተነሥተን በመጣንበት መንገድ ወደኋላ ተመለስን። የንጉሠ ነገሥቱን አጀብ ብዛት ለማመን አስቸጋሪ ነው። ድንኳናቸውን ነቅለው ከሚሄዱበት ቦታ ጀምሮ ሶስት ወይም አራት ሌግዋ ያህል ጥቅ ጥቅ ብለው በሕማማት ጊዜ የክርስቶስን አካል ምስል ተከትለው የሚሄዱ ሰዎችን ይመስላሉ። ከአጀቡ አንድ አስረኛው

በአለባበሱና በሁኔታው ነቃ ያለ ሲሆን ዘጠኝ አስረኛው ግን ወንዶችና ሴቶች፤ ወጣቶችና ድሆች፤ አንዳንዶቹም ቆዳ ሌሎቹም ጨርቅ የለበሱ ተራ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ተራ ሰዎች ከእንሥራና ከዋንጫ በስተቀር ሌላ ዕቃ ስለሌላቸው ይህንኑ ተሸክመው ሲጓዙ ይታያሉ። እነዚህ ድሆች ጉዞው አጭር ከሆነ ጉጆአቸውን ነቅለው እንደተከደነ ተሸክመውት ይሄዳሉ። ሩቅ ከሆነ ግን እንጨቱን ብቻ ተሸክመው ይወስዱታል። ሃብታም ሰዎች ግን ማለፊያ ድንኳኖች አሉዋቸው። ታላላቆቹ መሳፍንትና መኳንንት ግን እያንዳንዳቸው አንድ ቦታ ከትሞ ለመቀመጥ የሚያበቃ ድንኳኖች፤ ጭነቶች፤ ቁጥራቸው የበዛ ሰዎችና አጋሰሶች አስከትለው ስለሚሄዱ ስለነርሱ አልገረምም። በእግራቸው ስለሚጓዙት ደግሞ ከብዛታቸው የተነሣ ምን እንደምል አላውቅም። እኛ ፖርቱጊዞቹና ፈረንጆቹም ስለበቅሎቹ ብዛት ስንነጋገር በክረምቱ ወራት ታላላቆቹ መኳንንት ወደየርስታቸው በሚሄዱበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ በትንሹ ሃምሳ ሺ በቅሎች ከሌሉ በስተቀር ሊንቀሳቀስ አይችልም ማለትን ሰምተናል። አንዳንድ ጊዜም እስከ መቶ ሺ ይደርሳሉ ይባላል። ፈረሶች ብዙ አይደሉም፤ ከበቅሎች ቁጥር ውስጥ የማይገቡ አጋሰሶች ደግሞ ብዛታቸው ከበቅሎቹ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ይበልጣል። ጥሩና በጣም ማለፊያ የሆኑ ጥርኞች ቢኖሩም መጫሚያ ስለሌላቸው በቶሎ ደክመው ስለሚወድቁ ተቀምጠውባቸው አይጓዙም። ስለዚህ የፈረሶቹ ቁጥር በጣም ጥቂት ስለሆነ ብዙ ልናትተው አይገባም። ንጉሠ ነገሥቱ ወደሩቅ ቦታ በሄደ ቁጥር የደከሙትን ፈረሶች መንደር ሞልተው ይተዋቸውና በኋላ ቀስ ብለው ይወስዱዋቸዋል። የአጋሰሶቹ ብዛት ቁጥር የለውም፤ ወንድና ሴት በቅሎዎች በኮርቻ ይጫናሉ። የኮርቻ በቅሎች ለኮርቻ ብቻ አጋሰሶችም ለጭነት ብቻ እንጂ አንድ በቅሎ ለሁለት አገልግሎት አይውልም። ለጭነት የሚያገለግሉ ብዙ መጋዣዎች አሉ። ነገር ግን እነዚህም እንደፈረሶቹ ይደክማሉ። ይሁን እንጂ ከነዚህ ሁሉ በበለጠ የሚያገለግሉ በብዛት የሚገኙት አህዮችና የጭነት በሮች ናቸው። በቆላው ደግሞ ብዙ ግመሎች አሉ።

<u>ምዕራፍ ሰማንያ ዘጠኝ፤ የቤተ መንግሥቱ ቤተ ክርስቲያኖች፤ የጉዞአቸው አኳኋን፤ ለታቦት ያላቸው አክብሮት፤ ንጉሠ ነገሥቱ በያመቱ ለሕዝቡ ስለመታየቱ።</u>

ንጉሠ ነገሥቱ በጉዞው ላይ ቀጥተኛ መንገድ ተከትሎ የሚሄደው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ እንዲያውም የሚሄድበትን ቦታ የሚያውቅ ሰው የለም። ተከትሎ የሚሄደው አጀብ ነጫጭ ድንኳን ተተክሎ እስኪያገኝ ድረብ ይጓዝና በዚያ ሲደርስ እያንዳንዱ ሰው ቦታውን ይዞ ይሠፍራል። ንጉሠ ነገሥቱ አብዛኛውን ጊዜ በየቦታው በሚገኙ ገዳሞች ውስጥ እየገባ ያድራል። በከተማው ውስጥ ከበሮ እየተመታ ይዘፈናል፤ ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ በሚገኝበት ጊዜ የሚዘፈነውን ያህል አይደምቅም። ከአጀቡ ጋር ሁልጊዜ የሚጓዙ አስራ ሶስት ታቦቶች አሉ፤ ምንም እንኳ ንጉሠ ነገሥቱ ከጎዳናው እየወጣ ባቋራጭ ቢሄድም ታቦቶቹን የተሸከሙት ሰዎች ሁል ጊዜ አውራ ጎዳናውን እየተከተሉ ነው የሚሄዱት። ታቦቶቹ የሚጓዙት በታላቅ ክብር ሲሆን የሚሸከሙዋቸውም ሰሞነኛ ቄሶች ናቸው። ከያንዳንዱ ታቦት ጋር አራት ቄሶች ይሄዳሉ፤ እንዲሁም ሌሎች አራት ቄሶች ተራ ለመግባት ይከተላሉ። ታቦቶቹን ቃሬዛ በመሰለ ነገር ላይ አስቀምጠው ባማረ የወርቀ ዘቦና ግምጃ ሸፍነው ተሸክመው ያጉዙዋቸዋል። ባንድነት ታጅበው ከሚሄዱት ከያንዳንዱ ታቦት ጋር ሁለት ዲያቆኖች እየሄዱ አንዱ ጽናና መስቀል ሲይዝ ሌላው ምርዋ እየመታ ይሄዳል። በመንገድ ላይ የሚሄዱት ወንዶችና ሴቶች ሁሉ የምርዋውን ድምጽ በመስማት የታቦቱን መምጣት ሲረዱ መንገዱን በቶሎ ለታቦቱ ለቀው ገለል ይላሉ፤ በቅሎኛውም ከበቅሎው ወርዶ መንገዱን ለታቦቱ ይለቃል። ንጉሠ ነገሥቱ በተጓዘ ቁጥር ከፊት ቀድመው በሁለት ሰንሰለት ማለት ከኋላና ከፊት ታስረው አውራ መንገዱን ተከትለው የሚሄዱ አራት አንበሶች አሉ። ለነዚህም ሰዉ መንገድ ይለቃል፤ ሕዝቡ ለነዚህ መነገድ መልቀቁ ለአክብሮት ሳይሆን ግድ ስለሆነበት ነው።

በያለበት እያረፍን መንገዳችንን ቀጥለን ስንመጣ ባለፍነው በሮች ባሉበት ደረቅ ወንዝ ታህሣሥ 20 ቀን ደረስን። በዚያ ቦታ

ባንድ ትልቅ ሜዳ ላይ ሠፍረን ድንኳኖችም ከተተከሉ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ለልደት በዓል ሕዝቡን እየተቀበለ እጅ ለማስነሳት የሚቀመጥበት አንድ መደብ መሠራት ተጀመረ። ንጉሠ ነገሥቱ አብዛኛውን በዓመት ሶስት ጊዜ ማለት ለልደት በዓል፤ ለፋሲከና ለመስቀል ሕዝቡን እየተቀበለ እጅ ያስነሳል። በዓመት ሶስት ጊዜ በዚህ አኳኋን ሕዝቡን እየተቀበለ እጅ እንዲያስነሳ የተወሰነበት ምክንያት አያቴ እስከንድር ከሞተ በኋላ አሽከሮቹ ሬሳውን በመደበቅ ሶስት ዓመት አገሩን ገዝተው ነበር ይባላል፤ ይህ እስከተፈጸመበት ጊዜ ድረስ ካንዳንድ የእልፍኝ አሽከሮች በስተቀር ንጉሠ ነገሥቱን ማንም አላየውም ነበር ይባላል። ስለዚህ በሕዝቡ ጥያቄ የአጼ ዳዊት አባት በዓመት ሶስት ጊዜ ለመታየት ወስኖ ስለነበር ልጁም ይህንኑ ተከተለ። ወደፊት በሰፊው እንደምገልጸው ወደጦርነት በሄደ ጊዜ በግልጽ ሰው ሁሉ እያየው ነው።

ምዕራፍ ዘጠና፤ የልደት በዓል ዕለት የበዓሉን ቅዳሴ እንዳሰማው ንጉሠ ነገሥቱ እኔን ስለማስጠራቱ፤ ስለኑዛዜና ቁርባን።

ከንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ጥቂት እልፍ ብለን በተከልነው ድንኳናችን አጠገብ በሚገኘው ጸሎት ቤታችን በየቀኑ ቅዳሴ እናስታጉልም ነበር። የልደት በዓል ዋዜማ ዕለት ከእኩለ ቀን በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶኝ በማግሥቱ ጥዋት ምን ዓይነት በዓል እንደምናከብር ጠይቆኝ የክርስቶስን የልደት በዓል የምናከብር መሆናችንን ነገርሁት። እንዲሁም እንዴት ባለ ስነሥርዐት እንደምንፈጽም ጠይቆኝ በሙሉ በማስረዳት ሶስት ጊዜ የምንቀድስ መሆናችንን ነገርሁት። እርሱም መልሶ እናንተ ሶስት ጊዜ ከማስቀደሳችሁ በስተቀር በማናቸውም ነገር እንስማማለን ብሎኝ ከሶስቱ ቅዳሴዎች አንዱን መርጦ በተለይ ለርሱ እንዳሰማው ጠየቀኝ። እኔም መልሼ ግርማዊነትዎ የመረጠውን ላሰማዎ ዝግጁ ነኝ ብዬው የሶስት ሰዓቱን ቅዳሴ በተለይ ስለሚወድ ይህንኑ እንዳሰማውና ሥርዐቱንም

በፊት በምናደርገው አኳኋን እንድንፈጽም አዘዘ። ቅዳሴአችንን የምናከናውንበት ድንኳን ከነበረበት ቦታ ተነቅሎ በርሱው አጠገብ እንዲተከል አዘዘ። በንጉሣዊው ድንኳን አጠገብ የነበሩ ሁለት ድንኳኖች ተነቅለው በነሱ ቦታ በዋናው በር ፊት ለፊት የኛ ድንኳን ተተከለ። የኛ የቅዳሴ ስነ ሥርዐት ልክ ባገራችን በምናደርገው አኳኋን እንዲከናወንና እርሱም ሊያዳምጠን በአገሩ ቤተ ክርስቲያን ደንብ መሠረት በዶሮ ጩኸት ቅዳሴ እንገባ ዘንድ ሊያስጠራን ተወሰነ።

ድንኳናችን እንደተተከለ ወዲያውኑ ቀደስንበት፤ ንጉሠ ነገሥቱም ከድንኳኑ ውስጥ ሆኖ ያዳምጥ ነበር፤ አዳመጠ ማለቴ ከፍ ብዬ እንደ ገለጽሁት ድንኳናችን ከርሱው አጠገብ ስለነበር በውስጡ ሆኖ ስላየነው ነው። ከዚህ በኋላ ወደ ድንኳናችን ሄደን ልክ ዶሮ ሲጮህ አስጠርቶን ስለ ቤተ ክርስቲያንና ዜማ ደህና አድርገን የምናውቅ ከኔ ጋር ሰባት ሰዎች ማለት የቪላ ሬያል መስፍን አሽከር የነበረው ኦርጋን መቺ አማኑኤል ድ ማርሽ፤ የሊዝቦን ተወላጅ ሰአሊ አልአዛር ዲ አንድራድ፤ የኤምባሲው ጸሐፊ ዮሐንስ ኢሽኮላር፤ መምሕር ዮሐንስ፤ የካታሎኒያ ተወላጅ ኒኮላዎ፤ መምሕር ጴጥሮስ የተባለ አንድ የጄኖቫ ተወላጅና እኔም ሆነን የተጠየቀውን መጽሐፍ ሁሉ ይዘን ሄድን። እነዚህን መጽሐፍት መያዜ ለበዓሉ አከባበር ተስማሚ በመሆናቸው ሳይሆን ስለመጽሐፍ መጠየቅ ስለሚወዱ ቁጥር ላበርክት በማለት ነው። መጽሐፍቱን ከፍቼ በመሠውያው ላይ አኖርሁዋቸው።

የጥዋት ጸሎታችንን በተቻለ መጠን አሳምረን መጸለይ ጀምረን በእውነትም እግዚአብሔር የረዳንና ጸጋውንም የሰጠን መሆኑ ይሰማን ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ሰም የሌለን መሆኑን በመገመት ወዲውኑ ሃያ ጥዋፍ አስላከልን። በእውነቱም አራት ጥዋፍ ብቻ ነበር ያለን። ይህን ጸሎት ቅኔና መዝሙሮች እየጨማመርንበት ብዙ ጊዜ እንዲፈጅ አደረግነው። ለዚያን ዕለት የተሰናዳ ሌላ ንባብ ስላልነበረን ለጊዜው ምንም ለማድረግ ስላልተቻለን ተስማሚ የሆነ መዝሙር እንፈልግ ነበር። እኔ ጸሎቱን ሳከናውን የተቀሩት ይዘምሩ ነበር። ይህ ሁሉ በሚከናወንበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱም ከላይ እንደተገለጸው በድንኳኑ

ጥግ ተቀምጦ ሲያዳምጥ መዝሙረ ዳዊትና ሌሎች መዝሙሮችም
በመቀባበል ሲዘመሩ የተዘመረው ምን እንደሆነ ለመጠየቅ በየጊዜው
ሁለት መልእክተኞች እየመጡ ይሄዱ ነበር።

የማላውቀውን በጠየቁኝ ጊዜ ስለየሱስ ልደት የሚናገር ከኤር
ምያስ፤ ከዳዊት ወይም ከሌሎች ነቢያት የተወሰደ ጥቅስ ነው በማለት
በማስመሰል እመልስላቸው ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም በመደሰት መጽሐ
ፍቱን ያመሰግን ነበር። ረጅም ጊዜ የፈጀው ቅዳሴአችን ካለቀ በኋላ
ድምጻችን ሳይሰማ ትንሽ መቆየታችንን በሰማ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ
መምሕር የነበረና አሁንም በዚሁ አገልግሎት ያለ አንድ ሽማግሌ
ቄስ ወደኛ መጥቶ ጸሎቻሁን አበቃችሁን ሲል ጠየቀን። መጨረ
ሳችንን እንደነገሁት ይህን መዝሙር በሰማሁ ጊዜ በእውነተኛው
ከመላዕክት ጋር በመንግሥተ ሰማያት የነበርሁ ስለመሰለኝ ቅዳሴ
አችሁ እስከጥዋት ድረስ ቢቀጥል እወድ ነበር ሲል ስሜቱን ገለጸልን።
እስከቁርባን ድረስ ዝማሬ የሌለን መሆናችንንና እኔም የጌታን
ሥጋ የሚቀበሉትን ሰዎች ኑዛዜ የምፈቅድ መሆኔን ነገርሁት።
የመናዘዣው ቦታ ወዴት እንደሆነ ለመጠየቅ እንደመጣ ጸሎቱን
በምናደርግበት ጊዜ እንዲማታ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ በተላከልኝ
ከበሮ ላይ ተቀምጬ ኑዛዜ እሰማ ነበር። ይህን መልእክት ይዞ
የመጣው ያ ሽማግሌ በደንብ የሚነድ አንድ ችቦ አብርቶ በድንኳኑ
ያሉት እንዲያዩኝ በማለት በፊቴ አኖረው። እርሱም በኔ አጠገብ
በምድሩ ላይ ተቀምጦ ክርኖችን በጉልበቶቹ ላይ አኑሮ (አንድ
ተማላይ ደግሞ በሌላ በኩል ሆኖ) እኔ ሁለት ሰዎች አናዝዤ አብቅቼ
እስኪነጋ ድረስ ከዚያ አልተነሣም ነበር። ከዚህ በኋላ ይህ የተከበረ
ቄስ እናንተ ቅዱሳን በመሆናችሁ የምታደርጉትም ሁሉ ፍጹም በመሆኑ
ሕይወቴን በሙሉ ከናንተ ጋር እሆን ዘንድ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ
ይሰጠኝ ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳኝ አለ። ይህ ሰው ወዲያውኑ
ተመልሶ መጥቶ የናንተ የኑዛዜ ስነ ሥርዐት እንዴት እንደሆነ
ንጉሠ ነገሥቱ ለማየት ስለሚፈልጉ መናዘዙ እንዲቀጥል ጠይቀዋል
ሲል ነገረኝ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ በጠየቀበት ጊዜ ቅዳሴ
ለመግባት ጊዜው ተቃርቦ ስለነበር ይህንኑ በመግለጽ መልሼ
ላክሁት።

መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ የዚያን ዕለት ከኛ
ቅዳሴ በስተቀር ሌላ ሊሰማ ፈቃዱ ስላልነበር በፈቀድሁትና በተመቸኝ
ጊዜ እንዳናዝዝና እንድቀድስ ያዘዘኝ መሆኑን ነገረኝ። እኔም ያገል
ግሎት ልብሴን ደርቤ በከበሮው ላይ ተቀምጬ፤ ተናዛዦም ቆቡን
ደፍቶ ተንበርክኮ ንጉሠ ነገሥቱ በደንብ በሚያየን አኳኋን ማናዘዙ
ቀጠለ። ማናዘዙ ከተፈጸመ በኋላ ጊዜ ማለፉ ስለሆነ ቅዳሴ እንግባ
ብዬ እርሱም መልሶ በፈቀዳችሁ ጊዜ ልትገቡ ትችላላችሁ፤ እኔ
ለማየትና ለመስማት አይሰለቸኝም፤ ብሎን ቅዳሴውንም ለመስማት
ዝግጁ መሆኑን ገለጸልን። መስቀልና የእመቤታችንንም ስዕል እን
ዲሁም በእጃችን የበራ ጥዋፍ ይዘን በመስቀሉም ግራና ቀኝ የበራ
ችቦ ተይዞ በድንኳናችን ውስጥ መዞር ጀመርን። ንጉሠ ነገሥቱ
መልእክተኛ ልኮ ስንዞር በደንብ የተመለከተን መሆኑን ገለጸልን።
ሕዝቡ በሙሉ ሊያየን ይችል ዘንድ ከመንዲላቱ ውጭ ወጥተን
እንድንዞር ስለፈቀደ አብርተን በእጃችን እንድንይዘው አራት መቶ
የነጭ ሰም ጥዋፍ ከድንኳኑ ውስጥ ላከልን። ይህ ጥዋፍ ከፖርቱጌዞቹ
ጀምሮ እስከሚያልቅበት ድረስ ለርሱም ሰዎች ጭምር እንዲታደል
አዘዘ። እርሱ በፈቀደው አኳኋን በተሙዋላ ስነ ሥርዐት ዞረን ገባን።
ራቅ ወዳለ ቦታ በመዞራችን ምክንያት ብዙ ጊዜ የፈጀብን የጉዞው
ስነ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ቅዳሴ ጸበል መርጨት ጀመርን። ንጉሠ
ነገሥቱንም ረጨነው። እንደነገሩን ከርሱም ጋር የነበሩት እቴጌይቱ፤
እናቱ፤ እቴጌ እሌኒ፤ አቃቤ ሰዓቱና ሌሎችም ሰዎች ነበሩ። በጸሎት
ድንኳኑ ውስጥ የቤተ መንግሥቱ ታላላቅ ሰዎች ግጥም ብለውበት
ነበር። በድንኳኑ ውስጥ ስፍራ ያላገኙ ደግሞ በውጭ ቁመው ነበር።
ምንም እንኳ በድንኳኑ ውስጥ ትርፍ ቦታ ቢኖርም ንጉሠ ነገሥቱ
ስነ ሥርዐቱን በደንብ ለማየት እንዲችል በማለት በርሱ አንጻር
ፊት ለፊት ያለውን ቦታ ሰው ሳይቆምበት ግልጽ ነበር። በዚሁ አኳኋን
ሁሉም እስከ መጨረሻው ድረስ በቆዩበት የተናዘዙትን አቆረብን፤
ቆራቢዎቹ በእጃቸው መሐረብ ይዘው ንጉሠ ነገሥቱ በድንኳኑ ሆኖ
በሚያያቸው አኳኋን በሁለት ረድፍ ገብተው ተንበርክከው ነበር።
በድንኳኑ አጠገብ የነበሩት ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች (ማለት የእመ
ቤታችንና የቅድስት መስቀል) ከቅዳሴ በኋላ ንጉሠ ነጉሥቱን
ቅዳሴ ጸበል መርጨት ልምዳቸው ስለነበር እኛም ከስነሥርዐቱ

በኋላ እንደነርሱው ረጨነው። በግምት ሁለት የቴኒስ መጫወቻ ሜዳ የሚያህል ርቀው ቅዳሴ ጸበሉን በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የሚረጩበት ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው። አንድ ዲያቆን በማን ቆርቆርያ ውኃ ይዞ ቄሱን ይከተለውና በእጁ ላይ ውኃውን ሲጨምርለት ቄሱ ፊቱን ወደንጉሣዊ ድንኳን ይመልስና ለምልክት ያህል ይፈነጥቃል። እኛ ግን በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ላይ የፈነጠቅነው ሂጾጵ ነበር። ፈረንጆቹ፤ አስተርጓዎቻችንና በተለይም በዚህ ጊዜ ከኛ ጋር የነበረው ፔሮ ድ ኩቪሊያንና ያገሩን ቋንቋ የሚያውቁት ሰዎች ሁሉ በነገሩን መሠረት የኛ አገልግሎት የሚከናወነው በብዙ ብፅዕናና በተለይም እኛ ቁርባን የምንሰጠው በንጽሕና በመሆኑ የኛን ወግ በጣም ነበር ያመሰገኑት። ንጉሠ ነገሥቱም መልእክተኛ ልኮ የናንተ አገልግሎት በጣም መልካምና ፍጹም ነው ሲል አስተያየቱን ገለጸልን።

ምዕራፍ ዘጠና አንድ፤ ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሩንና ሌሎቹንም አሰናብቶ እኔን በቆይታ ተቀብሎኝ ባስተርጓሚ ማናቸውንም የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ሁሉ ጠየቀኝ፤ በማግሥቱ ከዚያ ቦታ ስለመሄዱ።

ማናቸውም ስነሥርዐት ማለት ጉዞው ቅዳሴውና ቁርባኑ ከተፈጸመ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮ እኔ ካንድ አስተርጓሚ ጋር እንድቀርና አምባሳደሩና ሌሎቹም ሄደው ምሳቸውን እንዲበሉ አዘዘ። እኔ በዚያ ብቻዬን እንደነበርሁ ያ ሽማግሌ ቄስ ወደኔ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ ማናቸውንም የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት የምታከብሩ መሆናችሁን ያረጋገጠ ቢሆንም ተራውን ሕዝብ እንደ ካህናት በቤተ ክርስ ቲያን የምናስገባው እንዲሁም ሴቶች ይገቡ ዘንድ የምንፈቅደው በምን መብታችን መሆኑን መጠየቁን ነገረኝ። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ለማንም ያልተዘጋች መሆንዋንና ክርስቶስም ወደርሱ የቀረቡትንና

የመጡትን ሁሉ እጁን ዘርግቶ የተቀበላቸው መሆኑን አሳስቤ እንግዲህ እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ክብር የተቀበላቸው ሲሆን ቤተ ክርስቲያንም ለመንግሥተ ሰማያት መንገድ ስትሆን ለምንድን ነው በርስዋ የማንቀበላቸው ስል መለስሁለት። ስለሴቶች ደግሞ ምንም እንኳ በጥንት ጊዜ በመቅደስ ውስጥ ለመግባት ያልተፈቀደላቸው ቢሆንም የእመቤታችን ድንግል ማርያም በጎ ተግባር እጅግ የበዛ ስለነበርና ስለሆነም ይህ የርስዋ ተግባር ብቻ ሴቶች በእግዚአብሔር ቤት እንዲገቡ አብቅቶአቸዋል። ከመሠውያው ላይ ሆኖ ስለማገልገልም ጉዳይ ሥልጣን ያላቸው ካህናት ሁሉ ለማገልገል የሚችሉ መሆናቸውን ገለጽሁለት።

ወዲያውኑ የኔን አስተያየት የሚስማሙበት መሆናቸውን ከማረጋገጣቸው በላይ ጥያቄአቸውን በማስከተል በቅዳሴ የገባኸው ቄስ አንተ ብቻ ስትሆን ጽናውን ከቄሱ በስተቀር ሌላ ሰው ሊይዘው የማይገባ ሲሆን በምን ምክንያት ነው ሌላ ሰው እንዲይዘው መደረጉ ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም መልሼ ጽናውን መያዝ በተለይ የዲያቆን ተግበር ነው አልኋቸው።

መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ የናንተ መጽሐፎች ማናቸውም ነገር ስለሚገኝባቸው ከኛዎቹ የተሻሉ ስለሆኑ ይህ ተጽፎ ይገኛልን ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም መልሼ በቅዱሳት መጽሐፍት ማለት በነቢያት፤ በወንጌሎችና በሐዋርያት መልእክቶች እንዲሁም በመድኃኒታችን የሱስ ክርስቶስ ተዘርተው የሚገኙትን ምስጢሮች እየቃረመ ባንድነት ማከማቸት ብቻ እንጂ ሌላ ሥራ የሌላቸው ያልነበራቸውም ብዙ ሊቃውንት ከሐዋርያት በኋላ በቅድስት እመ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ስላሉ የኛ መጽሐፍት በፍጹም ጉድለት የማይገኝባቸው መሆኑን አስረዳሁ። እንደገናም መልሰው እኛ በብሉይ ኪዳን ያሉን መጽሐፍት ቁጥር ሰማንያ አንድ ነው የናንተስ ሲሉ ጠየቁኝ።

እኔም መልሼ እኛም እነዚሁ ሰማንያ አንድ መጽሐፍት አሉን፤ እንዲሁም ብዙ መግለጫ የሚሰጡና የተሙዋሉ ከነዚህ የተወሰዱ አስር ጊዜ ሰማንያ አንድ የሚሆኑ ሌሎች አሉን አልኋቸው። ይህን

ባልኋቸው ጊዜ የኛን ያህል ብዙ መጽሐፍት የሌላቸው መሆናቸውን አምነው የማያውቋቸውንና ስማቸውን ያልሰሙዋቸውን መጽሐፍት ሁሉ ስም እንድዘረዝርላቸው አዘዙኝ።

በዚህ አኳኋን ሁለት መልእክተኞች ያለማቋረጥ ወዲያና ወዲህ ሲመላለሱ እኔም ያን ሁሉ ጊዜ በመቋሚያ ተደግፌ ቆሜ እስከማታ ጸሎት ድረስ ቆየን። እነዚህ ጥያቄዎችና መልሶች ሁሉ ይጻፉ ስለነበር ሁለት እጅ ወረቀት አልበቃም ነበር። ጥያቄውን ሲያቀርቡልኝ በጣም ያጣድፉኝ ስለነበር በቃል ለመያዝ አስቸጋሪ ነበር። አንዱን ጥያቄ ስመልስ ሌላው ይተካ ነበር፤ ጥያቄውንም የሚያቀርበው ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ሳይሆን እቴጌይቱና እናቱም እቴጌ እሌኒም ስለነበሩ አጠያየቁ አንድ መስመር ሳይከተል ልዩልዩ ጉዳዮችን የሚነካካ ነበር። ጥያቄው በዚህ አኳኋን ይቀጥል ነበር፤ ነገር ግን እኔን ረሃብና ድካም ስላሸነፈኝ ጥያቄውን በመመለስ ፈንታ ከትናንት እኩለ ቀን ጀምሬ እህልና ውኃ አፌን ሳይነከው እንቅልፍም በዓይኔ ሳይዞር በድካም ተሸንፌአለሁና ግርማዊነትዎ ለኔ ለሽማግሌው ይዘንልኝ ስል እንዲያሰናብተኝ ለመንሁት። መልእክተኛውም ተመልሶ መጥቶ እኔ ካንተ ጋር ለመነጋገር ስደሰት አንተ ለምንድን ነው ያለመደሰትህ ብለውሃል አለኝ። እርጅና ረሃብና ድካም አሸነፉኝ ስል መለስሁላቸው። መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ ለመብላት ከፈለግህ ምግብ ይላክልሃል ወደ ድንኳናችሁም ምግብ ተልኳልና ከዚያ ሄደህ ለመብላት ከፈለግህ ልትሄድ ትችላለህ ወይም ከፈቀድህ ምግቡ እዚህ ድረስ ይመጣልሃል አለኝ፤ ነገር ግን ወደ ድንኳናችን ሄጄ ለማረፍ ስለፈለግሁ ፈቃድ ስጥተውኝ ወዲያውኑ ሄድሁ።

ወደ ድንኳናችን ለመሄድ በመንገድ ላይ እንደነበርሁ አንድ ብላቴና በሩጫ ብዛት ሲቃ ይዞት በአጠገቤ መድረሱን በማየት እንድመለስ የሚጠራኝ የኃጢአቴ ብዛት መሰለኝ፤ ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ብላቴና አማካይነት ባርኔጣዬን እንድልክለትና ሳልበላ ብዙ ጊዜ በመቆየቴ ይቅርታ እንዳደርግለት ቅርም እንደይለኝ ለመነኝ። እንዲሁም ከኔ ሊያውቃቸው የሚፈልገው ብዙ ነገሮች ስላሉ ከበላሁ በኋላ በቶሎ እንድመለስ አዘዘኝ።

በድንኳናችን እንደደረስሁ ራሴን አዞሮኝ ሰውነቴም ቅዝቅዝ ብሎ ዓይኖቼ ማየት አቃታቸው። አንድ ሰዓት ተኩል ያህል እንደ ቆየሁ መልእክተኛ መጥቶ ጠራኝ። ጊዜው በጣም መሽቶ ስለነበር የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት የሚያውቁት ብቻ ከኔ ጋር ሄዱ፤ ለሌላ ፕሮግራም በቂ ጊዜ ስላልነበረ አንዳንድ ዜማ ብቻ ዘመርን። ከመዝሙሩ በኋላ መልእክተኛ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ ሊሄድ ስለሚዘጋጅና በመንገዱ ላይ ያሉትን መተላለፊያዎች ማንም ሳያውቅ ሊያልፍ በመፈለግ አሁን መሄዱ ነውና የመጸለያ ድንኳናችሁን እንድትነቅሉ ታዛችኋል አለን።

በድንኳናችን እንደተኛን በእኩለ ሌሊት ገደማ በኛ አጠገብ ሲያልፉ የብዙ ሰዎች ጫማና የበቅሎች ኮቴ የሚንጋጋ ድምጽም ሰማን። እኛም ንጉሡ ደሄዳል ማለትን ሰምተን ስለነበር ብቻችንን ተቆርጠን የምንቀር መስሎን በቶሎ ተዘጋጅተን መንገድ ቀጠልን። በመጀመርያው መተላለፊያ ላይ በደረስን ጊዜ በጦር ተከበን ከመሄድ በስተቀር ሌላ መድኃኒት ስላልነበረ በዚሁ አኳኋን የኛ ሰዎች ከፊትና ከኋላ ጦር ይዘው እኛም አንድ ሰው እንኳ በመካከላችን ሳናስገባ ተከበን ሄድን፤ እንዲህ ባናደርግማ ኖሮ ተጠፋፍተን እንቀር ነበር።

ንጉሣዊው ድንኳን በዋሻ ውስጥ በወንዞች መካከል በሚገኝ ባንድ ቦታ ተተክሎ አገኘነው። ይህ ቦታ ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት ይመራን የነበረው መነኩሴ ያካባቢውን ገበሬዎች የባቄላ አዝመራ ያበላሸበት ቦታ ነው። ያን መጥፎ መንገድ ማለፍ የቻለ ሰው ሁሉ በዚያ ቦታ ተኛ፤ እኛ ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከእኩለ ሌሊት በፊት አልፎ ሄዶ ነበር ማለትን ስለሰማን እርሱኑ ተከትለን ወዲያውኑ ስለሄድን ብዙ አልተኛንም፤ ስለዚህ መንገዳችንን ቀጥለን በመሄድ መጥፎዎቹን መተላለፊያዎች ከመንጋቱ በፊት አለፍናቸው። የዚያን ዕለት ሌሊት በመተላለፊያው ላይ ብዙ ወንዶችና ሴቶች፤ ብዙ በቅሎዎችና አህዮች፤ አጋሰሶችና መጋዣ በሮችም ሞቱ ማለትን ሰማን፤ እኛም ብዙዎች ሞተው ወድቀው አይተናል። ይህ ቦታ ከዚህ በፊት እንደተገለጸው በመጣን ጊዜ ያለፍነው አህያ ፈጅ የተባለው

ቦታ ነው። ከግራና ቀኝ ተደግፋ ከፊትም በቅሎዋን እያሳበች ትሄድ የነበረች አንዲት ሴት ወይዘሮ ከነአሽከሮቹዋና ከነበቅሎዋ ተንከባላ ገደል ስትገበ አይተናል። ከወንዙ ውስጥ ከመድረሳቸው በፊት ሁሉም ተፈጥፍጠው ብትንትናቸው ወጥቶ አለቁ። ይህን የመሰለ አደጋ ሊደርስ የቻለው ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት ገደሎቹ ለማመን በሚያስቸግር አኳኋን ረጃጅም በመሆናቸው ነው። እነዚህን ገደሎች ያየ ሰው ከሌላ ነገሮች ይልቅ ገሃነም እሳትን ያሳስቡታል።

በአገሩ ልምድ መሠረት የልደት በዓልን ስምንተኛ ቀን ማክበር ልምድ ቢሆንም በዓሉን ሳናከብር ጉዞአችንን ቀጠልን። የንጉሠ ነገሥቱ አጀብ ካንድ ቦታ ተነሥቶ ወደሌላው ለመሄድ አራት ወይም አምስት ቀን አይበቃውም ብያለሁ፤ በዚህ ቦታ ግን መጥፎውን መንገድ ለማለፍ ሶስት ሳምንት ፈጀባቸው። የንጉሠ ነገሥቱ ልብስና ጓዝም በየቀኑ በማለፍ ከአንድ ወር የበለጠ ጊዜ ፈጀ።

ምዕራፍ ዘጠና ሁለት፤ ንጉሠ ነገሥቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ አደረ፤ የኤምባሲው ሠራተኞች ይህን ቦታ እንድናየው ታዘዝን፤ እኔን አንድ ጥያቄ ከጠየቀኝ በኋላ በጣም ጌጠኛ የሆኑ ድባቦችን እንዲያሳዮኝ አዘዘ።

ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ ባለፍን ጊዜ ባየነው ግን ሳንጎበኘው ባለፍነው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አግጣጫ ታህሳስ 28 ቀን 1520 ዓም ደረስን። የንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ከቤተ ክርስቲያኑ በታች የኛም በተወሰነልን ቦታ ተተከለ። በማግሥቱ ጥዋት በማለዳ ከቤተ ክርስቲያኑ ድረስ ተጠራን። ሕንፃው በጥሩ ታሪኮች የተመሠረቱ በደንብ ተመዛዝነው በተሠሩ ስዕሎች አጊጦአል። እነዚህን ስዕሎች የሳለው ከዚህ በፊት የተጠቀሰው ኒኮላ ብራንካ ሌዎኔ የተባለ የቬኔዚያ

ተወላጅ ነው። ስሙም በስእሎቹ ላይ ተጽፎ ይገኛል፤ ሕዝቡ ግን መርቆርዮስ በሚያሰኝ ስም ነበር የሚጠራው። የቤተ ክርስቲያኑ ማህሌት ከላይ እስከ ታች ድረስ በወርቀዘቦ በከፈይና በሌላም ጌጠኛ ጨርቆችና መጋረጃዎች አጊጦአል። ገረገራውን አልፈን በማህሊቱ ውስጥ ለመግባት ስላልፈለግን መጋረጃውን ገልጠውልን በወርቅ የተለበደው ዋናው በር ታየ። ወርቅ ነው ሲሉን አላመንንም ነበር፤ ነገር ግን በደንብ ካየነው በኋላ እንዳሉትም የበሩና የመስኮቱ ሣንቃ በወርቅና በብር ቅጠሎች አምረው የተለበዱ መሆናቸውን ተረዳን። እነዚህን ነገሮች ባየን ጊዜ ትልቅ ክብር ያለው ሰው በመሆኑ እየዞረ የሚያስጎበኘን አቃቤ ሰዓቱ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ በመጋረጃው ውስጥ ተቀምጦ ባጠገቡ ስናልፍ ያየን ነበር፤ እኛም እናየው ነበር። ከዚያ ከመጋረጃው ውስጥ ስለቤተ ክርስቲያኑና ስለቤቶቹ ያለንን ግምት አስጠየቀን። እኛም አስተያየታችንን በመግለጽ ማለፊያ መሆኑንና በእውነተኛው ያንድ ትልቅ መስፍን ሃብት የሚመስል መሆኑን ነገርነው። ይህ የኛ አስተያየት ደስ ስላሰኘው መልእክተኛ ልኮ ይህን ቤተ ክርስቲያን ያሳነጸው አያቱ መሆኑንና በዚያም መቀበሩን ነገረን። በኛ አገር እንደዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጣቸው በእንጨት የተሠሩ እንዳሉ ከምን እንጨትስ እንደተሠሩ አስጠየቀን። ከዚህ በፊት እንደገለጽነው ቤተ ክርስቲያኑ ማለፊያ መሆኑ የማይካድ ቢሆንም፤ የኛ አገር ቤተ ክርስቲያኖች ጣርያቸው በድንጋይ የተሠራ መሆኑን፤ እንዲሁም በእንጨት የተሠሩ ቢኖሩም እንጨቱ በወርቅ የተለበደ ወይም በሰማያዊ ቀለም የተቀባ መሆኑን፤ ምሰሶዎቹም ከእብነ በረድና ከሌሎችም ከፍተኛ ዋጋ ካላቸው ድንጋዮች የተሠሩ መሆናቸውን ገልጸንለት፤ እርሱም እኛ ጥሩ የእጅ ጥበብ አዋቂዎች ስላሉን ሥራችን ሁሉ ታላቅና ጌጠኛ ጉድለትም የሌለበት መሆኑን የሚያውቅ መሆኑን በማስታወቅ መለሰልን።

የዚህ ቤተ ክርስቲያን ጣርያ የመርከብ ምሰሶዎች ያህል ውፍረት ባላቸው በሰላሳ ስድስት የእንጨት ምሰሶዎች ተደግፎአል። ምሰሶዎቹ እንደገና በእንጨት ተለብደው በግድግዳው ላይ የሚታዩትን የመሰሉ ስዕሎች ተስለውባቸዋል። ስለዚህ ይህ የንጉሥ ሕንፃ በመሆኑ ያገሩ ሕዝብ ትልቅ ክብር ይሰጠዋል።

የዚያን ዕለት ከቀትር በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶኝ ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ያለኝን አስተያየት ጠይቆኝ የኛ ሰዎች በእውነተኛው ከሰጡት አስተያየት ጋር በማስማማት የኔንም ሰጠሁት። ከዚህም በኋላ በተጨማሪ ስለቅዱሳን ገድልና ስለኛ ቤተ ክርስቲያኖችም ስነ ሥርዐት ጠይቆኝ የማውቀውን መለስሁለት። በንጉሣዊው ድንኳን አጠገብ ሆኜ የቀረበልኝን ጥያቄ ሁሉ ፈጽሜ እንድሄድ ካሰናበቱኝ በኋላ ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ጌጠኛ የሆኑ አራት ትልልቅ ድባቦች አወጡ። ከዚህ በፊት በሕንድ አገር ጌጠኛ የሆኑ ትልልቅ ድባቦች አይቻለሁ፤ ነገር ግን እነዚህን የመሰሉ ከቶ ባለማየቴ በጣም ተደነቅሁ። ድባቦቹን ያሳዩኝ ሰዎች መደነቄን ለንጉሠ ነገሥቱ ነግረውት ኖሮ ወዲያውኑ አስጠርቶኝ ተመለስሁ። በቤተ መንግሥቱ የነበሩት ፈረንጆች በደጁ ላይ ተቀምጠው ስለነበር እኔም ተመልሼ ከነርሱ ጋር ተቀላቀልሁ። ወዲያውኑ እነዚያን ድባቦች አቅርበውልኝ በደንብ እንድመለከታቸውና አስተያየቴን እንድሰጣቸው ጠየቁኝ። እኔም ከተመለከትሁ በኋላ ድባቦቹ ያንድ ትልቅ ንጉሥ ሃብት የሚመስሉኝ መሆናቸውንና፤ ምንም እንኳ ታላላቅና ጌጠኞች በሕንድ አገር ቢገኙም ነገር ግን እነዚህን የመሰሉ ከዚህ በፊት ያላየሁ መሆኔን ነገርኋቸው። ከዚያ በኋላ እነዚያ ድባቦች በጸሐይ ላይ እንዲተከሉ አዞ በጉዞው ላይ ባለ ጊዜ እርሱ ወይም እቴጌይቱ ዕረፍት ሊያደርጉ ሲፈልጉ ከነዚያ ድባቦች አንዱን አስተክለው በጥላ ሥር እንዳስፈለጋቸው እንደልብ የሚመገቡ ወይም የሚያርፉ መሆናቸውን ነገሩኝ። እሳይተውኝ ካበቁ በኋላ እነዚህ ድባቦች እጅግ ታላላቆችና ጌጠኞች በመሆናቸው ግርማዊነታቸው ከያንዳንዱ ጥላ ሥር ሊያርፍ ይችላሉ ስል ላክሁበት። ወዲያውኑ መልእክተኛው መጥቶ የፖርቱጋል ንጉሥ ይህን የመሰለ አለውን ሲል ጠየቀኝ። እኔም መልስ በመስጠት የፖርቱጋል ንጉሥ እኔ የደፋሁትን የመሰለ ነገር ግን ዙርያውን በወርቀዘቦ በከፈይ ወይም በሐር የተከፈከፈ ወይም ባሰኘው አኳኋን በወርቅ ክርና በሌላም ዓይነት ዘርፍ ያጌጠ ሌላ ዓይነት ባርኔጣ ያደርጋል እንጂ ድባብ የለውም፤ በተጓዘ ጊዜ ዕረፍት ማድረግ ሲሻው ብዙ ቤተ መንግሥቶች ስላሉ በነሱ ውስጥ ገብቶ ያርፋል፤ እንዲሁም ጥላ ከፈለገው አምረው የተተከሉ ዛፎችና አትክልቶች ስላሉ በነሱ ሥር ሊያርፍ ይችላል፤ እንዲያውም እነዚህ ድባቦች ለጥላ ከመፈ

ለጋቸው በላይ በተለይ ለነገሥታት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ይመስሉኛል ስል መልስ ሰጠሁ። ከዚህ በኋላ ሌላ መልእክተኛ ወዲያውኑ መጥቶ እኔ የተናገርሁት እውነት ነገር መሆኑን አረጋግጦልኝ እነዚያ ድባቦች የአያቱ ሃብት ሲሆኑ የሚቀመጡትም በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሆኑንና አሁን ግን ወደፊት ለምንጎበኘው ላንድ ቤተ ክርስቲያን በውሰት እንዲሰጡ ያዘዘ መሆኑን ነገረኝ፤ ድባቦቹ በጣም ሰፋፊ በመሆናቸው በያንዳንዳቸው ጥላ ሥር አስር ሰው ሊቀመጥ ይችላል። ለቀረቡልኝ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ሰጥቼ ካበቃሁ በኋላ እንደገና መልእክተኛ ልኮብኝ ከወይን ጠጅ፤ ከጠጅ፤ ወይም ከጠላ የትኛውን እንደምመርጥ አስጠየቀኝ። ጠጅ ሞቅ የሚያደርግ መጠጥ ጠላም ቀዝቃዛ በመሆኑ ሁለቱም ለሽማግሌ የማይስማሙ መጠጦች ናቸው፤ ይሁን እንጂ ግርማዊነትዎ እንደፈቀደው ወይን ጠጅም ሆነ ጠጅ ቢልክልኝ እቀበላለሁ ስል መልእክተኛውን መለስሁት። መልእክተኛውም ወዲያው ተመልሶ መጥቶ የትኛውን እንደምትመርጥ ንገረኝ ብሎኝ የወይን ጠጅ እንዲያመጣልኝ ነግሬው ወዲያው አራት ገንቦ አምጥቶልኝ በድንኳኑ አጠገብ ይገኙ የነበሩትን አስቀድመው የመጡትን ፈረንጆችና ጥያቄና መልሱን በተለዋወጥን ጊዜ በዚያ የነበሩትንም እንድጋብዝ ታዘዝሁ። እኔ የጠየቅሁት የወይን ጨጅ ሲሆን የተላከልኝ ግን ጠጅ ነበር። እያንዳንዳችን አንዳንድ ጠጥተን የተረፈውን ወደ ድንኳኑ ወሰድነው።

ምዕራፍ ዘጠና ሶስት፤ ስለንጉሠ ነገሥቱ ስነ ሥርዓትና ስለ አጀቡ።

በተባለው ወር ሃያ ዘጠነኛ ቀን ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮብኝ ካልተመራን በስተቀር በገዛ ራሳችን እንዳንሄድ አዘዘን። የርሱም መንገድ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው። ባለፉት ቀኖች የሚሄድባቸውን መንገዶች የሚያውቅ ማንም አልነበረም። ሕዝቡ ነጭ ድንኳን ተተክሎ በሚታይበት ቦታ ሲደርስ ይቆምና እያንዳ

ንዳችንም በግራ ወይም በቀኝ በቅርብ ወይም በሩቅ ሲባል አስቀድሞ በተወሰነልን ቦታ እናርፋለን። እርሱ ቢኖርም ባይኖርም የከተማው ስነ ሥርዓት በፍጹም አይጓደልም፤ ይሁን እንጂ በሌላ ጊዜ ስነ ሥርዐቱ በደንብ አይከበርም። በብላቴኖቹ አገልግሎት መቀዝቀዝና በሌሎቹም ምልክቶች ንጉሠ ነገሥቱ በከተማው አለመኖሩን ለይቶ ለመረዳት ይቻላል። እስከዚህ ጊዜ ድረስ እንዳሰኘው አንዳንድ ጊዜ ከፊታችን አንዳንድ ጊዜም ከኋላችን እየሆነ ይጓዝ ነበር። አሁን ግን ተገልጾና ዘውድ ጭኖ ከኋላ ከግራና ቀኝም ከፍ ብሎ በሰፊው የተያዘ ቀይ መጋረጃ ውስጥ ሆኖ ይጓዝ ጀመር፤ እርሱ በመጋረጃው ውስጥ ሲሆን መጋረጃውን የያዙት ሰዎች ደግሞ ጨርቁን ከእንጨት ላይ ወጥረው ከውጭ በኩል ሆነው ይሄዳሉ። ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በመጋረጃው ውስጥ ሆነው ስድስት ለጓሚዎች ቀጥሎ በተመለ ከተው አኳኋን ይጓዛሉ። በበቅሎይቱ ልጓም አልፎ ወደ ቀዳማው በሚሄደው ልባብ ግርጌ ማለት ከበቅሎይቱ አፍ ግራና ቀኝ በሐር ጆፍጆፌዎች የሚያልቁ ሁለት መገናኛዎች አሉ፤ ሁለቱ ብላቴናዎች በተባላው ቦታ በቅሎይቱን ይዘው በግራና በቀኝ ይሄዳው፤ ሌሎች ሁለት ደግሞ ከወዲያና ወዲህ የበቅሎይቱን ጋማ ይዘው ይከተላሉ። እንዲሁም ሁለት ሌሎት ብላቴናዎች በግራና በቀኝ ሆነው በበቅ ሎይቱ ሽንጥ ላይ እጃቸውን አኑረው ይከተላሉ። ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ከታላላቆቹ አሽከሮች ከሃያ የማያንሱ ሲሄዱ ከነርሱ ፊት ደግሞ በጣም አጊጠው የተጫኑ ስድስት ማለፊያ ጥሮኞች ደሄዳሉ፤ ከያንዳንዱ ጋር ባገር ደንብ ማለፊያ ልብስ የለበሱ ሰዎች ይከተላሉ።

እነዚህም ሰዎች የተጫነውን ጥርኝ እንደ ንጉሠ ነገሥቱ በቅሎ ሁለቱ ከፊት ልጓሙን ይዘው ይሄዳሉ። ሁለቱ ደግሞ ከግራ ከቀኝ ኮርቻውን ይዘው ይከተላሉ። ከጥርኞቹ ፊት በጌጠኛ ዕቃ የተጫኑ ስድስት በቅሎዎች ይሄዳሉ። ለበቅሎዎቹም ለያንዳ ንዳቸው አራት ሰዎች ተደልድለውላቸዋል። ከበቅሎዎቹ ፊት ቤዶም የደረቡ ሃያ ታላላቅ መኳንንት ሲሄድ እኛ ፖርቱጌዞቹ ደግሞ በተፈ ቀደልን ቦታ ማለት ከመኳንንቱ ፊት ስንጓዝ ነበር። ማንም ሰው ማለት ፈረሰኛም ሆነ በቅሎኛ ወይም በእግሩም የሚሄድ ሰው ቢሆን

እንዲቀርብ አይፈቀድለትም። ድንገት ከፊት ሰው ሲሄድ የታየ እንደሆነ ፈረሰኞች በግልቢያ ሄደው (ፈረሶቹ ደክመው ካልወደቁ በስተቀር) የታዩትን ሰዎች ከዚያ ቦታ ያርቋቸዋል፤ ፈረሶቹም ደክመው ቢወድቁ ሌላ ፈረሶች ይለውጣሉ። ቢትወደዶቹም ከጠባቂዎቹ ጋር ተቀላቅለው አንድ በግራ ሌላውም በቀኝ በኩል በትንሹ ያንድ ጠበንጃ ተኩስ ያህል ርቀው ይሄዳሉ፤ መንገዱ ሜዳ ከሆነ ግን እስከ ግማሽ ሌግዋ ያህል አንዳንድ ጊዜም እንደ መንገዱ ሁኔታ አንድ ሌግዋ ድረስ ይርቃሉ። መንገዱ ገደላም ከሆነና ሌላ መንገድ ካልኖረ ግን የቀኝ ቢትወደዱ ግማሽ ሌግዋ ያህል ቀድሞ ሲሄድ የግራው ደግሞ ይህንኑ ያህል ርቆ ይከተላል።

ከያንዳንዱ ቢትወደድ ጋር ከስድስት ሺ ሰዎች በላይ ያሉበት ሠራዊት ይሄዳል፤ እንዲሁም ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው ከፊትና ከኋላ በሰንሰለት ታሥረው የሚሄዱ አራት አንበሶች አሉ፤ ታቦቶቹም በታላቅ ክብር ይጓዛሉ። ንጉሠ ነገሥቱ በተጓዘ ቁጥር ከቶ የማይለይ አንድ ገንቦ ጠጅ ነው። እያንዳንዱ ገንቦ ስድስት ከናዳ ይይዛል፤ እነዚህ ገንቦዎች ማለፊያ ሆነው የተሠሩ እንደ ባልጭት ድንጋይ ጥቁር ሲሆኑ በሸክላ መግላሊት ተገጥመው በማህተም ታትመዋል። ማንም ሰው ትልቅ መኮንንም ቢሆን ያለ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ከጠጁ ሊለምን ወይም ሊቀምስ አይፈቀድለትም፤ ከዚህም በላይ በእንጀራ የተመሉ አንድ መቶ የስጋጃ ሞሰቦች ወንዶች በጭንቅ ላታቸው ተሸክመው ከንጉሠ ነገሥቱ ሳይርቁ ይከተላሉ። ጠጅና እንጀራ የያዙት ሰዎች በቅደም ተከተል ተራ ማለት ጠጅ የያዘ ሲቀድም እንጀራ የያዘ ሲከተል ከዚያም ጠጅ የያዘ ሲቀጥል በመስመር ተከታትለው ይሄዳሉ። ከነርሱም በኋላ ስድስት አሳላፊዎችና አዛዦች ይከተላሉ። የንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ተተክሎበት በሚገኘው በከተማው ሲደርሱ ምግቡንና መጠጡን በሙሉ በድንኳኑ ካስገቡት በኋላ ንጉሠ ለሚፈቅደው ሰው ከፍሎ ይሰጣል።

ምዕራፍ ዘጠና አራት፤ የንጉሠ ነገሥቱ ወደ መካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መሄድ።

በታህሳስ ወረ መጨረሻ ቀኖች ቅዳሜና እሁድ የንጉሠ ነገሥቱ ጓዝና እኛም ባንድ ወንዝ አጠገብ ባለ ሜዳ ላይ ሠፈርን። ንጉሠ ነገሥቱ ከዚህ በፊት ሲጓዝበት በነበረው አኳኋን በመጋረጃው ውስጥ ሆኖ ሁላችንም ሰኞ ዕለት መንገዳችንን ጀመርን። ጥር 1 ቀን 1521 ዓም ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ ስናልፍ አላስ ገባን ባሉን በመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ደረስን። ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ ፊቱን ተገልጾ ዘውዱን ጭኖ በእጁም መስቀል ይዞ በመጋረጃው ውስጥ ሆኖ እኛም ከፊት ቀድመን ስንጓዝ ከቤተ ክርስቲያኑ ለመድረስ አንድ ሌግዋ ያህል ሲቀረን ባገሩ ውስጥ ከፍተኛ ግምት ያላቸው ስምንት ትልልቅና በጥሩ ዕቃ የተጫኑ ፈረሶች አስመጥቶ ፖርቱጊዞች ተቀምጠውባቸው እያቅ በጠበጡዋቸውና እያስገሩዋቸው ከፊት ቀድመው እንዲሄዱ አዘዘ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ለመድረስ እሩብ ሊግዋ ያህል ሲቀር ብዙ ሰዎች ንጉሠ ነገሥቱን ለመቀበል መጡ። የሕዝቡ ብዛት ቁጥር አልነበረውም። መስቀሎቹም ብዛታቸው ለቁጥር ያስቸግር ነበር። ከልዩ ልዩ ገዳሞችና ቤተ ክርስቲያኖች ከሃያ ሺ የሚበልጡ ካህናት በየወገናቸው ተከፍለው መስቀላቸውን ይዘው ተሠልፈው ነበር፤ በአማራ ግዛት ውስጥ ትልልቅ ቤተ ክርስቲያኖችና የነገሥታ መቃብሮች እንጂ ገዳሞች ስለሌሉ በዚያ የሚገኙ መነኩሴዎች የሚገኙት ከሩቅ ቦታ ሳይሆን አይቀርም። ከካህናቱ ውስጥ አንድ መቶ የሚሆኑ ባለ ጥምጥሞች ይታዩ ነበር፤ እንዲሁም ከፍ ብለው የተያዙ በደንብ የተጌጡ ድባቦችም ይታዩ ነበር። ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ያየሁትን ያህል ጌጠኛ አይደሉም። ድባቦቹ ሁሉ የነገሥታት አጽም የሚገኝባቸው ቤተ ክርስቲያን ሃብት ሲሆኑ ነገሥታቱ ሲሞቱ

የሚናዘዙዋቸው ናቸው። ሰዎቹ ምንም እንኳ በብዛታቸው ከንጉሠ ነገሥቱ አጀብ ባይተካከሉም አብዛኞቻቸው ከየቤተ ክርስቲያኑና ገዳማቱ ንጉሠ ነገሥቱን ለመቀበል የመጡ ናቸው።

ንጉሠ ነገሥቱ ፊቱን ተገልጾ ሲሄድ ከዚህ በፊት ስላልታየ አብዛኛው ሰው የመጣው እርሱን ለማየት ነበር። በቤተ ክርስቲያኑ ደርሰን ጸሎት ካደረስን በኋላ ወደ ንጉሣዊው ድንኳን ተጠራሁ። አምባሳደሩና ጭፍሮቹም እንዲሄዱና እረፍት እንዲያደርጉ ታዘዙ። ስለተደረገለት አቀባበል አስተያየቱን እንድሰጥና ለፖርቱጋል ንጉሥስ ይህን የመሰለ አቀባበል ይደረግለታልን ሲል ንጉሠ ነገሥቱ አስጠየቀኝ። እኔም መልስ በመስጠት ለፖርቱጋል ንጉሥ ታላቅ አቀባበልና ድግሥም እንደሚዘጋጅለት የታወቀ ነው፤ ነገር ግን ይህን ያህል ብዙ ሰዎችና መስቀሎች ባለጥምጥሞችም የሚገኙበት የሰው ብዛት ከቶ አላየሁም። ይህ አቀባበል በዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሌለው ነው፤ ግርማዊነትዎ በክርስቲያን አገሮችና በመላውም ዓለም ዝናዎ በሰፊ የታወቀ ባይሆን ኖሮ የዚህን አቀባበል ወሬ የውጭ አገር ሰው ቢሰማው ሊያምነው አይችልም ነበር፤ ዳሩ ግን ዝናዎ የታወቀ ስለሆነ ሰዎች እንዲያምኑ ይገደዳሉ ስል አስተያየቴን ገለጽሁለት። መልእክተኛውም ተመልሶ መጥቶ በዚያ የነበሩት ሰዎች በእውነቱ ብዙ ነበሩ፤ ነገር ግን ራቁታቸውን ስለነበሩ ቁጥራቸው ጥቂት መስሎ ታየ፤ የናንተ ሰዎች ግን ምንም እንኳ ጥቂት ቢሆኑም ልብስ ያላቸው ደማቆች ስለሆኑ ብዙ መስለው ይታያሉ አለኝ። ከዚህ በኋላ ወደ አምባሳደሩ እንድሄድ ተፈቀደልኝ። ወደ ማረፊያችን ስሄድ አምባሳደሩን በመንገድ አግኝቼው ከርሱ ዘንድ እንደነበርሁ መልእተኛ መጥቶ ይህ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ስለሆነ ገና አልተ ቀደሰበትም አለኝ፤ ስለዚህ ወደቤተ ክርስቲያኑ የገባ ሁሉ አንዳንድ ነገር እንዲያበረክት ደንብ ስለሆነ አምባሳደሩም መሃርያውን እኔም በራሴ ላይ ደፍቼው የነበረውን እንድንሰጥ እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው ሊሰጥ የሚገባውን ነገር እንዲያበረክት መታዘዙን ነገረን። ይህን ያዘዘው ለቀልድ መሆኑን አወቅን፤ ይሁን እንጂ በኛ ሃሳብ በጣም ተደሰቶ ነበር።

ምዕራፍ ዘጠና አምስት፤ ስለመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃና መልክ፤ አምባሳደሩ የንጉሠ ነገሥቱን እናት ቤተ ክርስቲያን እንዲጎበኝ ስለመታዘዙና በዚያም ስለተፈጸሙ ነገሮች።

በማግሥቱ ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዲያስገቡን አዘዘ፤ እርሱም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ነበር፤ ግድግዳዎቹ በጥርብ ድንጋይ ተሠርተው በሃረግ ያጌጡ ናቸው። ግድግዳዎቹ በውስጥ ላያቸው ሰው ለመጀመርያ ጊዜ ማለፍያ መስለው ቢታዩም ተገናኝተው እርስ በርሳቸው ሳይያያዙ ማለት የማዕዘን ድንጋዩና ትንንሾቹ ድንጋዮች በደረቅ ካብ ስለሆነ የተሠሩት ሽክም ስለማይችሉ የጣርያው ማዋቀርያ እንጨት በግድግዳው ላይ አያረፍም። ከዚህ በፊት እንደጎበኘነው እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የዚህም ዋና በር መዝጊያ በወርቅና በብር ተለብዶአል። በዚህ የወርቅ ልባድ ውስጥ በደንብ የተቀመጡ አንዳንድ የከበሩ ድንጋዮችና ፈርጦችም አሉ። ከበሩ በላይ ባለው የግድግዳው ክፍል ላይ አምረው በብሩሽ የተሳሉ ሁለት የእመቤታችን ምስሎችና እንዲሁም አንድ ዓይነት የሆኑ የሁለት መላእክት ስዕሎች ይታያሉ። እነዚህን ስዕሎች የሠራቸው በገዛ ራሱ ሰዓሊነትን አጠና የሚሉት እኔ ራሴ ያየሁት አንድ መነኩሴ ነው።

ቤተ ክርስቲያኑ በግድግዳዎቹ ግቢ በስድስት ምሰሶዎች የተደገፉ ሶስት ቅስቶች አሉበት። እነዚህ ምሰሶዎች ለየብቻቸው ተገንብተው የወጡ ናቸው። ታዛው ደግሞ ዙርያውን በስልሳ አንድ ረጃጅም ምሰሶዎች ተደግፎአል። ጣርያው የተዋቀረባቸው ሰፋፊ ሣንቃዎች በነዚህ ምሰሶዎች ላይ ያርፋሉ። ከሰገነቱ ዙርያ እያንዳንዳቸው ከአስራ ስድስት ቅድ የወርቀ ዘቦ ጨርቅ የተሠሩ አስራ ስድስት ተካፋች መጋረጃዎች ተጋርደዋል። ይህን ሁሉ የሚያስጎበኘን ዓቃቤ ሰዓቱ ነበር። ጉብኝታችንን ከጨረስን በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ መልእተኛ ልኮብን ስለሕንፃውና ስለሌሎቹም ያየናቸው ነገሮች አስተ ያየታችንን ጠየቀን። እኛም መልስ በመስጠት ማለፊያ መሆኑን በመግለጽ የሕንፃው ባለቤት ማን መሆኑን ስለምናውቅ ይህ ውበት

የሚገባው መሆኑን አረጋገጥንለት። ከዚህ በኋላ ይህን ቤተ ክርስቲያን መከደኛ አረር ከፖርቱጋል ሊላክለት ይቻል እንደሆነ ጠየቀ። አምባሳደሩም መልሶ የፖርቱጋል ንጉሥ ማናቸውም የማዕድን ሃብት ስላለው ግርማዊነትዎ ሊያየው የሚችለውን ያህል በብዛት ይልካል አለ።

እርሱ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን በመጋረጃው ውስጥ እኛም በበቅሎቻችን ሆነን ብዙ ስነ ሥርዓት ሳይኖር ተከትለነው እስከ ድንኳኑ ድረስ አደረስነው። ከተማው የተከተመው በዚያ ቤተ ክርስቲያን መልክ በተሠራ ባንድ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ነበር። በከተማው ደርሰን ከበቅሎ ከወረድን በኋላ በዚያ አጠገብ የሚገኘውን የእናቱን ቤተ ክርስቲያን እንድንጎበኝ ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሩን አዞት ወደዚያው ሄድን። ቤተ ክርስቲያኑ እንደ አቅሙ በእውነተኛው በደንብ የተሠራ ነው። ይህን በምንጎበኝበት ጊዜ ምንም እንከን እንዳናወጣለት አስጠነቀቁን፤ ይህን ያሉበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱ እናት በሃሳብዋ የተደቀነውን ነገር መፈጸም እንጂ የማታስብ ሰው በመሆንዋ የቤተ ክርስቲያኑን ጉድለት ቢገግሩዋት ወይም ከልጁዋ ጋር አይተካከልም ያሉዋት እንደሆነ አስፈርሳ ሌላ እንዲሠራ ታዛለች ይባላል። ጉብኝታችንን አብቅተን በዚያው ውስጥ በምንገኝበት ጊዜ መልእክተኛ ልኮ በፖርቱጋል ብዙ ወርቅ ካለ ለምንድን ነው ለእስላሞች ማለፊያ ጨርቅ እየሰጣችሁ ወርቅ የምትሰበስቡ ሲል አስጠየቀን። አምባሳደሩም ለዚሁ መልስ በመስጠት የፖርቱጋል ንጉሥና የባሕር ኃይል ሹማምንቱም ያለማቋረጥ በብዙ ቦታ እስላሞችን ስለሚዋጉ ወጪቸው ከፍ ያለ ነው። ስለዚህ ባይነግዱ ኖሮ ይህን ለማድረግ አይችሉም ነበር። በተለይም ይህን ለማድረግ አስፈላጊ የሆነበት የውጊያዎቹና ገንዘብ የሚያወጡባቸው ቦታዎች እርዳታ ከሚመጠበት ከፖርቱጋል ሩቅ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ በባሕር ላይ በሚጓዙበት ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ሸቀጥ በመርከብ ጭነው እየሄዱ ላንዳንዶች ሲሸጡ ካንዳንዶችም ሲወስዱ በዚህ ዓይነት ወጪቸውን በከፊል ይችላሉ። ለዚህ አስተያየት ምንም መልስ አልተሰጠም። በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኙ የነበሩ በስዕሎች ያጌጡ ሁለት መጋረጃዎችን እንዲያሳዩን አዞ ካየን በኋላ በየት

እንደሚሠሩ አስጠየቀን። እነዚህ ጨርቆች ሁሉ በክርስቲያን አገር እንጂ በሌላ ቦታ አይሠሩም ስንል መለስንለት። የዚያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ መልሶ እነዚህን የመሰሉ ጨርቆች የላካችሁልኝ እንደሆነ ብዙ ወርቅ እልክላችኋለሁ አለን።

አምባሳደሩም መልሶ ግርማዊነትዎ ለፖርቱጋል ንጉሥ ደብዳቤ ቢጽፍ የሚያስፈልገውን ያህል የሚልክ መሆኑን ለንጉሠ ነገሥቱ በመግለጽ ላከበት። ወዲያውኑ ሌላ ብርቱ ጥያቄ ተከትሎ ምንድን ነው ያመጣችሁልኝ ሲል ጠየቀን። ያመጣነውን ገጸ በረከት ሁሉ ማለት አንድ ጌጠኛ ጎራዴ አንዴ ባለ ወርቅ እጀ ታ ጨቤ ሁለት ሰይፎች ከነማህደራቸው አለሎዎችና ባሩድ አራት መጋረጃዎችና ጥሩ ሆነው የተሠሩ የደረት ጋሻዎች ማስረከባችንንና እነዚህንም ገጸ በረከቶች ለምልክት ያህል የላከው ጠቅላይ ገዥው ሲሆን አስፈላጊ ከሆነ ለፖርቱጋል ንጉሥ ቢጽፍ የፈቀደውን ያህል የሚልክልት መሆኑን ለመልእክተኛው አምባባደሩ ገለጸ። መልእክተኛውም ተመልሶ መጥቶ ወደዚህ አገር አምባሳደር የሚልኩ ሁሉ በዙ የልብስ ገጸ በረከት መላክ ልምዳቸው ነበር፤ ይህ ከዚህ በፊት ለነገሠ ነገሥታት ሁሉ የተደረገ ነገር ሲሆን እናንተ ግን ባዶ እጃችሁን መጣችሁ አለን። አምባሳደሩም መልሶ የፖርቱጋል ንጉሥ ወይም ሹማምንቶቹ ሌሎች ነገሥታት ወይም መሳፍንት አምባሳደሮች ወይም መልእክተኞች ሲልኩ በወዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ምንም ገጸ በረከት መላክ አላስለመዱም፤ ይልቁንም የርሱን ወዳጅነት ለመፈለን ሲሉ ነገሥታትና መሳፍንት ሁሉ አስቀድመው ገጸ በረከት ይልኩለታል። የሕንድ ጠቅላይ ገዥ እነዚህን የተጠቀሱትን ዕቃዎች ቢልክም በታዛዥነቱ እንጂ ይህን የመሰለ ልምድ ኖሮ አይደለም። እንዲሁም የፖርቱጋል ንጉሥ በፊት በተላከው ግን እዚህ አገር ሳይደርስ በካማራን ደሴት ላይ በሞተው አምባሳደሩ እጅ ባንድ መቶ ሺ ክሩዛዱሽ የሚገመቱ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ልኮ ነበር፤ እነዚያን ገጸ በረከቶች ቢልክም የተለመደ ነገር ለመፈጸም ወይም ግዴታ ኖሮበት ሳይሆን በወንድምነት ብቻ ነው።

ከፖርቱጋል ንጉሠ የተላከልኝ ብዙ ገጸ በረከት አልደረሰኝም ሲል ንጉሠ ነገሥቱ ቅር ስለመሰኘቱ አምባሳደሩ በመደጋገም በጠቅላይ

ገዥው ደብዳቤ ላይ እንደተገለጸው የተላኩት ዕቃዎች የቶቹ መሆናቸውን ለመረዳት የሚቻል መሆኑን፤ እንዲሁም እንደ ፖርቱጋል ንጉሥ ያሉ ነገሥታት ሁል ጊዜ ጉዳያቸውን የሚያከናውኑት በንብረት ሹሞቻቸውና በጸሐፊዎቻቸው አማካይነት በመሆኑ የተላኩት ገጸ በረከቶች ሁሉ በሕንድ የሚገኙ መሆናቸውን ከነዚሁ ሰዎች ለማወቅ የሚቻል መሆኑን አስረድቶ ነበር። ምንም እንኳ ወኪሎቹ ቢላኩም ፖርቱጊዞች የተጣለባቸውን አደራ በታላቅ ታማኝነት መፈጸም እንጂ የሃሰት ተግባር የሌለባቸው መሆናቸውን እንዲሁም እውነተኛውን ነገር በመደጋገም ብዙ ጊዜ ጨምሮ ገለጸ። ስለዚህ እውነተኛውን ነገር ሊያምን ከፈለገ እንዲሁም ካልፈቀደ ያሻውን ለማድረግ የግርማዊነቱ ፈንታ መሆኑን አስገነዘበ። አምባሳደሩም ወቀሳውን በመቀጠል እኔ ወደዚህ የመጣሁበት የፖርቱጋል ንጉሥ እንደራሴ ሆኖ ሕንድን የሚገዛው ጠቅላይ ገዥው ሹሞኝ ሲሆን የተላክሁበት አኳኋን ለሌሎች ንጉሠ ነገሥታትና መሳፍንት አምባሳደር በሚላክበት አኳኋን ነው። በፖርቱጊዞች ዘንድ ባልተለመደ ነገር አይጠርጥሩኝ፤ ይልቁንስ መሄጃዬ ጊዜ ስለደረሰ ቢያሰናብቱኝ ይሻላል፤ ሲል ለመነ።

ንጉሠ ነገሥቱም መልሶ በቀድሞቹ ነገሥታት ዘመን እንዳሁኑ ባዶ እጃሁን ብትመጡ ኖሮ እኔ ያደረግሁላችሁን ክብርና አቀባበል አታገኙም ነበር ሲል ላከብን። አምባሳደሩም ለንጉሠ ነገሥቱ ቃል መልስ በመስጠት በዚህ አገር ከገባን በኋላ ልዩ ልዩ ጉዳት ደርሶብናል፤ ማናቸውም ሃብታችን ተሰርቆብን ያለ ልብስ እንኳ ቀርተናል፤ ለስንቃችንም የያዝነው በሙሉ ተሰርቆብናል፤ በእውነኛው በዚህ አገር ሶስት ወይም አራት ጊዜ ሊገድሉን ሞክረው ነበር፤ ነገር ግን እኛ ለእግዚአብሔርና ዜጎቹ ለሆንነው ለፖርቱጋል ንጉሠ ፍቅር ስንል ማናቸውንም ነገር በትዕግሥት አሳለፍነው፤ ስለዚህ እኛ ሁላችንም በዚህ አገር ብንሞት በትዕግሥት ያሳለፍናቸው ብዙ ነገሮች በሰማዕትነት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ያበቁናል። ማቴዎስ የግርማዊነትዎ አምባሰደር ነኝ ስላለ የፖርቱጋል ንጉሥ በጣም ነበር ያከበረው። የሆነ ሆኖ ፖርቱጊዞች እውነተኛ ነገርን ማድረግና መናገር ስለሆነ የሚፈቅዱት ያየነውን ነገር እንድንናገር በቶሎ

ስንብት እንዲሰጡን እንለምናለን ሲል ማናቸውንም ነገር ዘርዝሮ አመለከተ። የዚህን ጊዜ መልእክተኛው መጥቶ ፖርቱጌዞቹ ወይም አምበሳደሩ ሳንሆን ያበለው ማቴዎስ መሆኑን ገለጸልን፤ ስለዚህ እንዳትቀየሙ አስደስተን እንልካችኋለን፤ አሁን ወደ ምግባችሁ ልትሄዱ ትችላላችሁ ብሎን ተለያየን።

ምዕራፍ ዘጠና ስድስት፤ እኛና ሌሎቹም ፈረንጆች የጥምቀትን በዓል ስነ ሥርዓት እንድንመለከት ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ።

ጥር 4 ቀን ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮብን ጸሎት ማድረጊያ ድንኳናችንን ነቅለን ከዚያ ቦታ ግማሽ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኘው ወደ ጥምቀተ ባሕሩ እንድንሄድ አዘዘን። ይህ ቀን ክርስቶስ የተጠመቀበት ቀን ስለሆነ ይህንኑ ለማስታወስ በያመቱ ይጠመቃሉ። ወደዚሁ ቦታ አንዲት ትንሽ ድንኳን ለመጸለያችንና ለማረፊያችንም ይዘን ሄድን። በማግሥቱ የጥምቀት ዋዜማ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶን ያ ገንዳ የነበረበትን የታጠረ ቦታ ጎበኘን። ይህ በቁጥ ቋጦዎች የታጠረ ትልቅ ቦታ የሚገኘው ባንድ ሜዳ ላይ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም መልእክተኛ ልኮ ለመጠመቅ ትፈልጋላችሁን ሲል አስጠየቀን። ለዚሁም እኔ መልስ በመስጠት በሕፃንነታችን ጊዜ ስለተጠመቅን ለሁለተኛ መጠመቅ አያስፈልገንም አልሁ። ከኛ ሰዎች አንዳንዶቹ በተለይም አምባሳደሩ ግርማዊነታቸው ያዘዙትን መፈጸም አለብን አሉ። ይህን ካሉ በኋላ እንደገና መልእክተኛ ልከው ለመጠመቅ እንፈቅድ እንደሆነ እንድንነግራቸው ጠየቁን፤ እኔም ከዚህ በፊት የሰጠኋቸውን መልስ ደገምሁላቸው።

እንደገናም መልእክተኛ ልከውብን በገንዳው ውስጥ ለመጠመቅ የማትፈልጉ ከሆናችሁ እድንኳናችሁ ድረስ ውኃ እንልክላችኋላን አሉን። የዚህን ጊዜ አምባሳደሩ ግርማዊነታቸው ያዘዙት መፈጸም አለበት አለ። ፈረንጆቹና የኛ ሰዎች ልዩ ዝማሬ አዘጋጅተው ይህንኑ

ለማሰማት መፍቀዳቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ ላኩበት። ወዲያውኑ ተፈቅዶልን በገንዳው አጠገብ በአጥሩ ውስጥ ለማሰማት ሄድን። ይህ ዝማሬ ደህና አቀባበል አላገኘም ነበር፤ እንዲያውም ችላ አሉት። በጠቅላላው ቀዝቃዛ ነገር ሆኖ ቀረ። ጊዜው መሽቶ ስለነበር ከዚያ እምብዛም ርቆ ወደማይገኘው ድንኳናችን እንድንሄድ አሰናበቱን። ሌሊቱን ሁሉ እስከንጋት ድረስ ውኃውን በመባረክ በገንዳው አጠገብ ሲያዜሙ አድረው በግምት እኩለ ሌሊት ሲሆን ጥምቀቱን ጀመሩ። ሲያወሩ እንደሰማሁትና ሊታመንም እንደሚቻለው በመጀመርያ የሚጠመቀው ንጉሠ ነገሥቱ፤ ቀጥሎም አቡኑ፤ ቀጥሎም እቴጌይቱ ናት ይባላል። እነዚህ ሶስቱ ሰዎች ነውራቸውን ለመሸፈን ያህል ጨርቅ ሲያሸርጡ የተቀሩት ሰዎች ግን እርቃን ሥጋቸውን ነው ገብተው የሚንቦጫረቁት። የጸሐይ መውጪያ ጊዜ ከተቃረበ በኋላ ሕዝቡ በብርካቴ ገብቶ በሚጠመቅበት ጊዜ ገብተን እንድንመለከት ንጉሠ ነገሥቱ አስጠራኝ። በዚያ ሄጄ እስከ ሶስት ሰዓት ጸሎት ጊዜ ድረስ ሰዎቹ ሲጠመቁ አየሁ። በጉድጓዱ ዳር ከንጉሠ ነገሥቱ ገጽ ለገጽ አቁመውኝ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ሲጠመቁ አይቻለሁ።

ጉድጓዱ በአራት መዓዘን የተቆፈረ ሰፊና በጣም ጥልቅ ነው። በሳንቃ ተነጥፎ ሳንቃው ደግሞ ሰም በተነከረ ጨርቅ ተሸፍኖአል። ውኃው ወደ መስኖ አትክልት የሚመጣ ይመስል ካንድ ወንዝ እጉድጓዱ ድረስ ይመጣና ከዚያም በኋላ በቡዋንቡዋ ከጉድጓዱ ይገባል። ውኃው የሚገባው እየተጣራ ስለሆነ ከቡዋንቡዋው አፍ ላይ ከረጢት ታስሮ ይታያል። (እኔ ባየሁት ጊዜ ውኃው አይፈስም ነበር።) ጉድጓዱ በተባረከ ውኃ ተመልቶ ይታይ ነበር። እንደሚባለውና እንዳረጋገጡልኝም ቅብአ ቅዱስም አለበት። በጉድጓዱ ባንድ በኩል አምስት ወይም ስድስት ደረጃ አለው። ከደረጃው ፊት ለፊት ሰባት ክንድ ያህል ርቆ ንጉሠ ነገሥቱ ተቀምጦበት የነበረው መደብ ተሠርታል። በመደቡ ዙርያ የሰማያዊ ጨርቅ መጋረጃ ተጋርዶ የሚጠመቁትን ሰዎች ለመመልከቻ አንድ ስንዝር ያህል መካከሉ ተቀዶአል። የልደት በዓል ዕለት ከኔ ጋር የነበረው የንጉሠ ነገሥቱ መምሕር ሽማግሌ ቄስ እርቃን ሥጋውን ሆኖ (ሌሊቱን ኃይለኛ አመዳይ ጥሎ

ስለነበር) በዚያ ብርድ ራቁቱን ተቆራምዶ አንገቱ ድረስ በውኃው ውስጥ ሆኖ ይጠመቅ ነበር። የሚጠመቁት ሰዎች ራቁታቸውን ውኃው ውስጥ ለመግባት በደረጃው ሲያልፉ ጀርባቸውን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መልሰው ነው። እንዲሁም ተጠምቀው ሲወጡ በዚያው ስለሆነ የሚያልፉት ሴቶቹም ሆኑ ወንዶቹ የፊት ሰውነታቸውን እያሳዩ ነው የሚያልፉት። ተጠማቂዎቹ ወደቄሱ ሲቀርቡ እጁን በራሳቸው ላይ ይጭንባቸውና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሃለሁ እያለ ሶስት ጊዜ በውኃው ውስጥ ያጠምቃቸውና በመስቀሉ ይባርካቸዋል። ተጠማቂዎቹ አጫጭር ሰዎች ከሆኑ ግን ደረጃዎቹን በሙሉ ሳይወርዱ በመካከል እንዳሉ ቄሱ ይቀርባቸውና ያጠምቃቸዋል። እኔ ከጉድጓዱ ማዶ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊትለፊት እንድሆን አዘውኝ ስለነበር ተጠማቂዎቹ ወደ ውኃው ሲገቡ ንጉሠ ነገሥቱ ኋላቸውን ሲያይ እኔ ደግሞ ፊታቸውን ሲወጡ ደግሞ ሌላው በኩል ይታየኝ ነበር። የተጠመቁ ብዙ ሰዎች ካለፉ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ወደርሱ ዘንድ አስጠርራኝ፤ በጣም ተጠግቼ ስለነበር የቆምሁት አቃቤ ሰዓቱ የንጉሡን ቃል ሰምቶ ለአስተርጓሚ ለመንገር ወዲያ ወዲህ መመላለስ አላስፈለገውም ነበር። በመጀመርያ የቀረበልኝ ጥያቄ ስለ ስነ ሥርዐቱ ምን አስተያየት እንዳለኝ ነበር። ለዚሁም መልስ በመስጠት በቅን ልቡና እግዚአብሔርን ለማገልገልና እርሱንም ለመወደስ የተፈጸሙ ነገሮች ሁሉ የሚመሰገኑ ናቸው፤ ነገር ግን ይህን የመሰለ ስነ ሥርዐት በኛ ቤተ ክርስቲያን ካለመኖሩም ይልቅ ይህ የክርስቶስ የጥምቀት ቀን ሲሆን እኛም በዚሁ ቀን ተጠምቀን በክርስቶስ ቀን ተጠመቅን የማለት ስሜት እንዳያድርብን በማለት ይህን የመሰለው ተግባር እንዳይደረግ ተከልክሎአል። ስለዚህ ጥምቀትን የመሰለ የተቀደሰ በረከት ካንድ ጊዜ በላይ እንዳይሰጥ ቤተ ክርስቲያን ከልክላለች ስል መለስሁለት። ወዲያውኑ ጥያቄውን በማስከተል ሁለተኛ መጠመቅ ተከልክሎአል የሚል ቃል ተጽፎ ይገኛልን ሲል ጠየቀኝ።

እኔም መልሼ ሶስት መቶ አስራ ስምንት አበው በተገኙበት በጳጳስ ሌዎን ጉባኤ ላይ በተደነባው መሠረት የተጻፈ ቃል አለ፤ ይህም ቃል ቀጥሎ የተመለከተው ነው፤ «ለኃጢአቴ ስርየት አገኝ

ዘንድ እናዘዛለሁ እጠመቃለሁም።» ይህ ነገር እውነት መሆኑና በመጽሐፍትም ውስጥ ተጽፎ መገኘቱን አረጋገጡልኝ። ነገር ግን ከክርስትና ወደ እስላምነት ወይም ወደ አይሁድነት ተለውጠው የተናዘዙትን ሰዎችና በጥምቀት በደንብ የማያምኑትን ሰዎች ምን ማድረግ ይገባል ወይስ ምን ይበጃቸዋል ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም ቀጥሎ የተመለከተውን መልስ ሰጠኋቸው፤ በደንብ ላላመኑት ትምህርትና ስብከት በቂያቸው ነው፤ ነገር ግን ይህ የማይበቃቸው ከሆነ እንደከሃዲያን ተቆጥረው ማቃጠል ነው። የክርስቶስን ቃል ቅዱስ ማርቆስ እንዲህ ሲል ጽፎታል፤ ያመነና የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል። የእስላምን ወይም የአይሁድን ሃይማኖት ከተቀበሉ በኋላ በገዛ ራሳቸው ፈቃድ ስህተታቸውን ተረድተው ምሕረት የሚጠይቁትን አቡኑ ለነፍሳቸው በመማለል ኃጢአታቸውን ሊሽሩላቸው ይችላሉ፤ ይህንንም ማድረግ የሚችሉት ሥልጣን ካላቸው ብቻ ነው። ከሌላቸው ግን ሥልጣን ሁሉ በእጁ ለሆነው ወደሮም ጳጳስ መሄድ አለባቸው። በኃጢአተኛነታቸው በማዘን የማይጸልዩትን ግን በፈረንጅ አገርና በሮም ቤተ ክርስቲያን እንደሚደረገው ሁሉ ማቃጠል ነው። የዚህን ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱ ቃል መጥቶ በሃሳቡ የሚስማማበት መሆኑን ገለጸልኝ። ይሁን እንጂ ይህን ጥምቀት ያዘዘው ከታላላቅ ቀሳውስት ከተመካከረ በኋላ አያቱ ሲሆን የታዘዘበትም ምክንያት ብዙ ነፍስ እንዳይጠፉ ሲባል ነበር፤ ይህም ልምድ እስካሁን ድረስ ጸንቶ ቆይቶአል አለ። ንግግሩንም በመቀጠል የሮም ጳጳስ አስፈላጊውን ሥልጣን ለአቡኑ የሰጠ እንደሆነ ለዚሁ ምን ያህል እንደሚከፈልና ለማግኘትስ የቱን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅ ጠየቀኝ። እኔም መልሼ የሮም ጳጳስ የሰውን ነፍስ ከማዳን በስተቀር ሌላ ምኞት ስለሌለው አቡኑን አስፈላጊውን ሥልጣን ሰጥቶ መላክ አስፈላጊ ነገር መሆኑን ገለጽሁለት፤ ለዚሁም የሚያስፈልገው የመንገዱ ዋጋና የግርማዊነትዎ ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን የሚያረጋግጥ ጸሑፍ ብቻ ነው። አቡኑ በፖርቱጋል በኩል የሄደ እንደሆነ መንገዱ ደርሶ መልስ ሶስት ዓመት ይፈጅበታል፤ በየሩሳሌም በኩል የሄደ እንደሆነ ግን ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅበት አላውቅም አልሁ። ከዚህ በኋላ ምንም መልስ ወይም ጥያቄ ስላልተከተለ እንድሄድና ቅዳሴ እንዳደርስ አዘዙኝ፤ ነገር ግን ጊዜው ከእኩለ ቀን አልፎ ስለነበር የቅዳሴ

መግቢያ ጊዜ አይደለም ብያቸው ምሳ ለመብላት ወደኛ ሰዎችና ወደ ፈረንጆቹ ሄድሁ።

ጥምቀተ ባሕሩ ልዩ ልዩ ቀለም ባላቸው ድንኳኖች ዙርያውን ተከቡዋል፤ ብዙ ብርቱካንና ሎሚ ቅርንጫፎችም በቦታው ተተክው የጸደቁ ይመስላሉ። በላይ በኩል የነበረው ድንኳን በጣም ሰፊና ጣርያውም ባንድ ዋልታ ተወጥሮ የኮራ ነው፤ ጣርያው በሙሉ በቀይና ሰማያዊ የጨርቅ መስቀሎች አጊጦአል።

በዚሁ ቀን ወደ ማታ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሩን ከነጭፍሮቹ አስጠራው። የጥምቀቱ ስነሥርዐት ተፈጽሞ ነበር፤ ነገር ግን እንጉሣዊው ድንኳን ድረስ ሄደን በዓሉ እንዴት ይመስላችኋል ሲሉ አምባሳደሩን ጠየቁት። አምባሳደሩም መልሶ ምንም እንኳ ይህን የመሰለ ልምድ በኛ ዘንድ የማይከበር ቢሆንም ሃሳቡ መልካም መሆኑን ገለጸ። በዚህ ጊዜ ውኃው ከቡዋንቡዋው ወደ ጉድጓዱ ይፈስ ስለነበር ከኛ ከፖርቱጌዞቹ ውስጥ ዋና የሚችል ሰው አለወይ ሲል ንጉሠ ነገሥቱ አስጠየቀን። ወዲያውኑ ሁለት ሰዎች በውኃው ውስጥ ዘለው በመግባት የጉድጓዱ አቅም እስከሚፈቅደው ድረስ ዋናና ውስጥ ለውስጥ መሄድን አሳዩ፤ እነዚህ ሰዎች ባሳዩት ቅልጥፍና ንጉሠ ነገሥቱ የተደሰተ መሆኑን ከፊቱ ላይ ለማየት ይቻል ነበር። ከዚህ በኋላ ወደውጭ እንድንወጣና ከአጥሩ ጥግ እንድናርፍ አዘዘ፤ በዚህ ቦታ እንዳለን ባገሩ ልምድና ወግ መሠረት ምግብና ጠጅ ተዘጋጅቶ ግብር ቀረበን። ንጉሠ ነገሥቱ ወደከተማው ለመመለስ ስለፈለገ ድንኳናችንን ነቀልን። ቀድመን እንድንሄድ አዘዘ። ቀድመን እንድንሄድ የታዘዝንበት ፈረሰኞች ከእስላሞች ጋር ሲዋጉ የሚያደርጉትን የጦር ስልት የሚያሳይ ጉግስ እየተጫወቱ ሲሄድ እንድናይ ነበር። በዚህ አኳኋን ጉግሱን እያየን ስንሄድ በድንገት ኃይለኛ ዝናም መጣል ጀምሮ ፈረሰኞቹ የጀመሩትን ለመጨረስ አልቻሉም ነበር።

ምዕራፍ ዘጠና ሰባት፤ ካንድ አስተርጓሚ ጋር ሆኜ አቡነ ማርቆስን ልጎበኝ ስለመሄዴ፤ ስለግዝረት ሃሳብ ስለመለዋወጣችን፤ አቡኑ ክህነት ስለመስጠታቸው።

የጥምቀት ማግሥት አቡነ ማርቆስን ለመጎብኘት ሄድሁ፤ አቡነ ማርቆስን በጥምቀተ ባሕሩ ብርድ በጣም ቆፍኖአቸው አየኋቸው እንጂ ከዚህ በፊት አይቻቸው ወይም ጎብኝቻቸው አላውቅም ነበር። ስለአደረግሁት ጉብኝት በጣም ተደስተው ነበር፤ እጃቸውን ልስማቸው ስጠጋ በመዘርጋት ፊንታ ጫማዬን ሊስሙ የፈለጉ ይመስል ወደ ምድሩ ዝቅ አሉ። ከዚህ በኋላ ሁለታችንም ባንድ አልጋ ላይ ተቀምጠን ለመቀራረብ ላበቃን አምላክ ምስጋናችንን አቀረብን።

ንግግራቸውንም በመጀመር እኔ ያልሁትን ነገር ሁሉ ነግረዋቸው ስምተው ስለነበር መደሰታቸውን፤ በጥምቀተ ባሕሩና እንዲሁም በልዩ ልዩ ቦታ ለንጉሠ ነገሥቱ ማናቸውንም ነገር ግልጽ አድርጌ በመናገሬ የተደሰቱ መሆናቸውን ገለጹልኝ። አቡኑ ብቻቸውን በመሆናቸው ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ የርሳቸውን ቃል የማይሰማ መሆኑን አስረድተውኝ አንድ ወይም ሁለት ረዳቶች ቢኖሩዋቸው ኖሮ ንጉሠ ነገሥቱንና ሕዝቡን ከብዙ ስህተት የሚያድኑ መሆናቸውን ጨምረው ነገሩኝ። ይህን በምንነጋገርበት ጊዜ በዚያው አገር ተወልዶ ያደገ አንድ ግብጻዊ ቄስ መጣና ክርስቶስ የተገዘረ መሆኑ የታወቀ ሲሆን እናንተ የማትገዘሩት በምን ምክንያት ነው ሲል ጠየቀኝ። እኔም መልሼ ክርስቶስ የተገዘረ መሆኑ የታወቀ ነው፤ ይሁን እንጂ ይህን ማድረጉ ሕግ ጣሰ ተብሎ እንዳይከሰስ ጸንቶ የቆየውን የኦሪትን ሕግ ለመፈጸም ነው። ከዚያ በኋላ ግን ግዝረት እንዲቀር ተደርጓል አልሁት። ይህ ቄስ መልሶ የኔ አባት ፈረንጅ ስለነበር በሕፃንነቴ ወራት አላስገዘረኝም ነበር፤ ነገር ግን አባቴ ከሞተ በኋላ ሃያ ዓመት ዕድሜ እንደ ነበረኝ አንድ ቀን ብቻዬን ተኝቼ በማግሥቱ ጥዋት ተገዝሬ ተገኘሁ፤ እንግዲህ እግዚአብሔር ግዝረትን ካልፈቀደ የዚህ ምስጢሩ ምንድን ነው ሲል ጠየቀኝ። ለዚህም መልስ በመስጠት ይህ ነገር ትልቅ

ስህተት ሊሆን ይችላል፤ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ግዝረትን ባይከለክልም ከጎዶሎነት ወደ ፍጹምነት ሊለውጥህ ወይም ተአምራት ሊሠራልህ የሚያበቃህ ተግባር ወይም ቅዱስነት የለህም፤ ከተኛ ሁበት ስነቃ ተገዝሬ ተገኘሁ ብለሃል፤ ይህን ያደረገው ሰይጣን ይሆናል ሊቀልድብህ ስል መለስሁለት። በዚህን ጊዜ አቡኑና በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ መሳቅ ጀመሩ፤ አቡኑም በጣም ተደሰቱ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህ ቄስ የኔና የፖርቱጊዞቹ ሁሉ ታላቅ ወዳጅ ከመሆኑም በላይ በየዕለቱ ወደኛ ጸሎት ቤት እየመጣ ያስቀድስ ነበር። እዚያ ላለነው ጠጅና ፍሬ እንዲመጣልን አቡኑ አዘዙ። እንዲሁም ወደ ድንኳናችን ከኔ ጋር ብዙ እንጀራና ጠጅ አንድ ፍሪዳም አዘዙልን።

እኔ በተገኘሁበት ጥር 8 ቀን አቡነ ማርቆስ ክህነት ሲሰጡ አየሁ። ሰው በማይኖርበት ባንድ ትልቅ መስክ ላይ ትልቅ ነጭ ድንኳን ተተክሎ አምስት ወይም ስድስት ሺ ሰዎች ለክህነት ቀርበው ነበር። አቡኑ በበቅሎዎቻቸው ተቀምጠው ብዙ ሰው አጅቦአቸው ወደተባለው ቦታ ሄዱ። በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ባንድ ቄስ አስተርጓሚነት በአረብኛ ንግግር አደረጉ። አስተርጓሚው እንደ ገረኝ በንግግራቸው ላይ ሁለት ወይም ከዚህ የሚበልጡ ሚስቶች ያገባ ሰው ዳግመኛ ማግባቱ በመጀመሪያይቱ ሚስቱ ሞት ምክንያት ቢሆንም የቅስና ሥልጣን አይሰጠውም፤ ነገር ግን ሥልጣን ተቀብሎ የቀሰሰ እንደሆነ የሚገዝቱት መሆናቸውንና እግዚአብሔር የረገመው ነው ተብሎ የሚቆጠር ነው ሲሉ ማስጠንቀቃቸውን ነገረኝ። ንግግራ ቸውን ከጨረሱ በኋላ ከድንኳኑ ፊት በተዘጋጀው ወንበር ላይ ሲቀመጡ ከርሳቸው ፊት መጽሐፍ የያዙ ሶስት ቄሶችና ሌሎችም ስነ ሥርዓቱን የሚመሩ ሰዎች ተቀመጡ። ለክህነት የቀረቡት ሁሉ በተረከዛቸው ላይ ቁጢጥ ብለው እንዲቀመጡ አዘዙዋቸው። ከዚህ በኋላ በሶስት ረጃጅም ረድፍ የገቡና መጽሐፍ ይዘው ወደ ተቀመጡት ሰዎች አንድ በአንድ ይቀርቡና እነዚህም ፈተና ያቀርቡላቸዋል። ፈተናው የንባብ ችሎታ ብቻ ሲሆን እያንዳንዱ ሰው ከሁለት ወይም ከሶስት ቃላት በላይ አያነብም። እነዚህ ካለፉ በኋላ አንድ ቀንድ ቀለምና ማህተም ይዘው በስተኋላ ወደቆሙት ሰዎች ሲሄዱ እነዚህም

በቀኝ ውስጥ እጃቸው ላይ ያትሙባቸዋል። ከዚህ በኋላ ብድግ ብለው ይሄዱና የተካኑት ሁሉ ባንድነት ተጣበው ይቀመጣሉ። ፈተናው በጣም ቀላል በመሆኑ የማያልፉት ጥቂቶች ናቸው።

ይህ ስነ ሥርዓት ካለቀ በኋላ አቡኑ በድንኳናቸው ገብተው በወንበር ላይ ተቀመጡ። ድንኳኑ ሁለት በር ስላለው የተፈተኑት ሰዎች ባንድ ረድፍ ሆነው ባንድ በር ገብተው በሌላው በመውጣት በአቡኑ ፊት ያልፋሉ። የዚያን ጊዜ አቡኑ በያንዳንዳቸው ራስ ላይ እጃቸውን እየጫኑ ትርጉሙ ያልገባኝ አጭር ቃል ይናገራሉ። የተሰ በሰቡት ሰዎች ሁሉ በዚሁ ዓይነት ስነ ሥርዐቱን ተካፈሉ። በዚህ ጊዜ አቡኑ ራሳቸው አንድ መጽሐፍ ገልጸው ጥቂት ካነበቡ በኋላ ከርሳቸው ጋር የነበረው አንድ ቄስ ከድንኳኑ ውጭ ወጥቶ ከሐዋርያት መልእክት ወይም ከወንጌል አነበበ። ከዚህ በኋላ አቡኑ ቅዳሴ ገብተው አጭር ጸሎት ተደረገ፤ ለቅዳሴው ያስፈለገው ጊዜ «አምላክ ሆይ ምሕረትህን ስጠኝ» የሚለውን መዝሙረ ዳዊት ሶስት ጊዜ ለማንበብ የሚፈጀውን ጊዜ አይበልጥም ነበር። ቄሶቹና ዲያቆኖቹ ለየብቻቸው ስለሆነ የሚቀርቡት በዚህ ቀን ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ ሰባት ቄሶችን በሌላው ቀን ደግሞ ዲያቆኖችን አቀረቡ። ዲያቆኖቹ እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ በማናቸውም ማህበር ዲቁናን የሚቀበሉ መሆና ቸውን አቡኑ ራሳቸው ነገሩኝ። በሌላ ቀን ደግሞ ዲያቆኖችንና ቄሶችን ባንድነት ክህነት ሲሰጡ አይቻለሁ። ከዚያም በኋላ በዚሁ ዓይነት በየቀኑ ለብዙዎች ክህነት ሲሰጡ ነበር። በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት በሙላ ሥልጣን የሚሰጥ ሌላ አቡን ባለመኖሩ ከልዩ ልዩ አውራጃዎች በየቀኑ በብዛት ይመጣሉ። ክህነት የሚቀበሉት ሰዎች አይመዘገቡም ወይም ክህነታቸውን የሚያረጋግጥላቸው የምስክር ወረቀት አይሰጣቸውም። ከዚህ በላይ የቄሶቹን ቁጥር 2357 ነው ስል ጠቅሼ ነበር፤ ይህን ቁጥር መስጠቱ እኔ ቆጥሬአቸው ሳይሆን እንዲቆጥር የታዘዘው ሰው ነግሮኝ ነው። ቁጥሩም ትክክለኛ ለመሆኑ አልጠራጠርም። ስለዲያቆናት ክህነት ደግሞ በሚቀጥለው ምዕራፍ እገልጻለሁ።

ምዕራፍ ዘጠና ስምንት፤ ስለቅዱሳን ማህበር ስነ ሥርዓት ንጉሠ ነገሥቱ ጥያቄ አቀረበልኝ፤ ዲያቆናት ክህነት ሲቀበሉ አየሁ።

በማግሥቱ ጥር 9 ቀን ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶኝ ቀረብሁ፤ ወዲያው እንደደረስሁ መልእክተኛ መጥቶ ወደክህነቱ ቦታ ሄደህ ክህነት ሲሰጥ አይተሃልና አስተያየትህን ስጥ አለኝ። እኔ ራሴ ባላያቸው ኖሮ ወይም ያየ ሰው በመሃላ እንኳ ቃሉን ቢያጸናልኝ ላምናቸው የማልችል የነበሩ ሁለት ነገሮች አይቻለሁ፤ ከነዚህም አንደኛው ግርማዊነታቸውን ሊቀበሉ የመጡት ካህናትና የመስቀሎቹ ብዛት ሲሆን ሌላው ደግሞ ክህነት ሲቀበሉ ያየኋቸው ሰዎች ብዛት ነው። የክህነቱ ሥርዓት መልካም ይመስላል፤ ነገር ግን መልካም ነገር መስሎ ያልታየኝ ሥልጣን ሊቀበሉ የመጡት ሰዎች የቀረቡበት አኳኋን ነው። ስለዚህ በነዚህ ሰዎች ክህነት ሥርዓት ላይ አንድ ዋና የቤተ ክርስቲያን ሕግ ሲጣስ አይቻለሁ በማለት መልስ ሰጠሁ። ወዲያውኑ መልእክተኛ መጥቶ ግርማዊነታቸውን ለመቀበል የመጡት ካህናት በቀበሌው ባሉት ደብሮች የሚገኙት ብቻ ናቸው፤ እነዚህም ከቀድሞ ነገሥታት የተሰጣቸው ጥምጥምና ድባብ መስቀልም አላቸው፤ በየጊዜው ለክህነት የሚቀርቡት ሰዎች ቁጥር አምስት ወይም ስድስት ሺ ሲሆን አሁን ሥልጣን የተቀበሉት ቁጥር ትንሽ ነው፤ ይህ የሆነበት ምክንያት አቡኑ የሚመጡበትን ቀን ባለማወቃቸው ምክንያት ነው ሲል አስረድቶኝ፤ የማይገባ ነገር ሲፈጸም አይቻለሁ ያልሁትን ነገር በደንብ እንድገልጽለት ጠየቀኝ። የማይገባ ነገር ነው ያልሁት ምስጢር የሚያዩና የአምላክንም ሥጋ የሚቀበሉ ሰዎች ነውራቸውን እያሳዩ ተራቁተው መምጣታቸው ነው፤ አዳምና ሔዋን በኃጢአታቸው እንደወደቁ ራቁታቸውን መሆናቸውን ስለተረዱት በአምላክ ፊት ስለሚቀርቡ ሰውነታቸውን ሸፍነዋል።

እንዲሁም አንድ ዓይነ ሥውር ሥልጣን ለመቀበል ቀርቦ ነበር፤ እንግዲህ ይህ ከቶ ለማየት የማይችል ሰው እንዴት አድርጎ ይሆን የቅስናን ተግባር ሊያከናውን የሚችል? ከዚህም በላይ ቀኝ እጁ ፈጽሞ ሽባ የሆነ አንድ ሰውዬ እንዲሁም አራት ወይም አምስት

የሚሆኑ አንካሶችም ቀርበው ነበር። አንድ ቄስ በፍጹም የአካል ጉድለት የሌለበት መሆን ሲገባው እነዚህ ሰዎች ሥልጣን ሲቀበሉ አይቻለሁ አልኳቸው። ወዲያውኑ መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ ማናቸውንም ነገር በትክክል ከተመለከትሁ በኋላ የማይገቡ መስለው የታዩኝ እንዲታረሙ ስል አስተያየቴን በመስጠቴ ንጉሠ ነገሥቱ የተደሰተ መሆኑን ነገረኝ። ስለተራቆቱት ቄሶች ግን በተለይ የሚታ ሰብበት መሆኑን ገለጸልኝ። ስለ አካለ ጎዶሎዎች ጉዳይ ደግሞ በዚያው ስነ ሥርዓት ላይ ተገኝቶ ለነበረው ለአዛዥ ሩፋኤል እንድነግረው አዘዘኝ። አዛዥ ሩፋኤል እኛ በቤተ መንግሥቱ በደረስን ጊዜ ባልደረባ የተሰጠን በጣም የተከበረ ቄስ ነው። ከዚያን በኋላ ምሳ ለመብላት ወደርሱ ድንኳን ሄድሁ። ምሳ ከመቅረቡ በፊት አንድ መጽሐፍ አስመጥቶ ቄስ የአካል ፍጹምነት እንዲኖረው ይገባል የሚል ጥቅስ አነበበልኝ። እኔም መልሼ መጽሐፉ የሚናገረው እውነት ነው፤ አንድ ቄስ በዕድሜውም፤ በፍርዱም በትምህርቱም በአካሉም የተሙዋላ መሆን አለበት አልሁት። እነዚያ ያየሁዋቸው አካለ ጎዶሎ ያልኳቸው ደግሞ በእርግጥ በእጃቸው ላይ ጉድለት ያለባቸው ናቸው። በተለይ ዓይነ ሥውሩ እንዴት አድርጎ ተማረ እንዴትስ ይሆን ቅዳሴ ሊያደርግ የሚችል? አዛዡም መልሶ መጽሐ ፉችሁ እንዲህ ይል እንደሆነ የተናገርኸው እውነት ነው አለኝ። መጽሐፉችን ስለዚህ ጉዳይ በሃተታ የሚናገር መሆንን አረጋገጥሁለት። እርሱም መልሶ እነዚህ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን ምጽዋት ባያገኙ ኖሮ ምን ሠርተው ሊበሉ ይችሉ ኖሮአል ሲል ጠየቀኝ። ለዚሁም መልስ በመስጠት በዚህ አገር ምን ሠርተው እንደሚበሉ አላውቅም፤ በኛ አገር ግን እንደነዚህ ያሉት ሰዎች ለየቤተ ክርስቲያኑና ለየገዳማቱ እየተሰጡ ለሚያደርጉት አገልግሎት ምጽዋት ያገኛሉ። ዓይነ ሥውሮችም የሙዚቃ መሣርያ እየመቱ ደወል እየደወሉና ሌሎችንም በዚህ አገር የማይገኙ ነገር ግን በኛ አገር ያሉ ተግባሮችን እያከናወኑ ይተዳደራሉ። በገዳሞችና በቤተ ክርስቲያኖች ያልሠሩ እንደሆነ ነገሥታቱ በየከተማው ለዓይነ ሥውሮች፤ ለአካለ ጎደሎዎችና ለድ ውያን መጠጊያ የሚሆኑ ታላላቅ ሆስፒታሎች አሉዋቸው። አዛዡም መልሶ የተናገርሁት ማናቸውም ነገር መልካም መሆኑን ገልጾልኝ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ነገር የሰማ እንደሆነ ይደሰታል አለኝ።

ጥር 10 ቀን አቡኑ ዲቁና ሰጡ። ዲቁናውን የሚቀበሉት በወላጆቻቸው እቅፍ ካሉ ገና መናገር ከማይችሉ ሕፃናት ጀምሮ እስከ አስራ አምስት ዓመት ዕድሜ የደረሱ ታናናሾች ወንዶች ልጆች ስለሆኑ ምንም ዓይነት ፈተና አይደረግላቸውም። ወጣቶቹ ክህነት ከመቀበላቸው በፊት ሚስት ማግባት የለባቸውም፤ ያገቡ እንደሆነ ግን ክህነት ሊቀበሉ አይችሉም። ዲያቆኖች ሚስጢር የሚያዩ ቄሶች ሊሆኑ ከፈቀዱ ክህነት ከተቀበሉ በኋላ በቶሎ ሚስት ማግባት አለባቸው። ከማግባታቸው በፊት የቀሰሱ እንደሆነ ግን ሚስት እንዳያገቡ ይከለከላሉ። ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ለመግበት ስለማይችሉ ታናናሾቹን ሕፃናት ታቅፈው የሚያመጡዋቸው ወንዶች ናቸው። እነዚህ ሕፃናት መቁረብ ስላለባቸው ማታ ከቅዳሴ ውጭ እስኪሆን ድረስ ምንም ሳይቀምሱ ጾማቸውን ተከርተው ዋይ ዋይ ሲሉ ከእናቶቻቸው ተለይተው በጉሮኖ የዋሉ የፍየል ግልገሎችን ድምጽ ያስታውሳሉ። ከነዚህ ልጆች ጥቂቶቹ ብቻ ማለት ከፍ ያሉት ብቻ እንጂ ሕፃናቱ ንባብ እንደማይችሉ ተረድተናል። የነዚህ ሕፃናት ክህነት አቀባበል ስነ ሥርዐት ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው፤ እንደ ቤተ ክርስቲያን ቆጥረው በሚገለገሉበት ድንኳን ውስጥ በወንበር ላይ አቡኑ ይቀመጡና ሕፃናቱ በረድፍ ገብተው በፊታቸው ያልፋሉ። አቡኑ ጥቂት ጸሎት ካደረጉ በኋላ ከያንዳንዳቸው ራስ ላይ ጥቂት ጠጉር ይቆርጡና መጽሐፋቸውን ከትተው እንደገና መጸለይ ይጀምራሉ። ሕፃናቱ እንደገና ተመልሰው ሲመጡ አቡኑ ቁልፍ ይሰጡዋቸውና ያን ቁልፍ ይነኩታል፤ እነዚህም የድንኳኑን በር ይከፍታሉ ወይም እጃቸውን ያኖሩበታል። በራሳቸው ላይ አንድ ጨርቅ ያኖሩባቸው ነበር። እነዚህን ነገሮች ሁሉ በተራ ያደርጉ ነበር። ክህነት ለሚቀበሉት ልጆች ለያንዳንዳቸው የሚጠጣ ነገር በሸክላ ጽዋ ይሰጡዋቸውና አቡኑ እንደገና እጃቸውን ይጭኑባቸዋል። በያንዳንዱ ስነ ሥርዓት መካከል አቡኑ ሁሉ ጊዜ አጭር ጸሎት ያደርጉ ነበር። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ለክህነት ከመጡት ሕፃናት ውስጥ አንዳንዶቹ በእቅፍ ነበር የሚቀርቡት። በቁርባኑ ጊዜ እነዚህ የሚያደርጉት ትግል የሚያስገርም ነገር ነው። ዕድሜአቸው ስለማይፈቅድላቸውና በጩኸታቸው ምክንያት በውኃ እየጋቱዋቸው እንኳ (ማቁረቢያውን) ሥጋውን ሊውጡ አይችሉም ነበር።

ይህ ስነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ወደ ማረፊያቸው እንድሄድና ከርሳቸው ጋር ምሳ እንድበላ አቡኑ ጋበዙኝ። ከኔ ጋር ሃሳብ እንዲለዋወጡ ንጉሠ ነገሥቱ ጠይቋቸው ስለነበር፤ ይለቁንም እኔ በስነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝቼ ማናቸውንም ነገር ስላየሁ አስተያየቴን እንድገልጽላቸው ጠየቁኝ። እኔም የቅስና ሥልጣን ለመቀበል ስለቀረቡት ብዙ አካለ ጎዶሎዎችና ዓይነ ሥውሮች ጉዳይ ከዚህ በፊት ለአዛዥ ሩፋኤል የነገርሁትን ነገርኳቸው። ለዚሁ ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ የላከባቸው መሆኑን፤ ስለተደረገውና ስለሚደረገውም ውሳኔ፤ እንዲሁም አዛዡም ያቀረበውን ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ የገለጻላቸው መሆኑን ጭምር ካስታወቁኝ በኋላ ስለዲያቆናቱ ጠየቁኝ። ነገር ግን የክህነታቸው ሥርዓት መልካም መሆኑን ብገልጽም በእቅፍ ላሉ ሕፃናትና ትምህርት ለሌላቸው ወጣቶች ክህነት መስጠት ደግ ነገር አለመሆኑንና እንዲያውም በእግዚአብሔር ቤት ሊደረግ የሚገባው ነገር አለመሆኑን ጭምር አልሸሸግሁም። አቡኑም መልሰው እንዲህ አሉኝ፤ እግዚአብሔር ወደዚህ አገር የላከን እውነቱን እንድንናገር ነው፤ ስለዚህ እኔ በማርጀቴና በኔ ምትክ አቡን መቼ እንደሚመጣ ስለማይታወቅ ንጉሠ ነገሥቱ በገፍ ክህነት እንድሰጥ ባያዘኝ ኖሮ እኔ በፈቃዴ አላደርገውም ነበር። ይህ አገር ሃያ ሶስት ዓመት ያለ አቡን ስለነበር ከጥቂት ጊዜ በፊት ሁለት መቶ አንሳሽ ወርቅ ወደ ካይሮ ልከው አቡን ሲያስፈልኑ ነበር፤ ነገር ግን የግብጽ ሡልጣን ከቱርኮች ጋር በጦርነት ላይ ስለነበር ከመልእክተኞቹ ላይ ወርቁን ወስደውባቸው የተፈለገውን አቡን ሳይልኩላቸው ቀርተዋል። እውነቱን እንድንናገር እግዚአብሔር አሁን ወደዚህ አገር አምጥቶናል፤ የኔ ዕድሜ ወደ መጨረሻ ስለደረሰ ይህ አገር በቶሎ ሌላ አቡን እንዲኖው ያስፈልጋል ሲሉ ነገሩኝ።

የክህነት አሰጣጡን ስነ ሥርዓት ከላይ እንደተገለጸው ሁለት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በኋላ በመደጋገም ብዙ ጊዜ አይቼ ነበር። በየቀኑ እሁድና በሌሎች በዓላት በዓቢይ ጾም ወራትም ክህነቱ ይሰጥ ነበር። አቡኑ ክህነት መስጠቱን አንድ ቀን ያስታጎሉ እንደሆነ ከዚያ በፊት የማያውቁኝ ብዙ ሰዎች ወደኔ ይመጡና ስንቅ አልቆብናልና አቡኑ ክህነት እንዲሰጡን ያማልዱን ዘንድ በእግዚአብሔር

ስም እንለምንዎታለን ይሉኝ ነበር። ለማማለድ እንደተጠየቅሁት አቡኑን ስነግራቸው በማግሥቱ ክህነት ለመስጠት ድንኳን እንዲተከል ያዙ ነበር። ስለኔ መልካም ግምት ስለነበራቸው አንድ ነገር ለምኛቸው ከቶ ሳይፈቅዱልኝ ቀርተው አያውቁም ነበር። በማዕርግ እኩያቸው የሆንሁ ይመስል ማናቸውንም ነገር በአክብሮት ያከናውኑልኝ ነበር።

ምዕራፍ ዘጠና ዘጠኝ፤ ኢትዮጵያ ያለ አቡን ብዙ ጊዜ ስለመቆየትዋ፤ አቡኖቹ ከየት እንደሚመጡ፤ አሁን ስላሉት አቡን ሁኔታ።

ይህ አገር ሃያ ሰባት ዓመት ሙሉ ያለ አቡን ነበር ይባላል። በአጼ ዳዊት ቅድመ አያት በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የነበሩት አቡን በሞቱ ጊዜ በምትካቸው ሌላ አቡን ሳይመጣ አስር ዓመት አለፈ ይባላል። ይህ ሊሆንበት የቻለው ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ ከሮም እንጂ ከእስክንድርያ አቡን ሊያስመጣ ባለመፍቀዱና ይልቁንም ከከሃዲያን አገር አቡን ከማስመጣት ይልቅ አገሩን ማጣት የሚመርጥ መሆኑን በመቁረጥ ነው ይባላል። አጼ ዘረዐ ያዕቆብ በዚህ ዓይነት አስር ዓመት እንደቆየ ሞተ። አጼ እስክንድርም በነገሠ ጊዜ ያባቱን ውሳኔ በመከተል አስራ ሶስት ዓመት ሙሉ አቡን ሳያስመጣ ቆየ፤ ነገር ግን የካህናት ቁጥር በየጊዜው እየተቀነሰ በመሄዱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያኖች የሚዘጉ መሆናቸውን በማሳሰብና በተለይም በዚህ አገር ቤተ ክርስቲያኖች የጠፉ እንደሆነ የክርስትና ሃይማኖት የምትጠፋ መሆንዋን በማስገንዘብ ሕዝቡ አቤት ስላለ ለጊዜው በካይሮ ይገኙ ወደነበሩት ወደ እስክንድርያ ፓትርያርክ መልእክተኛ ላከ። ፓትርያርኩም አንዱ ሲሞት ሌላው እንዲተካ በማለት ሁለት አቡኖች ወደ ኢትዮጵያ ላኩ። እኛ በዚያ በነበርንበት ጊዜ ከሁለቱ አቡኖች አንዱ አቡነ ያዕቆብ ሞተው አሁን ያሉት አቡነ ማርቆስ ተተኩ። እኚህ አቡን በኢትዮጵያ ሃምሳ ዓመት መኖራቸውን ገለጹልኝ፤ ወደዚህ አገር ከመምጣታቸው በፊት እንዳሁኑ

የሸበቱና ዕድሜአቸውም ስልሳ አምስት ዓመት የነበረ መሆኑን ነገሩኝ። ስለዚህ አሁን ባገኘኋቸው ጊዜ ዕድሜአቸው ከመቶ ሃያ ዓመት በላይ ነበር።

እነዚህን አቡኖች ያስመጣው ንጉሠ ነገሥት እጅግ ጠንካራ ክርስቲያን ነበር፤ አቡኖቹ እንደመጡ ወዲያውኑ ሰንበት እንዳይከበር በመከልከል አዋጅ አወጣ። እንዲሁም ከዚያ በፊት በስህተት ይፈጸሙ የነበሩ ስነ ሥርዓቶች ሁሉ እንዲወገዱ፤ የአሳማም ሥጋ እንዲበላ፤ እንዲሁም አንገት በመቁረጥ ብቻ ሳይሆን በሌላ ዓይነት ዘዴ የተገደሉ ከብቶች ሥጋም እንዲበላ አዘዘ። ይህ አዋጅ ታውጆ በቤተ መንግሥቱና ባካባቢው ባሉ ቦታዎች ትዕዛዙ መፈጸም ሲጀምር መርቆርዮስ በራንካ ሌዎኔ የተባለ የቬኔዝያ ተወላጅና ከርሱም በኋላ ጴጥሮስ ደኩቪሊያን የተባለ አንድ ፖርቱጊዝ በቤተ መንግሥቱ ደረሱ፤ እነዚህ ሰዎች ወደዚያ ከመድረሳቸው በፊት በመንገዳቸው ላይ እንደ ቀድሞው ያገሩ ልምድ እየተመገቡ ሰንበትንም የሚያከብሩ ሰዎች አይተዋል።

መጽሐፍትን እናውቃለን የሚሉ አንዳንድ መነኩሴዎችና ቄሶች የነዚህን ሁለት ፈረንጆች ተግባር በመመልከት ከያገራቸው በቅርቡ የመጡ እነዚህ ሰዎች እንኳ ያገራችንን ልምድ ሲያከብሩ እኚሁ ከእስክንድርያ የመጡ አቡን በመጻሐፍት ተጽፎ የማይገኘውን ነገር የሚያዙን በምን ምክንያት ነው? ሲሉ በማማረር አቤቱታቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረቡ። ከዚህ በኋላ ይህን ምክንያት በማድረግ ወደ ቀድሞው ሕግ እንዲመለሱ ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ንጉሠ ነገሥቱ የኛን ቅዳሴ በመስማቱና በማየቱም አገልግሎታችንንና ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓታችንን በመውደዱ እግዚአብሔርን በማመስገን በኛ መምጣትና በሌሎችም በሚከተሉ አማካይነት ይህች አገር ወደ እውነቱ እንድትመለስ በእግዚአብሔር ተስፋቸውን የጣሉ መሆናቸውን፤ በዚች አገር የሮም ቤተ ክርስቲያን ተከታይ የሆነ መሪ ይነሣል የሚለው ትንግርት ሲፈጸም ለማየት እንዲችሉ፤ እንዲሁም የዚያ የከፋው መሐመድ ቤት በሆነችው በሜካ የላቲን ቅዳሴ ሲቀደስ እንዲያዩ እግዚአብሔር ዕድሜ እንዲሰጣቸው እንጂ ሌላ ነገር

የማይለምኑ መሆናቸውን አቡኑ ነገሩኝ። በዚች አገር አንድ መቶ አቡኖች ካገለገሉ በኋላ የሮም ቤተ ክርስቲያን የሆነ አንድ መሪ ይነግል የሚል ትንቢት ኢትዮጵያውያን ያላቸው መሆናቸውን እንዲሁም እርሳቸው መቶኛው መሆናቸውን በመግለጽ ይህ ጊዜ የተቃረበ መሆኑን ነገሩኝ። ከዚህም በላይ ፈረንጆች ከአጥናፈ ምድር በመርከብ መጥተው ከኢትዮጵያውያን ጋር ተቀላቅለው ሁለቱም በሕብረት ጅዳንና ቶሮን ሜካንም ያጠፋሉ፤ ብዙ ሰዎች ባሕሩን ተሻግረው ወደ ሜካ ዘልቀው ከተማይቱን ደርጸው ወዲያ ወዲህ መመላለስ ሳያስፈልጋቸው በተርታ ቆመው እጅ በእጅ በመቀባበል ብቻ ድንጋዩን በሙሉ በቀይ ባሕር እንደሚያሰምጡትና ሜካም ባድማ ሆና እንደምትቀር፤ ታላቁን የካይሮን መዲናም እንደሚወስዱና ማን ሊገዛው እንደሚገባ ለመወሰን ትልቅ ንትርክ እንደሚነግና በኋላም ፈረንጆች በዚህ ታላቅ መዲና የሚኖሩ መሆናቸውን የሚናገር ትንቢት መኖሩን ገለጹልኝ።

የአቡኑ ሁኔታና አለባበስ ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው። በመኖርያቸው ካንድ ጊዜ በስተቀር ስላላየኋቸው ክህነት በሚሰጡበት ድንኳን ውስጥ ሲቀመጡ አለባበሳቸውና ጠቅላላ ሁኔታቸው እንዴት እንደሆነ እገልጻለሁ። የዚህ አገር መኳንንት እንደሚደርጉት ሁሉ በአልጋ ላይ ተቀምጠው በፊታቸው መጋረጃ ተጋርዶአል። ስስ የከች ቀሚስ ለብሰው ሰማያዊ ካባ ደርበዋል። በራሳቸው ላይ ሰፊ የሰማያዊ ጨርቅ ጥምጥም አድርገዋል። ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት አቡኑ በጣም የሸመገሉ አጭርና ራሰ በራ ሰው ናቸው። ጢማቸው ነጭ ሱፍ ይመስላል፤ ያገሩ ካህናት ጢማቸውን ማሳደግ ስለማይወዱ የርሳቸውም ርዝመቱ በመጠኑ ነው። አቡኑ ንግግረ መልካምና ሲናገሩም ብዙ ጊዜ ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚያቀርቡ ሰው ናቸው። ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ወይም ክህነት ወደሚሰጡበት ቦታ ሲሄዱ በማለፊያ ዕቃ አጊጣ በተጫኑች በቅሎ ተቀምጠው ብዙ በቅሎኞችና በእግር የሚሄዱ ሰዎችን አስከትለው ይሄዳሉ። በእጃቸው መስቀል ይዘው ሲሄዱ በእንጨች ላይ የተዋደዱ ሶስት መስቀሎችን ከርሳቸው ቁመት በላይ ከፍ አድርገው በመያዝ ሶስት ሰዎች በጎን ይሄዳሉ። እነዚህን መስቀሎች የያዙ ሰዎች ከፊት መሄድ ይገባቸው

ነበር ስል አማክሬአቸው ነበር፤ ነገር ግን በጃቸው የያዙት መስቀል ስፋቱ በቂ ስለሆነ ሌላ እንዲቀድም የማያስፈልግ መሆኑን መለሱልኝ። አቡኑ በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ የማይለዩዋቸው አራት ቋሚ ድባቦችን የያዙ ሰዎች ከፊት ቀድመው ይሄዳሉ። እነዚህ ድባቦች በታላቅነታቸው ከንጉሠ ነገሥቱው ቢመዛዘኑም እንደርሱዎቹ ጌጠኛ አይደሉም። በሄዱበት ቦታ ሁሉ ከፊታቸው ቀድመው ሕዝቡን ከመንገዱ ወደ ግራና ቀኝ ገለል የሚያደርጉ አለንጋ የያዙ አራት ክልካዮች አሉ። በየቋንቋቸው ሆ እያሉ አቡኑን የሚከተሉ ወጣቶችና ጉልማሶች፤ ቄሶችና መነኩሴዎች አገሩን ያለብሱታል። በሆታቸው ላይ የሚሉት ቃል ምን እንደነበረ ጠይቄ ቀጥሎ የተመለከተው መሆኑን ነግረውኛል። «ጌታዬ ያደቁኑን፤ ያቅሱን፤ እግዚአብሔር ዕድሜዎን ያርዝምልን።»

ምዕራፍ መቶ፤ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በተመረቀበት ጊዜ የተሰበሰቡት ካህናት ብዛት፤ የንጉሠ ነገሥቱ አባት የአጼ ናአድ አጽም መዛወር፤ በዚያ አጠገብ ስለምትገኝ አንዲት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን።

ቅዳሜ ጥር 12 ቀን በተባለው ቤተ ክርስቲያን ብዙ ካህናት ተሰብስበው ሌሊቱን በሙሉ ሲያዜሙ ከበሮና ጽናጽልም ሲመቱ አደሩ። ይህን ማድረጋቸው ቤተ ክርስቲያኑን መባረካቸው ነው አሉኝ። የተቀደሰው በዚያ አቅራቢያ ባለ የንጉሠ ነገሥቱ አባት በተቀበረበት ውስጥ ነው። የንጉሠ ነገሥቱ አባት ካስራ ሶስት ዓመት በፊት ሞቶ ከተቀበረበት ከዚህ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን አጽሙን አውጥቶ በሕይወቱ ሳለ በጀመረው አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ለማዛወር ልጁ አጼ ዳዊት ፈልጎ ነበር። እሁድ ጥዋት ባዲሱ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመርያ ጊዜ ተቀደሰ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ገቢ ያላቸው

አራት መቶ ደብተራዎች ካሁኑ ስለሚገኙበት በሌሎች እንደሆነው ሁሉ እጅግ እንደሚበረክቱና የሚበሉትም እንደሚያጡ አይጠረ ጠርም።

በተባለው ወር አስራ አምስተኛ ቀን ሁላችንም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተጠርተን ሄድን፤ በቤተ ክርስቲያኑ ከሁለት ሺ በላይ የሚሆኑ ቄሶችና በዚሁ ቁጥር የሚገመቱ ዲያቆናች በዋና ዋና በሮቹ ቁመዋል። ንጉሡ ነገሥቱ ከዋናው ፊት ባሉት ደረጃዎች ማረፊያዎች ላይ በመጋረጃ ውስጥ ሳለ ካህናቱ ከርሱ ፊት ለፊት ከበሮና ጽናጽል እየመቱ እያዜ ሙም ያሸበሸቡ ነበር። የዚህ ስነ ሥርዓት አብዛኛው ክፍል ከተፈጸመ በኋላ ንጉሡ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮብን ሃሳባችንን ጠየቀን። እኛም መልሰን ለእግዚአብሔር አገልግሎት በስሙ የተፈጸሙ ተግባሮች ሁሉ በጎ ነገር የሚመስሉን መሆናቸውን በተለይም ይህን ለእግ ዚአብሔር አገልግሎት ሲባል የተደረገውን ስነ ሥርዓት ሁል ጊዜ የምናስታውሰው መሆናችንን ገለጽንለት። እንደገና መልእክተኛ ተልኮ መጥቶ ከናንተና ከኛ የትኛው ነው የሚሻል? ለናንተስ የትኛው ነው በበለጠ ደስ የሚያሰኛችሁ የሚታያችሁን ነገር ገልጻችሁ ብትልኩብን እናመሰግን ነበር አሉን። እኛም መልሰን እግዚአብሔር ሰዎች በልዩ ልዩ መንገድ እንዲያገለግሉት መፍቀዱን በማሳሰብ የናንተም የኛም ሥርዓት የሚፈጸምበት ዓይነተኛ ዓላማ አምላክን ለማገልገልና ለመወደስ ስለሆነ የሁላችንም መልካም ነው ስል መለስሁላቸው።

ወዲያው መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ በልባችን ያለውን ሳን ሸሽግ እውነቱን እንድንናገር የተጠየቅን መሆናችንን ነገረን። እኛም የተናገርነው እውነቱን ስለሆነ በልባችን የተሸሸገ ምንም የለም ስንል መልእክተኛውን ነግረን ልከነው ስነ ሥርዐቱ እስከሚያልቅበት ጊዜ ድረስ በዚያ ቆየን። ይህ ከተፈጸመ በኋላ ምዕመናኑና ቄሶቹ እኛም ከቤተ ክርስቲያኑ ውጭ እንድንወጣ ታዘን እኛን በሰሜን በኩል አንድ ቦታ ሰጥተውን በዚያ በጸጥታ እንድንቆይ አዘዙን። ካህናቱና ምዕመናኑ የንጉሡ ነገሥቱ አባት በተቀበረበት ወደ ትንሹ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱና በዚያም ቦታ እስከ በቃ ድረስ እንዲገቡ

ታዘዙ። ወደዚህ ቦታ የተላክንበትን ምክንያት ሳናውቅ እንዲያው ቆመን ሳለን በኛና በትልቁ ቤተ ክርስቲያን መካከል ካህናቱና ምዕመናኑ የንጉሡ ነገሥቱን አባት አጽም ይዘው በሚገባ አኳኋን በሰልፍ ገብተው ወደ ታላቁ ቤተ ክርስቲያን ገቡ። በፊት እንደተገለጸው አቡነ ማርቆስ በጣም ዕድሜአቸው የገፋ ሰው ስለነበሩ፤ በጉዞው ላይ በጣም ስለመድከማቸው ሁለት ሰዎች በግራና ቀኛቸው ሆነው ደግፈዋቸው ይሄዱ ነበር። ከርሳቸው ቀጥለው የንጉሡ ነገሥቱ እናትና እቴጌ ዕሌኒ የንጉሡ ነገሥቱ ባለቤት እቴጌይቱም ጥቁር ልብስ ለብሰው ተከትለው ይሄዱ ነበሩ። አቤቱ፤ አቤቱ እያሉ እየጮሁና እያለቀሱ ይሄዱ ነበር። የነዚህ ሰዎች ልቅሶ በእውነተኛው የሚያሳዝን ስለነበር እኛም በነበርንበት ቦታ ሆነን አለቀስን። አጽሙን የያዘው ሣጥን በጥሩ ጨርቅ ተሸፍኖ በአጎበር ውስጥ ተቀምጦ ነበር። በዚህ አኳኋን ሣጥኑን አምጥተው እኛ በፊት ቆመንበት በነበረው ቦታ አኖሩት። በስነ ሥርዓቱ ላይ ለመገኘት ማለዳ ጸሐይ ስትወጣ ሄደን ማታ በመብራት ተመለስን።

<u>ምዕራፍ መቶ አንድ፤ አምባሳደሩ ስለስጋጃ ጉዳይ ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር ስላደረገው ንግግር፤ ዘፈን እንድናይና እራትም እንድንጋበዝ ንጉሡ ነገሥቱ ስለማዘዙ።</u>

ጥር 17 ቀን ንጉሡ ነገሥቱ አስጠርቶን አምባሳደሩን ተከትለን ፖርቱጌዞቹና ሌሎቹም ፈረንጆች ሄድን። በድንኳኑ አጠገብ እንደ ደረስን ንጉሡ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮ ሃያ ስንዝር ቁመት ያለው ስጋጃ በፖርቱጋል ምን ያህል እንደሚያወጣ ጠየቀን።

አምባሳደሩም መልሶ እኔም አብረውኝ የመጡትም ሰዎች ከዚህ በፊት ነጋዴዎች ስላልነበርን ምን ያህል እንደሚፈጅ በእውነተኛው

አላውቅም ሲል መለስ። መልእክተኛውም ተመልሶ መጥቶ ሃያ ኮቫዱሽ ርዝመት ያለው አንድ ስጋጃ በአራት አንሳሽ ወርቅ ከካይሮ ገዝተው ያመጡለት መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ ነገረን። አምባሳደሩም መልሶ ይህን ያህል ስፋት ያለው ምንጣፍ በፖርቱጋል ሃያ ክሩዛዱሽ የሚያወጣ የሚመስለው መሆኑን ገለጸ። መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ በፖርቱጋል ሃያ ወይም ሰላሳ ኮቫዱሽ ርዝመት ያለው ምንጣፍ ይገኛልን ሲል ጠይቆን መገኘቱን አምባሳደሩ አረጋገጠለት። ተመልሶ በመጣው በዚህ መልእክተኛ አማካይነት ለጠቅላይ ገዥው ወርቅ ብልክለት ይህን ቤተ ክርስቲያን ለማንጠፍ የሚበቃ ስጋጃ ሊልክልኝ ይችላልን ሲል ንጉሠ ነገሥቱ ጠየቀን። አምባሳደሩም መልሶ ይህን ለመሰሉ አንድ ሺ ቤተ ክርስቲያኖች እንኳ ቢሆን ጠቅላይ ገዥው ሊልክ የሚችል መሆኑን አስታወቀ። መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ ወርቁ ቢላክ ጠቅላይ ገዥው ምንጣፉን ይልክ እንደሆነ እንደገና ጠየቀን። የዚህን ጊዜ የኛ ሰዎች ግርማዊነትዎ የሚጠይቁትን ማናቸውም ጉዳዮች የፖርቱጋል ንጉሥና ጠቅላይ ገዥውም ሊልኩልዎት ይችላሉ ሲሉ መለሱ።

ስለስጋጃው ጉዳይ መጠየቁን ትቶ በፖርቱጋል የአረብኛና የኢትዮጵያኛ ጽሑፎች ሊያነብ የሚችል ሰው አለ ወይ ሲል መልእተኛው ጠይቆን የማናቸውም ቋንቋ አስተርጓሚዎች በፖርቱጋል የሚገኙ መሆናቸውን አምባሳደሩ መለሰ። ንጉሠ ነገሥቱም መልሶ በፖርቱጋል ይህን የመሰሉ ሰዎች የሚገኙ መሆናቸውን የሚያምን መሆኑን አረጋግጦ፤ ነገር ግን በመርከቦቹ ውስጥ የተባሉትን ፊደሎች ለማንበብ የሚችሉ አሉወይ ሲል እንደገና አስጠየቀን። በፖርቱጋል ንጉሥ መርከቦች የሚጓዙ ብዙ እስላሞችና ኢትዮጵያውያን ያሉ መሆናቸውን ገለጹለት። እስላሞች ኢትዮጵያውያንን ከአገራቸው በመስረቅ በአረብ አገር፤ በፋርስ፤ በግብጽና በሕንድም ለፖርቱጊዞች የሚሸጡዋቸው መሆናቸውን ነገሩት። ፖርቱጊዞች እስላሞችን በማረኩ ቁጥር በመካከላቸው ሁል ጊዜ ኢትዮጵያውያን እንደሚገኙ ያውቁ ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መሆናቸውን በማወቅ ፖርቱጊዞች ወዲያውኑ በደንብ አልብሰውና አከባክበው ይዘው ነፃነታቸውን ይሰጡዋቸዋል። ለምሳሌ ግርማዊነትዎ የሚያውቀው

እነሆ አስተርጓሚው ጊዮርጊስ፤ ይህ ሰው ያንድ እስላም እስረኛ ሆኖ በሆርሙዝ አግኝተነው እኛ ነን ነፃ ያወጣነው። እንዴት አድርጎ ወደዚያ እንደሄደ ሊጠየቅ ይችላል በማለት በሰፊው በመግለጽ ለመልእክተኛው ነገርነው። ንጉሠ ነገሥቱም ጊዮርጊስን አስጠርቶ እንዴት ወደሆርሙዝ እንደሄደ አስጠይቆት እንዲህ ሲል መለሰለት፤ ለማታለል ክርስትና የተነሣ አንድ እስላም ሸጠኝ፤ ገዥዎቹም ወደሆርሙዝ ወሰዱኝ፤ አባ ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ ከግዞት እስኪያ ወጡኝ ድረስ በዚያ እኖር ነበር። አባ ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ በጎ ነገር የሠሩልኝና የሚሠሩልኝም ናቸው ሲል ለንጉሠ ነገሥቱ ተናገረ። በዚህ ጊዜ መልእክተኛው መጥቶ ለመብላት ትፈልጋላችሁ ወይ ሲል ጠይቆን ከጥቂት ጊዜ በፊት በልተናልና ግርማዊነትዎን እናመሰግናለን ስንል መልእክተኛውን መልሰን ላከነው። ወዲያውኑ ከዚህ በፊት ከቶ ወዳላየነው ወደ አንድ ድንኳን መሩን። ይህ ድንኳን በዋልታ ተወጥሮ የኮራ ሲሆን የተተከለውም በትልቁ የታቦት ድንኳን አጠገብ በአጥሩ ውስጥ ነበር። በጥምቀተ ባሕሩ ዳር የተተከለውን ድንኳን ይመስል ይህም ጣርያው በጨርቅ መስቀል አጊጦ ነበር። ድንኳኑ በሙሉ በስጋጃ ተነጥፎ ትልቅ አዳራሽ ይመስል ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮብን ለኔ ስትሉ በዚያ ገብታችሁ ተደሰቱ፤ በዚያም ሆናችው ጉዳያችሁን ተወያዩ ሲል ለመነን። በዚያ ተቀምጠን ስንጨዋወት ሳለን ብዙ ምግብና መጠጥ አቀረቡልን። ከምግቡም ውስጥ አንዱ ዓይነት የዶሮ ወጥ ነበር። የዶሮቹ አንገትና እግር ብቻ ሲቀር ማናቸውም ብልት በወጡ ውስጥ ነበር። አጥንቱን በሙሉ አውጥተው ሥጋውን በደቃቁ ከትፈው በቅመም አኩርጠው ነው የሠሩት። በወጡ ውስጥ የዶሮቹም ቆዳ ነበር። ነገር ግን ሥጋውን ከቆዳው ገፈው ያውጡት ወይስ ቆዳውን ከሥጋው ይገሽልጡት አጣርተን ለማወቅ አልቻልንም። የሆነ ሆኖ ወጡ በጣም ማለፊያ ነበር። ከዚህም በላይ የሥጋ ወጥና ባገሩ ባልትና የተሠራ ልዩ ልዩ ዓይነት ምግብ ቀረበልን። የሥጋ ወጡ ብዙ ቅቤ ገብቶበት ነበር የተሠራው፤ ጥብሱም ማለፊያ ሆኖ በስሎአል። ጠጅ በገንቦዎችና በደንበጃን ተሹሞ ቀረበልን። ሌሎቹ ጠጅ የቀረበባቸው ዕቃዎች ጥቋቁር ገንቦዎች ነበሩ፤ ከደንበጃኑ ጋር የወርቅ ሐረግ ያለበት አንድ ብርጭቆና አንድ የብር ዋንጫም ቀርቦ ነበር።

ከምግቡ በኋላ በአገራችን ባሕል እንድንዘፍንና እንድንጨፍር እንድንደሰትም ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ከዚህ በኋላ ይዘነው የነበረውን ክራራችንን እየመታን የኛ ሰዎች መዝፈን ጀመሩ። ጨዋታው ከደመቀ በኋላ ሁሉም ባንድነት ይዘፍኑና ይጨፍሩ ነበር። አንዳንድ ብላቴናዎችና ሌሎችም ሰዎች በዚያው ከኛ ጋር ነበሩ። እንዲሁም ንጉሠ ነገሥቱን ያጀቡ ይመስል በውጭም ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ከኛ ጋር ከድንኳኑ ውስጥ የነበሩትም ሰዎች ንጉሠ ነገሥቱ በውጭ የነበረ መሆኑን አረጋግጠውልን የማይገባ ነገር በመካከላችን እንዳ ይፈጸም አስጠነቀቁን። የዚህን ዕለት ሃያ አምስት ትልልቅ ነጫጭ ሻማዎችና አንድ የብረት መቅረዝ እንዲሁም መቅረዙን ማስቀመጫ አንድ ትልቅ ረከቦት ላኩልን። የተላኩት ሻማዎች በነበሩት ሰዎች ቁጥር እኩል ሲሆን መቅረዙ ሁሉንም ለመያዝ ይችል ነበር። በድግሱ ላይ እስከ እኩለ ሌሊት ከቆየን በኋላ ተሰናብተን ወደ ድንኳናችን ሄድን። አምሽተን ስለነበር የተኛነው ወዲያውኑ ነጋ።

ምዕራፍ መቶ ሁለት፤ ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደሩንና አብረውት የመጡትን ሁሉ ስለመጥራቱና በታላቁ ቤተ ክርስቲያን ስለተፈጸመው ጉዳይ።

በማግሥቱ ጥር 28 ቀን ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶኝ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንድንሄድ አዘዘን። በዚያ እንደደረስን ከዚህ በፊት ተቀምጦበት ባየነው በዋናው በር ፊት ለፊት ባለው ደረጃ ጫፍ በመጋረጃ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ እኛ ፊት ለፊት እንድንቆም ታዘዝን። ሁለቱን ተራ ደረጃ ወጥተን ቁመን እንደነበርን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተመልክተን የንጉሠ ነገሥቱ አባት አጽም ከተዛወረበት ቀን ይልቅ ዛሬ ብዙ ካህናት መኖራቸውን ተረዳን። እነዚህ ካህናት ከማዜምና ከማሸብሸብ በስተቀር ከቶ ሌላ ሥራ የላቸውም። ዝማሬና ሽብሸባውን በመመልከት ብዙ ጊዜ ካለፈ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮ በኛ አገር ይህን የመሰለ ነገር ይደረግ እንደሆነ

ጠየቀን። እኛም መልሰን የኛ ዝማሬ በዝግታና ዝቅ ባለ ድምጽ የሚዘመር መሆኑን፤ የድምጽ ድፋትና ቅናት የሰውነት እንቅስቃሴም ረጋ ያለ መሆኑን፤ ማሸብሸብም ከቶ አለመኖሩን አስረዳን። መልእክተኛው ተመልሶ መጥቶ እንግዲህ በናንተ ልምድ ይህን የመሰለ ወግ ስለሌለ የኛን መንቀፋችሁ ነውን ሲል ጠየቀን። በማናቸውም ሁኔታ ቢደረግም እግዚአብሔርን ለማገልገል የተደረገ ተግባር ሁሉ መልካም ይመስለናል ስንል ይህን ጥያቄ መለስን። ሥርዓቱ ከተፈጸመ በኋላ ሃያ አምስት ቄሶች እያንዳንዳቸው መስቀል በግራ እጃቸው እንደምርኩዝ ይዘው በቀኝ እጃቸው ደግሞ ጽና አንጠልጥለው ቤተ ክርስቲያኑን መዞር ጀመሩ። ሌሎች ደግሞ ጽና ብቻ ይዘው እያጠኑ ይሄዱ ነበሩ። እኛ በቆምንበት ደረጃ ላይ እጣን የተመላባቸው የተቀረጹና በወርቅ ሐረግ ያጌጡ ሁለት ትልልቅ የነሐስ ገበቴዎች ነበሩ። ቤተ ክርስቲያኑን በዞሩ ቁጥር በነርሱ ልምድ የተሠሩ አልባሶችንና ካባዎችን ያዞሩ ነበር። ከሚያዜሙትና ከሚያሸበሽቡት ውስጥ አንዳንዳቹ እነዚሁኑ የመሰሉ አልባሶች ለብሰው ነበር። በዚሁ ስነ ሥርዓት ላይ ብዙ ባለ ጥምጥም ካህናት ነበሩ።

ቁመንበት የነበርነውን ቦታ ለቀን የንጉሠ ነገሥቱ እናትና እቴጌይቱም ነጭ አጎበራቸውን አስተክለው በሚገኙበት ቦታ እንድ ንሄድ ታዘዝን። ከነርሱ ፊት ለፊት በሚገኘው በተወሰነልን ቦታ ቁመን ሳለን መልእክተኛ ልከው በኛ አገር ጽዋው ከምን እንደተሠራ ጠየቁን። እኛም መልሰን ከወርቅ ወይም ከብር የተሠራ መሆኑን ነገርናቸው፤ ወዲያውኑ መልእክተኛውን መልሰው ልከው በምን ምክንያት ነው ከሌላ ነገር ያልተሠራው ሲሉ ጠየቁን። ከሌላ ነገር የተሠራ እንደሆነ ዕቃው ወሰካም ሊሆን ስለሚችል ከወርቅ ወይም ከብር በስተቀር ከሌላ እንዳይሠራ ተከልክሎአል አልናቸው። መልእክተኛው እንደገና መጥቶ በእውነቱ በዚያ ብዙ ወርቅና ብር ቢኖር ለምንድር ነው ይህን በቁጠባ የሚሠሩት ሲል ጠየቀን። ይህን ጥያቄ በመመለስ ዋንጫው ከብር ወይም ከወርቅ እንዲሠራ መወሰኑ ለንጽህና ሲባል ነው፤ ለቁጠባ ሲባል ቢሆን ኖሮ ከሌሎች ርካሽ ነገሮች ለምሳሌ ከቆርቆሮ ከመዳብ ወይም ከአረር ለመሥራት ይቻል ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከነበረው መጋረጃ

ወጥቶ በበሩ አጠገብ በነበረው በባለቤቱ አጎበር ተዛውሮ ስለነበር ይህን ጥያቄ የሚያቀርብልን እርሱ መሆኑን ተረዳን። ጥያቄአችውን በማስከተል በፖርቱጋል እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ስንት ጾዋ እንዳለው ጠየቁን። እኛም መልሰን እያንዳንዳቸው ሁለት መቶ ያላቸው ቤተ ክርስቲያኖችና ገዳሞች አሉ፤ አንድ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ ድኃ ቢሆን ከሶስት ወይም ካራት ያነሰ የለውም አልናቸው። ሁለት መቶ ያለው ቤተ ክርስቲያን ወይም ገዳም ምን እንደሚባል ንጉሠ ነገሥቱ አስጠይቆን ይህን ያህል ያላቸው ብዙ ገዳሞች ቢኖሩም በተለይ «ባታሊያ» መሆኑን ነገርነው። ይህ ገዳም በምን ምክንያት ባታሊያ ተብሎ እንደተሰየመ አስጠየቀን። ገዳሙ ይህን ስም ያገኘበት ምክንያት የፖርቱጋል ንጉሥ በዚያ ቦታ ጠላቱን ድል ነሥቶ ስለነበር ገዳሙ እንዲሠራ አዘዘ። ገዳሙ ለእመቤታችን ተሰጥቶአል። ይህን ጥያቄ ያቀረቡበት ምክንያት በአማራ አውራጃ አንድ ገዳም ስለነበር ነው። በጥንት ጊዜ አንድ ንጉሠ ነገሥት የእስላምን ባላባቶች ድል ነሥቶ ስለነበር ለድሉ መታሰቢያ እንዲሆን በማለት ይህንኑ ገዳም ያሠራ ቢሆንም የኛውን ገዳም ይመስል ስም ያለው ገዳም አይገኝም። በባታሊያ ገዳም ውስጥ ስንት ነገሥታት እንደተቀበሩ አስጠይቆን አራት ነገሥታት አንድ ልዑልና ብዙዎች የነገሥታት ልጆች መቀበራቸውን፤ ከዚህም ሌላ በፖርቱጋል በሚገኙ በሌሎች ታላላቅ ገዳሞች ሌሎች ነገሥታት የተቀበሩ መሆናቸውን ለንጉሠ ነገሥቱ ነገርነው። አዘውትረን ቅዳሴ የምንገባበት ጊዜ በእኩለ ቀን ስለነበረ ይህ ጊዜ መቃረቡን በማወቅ ወደ ቅዳሴያችን እንድንሄድ ተፈቀደልን።

ምዕራፍ መቶ ሶስት፤ አምባሳደሩና ፈረንጆቹ ሁሉ አቡኑን ለመጎብኘት ስለመሄዳቸው።

አምባሳደሩ ከዚህ በፊት አቡነ ማርቆስን አይቶአቸው ስለማያውቅ እኛን ፖርቱጌዞቹንና ሌሎቹንም ፈረንጆች አስከትሎ ለጉብኝት ሄደ። አብዛኛውን ጊዜ እኔ እንደማገኛቸው አኳኋን በአልጋ ላይ

ተቀምጠው ነበር። አምባሳደሩ ሊስማቸው ፈልጎ ጠጋ ሲል እጃቸውን ሊሰጡት አልፈለጉም። በዚህ ፈንታ መስቀላቸውን ለርሱና አብረውት ለነበሩት ሁሉ አሳለሙዋቸው። አምባሳደሩ ከተቀመጠ በኋላ ከአቡኑ ጋር ንግግር ጀምሮ የፖርቱጋል ንጉሥ እንደራሴ ከነበረው ከሕንድ ጠቅላይ ገዥ ተልኮ ለጉብኝት መምጣቱን ገልጾ፤ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሳይጎበኛቸው በመቆየቱ ይቅርታ ለምኖ ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት ሌላ ሰው ለመጎብኘት ዕድል ያልተሰጠው መሆኑን ጨምሮ ገለጸ። አቡኑም መልሰው በቤተ መንግሥቱ ደንብ መሠረት አንድ የውጭ አገር ሰው ወደሌላ ሰው ቤት እንዲሄድ የማይፈቀድለት በመሆኑ ለጉብኝት ዕድል ስላልተሰጠው አምባሳደሩ እንዳይገረም ነግረውት ይህን ደንብ ያወጡት የቤተ መንግሥቱ መጥፎዎች መኳንንት መሆናቸውን ጨምረው ነገሩት። ንጉሠ ነገሥቱ መልካምና ቅዱስ ሰው ነው አሉት። አምባሳደሩም መልሶ ጠቅላይ ገዥው እጃቸውን እንዲስምለት ያዘዘው መሆኑን እንዲሁም በጸሎታቸው እንዳይረሱት የለመነ መሆኑን፤ በተለይም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሠራዊቱን ከፖርቱጋል ንጉሥ ሠራዊት ጋር እንዲያስተባብርና ባንድነት ሆነው ሜካን እንዲደርጹና ይህችንም ከተማ ከነዚያ ከከፋዎቹ ከመሐመድ ተከታዮች ነፃ ለማውጣት እንዲቻል ንጉሠ ነገሥቱን ያበረታቱት ዘንድ የሕንድ ጠቅላይ ገዥ በተለይ የለመናቸው መሆኑን ነገራቸው። አቡኑም መልሰው በሥልጣኔ ያለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ፤ ንጉሠ ነገሥቱም ሜካን ማጥፋት ብቻ ሳይሆን የየሩሳሌምንም ቅድስት ቤት ለመያዝ ቆርጦአል አሉት። ንግግራቸውንም በመቀጠል ኢትዮጵያውያን ከፈረንጆች ጋር ተባብረው ሜካን ያጠፋሉ፤ የሩሳሌምንም ይይዛሉ የሚል ትንቢት ያለ መሆኑን፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ፈረንጆችን ያሳያቸው ዘንድ በጸሎታቸው የለመኑት መሆናቸውንና እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ስለሰማላቸው ለዚሁ ምስጋናቸውን የሚያቀርቡ መሆናቸውን ለአምባሳደሩ ነገሩት። ለጊዜው ከኛ ጋር ሆኖ ነግግራቸውን ይተረጉምልን የነበረውን ጴጥሮስ ድኩቪሊያን የተባለውን ፖርቱጌዝም «ሲድ[1] ጴጥሮስ፤ አንተ በእድሜህ እንዳለህ ያገርህ ሰዎች ወደዚህ አገር ግዛቶች ይመጣሉና አትዘን» ይሉት ነበር። ስለዚህ ጴጥሮስ ድኩቪሊያን ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዲያቀርብ አሳሰቡት።

በዚህን ጊዜ አምባሳደሩ መልሶ የፖርቱጋል ንጉሥ ስለብጹዕነትዎ ከወንድምዎ ከማቴዎስና ከሌሎችም ሰዎች ሰምቶአል፤ ስለዚህ እርሱን ከመሰሉ ሰዎች እንደሚጠበቀው ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ ባቀደው ተግባር ጽኑና የማይበገር ያደርጉት ዘንድ የፖርቱጋል ንጉሥ አደራ ይልዎታል ሲል ነገራቸው። በዚህ ጊዜ አቡኑ እኔ አንድ ምስኪን ኃጢአተኛ እንጂ ብጹዕ አይደለሁም፤ ማቴዎስም ወዳጄ የነበረ አንድ ነጋዴ እንጂ ወንድሜስ አልነበረም፤ እርሱ የተጓዘው ሐሰትን ይዞ ነበር፤ ነገር ግን ከጉዞው ይህን የመሰለ ትልቅ አገልግሎትና ጠቃሚ ነገር እንዲከተል እግዚአብሔር ፈቀደ፤ ንጉሠ ነገሥቱ በክርስትና ሃይማኖት ያለው እምነት የማይበገርና ብርቱም ከመሆኑም በላይ የእስላምን ዓለም ለመደምሰስ የቆረጠ ሰው ስለሆነ ማበረታታት አያስፈልገውም አሉን። ንግግራቸውንም በመቀጠል የፖርቱጋልን ንጉሥ ታላቅነት በካይሮና በእስክንድርያም ሰፊ የነበረ መሆኑን ገልጨለት እርሱን የመሰለ ታላቅ ንጉሥ ስላወቅህና ስለተወዳጀህ በተለይ እግዚአብሔርን ልታመሰግን ያስፈልግሃል ስል ነግሬው እርሱም ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ያውቃል፤ የፖርቱጋል ንጉሥ ወዳጅነትም አስደስቶታል፤ አምላክን ለማመስገን በምጽዋና በዘይላ ላይ በሚሠሩት ምሽጎች ላይ የፖርቱጋልን ንጉሥ እንደራሴ ለማየት እንዲያበቃኝ እግዚአብሔርን ለምኜዋለሁ ሲሉ ምኞታቸውን ገለጹልኝ። ብዙ ጉዳዮች ካጫወቱን በኋላ አሰናብተውን ወደ ማረፊያችን ሄድን።

ምዕራፍ መቶ አራት፤ የጴጥሮስ[1] ድኩቪሊያን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት።

በዚህ አገር ስለሚኖር ጴጥሮስ ድኩቪሊያን ስለሚባል ፖርቱጌዝ ከዚህ በፊት ባንዳንድ ቦታ ስናገር እንደጠቀስሁት ሁሉ ይህ ሰው ከፍተኛ ግምትና ምስጋናም የሚገባው በመሆኑ ወደፊት ስሙን እጠቅሳለሁ። ወደዚህ እገር እንዴት እንደመጣ ማተት ተገቢ ነገር በመሆኑ እርሱ ራሱ በነገረኝ መሠረት እገልጻለሁ። ከሁሉ አስቀድሜ

ላትተው የምፈልገው ለዚህ ሰው እኔ የኑዛዜ አባቱ የነበርሁ መሆኔን ሲሆን ኃጢአቱን ለመናዘዝ ወደኔ ቀርቦ እንደነገረኝ ሰላሳ ሶስት ዓመት ሙሉ አልተናዘዘም ነበር። የዚህ አገር ቀሳውስት የምዕመናንን ኑዛዜ በምስጢር ስለማይዙ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደው ለእግዚአብሔር ለመናዘዝ ብቻ ነበር። የሕይወት ታሪኩን ቀጥሎ እንደ ተመለከተው ዘረዘረልኝ።

በኩቪሊያን ከተማ በፖርቱጋል ተወለድሁ፤ ከሴቪሊያ መስፍን ከዶም አልፎንሶ ጋር ለመኖር በወጣትነቴ ጊዜ ካስቴሊያ ሄድሁ፤ በካስቴሊያና በፖርቱጋል መካከል ጦርነት በተነሣ ጊዜ ከመስፍኑ ወንድም ከዮሐንስ ጉዝማው ጋር ወደ ፖርቱጋል ተመለስሁ። ይህም ሰው ለፖርቱጋል ንጉሥ አፎንሶ ሰጥቶኝ ልዑልነታቸው ፈረስ ሲጋልቡ በመጫሚያቸው መኮርኮርያ የማጠልቅና የማወልቅ እኔ ነበርሁ። ወዲያው ወደጋሻ ያዥነት ማዕርግ ተዛውሬ ከዚያም በኋላ ከንጉሡ ጋር ወደ ፈረንሳይ አገር ሄድሁ። ንጉሥ አፎንሶ ከሞቱ በኋላ በልጃቸው በዶም ዮሐንስ ቤት በጋሻ ያዥ ክፍል እያገለገልሁ እስከ ግዞቱ ጊዜ ድረስ ቆየሁ። ካስቴሊኛ ደህና አድርጌ ስለማውቅ ወደ ካስቴሊያ ሄጄ በዚያ የሚቀመጡት መኳንንት እነማን መሆናቸውን እንዳውቅ ንጉሡ ላኩኝ። ከካስቴሊያ እንደተመለስሁ ካሊም ለመግዛትና ከጥለምሰን ንጉሥ ጋር የሰላም ውለታ ለመደራደር ንጉሥ ዶም ዮሐንስ ወደ በርበርያ[2] ላኩኝ። ከዚያ ከተመለስሁ በኋላ የልዑል ዶም ፈርናንዶን አጽም ወደላከው ሞሊ ቤንሐጃጄ ወደተባለው ሰው እንድሄድ ወደበርበርያ ለሁለተኛ ጊዜ ተላክሁ። በዚያን ጊዜ መስፍን ለነበሩት ለልዑል አማኑኤል ዶም ዮሐንስ ንብረት ሊሰጡዋቸው ፈልገው ስለነበር ፈረስ እንድገዛላቸው አዘውኝ የርሳቸውን ገንዘብ ይዤ ሄጄ ነበር። የተገዙትን ፈረሶች እንዲያይ ፔሮ አፎንሶ የተባለ አንድ የቶማር ተወላጅ ታዞ ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ በርበርያ ሄጄ ስመለስ ሊቀበሉኝ ከታዘዙት ሰዎች አንዱ የካስቴሎ ብራንኮ ተወላጅ የነበረ አፎንሶ ድ ፓይቫ የተባለ አንድ ሰው ነበር። ከጉዞዬ ተመልሼ በንጉሡ ፊት እንደቀረብሁ በቆይታ ተቀብለውኝ ታማኝና መልካም አሽከሬ በመሆንህ ይልቁንም የታዘዝህበት ሁሉ የሚሳካልህ ዕድለኛ ሰው በመሆንህ ላንድ ትልቅ መልእክት

አስቤሃለሁ አሉኝ። ይህም መልእክት ከፍ ብዬ የጠቀስሁት አፎንሶ ድ ፓይቫና እኔ ቄስ ዮሐንስ የሚገኝበትን እንድንፈልግና የርሱንም ምስጢር እንድናውቅ፤ እንዲሁም የቬኒስ ተወላጅ ነጋዴዎች የእስላምን አገሮች እያለፉ ወደዚህ እያመጡ የሚሸጡት ቀረፋና ሌሎችም ልዩ ልዩ ቅመማቅመሞች የሚገኙበት ቦታ የት መሆኑን አጣርተን እንድናውቅ ነበር። ለዚህ ሥራ ከኔ በፊት ሁለት ሰዎች ማለት የሞንቴይሩ ቤት ሰብ ተወላጅ የነበረ አንድ ሰውና ቄስ እንጦንዮስ የተባለ የሊዝቦን ተወላጅ ተልከው ነበር። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች የሩሳሌም ድረስ ከተጓዙ በኋላ አረብኛን ደህና አድርገው ካልተናገሩ በስተቀር ወደዚያ አገር ለመሄድ የማይችሉ መሆኑን ስለተገነዘቡት ወደ ፖርቱጋል ተመለሱ። ስለዚህ እኔ ይህን መልእክት እንድቀበልና ከአፎንሶ ድ ፓይቫ ጋር እንድሄድ ልዑልነታቸው ጠየቁኝ። እኔም ልዑልነትዎን ለማገልገል ካለኝ ምኞት ጋር የሚመዛዘን ችሎታ ምነው እግዚአብሔር በሰጠኝ ስል ትዕዛዙን በደስታ ተቀበልሁ። ስለዚህ ግንቦት 7 ቀን 1487 ዓም ከሳንተረኝ ከተማ ጉዞአችንን ጀመርን። በዚያን ጊዜ መስፍን የነበረው ልዑል አማኑኤል በዚያ ተገኝቶ ሸኝቶን ከዓለም ካርታ ላይ የተቀዳ አንድ የባሕር ጉዞ መምርያ ካርታ ሰጠኝ። ይህን መምርያ ካርታ በመተባበር በፔሮ አልካሶቫ ቤት ሆነው የሠሩት ሊቁ የቪዜው ኤጲስቆጶስ ካልሳዲሊያ፤ በፔድራሽ ኔግራሽ ይኖር የነበረው ዶክተር መምሕር ሮዲሪጉና በዚያን ጊዜ አይሁድ የነበረው ዶክተር መምሕር ሙሴ ነበር። ለሁለታችንም ስንቅ እንዲሆን ከአልሜይሪኝ አትክልት ወጭ ከተመደበው ባጀት ላይ ንጉሡ አራት ማቶ ክሩዛዱሽ ሰጡን። ይህ ሁሉ ሲሆን መስፍን ዶም አማኑኤል በዚያው ነበር። በመንገድ ላይ ችግር ወይም አደጋ የደረሰብን እንደሆነ እርዳታ እንድንጠይቅ በማለት ንጉሡ በዓለም ላሉ አገሮች ሁሉ የተጻፈ አንድ የመታወቂያ ወረቀት ሰጠኝ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ በመስፍኑ ፊት መልካም ምኞታቸውን ገልጸውልን አሰናበቱን። ከተሰጠን አራት መቶ ክሩዛዱሽ ውስጥ ለስንቅ የሚያስፈልገንን አንስተን የተቀረውን ወደ ቫሌንሲያ እንዲያስተላልፍልን በርቶሎሜዎስ ለተባለ ላንድ የፍሎሬንስ ሰው ሰጠነው። መንገዳችንን ጀምረን ብዙ ከተጓዝን በኋላ የኮርፑስ ዶሚኒ በዓል ዕለት በባርሴሎና ደረስን። ገንዘባችን ከባርሴሎና ወደ ናፖሊ እንዲ

ዛወርልን አድርገን ጉዞአችንን ወደፊት ቀጥለን በቅዱስ ዮሐንስ ዕለት በናፖሊ ደርሰን ገንዘባችንን የኮስሞ ዲሜዲሲስ ልጅ መነዘረልን። ከዚያም ተነሥተን በሮዶስ ደረስን። በዚያን ጊዜ በሮዶስ ይገኙ የነበሩ ፖርቱጌዞች ቄስ ጎንሳሎና ፈርናንዶ የተባሉ ሁለት ሰዎች ስለነበሩ ከነርሱ ዘንድ ዐረፍን። ከዚያም በበርቶሎሜዎስ ፓሬድሽ መርከብ ተሳፍረን ወደ እስክንድርያ ሄድን። ነጋዴ መስለን ለማለፍ እንድንችል ብዙ ማር ገዝተን እስክንድርያ ደረስን። በዚያ እንደደረስን ሁለታችንንም ትኩሳት ይዞን ተኛን። ክፉኛ ታመን ስለነበርን የመዳን ተስፋ የሌለን መስሎት የእስክንድርያ ናኢብ (የሡልጣኑ ወኪል) ማራችንን ወረሰን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ጤንነታችንን ስለሰጠን የማራችንን ዋጋ እንደጠየቅነው ከፈሉን።

ከእስክንድርያም ሌላ ሸቀጥ ገዝተን ወደ ካይሮ ሄድን። በዚያም ትንሽ ከቆየን በኋላ ወደ ኤደን ይሄዱ የነበሩ ከፌዝና ከጥለምሰን [3] የመጡ የማቅሪብ [4] ነጋዴዎች አግኝተን ከነርሱ ጋር እስከ ቶሮ ድረስ ተጉዘን ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ ወደብ ከተማ ወደ ሱዋኪን ሄድን፤ ከዚህም በኋላ ወደ ኤደን ሄድን። ጊዜው ክረምት ስለነበር ጓደኛዬ ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄድ እኔም ወደ ሕንድ እንድሄድ ተቃጥረን ተለያየን። ከጉዞአችን በኋላ የመንገዳችንን ውጤት ለንጉሣችን ለማቅረብ እንድንችል በካይሮ እንድንገናኝ ተቃጠርን። እኔም ወደ ሕንድ ጉዞዬን ቀጥዬ ከናኖር ደርሼ ከዚያም ካሊኩት ሄድሁ። ከዚያም ወደ ኋላ ተመልሼ ጎዋ ሄጄ ከጎዋ ወደ ሆሮሙዝ ተጓዝሁ፤ ጓደኛዬን ለማግኘት እንደገና ወደ ኤደንና ወደ ካይሮ ተመለስሁ። ነገር ግን ብዙ ከፈለግሁት በኋላ መሞቱን ተረዳሁ። ወደ ፖርቱጋል ለመመለስ በመዘጋጀት ላይ እንደነበርሁ ሁለት ፖርቱጌዝ አይሁዶች እኔን በመፈለግ ላይ እንደነበሩ አወቅሁ። ከነዚህ ሰዎች ጋር በአጋጣሚ ተገናኝተን እነርሱም ከፖርቱጋል ንጉሥ አንድ ደብዳቤ አመጡልኝ። እነዚህ አይሁዶች የቤዣ ተወላጅ ረቢ አብርሃምና የላሜጎ ተወላጅ መጫሚያ ሰፊው ዮሴፍ ነበሩ። መጫሚያ ሰፊው ከዚህ በፊት ባቢሎንን ስለጎበኘ የሆርሙዝን ዝና ለንጉሥ ዶም ዮሐንስ ነግሮአቸው ስለነበር ንጉሡም በሰሙት ወሬ በጣም ተደስተው ነበሩ።

ረቢ አብርሃም ሆርሙዝን ሳይጎበኝ የማይመለስ መሆኑን ለንጉሡ ቃሉን በመሃላ አረጋግጦላቸው ነበር። በአይሁዶቹ እጅ በደረሰኝ ደብዳቤ መሠረት የመጣንበት መልእክት ሁሉ ተሳክቶልን እንደሆነ እንድንመለስና ብዙ መልካም ነገር የሚደረግልን መሆኑ የተረጋገጠልን ሲሆን የሚፈለጉት መረጃዎች የማይገኙ ከሆኑ ግን ያገኘነውን ያህል በመግለጽ መልእክት እንድንልክና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እንድንጥር ታዞን ነበር። በዚህ ደብዳቤ በተለይ የታዘዝነው የታላቁን የቄስ ዮሐንስን ምስጢር እንድናውቅና የሆርሙዝን ከተማ ለረቢ አብርሃም እንድናሳይ ነበር። ወዲያው ደብዳቤ ጽፌ ቀረፋና በርበሬ የሚገኘው በካሊኩት መሆኑንና ምንም እንኳ ቅርንፉድም ከዚህ አልፎ ከሚገኝ ቦታ ቢሆንም የሚመጣው ሁሉም በካሊኩት የሚገኙ መሆናቸውን በመግለጽ በመጫሚያ ሰፊው እጄ ለንጉሡ ደብዳቤ ላክሁላቸው። ከዚህም በላይ የካናኖርን፤ የካሊኩትንና የጎዋን ወደቦች የጎበኘሁ መሆኔን፤ ወደዚህም ለመድረስ ከዚህ በፊት እስከጎበኘሁት እስከ ሶፋላ ጠረፍ ወይም እስላሞች የጨረቃ ደሴት [5] እስከሚሉት ትልቅ ደሴት ድረስ በጊኒ ባሕሮች አድርጎ ወደተባሉት የሕንድ ከተማዎች ለመሄድ የሚቻል መሆኑን ገልጬ ነበር። ይህ ደሴት ሶስት መቶ ሌግዋ ርዝመት ያለው ጠረፍ አለው ይባላል። ስለዚህ ከዚህ ደሴት ወይም ከሶፋላ በመርከብ ወደ ካሊኩት ለመምጣት ይቻላል ስል ገልጬ ጻፍሁ። ይህን መልእክት በላሜጎው አይሁድ እጅ ለንጉሡ ልኬ ከሌላው አይሁድ ጋር ወደ ኤደን ሄጄ ከዚያም ወደ ሆርሙዝ አብረን ሄድን። አይሁዱን በዚያ ትቼው ወደ ኋላ በመመለስ ጂዳን ሜካንና መሐመድ የተቀበረባትን መዲናን ጎብኝቼ ከዚያም ወደ ደብረ ሲና ሄድሁ። ማናቸውንም ደህና አድርጌ ካየሁ በኋላ እንደገና ከቶሮ በመርከብ ተሣፍሬ ከባብ ኤል መንደብ ወሽመጥ ውጭ ወደምትገኘው ወደ ዘይላ ሄድሁ። ከዘይላም ተነሥቼ ወደመካከል አገሩ ተጉዤ እምብዛም ርቆ በማይገኘው በንጉሠ ነገሥቱ ከተማ ደረስሁ። በቤተ መንግሥቱ እንደደረስሁ በዚያ ጊዜ በአልጋ ለነበረው ለአጼ እስክንድር ደብዳቤዎቼን አቀረብሁ። ንጉሠ ነገሥቱም ከፍ ባለ ደስታ ተቀብሎኝ ከፍተኛ ክብር አጎናጽፎ ወደ አገሬ የሚመልሰኝ መሆኑን ተስፋ ሰጠኝ። አጼ እስክንድር በዚያኑ ጊዜ ገደማ ሞቶ ወንድሙ አጼ ናኦድ ነገሠ፤ ይህ ንጉሠ ነገሥትም በክብር ተቀብሎኝ ነበር። ነገር ግን ወደ አገሬ ለመመለስ ፈልጌ ፈቃድ በጠየቅሁ ጊዜ ከለከለኝ። አጼ ናኦድ ከሞተ በኋላ አሁን በአልጋ ላይ ያለው አጼ ዳዊት ነገሠ። በዚህም ንጉሠ ነገሥት ዘመን ወደ አገሬ ለመመለስ ፈልጌ ፈቃድ ብጠይቅ አንተ የመጣኸው በአባቴ ዘመነ መንግሥት ሲሆን በዚህ እየተደሰትህ እንድትኖርና አገር እንድትገዛ ሲሉ እርስት ተክለው ማዕርግ ሰጥተውሃልና እኔ ፈቃድ ልሰጥህ አይገባኝም ሲል ከለከለኝ።

ጴጥሮስ ድኩቪሊያን ክርስቲያኖች እስላሞችና አሕዛብም የሚናገሩባቸውን ቋንቋዎች አጣርቶ የሚያውቅና የተላከበትንም መልእክት ጠንቅቆ ያወቀ ሰው ነው። የነዚህን ሁኔታዎች ሃተታ አሁን በፊቱ በመፈጸም ላይ ያሉ ነገሮች ይመስል አስተካክሎ ነበር የሚነግረኝ።

ምዕራፍ መቶ አምስት፤ ንጉሠ ነገሥቱ ለፖርቱጋል ንጉሥና ለሕንድ ጠቅላይ ገዥ ደብዳቤ ለመጻፍ ወሰነ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ላምባሳደሩና ወደ አገራቸው ለመሄድ ለተነሡት ለሌሎችም ፈረንጆች የሰጣቸው ሽልማት።

አሁን ወደኛው ጉዞ ወይም ድግስ በተበላበት ድንኳን ውስጥ ወደነበርነው ሰዎች ታሪክ ልመለስ እፈልጋለሁ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የንጉሠ ነገሥቱ ጸሐፊ እኛ ለፖርቱጋል ንጉሥና ለጠቅላይ ገዥው ልንወስዳቸው የታሰቡትን ደብዳቤዎች ከመጻፍ አላቋረጡም ነበር። በነርሱ ልምድ ማናቸውም መልእክትና ግንኙነት የሚከናወነው በቃል መልእክት ስለሆነ ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ፈጀባቸው። የደብዳቤ መጻፍን ልምድ ያጸኑት ከኛ ጋር ከተገናኙ በኋላ ነው። ደብዳቤውን ከመጻፋቸው በፊት የአገሩ ሊቃውንት ተሰብስበው የቅዱስ ጳውሎስን፤ የቅዱስ ጴጥሮስና የቅዱስ ያዕቆብን መልእክቶች ሁሉ በደንብ ተመራምረው ደብዳቤውን በቋንቋቸው ጽፈውት ይህንኑ ያ ሲመራን የነበረው መነኩሴ እያነበበው ጴጥሮስ ድኩቪሊያን ወደ

ፖርቱጋልኛ ተርጉሞት የኤምባሲው ጸሐፊ ዮሐንስ ኤሽኮላር አረቀቀው። ከኢትዮጵያ ቋንቋ ወደ ፖርቱጋልኛ መተርጎም እጅግ አስቸጋሪ ነገር በመሆኑ በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ቋንቋውን በማስተካከል ረዳሁ። ስለዚህ ለጌታችን ለፖርቱጋል ንጉሥና ለሕንድ ጠቅላይ ገዥም ደብዳቤው በሶስት ቋንቋ ማለት በኢትዮጵያ ቋንቋና በአረብኛ በፖርቱጋልኛም ተጽፈው እያንዳንዳቸው በሶስት ኮፒ ረቀቁ። ከያንዳንዱ ቋንቋ አንዳንድ ኮፒ ተወስዶ በሁለት የወርቅ ዘቦ ከረጢት ውስጥ አኖሩዋቸው። እነዚህ ደብዳቤዎች የተጻፉት በብራና ነበር።

ሰኞ የካቲት 11 ቀን 1521 ዓም ንጉሠ ነገሥቱ አምባሰደሩንና ጭፍሮቹን እንዲሁም በዚያ የነበሩትን ሌሎቹን ፈረንጆች ሁሉ አስጠራ። በንጉሣዊው ድንኳን ፊት ብዙ ከቆምን በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በፊት ለመጡት ፈረንጆች ያማረ የወርቅ ዘቦና የሐር ጨርቅ ዱማስ ልብስና ከዚህም በላይ የሚካፈሉት ሰላሳ አንሳሽ ወርቅ ላከላቸው። ሰዎቹ አስራ ሶስት ስለነበሩ እያንዳንዳቸው ሁለት አንሳ ወስደው በቅርጫ የሚካፈሉት አራት ተረፈ። ለነዚህ ሸሽተው ወደዚህ አገር ለመጡት ፈረንጆች እንኳ ይህን የመሰለ ችሮታ ሲደረግላቸው በማየታችን ለኛ የበለጠ ይደረግልናል ብለን በማሰብ የወርቅ ዘቦ ልብስ ተዘጋጅቶልናል ብለን ገምተን ነበር። መልእክተኞቹ ያለማቋረጥ ይገቡና ይወጡ ነበር። በዚህ ጊዜ የግራ ቢትወደዱ የብር መስቀልና አንድ የተቀረጸ የተሸለመ ዘንግ አምጥቶ ሰጥቶኝ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ዘንግ የላከልኝ ለሰጠኝ ግዛት መብትና ምልክት እንዲሆን ነው ሲል አስረዳኝ። መስቀሉንና ዘንጉን ከተቀበልሁ በኋላ እንደገና ተቀመጥን። መልእክተኞቹ ወዲያ ወዲህ የሚመላለሱበት ጉዳይ ስለአምባሳደሩና ስለጊዮርጊስ ዲ አብሬው ምክንያት ነበር። በሌላ ጊዜ አንድ መልእክተኛ መጥቶ አምባሳደሩ ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር እንዲታረቅና በመጣንበት አኳኋን ሁላችንም መሄድ እንዳለብል ነገረን። አምባሳደሩም መልሶ ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር ለመታረቅ አልፈልግም፤ ይልቁንም ግርማዊነትዎን የምለምነው ይህ ሰው እገልሃለሁ እያለ ስለሚዝትብኝ እኔ ከሄድሁ በኋላ ሁለት ወር ያህል በቤተ መንግሥቱ አቆይተው እንዲልኩት

ነው ሲል ለመነ። በዚያን ጊዜ አንድ መልእክተኛ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ ለጓዛችን ማንሻ ሰላሳ አጋሰሶች ያዘዙልን መሆናቸውን ነግሮን ከነዚሁ ውስጥ ስምንቱ ለጊዮርጊስ ዲ አብሬውና አብረውት ለነበሩ ሰዎች ዕቃ ማስጫኛ እንዲሰጡ የተወሰነ መሆኑንም አስታወቀን፤ ከዚህም በላይ ንጉሠ ነገሥቱ ለአምባሳደሩ ሰላሳ አንሳ ለጭፍሮቹም በሙሉ ሃምሳ አንሳ ወርቅ አዞልን ከሃምሳው ውስጥ ለጊዮርጊስ ዲ አብሬውና አብረውት ለነበሩት ድርሻቸው እንዲሰጣቸው የተወሰነ መሆኑን ነገረን። አንድ መቶ ጭነት ዱቄት እንዲሁም ቁጥራቸው ይህንኑ የሚያህል ቀንዶች ጠጅ ለስንቃችን መሰጠታችንን በወደቡ እስከንደርስ ድረስ የምናቋርጣቸው አውራጃዎች ገዥዎች ሁሉ እንዲመሩን መታዘዙን፤ እኛ በመጣን ጊዜ አንዳንድ ባለ ሥልጣኖች አገሬውን አንገላትተውታል ማለትን ሰምቶ ስለነበር አገረ ገዥዎቹ ድጋ እንዳያንገላቱ መታዘዙን፤ ከዚህም በላይ የአውራጃ ገዥዎች ሁሉ የሚያስፈልገንን ማናቸውንም ነገር ሁሉ እንዲያስገኙልን መታዘዛቸውን ጭምር ነገረን። ከዚህ በኋላ ያቃቤ ሰዓቱ ልጆች በባልደረብነት ተሰጡን። ይህም መደረጉ የንጉሠ ነገሥቱ አባት አጽም በገባበት በመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ በነበረው በአቃቤ ሰዓቱ ርስት አልፈን ስለተጓዝን ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን በተመረቀ ጊዜ በውስጡ የነበሩት ደብተራዎች ቁጥር አራት መቶ ሲሆን ላንድ ዓመት ጊዜ ሊቀ ካህንነቱን ይዞ የነበረው የአቃቤ ሰዓቱ ልጅ ነበር። ይህ ማዕርግ ክርስቶስን በፊቱ ባቀረቡለት ጊዜ ኬፋ ይዞት ከነበረው ማዕርግ ጋር የሚመሳሰል ነው። አቃቤ ሰዓቱ በዚያ አውራጃ ለሚገኙት ለነገሥታት አድባራት ለሆኑት ለመካነ ሥላሴና ለሌችም አብያተ ክርስቲያን ሃላፊ ነው። ማዕርጉና ትርጉሙም ርዕሰ ርዕሳን ማለት ነው። ይህ የርሱ ምድር የኤጲስቆጶስ ግዛት ሆኖ ተቆጥሮ በሌሎቹ ሁሉ የበላይነት አለው።

ምዕራፍ መቶ ስድስት፤ ንጉሠ ነገሥቱ ወርቅ ሸልሞን ለፖርቱጋልና ለሕንድ ጠቅላይ ገዥም የምናደርሰው ደብዳቤ ሰጥቶን ከቤተ መንግሥቱ ተሰናብተን ሄድን።

የዚያን ዕለት ከቀትር በኋላ ለአምባሳደሩ ሰላሳ አንሳ ለኛም ሃምሳ አንሳ ወርቅ ተላከልን፤ ከዚህም ወርቅ ጋር ውስጡ በጨርቅ በተጎዘጎዘ ልጉም አገልግል ውስጥ የተቀመጠ በወርቅና በብር የተሠራ አንድ ትልቅ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ መጣ፤ ይህ ዘውድ እንደትልቅነቱ ግምቱ ከፍ ያለ አይደለም። ይህን ዘውድ ያመጣልን የብላቴኖች ሃላፊ የነበረ አብዲናጎ ካስረከበን በኋላ ይህ ነገር የተላከበትን ምክንያት በመግለጽ አምባሳደሩ ቀጥሎ የተመለከተውን መልእክት ለፖርቱጋል ንጉሥ እንዲነግር ንጉሠ ነገሥቱ የጠየቀው መሆኑን ገለጸለት፤ የንጉሠ ነገሥቱ ቃል ቀጥሎ የተመለከተው ነው። «ዘውድ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ የከበረ ነገር ነው፤ እኔ እርስዎን እንዳባት ስለም ገምትዎ ይህን የከበረ ዘውድ ከራሴ ላይ አንስቼ ልኬልዎታለው፤ ይህን ማድረጌ ከቀይ ባሕር አካባቢ አገሮች እስከየሩሳሌም ድረስ እስላምን ለመዋጋት በሚፈቅዱት ጦርነት የባሕር ኃይልዎ የሚያስፈልገውን ያህል ሠራዊትና ወርቅ ስንቅም ልረዳዎ ዝግጁ መሆኔን ልገልጽልዎ በመፈለጌ ነው።»

ልብስም የታዘዘልን መሆኑን እናውቅ ስለነበርን ስላልመጣልን ከኛ ሰዎች አንዳንዶቹ ማጉረምረም ጀመሩ፤ ወርቁንና ዘውዱን ይዘውልን የመጡት ሰዎች ይህን ማጉረምረም ሰምተው ልብሱ ያልመጣበትን ምክንያት በመግለጽ ከሁለት ቀን በፊት መገልኛይሽ የተባለ አንድ ፖርቱጌዝ ጊዮርጊስ ዲ አብሬው ነኝ ሲል ሲያታልል በመገኘቱ በንጉሣዊው ድንኳን ፊት ተገርፎ በበትርም መመታቱን፤ ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ሰው ተግባር በጣም የተቆጣ መሆኑን፤ አምባሳደሩም ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር አልታረቅም በማለቱ በተለይ ስለተቆጣ የሚያሰናብተን በታላቅ ቅርታ መሆኑንና ልብስና ሌላም ነገር እንዳንጠብቅ ይልቁንም ከፍ ብሎ በተጠቀሱት ምክንያቶች ብዙ ነገር ሊነሳን የሚገባ መሆኑን ጨምረው ነገሩን።

ማክሰኞ የካቲት 12 ቀን የካርኒቫል[1] በዓል በሚውልበት ዕለት ከዚህ በፊት በመንገዳችን ላይ ይመራን የነበረው መነኩሴ ለፖርቱጋል ንጉሥና ለጠቅላይ ገዥውም የተጻፈውን ደብዳቤ ይዞልን መጣ። ይህ ደብዳቤ ከዚህ በፊት ለአምባሳደሩ አልተሰጠም ነበር፤ ወይም ንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደር አላከም ነበር። እነዚህ ደብዳዎች በንዴት ያለ አኳኋን እንደተዘጋጁ ከዚህ በፊት ገልጬ ነበር፤ አሁን ግን እንደዚህ መሆናቸው ቀርቶ ለንጉሣችን የሚሄዱትን ከያንዳንዱ ቋንቋ ሶስት ኮፒ አዘጋጅተው በየቋንቋቸው በሶስት ከረጢት አኖሩዋቸው፤ የጠቅላይ ገዥውንም እንደበፊቱ በሁለት ትንንሽ ከረጢቶች አኖሩዋቸው፤ ደብዳቤዎቹን የያዙትን አምስቱን የወርቀ ዘቦ ከረጢቶች ውስጡዋ በጨርቅ በተጎዘጎዘች ልጉም ሙዳይ ቆልፎ አመጣቸው። መነኩሴው ከኛ ዘንድ ሲደርስ ሙዳይቱን ፈቶ ከረጢቶቹ የተሰፉ መሆናቸውን ደጋግሞ አሳይቶን በፊታችን ሙዳይቱን እንደገና ቆልፎ አስረከበን። ሙሉ ስንብት ስለተሰጠን በፈለግነው ጊዜ ተነሥተን ለመሄድ የምንችል መሆናችንን ለአምባሳደሩ ነገረው። አምባሳደሩም መልሶ ግርማዊነታቸው መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ሊቀበሉኝ ከፈቀዱ ከመሄዴ በፊት ለመቅረብ እፈልግ ነበር ሲል ለመነኩሴው አማከረው። ነገር ግን የዚያኑ ዕለት በማለዳ ንጉሠ ነገሥቱ የሄደ መሆኑን ነገሩን። ይህም እውነት ነበር። አምባሳደሩ ሰዎችን አጉላልቶአል በማለትና ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር አልታረቅም በማለቱ እንዲሁም ሊገልጻቸው ባልፈለገው ሌሎች ምክንያቶች ንጉሠ ነገሥቱ የተቀየመበት መሆኑን እንዲሄድም ያሰናበተው መሆኑን፤ መምሕር ዮሐንስና ሰዓሊው ግን በዚያ እንዲቆዩ መታዘዙንም ነገሩን። የተባሉት ሁለት ሰዎች በዚህ አገር ቀሩ። ሙሉ ስንብት የተሰጠን መሆኑን በመገንዘብ ጉዞአችንን በቶሎ ለመጀመር በመዘጋጀት ላይ እንዳለን መነኩሴው የተባሉትን ሰለሳ አጋሰሶችና ቁጥራቸው ይህንኑ የሚያህል ለስንቃችን ጠጅ የምንይዝባቸው ቀንዶች አስይዞልን መጣ። እነዚህ ቀንዶች በታዘዙልን ጊዜ በጠጅ ተመልተው እንጂ ባዶ እጃቸውን ይመጣሉ ብለን ከቶ አልጠረጠርንም ነበር። ነገር ግን ጊዜው የዓቢይ ጾም ወራት በመሆኑ በዚሁ ጊዜ መጠጣት ልምዳቸው ስላልነበረ የሚመሩን መኳንንት እንዲሰጡን ታዘዙ። ለጊዮርጊስ ዲ አብሬውና አብረውትም ለነበሩት ከአጋሰሶቹ ስምንት፤ ከቀንዶቹም የሚደርሱዋቸውን ያህል ከፍለው

ሰጡዋቸው። በዚህን ጊዜ ከኛ ሰዎች አንዳንዶቹ ለጉዞው የሚያስ ፈልጋቸውን ለመግዛት ወደ ገበያው ሄደው ዘግይተው ስለተመለሱ ጉዞአችንን ወደ ሌላ ቀን ማስተላለፍ ግድ ሆነብን። የዚያኑ ዕለት ኃይለኛ ነፋስ ነፍሶ የድንኳኖቻችንን ካስማ ነቅሎብን ድንኳኖቻችንን ጣለብን። በዚህ አኳኋን በባዶ ሜዳ ላይ መቅረታችንን በመረዳት በዚያ ያለነው ሁሉ ኑ ኑ አሰናብተውናልና እንሂድ ስንል ጮህን። ስለዚህ በዚያኑ ዕለት በካርኒቫል ማክሰኞ ዕለት መንገዳችንን ጀምረን ስንጓዝ ካመሸን በኋላ ከቤተ መንግሥቱ አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ባንድ ቦታ ሠፍረን አደርን። ጴጥሮስ ድኩቡሊያን ሚስቱንና ልጆቹን አስከትሎ እኛን ለመሸኘት ተከተለን። መነኩሴውም ጠባቂው ይመስል ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር ሆኖ በመሄድ ከኛ ተለይተው ሠፈሩ።

በማግሥቱ ረቡእ ተነሥተን መንገዳችንን ጀምረን በመጓዝ ላይ እንደነበርን ባባቱ ወይም በቤተ ክርስቲያኑ ምድር ብዙ ቀን ስንጓዝ የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊሰጠን የዓቃቤ ሰዓቱ ልጅ ባጠገባችን አለፈ። ይህንና ሌሎችን አውራጃዎችና ቀበሌዎች ካለፍን በኋላ በአብዲናጎ ምድር ላይ ማለፍ ስለነበረብን የብላቴናዎቹ ሃላፊ አብዲ ናጎም ባጠገባችን ወደ ርስቱ ሲሄድ አገኘነው። በጫፉ ላይ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በነበረበት ባንድ ተራራ አጠገብ ደርሰን በግርጌው በሚገኝ ባንድ እርሻ ላይ አደርን። ከእርሻው ድንበር ከፍ ብሎ ስማቸው የተጠቀሰው ሰዎችም ሠፍረው ነበር። እነርሱ በዚያ መኖራቸውን ያወቅነው ከሠፈርን በኋላ ነው። መነኩሴውና ጊዮርጊስ ዲ አብሬውም አብረዋቸው ነበሩ። ለእራታችን የሚያስፈልገን ምግብ የሚገኘው በነርሱ ዘንድ ነበር። በጉዞአችን ሁለተኛ ቀን በዚያ ዕለት በመካከላችን ሰይጣን ገብቶ አዲስ ጸብ አስነስቶብን የሐንስ ጎንሳ ልቭሽ የተባለው ወኪላችናን እርሱ ራሱ ካመጣው ወይም ጠቅላይ ገዥው ከሰጠው ዮሐንስ ፍርናንድሽ ጋር ተጣልተው በበትር ማታው። ጸቡ እንደተጀመረ በተቻለ መጠን ለማስታረቅ ሞክረን ነበር፤ ነገር ግን አምባሳደሩ ለዮሐንስ ፍርናንድሽ ስላደላ ወኪሉን ትቶ ከአምባ ሳደሩ ጋር ይሄድ ጀመር። በማግሥቱ እኛ ከአቃቤ ሰዓቱ ልጅ ጋር ባንድ ጓድ፤ ጊድርጊስ ዲ አብሬው ደግሞ ከመነኩሴው ጋር በሌላ ጓድ ሆነን ተጓዝን። የሚያስፈልገር ነገር ሁሉ በየቀኑ ይሰጠን ነበር።

በአንጎት አውራጃ በአቡነ ማርቆስ ገዳም አጠገብ የአቃቤ ሰዓቱ ምድር አልቆ በአብዲናጎ ምድር ለመግባት ስንጀምር ዮሐንስ ፍርና ንድሽ ተንኮል አስቦ ከዕቃው ጋር ብቻውን ይሄድ የነበረውን ወኪሉን አድፍጦ ጠብቆ በአምባሳደሩ ጦር ሁለት ጊዜ ማለት እጁንና ደረቱን ወጋው፤ በእጁ ላይ የተሰነዘረው ጣቶቹን አቆሰላቸው፤ በደረቱ ላይ የተሰነዘረው ግን የእግዚብሔር ፈቃዱ ሆኖ በጎድኑ ላይ ስላረፈ ሆዱን ዘንጥሎ ሳይገባ ቀረ። ስለዚህ ተበታትነን በየፊናችን ስንሄድ ሳለን ባንድ መንታ መንገድ ደርሰን ግማሻችን ባንዱ ሌሎቹ ደግሞ በሌላው ስንሄድ ቆይተን ከተገናኘን በኋላ ቁስለኛውን እኔ እንዳና ዝዘውና ሌላ ሰውም እንዲያክመው ጠሩን። ቁስለኛው በሞት አፋፍ ቀርቦ አግኝተነው ነበር፤ ነገር ግን በተደረገለት ጥንቃቄ ብቻ በጎ እንዲሆን እግዚአብሔር ፈቀደ። ወኪሉን ገድሎአል እያሉ ሌሎቹ እየ ጮሁ አባረው ሊይዙትና ሊያስሩት ሲሉ ዮሐንስ ፍርናንድሽ ሸሽቶ አምባሳደሩን ሙጥኝ ብሎ ነበር። ነገር ግን ተይዞ ታሠረ። ወኪሉም አምባሳደሩን በማማረር ለአሽከሩ ወይም እንዲያገለግለው ለተሰጠው ለዮሐንስ ፍርናንድሽ በማድላትና ጠሩንም ለርሱ በመስጠት ሊያስ ገድለኝ የሞከረው እርሱ ነው ሲል ጮኸ። አብዲናጎ እኛ ልንደርስበት ወዳሰብነው ወደምድሩ ቀድሞ ሄዶ ነበረ፤ ነገር ግን በጸቡ ምክንያት ባንድ ወንዝ ዳር ማደር ግድ ሆነብን። ምንም እንኳን ጊዜው የክረምት ዝናምና ነጎድጓድም ቢያሳይም ወንዙ ለጊዜው ጥቂት ውኃ ነበር ያለበት። ስለዚህ ዮሐንስ ፍርናንድሽ ሁለት እጁን ፍጥኝ እንደታሠረ በዚያው አደርን። እስረኛውን በጥንቃቄ እንዲጠብቁት አምባሳደሩ አዘዘ። እኔም ከወኪሉ አጠገብ እንድሆን አዘዘኝ። እኔና ወኪሉ አንድ ኮርቻ ተንተርሰን እንደተኛን አንድ ሰው በሹልክታ ሄዶ እስረኛውን ፈትቶት ኖሮ ሮጦ ሄዶ በዚያው ወንዝ ዳር ከኛው ግርጌ ከነበረው ከጊዩርጊስ ዲ አብሬው ጓድ ተቀላቀለ። ከዚህ በኋላ አምባሳደሩ የበለጠ ፍርሃት አደረበት። በማግሥቱ መንገዳችንን ቀጥለን ስንጓዝ ሳለን አብዲናጎ እኛን ፍለጋ ወደ ኋላ ሲመለስ አግኝተነው ከርሱ ጋር ስንሄድ ጊዮርጊስ ዲ አብሬውና የመነኩሴውም ጓድ ሌላ መንገድ ይዘው ከአብዲናጎ ምድር ሳይወጡ ወደፊት ቀጠሉ። ስለዚህ አብዲናጎ የርሱን ምድር አልፎ እስከሚገኘው እስከ ማናዴሌይ እስከንደርስ ድረስ ከኛ አልተለየም ነበር።

ምዕራፍ መቶ ሰባት፤ በማናደሌይ ከተማ እስላሞች አደጋ ጣሉብን።

ፍጹም ሰላማዊ በሆነውና ከዚህ በፊት እንደተባለው ተገኘ እስላሞች በሚኖሩበት በማናዴሌይ ከተማ እንደደረስን ከከተማው አልፎ በነበረው በዛፎች ሥር በሚገኘው ምንጭ አጠገብ አረፍን፤ ያገሩ ሕዝብ ብዙ ነፋስና ጸሐይ የሚያገኘውን ተራራማ ቦታ እንጂ ውኃና ጥላን ስለማይወድ እኛ በምንጩ አጠገብ ስናርፍ አብዲናጎ ግን በኮረብታው ላይ ብቻውን ድንኳኑን ተከለ። ከኛ ሰዎች አንዳንዶቹ በተለይም እስጢፋኖስ ፓልያርት የተባለው የአምባሰደሩ አሽከር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለመግዛት ወደ ከተማ ሄዱ። ይህ ሰው ካንድ እስላም ጋር ጸብ አንስቶ ስለነበር ሁለት ጥርሶቹን ሰበሩት፤ ለእርዳታ ከሄዱት ከኛ ሰዎችም አንዱን ጭንቅላቱን በድንጋይ ፈንክተው ለቀውት በሰው ሸከም ነፍሱን ሳያውቃት ወደ ድንኳኑ መጣ። ይህን አደጋ በሰማ ጊዜ አብዲናጎ እኛን ለመርዳት መጥቶ ጥፋተኛ ሆነው ያገኛቸው እስላሞች እንዲታሠሩ አዘዘ። የዚያን ዕለት ጊዜው መሽቶ ስለነበር በማግሥቱ ጥዋት እርሱ ወደ ነበረበት ቦታ አስጠርቶን ሁለቱ እስላሞች ታሥረው አገኘናቸው። እርሱ በምድር ተቀምጦ ወንበሩት ተደግፎ ስለነበር እኛም በምድር በሣሩ ላይ እንድንቀመጥ አዘዘን። በዚያ እንደተቀመጥን እስረኞቹ ቀርበው ልዩ ልዩ ጥያቄ ቀርቦላቸው በደለኛነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ልብሳቸውን አውልቀው በጭካኔ እንዲገረፉ አዘዘ። ጅራፉ ባረፈባቸው ቁጥር ምን ትሰጣለህ የሚል ጥያቄ በቀረበላቸው ቁጥር አንድ አንሳ! ሁለት! ሶስት! እያሉ ይጮሁ ነበር። ነገር ግን በዚህ ተስፋ ባለመደሰት ግርፋን ቀጥለው ምን ትሰጣለህ እያሉ ጠይቀዋቸው ሰባት አንሳ ለመስጠት ቃል ከገቡ በኋላ ተዋቸው። ይህን ሰባት አንሳ ወርቅ ለሁለቱ ቁስለኞች ካሣ እንዲሆን ተሰጠ። እስላሞቹም እንዲታሠሩ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ተላኩ። የነዚህ ሰዎች መጨረሻ ምን እንደሆነ ቀጥሎ እገልጸለሁ።

መንገዳችንን ይዘን ወደፊት ተጉዘን ከባሕሩ ስንመጣ ባረፍንበት በድባርዋ ከተማ ደርስን በዚያ ጥቂት ቀኖች እንደቆየን ከንጉሠ

ነገሥቱ ዘንድ መልእክተኛ መጥቶ ከመልእክተኛውም ጋር ከተገረፉት እስላሞች አንደኛውና የሌላውም ጭንቅላት መጣ። መልእክተኛውም ንጉሠ ነገሥቱ የእስላሞቹን ወንጀልና በፖርቱጊዞቹም ላይ የፈጸሙትን የመረመረ መሆኑን፤ ከሁለቱ ሰዎች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘውን ሰው ራሱን ማስቆረጡንና እውነተኛውንም እንድናውቅና ወንጀለኛው መቀጣቱን ለማስረዳት ጭንቅላቱን የላከው ሌላውን ግን በበኩሉ በደለኛ ሆኖ ስላላገኘው እኛ ያሻንን ነገር በመፈጸም ወይም ለመግደል ወይም ነፃ ለማውጣት ወይም በግዞት ለመያዝ ሙሉ መብት የተሰጠን መሆኑን ገለጸልን። ስለዚህ እስላም በንድነት ተሰብስበን ተመካክረን ምን ማድረግ እንደሚገባን አምባሳደሩ ጠየቀን። እኔ የሁሉንም ምኞት አውቅ ስለነበርሁ ስለ ሁሉም በመናገር ቀጥሎ የተመለከተውን አስተያየት ገለጽሁ። ንጉሠ ነገሥቱ ሰውዬውን በደለኛ ሆኖ አላገኘሁትም ሲል ስለላከው እኛ በበደለኛነት ልንይዘው አይገባም፤ እኛ የበኩላችንን ቅጣት ብንሰጠው ምሕረት የማያቁ ተብለን እንታማለን፤ ስለዚህ ይህን ሰው ወደመጣበት ብንመልሰው ንጉሠ ነገሥቱ መልካም ተግባር አድርጎ ይቆጥረዋል ስል አምባሳደሩን አማከሩሁት። በዚያ የነበሩት ሁሉ የኔን ሃሳብ ደግፈው ነበር፤ ነገር ግን አምባሳደሩ ይህን ሃሳብ ስላልተስማማበት ያን ሰው እንደባርያ አድርጎ ለመያዝ ስላሰበ በከባድ ሰንሰለት አስሮ አስር ቀን አቆየው። ዳሩ ግን ምንም እንኳ በጥብቅ ቢታሠርም አምልጦ ጠፋ።

ምዕራፍ መቶ ስምንት፤ ሁለት ታላላቅ የቤተ መንግሥቱ መኳንንት ከኛ ጋር እንደተወዳጁና ለጠቅላይ ገዥው ሊያስረክቡን ከኛ ጋር ስለመሄዳቸው።

ከዚህ በፊት እንደተባለው ወደ ባርዋ ለመሄድ የማናዴሌን ከተማ ትተን ብዙ አውራጃዎች አቋርጠን ስንሄድ አብዲናጎ እንደ ታዘዘው ከኛ ጋር መነኩሴውም ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር ይሄዱ ነበር። ወደፊት ብዙ ከተጓዝን በኋላ ጨካኝ ሰዎች የሚኖ

ሩበት አምባሰናይት በተባላ ባንድ ትልቅ ቀበሌ ደረስን። ጩካኝ ናቸው ያልሁበት ምክንያት ድንጋይ ሊወረውሩብን ስለሞከሩና እንዲያውም ስለወረወሩብን ነው። ይህ ቦታ የትግሬ አውራጃ የሚያልቅበት ድንበር ላይ ነው። በዚህ ቦታ ሠፍረን እንዳለን ሁለት መኳንንት ከቤተ መንግሥቱ ወደኛ መጡ። ከነዚህም አንዱ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በመደጋገም ስሙን የጠቀስሁት በቤተ መንግሥቱ በደረስን ጊዜ ባልደረባችን እንዲሆን የተሰጠን ሕዱግ ራስ ነው። ሌላውም ግራጌታ የሚያሰኝ ማዕርግ ያለው ራስ ነቢያት የተባለው በኋላም ባሕርነጋሽነት ከዚያም ቢትወደድነት የተሾመው ነበር። ከኛ እንደተገናኙ በመጀመርያ ያነሱብን ጉዳይ ምንም እንኳ ንጉሠ ነገሥቱ ቢለምነውም አምባሳደሩ በፊቱ ቀርቦ ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር ባለመታረቁ ቅር የተሰኘበት መሆኑን ነበር፤ ስለዚህ ሰዎቹ እንደተቀያየሙ በጠቅላይ ገዥው ፊት መድረስ ነውር ነገር ስለሆነ ይታረቁ ዘንድ ንጉሠ ነገሥቱ ለሁለተኛ ጊዜ የጠየቀ መሆኑን ነገሩን፤ በመንገድ ላይ የተጣሉት ሁለቱም ደግሞ እንዲታረቁ መጠየቁን ነገሩን። ከዚህ በኋላ የተጣሉትን አገናኝተን አስታረቅናቸው። ይህ ከሆነ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ለያንዳንዳችን የላከልንን አንዳንድ በቅሎ መኳንንቱ አከፋፈሉን፤ እነዚህ መኳንንት የመጡበት ጉዳይ እኛን ሕንድ ጠቅላይ ገዥው ድረስ ለማድረስና ባሕር ነጋሹና ሌሎችም ባሕር ነክ አውራጃዎችን የሚገዙ መኳንንት ለጊዜው በቤተ መንግሥቱ ስለሚገኙ በነርሱ ምትክ ጠቅላይ ገዥውን በንጉሠ ነገሥቱ ስም ለመገናኘት መሆኑን ነገሩን። የኛ ሰዎች ከታረቁና በቅሎዎቹም ከተሰጡን በኋላ ተመልሰን እስከ ባርዋ ድረስ ተጓዝን፤ መርከቦቹ እስከሚመጡበት እስከ ክረምቱ ወራት መጨረሻ ድረስ በዚያ ከተማ ቆየን። ጊዜው ካለፈ በኋላ አምበሳደሩ ዶም ሩዲሪጉ ድ ሊማ ለጊዮርጊስ ዲ አብሬው ወይም አብረውት ለነበሩት ሁሉ ምግብ እንዳይሰጥ ከለከለ። ወኪሉን ባቆሰለው በዮሐንስ ፍርናንድሽ መልእክተኛነት ጊዮርጊስ ዲ አብሬው አምባሳደሩን በመለመን ልኮበት ነበር። ነገር ግን አምባሳደሩ መልእክተኛውን ሊመታው ስለፈለገ ሸሽቶ አመለጠ። የዚህን ጊዜ ጊዮርጊስ ዲ አብሬው ለብቻዬ ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን አስጠርቶኝ አምባሳደሩ ምግቡን ለርሱና አብረውት ለነበሩት ሁሉ እንዲያዝለት እነግርለት ዘንድ በሽምግልና

ላከኝ። እኔም መልእክቱን ነግሬው ምግቡን ለጊዮርጊስ ዲ አብሬው ሊሰጥ ሲስማማ የተቀሩት ግን ከፖርቱጋል ንጉሥ አገልግሎት የከዱ ስለሆኑ የማይሰጣቸው ነው ሲል መወሰኑን ለጊዮርጊስ ዲ አብሬው ነገርሁት፤ ጊዮርጊስ ዲ አብሬው በነገሩ ባለመደሰት እኔ ምግቡን የጠየቅሁት አብረውኝ ለነበሩት ነው እንጂ ለራሴ አልነበረም፤ ስለዚህ የጠየቅሁት ካልተሰጠኝ እኔው ራሴ እወስደዋለሁ ሲል ዝቶ እንደገና ተለያየን። ወዲያውኑ ወደ ሕዱግ ራሱና ወደ ግራጌታው ሄዶ አቤቱታውን አቀረበ። ከዚህ በኋላ እነዚያ መኳንንት በሠፈሩበት መልካምና ሰፊ ቦታ ላይ ሳይሆን ባንድ ማረገጃ ላይ እንድንሰበሰብ አዘዙን። በዚያ እንደተሰበሰብን አምባሳደሩ ያገሩን ሰዎች በምን ምክንያት እንደበደላቸው ጠይቀውት እርሱ (ሕዱግራሱ) ያዘዘላቸውንም ስለከለከላቸው እርሱን ለመደገፍ ፈረሶችና በቅሎችን ለመሸጥ የማይችል መሆኑን ይህም የጨዋ ልምድ አለመሆኑን ገለጸለት፤ ሰዎቹን በንደዚህ ያለ መንገድ በመበደሉ ንጉሠ ነገሥቱ የቱን ያህል ቅር እንደሚለው ይገምተው ዘንድ አሳሰበው። ስለዚህ ሰዎቹን በተሻለ ሁኔታ ቢይዛቸው እርሱ ራሱ በተለየ አኳኋን ተይዞ ካሁኑ በበለጠ አኳኋን የሚደሰት መሆኑን ነግሮት ተስፋ በሰጠው መሠረት ከጊዮርጊስ ዲ አብሬው ጋር ወዳጅነቱን እንዲያጸና ለመነው። አምባሳደሩ ግን አቤት ባዮቹ ከፖርቱጋል መንግሥት አገልግሎት የከዱ ናቸው ሲል ምግቡን የማይሰጣቸው መሆኑን አስታወቀ፤ ጊዮርጊስ ዲ አብሬው የበፊቱን ቃል በመድገም ምግቡ ካልተሰጠው በገዛ ራሱ የሚወስድ መሆኑን አስታውቆ ሁላችንም ቅር እንዳለን ጉባኤው ተበተነ። ምግቡ ካልተሰጠኝ በገዛ ራሴ እወስደዋለሁ ሲል ጊድርጊስ ዲ አብሬው ማስፈራራቱን ወኪሉ ሰምቶ ስለነበር ድንገት አደጋ ጥሎ ይቀማኛል ብሎ በመፍራት አምባሳደሩ ባረፈበት ቤት ውስጥ ገብቶ አደረ፤ ቤቶቹ እንደ አገሩ ሁኔታ ጠንክረው በደንብ የተሠሩ ናቸው። የአምባሳደሩ ጸሐፊና እኔ አሳት የምሆነው አንድ ፖርቱጌዝ ወጣት እኔም ባንድነት ተኝተን እንደነበርን ሌሊቱ በጣም ከገፋ በኋላ «እዚህ ተኩስ እዚያ ተኩስ» የሚል ድምጽ ሰማን። ወዲያው የጠበንጃ ድምጽ ተከተለ። (የኔ ዘመድ ያይን ሕመም ስለነበረበት ወደኋላ ሲቀር) እኔና ጸሐፊው በፍጥነት ወደላይ ሮጠን ሄደን ቤቱን በድንጋይ ሲደበድቡት አየን። በቤቱ ላይ የሚያወርድበት የድንግይ

ውርጅብኝ በጣም ከፍ ያለ ስለነበር በውስጡ የነበሩት ሰዎች ያለቁ መስሎን ነበር። ስለዚህ በባሕር ነጋሹ ቤት አርፈው የነበሩት መኳንንት ወደኛ እንዲመጡና እንዲረዱን ለመለመን እነርሱ ወደነበሩበት በሩጫ ሄድን። ይህ ቤት ሁለት በር ስለነበረው እኛ ባንዱ በር ስንገባ አምባሳደሩና ሰዎቹ ዘውዱንና የንጉሡ ነገሥቱን ደብዳቤዎች እንዲሁም ሊይዙዋቸው የቻሉትን ዕቃዎች ይዘው በሌላው በር ገቡ። ከአምባሳደሩ ሰዎች አንዱ ጉልበቱን በጥይት ቆስሎ መጣ፤ ሰዎቹ ከአለሎ ሌላ ጥይትም ይዘው ስለነበር አምስት ሰዎች አቆሰሉ። አምባሳደሩና ሰዎቹ ሊያመልጡ የቻሉት እነዚያ ባለወቁት ባንድ ስርቆሽ በር ሾልከው በመውጣታቸው ነበር።

ከዚህ በኋላ እነዚያ መኳንንት ሰዎቹን በሙሉ አስረው እኔና ጸሐፊው ግን እርሱ ከላካቸው ሰዎች ጋር አብረን እንድንሄድ ፈቀዱልን። ሞገደኞቹ በውስጥ የነበሩትን ሰዎች ያገኙ መስሎዋቸው ቤቱን ያለማቋረጥ ሲደበድቡ ደርሰንባቸው በዚያን ጊዜ ባሩድ አልቆባቸው ስለነበር እንዲያውም ራሳቸውን መጠበቂያ እንኳን ምንም ስላል ነበራቸው በቡጢና በበትር መተው ወደ መኳንንቱ አቀረቡዋቸው። ትንሽ ካጉላሉዋቸው በኋላ በዚያ ከተማ አጠገብ በሚገኘው ጋዝሊያንዛ በተባለ ባንድ ሌላ ከተማ ወስደው ወዲያ ወዲህ ሳይንቀሳቀሱ በዘበኛ እየተጠበቁ እንዲቆዩ ታዘዙ። በዚህ አኳኋን ብዙ ጊዜ በማለፉና እነርሱንም ሊያዩዋቸው ባለመቻላቸው እንዲሁም ባገሩ ልምድ መሠረት ማንም መኮንን ከቤተ መንግሥቱ ያለ ፈቃድ ለመውጣት ወይም ካልተጠራ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሊሄድ ስለማይችል ሕዱግ ራሱና ግራጌታው ሊተዉን ወይም ሊወስዱን አልደፈሩም ወይም ሊያስታርቁን ባለመቻላቸው መላው ጠፍቶአቸው ነበር። በመጨረሻው ግን ወደ ቤተ መንግሥቱ ሊመልሱንና ይህን በማድረጋቸው የሚደርስባቸውን ቅጣት ለመቀበል ቆረጡ።

ምዕራፍ መቶ ዘጠኝ፤ ወደ ቤተ መንግሥቱ በሚመልሰው መንገድ እንደወሰዱንና ወደዚህ አገር መልሰው እንዳመጡን።

እነዚህ መኳንንት ወደኛ ለመምጣት ጊዜ ያለፈ መሆኑን በመረዳትና በፊት እንደተገለጸው በመካከላችን ሰላም በመጥፋቱ በደኋላ መልሰውን እኛና የሚሸኙንም ፈረንጆች ጉዞአችንን ቀጠልን። ከዚህ በፊት በተጠቀሰው በመጀመርያው ከተማ በአምባ ሠናይት ስንደርስ ሕዝቡ እኛን አለመቀበል ፈልጎ በመከላከል በሰልፍ ቆሞ አገኘነው፤ ብዙዎች ካህናት እንደበጎች እየተንጋጉ ከአንድ ተራራ ወደ ታች መጡ፤ ሁሉም ቀስታችውንና ሌላም የጦር መሣርያ ይዘው በሜዳ ላይ ጦርነት የገጠምን ይመስል ነበር። ከሁለቱም በኩል የቆሰሉ ነበሩ። ነገር ግን ሜዳው ከኛ በኩል ስለነበር እኛ በከተማው ውስጥ ለማደር ስንገባ የከተማው ነዋሪዎች ደግሞ ወደ ተራራው ሄዱ። የነዚያ መኳንንት ጭፍሮች ያን ከተማ ልክ እንደ እስላም ከተማ አድርጎ በመገመት ማናቸውም ነገር ማለት ስንዴና ገብስ፤ ዶሮችና በጎች፤ የቤት ዕቃና በእጃቸው የገባላቸውን ነገር ሁሉ በሙሉ ዘረፉ። ከዚህ ቦታ ተነሥተን በልዩ ልዩ ቦታ ተከፋፍለን ማለት ጊዮርጊስ ዲ አብሬው ከሰዎቹና ከመነኩሴው ጋር፤ እኛ ከአምባሳደሩ ጋር እንዲሁም ሕዱግ ራሱና ግራጌታው ሆነው ጉዞአችንን ወደፊት ቀጠልን። የኛ ሰው በቆሰለበት በማናዴሌይ ከተማ ደረስን፤ ያን ከእስር ያመለጠውን እስላም በዚያ አግኝተነው ነበር፤ ነገር ግን ግን አምባሳደሩን በማየቱ ጥቂት እንኳን ደንገጥ አላለም። ከዚህ ከተማ ግማሽ ሌግዋ ያህል ወደፊት እንደተጓዝን መኳንንቱና እኛም ምን ማድረግ እንደሚገባን ሳናውቅ መልእክት ይዞ ከቤተ መንግሥት ሲመጣ ባሕር ነጋሹን በመንገድ አግኝተነው ሁላችንም ባንድነት ተሰብስበን ባንድ እርሻ ውስጥ በሚገኝ ዛፍ ሥር ተቀመጥን። እነዚህ መኳንንት ያለ ፈቃድ እኛን እዚያ ድረስ መልሰው ስላመጡን ባሕር ነጋሹ ከፉኛ ገሠጻቸው። አምባሳደሩንና ጊዮርጊስ ዲ አብሬውንም በጣም ጮኸባቸው፤ አምባሳደሩ የያዘውን የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድና ለፖርቱጋል ንጉሥና ለጠቅላይ ገዥውም የተላኩትን ደብዳቤዎች በቶሎ እንዲያስረክበው ባሕር ነጋሹ አዘዘው። በዚህን ጊዜ አምባሳ

ደሩና ጊዮርጊስ ዲ አብሬው በጣም አጸያፊ የሆነ የስድብ ቃል ተለዋወጡ። ከዚህ በኋላ ሌሎቹ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሄደው ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ አዘዘ። እኛንም በተለይ የሚመሩን ባለሥልጣኖች አዘዘልን። ስለዚህ በኃይለኛ ዝናም ውስጥ እርሱን ተከትለን እስከ ግዛቱ ድረስ ሄድን። ከአምባሳደሩ ጋር የሄድነውን ጸቡ ወደተጀመረበት ወደ መናገሻ ከተማው ወደ ባርዋ ወሰደን፤ ጊዮርጊስ ዲ አብሬውና ጓደኞቹን በሰራዌ አውራጃ ግዛት ዋና ከተማ በባራ[1] ከተማ ሠፈሩ፤ ይህን ያደረገበት ምክንያት ከአምባሳደሩ ጋር እንዳይጣላ በማለት ነበር፤ በዚህ ጊዜ በስንቅ ረገድ በጣም ተበድለን ነበር። ጊዮርጊስ ዲ አብሬውና ጓደኞቹ ከኛ በተሻለ አኳኋን ስንቅ ያገኙ ነበር። ነገር ግን በሠፈርንበት አጠገብ ወንዝ ስለነበር አሣ እያጸመድንና እያደንንም ራሳችንን ደግፍን።

ምዕራፍ መቶ አስር፤ ስለ ዓቢይ ጾም።

በመላ ኢትዮጵያ የዐቢይ ጾም ከኛ ጾም አስር ቀን ቀደም ብሎ ይጀምራል፤ ከንጻት ቀን በኋላ ካህናት መነኩሴዎችና ተራው ሕዝብ የሚጾሙበት የነነዌ ጾም ይጀምራል። ይህን ጾም በያመቱ የሚጾሙበት ምክንያት በነነዌ ከተማ ሶስት ቀን ጾምና ጸሎት የተደረገውን ለማስታወስ ነው ይላሉ፤ በዐቢይ ጾም ወራት ከእንጀራና ከመጠጥ በስተቀር ሌላ ምግብ እምብዛም አይበላም። ምክንያቱም ምንም እንኳ አሣ ለመብላት ቢፈቀድላቸውም በአገሩ በመላ የባሕር አሣ አይገኝም። በየወንዞቹ ብዙ አሣ ይገኛል፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ባንዳንድ መኳንንት ምግብ ቢጠመድም በጠቅላላው ሕዝቡ ያሣ አጥማጅነት ዘዴ የለውም። በጾሙ ወራት የሚበላውም የዘወትር ምግብ እንጀራ ነው። በክረምቱ ወራት ካልሆነ በስተቀር በዚህ ጊዜ ጎመን አይገኝም። ፍራፍሬንና ቅጠላቅጠል አትክልትንም ማጽደቂያ በቂ ውኃ ስላለ ሕዝቡ ዘዴ ቢኖረው ኖሮ ይህ ሊጠፋ አይችልም ነበር። በብዙዎቹ ገዳሞች ዓመቱን በሙሉ ቅጠሉን እየለመለሙ የሚበሉት ጎመን አይቻለሁ። የወይንና የኮክ ጊዜ ከየካቲት

መጨረሻ እስከ ሚያዚያ መጨረሻ ድረስ ስለሆነ እነዚህ ፍሬዎች ባሉባቸው አውራጃዎች የሚኖሩ ሰዎች የሚበሉት አላቸው። አብዛኛውን ጊዜ የሚበሉት ከንፋ የተባለ ቅጠል ፍሬ ሲሆን ከዚሁ ቅጠል ጸብሃ የተባላ የሚያቃጥል ሾርባ ሠርተው እንጀራውን በዚያ ውስጥ ይፈተፍቱታል። ከዚህም በላይ ሰናፍጭም ይመገባሉ። እነዚህ ሶስት ማባያዎች በዐቢይ ጾም ጊዜ አዘውትረው የሚበሉ ናቸው። በጾሙ ወራት ወተትና ቅቤ መመገብ የወይን ወይም የማር ጠጅ መጠጣት አይፈቀድም። በማዘውተር የሚጠጣው የገብስ ጠላ ነው፤ ይህ መጠጥ ከማሽላና ከዳጉሳም ይጠመቃል። በትክክለኛነቱ የጠጡት እንደሆነ አዙሮ ስለሚደፋ ከቀዘቀዘና ከተጣራ በኋላ ነው የሚጠጡት። ጠላ በአገሩ በሙሉ በጣም የተወደደ መጠጥ ነው። አንዳንዶች መነኩሴዎች በዐቢይ ጾም ወራት አንዳንዶቹም ዓመቱን በሙሉ ሌሎችም ዕድሜአቸውን በሙሉ እንጀራ አይበሉም፤ ስለዚህ ያየሁትን ከዚህ በታች እገልጻለሁ።

አምባሳደሩና እኔ ወደ ቤተ መንግሥቱ ስንጓዝ ሳለን ጃኖሞራ በተባለ ቀበሌ እንደደረስን ቀማኛዎች እንዳይተናኮሉት በመፍራት አንድ መነኩሴ ከኛ ጋር ተቀላቅሎ ሳይለየን አንድ ወር ያህል ተጓዘ፤ ይህ ሰው መነኩሴ ስለነበር እኔ በጣም አስጠግቼው ነበር። ወደ ክህነት የሚሄዱ ስድስት ወይም ሰባት ወጣቶች አስከትሎ ነበር። እንዲሁም የሚሸጡ አራት ትልልቅ መጽሐፍት በበቅሎ ላይ ጭኖ ይዞ ነበር። በኔ ድንኳን ውስጥ ገብቶ እንዲያድር ፈቅጄለት ስለነበር የመጀመርያው ዕለት የአራት መብያ ሰዓት በደረሰ ጊዜ ከኔ ጋር እነዲበላ ጋበዝሁት። ነገር ግን ይቅርታ ጠይቆኝ ሊበላ የማይፈቅድ መሆኑን ገለጸልኝ። በዚህን ጊዜ ወጣቶቹ ቅጠል ይዘው መጥተው ይህን ቅጠል ያላንዳች አማካይ ነገር አገንፍለው በሉ። ይህን የሚያደርጉበትን ምክንያት ለመረዳት ወጣቶቹን ብጠይቃቸው እንጀራ የማይበሉ መሆናቸውን ገለጹልኝ። እንጀራ የማይበሉ ብዙ መነኩሴዎች አሉ ማለትን ደጋግሜ ብሰማም እጠራጠር ስለነበር መነኩሴውን በቅርብ ሆኜ ሌት ከቀን እመለከተው ነበር። የእልፍኝ አሽከር ይመስል ቀኑን ሙሉ ከኔ ሳይለይ ሌሊትም በኔው አጠገብ ቀን የለበሰውን ልብስ ሳያወልቅ በምድር ላይ ይተኛ ነበር። ከኔ

ጋር በነበረበት ጊዜ ሁሉ የሚያገኛቸውን ቅጠላ ቅጠል ምግቦች እንጂ ከቶ ሌላ ነገር ሲበላ አላየሁትም፤ ለምሳሌ ባንድ ገዳም አጠገብ ያለፍን እንደሆነ ወደዚያ ገዳም መልእክተኛ ይልክና ጎመን እንዲያመጡለት ይጠይቃል። ይህ ያልተገኘ እንደሆነ በቅል ውኃ ውስጥ ተነክሮ የበቀለ የምስር ቦቀልት ያመጡለትና ያንን ይመገባል። ይህን ቦቀልት እኔ ራሴ ቀምሼው በዓለም ከሚገኝ ምግብ ሁሉ ቃና ቢስ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ይህ መነኩሴ ከኛ ጋር አንድ ወር ያህል በተጓዘ ጊዜና በቤተ መንግሥቱም ከደረስን በኋላ ከኛ ጋር ሶስት ሳምንት ሲቀመጥ እላይ የተጠቀሱትን ቅጠላ ቅጠል እንጂ ከቶ ሌላ ነገር አልበላም። ከዚህ ጊዜ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ልኮን በአክሱም ከተማ ስምንት ወር ተቀምጠን ስለነበርን ይህን መነኩሴ በዚያው አገኘነው። በዚያ መገኘቴን እንደሰማ ሊያገኘኝ በቶሎ መጥቶ ጥቂት ሎሚም ይዞልኝ መጣ። እጅጌ የሌለው የቆዳ ልብስ እንደለበሰ ክንዱም ባዶውን እንደሆነ ወደኔ ዘንድ መጥቶ ተሳሳምን። በተሳሳምን ጊዜ እጄን በክንዱ ሥር አኑሬ ስለነበር በሽንጡ ዙርያ አራት ጣት ስፋት ያለው ብረት የታጠቀ መሆኑን ተረዳሁ። ከዚህ በኋላ እኛ ወዳረፍንበት ቤት ወስጄው ያንን የቀነተውን ብረት እኔ አጎት ለምሆነው ለጴጥሮስ ሎፕሽ አሳየሁት። ከዚህም በላይ ይህ ብረት ዳርና ዳሩ ተጋጥሞ የመጋዝ ጥርስ የሚመስሉ ወፍራም ሾል ጫፎች ያሉበት ጎኑ በሰውነቱ ላይ አርፎበት አየን፤ ይህን ያደረገው በዐቢይ ጾም ወራት አልነበረም። መነኩሴው ይህን ስላየንበት ተቆጥቶ ዳግመኛ አልጎበኘንም፤ እንዲያውም በዚሁ ምክንያት ብቻ ከተማውን ለቆ ሄዳ።

በዚህ ዓይነት ኑሮ የሚኖሩ ሌሎች ብዙ መነኩሴዎችም አየን። በዐቢይ ጾም ወራት ከቶ ሳይቀመጡ ቆመው ጊዜ ውን የሚያሳልፉት መነኩሴዎችም አሉ ማለትን ሰምተናል። እኛ ከነበርንበት ቦታ ሁለት ሌግዋ ርቆ በሚገኝ ባንድ ዋሻ ውስጥ ይገኝ የነበረ አንድ የበቃ ሰው ይህን የመሰለውን የመቆም መማለል ያደርጋል ማለትን ሰምተን (በዐቢይ ጾም ወራት) እኔና ሌሎቹም ፖርቱጊዞች በበቅሎ ተቀምጠን እቦታው ድረስ ሄድን። በርሱው ቁመት ልክ በተሠራ ባንድ ጎጆ ውስጥ ቆሞ አገኘነው። ጎጆው ክዳን የሌለው ሣጥን መስሎ የተሠራ ሲሆን ግድግዳው በጭቃና በእበት ተመርጓል። ይህ ጎጆ በተሠራበት ቦታ ላይ ተሠርተው የነበሩ ሌሎችም ነበሩ፤ ጎጆው አርጅቶአል። ታፋው በሚደርስበት ላይ ሶስት ጣት ስፋት ያለው ሳንቃ አለ፤ ክርኖቹም በሚደርሱበት ለያንዳንዳቸው ሳንቃ አላቸው። በፊት ለፊቱም መጽሐፍ የተቀመጠበት አንድ አረፍት ነበር። ይህ ሰው ከበሬ ጅራት ጠጉር ጋር ተቀላቅሎ የተሠራ ማቅ ለብሶአል። በአክሱም እንዳየነው መነኩሴ ይህም ሽንጡን በሰንሰለት ቀንቶአል። ይህ መነኩሴ ትጥቁን ያሳየን እኛ ሳንጠይቀው በገዛ ፈቃዱ ነው። ይህን የመሰለ ትጥቅ ያለው መሆኑን እኛ ከቶ አላወቅንም ነበር። ይህ መነኩሴ ከሚኖርበት አጠገብ በነበረ ባንድ ዋሻ ውስጥ የሚኖሩ መነኩሴውን ቅጠላ ቅጠል ምግብ የሚያቀብሉ ሌሎች ሁለት ወጣት መነኩሴዎች ነበሩ። በነዚህ ዋሻዎች ውስጥ መቃብር ስለነበር ዋሻዎቹ ብዙ ጊዜ የመማለያ ቦታዎች ነበሩ። መነኩሴው ከዚያ ጉብኝት በኋላ በጣም ተወዳጅቶን ስለነበር ከጾሙ በኋላ እየመጣ ይጎበኘን ነበር።

በሌላ የዐቢይ ጾም ወራት በድባርዋ ከተማ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በግርና ቀኝ ሆነው ሁለት መነኩሴዎች ይህንኑ የመሰለ መማለል ሲያደርጉ አይተናል። ከዚህ በፊት እንዳየነው መነኩሴ እነዚህም የሚመገቡት ቅጠላ ቅጠልና የምስር በቀልት ነበር። ብዙ ጊዜ እጎበኛቸው ነበር፤ በዚሁ ጉብኝቴ የተደሰቱ መሆናቸውን አሳይ ተውኛል። ሳልጎበኛቸው ጥቂት ቀኖች ያለፉ እንደሆነ ሰው ልከው ያስጎበኙኝ ነበር። ባየኋቸው ጊዜ ልብሳቸውን ለብሰው ነበር። ከልብ ሳቸው በታች ማቅ አሸርጠው ወይም ሽንጣቸውን በሰንሰለት ቀንተው እንደሆነ አላውቅም። ከዚያ ጎጆ ወደ ውጭ ይወጡ እንደሆነ ብጠይ ቃቸው ወዲያ ወዲህ እየተዘዋወሩ ነገር ግን ሳይቀመጡ እንደሚጎበኛኙ ነገሩኝ። ከነዚሁ መነኩሴዎች አንደኛው የንጉሠ ነገሥቱ ዘመድ ነበር ይላላል። በዚህ ዓይነት በሱባኤ እስከ ፋሲከ ድረስ ይቆዩና ከትንሣኤ ቅዳሴ በኋላ ይወጣሉ።

በዐቢይ ጾም ወራት ረቡእና አርብ እስከ አንገታቸው ድረስ በውኃ ውስጥ ጠልቀው የሚተኙም አሉ ማለትን ሰምተናል፤

ነገር ግን ልናምን አልቻልንም ነበር። ስለአክሱም ከተማ ከዚህ በፊት ባተትሁ ጊዜ በጠቀስሁት በዐቢይ ጾም ወራት በአጠገቡ ትልቅ ገበያ በሚውልበት ባንድ ትልቅ የውኃ ማጠራቀሚያ ውስጥ እየተኙ የሚጸልዩትን ሰዎች ለማየት የሚቻል መሆኑን ነገሩን። የኤምባሲው ጸሐፊ ዮሐንስ ኤሽኮላርና የኔ ዘመድ ጴጥሮስ ሎፕሽ ወደተባለው ውኃ ማጠራቀሚያ በምሽት ሄደው ብዙ ሰዎች እስከ አንገታቸው ድረስ ጠልቀው በማየታቸው ተገርመው ተመለሱ። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው በከተማው ብዙ ካህናት ስለሚገኙ በውኃው ውስጥ የነበሩት ሁሉ ደብተራዎችና ባለቤቶቻቸው፣ መነኩሴዎችና መነኩሲቶች ነበሩ። ይህን ግሩም ነገር ሰምቼ እኔም ሐሙስ ጥዋት እቦታው ድረስ ሂጄ ማጠራቀሚያው ዙርያውን ድንጋይ ተኮልኩሎበት አየሁ። በጣም ጥልቅ ባልሆኑት ክፍሎች አንዳንድ ድንጋዮች ተቀምጠዋል። እየጠለቀ እንደመሄዱ መጠን ደግሞ ድንጋዮቹ እየተደራረቡ ተቀምጠዋል። እነዚህ ድንጋዮች ሁሉ ሰዎቹ በውኃው ውስጥ እስከ አንገታቸው ድረስ ጠልቀው የሚጸልዩባቸው ናቸው ሲሉ ነገሩኝ። በዚህ ወራት በከተማውና በአካባቢው የሚገኙ አመዳይ የሚጥልበትና ሌሊቱም በጣም የሚቀዘቅዝበት ነበር። ይህን ካየሁ በኋላ ጴጥሮስ ድኩቩሊያንን ደራ በተባለ ቦታ አግኝቼው ያየሁትን ነገርሁት። ነገር ግን ይህን ትርኢት እርሱም ያውቀው ስለነበር በነገሩ በፍጹም ያልተጠራጠረ ከመሆኑም ይልቅ ይህን የመሰለ ተግበር በመላ ኢትዮጵያ የሚደረግና ከዚህም በላይ ከቶ ሰው ባልደረሰባቸው ውኃ በሚገኝባቸው ቦታዎች መንነው በዱር በገደል የሚኖሩ ብዙ ሰዎች ያሉ መሆናቸውን እንዳውቅ ነገረኝ።

ከዚህ በፊት እንደተገለጸው በደራ አጠገብ ሰው በማይኖርበት ባንድ ትልቅ ሜዳ ላይ የሚገኙ በጣም ትልቅ የሆኑ ገደሎች አሉ። በነዚህ ገደሎች ውስጥ የሚገባ አንድ ትልቅ ወንዝ አለ። ፏዋፏዋቴው ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ ከገደሉ እየተወረወረ ወደ መሬት ሲወድቅ ጉም ይመስላል። ጴጥሮስ ድኩቪሊያን በጣም የማይታይ አንድ ዋሻ በዚያ ገደል ውስጥ አሳየኝ። በዚያ ዋሻ ውስጥ አንድ ባሕታዊ መኖሩን ገለጸልኝ። ከዋሻው በታች ቅጠላቅጠል የሚታይበት አንድ ቦታ ስላሚታይ አትክልት ይመስላል። በባሕታዊነት የኖረ አንድ

ያልታወቀ ፈረንጅ የሞተበትን ከገደሉ ቁልቁለቶች አንዱን አሳዩኝ። ይህ ሰው በዚያ ቦታ ሃያ ዓመት ሙሉ በባሕታዊነት ከኖረ በኋላ መቼ እንደሞተ ሳይታወቅ ከተራራው ስለጠፋ ሊፈልጉት ወደዋሻው ሄዱ። በዚያ እንደደረሱ ዋሻው ከውጭ ሰው እንዳይገባበት በጥብቅ ተዘግቶ አግኝተውት ጉዳዩን ለንጉሡ ነገሥቱ ገለጹለት፣ እርሱም ዋሻው እንዳይከፈት አዘዘ።

ምዕራፍ መቶ አስራ አንድ፤ በመላ ኢትዮጵያ የዐቢይ ጾም፤ ሆሣእናና ሕማማት በንዴት ያለ አኳኋን እንደሚከበር።

በአቢይ ጾም ወራት አብዛኛዎቹ መነኩሴዎችና መነኩሲቶች ከካህናቱም አንዳንዶቹ የሚመገቡት በየሁለት ቀን አንድ ጊዜ ማለት እራታቸውን ብቻ ነው። እሁድ የጾም ቀን አይደለም። ከዓለማዊ ኑሮ የተለዩ መነኩሲቶች ይህን ጾም ይጾማሉ። እቴጌ እሌኒም በሳምንት ሶስት ቀን ማለት ከማክሰኞ ሐሙስና ቅዳሜ በስተቀር ዓመቱን በሙሉ ትጾማለች ይባላል።

በባሕር ነጋሹና በትግሬ መኮንኑ ግዛቶች በዐቢይ ጾም ወራት አብዛኛው ሕዝብ በእሁድና በቅዳሜ ሥጋ ይበላል፤ በነዚህ ሁለት ቀኖች የሚያርዱዋቸው ፍሪዳዎች ቁጥር በዓመቱ በሙሉ ከሚያርዱዋቸው ይበልጣል። ይልቁንም የመጀመርያ ወይም ሁለተኛ ሚስታቸውን ከካርናቫል ማክሰኞ ዕለት በሚውለው ሐሙስ ዕለት ያገቡ እንደሆነ ደግሞ የበለጠ ያርዳሉ፤ በዚያን ቀን የሚዳሩት ሁለት ወር ሙሉ በማናቸውም ቀን ሥጋ እንደልብ እንደሚበሉ መቻላቸውን በማወቅ ነው። ስለዚህ በነዚህ ሁለት ጠቅላይ ግዛቶች የሚዳሩ ሰዎች በዓቢይ ጾም ወራት ሥጋና ቅቤ ለመብለት ወይም ጠጅም ለመጠጣት ይችላሉ። ይህን ተግባር በባሕር ነጋሹ ግዛት አይቻለሁ፤ ስለዚሁም በትግሬ መኮንኑ ግዛት ሲወራ ሰምቻለሁ። ምንም እንኳ

«ሁለተኛ ሚስት ሲያገቡ» ስል ብገልጽም ወንዶች ሁሉ ሁለት ጊዜ ማግባት አለባቸው ሲባል ሊገመት አያስፈልግም። ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንደተገለጸው አብዛኞቹ ባንድ ሚስት ጸንተው የሚኖሩ ናቸው። በቂ ሃብት ያለው ሰው ግን ሁለት ወይም ሶስት ሚስቶች አሉት፤ ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት ሁሉ ይህን በማድረጋቸው በረከትን እንዳይቀበሉ በመከልከል የምትገስጻቸው ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንጂ የፍትሐ ብሔር ሕግ የለም። ከላይ በተጠቀሰው ሐሙስ ዕለት ወዳጆቼ የሆኑ ትዳር የያዙ ወንዶች አጉል ተግባር ለመፈጸም ሌሎች ሴቶችን ወደቤታቸው ሲወስዱ አይቻለሁ። ይህ ቦታ የክርስትና ሃይማኖት መጀመርያ የተሰበከበት ቢሆን በዚህ መጥፎ ተግባር ምክንያት የሌሎች ግዛት ሰዎች እነዚህን በጣም ይወቅሱዋቸዋል። በሌሎች ጠቅላይ ግዛቶች ግን ወንዶችና ሴቶች ወጣቶችና ሽማግሌዎች ልጆችም ሳይቀሩ በጥብቅ ዐቢይ ጾምን ያከብራሉ። ከልደት በኋላ ያለውን ጾምም ምንም እንኳ እንደ ዐቢይ ጾም በጥብቅ ባይሆንም ይጾማሉ።

የሆሳእናን በዓል ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ያከብራሉ፤ እኩለ ሌሊት ከሆነ በኋላ ቅዳሴ ይገቡና ጎሕ እስኪቀድ ድረስ ልዩ ልዩ ሥዕሎችን ገልጸው ይዘው ሲዘምሩና ሲያዜሙ ቆይተው የጥዋት ጸሎት የሚደረግበት ጊዜ ሲደርስ እያንዳንዳቸው በእጃቸው ቅርንጫፍ ይይዙና (ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክህነት የሌለው ሰው ወይም ሴቶች ሊገቡ ስለማይፈቀድላቸው) ወደ መቅደሱ ይገባሉ፤ ወይም ወደዋናው በር ይሄዳሉ። ከዚህ በኋላ ካህናቱ ቅርንጫፉን ይዘው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ይገቡና በዚያው ሆነው ከፍ ባለ ድምጽ በችኮላ ያዜማሉ። ይህ ከተፈጸመ በኋላ መስቀላቸውንና ቅርንጫፉን በጃቸው ይዘው ወደውጭ ወጥተው ለያንዳንድ ሰው ካከፋፈሉ በኋላ በእጃቸው ዘንባባ ይዘው ቤተ ክርስቲያኑን ይዞሩታል። ወደዋናው በር ይመለሱና እኛ በምንገባበት አኳኋን ስድስት ወይም ሰባት ካህናት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ይገቡና በሩን ይዘጋሉ። ሰሞነኛው ቄስ ብቻ መስቀሉን በእጁ እንደያዘ ይቆያል። ቋንቋው ብቻ ልዩ ሲሆን ልክ እኛ እንደምናደርገው ሁሉ ከቤተ ክርስቲያኑ ግቢና ውጭ ይቀድሳሉ፤ በወጋቸው ቅዳሴውን ካደረሱ በኋላ በዚያ የሚገኙትን ሁሉ ያቀርባሉ።

በሕማማት ሳምንት ቅዳሴ ያለው ሐሙስና ቅዳሜ ብቻ ነው። ብዙዎች በተለይም ታላላቅ ሰዎች በቀን አንድ ጊዜ ሲገናኙ ትከሻቸውን መሳሳም ልምዳቸው ነው። በሕማማት ሳምንት ግን ሰላምታ ሳይሰጣጡ ወይም ሳይነጋገሩ ወደ ምድር እየተመለከቱ ድዳ ይመስል ዝም ብለው ይተላለፋሉ። ከፍተኛ ማዕርግ ያላቸው ሰዎች በዚህ ሳምንት ጥቁር ወይም ከል የተነከረ ልብስ እንጂ ነጭ ልብስ አይለብሱም። በዚሁ ሳምንት ማናቸውም ዓይነት ሥራ ይቆማል። በየቀኑ በየቤተ ክርስቲያኖቹ ይቀደሳል፤ ነገር ግን በኛ ዘንድ እንደ ተለመደው መብራት አይዙም። የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ከቀትር በኋላ ቄሰ ገበዙ ትልቅ ፎጣ በወገቡ ላይ አሸርጦ በበርጩማ ላይ ተቀምጦ በታላቅ ገበቴ በተያዘ ውኃ ከቀሳውስቱ ጀምሮ እስከ ተራው ሕዝብ በዚያ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ እግር ያጥባል። ከዚህ በኋላ ዝማሬአቸውን ይጀምሩና ቄሶቹ መነኩሴዎቹና ዲያቆኖቹም ሌሊቱን ሁሉ ሲዘምሩ ያድራሉ። አክፍለት የሚጀመረው በዚህ ዕለት ስለሆነ ካህናቱ ከቤተ ክርስቲያኑ አይወጡም። አርብ በእኩለ ቀን ላይ ቤተ ክርስቲያኑን በልዩ ልዩ ዓይነት መጋረጃ ማለት በወርቀዘቦ ወይም በግምጃ ወይም በተገኘው ዓይነት ምዕመናን በብዛት የሚገኙበትን ዋናውን በር ይጋርዱታል። ከበሩ ፊት ለፊት በሚገኘው መጋረጃ ላይ የክርስቶስን ስቅለት የሚያሳይ ስዕል በትንሽ ጨርቅ ተሸፍኖ ተሰቅሎአል። ሌሊቱን እየዘመሩ ሲያድሩ በቀን ግን ሕማማቱን የሚያስታውሱ ጥቅሶች ያነባሉ። ከዚህ በኋላ ስዕሉን የሚሸፍነውን መጋረጃ ይገልጹትና ምዕመናኑ ለምልክት ያህል እርስ በርሳቸው በጥፊ ይማቱና የቤተ ክርስቲያኑን ግድግዳ መሳለምና በግንባራቸው በምድር ላይ መደፋት ይጀምራሉ። ይህ የመሪር ሐዘን ጊዜ ሁለት ሰዓት ያህል ከቆየ በኋላ ከሶስቱ በሮቹ በያንዳንዳቸው ግራና ቀኝ ሁለት ቄሶች ባለ አምስት መንታ አለንጋ ይዘው ጥብጠባ ይጀመራል። በበሮቹ ፊት ለፊት የሚቆሙ ሁሉ ወደውጭ ሲወጡ ከወገባቸው በላይ እየተጠበጠቡ ይወጣሉ። ወደውጭ የሚወጡት ሰዎች ሁሉ በአለንጋዎቹ ፊት ሲደርሱ ለጥብጠባ ጀርባቸውን ለመስጠት ጎንበስ ይላሉ። ሰዎቹ አለንጋው በቃን ብለው ገለል ካላሉ በስተቀር ጥብጠባው አያቋርጥም። በቶሎ የሚያልፉትን ግን አለንጋውን ብዙ አያገኛቸውም። አንዳንዶቹ ግን ረጅም ጊዜ በመቆየት

ብዙ ጥብጠባ ይቀበላሉ። ሽማግሌዎችና አሮጊቶች ግን ደም እስኪ ወጣቸው ድረስ እኩል ሰዓት ያህል ይጠበጠባሉ። ከዚህ በኋላ በቅኔ ማህሌቱ ውስጥ ይተኙና እኩለ ሌሊት ሲሆን ተነሥተው አስቀድሰው ይቆርባሉ። የትንሳኤ ዕለት በእኩለ ሌሊት ጸሎት ያደርጉና ከመንጋቱ በፊት ቤተ ክርስቲያኑን ዞረው ይገባሉ። ጎሕ ከቀደደ በኋላ ቅዳሴ ይገባሉ፤ ከትንሳኤ እሁድ ቀጥሎ ካለው እሁድ (ዳግማዊ ትንሳኤ) እስከሚቀጥለው ሰኞ ድረስ በየቀኑ ቅዳሴ አይታጎልም። ስለዚህ ከሆሣእና ዋዜማ ቅዳሜ ጀምሮ እስከ ተጠቀሰው ሰኞ ድረስ ማለት አስራ ስድስት ቀን ሙሉ ቅደሴ በየቀኑ አይታጎልም ማለት ነው።

ምዕራፍ መቶ አስራ ሁለት፤ በጉራጌ አገር በቤተ መንግሥቱ ዐቢይ ጾምን ስለማክበራችን፤ በኛ ሥርዓት እንድንቀድስ አዘውን ይህን ትዕዛዝ ስላለመቀበላችን።

እጅግ ርቆ በሚገኝ ጉራጌ የተባሉ አሕዛብ በሚኖሩበት አገር አንድ የዐቢይ ጾምን ወራት አሳልፈናል። ጉራጌዎች መጥፎ ሰዎች ናቸው ይባላል። በነርሱ ውስጥ ባሮች አይገኙባቸውም፤ ክርስቲያኖችን ከማገልገል ይልቅ መገደልን ወይም ራሳቸውን መግደልን የሚመርጡ ሰዎች ናቸው። የንጉሡ ከተማ የተከተመበት ይህ ቦታ የጉራጌዎች አገር ነበር። ጉራጌዎች በዋሻ ውስጥ ነው የሚኖሩት እያሉ ሐበሾች ያወራሉ። የንጉሣዊው አጀብና እኛም በግራ ቀኙ ትልቅ ገደሎች በሚገኙበት ካንድ ትልቅ ወንዝ በላይ ከትመን ተቀመጥን፤ በፖርቱጋል የሚገኘውን ስርናሽ ዱዝ አልዩሽ የተባለውን ሜዳ የሚመስል ሜዳ በወንዙ ግራና ቀኝ ይገኛል። ወንዙ በሚሄድበት ቦታ ሁሉ በየገደሎቹ ላይ ተደራርበው የተሠሩ ብዙ መንደሮች ነበሩ። እያንዳንዶቹ ቤቶች ከፍ ያሉና በራቸውም አንድ ሰው ብቻ በቀላሉ ሊያልፍባቸው እንዲችል በማለት ካንድ ያዋሽ በርሜል አፍ ሳይበልጥ የተሠራ ነው። በየበሮቹ ድንጋይ ጉበኖች ውስጥ የተተከለ ብረት አለ፤ ይህ ብረት ሰው ከታች ወደላይ እየተንጠላጠለ የሚወጣባቸው ገመዶች

ታሥረውበታል። ይህን መንጠላጠያ አሁን ማበጀታቸው በነዚህ ትንንሽ ቤቶች ውስጥ ብዙዎቹ ዝቅተኞች የቤተ ምንግሥቱ ሰዎች ስላረፉባቸው ነው። ቤቶቹ ምንም እንኳ ከውጭ ትንንሽ መስለው ቢታዩም ሃያ ወይም ሰላሳ ሰዎች ከነዕቃቸው በቀላሉ ሊገቡባቸው ይችላሉ። በዚህ ወንዝ አጠገብ ምሽግ የሚመስል አንድ ከተማ ነበር። የከተማው ወንዝ ነክ ክፍሉ እንደ ግድግዳ በቆሙ በታላቅ ቋጥኞች ሲያልቅ ወደሜዳው በኩል ያለው ክፍሉ ደግሞ አስራ አምስት ክንድ ጥልቀት ስድስት ክንድ ስፋት ባለው ገደል ያልቃል፤ በሁለቱም በኩል ወንዙ አለ፤ በዚህ ጎድጓዳ ቦታ ከላይ የተጠቀሱትን የመሰሉ ቤቶች በሁለቱም በኩል ተሠርተው ነበር። በዚህ በተከበበ ቦታ ላይ አጫጭር ግድግዳዎች ያላቸው ባለ ሣር ክዳን አሁን ክርስቲያኖች የሚኖሩባቸው ቤቶች አሉ። በዚሁ ቦታ አንድ ማለፊያ ቤተ ክርስቲያን አለ። ወደዚህ ከተማ የሚያስገባው በር እየተጠመዘዘ የሚሄድና በድንጋይ የተሠራ ዝቅተኛ ስለሆነ በቆሎች ወይም ላሞች የሚገቡበት አይመስልም፤ ነገር ግን ሲሶ ሌግዋ ያህል ያለ ችግር ያስሄዳቸዋል። ከወንዙ በላይ በኩል ከላይ እስከታች የተጠረበ የሚመስል ትልቅ ቋጥኝ ነበር፤ ከድንጋዩ ራስጌ ለጥ ያለ ሜዳ ነበር። በቋጥኙ መካከል በእመቤታችን ስም የሚጠራ አንድ ገዳም አለ። የጉራጌዎች ንጉሥ ቤተ መንግሥት በዚያ ቦታ ነው ያለው ማለትን ሰምቻለሁ። ገደሉ ያለው በምስራቅ በኩል ነው፤ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚያስመጣ አንድ ተንጠልጣይ የእንጨት መሰላል አለ። ንጉሡ ነገሥቱ ከዚህ ቦታ ከሄደ በኋላ ጉራጌዎችን በመፍራት ይህን መሰላል ሌሊት ያነሱት ነበር። ከዚህ በኋላ በድንጋይ ደረጃ ወደ ግራ በኩል ይወጠል፤ ወደ ወንዙ የሚያሳዩ መስኮቶች ያሉዋቸውን የመነኩሴዎች መኖርያ አስራ አምስት ክፍሎች ደጃፍ የሚያልፍ አንድ በረንዳ አለ። በጣም ከፍ ብለው የሚገኙ ግምጃ ቤታቸውና የግብር ቤቶቻቸው የስንቃ ቸው ማስቀመጫ ቤትም አሉ።

ወደቀኝ በኩል ዞሮ ባንድ ጨለማ መንገድ ከሄዱ በኋላ የቀኑ ብርሃን በማይታይበት የገዳሙ ዋና በር ባለበት ቦታ ይደረሳል። ይህ በር ገዳሙ ከታነፀበት ድንጋይ አይደለም የተሠራው፤ ገዳሙ ምንም እንኳ ትንሽ መስሎ ቢታይም በጥንት ጊዜ ትልቅ አዳራሽ

የነበር ይመስላል። በወንዙ በኩል ባለው ጎን ብዙ መነኩሴዎች ስላሉ ሰፊ ይመስላል። ለገዳሙና ለመነኩሴዎቹም ባላቸው ክብር ምክንያት ብዙዎች የቤተ መንግሥቱ ሰዎች ቁርባን ለመቀበል ወደዚሁ ይመጡ ነበር። መነኩሴዎቹን የሚያከብሩበት ምክንያት ቅን ኑሮ ስለሚኖሩና የአካባቢው ሕዝብ የሚጥልባቸውን አደጋ ችለው ስለሚኖሩ ነው ይባላል። ከንጉሠ ነገሥቱ ከተማ እልፍ ብሎ የሠፈረው የግራ ቢትወደዱ ሠራዊት የነበረው ጉራጌዎች ከሚመጡበት በኩል ስለነበር «ትናንት ማታ ጉራጌዎች ከግራ ቢትወደዱ ሠራዊት ይህን ያህል ሰው ገደሉ፤» የሚል ወሬ በየቀኑ ይሰማል። ሠራዊቱ በምንም አኳኋን ጾሙን ሊገድፍ ስለማይፈቅና በዚሁ ጾም ምክንያት በመድከም ሊዋጉ ስለማይችሉ ጉራጌዎች አደጋ የሚጥሉት በዐቢይ ጾም ወራት ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ የኛን ቅዳሴ ለመስማት ፈልጎ በሕማማት ሳምንት በድንኳኑ አጠገብ በኛ ሥርዐት እንቀድስ ዘንድ እንድንዘጋጅ አዘዘን። እኔም መልእክተኛ በመላክ የተዘጋጀን መሆናችንን ገለጽሁለት፤ ነገር ግን ከዚህ በፊት የተሰጠን ድንኳን በዝናሙ ምክንያት የበሰበሰና ያረጀ መሆኑን በማስታወቅ ድንኳን የሌለን መሆናችንን ነገርናቸው። ንጉሠ ነገሥቱም ወዲያውኑ መልእክተኛውን በመላክ ድንኳኑን የሚያዝልን መሆኑን ገልጾልን በተጠራን ጊዜ እንድንሄድ መጣርያችንን እንድናዘጋጅ አዘዘን። እኩለ ሌሊት ከሆነ በኋላ ተጠርተን በንጉሣዊው መኖርያ በር አቀረቡን። በታላቁ ንጉሣዊው ድንኳን አጠገብ የነበረው የጀጎሉ አጥር እስከ ቅድስት መስቀል ቤተ ክርስቲያን ደርሶአል። የጥይት ርቀት ያህል ርዝመት ባለው ሳልፍ በግራና ቀኝ በኩል ከስድስት ሺ በላይ የሚሆኑ የጡዋፍ መብራቶች ተይዘው ነበር። ፊት ለፊት እየተያዩ በግራና ቀኝ በኩል በቆሙት ሰዎች መካከል ያለው ርቀት ሁለት የቴኒስ ሜዳዎችን ያህላል፤ የቆሙበት ቦታ ለጥ ያለ ሜዳ ነበር። ጡዋፎቹን ይዘው ከቆሙት ሰዎች በስተኋላ ከአምስት ሺ በላይ የሚገመቱ ሰዎች ቁመው ነበር። ሕዝቡን ለማገታት እንደመከታ ከተተከለው ደረቅ መቃ ኋላ መብራቱን ይዘው የቆሙት ሰዎች አጥር ይመስሉ ነበር። በንጉሣዊው ድንኳን ፊትለፊት በፈረስ ተቀምጠው ወዲያ ወዲህ ይንቆራጠጡ በነበሩ አራት መኳንንት አጠገብ ወስደው

አቀሙን። በዚህን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ጥንዚዛ በመሰለ ባንድ ዋርዳ ምስንጅር በቅሎ ተቀምጦ መጣ፤ ለዚህ በቅሎ ያለው ግምት እጅግ ከፍ ያለ ስለነበር በሄደበት ሁሉ አይለየውም፤ በዚህ በቅሎ ካልተጓዘ ግን በፊት እንደተገለጸው በአጎበር አልጋ በሰው ሸክም ነው የሚሄደው። ንጉሠ ነገሥቱ የለበሰው በወርቅ የተጠለፈ ምድር የሚነካ ትልቅ ካባ ሲሆን በቅሎውም በሙሉ ተሸፍኖ ነበር። ዘውዱን ጭኖ መስቀሉን በእጁ ይዞ በበቅሎው ተቀምጦ ሲሄድ በግራና ቀኙ ትንሽ ቀደም ብለው ማለት ታፋቸውን በበቅሎው ጭንቅላት አግጣጫ አድርገው ራቅ ብለው የሚሄዱ በያንዳንዱ በኩል ሁለት ፈረሶች ነበሩ።

እነዚህ ፈረሶች ማለፊያ በሆነ ዕቃ ተጭነው በወርቀዘቦ በተን ቆጠቆጠ ግላስና ልዩ ልዩ ጌጥ ተሸፍነው ሲሄዱ በብርሃን ከሩቅ ሲመለከቱዋቸው በወርቅ ተለብደው የሚሄዱ ይመስላሉ። ከጭንቅ ላታቸው እስከታች ድረስ የሚወርዱ በላባ የተጌጡ ልዩ ልዩ ፈርጦች አድርገውላቸዋል። በመብራቱ መካከል በፈረስ ተቀምጠው ይንቆ ራጠጡ የነበሩት መኳንንት ንጉሠ ነገሥቱ እንደመጣ ከዚያ ቦታ ሄዱ፤ ሁለተኛም አልተመለሱም። ንጉሠ ነገሥቱ ባለፈ ጊዜ ሊጠሩን የመጡት ሰዎች ከጡዋፉ ብርሃን በፊት ማንም ሳያልፍ እኛን መርተውን ከንጉሠ ነገሥቱ በስተኋላ እንድንቆም አዘዙን። በዚህ ብርሃን ውስጥ ከኛ ሌላ ያለፉ ሌሎች ሰዎች ራቅ ብለው ከንጉሠ ነገሥቱ ፊትለፊት ይሄዱ የነበሩት ሃያ ወይም ሰላሳ መኳንንት ብቻ ነበሩ። በቅድስት መስቀል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በደረስን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ የትንሳኤን ቅዳሴን ለማስቀደስ ከበቅሎው ወርዶ በተዘጋጀለት መጋረጃ ውስጥ በቤተ ክርስቲያኑ ገብቶ እኛም በበሩ ላይ ቆየን። ወዲያውኑ ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ካህናት ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥተው ቦታ በማጣት በውጭ ቁመው ከነበሩት ካህናት ጋር ተቀላቅለው ቤተ ክርስቲያኑን ለመዞር ተዘጋጁ። በሚዞሩበት ጊዜ እኛን በፊት አስቀድመውን እጅግ አከበሩን። በዚህ አኳኋን ዞረን ተመልሰን ቦታ እስከበቃ ድረስ ብዙዎች ወደውስጥ ሲገቡ የተቀሩት ግን በውጭ ቆዩ፤ እኛ ግን ወደ ውስጥ እንድንገባ አዘውን ከቅዳሴ ውጭ እስኪሆን ድረስ በመጋረጃው አጠገብ ቆየን። ቁርባን ሊጀመር ሲቃረብ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ልኮብን በተተከለልን ድንኳን

ውስጥ በኛ ሥርዐት ቅዳሴ እንድንገባ እንዘጋጅ ዘንድ አዞን እርሱም በቅዳሴው የሚገኝ መሆኑን አስታወቀን። መልእክተኞቹንና ከኛ ጋርም የነበሩትን ሌሎች ሰዎች አስከትለን አንድ ጥቁር ድንኳን በተተከለበት ቦታ ደረስን፤ እኛም ያን ጥቁር ድንኳን በማየታችን «ይህን ጥቁር ድንኳን የተከሉልን ሊያላግጡብን ፈልገው ነው» አልን። ወዲያውኑ አምባሳደሩ «አባ፤ ይህን የመሰለ ተግባር መደረጉ እኛን ለመፈተን ነውና ቅዳሴ ባይገቡ ይሻላል» አለኝ።

እኔም ይህንን የመሰለውን ነገር ከቶ የማላደርገው መሆኔን መልሼለት ወደ ድንኳናችን እንድንመለስ የኛን ሰዎች ጠየቅኋቸው። ይህ የሆነው በማለዳ ጎሕ በቀደደበት ጊዜ ነበር። በወንዙ አጠገብ በሜካው ውስጥ ተተክለው ወደ ነበሩት ድንኳኖቻችን ሄድን። ወዲያውኑ ሁለት መልእክተኞች በቋጥኙ ላይ እየዘለሉ በመሮጥ ወደኛ ዘንድ መጥተው በቁጣ ቃል ጠሩን። ለመሄድ አላሰብንም ነበር፤ ነገር ግን ስለተጠራን ሄደን ፀሐይ መፈንጠቅ ሲጀምር በንጉማዊው ድንኳን አጠገብ ደረስን። ወዲያውኑ አንድ መልእክተኛ ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ መጥቶ በንደዚያ ያለ ትልቅ አውደ ዓመት በምን ምክንያት ቅዳሴ ማስታጎላችንን ጠየቀን። እኔም መልሼ ለፈረሶች ወይም ለሽፍቶች እንጂ ለቅዳሴ ማቅረቢያ ሊተከል የማይገባውን ይህን ጥቁር ድንኳን ስለተከሉልን የተደፈርነው እኛ ሳንሆን በቀጥታ አምላክና ቅዱስ ትንሳኤ መሆኑን በመረዳት ቅዳሴውን ያስታጎልሁ እኔ ነኝ ስል መለስሁለት። መልእክተኛው ወዲያውኑ ተመልሶ መጥቶ ምን ዓይነት ድንኳን እንዲተከልልን የምንፈልግ መሆናችንን ጠየቀን። የትንሳኤውን ግርማና እመቤታችንም እንከን የሌለባት ንጽህት መሆንዋን ለማስረዳት ነጭ መሆን አለበት፤ ቀይ ደግሞ ክርስቶስ ለኛ ያፈሰሰውን ደምና ሐዋርያትና ሰማዕታትም ለርሱ ፍቅር ያፈሰሱትን ደም ሊያስታውስ ስለሚችል ድንኳኑ ቀይ ሊሆን ይችላል አልሁት። መልዕክተኞቹ ይህን ካደረሱ በኋላ ወዲያውኑ ወደኛ ተመልሰው መጥተው ይህን ድንኳን የተከለው ሰው ማን መሆኑን እንድንነግረው ንጉሠ ነገሥቱ የጠየቀ መሆኑንና ይህን ያደረገውን ሰው የሚፈጸምበትን ፍርድ የምናይ መሆናችንን አስረዱን። እኛም መልሰን ሰውዬው ማን መሆኑን አናውቅም፤ ብናውቀውም ኖሮ

የበደለው አምላክን ራሱን ስለሆነ እንዲቀጣ የማንፈልግ መሆናችንን አስታወቅን። በተለይም በንደዚህ ያለ ትልቅ አውደ ዓመት ቅዳሴ በመታጎሉ በይበልጥ ያዘንነው እኛ መሆናችንን ጨምረን ገለጽንለት። መልእክተኞቹ ተመልሰው መጥተው ንጉሠ ነገሥቱ በደለኞቹን የሚቀጣ መሆኑን አስታውቀውን ድንኳኑ ለቅዳሴ ስለማያገለግል በውስጡ ገብተን እንድንመገብበት አዘዙን። እኛም መግባት ወይም አለመግባት ያስፈልገን እንደሆነ ጥቂት ሃሳብ ከተለዋወጥን በኋላ በመጨረሻ ወደ ድንኳኑ ለመግባት ወሰንን። እዚያው ድረስ ልዩ ልዩ ምግብና ጠጅ ተላከልን። ቃናው በጣም የሚጥም ቀይ የወይን ጠጅም ተልኮልን ነበር። የዚያን ዕለት ቀንና ሌሊት ከኛ ሳይለይ ማናቸውንም ነገር ተመልክቶ የነበረው ጴጥሮስ ድኩቬሉያን በምሳ ላይ ተቀምጠን በነበርንበት ጊዜ «በዚህ ድንኳን ውስጥ ባለመቀደሳችንና ለንጉሠ ነገሥቱ በሰጠነው መልስ ምክንያት በዚህ አገር ከመጣሁ ጀምሮ ያገኘሁትንና አገኘዋለሁ ብዬ ያልገመትሁን የበለጠ ነው ደስታ ያገኘሁት» ሲል ነገረን። ያን የመሰለ ሥራ መፈጸሙ የአምላክና የቤተ ክርስቲያን ለሆኑም ነገሮች የቱን ያህል ክብር እንዳለን ለመፈተን መሆኑን ካሁን በኋላ ግን በእውነተኛ ክርስቲያንነታችን የሚያከብሩን መሆናቸውን ጴጥሮስ ድኩቪሊያን ጨምሮ ገለጸልን። በዐቢይ ጾም ምግብና መጠጥ ብዙ ወይንና ኮክም እየሰጡን በደንብ አከባክበው ይዘውን ነበር። ያ ከዚህ በፊት በጥምቀተ ባሕሩ ሕዝቡን ያጠምቅ የነበረው ሽማግሌ ቄስ ከምሳ በኋላ ወደኛ ዘንድ መጥቶ ንጉሠ ነገሥቱ በሚቀጥለው እሁድ ቅዳሴውን እንዳናስታጉል የጠየቀን መሆኑን፤ ለቅዳሴውም ስነ ሥርዐት ማከናወኛ ጥሩ ድንኳን የሚያዝልን መሆኑን ነገረን፤ በተጠቀሰው ቀን በኛ ሥርዐት ቅዳሴ እንድናደርስ መታዘዛችን በዚያን ዕለት የንጉሠ ነገሥቱ እናት የሙት ዓመት ተዝካር ስለነበረ ነው። እኛም በዚሁ ዕለት በኛ ወግና ሥርዓት ቀደስን።

ምዕራፍ መቶ አስራ ሶስት፤ አምባሳደሩ እንዲመለስ በመጠየቅ ዶም ሉዊሽ ድ ምኔዝሽ ደብዳቤ ስለመጻፉ፤ የአምባሳደሩ በቤተ መንግሥቱ አለመገኘት፤ የንጉሥ ዶም አማኑኤል ሞት።

ቅዳሴ እንድናደርስ የታዘዝንበት ቀን የትንሳኤ በዓል ሳምንት ሚያዚያ አስራ አምስት ቀን ነበር። በዚሁ ቀን ለንጉሠ ነገሥቱ እናት ነፍስ ተገቢውን ጸሎት አደረስን። በማለዳ ተነስተን ሄደን በአገሩ ወግ መሠረት በመካከሉ የሐር መጋረጃ የተጋረደበት በንጉሠዊው ድንኳን አጠገብ የተተከለ አንድ ትልቅ አዲስ ድንኳን አገኘን። አምባሳደር ሆኖ እንዲሄድ የተሾመው መነኩሴም ከሌሎች ካህናት ጋር ሆኖ በዚያው ይገኝ ነበር። እኛም ወዲያውኑ የሐዘን መዝሙር ዘምረን ቅዳሴ ገባን። ከቅዳሴ ውጭ ከመሆኑ በፊት ዶም ሉዊሽ ድ ምኔዝሽ የላካቸው ሁለት ደብዳቤዎች ደረሱን። እኛን ለመውሰድ በመርከብ ሆኖ በምጽዋ ወደብ ላይ ይጠብቀን የነበረ መሆኑን በደብዳቤው አስታወቀን። ሁለቱ ጥቅሎች በሁለት መንገዶች የመጡ ቢሆኑም መልእክተኞቹ የደረሱት ባንድነት ነበር። በነዚህ ጥቅሎች ከመጡት ደብዳቤዎች ውስጥ አንደኛው ንጉሠ ነገሥቱ በቶሎ እንዲያሰናብተን በተለይ ለርሱ የተጻፈ ነበር። ዶም ሉዊሽ ድ ምኔዝሽ የክረምቱ ወራት ከመድረሱ በፊት መሄድ ስለነበረበትና በተይም በሕንድ እንዲደርስ ተፈልጎ ስለነበር ሚያዚያ አስራ አምስት ቀን በምጽዋ እንድንደርስ በጻፈልን ደብዳቤ ላይ አዘዘን። በዚሁ ደብደቤ ላይ የንጉሥ አማኑኤልንም ሞት አረዳን። ይህ ወሬ በእውነተኛው ልባችንን ሰበረው፤ ወዲያው ባንድነት ተሰብስበን ጉዳዩን እንግለጽ አንግለጽ በማለት ሃሳብ ከተለዋወጥን በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ከሕንድ በየቀኑ በሚመጡ የእስላም ነጋዴዎች አማካይነት ማናቸውንም ነገር ሊሰማው ስለሚችል ጉዳዩን ከሌሎች ከሚሰማው ይልቅ ከኛ ቢሰማው ይሻላል ስንል ወሰንን። በአገሩ ልምድ መሠረት ጢምን ትቶ ጠጉርን መላጨትና ጥቁር መልበስ ደንብ በመሆኑ እኛም እንዲሁ አደረግን። በዚህን ጊዜ ምግባችን ተሰናድቶ መጣልን፤ ምግባችንን ይዘው የመጡት ሰዎች የኛን ሁኔታ ባዩ ጊዜ ምንም ሳይናገሩ ምግቡን አኑረውልን ሄደው የሆነውን ነገር ለንጉሠ ነገሥቱ ነገሩት። እርሱም የሆነውን

ለማወቅ ሁለት መነኩሴዎች ላከብን። አምባሳደሩ እንባ እያነቀው ሊናገር ባለመቻሉ ከኛ አንድ ሰው ሄዶ እንዲነግራቸው ታዘዘ። እኔ ወደ መነኩሴዎቹ ሄጄ በአገሩ ልምድና አነጋገር ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ጉዳዩን ገለጽሁላቸው፤ «ጨረቃና ከዋክብት መውደቃቸውን ለግርማዊነታቸው ንገሩዋቸው፤ ጸሐይም ጨለማ ለበሰች፤ ብርሃንዋንም አትሰጥም፤ እኛም ከንግዲህ ወዲህ የሚያስጠጋን ወይም የሚጠብቀን የለንም፤ የሁላችን አባት ከሆነው ከእግዚአብሔር በስተቀር ከንግዲህ ወዲህ አባት ወይም እናት የለንም፤ ንጉሥ ዶም አማኑኤል ከዚህ ዓለም ኑሮ አረፉ፤ እኛም ተመልካች የሌለን የሙት ልጆች ሆንን።» ልቅሶአችንን ወዲያውኑ ቀጥለን መነኩሴዎቹም ትተውን ሄዱ።

በዚያኑ ሰዓት አዋጅ ተለፎ ምግብና ጠጅ ሌላም ሸቀጦች የሚሸጡባቸው ቦታዎች በሙሉ እንዲሁም መሥርያ ቤቶችም ሁሉ ሶስት ቀን እንዲዘጉ ታዘዘ። በነዚህ ሶስት ቀኖች አንድም ሱቅ አልተከፈተም ነበር። ከሶስቱ የሃዘን ቀኖች በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶን እንዲህ ሲል የመጀመርያ ጥያቄ አቀረበል። «የአባቴን የንጉሡን አልጋ የሚወርሰው ማን ነው?» አምባሳደሩም መልሶ ልዑል ዶም ዮሐንስ መሆኑን ገለጸ።

ይህን ከሰማ በኋላ «አትፍሩ፤ አትፍሩ፤ በክርስቲያን አገር ነው ያላችሁት፤ አባትየው መልካም ሰው ነበሩ፤ ልጁም መልካም ሰው ይሆናል፤ ደብዳቤ እጽፍለታለሁ» ሲል አጽናናን። የማጽናናቱ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ መርከቦቹ በምጽዋ የሚጠብቁን መሆናቸውን፤ እንዲሁም ከንግዲህ ወዲህ በዚህ አገር መቆየት መልካም ነገር ስለማይመስል ስንብት እንድንጠይቅ ዶም ሉዊሽ ምኔዝሽ ያዘዘን መሆኑን ነገርነው። ንጉሠ ነገሥቱም ወደድንኳናችን ሄደን እንድንመገብ ፈቀዶልን፤ በማግሥቱም የሚያሳናብተን መሆኑን ገልጸውልን የመጣውን ደብዳቤ በነርሱ ቋንቋ እንድንተረጉም ታዘዝን። መልእክቱ ምን መሆኑን እናውቀው ስለነበርን ደብዳቤው እሁድ እንደደረሰን የዚያኑ ዕለት አይርሽ ዲያሽ የተባለውን የኛን ሰው ካንድ ኢትዮጵያዊ ጋር ሆኖ ለዶም ሉዊሽ ድ ምኔዝሽ ደብዳቤ እንዲያደርስለት ላክነው።

በማግሥቱ ደብዳዎቹን በአገሩ ቋንቋ ተርጉመን ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረብንለት። በዚሁ ዕለት ንጉሠ ነገሥቱ ከዚያ ቦታ ወደሌላ ዘንድ ስለሄደ እኛም ከርሱ ጋር ሄድን። በጉዞው ላይ እንደነበርን የመጸለያውን ድንኳን ማን እንደተሸከመልን ጠየቁን። እኔም መልሼ ድንኳኑ የኔ ስላልነበረ አላመጣሁትም፤ ቅዳሴውን ከጨረስን በኋላ በተተከለበት ቦታ ትተነው መጣን አልኳቸው። ንጉሠ ነገሥቱ አንድ ጊዜ የሰጠውን ነገር መልሶ መውሰድ ልምዱ ስላይደለ ድንኳኑን ትተህ መምጣትህ አጥፍተሃል አሉኝ፤ ድንኳኑ ከነመጋረጃው ከመቶ አንሳሽ ወርቅ በለይ የሚገመት መሆኑንና በተለይም ንጉሠ ነገሥቱ እንድትቀድሱ ቢያዝ ድንኳን የለንም ብትሉ በእውነተኛው ቅር የሚያሰኝ ነገር ሊሆን ይችላል አሉን። ሶስት ቀን ከተጓዝን በኋላ እንደሠፈርን እንዲያሰናብቱን ፈቃድ ጠየቅን። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ እንዲትሄዱ ፈቃድ ሰጥቻለሁና አትፍሩ ብለዋችኋል አሉን። እኛ አጥብቀን ስንለምነው ምንም መልስ ሳይሰጠን ወኪላችንን ዮሐንስ ጎንሳልቭሽን ጠርቶ አንድ ሰጋር በቅሎና ማለፍያ ልብስና አስር አንሳሽ ወርቅ ሸልሞ የርሱንና የኛን ወርቅ ይዞ ወደ ወደቡ እንዲሄድ አዘዘው። በቶሎ እንዲሄድ ታዞ ስለነበር ከንጉሠ ነገሥቱ አሽከሮች ሁለቱን አስከትሎ ወዲያው ተነሣ። እኛ ግን በዚያ ቆየን፤ ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ለሁላችንም ማለፊያ ልብስና በቅሎዎችም ሸለሙን። ለአራት ሰዎች በተለይ የወርቅ መስቀሎች ከነሰንሰለታቸው ሰጡን፤ ለኔ የተሰጠችኝ በቅሎ በተለይ የንጉሠ ነገሥቱ በቅሎዎች ከሚኖሩበት ግርግም ውስጥ የወጣች ስትሰግርም ክንፍ አውጥታ የምትበር እንጂ በእውነተኛውስ በእግርዋ የምትሄድ የማትመስል ነበረች። ከዚህም በላይ ለሁላችንም ሰማንያ አንሳሽ ወርቅና ለመንገዱም አንድ መቶ ልብሶች ሸልሞ በረከቱን ሰጥቶ አሰናበተን። ጉዞአችንን ጀምረን ጥቂት ከተጓዝን በኋላ ከዚህ በፊት ወደ ወደቡ የላክናቸው የኛ ሰዎች ተመልሰው መጥተው ዶም ሉዊሽ ድ ምኔዝሽ ከሄደ ብዙ ጊዜ ሆኖታል ሲሉ ነገሩን። በክረምቱ ምክንያት በዚያ እንደማናገኘው እርግጠኛ ነበርን፤ የሆነው ሆኖ እቦታው ድረስ ሄደን ለሥንቃችን የተወልንን ብዙ ጨርቅና በርበሬ እንዲሁም ለኛና ለንጉሠ ነገሥቱ የጻፈውን ደብዳቤዎች አገኘን። ዶም ሉዊሽ በሚቀጥለው ዓመት ተመልሶ የሚመጣ

መሆኑን በመግለጽ በምንም አኳኋን ከወደቡ እንዳንርቅ አዘዘን። እንዲሁም ደብዳውን ለማድረስና በሐርኪኮ ወደብ ላይ ስለተገደሉት አራት ሰዎች ጉዳይ ፍርድ ለመጠየቅ ሁለት ሰዎች ብቻ ወደ ቤተ መንግሥቱ እንዲሄዱ ሲል የጻፈውን ምክንያት በማድረግ ምንም እንኳ ከኛዎቹ አንዳንዶቹ በርበሬውን ለራሳችን እናስቀረው የሚል አስተያየት ቢኖራቸውም ስለዚህ ምን ማድረግ እንደሚገባን ለመመ ካከር ጉባኤ አደረግን። ከበርበሬው ግማሹ ተከፍሎ ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲላክና ይህንኑም እኔና ወኪሉ ይዘን ወደ ቤተ መንግሥቱ እንድንሄድ፤ እኔም ደብዳቤውን እንዳነብና በአገሩ ቋንቋ እንድተረጉም በጉባኤው ላይ ተወስኖ በማግሥቱ ጥዋት እንድንሄድ ተቆረጠ። ለመሄድ በተነሣንበት ጥዋት አምባሳደሩ ወደኔ ዘንድ ቀርቦ አባ፤ ከርስዎ ጋር ወደ ቤተ መንግሥቱ የሚሄድ ሰው ልሰጥዎ እወዳለሁ አለኝ። እኔም የምታዝልኝን ሰው ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ስል መልስ እንዳሰጠሁት «በርበሬውን ሁሉ ይዤ ከርስዎ ጋር ለመመለስ አስቤአለሁና የኔን ጓደኝነት ይፈቅዳሉን ሲል ጠየቀኝ።»

ምንም እንኳ ለኛ ሰዎች ስንቅ ከበርበሬው ያልተረፈ መሆኑንና የርሱን ሃሳብ ያልተስማማሁበት መሆኔን ብገልጽለትም ይዤ መሄድ አለብኝ ሲል አሻፈረኝ አለ። ይህን ለማድረግ ያቀደበት ምክንያት ከንጉሠ ነገሥቱ ትልቅ ስጦታ በመከጀልና የሚያገኘውንም ሁሉ ለራሱ ለማስቀረት ሲል ነበር። ስለዚህ አምባሳደሩ እንዳሰበው በርበሬውን በሙሉ አስይዞ ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመሄድ መንገ ዳችንን ወዲያው ጀመርን። እኔ የሄድሁበት ምክንያት ደብዳቤውን ለንጉሠ ነገሥቱ ለማድረስና በቋንቋው ለመተርጎም ብቻ ነበር። ጉዞአችንን መስከረም አንድ ቀን ጀምረን ዕቃውን አስጭነን በበቅሎ ሆነን ሳንለያይ ከተጓዝን በኋላ በሕዳር ወር መጨረሻ በቤተ መንግሥቱ ደረስን። እኛ በደረስንበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ የበርበራና የዘይላ ከተሞች ካሉበት ከአዳል አውራጃ ከሚዋሰነው ፈጠገር ከተበለው አውራጃ ይገኝ ነበር። የአዳል ንጉሥ ታላቅና ኃይለኛም ከመሆኑ ይልቅ ያለማቋረጥ ክርስቲያኖችን የሚዋጋ በመሆኑ በእስላም ነገሥታት ሁሉ ዘንድ በጣም የተከበረና እንደ ቅዱስም የሚታይ ነው ይባላል። እንደሚወራው ይህ ንጉሥ ከአረብ ንጉሥና ከሜካ

ሼህ እንዲሁም ከሌሎች የእስላም ነገሥታትና መሳፍንት ለዚሁ ተግባሩ መርጃ ብዙ ፈረሶችና መሣርያም ይቀበላል። በጦርነቱ ላይ የሚማርካቸውን ኢትዮጵያውያን ባርያ እያደገረ በያመቱ በግብር ስም ወደ ሜካ ይልካል። እነዚሁኑ ባሮች ለአረብ ንጉሥና ለሌሎችም የእስላም ልዑላን ገጸ በረከት ይልካቸዋል። በአዳል አውራጃ ከሚገኘው ከመጀመርያው የገበያ ከተማ ንጉሠ ነገሥቱ ከትሞ እስከተቀመጠበት ድረስ ያንድ ቀን ጉዞ ሲሆን ከዘይላ እስከዚህ ያለው ርቀት ግን የስምንት ቀን መንገድ ነው። የፈጠገርን አውራጃ ስንወጣና ስንገባ እንዳየነው ምንም እንኳ አንዳንድ ዝቅተኛ ተራሮች ቢኖሩበትም አብዛኛውን ስንዴና ገብስ የተዘራበት ሰፊ ሜዳ ነው። የተጠቀሱት እህሎች ከተዘሩበት እርሻ ሌላ የታረሱ ቦታዎች በያለበት ይታያሉ። ልዩ ልዩ ዓይነት መንጋዎች ማለት የቀንድ ከብቶች በጎችና ፍየሎች፣ ፈረሶችና ስናር አህዮች በሜዳው ላይ ተሰማርተው ይታዩ ነበር። በዚህ ሜዳ ላይ ሆኖ በሩቅ የሚታይ ቋጥኝ ያልሆነ ጥግጥጉን የታረሰና በጫካ የተሸፈነ ትልቅ ተራራ [1] ይታያል። ይህ ተራራ ብዙ ገዳሞችና ቤተ ክርስቲያኖች ይገኙበታል፣ አፈሩም አብቃይ ነው ይባላል። በተራራው ጫፍ ላይ አራት ሌግዋ ያህል ስፋት ያለው አንድ ትልቅ ሐይቅ ስላለ ልዩ ልዩ ዓይነት ዓሦች እየተጸመዱ ብርቱካንና ሎሚ፣ ትርንጎና የሕንድ በለስ እየተቀጠፉ ወደ ቤተ መንግሥቱ ይላካሉ። ጴጥሮስ ድኩቪሊያን እንደነገረኝ የተራራውን ግርጌ ለመዞር የስምንት ቀን መንገድ ይጠይቃል። የሐይቁንስ ፋት ጴጥሮስ ድኩቪሊያን በአራት ሌግዋ ገመተው። የንጉሠ ነገሥቱ ጓዝ ተነሥቶ ከሄደ በኋላ ከነበርንበት ቦታ ሁለት ቀን ተኩል ወደ ተራራው ተጓዘን ባጠገቡ በደረስን ጊዜ ከሰማነው የበለጠ ከፍ ያለና በጣም ለምለም ምድር መሆኑን ተረዳን። ዓሦች የሚገኙባቸው ብዙ ጅረቶች ከተራራው ይፈሳሉ።

አንድ ቀን ተኩል የተራራውን ግርጌ አልፈን ከተጓዝን በኋላ ዞረን ከፈጠገርም አውራጃም ወጥተን ሸዋ ገባን፣ በዚህ እንደደረስን በርበሬውንና በኢትዮጵያ ቋንቋ የተተረጎመትን ደብዳቤዎች ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበን ምንም መልስ ሳናገኝ ቀረን። እርሱ በዚህ መንገድ የሄደበት ምክንያት ሃብት ከእህቶቹ ጋር ለመካፈል ነበር፣ አባቱ

አጼ ናኦድ አምስት ሚስቶች ነበሩት፣ ነገር ግን እነዚህ ሃብት የሚካፈሉት ሁለት እህቶቹ ያንድ እናትና ያንድ አባት ልጆች ነበሩ። ይህ ሃብት እናታቸው ስትሞት ያወረሰቻቸው ነበር። በዚህ ቦታ አራት ቀን በቆየንበት ጊዜ እጣ በመጣጣል እርስቱን ለሶስት ተካፈሉት፣ ጴጥሮስ ድኩቪሊያን እንደነገረን ይህ የተካፈሉት ርስት ያስር ቀን መንገድ ስፋት አለው። ርስቱ በሶስት ተከፍሎ እህትማማቾቹ ድርሻቸውን ከወሰዱ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ የራሱን ድርሻ ለሁለቱ ሕፃን ልጆቹ አከፋፈለው። ኮረብቶቹንና ሜዳውን ሸለቆዎቹንም አልብሰውት የነበሩትን የቀንድ ከብቶች፣ ፈረሶች፣ በጎችና ፍየሎች ሁሉ ከርስቱ ጋር ተካፈሉዋቸው። መሬቱና ብዙ በተፈጥሮ ሁኔታው በጣም የተለያየ ስለነበረ ንጉሠ ነገሥቱ ወደፊት ሳይሄድ ወይም ሳይመለስ በዚያው እንዳለ ወደፊት የሚገኘው እንዳሁኑ በሶስት እንዲተነተንና የርሱም ድርሻ ለልጆቹ እንዲከፈል አዘዘ። የተካፈሉት ወርቅና የሐር ጨርቅ ብዛቱ ልክ የለውም ማለትን ሰምተናል። በክፍያው ላይ የደረሱትን የሐር ጨርቆች ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ በናቱ ርስት ላይ ተቀርቁረው ለነበሩት ገዳሞች እንዲሰጡ አዘዘ ይባላል። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ባሕታውያን ወደሚኖሩበት ጫካና አንድ ፈረንጅም የሞተበት ዋሻ ወደሚገኝበት ወደ ደራ ተጓዝን።

ምዕራፍ መቶ አስራ አራት፣ ንጉሠ ነገሥቱ በአዳል ንጉሥ ላይ ስለመዝመቱ፣ የአዳል ጦር ሠራዊት መሐመድ [1] ድል መነሣት።

ከብዙዎች ሰዎችና በተለይም ከጴጥሮስ ድኩቪሊያን እንደሰማነው ስለአዳል አውራጃና በዚያም ይኖር ስለነበር አንድ ታላቅ የጦር አዛዥ ቀጥሎ የተመለከተውን አትታለሁ። እስካሁን ድረስ የቤተ መንግሥቱ ሰዎች በጉዞአቸው ላይ እየዘፈኑ ሲሄዱ ስሙን የሚያነሱት ማህፉድ የተባለ አንድ ታላቅ የእስላሞች አዛዥ በዚህ

በአዳል አውራጃ ያለ መሆኑ የታወቀ ነው። ዐቢይ ጾም የሕዝቡን ኃይል ስለሚቀንሰውና መዋጋትም የማይችል መሆኑን በማወቅ ይህ የእስላሞች አዛዥ ሂያ አምስት ዓመት ሙሉ በዐቢይ ጾም ወራት የንጉሠ ነገሥቱን ግዛት ይወር ነበር ይባላል። ብዙ ጊዜ ሂያ ሌግዋ ያህል በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ውስጥ እየገባ ይወር ነበር ይባላል። አንዳንድ ጊዜ ያማራን ወይም የሸዋን ግዛት በሌላም ጊዜ ፈጠገርን አንዳንድ ጊዜም በልዩ ልዩ ቦታ እየተዘዋወረ የወረራውን ሥራ ያከናውን ነበር ይባላል። ማህፉድ ይህን የወረራውን ሥራ የጀመረው በአጼ እስክንድር ዘመነ መንግሥት ሲሆን በዚሁ ንጉሠ ነገሥት ዘመን አስራ ሁለት ዓመት ሙሉ ውጊያውን ቀጠለ፤ ወራሽ ሳይተው የሞተውን የአጼ እስክንድርን አልጋ ወርሶ በነገሠው በወንድሙ በአጼ ናኦድም ዘመነ መንግሥት ወረራው አላቋረጠም ነበር።

አጼ ዳዊት የነገሠው የአስራ ሁለት ዓመት ዕድሜ በነበረው ጊዜ ስለነበር አስራ ሰባት ዓመት እስኪሆነው ድረስ ማህፉድ የዐቢይ ጾምን እየጠበቀ አገሩን መውረሩን አላቋረጠም ነበር ይባላል። ወረራው ከፍ ያለ ስለነበረ ማህፉድ ባንድ ጊዜ አስራ ዘጠኝ[2] ኢትዮጵያውያን ማርኮ እነዚህን ምርኮኞች ለሜካና ለልዩ ልዩ የእስላም ነገሥታት አከፋፈላቸው ይባላል። እነዚህ ሰዎች ከክርስቲያኖች ብርቱ ጾም ወጥተው የእስላሞችን የገፍ ኑሮና ከንቱ ልምድን በመከተል ታላላቅ ሰዎች ሆነው ይኖራሉ ይባላል፤ ከሰዎችም ሌላ ብዙ ከብት እየዘረፈ ይወስድ ነበር። በሃያ አራተኛው ዓመት ወረራው በፈጠገር አውራጃ በገባ ጊዜ ሕዝቡ በሙሉ ሸሽቶ ከዚህ በፊት በተጠቀሱት ተራሮች ውስጥ ሲደበቅ ማሕፉድ ሕዝቡን እየተከታተለ በየተራሮቹ ላይ የሚገኙትን ቤተ ክርስቲያኖችና ገዳሞችን ሁሉ አቃጠለ ይባላል።

በነዚህ አውራጃዎች የሚኖሩ ገበሬዎች ወደ ዘመቻ ሄደው ስለማይዋጉ በመላ ኢትዮጵያ «ጨዋ» የተባሉ መሣርያ የያዙ ሠራዊቶች አሉ ብዬ ከዚህ በፊት አትቻለሁ። እየሸሹ በየተራሮቹ ላይ የተደበቁት ገበሬዎችና እነዚህ ጨዋዎች ነበሩ። ማህፉድ እነዚህን በሙሉ ከማረካቸው በኋላ ገበሬዎቹን ከጨዋዎቹ ለይቶ ወደመጡበት እንዲ መለሱና በሚቀጥለው ዓመት ተመልሶ ሲመጣ ሠራዊቶቹና ፈረሶቹ

በቂ ምግብ ለማግኘት እንዲችሉ ብዙ ስንዴና ገብስ እንዲያመርቱ አዞ አሰናበታቸው። መሣርያ የያዙትን ሰዎች ግን «እላንት የንጉሣችሁን እንጀራ የምትበሉ፤ ነገር ግን አገሩን በደንብ የማትጠብቁ ወስላቶች በጎራዴ እንድትጨፈጨፉ ተፈርዶባችኋል» ሲል አስራ አምስት ሰው አስገድሎ ምንም ተከላካይ ኃይል ሳይኖርበት ወደ ዘረፋው ተመለሰ። ንጉሠ ነገሥቱ በተለይ በገዳሞችና በቤተ ክርስቲያን መቃጠል በመናደድ ከማሕፉድ ሠራዊት ይህን ወረራ ለመቀጠል የቀረጠው የትኛው ክፍል መሆኑን ለማወቅ ሰላዮች ልኮ፤ የአዳል ንጉሥ ራሱ ማህፉድንና ብዙ ሠራዊትም አስከትሎ ሊዘምትበት በመዘጋጀት ላይ መሆኑን፤ እንዲሁም የፈጠገር አውራጃ ተወሮ የሚገኝ መሆኑን፤ ይልቁንም በዓቢይ ጾም ወራት ወደ መካከል አገር ገብተው የገብስና የስንዴ ቡቃዮችን ለማጥፋትና በዚሁ ጊዜ በሌላ ቦታም አደጋ ለመጣል በመሰናዳት ላይ መሆናቸውን ተረዳ። ንጉሠ ነገሥቱ ይህን በተረዳ ጊዜ አዳሎችን በመንገድ ላይ ሆኖ ሊጠብቃቸው ቆረጠ። ዳሩ ግን ዕድሜው ገና አስራ ሰባት ዓመት ብቻ ከመሆኑ ይልቅ፤ የአገሩ ቢትወደዶችና የጦር አዛዦች ይበቃሉ እንጂ እርሱ ሊዘምት አይገባውም ሲሉ ብዙ የቤተ መንግሥቱ ሰዎችና መኳንንት ተቃውመው ነበር ይባላል። ነገር ግን በአባቱ በአጼ ናኦድና በአጎቱ በአጼ እስክንድር ላይ እስላሞች የፈጸሙትን ግፍ ለመበቀል ራሱ መሄድ የሚገባው መሆኑንና እግዚአብሔር ኃይል እንደሚሰጠው የሚተማመን መሆኑን በመግለጽ ራሴ መሄድ አለብኝ ሲል ቆረጠ ይባላል።

ስለዚህ ወሬው እንዳይሰማ በማለት በሩቅ ቦታ የሚገኘውን ሠራዊቱን ሳያስጠራ የነበረውን ሠራዊቱንና አጀቡን ብቻ አስከትሎ ጉዞውን ጀመረ ይባላል። ሌትና ቀን ከተጓዘ በኋላ ከአዳል አውራጃ ከመጀመርያው ገበያ ያንድ ቀን መንገድ ርቆ በሚገኘው በርበሬውን ባመጣንለት ጊዜ ባገኘነው ቦታ ኅሕ ከመቅደዱ በፊት እንደደረሰ ድንኳን እንዲተከልና ዕረፍት እንዲደረግ አዘዘ ይባላል። ንጉሠ ነገሥቱ በዚያ ቦታ ከመድረሱ አንድ ቀን በፊት የአዳል ባላባት አርፎበት የነበረው አንድ መተላለፊያ በዚያ ቦታ ይገኝ ነበር ይባላል። የአዳል ባላባት የሠፈረው ግማሽ ሌግዋ ያህል ከወሰኑ ውጭ ሲሆን ንጉሠ

ነገሥቱ ደግሞ በአዳል ግዛት ውስጥ ከትሞ ሠፍሮ ነበር። ከነጋ በኋላ የቀኑ ብርሃን እንደወጣ እርስ በርሳቸው መተያየት እንደ ጀመሩ በታላላቅ ቀኖች ብቻ የሚተከለው ቀይ ድንኳን የተተከለበትን የንጉሠ ነገሥቱን ከተማ ማሕፉድ አይቶ ለአዳል ንጉሥ ቀጥሎ የተመለከተውን ነገረው ይባላል። «ጌታዬ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ራሱ መጥቶ በዚህ ይገኛልና ዛሬ የሞታችን ቀን ነው፤ እኔ በዚሁ ለመሞት ቆርጫለሁና እርስዎ ግን ነፍስዎን ለማዳን ይሞክሩ።»

የዚህን ጊዜ የአዳል ባላበት አራት ፈረሰኞችን አስከትሎ ለማምለጥ ቻለ ይባላል፤ ከፈረሰኞቹ አንዱ አሁን በቤተ መንግሥቱ የሚገኘው የቢትወደዱ ልጅ ነበር። ብዙዎቹ ሰዎች እስላሞች የሚሆኑት ወደው ስላልሆነ እንደገና ተጠምቀው ወደ ክርስትና ይመለሳሉ። በእስላሞቹ በኩል የሆነውን ማናቸውንም ነገር ያተተው ይህ ሰው ነበር ይባላል።

የአዳል ባላባት በማለዳ ከዚያ ቦታ እንዳመለጠ (ንጉሠ ነገሥቱ ግን ማምለጡን አላወቀም ነበር) ሠራዊቱ ሁሉ እንዲቆርብና በእግ ዚአብሔር እምነቱን እንዲጥልና ቁርስ አድርጎ እንዲዘጋጅ ታዘዘ ይባላል። የሶስት ሰዓት ጸሎት በሚደረግበት ጊዜ ሠራዊቱ ተሰልፎ ከከተማው ወጥቶ እስላሞቹን ለመግጠም ቀረበ። የንጉሠ ነገሥቱን ሠራዊት መንቀሳቀስ እስላሞች ባዩ ጊዜ መሪያቸው ማሕፉድ ወደ ክርስቲያኖች ብቅ ብሎ ከኔ ጋር ለመዋጋት የሚደፍር መኮንን ከመካከላችሁ ይገኛልን? ሲል ጠየቀ ይባላል። ለቀረበው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሲል በዚያኑ ጊዜ አባ ገብረ እንድርያስ የተባለ አንድ መነኩሴ ተንደርድሮ ሄዶ የማሕፉድን አንገት በጎራዴ ቀላው ይባላል። ይህ መነኩሴ እስካሁን ድረስ በቤተ መንግሥቱ የሚገኝ እጅግ የተከበረ ሰው ነው። በዚያን ጊዜ ሠራዊቱ ባንድነት በእስላሞች ላይ ግልብጥ ብሎባቸው ውጊያው ተፋፋመ፤ በመተላለፊያው ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ከተማ ይገኝ ስለነበር እንዲሁም የአዳል ባላባትም ያመለጠበት ሌላው መተላለፊያም ተይዞ ስለነበር እስላሞች የሚሄዱበት ቦታ ጠፋቸው። በፍጹም ድል ተነስተው ካለቁ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ

ወደ ከተማው ሄዶ አንድ ቀን ዕረፍት ካደረገ በኋላ በማግሥቱ ወደ አዳል ንጉሥ ማለፊያ ቤተ መንግሥት ሄደ፤ ነገር ግን በዚያ ማንም ሳይኖር ተዘግቶ አገኘው። ንጉሠ ነገሥቱ በጣም ተጠግቶ በሩን በጦር ሶስት ጊዜ ከወጋው በኋላ ወደዚህ የመጣበት ዋናው ምክንያት ሃብት ለመዝረፍ ነው ሲሉ እንዳያሙት በማለት ሌላ ሰው በሩን በጦር እንዳይወጋ ወይም ወደውስጥ እንዳይገባ እንዲያውም እንዲጠጋ አልፈቀደም ነበር፤ ከዚህም በላይ ንጉሠ ነገሥቱ ወደዚህ መምጣቱ ግልጽ ጦርነት ለማድረግ ስለነበር በዚያ ቤተ መንግሥት ውስጥ ባላባቱን ወይም ሌላ ሰው ቢያገኝ ኑሮ ቀድሞ የሚገባ እርሱ ራሱ የነበረ መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ ገለጸ። ስለዚህ በቤቱ ውስጥ ሰው ስላልነበረ ማንም እንዳይገባ ከልክሎ ሁሉም ተመለሱ። ይህ በሐምሌ ወር በተደረገው ጦርነት ድል ዕለት ሎፑ ስዋርሽ (እኔም በመርከቡ ላይ ነበርሁ) የዘይላን ከተማ ያቃጠለበት ቀን ነበር። በጦርነቱ ላይ የተማረኩት እስላሞች የአዳል ባላባት ለጦርነቱ የመጣ መሆኑን አረጋገጡ። በዚህ ጦርነት ላይ ንጉሠ ነገሥቱ የማረከውን ማናኛ ሆነው የተሠሩ አራት ወይም አምስት ባለ ብር ጫሜ ጎራዴዎች እንድናይ አዘ ነበር። ከዚህ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ ለኛ የሰጠን የወርቀ ዘቦና የከፈይ ድንኳንም በዚያው ጦርነት ላይ የተማረከ ነው፤ ያ ድንኳን የባላባቱ የግል ድንኳን ስለነበር በውስጡ እስላም ኃጢአት ሠርቶበታል ብሎ በመጠርጠር ለአገልግሎት ከማዋላችን በፊት እንድንባርከው አዘዘ። የማሕፉድን ጭንቅላት እኛ እዚያ ከመምጣታችን በፊት ሶስት ዓመት ሙሉ በቤተ መንግሥቱ ያዞሩት ነበር። እሁድና ቅዳሜ በበዓልም ቀን ተራው ሕዝብ፤ ሴቶችና ወንዶች፤ ወንዶች ልጆችና ልጃገረዶችም ለዚህ ጭንቅላት ይዘፍኑበት ነበር። የማህፉድ ጭንቅላት ለጊዜው የሚገኘው በቤተ መን ግሥቱ ውስጥ ነው፤ በጣም ስለሚወዱት ለዘለዓለም ከዚህ የሚወጣ አይመስልም።

(ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት) አባ ገብረ እንድርያስ በጣም የተከበረና ብዙ ገቢ ያለው መነኩሴ ነው። ከዚህ የጀብድ ሥራ ሌላም ታላላቅ የጀግንነት ሥራ ያከናወነ ነው። እንደሚወራውም በጣም ንግግር አዋቂ ነው ይባላል፤ ፖርቱጊዞችን የሚወድና የቤት

ክርስቲያንም ጉዳይ በጣም የሚገባው፤ ስለዚህም ማውራት የሚወድ ነው። ይህ ሰው በጣም ማውራት የሚወድ ስለነበር በዚሁ ምክንያት ብቻ አጼ ናኦድ ምላሱን አስቆነጠበው ይባላል።

ምዕራፍ መቶ አስራ አምስት፤ እኛ ያመጣንለትን የዓለም ካርታ ጽሑፎች ወደ ኢትዮጵያ ጽሑፎች እንድንተረጉምለት ንጉሠ ነገሥቱ ስለማዘዙ፤ ለሮም ጳጳስ የተጻፉ ደብዳቤዎችና ሌሎችም ጉዳዮች።

ዲዮጊ ሎፕሽ ድ ስኬይራ የላከለትን በኛ እጅ የደረሰውን የዓለም ካርታ እርሱ ለማንበብ እንዲችል እያንዳንዱን አገር የሚያሳዩትን ጽሑፎች በግርጌአቸው በነርሱ ፊደል እንድንጽፍለት ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዘን መሆኑን ደራ በነበርንበት ጊዜ ነገሩን። አምባሳደሩ፤ አባ ፀጋ ዘአብና እኔም ሥራውን ወዲያውኑ ጀምረን እኔ ሳነብለት መነኩሴው ወዲያውኑ በነርሱ ፊደል በግርጌ በኩል ይጽፍ ነበር። የኛ ፖርቱጋል በካርታው ላይ ከካስቴላ ጋር በትንሽ ቦታ የተደባለቀ ስለነበር ሴቪሊያም ከሊዝቦንና ከኮሩኛ አጠገብ የሚገኝ ስለነበረ ለእስፓኝ ሴቪሊያን፤ ለፖርቱጋል ሊዝቦንን፤ ለጋሊዛ ኮሩኛን ጠቀስሁ። የዓለም ካርታው ሥራ በሙሉ ተጠናቅቆ እንዳለቀ ወሰዱት። በማግሥቱም አምባሳደሩንና አብረውትም የነበሩትንም ሁሉ አስጠርቶ ቀርበን ንግግሩን በመጀመር የፖርቱጋልና የካስቴላ ነገሥታት የሚገዙዋቸው አገሮች በጣም ትንንሽ ናቸው፤ የፖርቱጋል ንጉሥ ከቀይ ባሕር ላይ የሩሚ ዎችንና የቱርኮችን ኃይል ለመከላከል የሚያስችለው ኃይል ያለው አይመስለኝም ሲል ገለጸልን። ስለዚህ የስፓኝ ንጉሥ በዘይላ ላይ የፖርቱጋል ንጉሥ በምጽዋ ላይ የፈረንሳይ ንጉሥም በሱዋኪን ላይ ምሽግ እንዲያሠሩ ቢጽፍ የተሻለ መሆኑንም ጨምሮ ገለጸልን። እነዚህ ሶስቱ ከርሱ ሠራዊት ጋር ሆነው ቀይ ባሕርን ሊጠብቁ ከመቻላቸው በላይ ጅዳንና ሜካን ካይሮንና የሩሳሌምን ይወስዳሉ፤ በፈቀዱትም አገር አቋርጠው ለመሄድ ይችላሉ አለ።

አምባሳደሩም መልሶ «ግርማዊ ሆይ፤ ተታለዋል ወይም ስህተት ወሬ ነው የሰሙት፤ ይህን ወሬ የነገረዎ ሰው ቢኖርም እውነቱን አልነገረዎትም፤ ካርታውን በመመልከት ብቻ አስተያየትዎን ቢሰጡ ስለአገሮቹ ትክክለኛ ዕውቀት ሊያገኙ አይችሉም፤ ፖርቱጋልና እስፓኝ በካርታው ላይ የተመለከቱት በጣም የታወቁ በመሆናቸው ነው እንጂ ገና ሊታወቁ የሚፈለጉ አይደሉም። ግርማዊነትዎ በካርታው ላይ ከተማዎችና ገዳሞችም እንዴት እንደተመለከቱ ሊረዳ ይችላል፤ ኢትዮጵያም በካርታው ላይ ያልታወቀች ሆና በሰፊ ቦታ ላይ ተበታትና አንበሶችና ዝሆኖች፤ ብዙ የተራራ ሰንሰለቶችም በዝተውባት ምንም ከተማና ግንቦች ሳይታይባት ያልታወቀች ሆና እንደተመለከተች ሊረዱት ይችላሉ። ግርማዊነትዎ የፖርቱጋልን ንጉሥ የጦር ሹማምንት በማየት ይህ ንጉሥ ከቀይ ባሕር ላይ ቱርክን ለመከላከል የሚችል መሆኑን ሊያውቀው ይገባል። የፖርቱጋል ንጉሥ በአፍሪካ ክፍል ውስጥ የማሮኮንና የፌዝን ንጉሦች እንዲሁም ሌሎችንም ነገሥታት ድል ነሥቶ የወሰደው ግዛት አለው። የሕንድን ነገሥታት ሁሉ አስገብሮ ሕንድን በሙሉ የሚገዛ ነው። ይህንንም ግርማዊነትዎ ከፖርቱጋል ንጉሥ ተቃዋሚ ከሆኑት ከሕንድ ወደ ቤተ መንግሥትዎ ሸቀጥ እያመጡ ከሚሸጡት ከእስላም ነጋዴዎች ተረድተውታል።» ለዚህ ምንም መልስ ሳይሰጠን ሌላ ጥያቄ አቀረበልን። ከዚህ በኋላ ወደ ማረፊያችን እንድንሄድ አሰናብቶን በቤተ መንግሥቱ በነበርንበት ጊዜ በሚልክልልን ዓይነት ብዙ ምግብና መጠጥ አዘዘልን።

የዓለም ካርታው ጉዳይ አልፎ አራት ወይም አምስት ቀን በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አስጠርቶን ለሮም ጳጳስ ደብዳቤ ለመጻፍ ምኞቱ መሆኑን ገለጸልን። የሮምን ጳጳስ በነርሱ ቋንቋ «ንጉሠ ሮሜ ወሊቀ ጳጳሳት» ይሉታል። ለጳጳሱ ደብዳቤ መጻፍ ልምድ ስለሌላቸው እንዴት እንደሚጻፍ ስለማያውቁ ደብዳቤውን እንድጀምርላቸውና ካለቀም በኋላ እኔ ለጳጳሱ እንድወስድላቸው አዘዘኝ። አምባሳደሩ ዶም ሩድሪጉ ድ ሊማም እኛ እዚህ የመጣነው ደብዳቤ ለመጻፍ አይደለም፤ ለጳጳሱ የሚጽፍ ሰው በመካከላችን የለንም አለ። እኔም መልሼ የደብዳቤውን መግቢያ ብቻ እነግራቸውና ከዚያም በኋላ

በልባቸው ያለውን ሁሉ ሊጽፉ ወይም ሊጠይቁ ይችላሉ አልሁት። ከዚህ በኋላ መልእክተኛ መጥቶ ወደ ማዕድ እንድንሄድና ከማዕድ በኋላ እኔና መነኩሴው ተመልሰን እንድንመጣ እኔም ደብዳቤዎቼን ለማርቀቅ መጽሐፍቴን ሁሉ ይዤ እንድመጣ ታዘዝሁ። ተመልሰን በመጣን ጊዜ ሊቃውንት በሙሉ መጽሐፍታቸውን ሰብስበው በዚያ ተቀምጠው አገኘናቸው፤ እኔንም መጽሐፎቼን ሁሉ ይዤ እንደሆን ጠይቀውኝ የግርማዊነታቸውን ሃሳብ ካወቅን በኋላ በዚሁ ተመርተን መጻፍ ብቻ እንጂ መጽሐፎች አስፈላጊ አይደሉም አሉኋቸው። ከዚህ በኋላ ከሊቃውንቱ መካከል በማዕርግና በትምህርት ከፍ ያለው አቡሄር የተባለው ሰው የንጉሡ ነገሥቱን ሃሳብ ለመነኩሴው ገልጾለት መነኩሴውም ለኔ ተረጎመልኝ።

ወዲያውኑ ደብዳቤውን መጻፍ ጀምሬ ጥቂት እንደገፋሁ ጀምሩ ለንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦለት ከተመለከተው በኋላ ወዲያው መለሰቱ። በዚያኑ ጊዜ በነርሱ ቋንቋ ተርጉመነው መልሰን ላክነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደብዳቤውን በመመለስ ንጉሠ ነገሥቱ በጣም የተደሰተ መሆኑንና ደብዳቤው የመጽሐፍ ጥቅስ ሳይገባበት እንዲህ ጥሩ ሆኖ በመዘጋጀቱ መደነቁንም ነገሩን። ይህ ረቂቅ በቶሎ በቁም ጽሕፈት በሁለት ኮፒ እንዲገለበጥ አዘዘ። እንዲሁም በደብዳቤው ላይ በተጨማሪ የሚገለጹ ነገሮች ለማግኘት ሊቃውንቱ በተቻለ መጠን መጽሐፍትን እንዲመራመሩ አዘዘ። መነኩሴውና እኔ በድንኳናችን በተመለስን ጊዜ አምባሳደሩ እንዲህ አለኝ፤ «አባ፤ ለጳጳሱ ደብዳቤ መጻፍ የሚያውቅ ሰው በመካከላችን የለም ስል ዛሬ ለንጉሠ ነገሥቱ በሰጠሁት መልስ በጣም አዝኛለሁ፤ ምክንያቱም ይህ የኔ መልስ ዕውቀት የላቸውም የሚል ግምት ሊያስጥልብን ስለሚችል ነው፤ ስለዚህ በዚህ ሥራ ላይ የተቻለዎትን ያህል እንዲደክሙበትና የሚያውቁትንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አደራዎን።» እኔም መልሼ ደብዳቤውን ጥሩም ሆነ መጥፎ በተቻለ መጠን አዘጋጅቼዋለሁ፤ ሥራዬንም በዚሁ ላይ ሊረዳው ይችላል አልሁት። ንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤውን እንደተመለከተ በጣም ተደሰተ። እኔ ያቀረብሁት «ብሩክ ቅዱስ አባት ሆይ» በሚል ቃል የሚጀምረው ደብዳቤ አነስ ያለ ሲሆን ባንድ ቅጠል እንደተጻፈ ለብቻው ሄደ። ሌላውን ደብዳቤ ለማዘጋጀት ሶስት ቀን

ፈጀባቸው። ከደብዳቤው ጋር ለጳጳሱ የሚላከውን አንድ ክሩዛዱ ክብደት ያለው የወርቅ መስቀል ለመሥራት አስራ አምስት ቀን ፈጀባቸው።

ምዕራፍ መቶ አስራ ስድስት፤ ዶም ሉዊሽ ስለተገደሉበት ሰዎች ፍርድ እንድንጠይቅ በደብዳቤው ስለማዘዙ፤ ንጉሠ ነገሥቱ አፈ ንጉሡን ወደ ምጽዋ አባ ፀጋ ዘአብንም ከዶም ሩድሪጉ ጓድ ጋር ወደ ፖርቱጋል ስለመላኩ።

ዶም ሉዊሽ ድ ምኔዝሽ ለንጉሠ ነገሥቱ በጻፈው ደብዳቤ ላይ በግዛቱ ወደብ በሐርሲኮ ላይ እስላሞች አራት ፖርቱጊዞችን ስለገደሉ ፍርድ በመጠየቅ አቤቱታ አቅርቦ ነበር። ዶም ሉዊሽ በዚሁ ደብዳቤ ላይ እንደገለጸው ንጉሠ ነገሥቱን ለማገልገል እንጂ ለማሳዘን ምኞት ስላልነበረው በርሱ አገር ሳለ ስለተፈጸመበት ጉዳት በገዛ ራሱ ያለመበቀሉ ይህንኑ ምክንያት በማድረግ መሆኑን ጨምሮ ገልጾ ነበር። ጥፋተኞቹ እንዲቀጡ እኛም ደጋግመን አስታውሰን ነበር። ሉዊሽ ራሱ ባለመበቀሉና ሐርኪኮ ከተማ የሚገኙትንም እስላሞች ሁሉ ባለመፍጀቱ ያዘነ መሆኑን፤ ይልቁንም በአገሩ ውስጥ ከሚገኙት እስላሞችና ጥቁሮች ሁሉ ይልቅ አንድ ፖርቱጌዝን አብልጦ የሚገምት መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ ገለጸልን። ስለዚህ ዶም ሉዊሽ ራሱ ሊበቀል ባለመቻሉ በደለኞቹ እንዲቀጡ የሚያዝ መሆኑን ነገረን፤ አፈ ንጉሡን አስጠርቶት ከኛ ጋር በድንኳኑ ፊት እንደቆመ፤ ወደ ሐርኪኮ እንዲሄድና የዶም ሉዊሽ ምኔዝሽ ጭፍሮች በተገደሉበት ጊዜ በዚያ የነበሩትን እስላሞች ቱርኮችንና ክርስቲያኖችን ሁሉ እንዲያሥር በአቃቤ ሰዓቱ አማካይነት አዘዘው። ገዳዮቹን ወይም ጸጥታ ሊጠብቁ የሚገባቸውን ሰዎች ያገኝ እንደሆነ አሥሮ ከፖርቱጋል ለሚመጣ ለማናቸውም ለባሕር ኃይል አዛዥ አሳልፎ እንዲሰጣቸውና አዛዡም ክርስቲያኖቹንና እስላሞቹን ሳይለይ የፈቀደውን ዓይነት ቅጣት ሊፈጽምባቸው ማለት ሊገድላቸው፤ አንገታቸውን ሊቀላ ወይም

በግዞት ሊይዛቸው የሚችል መሆኑን ገለጸለት። ለወደፊቱ ግን ስለዚህም ሆነ ስለሌላ ጉዳይ እራሳቸው መበቀል አለባቸው እንጂ ቅጣት እንዲሰጥላቸው በመጠየቅ አቤቱታ ማቅረብ አይገባቸውም ሲል አዘዘ።

ንጉሠ ነገሥቱ ከዚህ በፊት ወደ ፖርቱጋል አምባሳደር ልኮ ስለማያውቅ በዚያኑ ዕለት አንድ አምባሳደር ሹሞ ወደ ፖርቱጋል ለመላክ አስቦ አምባሳደሩንና እኔን አስጠርቶን እንደራሴውን የላከው እንደሆነ ምኞቱ በቶሎ የሚፈጸምለት መሆኑን በመገመት ከኛ ጋር አንድ ሰው ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ ለመላክ የወሰነ መሆኑን ነገረን። አባ ፀጋ ዘአብ የኛን ቋንቋ መናገር ስለሚችልና ከዚህ በፊትም በኛ አገሮች ስለነበር ለዚህ ሥራ ቢመረጥ ምን አስተያየት እንዳለን ጠየቀን። እኛም መልሰን ይህ ሰው የተጣለበትን አደራ ለመቀበልና የግርማዊነትዎም እንደራሴ ለመሆን ሙሉ ችሎታ አለው፤ ከኛ ጋር ያለ ችግር ሃሳብ ለመለዋወጥ ስለሚችል በቋንቋ ረገድ አስተርጓሚ አያሻውም አልነው፤ ይልቁንም የተላከበትን ጉዳይ አከናውኖ ሲመለስ የውጭ አገር ሰዎች ስለራሳቸው ከሚያወሩት ይልቅ ያገሩ ሰው ያየውን ማመን ስለሚቀል የአባ ፀጋ ዘአብን መመረጥ በተለይ መልካም ነገር አድርገን የምንቆጥረው መሆናችንን አረጋገጥንለት። ወዲያውኑ መልእክተኛ መጥቶ አባ ፀጋ ዘአብን ጓደኛችሁ አድርጋችሁ እንድትቀበሉት አደራ ተብላችኋል አለን። በማግሥቱ ልብስና ሰላሳ ወቄት ወርቅ እንዲሁም ለስንቃችን ወጭ እንዲችለን አንድ መቶ ብትን ጨርቅ ሰጠን። ከዚህ በኋላ በተጨማሪ አዘገዩን፤ ይህም የሆነበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ዘግይቶ በመምጣቱ ምክንያት መሆኑን አምባሳደር ፀጋ ዘአብ በኋላ ነገረኝ። አባ ፀጋ ዘአብ ለጉዞው ሊይዝ የሚገባው ነገር ማለት፤ ልብስና ወርቅ እስኪመጣ ድረስ ሊሰናበት ስላልቻለ መዘግየቱ ግዴታ ነበር። ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው ከኛ ጋር እንዲሄድ የታዘዘውን አፈ ንጉሡንም ጠብቀነው ሁለቱም ስላልመጡ ይደርሱብናል በማለት ቀስ እያልን መሄድ ጀመርን። ይህን ያደረግነው ስንብታችንን ጨርሰን ለመሄድ የምንችል መሆናችንን ካወቅን በኋላ ነበር። ስለዚህ እኛ መንገዳችንን ቀጥለን ሁለቱ ሰዎች በየተራቸው በጎዳናው ሳለን ደርሰውብን፤ በዚህ አኳኋን

እስከ ባርዋ ድረስ አብረን ተጓዝን። ከዚህ በፊት የኛ ጓዝ ያረፈው በዚህ ከተማ ነበር። ስለፖርቱጌዞች ወደ ወደቡ መምጣት ምንም ወሬ ስላልሰማን የክረምቱ ወራት እስኪያልፍ ድረስ ሁላችንም ባንድነት ቆየን። በዚህ በነበርንበት ጊዜ አፈ ንጉሡ ፖርቱጌዞቹ በተገደሉ ጊዜ በሐርኪኮ ይገኝ የነበረውን የከተማውን ሽማግሌ አሠረው። ሽማግሌ የሚባለው የማዕርግ ስም ርስት ለሌለው አነስተኛ መኮንን የሚሰጥ ነው። ይህ ሰው የታሠረበት ምክንያት በዚያን ጊዜ ዳኛ ስለነበር የግዴታ ተግባሩን ስላልፈጸመ ነው። ገብረ የሱስ የተባለው ሰውዬም ምንም እንኳን ሥልጣን ቢኖረውም አንዳች ነገር ስላላደረገ ታሠረ። በዚያን ጊዜ ባሕር ነጋሽ የነበረው ራስ ያዕቆብም ታሠረ። ትልቅ ሥልጣን ለነበረው ደፍላ ለተባለ ሰው የዶም ሉዊሽን ጭፍሮች የገደሉት ቱርኮችና እስላሞች በሐርኪሶ የሚገኙ መሆና ቸውን እያወቀ በርሱ ግዛት እንዲገቡ መጠጊያ ስለሰጣቸው ታሠረ። እነዚህን አራቱን መኳንንት አሥሮ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲልካቸው ማንም ሊከሳቸው የተነሣ አልነበረም። ምንም እንኳ ቢጉላሉም በመጨረሻ ነፃ ተለቀቁ። አፈ ንጉሡ በቤተ መንግሥቱ እንደደረሰ ፖርቱጌዞቹ ገና በወደብ ላይ አለመድረሳቸውንና እኛም በችግር ያለን መሆናችንን ለንጉሠ ነገሥቱ ገልጾለት እርሱም ወዲያውኑ ቀላጤ ልኮ ወደአክሱም እንድንሄድ አዘዘ፤ ከዚህ በፊት የነበርንበት ይህ አክሱም ንግሥተ ሳባና ንግሥት ሕንደኬ ይኖሩበት የነበረ ከተማ ነው። በዚያም ሃምሳ ጭነት ስንዴ፤ አንድ መቶ ፍሪዳ፤ አንድ መቶ በጎች፤ አንድ መቶ ማር አንድ መቶ ቶፋ ቅቤ ተሰጠን። ለአባ ፀጋ ዘአብ ደግሞ ሃያ ጭነት ስንዴ፤ ሃያ በጎች፤ ሃያ ቶፋ ማርና ሃያ ቶፋ ቅቤ ታዘዘለት።

ምዕራፍ መቶ አስራ ሰባት፤ አምባሳደር ፀጋ ዘአብ ለግል ጉዳዩ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲመለስ እኔም አብሬው ስለመሄዴ፤ አፈ ንጉሡና ሁለት መነኩሴዎች ስለመገረፋቸው።

በአክሱም ከተማ በነበርንበት ጊዜ አምባሳደር ፀጋ ዘአብ ከግዛቱ አንድ ትንሽ ቀበሌ የተወሰደበት መሆኑን አንድ መልእክተኛ ስለነ ገረው ወደ ቤተ መንግሥቱ ከርሱ ጋር ሄጄ ፍርድ እንድለምንለት ጠየቀኝ። እኔም አብሬው ሄጄ ዋና ጠላቱ የንጉሠ ነገሥቱ ብላቴናዎች አለቃ አብዲናጎ መሆኑን ተረዳሁ። ከዚህ በፊት እንደተባለው ይህ ሰው የበላይ ሃላፊ የሌለው አንድም ሥራ የሌለው ሰው ነው። ማናቸውም መልእክት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ የሚደርሰው በብላቴናዎቹ አማካይነት ስለነበር በነርሱ በኩል ንጉሠ ነገሥቱን መድረስ ስላል ተቻለን ወደ ታላቁ መኮንን ወደ አዛዡ መሄድ ግድ ሆነብን። ምንም እንኳ ይህ ሰው የተቃዋሚያችን የአብዲናጎ ወዳጅ ቢሆንም ፍርድ እንዳይጎድል ሲል ጉዳዩን ለንገሡ ነገሥቱ አቅርቦ በምን ምክንያት ተመልሰን እንደመጣን ነገረልን። ከዚህ በኋላ መልእክተኛ ወደኔ ዘንድ መጥቶ አንተስ በምን ምክንያት ነው ተመልሰህ የመጣኸው ሲል ጠየቀኝ። እኔም ማናቸውንም ነገር ዘርዝሮ በማስረዳት ቀጥሎ የተመለከተውን ነገርሁት፤ «አባ ፀጋ ዘአብ በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድ የፖርቱጋልን ንጉሥ እንዲያገለግል ከኛ ከፖርቱጊዞች ጋር ሆኖ ከአገሩና ከግዛቱ ውጭ በሚገኝበት ጊዜ የተፈጸመው አግባብ ያልሆነ ተግባር በፖርቱጋል ንጉሥና በኛም በዜጎቹ ላይ እንጂ በእርሱ ላይ አይደለም። ስለዚህ መሬቱ እንዲጸናለት እንጂ እንዲወስድበት ወይም እንዲቀማ አያስፈልግም። በኛ አገር ደንብ ነገሥታትን ለማገልገል ወደውጭ የሚላኩ ሰዎች ራሳቸው ብቻ ሳይሆኑ አሽከሮቻቸው፤ ሃብት ጠባቂዎቻቸው፤ የቤት ሃላፊዎቻቸው፤ ገቢያቸውን ግዛቶቻቸው ሁሉ ተከብረው ይጠበቁላቸዋል። ስለዚህ ግርማዊነታቸው መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ለአምባሳደራቸው መልካም አስተያየት እንዲያደርጉለትና ግዛቱ እንዲመለስለት ያዙ ዘንድ በተስፋ እንጠብቃለን።» ወዲያውኑ የንጉሠ ነገሥቱን መልስ መልእክተኞች ይዘው መጥተው የበደለን ማን መሆኑን እንድንነግራቸው ጠየቁን። ይህን

የሕግ ተላላፊነት ሥራ የፈጸመው ሰው በቤቱ ሃላፊዎችና በንብረት ሹሞቹም አማካይነት የብላቴናዎቹ አለቃ አብዲናጎ መሆኑን ገለጽን፤ ቅን የሆኑ ዳኞች እንዲሰጡን ለመንን፤ እንዲሁም ስለዚህ ጉዳይ አስፈላጊ የሚሆነውን መልእክት ሁሉ እንዲያደርሱለት ብላቴናዎቹን እንዲያዝ ንጉሠ ነገሥቱን በተጨማሪ ለመንነው። ወዲያውኑ አራት ብላቴናዎች ወደኛ መጥተው ስለዚህ ጉዳይ የምትጠይቁትን ነገር ሁሉ ማንንም ሳንፈራ በሙሉ ልብ እንድናከናውን ጌታችን አዞናል አሉ። ጉዳዩን እንዲመለከቱልን የታዘዙት ዳኞች አዛዥ ዳረጎትና አዛዥ እሳት ነበሩ። ወደዳኞቹ ወዲያውኑ ቀርበን ፀሐይ በዚህ ቦታ ስትደርስ በንደዚህ ያለ ቦታ እንድትመጡ ብለውን በቀጠሮ አሰናበቱን። በቀጠሮአችን መሠረት በዳኞቹ ፊት ቀርበን የአብዲናጎ እንደራሴዎችና አምባሳደር ፀጋ ዘአብ ራሱ ቀረበ፤ ከሳሽና ተከሳሽ ብዙ ጊዜ ከተከራዘሩ በኋላ በቃል ፍርድ ተሰጠ፤ በዚህ አገር ማናቸውም ዓይነት የፍርድ አፈጻጸም በጽሑፍ ስለማይሠፍር ፍርድ የሚሰጠው በቃል ነው። ዳኞቹም ፀጋ ዘአብ የሚከራከርበት ምድርና ጉልት በጣም ትንሽ በመሆኑ አብዲናጎ ከሚገዛው ምድር ጋር የግዴታ መደረብ አለበት አሉ፤ ስለዚህ አብዲናጎ ትልቅ ሰው እንደመሆኑ ገቢው ሊነሣው አያስፈልግም ሲሉ ፈረዱ። ይህ ፍርድ ከፉኛ ቅሬታ ስላሳደረብን ይግባኝ ለማለት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሄድን። እርሱም መልእክተኛ ልኮ ማናቸውም ነገር በሚገባ አኳኋን እንዲከናወን ይደረጋልና አታስቡ፤ ለጊዜው ግን ወደ ማረፊያችሁ ልትሄዱ ትችላላችሁ ሲል አዘዘ፤ ከዚህም በላይ በነጋታው በደ አፈንጉሡ ተመልሰን እንድንሄድና እንድንለምነው እርሱም ደህና ፍርድ የሚሰጠን መሆኑ ተነግሮን ሄድን። በማግሥቱም አፈ ንጉሡን ለማግኘት ሄደን ወደ ድንኳኑ በሚወስደው መንገድ ላይ ሆነን ስንጠብቀው ከቆየን በኋላ አግኝተነው በደንብ ተቀብሎን ያነጋገረን ከመሆኑም ይልቅ እኛን ተቀብሎ እንዲያነጋግረን ከንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ትዕዛዝ የደረሰው መሆኑን ነገረን። ለጊዜው ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመሄድ ተነሥቶ ስለነበር ሲመለስ የሚያነጋግረን መሆኑን ገልጾልን በፍርድ ድንኳኑ ውስጥ ገብተን እንድንጠብቀው አዘዘን። የሆነው ሆኖ ከንጉሠ ነገሥቱ ለመገናኘት ሲገባ ሕዝቡን ትቶ እስከሚሄድበት ቦታ ድረስ ተከትለነው ይህ ሰው ባሳየን በጎ ፈቃድ መሠረት ተቀብሎ ያነጋግረናል በማለት

በዚያ ቆመን ስንጠብቅ ሁለት ብላቴናዎች ተከትለውት ሰው ወደሚገረፍበት ቦታ ሄደ። በዚያ እንንደደረሰ ሁለት ገራፊዎች መጥተው ልብሱን አውልቀው በምድር ላይ አጋደሙት። ከዚህ በፊት በገለጽሁት አኳኋን በሆዱ አጋድመው ሁለት እጆቹን ከሁለት እንጨት ጋር ወጥረው አሥረው እግሮቹንም በጠፍር አሥረው ሁለት ሰዎች ወጥረው ይዘው ከመገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ ግርፋ ተጀመረ። ሁለት ገራፊዎች አንዱ በግራ ሌላውም በቀኝ ሁነው ይገርፉት ነበር። አብዛኛውን ጊዜ መሬቱን ነበር የሚመቱት። ግረፉት የሚል ተዕዛዝ ከንጉሠ ነገሥቱ በመጣ ጊዜ ግን ሥጋውን አልፎ አጥንቱን እስኪሰማው ድረስ ጅራፉን አሳረፉበት። በዚህ ዓይነት ግርፍ ይህን ሰው ሶስት ጅራፍ አሳረፉበት። አፈንጉሡ ከዛሬ ጋር ሶስት ጊዜ ሲገረፍ ማየቴ ነው። ግርፍ እንደውርደት ስለማይቆጠር ከሁለት ቀን በኋላ ወደሥራው ተመለሰ። እንዲያውም የሚገረፍ ሰው ሁሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ችሮታ የታጨ ሰው ስለሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተጠርቶ ሃብት ይሰጠዋል ይባል ነበር። አፈ ንጉሡ በተገረፈ ጊዜ ብጫ ልብስ የለበሱ መነኩሴዎችም በዚያ ይገኙ ነበር። አፈንጉሡን ገርፈው ካበቁ በኋላ የነዚያን መነኩሴዎች አለቃ የነበረውን አንድ የተከበረ ሽማግሌ ጥለው ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ሁኔታ ገረፉት፤ ይህን ሽማግሌ አንድ ጊዜ እንኳ ጅራፍ አላሳረፉበትም። ከዚህ በኋላ ዕድሜው ከአርባ ዓመት ጥቂት በለጥ የሚለው ጨዋ መሰል አንድ መነኩሴ ጥለው እንደሌሎቹ ገረፉት። ይህን ግን ሁለት ጅራፍ አሳረፉበት። ጅራፉ ካበቃ በኋላ መነኩሴዎቹ የተገረፉበት ምን በድለው ነው ስል ብጠይቅ ቀጥሎ የተመለከተውን መልስ ሰጡኝ። በመጨረሻ የተገረፈው መነኩሴ የአጼ እስክንድርን ልጅ አግብቶ የነበረ ሲሆን ይህችኑ ሴት ፈቶ የአጼ ዳዊትን እህት አግብቶ ይኖር ነበር። ነገር ግን ሁለተኛይቱ ሚስቱ ያሻትን ነገር ሁሉ የምትፈጽም ሴት ስለነበረች ባልዩው ንጉሠ ነገሥቱን በመፍራት ይልቁንም በዚህ አገር የሴትን በደል በማድነቅ ስለማይመለከቱት ይህችን ፈትቶ የመጀመርያ ሚስቱን ታረቀ። እህቱን እንዲታረቅለት ንጉሠ ነገሥቱ አዞት ነበር፤ ነገር ግን ይህን ከማድረግ ይልቅ ምንኩስናን መረጠ። ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ መነኩሴዎቹን ጠርቶ ወደ አፈንጉሡ ቀርበው የዚህ ሰው ምንኩስና ሕጋዊ መሆኑ እንዲጣራ አዘዘ። ጉዳዩን ካጣራ በኋላ ሕጋዊ መሆኑን ስላረጋገጠ አፈንጉሡ እንዲገረፍ ታዘዘ። ሽማግሌው መነኩሴ የተገረፈበት ምንኩስናውን በመስጠቱ ነው፤ ሶስተኛው ደግሞ ምንኩስናውን በመቀበሉ ነው። ይህ ሰው ምንኩስናውን ትቶ ከንጉሠ ነገሥቱ እህት ጋር እንዲታረቅ አዘዙት። በገዳሙ ውስጥ በተፈጸመው ተግባር ምክንያት ጉዳያችን ሳይሰማልን አስራ አምስት ቀን ቆየን፤ እነዚህ ጉዳዮች ምን መሆናቸውን እገልጻለሁ።

ምዕራፍ መቶ አስራ ስምንት፤ እቴጌ እሌኒ ከሞተች በኋላ ታላቁ ቢትወደድ የግዛትዋን ቀረጥ ሊሰበስብ ስለመሄዱ፤ የሐዲያ ወይዘሮ እርዳታ ልትጠይቅ ስለመምጣትዋ አብረዋትም በበቅሎ ስለመጡት ሰዎች።

የጎጃምን አብዛኛውን ክፍል ትገዛ የነበረች እቴጌ እሌኒ ከሞተች በኋላ ስምንት ወይም ዘጠኝ ወር በቤተ መንግሥቱ የሚመጡ ሰዎች ሁሉ በተለይ ለሃዘንተኞች መቀበያ እንዲሆን በተተከለው ድንኳን ውስጥ እየገቡ ያለቅሱ ነበር። እኛም በመጣን ጊዜ እንዲሁ አደረግን። እቴጌይቱ ከሞተች በኋላ ከርስዋ ምድር ለንጉሠ ነገሥቱ በያመቱ የሚከፈለውን ግብር እንዲሰበስብ ታላቁ ቢትወደድ ወደ ጎጃም ሄደ። ቢትወደዱም ግብሩን ሰብስቦ ሲመለስ 3000 በቅሎዎች፤ 3000 ፈረሶች፤ 3000 ባዘቶ አመጣ። ርካሽ የሆነ እያንዳንዱ አንድ ወይም ሁለት ድራክም የሚያወጣ ይህ ጨርቅ ባዘቶ ይባላል። ባዘቶ ታላለቅ ሰዎች በአልጋቸው ላይ የሚደርቡት ሥጋጃ ይመስል ጭገራም ሆኖ የተሠራ ልብስ ነው፤ ከዚህም ለላይ በጣም ርካሽ የሆነው ከአንድ ወቄት ወርቅ በታች የማይገኝ 30000 የጥጥ ጨርቅችም ነበሩ። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ ዋጋቸው ከሁለት እስከ አምስት ወቄት ወርቅ ያወጣል። ከዚህም በላይ ከጎጃም ሰላሳ ሺ ወቄት ወርቅም መጥቶአል ይባላል። አንድ ወቄት ወርቅ አስራ አንድ ክሩዛዱሽ ይከብዳል።

ግብሩን በሚያስረክቡበት ጊዜ ወርቁን በገበታ ላይ አስቀምጠው ሸፍነው ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ሲያቀርቡ እኔ ራሴ አይቻለሁ። ቢትወደዱ የካስቴላ አጋሰስ ነጅዎች የሚደፉትን ቆብ የሚመስል ተክሊል በራሱ ላይ ደፍቶ ከወገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ ወደ ንጉሣዊው ድንኳን ተጠግቶ በሁለት ድንኳኖች መካከል ንጉሠ ነገሥቱ ሊሰማው በሚችልበት ቦታ ሆኖ በፍጥነት በመደጋገም ሶስት ጊዜ አቤቶ ሲል ጮኸ። እነርሱም ከድንኳናቸው ውስጥ ሆነው አንተ ማን ነህ ሲሉ በቋንቋቸው ሁለት ጊዜ ጠየቁት። እርሱም መልስ በመስጠት «እኔ ድምጼን የማሰማው ከቤትህ ካሉት ሁሉ በጣም ዝቅ ያልሁት ነኝ፤ በቅሎሆህን የምነዳና ያዘዝሽኝን ሁሉ የምፈጽም ነኝ፤ ጌታዬ ሆይ ያዘዝሽኝን ይገፎ መጥቻለሁ።» ሲል ሶስት ጊዜ በመደጋገም አሰማ። ከዚህ በኋላ በውስጥ ያለው ድምጽ «ዝለቅ፤ ዝለቅ» ሲል አዘዘው። ወደፊት ጥቂት እልፍ ብሎ ከድንኳኑ ፊት ለፊት እንደደረሰ እጅ ነስቶ ወደፊት አለፈ። ከርሱ በኋላ ፈረሶቹ አንድ በአንድ ረድፍ ገብተው እያንዳንዱን ፈረስ አንድ ሰው ሸብቦ እየሳበው አለፉ። በመጀመርያ ያለፉት ሰላሳዎቹ የተጫኑ ሲሆኑ ሁኔታቸውም የሚያሳጣ አይደለም። ከነሱ ከሚከተሉት ግን በጣም የተሻለ የተባለውን ቢገምቱት ሁለት ድራክም ይበዛበታል። ብዙዎቹ ከአንድ ድራክም በላይ አይገመቱም። እነዚህ ፈረሶች እኔ ከገመትሁት ዋጋ በታች ሲሸጡ አይቻለሁ። የፈረሶቹ ቁጥር ከሶስት ሺ አያንስም። እነዚህ ምስኪን ቀጫጫ ፈረሶች ካለፉ በኋላ በቅሎዎቹ ተከተሉ። ከበቅሎዎቹ ማለፊያዎቹን ሰላሳውን እንደተጫኑ አስቀድመው መናኛዎቹን አስከትለው በድንኳኑ ፊት አሳለፉዋቸው። ለጭነት የደረሱት በፊት ቀድመው ያለፉት ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት ግን በአንድና በሶስት ዓመት ዕድሜ መካከል የሆኑ ገና ያልተገሩ ነበሩ። እነዚህ ከሶስት ሺ የማያንሱ በቅሎዎች ካለፉ በኋላ ባዘቶ የተሸከሙት ሰዎች ተከተሉ። ባዘቶዎቹ በጣም ከባድ ስለነበሩ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ተሸክመው አለፉ። ከነዚህ በኋላ የቤት ሥር ሸማ የያዙት ሰዎች ተከተሉ። እያንዳንዱ ሰው አስር ሸማ ባንድነት አስሮ ተሸክሞ ነበር ይባላል፤ ባዘቶውን የተሸከሙት ሰዎች ሶስት ሺ እንዲሁም የቤት ሥር ሸማውን የተሸከሙት ሰዎች ደግሞ ቁጥራቸው ከዚሁ እኩያ ነበር። እነዚህ ሰዎች ሁሉ ግብር ይዘው ከጎጃም የመጡ ናቸው። ከልብሱ በኋላ

ማዕድ የሚቀርብበትን ገበታ የመሰለ በአረንጓዴና በቀይ መሶብ ልብስ ሸፍነው በጭንቅላታቸው ተሸክመው ሶስት ሰዎች ተከተሉ። ከገበታው በኋላ የቢትወደዱ ጭፍሮች ተራ ገብተው እንደ አለቃቸው አለፉ። በገበታው ውስጥ ተሸፍኖ ያለፈው ወርቅ ነበር ይባላል። ከዚህ በኋላ ቢትወደዱ ግብሩን በሙሉ እንደያዘ ወደ ማረፊያው እንዲሄድ ታዘዘ። ግብሩን የማስረከቡ ስነ ሥርዐት ከጥዋት ጀምሮ የማታ ጸሎት እስከ ሚያልቅበት ጊዜ ድረስ ማለት በጠቅላላው አስር ሰዓት ያህል ፈጀ።

የሐዲያ ንጉሥ ሚስት የነበረችው አንዲት ሴት ወይዘሮ እስላም ወደ ቤተ መንግሥቱ ከመጣች አስራ አምስት ቀን አልፉዋት ነበር፤ የዚችው ሴት ወይዘሮ እህት ለንጉሠ ነገሥቱ ሚስት እንድ ትሆን ታጭታለት ነበር፤ ነገር ግን ሁለቱ የፊት ጥርሶችዋ ወደፊት የገጠጡ ስለነበሩ አሁን የቢትወደድነቱን ማዕርግ ይዞ ለሚገኘው ለጥንቱ ባሕር ነጋሽ ዳራት። ሴት ወይዘሮይቱ የመጣችበት ምክንያት የባልዋ ወንድም የሆነ አንድ ሰው ግዛትዋን ሊወስድባት ስለፈለገ አቤቱታ ለማቅረብ ነበር። ይህች ሴት በበቅሎ የተቀመጡ ሃምሳ ሰዎች በእግራችው የሚሄዱ መቶ ሰዎች እንዲሁም እርስዋን በተለይ የሚያጅቡ በበቅሎ የሚሄዱ ስድስት ሴት ወይዘሮች አስከትላ እቴጌ መስላ ነበር የመጣችው። የተከተሉዋት ሰዎች በጣም ጥቂር አልነበሩም። በመጣች በሶስተኛው ቀን በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርባ በክብር ተቀ በላች፤ የራስዋን ጥቁር አጎበር አስይዛ ነበር የመጣችው። የዚያን ዕለት ሁለት ጊዜ ልብስዋን ለወጠች። ሁለቱም ቀሚሶች በተለይ እስላሞች የሚለብሱዋቸው ከሕንድ የመጡ በወርቅ ሃረግ የተጠለፉ ከከፈይ ጨርቅ የተሠሩ ናቸው። ይህች ወይዘሮ ወደማረፊያዋ ሄዳ ሃሳቡዋን ጥላ እንድታርፍና የለመነችውንም ሁሉ የሚፈጽም ላት መሆኑን ንጉሠ ነገሥቱ ነገራት። ባሕር ነጋሹና ትግሬ መኮንኑ እንደመጡለት ከግዛቱ ድረስ የሚሄድ መሆኑን ነገራት ወይም ላከባት ይባላል። ከመጣች አስራ ስምንት ቀን ካለፉት በኋላ ሴት ወይዘሮይቱ ለሁለተኛ ጊዜ ያማረ ልብስ ለበሰች።

በማግሥቱ ባሕር ነጋሹ መጣ። እርሱም በመጣ በማግሥቱ ትግሬ መኮንኑ ደረሰ። ሁለቱም የመጡት ግብር ይዘው ነበር። ከነርሱም

ጋር ጨዋዎችና መሣርያ የያዙ ሌሎችም ታላላቅ መኳንንት መጡ። እነዚህ መኳንንት ባንድነት ተሰብስበው ግብራቸውን ከማቅረባቸው በፊት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ከጎጃም የመጣው ግብር እንዲቀርብለት ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ቀኑ አርብ ስለነበር በሚቀጥለው ሰኞ ቢትወደዱ ግብሩን በበፊቱ ስነ ሥርዓት ባሕር ነጋሹና ትግሬ መኮንኑ አብረዋቸውም የመጡት ሌሎች መኳንንት በሚገኙበት አስረከበ። የማበርከቱ ስነ ሥርዐት ከጥዋት እስከ ማታ ያለውን ጊዜ ፈጀ። በማግሥቱ ከጥዋት ጸሎት ጊዜ በኋላ ባሕር ነጋሹ ግብሩን ማስረከብ ጀመረ። በመጀመርያ ያቀረበው እጅግ ማለፊያ የሆኑ ፈረሶችን ነበር፤ በዚህ ቀን ሌላ ምንም ሳይሠራ እነዚያን ፈረሶች በማየትና ወዲያና ወዲህ በመንቆራጠጥ ብቻ ጊዜው አለፈ። በማግሥቱም ብዙ ሐርና ከሕንድ የመጡ ስስ ጨርቆችን አቀረበ ይባላል። የዚያን ዕለት አሞኘ ስለነበር በርክክቡ ስነ ሥርዐት ላይ አልተገኘሁም። ይህ አስረክቦ ከጨረሰ በኋላ በማግሥቱ በጥዋት ትግሬ መኮንኑ ግብሩን ማስረከብ ጀመረ። እርሱ ያቀረባቸው ፈረሶች ሁለት መቶ ሲሆኑ ከባሕር ነጋሾቹው ከፍ ከፍ ያሉና የመጡበትም አገር እሩቅ ስላልነበረ መንገድ ስላል ጎዳቸው ከበፊተኞቹ በጣም የተሻሉ ናቸው። ሁለቱም ያቀረቡዋቸው ፈረሶች የመጡት ከግብጽ አገር ሲሆን አንዳንዶችም ከአረብ አገር የመጡ ይገኙባቸዋል። ያ ቀን ፈረሶችን በመረካከብ ብቻ አለፈ። በማግሥቱ ያስረከቡት ሐር ሲሆን በሕይወቴ ይህን ያህል ብዙ ሐር አላየሁም። የዚያን ዕለት ሌላ ነገር ሳይሥራ ሐሩን በመረካከብ ብቻ ጊዜው አለፈ።

በሚከተለው ሰኞ በእኩለ ቀን ላይ ሮቤል የሚባል የትግሬ መኮንኑ ጭፍራ ለብቻው ግብሩን አቀረበ። በግብር ስም ያቀረበው ሰላሳ ፈረሶች ሲሆን እነዚህ ፈረሶች በሙሉ ከግብጽ የመጡና ቁመታቸው ዝሆን የሚያህል በሚገባ የተቀለቡ ናቸው። ፈረሶቹን አንድ በአንድ ይስቡ የነበሩት መታወቂያ ማዕርግ የሌላቸው ሸማግሌ በሚያሰኝ መጠሪያ የሚታወቁ ሰዎች ነበሩ። ከነዚህ ሸማግሌዎች ስምንቱ የኛን የሚመስሉ በነሐስ ምስማር የተጣበቁ የባሕር አረብና የከፊይ ገበር ያላቸው ያማሩ የደረት ጋሻዎች አድርገው ነበር። እነዚሁ ስምንቱ ሸማግሌዎች የኛኑ የመሰለ የራስ መጠበቂያ ባርኔጣ ደፍተው

ነበር። ባለጋዳ[1] ሮቤል በስምንቱ ውስጥ ነበር የሚገኘው፤ የተቀሩት ሃያ ሁለቱ ግን እጅጌው ረጅም የሆነ በሰውነታቸው ላይ ልክክ የሚል ሙሉ የብረት ልብስ ደርበው ነበር። ሁሉም እያንዳንዳቸው ሁለት ጦርና ቱርኮችን ይመስል ትንንሽ ፋስ ይዘዋል፤ በራሳቸውም ላይ ነፋስ ጫፉን የሚያውለበልበው ሾል ያለ ቆብ ደፍተው ነበር። ከነዚህ ሰዎች ፊት ሁለት ጥቋቁር ወጣቶች ቀይና ብጫ የመለያ ልብስ ለብሰው ይህንኑ በሚመስል ጨርቅ በተሸፈኑ ግመሎች ላይ ተቀምጠው ነጋሪት እየጎሰሙ ይሄዱ ነበር። በንጉሣቸው ድንኳን ፊት ለፊት በደረሱ ጊዜ ፈረሶቹን ለቀው ባንድ ቦታ አቁመዋቸው ጉሰማው ቀጠለ፤ ሸማግሌዎቹም የጉግስ ጨዋታ አሳዩ። ጨዋታው በጣም በመድራቱ ምክንያት ባሕር ነጋሹና ትግሬ መኮንኑ ካመጡዋቸው ፈረሶች ውስጥም ሌሎች አምጥተው በጨዋታው እንዲያስገቡ ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ጨዋታው እስከ ጀንበር ጥልቀት ድረስ ቀየ። ባለጋዳ ሮቤል ወደዚህ አገር በመጣን ጊዜ ዶም ሩድሪጎ ከብረት የተሠራ ባርኔጣ ያበረከተው ከርሱም አንድ ጉራዴ ባንድ በቅሎ የገዛው ሰው ነው።

ምዕራፍ መቶ አስራ ዘጠኝ፤ ለሐድያ ንጉሥ ሚስት እርዳታ ስለመሰጠቱ፤ ታላቁ ቢትወደድ ስለመታሠሩና ስለመፈታቱ፤ ሌሎችም መኳንንት ስለመታሠራቸው።

ባሕር ነጋሹንና ትግሬ መኮንኑን ተከትለው ከመጡት ባለመሣርያ ጨዋዎችና ከመኳንንቱም አስራ አምስት ሺ ሰዎች (በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ የጠቀስነው) ሕዱግ ራስ በሚያሰኝ መጠሪያ በሚታወቅ አንድ መኮንን እየታዘዙ በቶሎ ሄደው ንጉሡን በሰላም በሥልጣኑ ላይ እንዲመልሱትና ባለቤቲቱም ቀስ ብላ ወደ አገርዋ እንድታዘግም ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ሕዱግ ራሱና ወይዘሪቱ ወዲያውኑ መንገዳቸውን ጀመሩ፤ በሐድያ አውራጃ ለመድረስ አንድ ወር መንገዝ ያስፈልጋል ይባላል።

ወይዘሪቱ በሄዶች በማግሥቱ ከጎጃም ግብር ሰብስቦ የመጣው ቢትወደድ እንዲታሠር ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ሁሉም በዚያው ቀን እንደታሠሩ ከነአጀቡ ወደሌላ ቦታ ለመሄድ በማለዳ ጉዞውን ጀመረ። እኛም ለመመለስ ተነሣን። አምባሳደር ፀጋ ዘአብና እኔ ባንድ ወንዝ አጠገብ በቅሎቻችንን ሣር ስናስግጥ ሳለን ግብሩን ያመጣው ቢትወደድ ባጠገባችን ሲያልፍ አባ ይባርኩኝ አለኝ። እኔም መልሼ እግዚአ ብሔር ይባርክህ አልሁት። ይህን ቢትወደድ አስራ አምስት በቅሎች አጅበውት ነበር። እኛም በቅሎቻችንን ተቀምጠን እርሱን ተከትለን ሄድን። ባጠገቡ እንደደረስሁ እጄን ስሞኝ እንደጎና እንድባርከው በመጠየቅ እንዲህ አለኝ። ይህ ነገር ምን ይመስልዎታል? በናንተ አገርም ታላላቅ ሰዎችን እንዲሁ ያሥሩዋቸዋልን? እኔም ለዚህ ጥያቄ መልስ በመስጠት በኔ አገር ታላላቅ ሰዎች በትንሽ ጥፋት ወይም ነገሥታትን በማስቀየም እንዲታሠሩ ሲፈረድባቸው ነገሥታቱ የራሳቸውን ቤት ለመታሰርያ ይሠጡዋቸዋል። ጥፋታቸው ትልቅ ከሆነ ግን በታላላቅ ግንብ ቤቶችና በእሥር ቤት ያኖሩዋቸዋል ስል መለስ ሁለት። እርሱም በፊቱ ላይ እንባውን እያንቆረቆረ አባ በዚህ ሁኔታ እንዳለሁ መሞቴ ነውና እግዚአብሔርን ይለምኑልኝ አለኝ። ከቀትር በኋላ ከኛ ተለይቶ እስኪሄድ ድረስ በተቻለኝ መጠን ሳበርታታውና ሳጽናናው ቆየሁ። አብረውት የነበሩት በቅሎኞችም ሆኑ በእግር የሚከተሉት የርሱ ሰዎች አልነበሩም። በማግሥቱ ተገናኝተን እንዳ ለፈው ቀን ቀጠልን። እርሱም እንደበፊቱ በዚህ ቦታ መሞቴ ነውና እግዚአብሔርን ይለምኑልኝ አለኝ። የታሠረበት ሰንሰለት እጆቹ ቁርጭምጭሚቶች ላይ ከነበሩት አንባር ከሚመስሉ ብረቶች ጋር የተያያዘ የውሻ ማሠርያ ሠንሰለት የሚመስል በቀጭኑ የተሠራ ሲሆን በሄደ ቁጥር ሰንሰለቱን በእጆቹ ውስጥ ያኖረዋል፤ የተከተሉት ሰዎች ሁሉ ጠባቂዎቹ ነበሩ። በከተማው ረቡዕ ዕለት ደረስን። የዚያኑ ዕለት ቢትወደዱን እንዲያቀርቡለት ንጉሠ ነገሥቱ ጠይቆ አብረውት የነበሩት ጠባቂዎች አቀረቡት ይባላል። ከቢትወደዱ ልጆች ሁለቱ የዚያኑ ዕለት ማታ አባታቸውን ተከትለው ሄደው ነበር ይባላል። በንጉሣዊው ድንኳን በር እንደደረሱ ንጉሠ ነገሥቱ በተለይ ቢትወደዱን ሊያነጋግረው ስለፈለገ ከድንኳኑ ጓሮ ዞሮ እንዲቀርብ ጠባቂዎቹና ልጆቹም ጥቂት እልፍ ብለው እንዲጠብቁ

መታዘዙን ለመንገር ብላቴናዎቹ መጡ። በማግሥቱ ንጉሠ ነገሥቱና እኛም ከዚያ ቦታ ተነሥተን እስክንሄድ ድረስ በዚያ ቦታ ሆነው ሲጠብቁ አደሩ። ስለዚህ ቢትወደዱ በሕይወቱ መሆኑ ወይም መሞቱ ሳይረጋገጥ ወይም ወዴት እንደደረሰ ሳይታወቅ ጠፍቶ ቀረ። ለአካለ መጠን የደረሱና እንደሚባለውም ስመ ጥር ወታደሮች የነበሩት እበሩ ድረስ ተከትለውት የመጡት ሁለቱ ልጆቹና በቤት የነበሩት ሌሎቹ ሶስቱ ልጆች አሽከሮቻቸውን ሁሉ ሰብስበው የነገሥታት መኖርያ በሚመስለው ባባታቸው ቤት ውስጥ ትልቅ ለቅሶ ተደረገ። የቢትወደዱ ልጆች የራሳቸውን ወይም ያባታቸውን አሽከሮች ሳያስከትሉ ብቻቸውን እንዲሄዱ ንጉሠ ነገሥቱ አዞ እንዲሁ አደረጉ። አምስቱ ልጆች አንድም አሽከር ሳያስከትሉ ከወገባቸው በታች ጥቁር ልብስ አሸርጠው በቅሎዎቻቸውንም በጥቁር ልብስ ሸፍነው በትከሻቸው ላይ የጥቁር በግ ለምድ ደርበው ሲሄዱ አይቻቸዋለሁ። አሽከሮቻቸውም በሃዘን ተጨብጠው የተጫኑ በቅሎዎቻቸውንም ከፊት አስቀድመው በእግራቸው ይጓዙ ነበር።

በሚቀጥለው ሰኞ በወጅ አውራጃ ድንበር ላይ እረፍት ተደርጎ ከዚህ በፊት የተጠቀሰውን የጥምቀትን በዓል ለማክበር ዝግጅት ተጀመረ። በዚህ ቦታ ካደርን በኋላ የቢትወደዱ ልጆች በማግሥቱ በጥዋት ተነሥተው በየመኳንንቶቹ ድንኳኖች እየዞሩ አባታቸው በሕይወቱ እንዳለ ወይም የት እንደደረሰ ወይም ምን ሊደረግ እንደታሰበ ለማወቅ መጠየቅ ጀመሩ። ነገር ግን ይዘውት የሄዱት ሰዎች ከአስራ አምስት ቀን በኋላ እስኪመለሱ ድረስ ስለአባታቸው ምንም ወሬ አላገኙም። አባታቸውን ወስደው ያሠሩበት ቦታ በፈጠገር አውራጃ በአዳል ድንበር በሚገኝ መካከሉ ጎድጓዳ በሆነ አንድ መግቢያ ብቻ ባለው ባንድ አምባ ላይ ነበር። ይህ አምባ ብዙ የቀንድ ከብቶች አሉበት ይባላል። በዚያ ቦታ አዲስ የሚገባ ሰው ትኩሳት ይዞት ከአራት ወይም ከአምስት ቀን የበለጠ ሳይቆይ ይሞታል ይባላል። ከዚህም በላይ እስኪሞት ድረስ ከሚጠብቁት ከእስላሞች በስተቀር የሚያገለግለው ማንም ሰው ሳይኖረው ብቻውን ነበር ጥለውት የመጡት ይባላል። ይህ ዝርዝር ወሬ በተሰማ ጊዜ ከበፊቱ የበለጠ ልቅሶው መሪር ሆነ። ሰውዬው በንደዚህ ያለ አኳኋን እንዲሞት

የተደረገበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱን እናት ስላባለገ ነው የሚል ወሬ በቤተ መንግሥቱ ይሰማ ጀመር። ይህ ወሬ እቴጌይቱ በሕይወትዋ እንዳለች ተሰምቶ ነበር። እንዲያውም ከዚሁ ሰው አንድ ልጅ ደቅላ ነበር። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ እናቱ በበለጠ እንዳትዋረድ በማለት በሕይወትዋ በነበረችበት ጊዜ ይህን ሰው ሊያስገድለው አልፈቀደም ነበር ይባላል። ወሬው አየተራባ መሄዱ እንደተሰማ ስለቢትወደዱ አንዳች ነገር የሚያወራ ሰው ይሙት በቃ ይፈረድበታል የሚል አዋጅ ታወጀ። ከዚህ በኋላ ይነዛ የነበረው ወሬ ጠፋ። ከሶስት ወር በኋላ በባሕሩ አጠገብ በትግሬ መኮንኑ ግዛት በነበርንበት ጊዜ የቢትወድዱ ልጆች በአዳል ንጉሥ እርዳታ አባታቸውን ነፃ አውጥተውት ከርሱው ጋር ሆነው ንጉሠ ነገሥቱን መዋጋት ጀምረዋል የሚል ወሬ ሰማን። ቢትወደዱን የጠበቁት ሃያ እስላሞችና ሄደው ያነጋገሩት ሁለት የራሱ አሽከሮች አንገታቸውን በጎራዴ እንዲቀሉ ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ የሚል አዲስ ወሬ መሰማት ጀመረ። እስላሞቹ የተፈረደባቸው አንዱ ምክንያት አሽከሮቹ ከቢትወደዱ እንዲገናኙ በማድረጋቸው ነበር። ይህም እውነት መሆኑን ሰማን። ከዚህም በላይ ምንም እንኳን ቢትወደዱ በንደዚህ ያለ አደገኛ ቦታ ቢጣልም እግዚአብሔር ዕድሜውን ስላስረዘመለት ንጉሠ ነገሥቱ ምሕረት ሊያደርግለት ፈቀደ፤ በተለይ ይህን ማድረጉ እስረኛው ብልህና ብርቱ ጦረኛ በመሆኑ እንዲርቀው የማይወድ መሆኑ ይወራ ነበር።

ምዕራፍ መቶ ሃያ፤ የትግሬ መኮንኑ ሞት፤ ሌላው ቢትወደድና አብዲናጎ ከግዛታቸው ስለመሻራቸው፤ ለአምባሳደር ፀጋ ዘአብ ስለመ በየኑ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ራሱ ወደ ሐዲያ አውራጃ ስለመሄዱ።

የጥምቀትን በዓል በምናከብርበት ቦታ እንደደረስን ይህ ቢትወደድ በየት እንደነበረ ከመገለጹ በፊት በማግሥቱ ማታ ትግሬ መኮንኑ እንዲወሰድ ንጉሠ ነገሥቱ አዘዘ። ወዴት እንደወሰዱትም አል ታወቀም። በማግሥቱ ጀምረው ሶስት ቀን ሙሉ በድንኳኑ ውስጥ

የነበረውን ሃብት ማለት ልዩ ልዩ የሐር ጨርቅ፤ ብዙ የሱፍና ከሕንድ የመጣ ጨርቅ እየቆጠሩና እየተረካከቡ ይጓዙ ነበር። በዚህ ቦታ ለምንገኝ ስድስት ኤውሮፓውያን ማለት ለኔና ላንድ ሌላ ፖርቱጊዝ እንዲሁም ለአራት ጄኖቫውያን ሶስት የሱፍ ጨርቅና ሶስት የሕንድ ጨርቆች እንዲሰጡን ታዘዘልን። ትግሬ መኮንኑ በዳሞት አውራጃ በሚገኝ ሰው በማይኖርበት ብርዳም በሆነ ባንድ አምባ ላይ ታሥሮ በቶሎ እንዲሞት ንጉሠ ነገሥቱ አዘዋል የሚል ወሬ ከጥቂት ወራት በኋላ መሰማት ጀመረ። በትግሬ መኮንኑ ግዛት በነበርን ጊዜ ቢትወደዱ ከታሠረበት አምባ አምልጦ ወጥቶዋል የሚል ወሬ ሃሰት መሆኑን ተረዳን፤ ትግሬ መኮንኑም በዚያ አምባ ላይ እንደነበረ በረሃብና በብርድ ሞተ የሚል ወሬ ከሚታመን ምንጭ ሰማን።

በቤተ መንግሥቱ በነበርንበት ጊዜ ታሥሮ የነበረው ቢትወደድ ከማዕርጉ ተሽሮ በርሱ ቦታ በፊት ባሕር ነጋሽ የነበረው ራስ ነቢያት ተተካበት። ሰላሳ ማለፊያ ፈረሶች ይዞ መጣ ላልሁት ለባለጋዳ ሮቤል የትግሬ መኮንንነቱን ማዕርግ ሰጡት።

እቴጌ ዕሌኒ ከሞተች ጀምሮ እስካሁን ድረስ ትልልቆችና ትንንሾች ሁሉ አለቁ። እርስዋ በሕይወታ በነበረችበት ጊዜ ሁሉም ተከብረውና ተጠብቀው ይኖሩ ነበር እየተባለ የርስዋ ሞት በቤተ መንግሥቱ ይታወስ ነበር፤ እርስዋ የሁሉም እናትና አባት ነበረች፤ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ተግባር ከቀጠለ አገሩ ባዶውን ነው የሚቀረው። በቤተ መንግሥቱ ሲፈጸም የነበረውን ታላላቅ ነገር በማየት ልመና ችንን ለመቀጠል ሳንደፍር ዝም ብለን በምንገኝበት ጊዜ ከጥምቀቱ በዓል በኋላ አባ ፀጋ ዘአብና እኔን አስጠርቶን አብዲናጎ ይዞት የነበረውን መሬት ነጥቆ ከገዥነቱ ማዕርግ ጭምር ለአምባሰደር ፀጋ ዘአብ ሰጥቶት በደስታ አሰናበተን።

ከዚያ ቦታ ከመሄዳችን በፊት የሐዲያ ባላባትን ለመርዳት ከእስ ላሚቱ ወይዘሮ ጋር ሄዶ የነበረው ሕዱግ ራሱ ዘንድ መልእክተኛ መጥቶ ሕዝቡ የማይታዘዘውና ወደነርሱም በሄደ ቁጥር እየሸሹ በየተራሮቹ የሚጠጉ መሆናቸውን በማስታወቅ ንጉሠ ነገሥቱ በተጨማሪ ሰው

እንዲልክለት መለመኑን ገለጸ። ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ወሬ እንደሰማ ባለቤቱን እቴጌይቱንና አጀቡን በሐድያ አውራጃ ድንበር በሚገኝ ከዚህ በፊት አብረነው በሄድንበት ውርበረግ በተባለ ቦታ ትቶ እርሱ ራሱ ከቦታው ድረስ ለመሄድ ቆረጠ። ከርሱ ጋር አንዳንድ ፖርቱጊዞች ማለት ጊዮርጊስ ዲ አብሬው፤ ዲዮጉ ፍርናንድሽ፤ አፎንሱ ሜንድሽና አልቫሬንጋ እንዲሁም አምስት ወይም ስድስት ጄኖቫውያን ሄዱ። እነዚህ ሰዎች በነገሩን መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ በሐዲያ አውራጃ መድረሱን በማወቅ ሕዝቡ ለጥ ብሎ ተገዛ፤ ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከመቃዲሾ በጣም ቀርቦ በሚገኝ ቦታ ድረስ ዘለቀ። ይህ አውራጃ በጣም ለምለምና ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሸፈነ ከመሆኑ የተነሣ ዛፎቹን እየጣልን መንገድ እያወጣን ነበር ለማለፍ የቻልነው አሉኝ። ከዚህም በላይ ብዙ ምግብ ብዙ የቀንድ ከብቶችና ልዩ ልዩ ዓይነት የዱር አራዊት የሚገኙበት መሆናቸውን ጨምረው ገለጹልን። በአውራጃው ባሕር የሚመስል ከዳር እስከ ዳር ሊታይ የማይቻል በውስጡ አንድ ደሴት ያለበት አንድ ትልቅ ሐይቅ አለ አሉ። ምንም እንኳ ይህ አገር አካባቢው የእስላሞች አገር ቢሆንም በጥንት ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥቱ በደሴቱ ላይ አንድ ገዳም አሠርቶ መነኩሴዎች አኑሮበት ነበር ይባላል። ይህን የነገረን ጴጥሮስ ድኩቪሊያን ነበር። አሁን ግን ቦታውን ጎብኝተው የተመለሱት ፖርቱጊዞችና ጄኖቫ ውያን በነገሩን መሠረት በገዳሙ ከነበሩት መነኩሴዎች ጥቂት ብቻ ሲተርፉ ሌሎቹን የትኩሳት በሽታ ፈጃቸው፤ የተረፉት ግን የሚገኙት ከሐይቁ አጠገብ በሚገኝ ባንድ ሌላ ገዳም ሲሆን ሄደው ያዩዋቸው መሆናቸውን ጨምረው አስረዱን። ንጉሠ ነገሥቱ ያንን አውራጃ በጎበኘበት ጊዜ ብዙ ገዳሞችና ቤተ ክርስቲያኖች እንዲሠሩ አዞ ብዙ መነኩሴዎችንና ቄሶችን ተራ ሰዎችም በአውራጃው ትቶ ሄደ። አውራጃው ሰላም ከሆነ በኋላ አጀቡን ትቶ ወደመጣበት ቦታ ተመለሰ። የዚህ አውራጃ ሕዝብ ቀረጥ የሚከፍለው በከብት ነው ይባላል፤ ከዚያ የመጡ ትልልቅ ፈረሶችን የሚያህሉ ንጣታቸውም በረዶ የመሰለ ጆሮዋቸው የሚንጠለጠል ብዙ ጎዳ ላሞች በቤተ መንግሥቱ አይተናል።

ምዕራፍ መቶ ሃያ አንድ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ከነአጀቡ በንዴት ያለ አኳኋን ከትሞ እንደሚያርፍ።

ለሁሉም ቦታ እንዲገኝ በማለት ከተማው ሁሉ ጊዜ የሚ ከተመው በሜዳ ላይ ሲሆን ከፍ ያለ ቦታ የተገኘ እንደሆነ ንጉሣዊው ድንኳን የሚተከለው በዚያ ላይ ነው። የድንኳኖቹ በር ሁልጊዜ ወደ ምዕራብ በኩል ነው። ለንጉሠ ነገሥቱ አራት ወይም አምስት ድንኳኖች ባንድነት ይተከሉና እነዚሁ ድንኳኖች በሙሉ የሰንጠረዥ መጫወቻ ገበታ ይመስል በአራት መዓዘን መልክ በተሸለሙ ጥቁርና ነጭ በሆኑ «መንዲላት» በሚሉዋቸው መጋረጃዎች ይጋርዱዋቸዋል። ባንድ ቦታ ብዙ ጊዜ የሚቆይ ከሆነ ግን ድንኳኖቹን ግማሽ ሌግዋ ርዝመት ባለው አጥር ያጥሩዋቸዋል። ይህ ጆጎል አስራ ሁለት በሮች አሉት ይባላል። ዋናው በር በስተምዕራብ በኩል ያለው ሲሆን ከዚሁ በስተኋላ ጥቂት ራቅ ብለው በየበኩሉ ሁለት በሮች አሉ፤ ከነዚህ አንደኛው በስተሰሜን በኩል ወደሚገኘው ወደ ቅድስት መስቀል ቤተ ክርስቲያን ይመራል። ወደ ቤተ ክርስቲያኖቹ ከሚወስዱት ሁለቱ በሮች በስተኋላ ከዋናው በር እስከነዚህ በሮች ድረስ ያለውን ርቀት ያህል እልፍ ብለው በያንዳንዱ በኩል የሚገኙ ሁለት በሮች አሉ፤ ከነዚሁ በስተደቡብ በኩል የሚገኘው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ባለቤት ወደ እቴጌይቱ ድንኳን ሲመራ በስተሰሜን በኩል ያለው ደግሞ ወደብላቴናዎቹ ድንኳን ይመራል። በያንዳንዱ በር ዘበኞች ይቆማሉ። እነዚህ ዘበኞች ማንንም ስለማያስገቡ ወደ ግቢው ዘልቄ አላውቅም፤ በጠቅላላው አስራ ሁለት በሮች አሉ ይባላል፤ እኔ አጣርቼ የማውቀው ወደ ማዕድ ቤቱ የሚወስደውን ብላቴኖቹ የሚመላለሱበትን በር ነው፤ ይህን ላውቀው የቻልሁት አሽከሮቹ ምግብ ይዘው ሲገቡና ሲወጡ ከሩቅ ሆኜ በመመልከት ነበር። በሮቹ የሚሠሩት ንጉሣዊው ድንኳን በጆጎሉ ውስጥ የተተከለ እንደሆነ ብቻ ነው፤ ይህ ካልሆነ ግን በፊት እንደተገለጸው ከድንኳኖቹ ያንድ ወስፈንጥር ርቀት ያህል ወይም ርቆ በሚገኝ ቦታ ለማዕድ ቤትና ለወጥ ቤትም ድንኳኖች ተተክለዋል። የቀኝና የግራ ወጥቤቶች ስላሉ ድንኳኖቹ የሚተከሉት በሁለት ቦታ ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ከነአጀቡ

ከትሞ የሚያርፈው ለጥ ያለ ሜዳ ላይ በመሆኑ በንጉሣዊ ቤተ ሰብ ድንኳን ውስጥ ያለውን ልዩ ልዩ ሥነ ሥርዐት በደንብ ለማየት ስለማይቻል ውርበረግ በተባለ ቦታ በነበርን ጊዜ ካንድ ኮረብታ ላይ ሆኜ ቁልቁል በመመልከት ቀጥሎ በተመለከተው ዓይነት ምግብ ከማዕድ ቤቱ ሲወጣ አይቻለሁ። ተገጣጥመው የታሰሩ ስድስት ቁርጥራጭ ቀይና ሰማያዊ ጨርቆች አጎበር ይዘው መጡ። አጎበሩ በጥሩ ዓይነት ቀርከሃ ላይ ተወጥሮ ነበር። በትልልቅ ገበታ ላይ ጥሩ ዓይነት ምግቦች ማለት የዶሮ ወጥ አይብና እርጎ የያዙ ከጥቁር ሸክላ የተሠሩ ወጭቶች አኑረው ብላቴናዎቹ ይሄዱ ነበር። ልዩ ልዩ ዓይነት ወጥ የያዙ ድስቶችም ይዘው ይሄዱ ነበር። የነበርሁበት ቦታ ራቅ ያለ ስለነበር በገበታው ላይ አኑረዋቸው የነበሩትን ወጭቶች ለማተት ስላልተቻለ ለኛ ምግብ ሲያመጡልን አጎበሩ ብቻ ሲቀር ልክ በዚሁ ዓይነት ስነ ሥርዐት ስለሆነ የኛን በማየት ነው ይህን ሃተታ ለመስጠት መቻሌ። ድስቶቹም የሚመጡት በመክላሊታቸው ተገጥመው ዙርያ ቸውን በሊጥ ተመርገው ነው። የሚልኩልንም ገበታ የነቀነቁት መሆኑ ሳይታወቅ ጢም እንዳለ ነበር የሚደርስን።

በወጡም ውስጥ ዝንጅብልና በርበሬ ስለሚሞጅሩበት እንደ እሳት የሚያቃጥል በመሆኑ ልንበላው አንችልም ነበር። በማዕድ ቤቱና በወጥ ቤቱ ድንኳኖች መካከል በስኋላ በኩል የቅዱስ እንድ ርያስ ቤተ ክርስቲያን አለ፤ ይህን የወጥ ቤቶች ቤት ክርስቲያን ይሉታል። ማዕድ ቤቶቹ ባሉበት ቦታ ወይም በስተኋላ ማንም እንዲሄድ አይፈቀድለትም።

ምዕራፍ መቶ ሃያ ሁለት፤ የዳኞች ድንኳንና አሠራሩም፤ ባለጉዳዮችን እንዴት እንደሚሰሙ።

ከንጉሣዊው ድንኳን ወይም ከአጥሩ ፊት ለፊት የሁለት ቀስት ውርወራ ርቆ በሚገኝ ቦታ ላይ የሚተከል አንድ ሰቀላ አለ። ይህ ሰቀላ የፍርድ ቤቱ ነው። ለንጉሡ ነገሥቱና ለፍርድ ቤቱ ያላቸውን

ክብር ለመግለጽ ሲሉ ፈረሰኞችም ሆነ በቅሎኞች በንጉሣዊው ድንኳንና በፍርድ ቤቱ መካከል ባለው ቦታ ሲደርሱ ወርደው በእግ ራቸው ይሄዳሉ። ይህን ልምድ ላውቀው የቻልሁት ከበቅሎቻችን ሳንወርድ በዚያ ቦታ ስለገባን የውጭ አገር ሰዎች በመሆናችን አልፈውን ለወደፊቱ ግን ያን የመሰለ ተግባር እንዳንፈጽም ቃል ስላስገቡን ነው። በሰቀላው ውስጥ ማንም እንዲገባ አይፈቀድለትም። ከብረትና ከቆዳ የተሠሩ አስራ ሶስት ወንበሮች አሉ፤ ከነዚህ አንደኛው አንድ ሰው ደረት ድረስ ከፍ ያለ ሲሆን አስራ ሁለቱ ግን እኛ በጠረጴዛ አጠገብ የምናስቀምጣቸውን ተራ ወንበሮች ይመስላሉ። ወንበሮቹን በየቀኑ ወደ ውጭ እያወጡ ስድስቱን ባንድ በኩል ሌሎቹን ስድስቱን ደግሞ በሌላ በኩል አኑረው ትልቁን ወንበር ደግሞ በስተኋላ በኩል ያስቀምጡታል። እነዚህ ወንበሮች በዚያ የሚቀመጡበት ለስነ ሥርዓት ያህል ብቻ እንጂ ለመቀመጫ ስላልሆነ ዳኞቹ በምድሩ ላይ ተቀምጠው እያንዳንዳቸው በየሥልጣናቸው ያሙዋግታሉ። በየሥልጣናቸው ያልሁበት ምክንያት ወጥ ቤቶቹ በቀኝና በግራ ስለተከፈሉ ነው። የፍርድ ስነ ሥርዓት የሚከናወነው ቀጥሎ በተመለከተው ስነ ሥርዐት ነው።

ከሳሽ ጉዳዩን በማቅረብ የተቻለውን ያህል ይናገራል፤ ተከሳሽም እንዲሁ ያደርጋል። ተከሳሽ ተናግሮ ካበቃ በኋላ ከሳሽ (ከፈቀደ) መልስ ይሰጣል፤ ተከሳሽም ከፈቀደ ማንም ሳያቋርጠው መልስ ይሰጣል። ከሳሽና ተከሳሽ በራሳቸው ወይም በፈጃቸው አማካይነት ሙግታቸውን ካበቁ በኋላ በዚያ ቁሞ የሚገኝ አንድ ቃል አቀባይ ባለጉዳዮቹ የተናገሩትን ሁሉ እንደገና በዝርዝር ካሰማ በኋላ በርሱ አስተያየት በሚገባ የተናገረውና ፍርድም የሚደግፈው የትኛውን ክፍል መሆኑን ይገልጻል። ከዚህ በኋላ ከተቀመጡት አንዱ ማለት ከመጨረሻው ቀጥሎ የተቀመጠው ቃል አቀባይ እንዳደረገው ሁሉ ከሳሽና ተከሳሽ የተናገሩትን ቃል እንደገና ካሰማ በኋላ በርሱ አስተያየት በሚገባ የተናገረውና ፍርድም የሚደግፈው የትኛውን ክፍል መሆኑን ይገልጻል። አብረውት የተቀመጡት ወንበሮች ሁሉ አንድ በአንድ እንዲሁ ያደርጋሉ። ወንበሮቹ በሚናገሩበት ጊዜ ቆመው ነው፤ ይህ ሁሉ በሚፈጸምበት ጊዜ የያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ ያዳምጥ የነበረው አፈ ንጉሡ ምስክሮቹን ሳይጠይቅ ፍርድ ይሰጣል። ነገር

ግን ማስረጃ እንዲኖር አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የባለጉዳዮቹን አገር ርቀት በማመዛዘን ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። ይህ ሁሉ የሚከናወነው በቃል ብቻ እንጂ በጽሑፍ የሚሠፍር አንድም ነገር የለም። ከዚህም ሌላ ቢትወደዱና አዛዡ የሚገኙበት የንጉሠ ነገሥቱ ችሎት አለ። ሁለቱ ሰዎች የሚያስችሉት በሰቀላውና በንጉሣዊው ድንኳን መካከል በሚገኘው ቦታ ቁመው ሲሆን ባለጉዳዮች የሚያቀርቡትን ሃተታ ይሰሙና ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሄደው ይነግሩታል። በንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ውስጥ ሳይገቡ ከመንዲላቱ ግቢ ሆነው የባለ ጉዳዮቹን ቃል ያቀርቡለትና ውሳኔውን ተቀብለው ወደ ባለ ጉዳዮቹ ይመለሳሉ። አንዳንድ ጊዜ እንደጉዳዩ መጠን በመመላለስ አንድ ቀን በሙሉ ይፈጃሉ።

ምዕራፍ መቶ ሃያ ሶስት፤ የእሥር ቤቶች ሁኔታ።

ከፍርድ ቤቱ ድንኳን ፊት ለፊት በጣም እልፍ ብሎ በግራና በቀኝ በኩል የያንዳንዱ ክፍል እስረኞች የሚታሠሩበት «የመንግሥት ቤት» የሚባሉ ድንኳኖች አሉ። እስረኞቹ ቀጥሎ በተመለከተው ዓይነት ይጠበቃሉ። ጠባቂዎቹና እስራቱም እንደክሱ አኳኋን ነው። እስረኛው ከእስር ቤት እስካለ ድረስ ጠባቂዎቹን የሚቀልብና የሚከፍላቸውም እርሱ ራሱ ነው። በሰንሰለት ወይም በእግር ብረት የታሠረው እስረኛ ጉዳዩን ያመለክት ዘንድ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንዲቀርብ በታዘዘ ጊዜ ታቅፈው የሚወስዱት ጠባቂዎቹ ናቸው። ሁለቱ ጠባቂዎች እጅ ለእጅ ይያያዙና እስረኛው በክንዳቸው ላይ ተቀምጦ እጆቹን በጭንቅላቱ ላይ አኑሮ ሲሄድ ሌሎች ጠባቂዎች መሣርያ ይዘው ከበውት ይሄዳሉ። እስረኞቹን ወዲያ ወዲህ የሚያመላልሱት በዚህ አኳኋን ነው።

ከዚህም በላይ እስረኞች የሚታሠሩበት ሌላ ዓይነት መንገድ አለ፤ ይኸውም ከሳሽ ባለጋራው እንዲታሠርለት የጠየቀ እንደሆነ የእስረኛውንና የጠባቂዎቹንም ቀለብ እንዲችል የሚያዘው ደንብ

ነው። ይህን ላውቅ የቻልሁት እኛ ፖርቱጊዞች በቅሎች ስለተሠረቁበን ሰዎች አሳስረን ስለነበርን ነው። እስረኞቹን መቀለቡ ከፍ ያለ ወጭ የሚጠይቅ ነገር ስለነበር እንዲፈቱላቸው ፖርቱጊዞቹ ራሳቸው ጠየቁ። እንዲሁም እኔ የማውቀው አንድ ጀኖቫዊ በቅሎ ተሠርቆበት ስለነበር ጉዳዩን አቅርቦ ሌባውም መስረቁን አመነ። ነገር ግን በቅሎው ከርሱ ጋር የማይገኝ ስለመሆኑና የሚከፍለውም ገንዘብ የሌለው መሆኑን አስታወቀ፤ ስለዚህ ይህ ሌባ ለጀኖቫዊው አሽከር እንዲሆን ተፈርዶበት ነበር። ነገር ግን ሰውዬው ኃይለኛ ስለነበር ይዘርፈኛል ወይም ይገድለኛል በማለት ጀኖቫዊው ሌባውን አሰናብቶት በቅሎውም እንደጠፋ ቀረ።

ምዕራፍ መቶ ሃያ አራት፤ የአፈ ንጉሦቹ መኖርያ የሚገኝበት፤ ስለገበያውና በውስጡም ስላሉ ነጋዴዎችና ቸርቻሪዎች።

በእሥር ቤቶቹ ድንኳኖች ፊት ለፊት ብዙ ንግድ ይከናወናል፤ የአፈ ንጉሦቹ ድንኳኖች እያንዳንዳቸው በየበኩላቸው ቀጥታ መስመር ይዘው ነው የተተከሉት፤ የሁለቱ ድንኳኖች አቋራጭ በሆነው መካከለኛ ቦታ ላይ የዳኞች ቤተ ክርስቲያን የተባለ አንድ ቤተ ክርስቲያን አለ። ከዚህ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በጣም እልፍ ብሎ በሚገኝ ቦታ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ በሄደበት ቦታ ሁሉ የማይለዩ አራት አንበሶች ነበሩ። ከአንበሶቹ በጣም እልፍ ሲሉ አንድ ሌላ ቤተ ክርስቲያን አለ። በገበያው ውስጥ የሚገኙት ሰዎች ይበልጡ እስላሞች ስለሆኑ የገበያው ቤተ ክርስቲያን የተሠራው ለክርስቲያኖቹ ብቻ ነው። ውድ ሸቀጦችና ልብሶች የሚሸጡት እስላሞች ሲሆኑ ክርስቲያኖች ግን እንጀራ፤ ጠጅ፤ ዱቄትና ሥጋ የመሳሰሉትንም ርካሽ ነገሮች ይሸጣሉ። የዚህ አገር ክርስቲያኖች እስላሞች ያዘጋጁትን ምግብ ስለማይበሉና እነርሱም ያረዱትን ከብት ሥጋ ስለማይቀምሱ እስላሞች ምግብ ሊሸጡ አይችሉም። ገበያው ምንም እንኳን ከንጉሣዊው ድንኳን ሆኖ የማይታይ ቢሆንም የሚገኝበት ቦታ ከድንኳኑ ፊት

ለፊት ነው። ከተማው የሚከተምበት ቦታ ኮረብታና ጉብታ የሌለው ሰፊ ሜዳ ከሆነ ገበያው የሚውልበት ቦታ ከድንኳኑ እጅግ ቢያንስ ግማሽ ሴግዋ አንዳንድ ጊዜም አንድ ሴግዋ ያህል ወይም ከዚህ ርቆ ነው የሚገኝ። ምንም እንኳ ንጉሠ ነገሥቱ ቦታውን በየጊዜው ቢለውጥም ከተማው ቀጥሎ የተመለከተውን ቅያስ መከተል አለበት። በንጉሣዊው ድንኳንና በገበያው መካከል ባለው ቦታ ላይ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች ማለት የዳኞቹና የገበያው እንዲሁም አንበሶቹ እንጂ ሌላ ምንም የለም። እነዚህ ቤተ ክርስቲያኖችና አንበሶቹ የሚገኙበት ቦታ ከሌሎቹ ድንኳኖች በጣም የራቀ ነው።

ምዕራፍ መቶ ሃያ አምስት፤ አገረ ገዥዎችና መኳንንት ሌሎች ሰዎችም በተገለጸው አኳኋን ድንኳናቸውን እንዴት እንደሚተክሉ።

ከንጉሣዊው ድንኳን አጠገብ በውጭ በኩል ለያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ድንኳኖች ተተክለዋል። ከድንኳኖቹ በጣም ሻል ያለውና ንፁሁ የቤተ ክርስቲያኑን አልባሳት የሚያኖሩበት ሲሆን ሌላው በጭስ የጠቆረው ቁርባኑን የሚያዘጋጁበት ነው። እንደዚህ ያሉ ድንኳኖች በየቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ይገኛሉ። ከነዚህ ቤተ ክርስቲያኖች ፊት ለፊት የሚገኙ የንጉሠ ነገሥቱ ልብስና ሃብት የሚቀመጥባቸው በሁለቱም በኩል በወርቀዘቦ ያጌጡ ጣራቸው ከፍ ያለ ሌሎች ድንኳኖች አሉ። እነዚህን ግምጃ ቤቶች የሚጠብቁ ሁልጊዜ ጀንደረባዎች ናቸው። ከግምጃ ቤቱ ድንኳኖች ፊት ለፊት በግራና በቀኝ በኩል የብላቴናዎቹ ድንኳኖች ይገኛሉ። ከነዚህም ወደፊት በጣም እልፍ ብሎ የራሳቸውና የጭፍሮቻቸው ድንኳኖች የተተከሉባቸው ራሱን የቻለ አንድ ከተማ የሚመስል የአዛዦቹ መኖ ርያ አለ። ከዚህም በጣም ወደፊት እልፍ ሲሉ እንዲሁ እያንዳንዳቸው ከተማ የሚመስሉ የቢትወደዶቹ መኖርያዎች አሉ። እነዚህ ድንኳኖች የጠባቂዎች መኖርያ ይመስል በጣም ከከተማው ውጭ ነው የሚገኙት። እንደጠባቂዎቹ መኖርያዎች ከከተማው ውጭ በስተቀኝ በኩል የሚገኝ

ራሱን የቻለ አንድ ቀበሌ የሚመስል የአቡኑ መኖርያ አለ። የውጭ አገር ሰዎች ከአቡኑ እርዳታና ጥበቃ ስለሚያገኙ ብዙዎቹ ወደር ሳቸው ሠፈር ይሄዳሉ። የአቃቤ ሰዓቱቹ ድንኳን ከአቡኑ ይልቅ ለከተማው ይቀርባል። አቃቤ ሰዓትነቱ የሚሰጠው ሁል ጊዜ ለመንኩሴ ስለነበር ይህ ባለሥልጣን ተግባሩን በሚያከናውንበት ቤት የሚገኘው ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቀጥሎ ነበር፤ ነገር ግን ያሁኑ አቃቤ ሰዓት ቄስ በመሆኑ ሚስት ስለነበረው በዚያ ቦታ ለመሆን ስላልተፈቀደለት ከአቡኑ ሠፈር አጠገብ ቦታ ተሰጠው። ከውስጥ ወደውጭ ባለው ተራ በመጀመርያ ያለው የመኳንንቱ ድንኳን፤ ከመኳ ንንቱ ከጥሎ ሌሎች የተከበሩ ሰዎች አሉ፤ ከነዚህም የሚቀጥሉት ጠጅ ሻጮችና እንጀራ ጋጋሪዎች ናቸው፤ ከነርሱም ጋር ሴቶች ይገኛሉ። በዚህ ተራ መጨረሻ ማለት በገበያው አቅራቢያ በየበ ኩላቸው የሚገኙ ባለጆች ትልቅ መንደር ሠርተው ይሠፍራሉ። ከውጭ ለንግድ የሚመጡት ሰዎች ብዙ ጊዜ ሁለት ሴግዋ ርዝመት ባለው ቦታ ላይ ሠርተው ይሠፍራሉ።

ምዕራፍ መቶ ሃያ ስድስት፤ የአገረ ገዥዎችና መኳንንት ወደ ቤተ መንግሥቱ አመጣጥ፤ በቤተ መንግሥቱም መዘዋወርና ከዚያም መሄድ።

አገረ ገዥዎችና መኳንንት ወደ ቤተ መንግሥቱ የሚመጡትና የሚሄዱት ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው፤ በግዛቱ ላይ የሚገኝ አንድ አገረ ገዥ በንጉሠ ነገሥቱ ካልተጠራ በስተቀር ግዛቱን ትቶ ለመሄድ አይችልም። የተጠራ እንደሆነ ግን በምንም ዓይነት ምክንያት ሊቀር አይችልም። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ንጉሠ ነገሥቱ የሚሾመውና የሚሽረው እንዳሰኘው ስለሆነ አንድ አገረ ገዥ ከግዛቱ የመጣ እንደሆነ ሁለተኛ እንደማይመለስ በመገመት ሚስቱንና ልጆቹን ጓዙንም አስከትሎ ነው የሚመጣው። አንድ ገዥ ተሽሮ በግዛቱ እንዳለ ምትኩ የመጣ እንደሆነ የቀድሞውን ገዥ ማና ቸውንም ንብረት ይወስድበታል። ስለዚህ ይህን በመፍራት ገዦዎቹ ሃብታቸውን በሙሉ ይዘው ይሄዳሉ ወይም ወደሌላ ግዛት ያሸሻሉ።

አንድ አገረ ገዥ ወደ ቤተ መንግሥቱ በመጣ ጊዜ በታላቅ አጀብ ይመጣናት እጅግ ቢያንስ ከቤተ መንግሥቱ አንድ ሌግዋ ያህል እልፍ ብሎ ያርፍና ከዚያ ቦታ ሳይንቀሳቀስ አንድ ወይም ሁለት ወር ይቆያል። ንጉሠ ነገሥቱ አስታውሶ እስኪጠራቸው ድረስ እንደተረሱ ሰዎች ሆነው ነው የሚቆጠሩ። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በንደዚህ ያለ ሁኔታ ላይ ቢገኙም ይቀርቡ ዘንድ እስኪፈቀድላቸው ድረስ እንደበፊቱ ብዙ አጀብ ሳይኖራቸው ወይም አጊጠው ሳይለብሱ ሁለት ወይም ሶስት አሽከሮች ብቻ አስከትለው ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን ሆነው በትከሻቸው ላይ የበግ ለምድ ደርበው ወደ ቤተ መንግሥቱ እየሄዱ ከሌሎች መኳንንት ጋር ደጅ መጥናታቸውን አያቋርጡም። እንዲቀርቡ በተፈቀደላቸው ጊዜ ብዙ አጀብ አስከትለው ነጋሪት እያስመቱና ጥሩንባ እያስነፉ ይሄዱና ለያንዳንዱ በተወሰነው ቦታ ላይ ይቀመጣሉ። ምንም እንኳ እያንዳንዱ መኮንን በገባ ጊዜ በማዕርግ ለብሶ ቢገባም በተሰጠው ቦታ ባለበት ጊዜ ግን እንደበፊት ከወገቡ በላይ ሆኖ ነው ወዲያ ወዲህ የሚለው። በዚያን ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ «እገሌን ጌታችን ገና ስላላስታወሰው ራቁቱን ይሄዳል» የሚል ወሬ በሰፊው ይነዛል። ከንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ እንደመጣ ወዲያውኑ ገዥው በቶሎ ለብሶ ይመጣል። በዚያን ጊዜ «እገሌን ጌታችን አስታወሰው» የሚል ወሬ ይጀመራል።

ከዚህ በኋላ አገረ ገዥው የተጠራበት ምክንያት ወሬ ይጀመራል። ብዙ ጊዜ ወደ ግዛታቸው ይመለሳሉ፤ አንዳንድ ጊዜም አይመለሱም። የመለሱዋቸው እንደሆነ በቶሎ አሰናብተው ነው የሚልኳቸው፤ የተሻሩ እንደሆነ ግን ከቤተ መንግሥቱ ሳይለዩ ስድስት ወይም ሰባት ዓመት ይቆያሉ። እነዚህ ሰዎች ከልክ ያለፈ ታዛገሮችና ንጉሠ ነገሥቱንም የሚፈሩ በመሆናቸው በምንም ዓይነት ምክንያት ቢሆን ያለ ፈቃድ ከቤተ መንግሥቱ አይወጡም። ከዚህ በፊት ብዙ አጀብ አስከትለው ያልሄዱትን ያህል አሁን ችላ ተብለው ሁለት ወይም ሶስት አሽከሮች ብቻ አስከትለው በበቅሎ ወዲያና ወዲህ ይኳትናሉ። በፊት ያጅቡዋቸው የነበሩት ሰዎች በግዛታቸው ላይ የሚኖሩ ስለነበሩ ከሽረቱ በኋላ ያዲሱ ገዥ ጭፍሮች ይሆናሉ። ይህንንም በየቀኑ እናይ ነበር።

ምዕራፍ መቶ ሃያ ሰባት፤ ከጦርነት የሚመጡትና የሚሄዱት ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንዴት እንደሚቀርቡና የሚሰጣቸውም ስንቅ።

እነዚህ መኳንንት ወደ ቤተ መንግሥቱ የተጠሩበት ምክንያት ወደ ጦርነት ይሄዱ ዘንድ ለመታዘዝ ከሆነ ግን ብዙ ጊዜ እንደ ተመለከትነው ደጅ ሳያስጠኑ በቶሎ ያስገቡዋቸዋል። ብዙ ሰዎች አስከትለው እንደመጡ ይገባሉ። ከዚህ በፊት በስጠሁት ሃተታ መሠረት በበቅሎ ወይም በፈረስ የተቀመጠ ሰው በንጉሣዊው ድንኳንና በሰቀላው መካከል ባለው ቦታ እንደተቀመጠ ማለፍ የለበትም ያልሁት ደንብ እነዚህን ሰዎች አይመለከትም። ለጦርነት የመጡ ሰዎች በፈረሳቸው እንደተቀመጡ በንጉሣዊው ድንኳን አጠገብ ቀርበው ንጉሠ ነገሥቱን ለማስደሰት የተሻለ መስሎ በታያቸው አኳኋን ጉግስና ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት ስፖርት በመጫወት የጦርነቱን ስልት ያሳያሉ። ይህን ትርኢት ያየነው ብዙ ጊዜ ነበር።

ለጦርነት ዝግጅት ሲደረግ ካስፈለገ በሁለት ቀን ውስጥ አንድ መቶ ሺ ሰዎች እንዲሰበሰቡ ሲታዘዝ ሰዎቹ ወዲያውኑ እንደመጡ ስለሚላኩ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ከሁለት ቀን በላይ አይቆዩም። ወታደሮቹ ወደ ቤተ መንግሥቱ በመጡ ጊዜ ስንቃቸውን ይዘው ነው የሚመጡት። ለስንቃቸው የሚይዙት በሶና የሽንብራ የማሽላም ቆሎ ነው። በጦርነቱ ጊዜ የሚያገኙዋቸውን ከብቶችም እያረዱ ይበላሉ። የበልግ ስንዴም በተገኘ ጊዜ ወታደሮቹ ይህንኑ እንዲበሉ ተፈቅዶላቸዋል።

ምዕራፍ መቶ ሃያ ስምንት፤ የንጉሠ ነገሥቱን ጓዝ እንዴት እንደ ሚያጓጉዙ፤ ወደየሩሳሌም ስለተላከው ለምድና ወርቀዘቦ።

እኛ እንዳየነው ንጉሠ ነገሥቱ በንዴት ያለ አኳኋን ከቦታ ወደ ቦታ እንደሚዘዋወር ከዚህ በፊት የተገለጸ ሲሆን አሁን ደግሞ በግምጃ ቤቱ የሚገኙ ልዩ ልዩ ዕቃዎች በንዴት ያለ አኳኋን እንደ

ሚጓዙ ይገለጻል። ግምጃዎቹ በሙሉ ርዝመቱ አራት ስንዝር ስፋቱም ሁለት ወይም ሁለት ተኩል ስንዝር በሆነ አገልግል ይቀመጣሉ። አገልግሎቹ ባልተፋቀ ቆዳ ተለጉመዋል። በአገልግሎቹ ማዕዘኖች ላይ የታሠሩትን ሰንሰለቶች በክዳኖቹ ላይ ባሉት ቀለበት የሚመስሉ ነገሮች ውስጥ አሳልፈው ይቆልፉዋቸዋል። ከዚህ በኋላ አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ሰዎች ተሸክመዋቸው ይሄዳሉ። በመካከላቸው የነበሩት ጠባቂዎችም ቁጥር ይህንኑ ያህል ነበር። ለንጉሠ ነገሥቱ በያመቱ በግብር ስም የሚገባለትና እርሱም በየጊዜው የሚገዛው ግምጃና ወርቀዘቦ ልብስ ብዛት እየበረከተ በመሄዱና ብዙዎቹንም ስለማይጠቀምባቸው እየተሸከሙ ከመሄድ ፈንታ ለዚሁ አገልግሎት በታቀደ ዋሻ ውስጥ በያመቱ ያኖሩታል። ከዚህ በፊት በጠቀስኳቸው ታላላቅ ገደሎች በሚገኙበት አጠገብ በነበረው በበደበጅ በሮች አጠገብ ስላለፍን በዚሁ መንገድ አቅራቢያ የሚገኘውን የሃብት ማከማቻ ዋሻ አይተናል። ይህን ዋሸ የሚጠብቁ ብዙ ሰዎች አሉ፤ በዚያ የሚያልፉ ነጋዴዎች ሁሉ ቀረጥ ይከፍላሉ። ልብሱን እንደሚያጓጉዙት ሁሉ ሌላውንም ሃብት በልጉም አገልግል ውስጥ አኑረው ያጓጉዙታል። እነዚህን አገልገሎች ከቆለፉዋቸው በኋላ በርጥብ ቆዳ ስለሚሰፉዋቸው በበለጠ ይጠነክራሉ። እነዚህ ለቁጥር የሚያስቸግሩ ሃብት የሚቀመጥባቸው አገልግሎቶች በብዙ ሰዎች እየተጠበቁ ይጓዛሉ። የሃብቱ ብዛት በየጊዜው እየበረከተ ስለሚሄድ ለሸክም ስለሚያስቸግር ከዚህም ወደ ዋሻዎቹ በያመቱ ብዙ ይላካል ይባላል። ቤቱ ከዋሻው አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ ይገኝ የነበረው ጴጥሮስ ድኩቪሊያን በዚያ የነበረውን ሃብት ብዛት በመግለጽ በያመቱ በዚያ ዋሻ ውስጥ ብዙ ወርቅ ማስቀመጥ እንጂ ምንም ስለማይወስዱ በዚያ የተጠራቀመው ወርቅ ዓለምን ሊገዛ ይችላል ሲል ነገረኝ። ጴጥሮስ ድኩቪሊያን እንደነገረን በዚያ የሚገኘውን የወርቅ ግምጃና ሐር ብዙ ጊዜ እየወሰዱ ለቤተ ክርስቲያንና ለገዳሞች ይሰጡዋቸዋል። ስለዚህ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ሃብት ስላለው እኛ ከመምጣታችን ከሶስት ዓመት በፊት ብዙ ገጸ በረከት ወደየሩሳሌም ልኮ ነበር ማለትን ሰምተናል። በተራራው ሥር ከነበረው እኛ ካየነው ዋሻ እንደዚሁ ሃብት የሚቀመጥባቸው ሌሎች ብዙዎች ዋሻዎች አሉ። ገጸ በረከቱን ወደ የሩሳሌም ወስዶ

ያስረከበው ሰው አሁን የንጉሠ ነገሥቱን እህት የሚጠብቅ አባ አሥራት የሚባል ሰው ነው። ይህን ገጸ በረከት ይዞ በሄደበት ጊዜ አባ አሥራት አስራ አምስት [1] ሰው አስከትሎ ሲሄድ ከነዚሁም ውስጥ ሰላሳ ነጋሪቶች ያስያዙ መኳንንቶች ይገኙባቸው ነበር ይባላል። ከነርሱ ጋር ሄደው የነበሩት ሰዎች ሲያወሩ እንደሰማሁት የሩሳሌም እስኪደርሱ ድረስ በጉዞአቸው ላይና በካይሮም ላይ ነጋሪት ያስመቱ ነበር ይባላል። በተመለሱ ጊዜ ግን ቱርኮች በግብጽ ሡልጣን ላይ ለመዝመትና ካይሮንም ለመውረር በመምጣት ላይ ስለነበሩ፤ በሽሽት ነበር ወዳገራቸው የተመለሱ።

ምዕራፍ መቶ ሃያ ዘጠኝ፤ ከባርዋ ወደ የሩሳሌም ለስግደት ይሄዱ የነበሩ ሶስት መቶ መነኩሴዎች በመንገድ ስለመፈጀታቸው።

ከዚህ አገር በያመቱ ብዙ መነኩሴዎችና አንዳንድ ቄሶችም ለስግደት ወደ የሩሳሌም ይሄዳሉ። እኛ ፖርቱጊዞችና ሌሎችም ፈረንጆች በባሕር ነጋሹ መናገሻ ከተማ በባርዋ በነበርንበት ጊዜ መነኩሴዎቹ የተለመደውን የስግደት ጉዞአቸውን ለመጀመር በመዘጋጀት ላይ ነበሩ። ወደ የሩሳሌም ለመሄድ የተነሱት መነኩሴዎች ቁጥር ሶስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሲሆን በነርሱም ውስጥ አስራ አምስት መነኩሲቶች ይገኙባቸው ነበር። ጉዞአቸውን የጀመሩት ከጥምቀት በዓል በኋላ በልደት በዓል ገደማ ሲሆን መንገዳቸውን የሚቀጥሉት ቀስ እያሉ ስለሆነ በዚያ የሚደርሱበት ጊዜ በሕማማት ሰሞን ነበር። በዓመቱ በዚህ ጊዜ መንገዳቸውን የሚጀምሩበት ምክንያት በምድረ ግብጽ መግቢያ ላይ በሚገኘው በኑቢያ በዚህ ወር የክረምቱ ጊዜ ስለሚያልቅና ውኃም ስለሚገኝ ነው ይላሉ። በምድረ ግብጽ ወይም በካይሮ ከተማ ግን ምንም ዝናም አይጥልም። መነኩሴዎቹ የተጓዙት ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው። ከአገሩ ልዩ ልዩ ክፍሎች ወደተባለው ከተማ መጥተው ከተሰበሰቡ በኋላ የጥምቀቱ በዓል እንዳለፈ እስላሞቹ በደህና እንዲያደርሱዋቸው

በማለት (በዚያን ጊዜ ጠቅላይ ግዛቱን ይገዛ የነበረው) ባሕር ነጋሽ ዶሪ መነኩሴዎቹን ለነዚሁ አስረከባቸው። እስላሞቹም በሱዋኪንና በሪፋ የሚኖሩ ነበሩ። ሱዋኪን በኢትዮጵያና በግብጽ ድንበር ላይ የምትገኝ ከተማ ስትሆን ሪፋ ደግሞ የናይል ወንዝ የሚያልፍባት በግብጽ መካከል የምትገኝ ከተማ ናት። እነዚህ እስላሞች በኢትዮጵያ የታወቁ ነጋዴዎች ስለነበሩ መንገደኞቹን በደህኛ በካይሮ ከተማ እንዲያደርሱ እምነት ተጣለባቸው። ከዚህ ቦታ ያንድ ቀን መንገድ ርቆ ወደሚገኝ ሐማሴን ወደተባለ ምግብ በብዛት ወደሚገኝበትና ብዙ ደብሮች ወዳሉበት ከተማ ጉዞአቸውን ጀመሩ። በዚህ ከተማ እንደደረሱ ዝግጅታቸውን አከናወኑ። ይህ ከተማ በባሕር ነጋሹ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ያለ ደፍላ የተባለ ሰው የሚገዛው ነው።

መነኩሴዎቹ መንገዳቸውን በጀመሩ ጊዜ ብዙ አይጓዙም ነበር፤ የቀትር በኋላ ጸሎት ሰዓት ያርፉና የያዙዋቸውን ሶስት ታቦቶች በድንኳኖቹ ውስጥ አኑረው ቅዳሴ ይገቡና ሁሉም ቆርበው በዚያ ካደሩ በኋላ በማግሥቱ በሶስት ሰዓት መንገዳቸውን ይቀጥላሉ። እያንዳንዳቸው ስንቃቸውንና እንዲሁም ውኃ በቅል ወይም በቀርበታ ተሸክመው የጸሎት ድንኳናቸውን በግመሎች ጭነው መንገዳቸውን ይቀጥላሉ። በየቀኑ ከሁለት ሌግዋ በላይ አይጓዙም ነበር። ከዚህ በላይ ያተትሁን ለማየት የቻልሁት ይህንኑ ለማየት ስል ከነርሱ ጋር ሁለት ቀን አብሬ ተጉዤ ስለነበር ነው። አብሬአቸው በነበርሁበት በነዚህ ቀኖች በመካከለኛ ግምት ሶስት ሌግዋ ተኩል ለመጓዝ ይቻል ነበር። ከሐማሴን ከተማ እስከ ሱዋኪን ድረስ ያለውን ክፍል ይገዙ የነበሩ ዳፍላና ቃፍላ የተባሉ ከባሕር ነጋሹ በታች የሆኑ ሁለት መኮንኖች ናቸው። በቀን ሶስት ሌግዋ ሂሳብ ከዚህ ከተማ እስከ ሱዋኪን ድረስ ነጋዴዎችን የአስራ አምስት ቀን ጉዞ የሚጠይቅ መንገድ አለ ይባላል። በዚሁ ፍጥነት በመጓዝ ከሱዋኪን እስከ ሪፋ አስራ አራት ቀን የሚፈጅ የነጋዴ መንገድ አለ። ይህን መንገድ በመከተል ከሱዋኪን ሲወጡ የግብጽ ግዛት ይጀምራል። በዚህ መንገድ ላይ ውኃና ሰው ከማይገኝበት ከሁለት ቀን መንገድ በስተቀር አገሩ በሙሉ ሰው ይኖርበታል ይላሉ። ምንም እንኳ በእስላሞች ሥልጣን ሥር ቢተዳደርም መንገዱ በሚያልፍበት ቦታ ሁሉ የሚኖሩ

ለስግደት ለሚሄዱ ለክርስቲያን መንገደኞች ሁሉ ምጽዋት የሚሰጡ ብዙ ክርስቲያኖች ይገኛሉ ይባላል። በዚህ መንገድ ላይ የሚገኝ ቅዱስ እንጦንዮስ የኖረበት ነው የሚባል ባንድ ገዳም ውስጥ ያሉት መነኩሴዎች በሙሉ ከኢትዮጵያ የመጡ ናቸው። ከሪፋ እስከ ካይሮ ያለው መንገድ አየሩ በጣም ቀዝቃዛና የናይልን ወንዝ ተከትሎ ሲሄዱ የስምንት ቀን መንገድ ነው ይላሉ። ከኛ ቀድመው ይሄዱ የነበሩት እነዚህ መነኩሴዎች ሱዋኪንን እንዳለፉ ይመሩዋቸው ከነበሩት እስላሞች በጣም ብርቱ የነበሩ ሌሎች እስላሞች አግኝ ተዋቸው አደጋ ጣሉባቸው፤ በዚሁም አደጋ ላይ ሽማግሌዎቹን በሙሉ ፈጅተዋቸው ወጣቶቹን በግዞት ይዘው ከዚያ በኋላ ሸጡዋቸው ይባላል። ለስግደት ከሄዱት በጠቅላላው ሶሶት መቶ አርባ ስምንት ከሚሆኑ መነኩሴዎች ውስጥ ሊያመልጡ የቻሉት አስራ አምስት ብቻ ነበሩ። እነዚህ ያመለጡት ወደ የሩሳሌም ለመሄድ ችለው ከተመለሱ በኋላ አግኝተናቸው የደረሰባቸውን ነገሩኝ፤ ከዚህም በላይ በተለይ እስላሞች እንደዚያ ያጠቁዋቸው የኛ የፖርቱጌዞች ወዳጆች በመሆናቸው ምክንያት መሆኑን ጨምረው ነገሩን፤ እነዚህ ሰዎች ለኛ ሲሉ መሰቃየታቸው እርግጠኛ ነገር ነው። ከሪፋ እስከ ካይሮ ያለው ክፍል እስላሞችና አይሁዶች ክርስቲያኖችና ነጭ ሰዎች የሚኖሩበት እጅግ ደስ የሚያሰኝ ቦታ ነው። ካይሮ በደረሱ ጊዜ ባንድ ምንጭ አጠገብ በሚገኙ «ቅዱስ ቆስም ወዳሚያን» ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በቅድስት ባርባራ ደብር ዐረፉ። ከካይሮ እስከ የሩሳሌም ያለው መንገድ የስምንት ቀን መንገድ ነው ይባላል። ከዚህ አደጋ በኋላ መነኩሴዎቹ ወይም ቄሶቹ በማህበር ሆነው ለስግደት ወደ የሩሳሌም መሄዳቸውን ተውት ይባላል። አንዳንድ የሚሄዱም ቢኖሩ ባለባበሳቸውና በሁኔታቸው መንገደኞችን መስለው ነው ይባላል። እነዚህ የሩሳሌም ደርሰው ከተመለሱ በኋላ እንደቅዱሳን ነው የሚቆጠሩ። የየሩሳሌም ሰዎች እንደኛው ነጮች ስለሆኑ እኛ በዚህ አገር በደረስን ጊዜ የየሩሳሌም ክርስቲያን ያሉን በዚህ ምክንያት ነው። ከኢትዮጵያ ወደየሩሳሌም የሚወስድ ሌላ አጭር መንገድ አለ፤ ይኸውም ከምጽዋ እስከ ደብረ ሲና ያለው የባሕር መንገድ ነው። ይህ መንገድ ከአስራ አምስት ቀን በላይ አይፈጅም፤ ከደብረ ሲና እስከ የሩሳሌም ያለው መንገድ ደግሞ ስምንት ቀን ይፈጃል።

ኢትዮጵያውያን መርከቦች ስለሌሎዋቸው ይህን መንገድ እምብዛም አይጠቀሙበትም። ይሁን እንጂ የፖርቱጋል ንጉሥ በምጽዋ ላይ ምሽግ እንዲሠራ በማዘዝ ይህን መንገድ ከማናቸውም ዓይነት ሥጋት ነፃ እንደሚያደርገው ተስፋ አላቸው።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ፤ ኢትዮጵያን የሚያዋስኑ ግዛቶች።

ኢትዮጵያን የሚያዋስኑ አገሮች የባላባትና የመኳንንት ግዛቶች ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው። የመጀመርያው በቀይ ባሕር ላይ የሚገኘው ምጽዋ ነው። ከዚህም በኋላ በእስላሞቹ አረቦች ግዛት ድንበር የሚገኙት የባሕር ነጋሹን ግዛት መኳንንት ከብቶች የሚጠብቁ ሰላሳ ወይም አርባ እየሆኑ ከልጆቻቸውና ከሚስቶቻቸው ጋር ወዲያ ወዲህ የሚዞሩ ዘላኖች የሚኖሩበት አገር አለ። እነዚህ ዘላኖች ክርስቲያኖች አለቃዎች ያሉዋቸው እስላሞች ሲሆኑ በኃይላቸውና ከብቶቻቸውን በሚያስጠብቁዋቸው መኳንንት በሚያደርጉላቸው አስተያየት ምክንያት መንገደኞችን እየቀሙ የሚኖሩ ናቸው። ከነዚህ ዘላኖች አገር ቀጥሎ ያለው ደንከል ነው። ይህ ግዛት ቤይሉል የተባለ ከባብ ኤል መንደብ ወሽመጥ በስተግቢ በኩል የሚገኝ የራሱ ወደብ አለው። ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘው ከዘይላና ከበርበራ ባላባቶች ሥልጣን ሥር የሚገኘው የአዳል ግዛት ነው። እነዚህ ሁለት ግዛቶች ከሚዋሰኑበት ቦታ ጀምሮ ወደ መካከል ኢትዮጵያ ሲጓዙ ዶባዎች የሚኖሩበት ሃያ አራት ወረዳዎች አሉ። ስለዶባዎች ከዚህ በፊት በምዕራፍ አርባ ስምንት በሰፊው አትቻለው።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ አንድ፤ የአዳል ግዛቶች።

ሲወራ እንደሰማሁት የአዳል ግዛት የጓርዳፊው ርዕሰ ምድርንም የሚጠቀልል ትልቅ አገር ነው ይባላል። በዚያ የሚገኘውን ክፍል የሚገዛው የዚሁ ግዛት ታዛዥ የሆነ ሌላ ገዥ ነው። የአዳል ንጉሥ

ሁልጊዜ ክርስቲያኖችን ይዋጋ ስለነበር በእስላሞች ዘንድ እንደ ቅዱስ ሆኖ ነበር የሚገመተው። በየጊዜው ከክርስቲያኖች ከዘረፈው ሃብት ለሜካና ለካይሮ ለሌሎችም እስላሞች ነገሥታት ገጸ በረከት ይልካል፤ እነርሱም ለጦርነቱ መርጃ የሚሆን የጦር መሣርያዎች ፈረሶችና ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮች ይልኩለታል። ይህ ባላባት በክርስቲያኖች ድል እንደተነሣና የጦር ሠራዊቱ አዛዥ ማሕፉድም ስለመገደሉ ከዚህ በፊት በምዕራፍ መቶ ሃያ አራት ገልጫለሁ። የአዳል ግዛት የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ከሆኑት ከሸዋና ከፈጠገር ይዋሰናል።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ ሁለት፤ የሐድያ ግዛት።

የንጉሠ ነገሥቱ ዜጋዎች የሆኑ ሰላማዊ እስላሞች የሚኖሩበት የሐድያ ግዛት እስከ መቃድሾ ይደርሳል ይባላል። ከዚህ በፊት በምዕራፍ መቶ ሃያ ዘጠኝ እንደገለጽሁት ንጉሠ ነገሥቱ ራሱ ወደዚህ ግዛት ሄዶ ፀጥታን አስከብሮ ቤተ ክርስቲያኖችንና ገዳሞችን አሠርቶ ካህናትም በዚያው ትቶ ተመልሶአል። ሐድያ የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ከሆነው ከወጅ ይዋሰናል። ከዚህ በላይ የዘረዘርኋቸው ግዛቶች ሁሉ ባሕሩን የሚነኩ በስተሰሜን የሚገኙ ናቸው።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ ሶስት፤ ስለገንዝና ስለገሙ ስለጉራጌም ግዛት።

ከሐድያ ግዛት መካከል ወደ ምዕራብ በኩል ሲጓዙ በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ግዛት ድንበር የሚገኙ የአሕዛቦች መኖርያ አገር አለ። ከሁለቱ ቦታዎች አንዱ ገንዝ የተባለ ክርስቲያኖች በየጊዜው የሚገቡበት የአሕዛብና የክርስቲያን መኖርያ ነው። ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘው ስፋቱ ካንድ አውራጃ የሚቃረብ ገሙ የተባለ አንድ ትልቅ ቦታ አለ። በዚህ ቦታ የሚገኙት ሰዎች ለባርነት እምብዛም

የማይፈለጉ በልዩ ልዩ ሹማምንት የሚገዙ ናቸው። ይህ ቦታ የሚገኘው በምዕራብ በኩል ነው። ወደ ደቡብ በኩል ሲጓዙ በንጉሥ የሚገዙት የጉራጌዎች አገር ይገኛል። ስለጉራጌ አገር ከዚህ በፊት በምዕራፍ መቶ አስራ ሁለት አትቻለሁ። ይህ አገርና ከፍ ብለን የጠቀስናቸው ገንዝና ገሙ ከዋግና ከሸዋ ድንበረተኞች ናቸው።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ አራት፤ ስለዳሞትና ከዚያም ስለሚገኘው ወርቅ፤ ከዚህ በስተ ደቡብ ስለሚገኙት ወንዲላ ሴቶች።

ከሸዋ በስተምዕራብ በኩል ዳሞት የተባለ አንድ ትልቅ ግዛት አለ። የዚህ ግዛት ባሮች እጅግ የተወደዱ ስለሆኑ እስላሞች በቀላል ዋጋ አይሸጡዋቸውም። ከዚህ ቦታ የሄዱ ባሮች በአረብያና በፋርስ በሕንድና በግብጽ በግሪክም አገር በብዛት ይገኛሉ። የእስላምን እምነት ከተቀበሉ በኋላ በሃይማኖታቸውና በወታደርነታቸው በጣም የታወቁ ናቸው ይባላል። የዳሞት ሰዎች አሕዛብ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ከነርሱው ውስጥ ብዙ ክርስቲያኖች ይገኛሉ። በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ከነርሱ ጥቂቶቹን አይቻለሁ። ከዚሁ ግዛት ብዙ ቄሶች መነኩሴዎችና መነኩሲቶች ይገኛሉ። ቤተ ክርስቲያኖችና ገዳሞች በብዛት ይገኛሉ ይባላል። የንጉሡ የማዕርግ ስም የአሕዛብ ንጉሥ የሚያሰኝ ነው ይባላል። በመላ ኢትዮጵያ የሚገኘው ጥሩ ዓይነት ወርቅ የሚመጣው ከዚህ ቦታ ነው። ከዚህም በላይ ልዩ ልዩ ዓይነት ፍራፍሬ ይገኝበታል። ለምሳሌ በጉራጌ አገር በነበርንበት ጊዜ የዓቢይ ጾምን ስናከብር ብዙ ዝንጅብል ወይንና ኮክ መጣልን። ጾሙም ከተፈታ በኋላ ብዙ ሙክቶችና ፍሪዳዎች አመጡልን።

ከጉራጌና ከዳሞት ግዛቶች መጨረሻ በስተደቡብ በኩል ወንዲላ ሴቶች የሚኖሩበት ግዛት ይገኛል ይባላል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሴቶች ዓመቱን በሙሉ ባንድነት ሆነው ከባሎቻቸው ጋር ጊዜውን ስለሚያሳልፉት ስለወንዲላ ሴቶች ከሚገመተውና ከሰማነው ይልቁንም በልዑል

ዶም ፔድሮ መጽሐፍ ላይ ከተገለጸው ሃተታ በጣም የተለየ ነው። የምትገዛቸው አንዲት ንግሥት ናት፤ ንግሥቲቱ ባል የሌላት መሆኑዋ የታወቀ ቢሆንም ልጆች ወልዳለች ።የንግሥትነቱን ማዕርግ የምትወርሰው ሴት ልጅዋ ናት። የዚህ ግዛት ሴቶች የጦረኛነት ዝንባሌ ያላቸው ናቸው ይባላል። በከብቶች ላይ ሁልጊዜ ይዋጋሉ ይባላል። በቀስተኛነታቸው የታወቁ ስለሆኑ ቀስት በሚያስፈነጥሩበት ጊዜ እንዳያስቸግራቸው በማለት በሕፃንነታቸው ጊዜ ግራ ጡታቸውን ያሙዋሽሹታል ይባላል። በዚህ ቦታ ብዙ ወርቅ አለ፤ ከዚህ የሚገኘው ወርቅ በዳሞት እያለፈ ወደ ልዩ ልዩ ቦታዎች ይሄዳል ይባላል። ባሎቻቸው ጦረኞች አይደሉም ይባላል። ለዚሁም ባሎቻቸውን ይፈቅዱላቸዋል። በዳሞት ውስጥ በዓባይ ፊት ለፊት አንድ ትልቅ ወንዝ ይነሣል ይባላል። የአባይ ወንዝ ወደ ግብጽ የሚሄድ መሆኑ ሲታወቅ ይህ ወንዝ ግን ወዴት እንደሚሄድ አይታወቅም። እንዲሁ በጠቅላላው ብቻ ወደ ሚኒ ኮንጎ ይሄዳል እየተባለ ይገመታል። ወርቅ የሚወጣው ቀጥሎ በተመለከተው መንገድ መሆኑን ሰምቻለሁ። ሕዝቡ የክረምቱ ጊዜ እስኪመጣለት ድረስ ይጠብቅና መሬቱ እንዲለሰልስለት በማለት ይቆፍረዋል ይባላል። ከዚህ በኋላ ዝናሙ አፈሩን ያጥበውና ወርቁ ከላይ ፍጥጥ ብሎ ይገኛል ይባላል። ወርቁን የሚፈልጉት ማታ በጨረቃ ነው ይባላል። ይህንንም የሚያደርጉበት ምክንያት ወርቁ በጨረቃ ስለሚብለጨለጭ ነው። በአክሱምም ወርቁን በንደዚህ ያለ አኳኋን ሲያወጡ አይቻለሁ፤ የሁን እንጂ ፍለጋ የሚጀምሩት በምሽት አይደለም። ዳሞት ከንጉሡ ነገሥቱ ግዛት ከሸዋ ይዋሰናል።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ አምስት፤ አይሁዶች ነበሩ የሚባሉት ጋፋቶች ስለሚኖሩበት ግዛትና ስለጦረኝነታቸውም።

ዳሞትን አልፎ ወደ ምዕራብ በኩል ቁመታቸው ረጅም ጋፋት የተባሉ ሰዎች የሚኖሩበት ግዛት አለ። እነዚህ ሰዎች ከአይሁዶች ዘር ናቸው ይባላል። ነገር ግን እንደዚህ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ

መጽሐፍ ወይም ምኩራብ የላቸውም። በዚህ አገር ካየናቸው ነገዶች ሁሉ በጣም ብልሆች እነዚህ ናቸው። አገራቸው ከንጉሠ ነገሥቱ ግዛቶች ከሸዋና ከጎጃም ወሰነተኛ ነው። ይህን ሃተታ የምጽፈው ቦታውን አይቼው ሳይሆን ሲወራ በሰማሁት መሠረት ነው። ታላቁ ቢትወደድ ወደዚህ በሄደ ጊዜ ከኛ ሰዎች አንዳንዶቹ አብረው ሄደው ነበር። ጋፋቶች በሌሊት እየመጡ በመግደልና በመዝረፍ ቀንም እየሸሹና በየተራሮችና በየጫካዎቹ በመደበቅ ብዙ ጉዳት አድርሰው ነበር ይባለል። እንደሚባለውም ተራሮቹ አዘቅቶች እንጂ ቁመት ያላቸው አይደሉም ይባላል።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ ስድስት፤ የንግሥት እሌኒ ግዛት ስለነበረው ስለጎጃም ግዛትና በውስጡም ስለሚገኘው ወርቅ።

ደቡብን ትቶ ወደምዕራብ ሲጓዙ በንጉሠ ነገሥቱ የሚገዛ ጎጃም የተባለ ግዛት አለ። ከዚህ ግዛት አብዛኛው የንግሥት እሌኒ ንብረት ነበር። በዚህ አገር አጠራር ጊዮን የሚሉት የዓባይ ወንዝ የሚነሣው ወይም የሚመነጨው ከዚህ ነው። በዚህ ወንዝ ውስጥ ባሕር የሚመስሉ ታላላቅ ሐይቆች ይገኛሉ ይባላል። በነዚሁ ሐይቆች ውስጥ ከወገባቸው በላይ የሰው መልክ ከዚያ በታች የአሣ መልክ ያላቸው ፍጥረቶች ይገኛሉ ይባላል። አንዳንድ ሰዎችም እንዳዩዋቸው ይነገራል። ታቦት እንዴት እንደሚሠራ ለማየት ጴጥሮስ ድኩቪሊያን በንግሥት እሌን ትዕዛዝ ወደ ጎጃም ሄዶ ነበር። የተቀበረችውም በዚሁ ባሠራችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። መሠውያውን በእንጨት አጋጥመው መካከሉን በወርቅ መሉት፤ ታቦቱም የተቀረጸው ካንድ ጥፍጥፍ ወርቅ ነው ይባለል። ይህን የምጽፈው ጴጥሮስ ድኩቪሊያን በነገረኝ መሠረት ነው፤ እርሱም የነገረኝ ሁሉ እውነት ነገር ነው። ታቦቱን የባረኩት አቡኑ ስለነበሩ ትልቅ ግምት ያለው መሆኑን እርሳቸው ራሳቸው ነግረውኛል። በዚህ ግዛት አቅራቢያ በነበርንበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑ ብዙ ወርቅ ስለሚገኝበት በብዙ

ጠባቂዎች ይጠበቃል ማለትን ሰምቻለሁ። በጎጃም የሚገኙ ተራራማ ምድረ በዳዎችን አልፎ አይሁዶች ይገኛሉ ማለትን ሰምቻለሁ እንጂ የሚያዋስናቸው ግዛት ምን እንደሚባል አላውቅም። ይህን ቃል የሰማሁት ቃላቸውን በመተማመን ከምጠቅሳቸው ሰዎች ሳይሆን ተራው ሰው ሲያወራ የሰማሁትን ስለሆነ ላምነው አልችልም።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ ሰባት፤ ስለ በጌምድር ግዛትና በተራሮቹም ስለ ሚገኘው የብር ማዕድን።

ከጎጃም ቀጥሎ ከንጉሠ ነገሥቱ ግዛቶች ሁሉ በጣም ሰፊው የቤጌምድር ግዛት ነው። ይህ ግዛት ከአባይ ድንበረተኛ ነው ይባላል። በጌምድር ከጎጃም ጀምሮ እስከ አማራና እስከ አንጎት ግዛቶች እስከ ትግሬ መኮንኑና እስከ ባሕር ነጋሹም ግዛቶች ስለሚደርስ እንደተ ባለው በስፋቱ ሁሉንም የሚበልጥ ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ ከሁለት መቶ ሌግዋ በላይ ስፋት አለው። በአንጎትና በትግሬ መካከል ክርስቲያኖችና አሕዛብ ተቀላቅለው የሚኖሩበት የአገዎች አገር አለ። ይህ ቦታ የትኛውን ግዛት እንደሚያዋስን ባላውቅም ምናልባት ቤጌምድርን ሳይሆን አይቀርም በማለት እገምታለሁ። በበጌምድር ተራሮች ብር ይገኛል ማለትን ከብዙ ሰዎች ሰምቻለሁ፤ ነገር ግን እንዴት ለማውጣት እንደሚቻል አያውቁም ይባላል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ሲያወጡም ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው ይላሉ። ዋሻ ወይም ጉድጓድ ባገኙ ጊዜ እንጨት ጨምረውበት እሳት ያነዳሉ ይባላል። በዚያን ጊዜ ብሩ እየቀለጠ በቡዋንቡዋ ባንድ በኩል ይፈሳል ይባላል። ምንም እንኳ ይህ ዘዴ ሊታመን የማይቻል ቢመስልም ጉዳዩን ለጴጥሮስ ድኩቪሊያን ነግሬው እውነት መሆኑን አረጋግጦልኛል። ይህን የጻፍሁት ሲወራ በሰማሁት መሠረት ነው። ይሁን እንጂ ብሩ በጣም የሚፈለግ መሆኑን አላውቅም።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ ስምንት፤ ቀድሞ ክርስቲያኖች የነበሩ ኖብያዎች የተባሉ ሰዎች ስለሚኖሩበት ግዛት፤ የነርሱ አገር በሚያዋስነው አገር ስለሚገኙ ቤተ ክርስቲያኖች።

ከበጌምድር ግዛት መጨረሻ ነገደ በለው የሚባሉ እስላሞች የሚኖሩበት ቦታ አለ። እነዚህ እስላሞች በያመቱ ለንጉሠ ነገሥቱ ይገብራሉ። በስተሰሜን በኩል በለዎች ቀድሞ ክርስቲያኖች የነበሩና በሮማውያን ከሚገዙት ከኖቢሶች አገር ይዋሰናሉ። ከኛ ጋር በኢትዮጵያ ሶስት ዓመት ሙሉ የቆየ ከዚህም በኋላ አብሮን ፖርቱጋል የሄደ ዮሐንስ ዘሶርያ የተባለ በጥርንቡሌ (ሶርያ) የተወለደ አንድ ሰው በነገረን መሠረት በዚያ አገር የክርስቶስ ስቅለት ምስልና የእመቤታችን ስዕል እንዲሁም ሌሎች ምስሎች የተሳለባቸው አንድ መቶ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ፤ ሰዎቹም ለጊዜው ክርስቲያኖች ወይም እስላሞች ወይም አይሁዶች ያይደሉ ነገር ግን ክርስቲያን ለመሆን ሁልጊዜ በመመኘት የሚኖሩ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኖቹ የሚገኙት በአገሩ ተሰራጭተው በሚገኙ በጥንታዊ ግንቦች ውስጥ ነው። ስለዚህ በግንቦቹ ልክ ቤተ ክርስቲያኖች አሉ። በቤተ መንግሥቱ በነበርንበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ የክርስትናን ሃይማኖት የሚያስተምሩ ቄሶችና መነኩሴዎች እንዲልክላቸው ለመለመን ከዚያ አገር ስድስት ሰዎች መጥተው ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ለራሱም አገር የሚያስፈልጉትን ቄሶችና መነኩሴዎች የሚያስመጣው ከእስላሞች አገር ማለት ከእስክንድርያ ስለሆነ እነዚህ ሰዎች የጠየቁትን የማይፈጽምላቸው መሆኑን ነገራቸው። እነርሱም በዚሁ ጉዳይ አዝነው ተመለሱ ይባላል። የዚህ አገር ሰዎች ማናቸውንም ነገር የሚያገኙት ከሮም ነበር ይባላል። ከሮም የተላከላቸው ኤጲስቆጶስ ከሞተ ብዙ ጊዜ አልፎታል ይባላል። በእስላሞች ጦርነት ምክንያት ከሮም ጋር የነበራቸው ግንኙነት ስለተቋረጠ ምትክ ኤጲስቆጶስ ባለማግኘታቸው ክህነትና የክርስትና ሃይማኖት ጨርሰው ጠፉ። አገራቸው ከግብጽ ጋር የሚዋሰን ሲሆን ጥሩ ወርቅም ይገኝበታል ይባላል። ይህ አገር ከሰዋኪን ፊት ለፊት በቀይ ባሕር አጠገብ ይገኛል። ኑብያ በናይል ወንዝ ግራና ቀኝ ነው የሚገኘው። ንጉሥ ስለሌላቸው በሹማምንት ነው የሚገዙት፤

ስለዚህ እያንዳንዱ ሹም የራሱ ግንብ አለው። በኢትዮጵያ ግዛት መጨረሻና በግብጽ ድንበር ላይ በሚገኘው በሱዋኪንና በኑብያ መካከል የበለዎች አገር ይገኛል። ከሱዋኪን እስከ ምጽዋ ድረስ ያለው ጠረፍ ጫካ ነው ይባላል። እነዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ የድንበር ግዛቶች ናቸው ይባላል። ጥቂቶቹን ብቻ ባይኔ ሳያቸው ሌሎቹን ግን ሲወራ በሰማሁት መሠረት ነው የጻፍሁት።

ምዕራፍ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ፤ ንጉሥ ሰሎሞን ከንግሥተ ሳባ ለወለደው ልጁ ስለሾመለት ሹማምንት፤ ዘሮቻቸው በዚሁ ማዕርግ እስከ ዛሬ ድረስ ስለሚጠሩበት።

ንጉሥ ሰሎሞን ከየሩሳሌም ልጁን ወደናቱ አገር በላከው ጊዜ ከርሱ ጋር ስለላካቸው መኳንንት ሲወራ የሰማሁትን ከዚህ በታች አስከትላለሁ፤ የነዚህ መኳንንት ማዕርግ ከአባት ወደልጅ እየተዋረሰ የሚወርድ ነገር ስለሆነ እስካሁን ድረስ ዘሮቻቸው ይጠሩበታል ማለትን ስምቻለሁ። ንጉሥ ሰሎሞን ልጁን ወደናቱ ወደ ንግሥተ ሳባ በላከው ጊዜ ለቤቱ ሃላፊ የሚሆኑ ከያንዳንዱ አገር አንዳንድ ሹም ሰጠው፤ እነዚህም ሹማምንት አዛገሮች፤ አዋጅ ነጋሪዎች ተቆጣጣሪዎች፤ ባልደራሶች፤ ጥሩንባ ነፊዎች፤ ጋሻ ጃግሬዎችና ወጥቤቶች፤ ሌሎችም ለቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ሹማምንቶች ነበሩ። ስለዚህ ይህን የመሰለ ማዕርግ ያላቸው ሰዎች የእስራኤል ልጆች ወይም መኳንንት በመባል በጣም ይከበራሉ። የአዛገሮች ዘሮች ይህን ሥራ ብቻ እንጂ ሌላ ነገር ስለማይሠሩ በዚህ ማዕርግ ያሉት ሰዎች ቁጥር እጅግ የበረከተ ነው። ስለዚህ የሌሎችም ሹማምንት ዘሮች እንዲሁ ማዕርጉን እየተወራረሱ ይኖራሉ። ከአባት ወደ ልጅ የማይተላለፍ ሥራ ብላቴናነት ብቻ ነው። ምክንያቱም ለዚህ ሥራ የሚመረጡት የመኳንንት ልጆች ብቻ ናቸው። አሁን ግን እንዲህ መሆኑ ቀርቶአል። ይህም የሆነበት ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ መኳንንቱን ባስጠራቸው ቁጥር የተጠሩበትን ምክንያት መግለጽ ልምድ አልነበረም፤ ነገር ግን

ልጆቻቸው ብላቴኖች ስለሆኑ ሁልጊዜ ይገልጹላቸው ነበረ፤ ስለዚህ ከዚያ በኋላ በውስጥ ብላቴናነት የሚያገለግሉ በጦርነት ላይ የሚማረኩ የእስላም ባላባቶች ልጆች ነበሩ። ተስማሚ ሆነው ያገኙዋቸው እንደሆነ በውስጥ ከመግባታቸው በፊት እንዲማሩ ይታዘዛል። ከዚህ በኋላ ሥልጡንና መልካም ሆነው ያገኙዋቸው እንደሆነ ገብተው እንዲያገለግሉ ያዙዋቸዋል። የታላላቅ መኳንንት ልጆች ግን ባጋፋሪነት በወጥቤትነት፤ ወይም በባልደራስ ክፍል ያገለግላሉ ይባላል። ይህም እንዲህ መሆኑን አይተናል። ደብተራዎችም ከየሩሳሌም የመጡት መኳንንት ዘሮች ናቸው ስለሚባል ከካህናት ሁሉ የበለጠ ክብር አላቸው።

ምዕራፍ መቶ አርባ፤ የንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደር ግዛቱ ከነማዕርጉ እንዲመለስለት ስለመታዘዙ፤ ወደ ባሕሩ ጉዞአችንን ስለመጀመራችን።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሐዲያ ለመሄድ በተነሣበት ቀን እኔና አምባሳደሩ አባ ፀጋ ዘአብ ወደ ግዛቱ ለመሄድ መንገዳችንን ጀመርን። ይህ መንገድ የኛ ሰዎች ወዳረፉበት የሚወስድ ነበር። ከኛ ጾም አስር ቀን ቀድሞ በሚገባው በነርሱ ጾም ቅበላ ዕለት ለአባ ፀጋ ዘአብ በተሰጠው ርስት ደረስን። ከዚህ በፊት የተወሰደበትንና አሁንም አዲስ የተሰጠውን ከተረከበ በኋላ ለመሄድ ተዘጋጀን። ተወስዶበት የነበረው ርስት ሰማንያ ቤተ ሰቦች ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች የሚገኙበት ሲሆን ለርሱ የተሰጠበት ምክንያት በዚያ የነበረ አንድ ገዳምን እንዲያስተዳድርበት ነው። አሁን የተሰጠው ርስት በአቡ ጂማ የሚገኙትን ጨዋዎች እንዲያስተዳድርበት ከራስነት ማዕርግ ጋር የተሰጠው ነው። እነዚህ ጨዋዎች ቁጥራቸው ከስምንት መቶ በላይ ነው።

የዓቢይ ጾም ወራት ግማሽ ላይ የኛ ሰዎች ሠፍረውበት በነበረው ደረስን፤ ወዳገራችን የሚወስዱን ፖርቱጊዞች ለትንሳኤው በዓል

በዚያው ይመጣሉ በማለት በትልቅ ዝግጅት ይጠበቁ ነበር። ስላልመጡ ሁላችንም አዘንን። ስለዚህ ፖርቱጊዞች ያልመጡልን መሆናቸውን ንጉሠ ነገሥቱ ካወቀ በኋላ ከኛ ጋር የነበረውን የርሱን አምባሳደር አስጠርቶ ወደ አቡ ጂማ እንዲሄድ አዘዘው። የአቡ ጂማ ገዥ የነበረውን ባለሥልጣን «አቢብ ራስ» የሚያሰኝ ማዕርግ ሰጠው። ይህ ሰው ምንም እንኳ ከአስር ሺ በላይ ገባሮች ቢኖሩትም እንደሌሎቹ መኳንንት ሁሉ በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ሥር የሚተዳደር ነው። ለርሱ ይህ መልእክት በደረሰው ጊዜ እኛም አብረነው እንድንሄድ ታዘዝን፤ በአባ ፀጋ ዘአብ ምድር ላይ ያለው ሰብል ተወቅቶ ስለተከተተ ለጊዜው ምንም ሊሰጠን ስላልተቻለ እቦታው ድረስ ሄደን አምስት መቶ ጭነት ስንዴ፤ መቶ ፍሪዳ፤ መቶ ሙክትና ለጠጅም መጣያ ማር ከአምባሰደሩ እንድንቀበል ታዘዝን። ቦታው ከባሕሩ ሩቅ በመሆኑ ተመልሰን ስንመጣ መንገዱ በግስጋሴ አንድ ወር የሚፈጅብን በመሆኑ ወደ ባሕሩ ለመድረስ ያቅተናል ብለን በመፍራት መንገዱን ከመጀመራችን በፊት ብዙ አቅማማን። በመጨረሻ ግን እተባለው ቦታ ድረስ ሄደን ስንቃችንን ተቀብለን መምጣት ብቻ እንጂ እንደማንቆይ በመወሰን ለመሄድ ቆረጥን። ስለዚህ እቦታው ድረስ ሄደን በሚቀጥለው ጥር ወር አባ ፀጋ ዘአብን ሳናማክር ወይም ፈቃድ ሳንጠይቅ በገዛራሳችን መንገዳችንን ይዘን ከዚህ በፊት ወዳረፍንበት በባሕሩ አጠገብ በነበረው ቦታ ጉዞአችንን ጀመርን፤ ይህን ያደረግንበት ምክንያት እርሱ ያዘገየናል ብለን በመፍራት ነበር። እኛ መንገዳችንን ከጀመርን በኋላ ከርሱ ዘንድ ተልከው የመጡ ሁለት ሰዎች እየሮጡ መጥተው አስከትለናቸው እንድንሄድ በአምባሳደሩ ስም ለመኑን። የፖርቱጊዞቹ መምጣት ሲታወቅ ከሁለቱ ሰዎች አንደኛውን መልሰን በቶሎ እንድልክበት አምባሳደሩ የለመመንን መሆኑን ነገሩን።

<u>ምዕራፍ መቶ አርባ አንድ፤ የሚወስዱን ፖርቱጊዞች ባዲስ አለቃ እየታዘዙ በወደቡ ስለመምጣታቸው።</u>

እኛ ፖርቱጊዞቹና ሌሎቹ ፈረንጆች ባንድነት በባርዋ ከተማ ሆነን የመርከቦቹን መምጣት ስንጠብቅ ሳለን ሁለት ሰዎች ወደ ወደቡ ሄደው መምጣታቸውን እንዲመለከቱ ላክናቸው። እነዚህ ሰዎች የቅዳሜ ስዑር ዕለት በድንጋጤና በሃዘን ተመልተው መጥተው «ፖርቱጊዞቹ በሙሉ ድል ስለተነሡና የሕንድ ግዛታቸውንም ስለተ ነጠቁ ወደ ወደቡ አይመጡም፤ ወደ ሕንድም አይሄዱም» አሉን። ይህንንም ወሬ የነገሩዋቸው በሶስት መርከቦች ሆነው በሙዚቃ ድምጽ በመደሰትና በሆታ ብዙ ሸቀጥ ጭነው በምጽዋ ወደብ ከወረዱት እስላሞች ነው። ምንም እንኳ እስላሞች ይህንን ለመናገር የቻሉበት ምክንያት ዲዩ በተባለው በጉጀራት ንጉሥ ወደብ ላይ አንድ የኛን መርከብ አግኝተው መያዛቸውን ምክንያት በማድረግ ቢሆንም ይህን የመሰለውን ወሬ የሚነዙበት ዋናው ምክንያት የፖርቱጊዞቹን ሞራል ለማዳከም በማለት ነበር። መልእክቱን ያመጡልን ሰዎች በድንጋጤ ምክንያት ነፍሳቸውን አያውቁም ነበር። ይህ ወሬ እኛንም ከፍ ያለ ሐዘን አሳደረብን። አምባሳደር ዶም ሩድሪጉም እንዲህ አለኝ፤ «አባ፤ ነገ ጥዋት በማለዳ ልዩ ቅዳሴ እናድ ርግና ከአምላካችን ጋር እንማጠን።» እኔም ቅዳሴ ለመግባት የሚያ ስችለኝ የልብ እረፍትና ሰላም ስለሌለኝ ነገ ጥዋት ተነሥተን ወደ ታላቁ ቤተ ክርስቲያን ሄደን ከባሕር ነጋሹ ጋር ሆነን ብናስቀድስ ይሻላል አልሁት። ስለዚህ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄደን ከነጋ በኋላ የትንሳኤ ቅዳሴ እንደተፈጸመ ከርሱ ጋር ሄደን እንድንመገብ ባሕረ ነጋሹ ጋበዘን። ነገር ግን ቀኑ የደስታ ዕለት ስለነበረ እያንዳንዱ ሰው በቤቱ ሆኖ ቀኑን ማክበር አለበት ስንል ምክንያት ሰጥተን ወደ ቤታችን ሄድን። ይህን ምክንያት የሰጠነው በሐዘን ላይ ስለነበርን ነው። ለምሳ ከጋበዝኋቸው ከስምንት ጄኖቫያውያን ጋር ወደ ቤት ሄጄ ከምሳው በኋላ እንግዶቼን ከዘመዴ ጋር ትቻቸው አንድ ወንዝ ተከትዬ ወደላይ ወጥቼ አንድ ትልቅ ድንጋይ ጥላውን በጣለበት በወንዙ ዳር በሚገኝ አሸዋ ላይ ተጋድሜ አለቀስሁ። ከዚህ በኋላ

ሐዘኔን በማሸነፍ እንዲህ ስል ራሴን አጽናናሁ። ይህ የመጣው ከእግ ዚአብሔር ነው፤ ይህ አደጋ በዚህ አገር እንዲደርስብኝ ፈቀደ፤ ለዚሁም ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው፤ በአደን ምክንያት ወዲያ ወዲህ በመዞር የዚህን አገር ተራሮችና ለእርሻ የሚያመቹትንም ምድሮች ካገሩ ተወላጆች አብልጬ አውቃለሁ። መልካም አገልጋዮ ችና አስራ አራት የቀንድ ከብቶች አሉኝ፤ እንዲሁም በእንስት በጎች ልለውጣቸው የምችል ወንዶች በጎች አሉኝ። ስለዚህ እኔ በዚህ አገር እንድኖር እግዚአብሔር ስለፈቀደ ባንድ ወንዝ ዳር ድንኳን ተክዬ የዱር አራዊት ወደ ውስጥ እንዳይገቡ ዙርያውን ባጥር ከብቤ ካሽከሮቼ ጋር ሆኜ በየቀኑ እግዚአብሔርን እየወደስሁ እኖራለሁ። ባካበቢው የሚገኘውን ጫካ አስመንጥሬ አታክልት አስተክዬ ልዩ ልዩ ዓይነት እህል እዘራበታለሁ። ስለዚህ ከዚህ በማገኘው አዝመራና በአደንም ራሴንና አሽከሮቼን ደግፌ ለመኖር እችላለሁ። ደስ የሚያሰኝ ወሬ የሰማሁ ይመስል በዚህ ሃሳቤ ተጽናንቼ ወደ ቤቶ ተመለስሁ። በዚያም እንግዶቼና አምባሳደር ዶም ሩድሪጉ ደ ሊማና የኛም ፖርቱጊዞች በሙሉ በደስታ ሲጫወቱ አገኘኋቸው። ወዲያውኑ እንደገባሁ አም ባሳደሩ እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረበልኝ፤ «አባ፤ ምን ማድረግ ይገባናል፤ በኔ አስተያየት የሚበጀውስ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ቤተ መንግ ሥቱ እንዲመልሰን ለወዳጆቻችን ደብዳቤ መጻፍ ነው።» ወደዚያ ከሄድሁ ሁለተኛ ልመለስ አልችልምና ደብዳቤ እንዳትጽፍ ስል መለስሁለት። ነገር ግን እንድንመለስ ንጉሠ ነገሥቱ የጠየቀ እንደሆነ ምን ማድረግ ይበጀናል ሲል ላቀረበው ጥያቄ እንዲህ ስል መለስ ሁለት፤ «ንጉሠ ነገሥቱ በተለይ የኔን ስም ሳይጠቅ ፖርቱጊዞቹ ይመለሱ የሚል ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ አልሄድም፤ ነገር ግን ስሜን ከጠቀሰ ምንም እንኳ ቅር ቢለኝም መሄድ አለብኝ።» ያልሄድሁ እንደሆነ ምን ለማድረግ እንደማስብ ጠይቆኝ ከምሳ በኋላ አንድ ሃሳብ አቅጄ በዚሁ ሃሳብ መጽናናቴን ነገርሁት። በሃሳቡ አምባሳደሩ ብቻ ሳይስማማ በዚያ የነበሩት ሁሉ ተደስተው አንድ በአንድ ተነሥተው ሳሙኝ። እያንዳንዳቸውም እንዲህ ሲሉ ሃሳቤን ደገፉ። «ይህ ከእግዚአብሔር የመጣ አቅድ ነው፤ ሚስቶቻችንን፤ ልጆቻችንን፤ አሽከሮቻችንንም ይዘን እንከተልዎታለን። መልካም አጋሰሶች ስላሉን ወደባሕሩ የሚወስደውንም መንገድ ስለምናውቀው አንዳንዶቻችን

ከርስዎ ጋር ስንቆይ ሌሎቻችን ደግሞ እንነግዳለን። ስለዚህ ሃብታሞች እንሆናለን፤ ከተማም እንቆረቁራለን፤ ከብትም እናረባለን፤ እርሻም እናርሳለን።» አምባሳደሩ ይህን ከሰማ በኋላ ስለዚህ ጉዳይ ምንም መልስ አልሰጠም። ወዲያውኑ ይህን ጉዳይ ትቶ እንዲህ አለኝ። አባ፤ እርስዎ አድነው ያገኙት ብዙ ሥጋና መልካም ምግብ አለዎ፤ ዛሬ እዚህ እንድንበላ እራት ይጋብዙን፤ ነገም እዚሁ ምሳ በልተን ከምሳ በኋላ ከርስዎ ጋር ወደ አደን እንሄድና እራት ከኔ ጋር ይበላሉ አለኝ። ይህ ጉዳይ በጣም አስደሰተኝ፤ ስለዚህ በትንሳኤ ዕለት አብረን ራት በልተን በማግሥቱ ሰኞ ዕለትም ምሳ በላን። ከዚህ በኋላ ወደ አደኑ ቦታ ሄደን ብዙ ጥንቸሎችና ሶስት ወይም አራት ወፎች ገድለን ለእራት ወደ አምባሳደሩ ቤት ሄድን። ፖርቱጌዞቹ ሁሉና በዚያም ይገኙ የነበሩት ሌሎቹ ፈረንጆች እኔ ባቀድሁት ፕላን ተስማምተው ከራት በኋላ ሁሉም ባንድነት ሆነው ወደ ቤቴ ሊያደርሱኝ ተስማሙ።

በመንገድ ላይ እንደነበርን ሃብቴ የተባለ የኔ አሽከር የነበረ አንድ ሰው ሲቃ እስኪይዘው ድረስ እየሮጠ መጥቶ እንዲህ አለኝ፤ «ጌታዬ፤ ጌታዬ፤ ፖርቱጌዞቹ በባሕሩ ላይ ናቸው።» እኔም መለስሁና ሃብቴ ይህን የነገረህ ማነው ስል ጠየቅሁት። እርሱም መልሶ ወሬውን የነገረው በበቅሎ የመጣ አንድ ሰው መሆኑን ነግሮኝ ያ ሰው ለጊዜው በባሕር ነጋሹ ቤት የሚገኝ መሆኑን ነገረኝ። እኔም መለስሁና እንዲህ አልሁት፤ «ሃብቴ፤ ይህ ነገር እውነት ከሆነ ንጉሠ ነገሥቱ ከሰጠኝ በቅሎ በስተቀር ከሌሎቹ ዘጠኙ ውስጥ ምርጥ የሆነውን እሰጥሃለሁ፤ ስለዚህ ያን ሰው አግኝቼ ነገሩን ከላረጋገጥሁ አልተኛም።» ከዚህ በኋላ ጓደኞቼን ተሰናብቼ ወደ ባሕር ነጋሹ ቤት ሄድሁ፤ እዚያም እንደደረስሁ በሩን ዘግተው አንከፍትም አሉን፤ ነገር ግን ከመልእክተኛው ጋር ሆኜ ዶሮ እስኪጮህ ድረስ በዚያ ቦታ ከጠበቅሁ በኋላ ሰውዬው መጣ፤ ሌላ ንግግር ከመጀመራችን በፊት ፖርቱጌዞቹን በባሕሩ ላይ ያየህ አንተ ነህን ስል ጠየቅሁት። እርሱም መልሶ ዳህላክን በመድፍ ሲደበድቡ አየኋቸው እንጂ በዓይኔስ አላየኋቸውም፤ ይህን መልእክት ለባሕር ነጋሹ ያመጣሁት ከሐርኪኮ ሡልጣን ነው አለኝ። ጨረቃ ስትወለድ መደሰት የእስላሞች ልምድ ነው፤ ነገር ግን ጊዜው የጨረቃ መወለጃ ስላልነበረ ያ ተኩስ የሩሚዎች

ይሆን ወይስ የቱርኮች ወይስ የክርስቲያኖች የሚለት ጥርጣሬ አደረብኝ። እኔ ወሬውን ለማጣራት መሄዴን የኛ ሰዎች ያውቁ ስለነበር የሆነውን ነገር ለማጣራት ማክሰኞ ዕለት ጥዋት ሁሉም መጥተው ማናቸውንም ነገር ገለጽሁላቸው። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደር የፖርቱጌዞቹ መምጣት እንደታወቀ በቶሎ ወሬውን እንዲያመጡለት በማለት ከኛ ጋር ሁለት ሰዎች ልኮ ነበር። ስለዚህ ከነዚህ ሰዎች አንዱን ላክነው፤ ከዚህም ሌላ ካገሩ ሰዎች አንድ ሰው በግሥጋሴ እንዲሄድና እስካሁን ድረስ የሰማነውን ወሬ ለአምባሳደሩ እንዲነግረውና እንዲሰናዳ ላክንበት። የሰማነውን ደግ ወይም መጥፎ ወሬ ሳናምን በምንገኝበት ጊዜ በዚያኑ ዕለት ማታ ከሕንድ ግዛት የባሕር ኃይል አዛዥ ከኤይቶር ደ ሲልቬይራ ደብዳቤ ደረሰን። በዚህም ደብዳቤ ላይ እኛን ለመውሰድ በምጽዋ ላይ ሆኖ የሚጠብቀን መሆኑን ነገረን። ይህ እንደደረሰን የቱን ያህል እንደተደሰትን ከቶ ለመግለጽ አልችልም። ከደስታው ብዛት የተነሣ የምናደርገውን አናውቅም ነበር። አምባሳደር ዶም ሩድሪጉ ደ ሊማ ወደኛ መጥቶ መንገዳችንን በማግሥቱ ጥዋት እንድንጀምር አዘዘ። አንዳንድ ሰዎችም የርሱን ሃሳብ ደገፉ። ነገር ግን በዚህ አገር በቆየንበት ጊዜ ሁሉ በመልካም ክርስቲያንነት ስለታወቅን በዚህ አውደ ዓመት ዕለት ብንሄድ ክርስቲያን አይደሉም ብለው ስለሚገምቱን እስከ ትንሳኤ በዓል ሳምንት ሰኞ ድረስ ብንቆይ መልካም ነው ስል የአምባሳደሩን ሃሳብ ተቃወምሁ። ከዚህ በኋላ የዚያኑ ዕለት ማታ አንድ ፖርቱጌዝንና አንድ ጠረፈኛ ያገሩን ተወላጂ ወደ ኤይቶር ደ ሲልቬይራ ላክናቸው። ከኛ ጋር የነበረውን የኢትዮጵያን አምባሳደር አሽከርና አንድ ያገሩን ተወላጅ ሌት ከቀን በግሥጋሴ እንዲሄዱና ይህን እርግጠኛ ወሬ እንዲነግሩት አምባሳደሩም በሐርኪኮ በኩል ወደ ባሕሩ በሚወስደው አቋራጭ መንገድ በግስጋሴ እንዲደርስብን ላክንበት።

ምዕራፍ መቶ አርባ ሁለት፤ ባሕር ነጋሹ ስለመዘጋጀቱና እኛም ከርሱ ጋር ወደ ባሕሩ ስለመጓዛችን።

ከትንሳኤው በዓል ማግሥት ሰኞ ዕለት ሚያዚያ ዘጠኝ ቀን እኛና ባሕር ነጋሹ ከኛ ጋርም የነበሩት ሶስት ሌሎች ፈረንጆች ካባርዋ ተነሥተን ወደሐርኪኮ ተጓዝን። ባሕር ነጋሹን የተከተሉት ያሽከሮቹና የጭፍሮቹ ቁጥር በጠቅላላው አንድ ሺ በቅሎዎች፤ ጥቂት በቆሎኞችና ስድስት መቶ እግረኞች ነበሩ። የዚያኑ ዕለት ከባርዋ ሁለት ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኝ ድንግል በሚባል መንደር አጠገብ በሚገኝ ሜዳ ላይ ድንኳን ተክለን አደርን። ይህ ሜዳ ወደ ሐርኪኮ ገበያ የሚሄዱ ገበያተኞች በየሳምንቱ ሰኞ ማታና ማክሰኞ ጥዋት የሚሠፍሩበት ነበር። በመንገዱ ላይ በብዛት የሚገኙትን አውሬዎችና የአረብ ቀማኞችን በመፍራት ገበያተኞቹ ባንድነት አጋሰሶቻቸውን እየነዱ ነው የሚሄዱ። በዚህ ቦታ እንደነበርን ሁለት ሺ ገበያተኞች ከኛ ጋር ተቀላቀሉ፤ እንዲያውም በመንገዱ ላይ ውኃ የሚገኝ ቢሆንማ ኖሮ ከዚህ የበለጠ ሰው ይመጣ ነበር አሉን። ባሕር ነጋሹን ባጀቡት ሰዎችና ከድንግልም በመጡት ሰዎች ምክንያት ጥቂት ውኃ በሚገኝበት በዚህ ሜዳ ላይ አረፍን። ምንም እንኳ ከባርዋ እስከ ሐርኪኮ ያለው ርቀት ከአስራ ሁለት ወይም እጅግ ቢበዛ ከአራ አምስት ሌግዋ ባይበልጥም ሳምንቱን በሙሉ ስንጓዝ ቆይተን ቅዳሜ ጥዋት በሐርኪኮ አጠገብ ድንኳን ጥለን ሠፈርን። ለኛ መርከቦች የሚያቀርበን ባሕር ነጋሹ ስለ ነበር እንዲሁም ከባርዋ አጅበውት ከመጡት ሰዎች ሌላ ወደ ሱዋኪን የሚሄዱት ሰዎች ገና ስላልመጡለት እነርሱን በመጠበቅ ወደ መርከቦቹ አልቀረብንም ነበር። እነዚህ ሰዎች እስከሚቀጥለው ሰኞ ድረስ በዚያ ቦታ አልደረሱም ነበር። ከመሸ በኋላ የኛን ሰዎች ሄደን አገኘናቸው። ሙቀቱ ከልክ ያለፈ በርትቶ ስለነበር ይልቁንም

በሰዉ ብዛት ምክንያት በድንኳኑ ውስጥ ወበቁ ከመጠን በላይ ስላፈነን ባሕር ነጋሹና ሹማምንቱ ዳስ እንዲጣል አዘዙ። ለኛም ለፖርቱጊዞቹ ለጥላ ያህል ሰፊ አጎበር ተከሉልን። መርከበኞቹ ፖርቱጊዞች በነፋሻው ላይ በባሕሩ ዳር ሠፈሩ። ሌሎቹም በደሴቱ ላይ ባሉ ጣርያቸው ጠፍጣፋ በሆኑ ቤቶች ውስጥ ገብተው አደሩ። ማክሰኞ ጥዋት ባሕር ነጋሹና መኳንንቱ ባንድነት ሆነው እየመሩ ወስደውን ከታላቅ ደስታና ምስጋና ጋር ለኤይቶር ደ ሲልቬይራ አስረከቡን። ለመርከበኞቹም ስንቅ ባሕር ነጋሹ ሃምሳ ፍሪዳ ብዙ ሙክት ዶሮችና አሣም አዘዘላቸው። የንጉሠ ነገሥቱ አምባሳደር ሌትና ቀን ተጉዞ በሚቀጥለው ሐሙስ ደረሰብን። የመጀመርያው መልእክተኛ እንደደረሰው በቅሎውን አስጭኖ ዝግጁ ሆኖ ትክክለኛውን ወሬ ይዞለት የሚመጣውን መልእክተኛ ይጠብቅ ነበር። ስለዚህ ይህ እንደደረሰው ሌትና ቀን ተጉዞ ሊደርስብን ቻለ። እኛ ፖርቱጊዞቹ ሐርኪኮ ድረስ ሄደን ስንቀበለው ባሕር ነጋሹም ለመርከበኞቹ ሊያስረክበው እዚያው ድረስ መጣ። በሚያዚያ 26-27 እና በግንቦት 3-4 የሚመጣውን ለመርከቦቹ ጉዞ የሚመቸውን የሞንሱንን ነፋስ በመጠበቅ ላይ ነበርን። ስለዚህ በዚያ ጊዜ ባንሄድ ኖሮ እስከ ነሐሴ ወር መጨረሻ ድረስ መጠበቅ ግድ ይሆንብን ነበር። በዚያ ሆነን ስንጠብቅ ሳለን ንጉሠ ነገሥቱ የፖርቱጊዞቹን መርከቦች በቀይ ባሕር መግባት በዘይላ በኩል ሰምቶ ስለነበረ አራት መልእክተኞች ልኮ ከቤተ መንግሥቱ ከሄዳችሁ ብዙ ጊዜ እልፎአልና ቅር መሰኘታችሁ ስለማይቀር በቶሎ ተመልሳችሁ ወርቅና ልብስ ውሰዱ፤ ወደ ፖርቱጋል ንጉሥም አስደስቼ እልካችኋለሁ አለን። እኛን ለመድረስ ሲሉ ባለፉበት ከተማ ሁሉ አዳዲስ በቅሎዎች እየለዋወጡ ሌት ከቀን በግስጋሴ የመጡት መልእክተኞች እንድንመለስ አጥብቀው ለመኑን። አምባሳደራችውንም እንዲመለስ ለመኑት። ቅር ብሎን የሄድን እንደሆነ ንጉሠ ነገሥቱ ስለማይደሰት ለመመለስ እንዲፈቅድልን ኤይቶር ድ ሲልቬራንም ለመኑት። ነገር ግን አሁን ካልሄድን ለወደፊቱ መርከብ የማይመጣልን መሆኑን እንዲሁም ለመመለስ ወይም ለመቆየት ነፋሱ ጊዜ የማይሰጠን መሆኑን በማስታወቅ በምንም ምክንያት ለመመለስ የማንችል መሆናችንን እኛም ኤይቶር ድ ሲልቬይራም ለመልእክተኞቹ ነገርናቸው። አምባሳደራቸውም ከፈለገ ለመመለስ

የሚችል መሆኑን ነገርናቸው። ይህም ጉዳይ ለአምባሳደሩ ተገልጾለት ነበር። ነገር ግን ብቻውን የተመለሰ እንደሆነ ለአንበሶች የሚጣል መሆኑን በመፍራት ፈጽሞ የማይሄድ መሆኑን እርሱም ለመልእክተኞቹ ነገራቸው። ስለዚህ ሁላችንም ተደሰትን፤ ነገር ግን መልእክተኞቹ ድካማቸው ከንቱ መሆኑን በመገንዘብ በጣም አዘኑ።

ክፍል ሁለት

በሚቀጥሎት ምዕራፎች ከኢትዮጵያ ወደ ፖርቱጋል ያደረግነውን ጉዞ ኀተታ አስከትላለሁ።

ምዕራፍ አንድ፤ ከምጽዋ ደሴትና ወደብ ተነሥተን ወደ ሆርሙዝ ስለመሄዳችን።

ሶስት ጋሌዎኖችና ሁለት ካራቬሎች የሚገኙበት የመርከብ ጓዳችን ሚያዚያ 28 ቀን 1526 ዓም መንገድ ጀመረ። ግንቦት አንድ ቀን በካማራን ደሴት እንደደረስር ነፋሱ ጠፋ። በዚያ ሆነን የነፋሱን መምጣት ስንጠብቅ ሳለን ንጉሣችን ወደ ኢትዮጵያ በመጀመርያ የላከውን አምባሳደር ድዋርት ጋልቫውን በዚያ ደሴት ላይ እንደ ቀበርነው ትዝ አለኝ። በሞተ ጊዜ እኔ በዚያ እገኝ ነበር። በቀብሩም ላይ ተገኝቼ ነበር። በዚያን ጊዜ ዳኛ የነበረው ሊቅ ጎምሽ ቴይሼራና እኔ ለወደፊቱ የሙዋቹ ዘመዶች የመጡ እንደሆነ ከዚያ ቦታ አጽሙን አውጥተው ወደ ክርስቲያን አገር እንዲወስዱት በማለት መቃብሩን ምልክት አድርገንበት ነበር። ስለዚህ ካሽከሬ ጋር ከመቃብሩ ድረስ ሄደን መቃብሩ ተከፍቶ አጽሙ በደንብ እንዲለቀም አዘዝሁ። ነገር ግን ከሶስት ጥርሶች በስተቀር ሌላ ምንም ስላልተገኘ ጥርሶቹን ባንድ ትንሽ ሣጥን ውስጥ ከትቼ ቅዱስ ሌዎን በተባለው እኔ

በነበርሁበት መርከብ ውስጥ አኖርሁት። በሙዋቹ ቤት ያደገ አሁን በነዚህ መርከቦች ውስጥ የንብረት ሹም ሆኖ ከሚያገለግለው ጋስፓር ድ ሳ ከተባለው ሰው በስተቀር የሚያውቅ ሰው አልነበረም። የሙዋቹን ተረፍ በመርከቡ ውስጥ እንዳስገባን ተስማሚ ነፋስ ነፍሶ መንገዳችንን ጀመርን። የዚያን ጊዜ የንብረት ሹሙ እንዲህ አለኝ፤ «ድዋርት ጋልቫው እግዚአብሔርን በማገልገል የሞተ ሰው ስለነበር ለርሱ ሲል እግዚአብሔር ተስማሚ ነፋስ ያነፍስልናል።» ከኤደን እንደተነሣን እስከ ግንቦት አሰር ቀን ድረስ ተስማሚ ነፋስ ይነፍስ ነበር። ከኤደን ሰላጤ በገባን ጊዜ ከሕንድ ወደዚህ የሚነፍሰው የክረምት ነፋስ ፊት ለፊት ገጠመን። በሁለተኛው ሌሊት ነፋሱ በጣም ስለበረታብን እርስ በርሳችን ለመተያየት ካለመቻላችን በላይ መርከቦቻችን ተጠፋፉ። ወዴት እንደምንሄድም አናውቀውም ነበር። እኔ በነበርሁበት ቅዱስ ሌዎን በተባለ መርከብ ላይ በሶስት ትልቅ ገመድ የታሠረ አንድ ጀልባ ነበር። ይህንም ጀልባ የሚነዳው አንድ ፈረንሳይ ነበር። ባራተኛው ሌሊት ማዕበሉ በጣም በርትቶ ስለነበር ሁላችንም በአደጋ ላይ የምንወድቅ መስሎን ነበር። እኩለ ሌሊት ሲሆን ጀልባው የታሰረባቸው ሶስት ገመዶች ስለተበጠሱ መርከቡ በጣም ተነቃነቀ። እንዲያውም ሁላችንም የሰጠምን መስሎን ነበር። የመርከቡ አዛዥ የፍሽካ ድምጽ ካሰማ በኋላ ጀልባውን ይነዳ ለነበረው ወጣት ነፍስ እንድንጸልይ የጸሎት መጽሐፍ አቀረበልን። በማግሥቱ ጥዋት የሙዋቹን ንብረት በሐራጅ ለመሸጥ ታስቦ ጠቅላላ ሃብቱና የነበረው አንድ ባርያ በ 120 ፓርዶሽ[1] ተገመቱ። በሆርሙዝ ወሽመጥ እስከንደርስ ድረስ በዚህ አኳኋን ተጉዘን ግንቦት 28 ቀን በመስቃጥ ወደብ ደረስን። መስቃጥ የሆርሙዝ ንጉሥ ግዛት ቢሆንም ለጌታችን ለፖርቱጋል ንጉሥ ግብር ይከፍላል።

በዚያ እንደደረስን ከመርከቦቻችን አንዱን (ካራቬሉን) በዚያ አግኝተነው ከማዕበሉ ጋር በመታገል ያሳለፉትን ጊዜ መርከበኞቹ ነገሩን። ከሶስት ቀን በኋላ ሌላ ካራቬል በዚያው ደረሰ። የዚያኑ ዕለትም አንድ ጋሌዎን ደረሰ። መርከበኞቹ በያንዳንዱ መርከብ ላይ የደረሰበትን የማዕበል ትግል ማውራት ጀመሩ። በመስቃጥ ወደብ ከደረስን ካስር ቀን በኋላ የጓዱ ሰንደቅ ዓላማ ያዥ የነበረው

ቅዱስ ዲኒሽ የተባለው ጋሌዎን ወደቡን ስቶ ወዲያ ወዲህ ሲንቀዋለል የኛ ሰዎች አዩት፤ በመስቃጥ ወደብ ላይ ሆነው የባሕሩን ወሽመጥ ይጠብቁ የነበሩ ሁለት ጀልባዎች ወዲያውኑ ወደ ጋሌዎኑ ገሠገሡ። በዚያ እንደደረሱ መርከበኞቹ በረሃብና በተለይም በውኃ ጥም በሞት አፋፍ ተኮልኩለው ስላገኙዋቸው ምግብና ውኃ ለመውሰድ በፍጥነት ወደ ወደቡ ተመለሱ። ጀልባዎቹ በዚያ አደሩ፤ በማግሥቱ ጥዋት የኛና ሌሎቹም የወደቡ መርከቦች ሁሉ ወደ ጋሌዎኑ ሄደው ከቀትር በኋላ ወደ ወደቡ አመጡት። የደረሰባቸውን ታላቅ ችግር በመግለጽ ማዕበሉ በኤደን ሰላጤ በር ላይ ሲደርሱ እንዳጋጠማቸውና ከዚያም እስከ ካምባያ ጠረፍ (ሕንድ) ድረስ ወስዶ ከዚያም ለመውጣት እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው ነገሩን። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ማዕበሉ ለብዙ ጊዜ ስለቆየ በማዕበሉ ላይ የጠላት መርከቦች በፍጹም አይገኙም ነበር። ሶስት ቀን ያለ ምግብና ያለ መጠጥ መቆየታቸውን ነገሩን። የዚህ መርከብ ጓድ ጠቅላይ አዛዥ ኤይቶር ደ ሲልቬይራ ሰዎቹ የታመሙ መሆናቸውን በማወቅ ከሁሉ አስቀድሞ የራሱን ውኃ በመሰዋት አያለቀሰ ለበሽተኞቹ ውኃውን በማደል ያሳየውን ታላቅ ርህራሄና ደፋርነት ገለጹ። እንዲያውም ይህን የመሰለ ታላቅ አደጋ በሰዎቹ ላይ የደረሰ መሆኑን ካወቀ በኋላ ወደ ክፍሉ ሄዶ ውኃ ሊጠጣ መርከበኞቹን ትቶ ሄደ ተብሎ እንዳይታማ በማለት ባይኑ እንቅልፍ ሳይዞር ከሰዎቹ ጋር ቁጭ ብሎ አደረ አሉ። የብሱን በመጀመርያ ባዩ ጊዜና እርዳታ በመጣላቸው ጊዜ በመርከቡ ውስጥ ለበሽተኞቹም ሆነ ለጤነኞቹ አንድ ጠብታ እንኳ ውኃ አልነበረም አሉ፤ ይህም እውነት ነበር። በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሁሉ እንሞታለን ብለው ተስፋ ቆርጠው ስለነበር ወደ ወደቡ ሊደርሱ መቻላቸው እንደታላቅ ተአምር የሚቆጠር ነበር። ይህንም ነገር ከአምባሳደሩ ከዶም ሩድሪጉ ደ ሊማና ከኢትዮጵያ አምባሳደር ከመስማቴ በላይ በጋሌዎኑ የመጡት ሰዎች ሁሉ ስለዚሁ ያወሩ ነበር። መርከበኞቹ በወደቡ ከደረሱ በኋላ ተመግበው ዕረፍት አደረጉ።

በመስቃጥ ወደብ ጥቂት ቀኖች ከቆየን በኋላ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና መርከቦቻችን በሙሉ የመስቃጥን ወሽመጥ

ከሚጠብቁት ጀልባዎች ጥቂቶቹ ከዚያ ተነሡ። ጉዞአችንን ወደፊት ከቀጠልን በኋላ የጌታችን የፖርቱጋል ንጉሥ ምሽግ በሚገኝበት በሆርሙዝ ከተማ ደረስን። በዚያም ያሕንድ ጠቅላይ ገዥ ሎፑ ቫሽ ድ ሳምፓዩን አገኘነው። በወደቡ በደረስን ጊዜ በምሽጉ የነበሩት መኳንንትና የልዩ ልዩ መርከቦች አዛገሮች ሌሎች ሰዎችና ጠቅላይ ገዥውም ከምሽጉ አጠገብ በውኃው ዳር መጥተው ተቀበሉን። ከዚህ በኋላ በምሽጉ ውስጥ በነበረው ቤተ ክርስቲያን ባንድነት ሄደን ጠቅላይ ገዥው ሁለቱን አምባሳደሮች እኔንና አንዳንድ የኤም ባሲውንም ሠራተኞች ሳመን። ከዚህ በኋላ ለያንዳንዳችን ወደተዘ ጋጀልን ቦታ ሄድን። በማግሥቱ ሁላችንም ባንድነት ሆነን ካስቀደስን በኋላ በጠቅላይ ገዥው ፊት ቀረብን። እኛ ወደ ኢትዮጵያ በሄድ ንበት ጊዜ ወደዚያ የወሰደንና ሕንድንም ይገዛ የነበረው ዲዮጉ ሎፕሽ ድ ስኬይራ ስለነበር ንጉሠ ነገሥቱ ለርሱ ደብዳቤ ጽፎለት ነበር። ነገር ግን አሁን በርሱ ፈንታ ሕንድን የሚገዛው ሎፑ ቫሽ ድ ሳምፓዩ ስለነበር ደብዳቤውን ሰጠነው። ከዚህም ሌላ ከወደፊት አምስት ከወደኋላ አምስት ከግራና ከቀኝ ትከሾቹ ሁለት በጠቅላላው አስራ ሁለት ጠፍጣፋ የወርቅ ልባድ የተያያዘበት አንድ የሐር ቀሚስ ሰጠነው። ንጉሠ ነገሥቱ ለዲዮጉ ሎፕሽ የላከው ይህ ወርቅ እያንዳንዱ ስፋቱ ያንድ ሰው የውስጥ እጅን ያለብስ ነበር። ጠቅላይ ገዥውም ለፖርቱጋል አምባሳደር ሁለት መቶ ፓርድዋ ለኢትዮጵያ አምባሳደር ሁለት መቶ ፓርድዋ ለኔም አንድ መቶ ፓርድዋ ሰጠን። ኤይቶር ደ ሲልቬይራ በሆርሙዝ ጥቂት ቀኖች ከቆየ በኋላ ከጅዳ ወደ ዲዩ የሚሄዱትን መርከቦች ሁሉ አስነሥቶ ሄደ። እነዚህ መርከቦች የሞንሱንን ነፋስ ተከትለው መጥተው ተስማሚ ነፋስ ሲመጣ ጉዞአቸውን ለመቀጠል የክረምቱን ወራት በኤደን ወደብ አሳለፉ። እኛ ግን ክረምቱ በደንብ ማለፉን እስክ ናውቅ ድረስ ከነበርንበት አልተነሣንም ነበር።

<u>ምዕራፍ ሁለት፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለዲዮጉ ሎፕሽ የጻፈው ደብዳቤ።</u>

ሁልጊዜ ለነበረው፤ መጀመርያም በማይገኝለት በእግዚአብሔር አብ ስም፤ የውቅያኖስ መሠረት ከመጣሉ በፊት ከሁሉ አስቀድሞ የከዋክብት ብርሃን በነበረው፤ ሳይታይ እርሱን በሚመስለው፤ በልጁ ስም፤ በሌላ ጊዜ ያለ ወንድ ዘር ወይም ያለጋብቻ እርሱ ብቻ በሚያ ውቀው ዓይነት በድንግል ማሕፀን ገብቶ ተፀነሰ። ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ወይም ከሰሜን ወደ ደቡብ ሳይል አስቀድሞ ያልነበረውን ምድርን ፈጥሮ ያለ ድጋፍ ወይም ያለ አውታር ባቆመው፤ መጀመርያ ከነበረበት ከአርያም ሆኖ ማናቸውንም ምስጢር በሚያውቀው በቅድ ስና መንፈስ በጰራቅሊጦስ ስም። እርሱ የመጀመርያ ወይም ሁለተኛ ሳይሆን ባንድ ቃልና ፈቃድ ማናቸውንም ነገረ የፈጠረ አምላክ የተባበረ ሥላሴ ነው። ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም፤ አሜን።

የጥምቀት ስሙ እጣነ ድንግል የሚያሰኝ፤ ዘውድ ከጫነ በኋላ ግን ንጉሥ ዳዊት የተባለው የኢትዮጵያ ግዛቶች ባለቤት፤ እግዚአ ብሔር ያፈቀረው የሃይማኖቱ ምሰሶ የዳዊት ልጅ፤ የሰሎሞን ዘር፤ የይሁዳ ዘር፤ የአምደ ጽዮን ዘር፤ የዘርአ ያዕቆብ ዘር፤ የበዕደ ማርያም ዘር፤ የናኦድ ልጅ የታላቂቱና የልዕልቲቱ የኢትዮጵያ ከተማ ንጉሥ ይህን ደብዳቤና ይህን ኤምባሲ ይልካል።

ይድረስ ለዲዮጉ ሎፕሽ ድ ስኬይራ የሕንድ ጠቅላይ ገዥ፤ የፖርቱጋል ንጉሥ ታዛዥ ሆነህ በተላክህበት የጦር ሜዳ ሁሉ ደጋግመህ ድል የነሣህ መሆንህን፤ ቁጥራቸው የበረከተ እስላሞች የማያስደነግጡህ በፈረስ ተቀምጠህ የሚደርስብህን ነገር ሳትፈራ እምነትህን ጋሻ አድርገህ የምትሄድ ሰው ነህ ማለትን ሰምቻለሁ። የተሸሸጉ ነገሮች እንኳ ድል የማይነሡህ፤ የወንጌል እውነትን መሣርያ የምታደርግ የመስቀል አርማን እጀታ የምትመረኮዝ መሆንህን

ሰምቻለሁ። ለጌታችን ለየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ሲል ደስታችንን ለዋጀልን ስለዚያ እምነት ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው። የጌትህን የንጉሥ አማኑኤልን መልእክት ለማድረስ ስትመጣ ምንም እንኳ በባሕር ላይ በነበርህበት ጊዜ ሞገድና ማዕበል ቢታገልህም በመርከብ ላይ ሆነህ ትዕግሥትህን ሳታጣ ገጸ በረከቱን በባሕርም በምድርም ይዘህ በመድረስህ፤ ያን ያህል ረጅም መንገድ አቋርጠህ አሕዛብንና እስላምን ለመግደል መምጣትህ በጣም እስደንቆናል። መርከቦችህ ወደተመሩበት ቦታ ሁሉ መሄዳቸው ታላቅ ተአምር ነው። አንድ ቀን ወይም ሌሊት እረፍት ሳታደርግ ሁለት ዓመት ሙሉ በባሕር ጉዞና በጦርነትም በብዙ ልፋት መቆየትህ በጣም አስደንቆናል። ቀኑ ሰዎች የሚሸጡበትና የሚገዙበት ወይም የሚጓዙበት ጊዜ ሲሆን ሌሊቱ ግን በቅዱሳት መጽሐፍት እንደተገለጸው የመኝታና የማረፍያ ጊዜ ነው። ከጥዋት እስከ ማታ ያለው ጊዜ ሰዎች ሥራቸውን የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው። አንበሳ በሌሊት መሬቱን እየጫረ እግዚአብሔር ምግብ እንዲያዝለት እየለመነ ያድራል። ፀሐይ ስትወጣ ግን ወደ ጉድጓዱ ይመለሳል። የሰዎችም ልምድ ከእንስሶች የተለየ አይደለም። እንስሶቱ ከመጀመርያ ጀምሮ በዓለም ላይ የሚኖሩ ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚለው እንተ እውነተኛይቱን እምነት በማፍቀርህ የሌሊት ወይም የቀን እንቅልፍ ድል አልነሡህም። እነዚህን ቃሎች ማነው ሊቃወም የሚችል? በሞትም ሆነ በሕይወት ከምናምንባት ከክርስቶስ ሃይማኖት ደዌም ሆነ ሥቃይ፤ ረሃብም ሆነ ጭካኔ፤ ሰይፍም ሆነ ጎራዴ ሊለዩን አይችሉም። ታላላቅ መኳንንትና ሃብታም ሰዎች በአምባሳደርነት መላካቸው ታላቅ ነገር ነው። ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን የለም። ከዚህም በላይ ሐዋርያው እንዲህ ይላል፤ «በጎንና መጥፎን ነገር በመታገስ ትህትናን የሚያሳይ ሰው የተባረከ ነው፤ በመጨረሻም የሕይወትን ዘውዱ ይጭናል፤ የልቡን ምኞት እግዚአብሔር ይስጠዋል።» ላንድ ነገር ምኞት ያላቸው ያንንም ለማግኘት የሚጥሩ ሰዎች አሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔርም የሚፈቅደው ሌላ ነገር ነው። እግዚአብሔር ሰውን ለመጥፎ ነገር አይመርጠውም። አምላክ የልብህን ምኞት እንዲፈጽምልህና በደህና ወደ ጌታህ ወደ ንጉሥ አማኑኤል እንዲመልስህ እመኝልሃለሁ፤ እንዲሁም በክርስቶስ ሃይማኖት የማያምኑትን ድል የነሣሃቸውን

አሕዛብ የዘረፉትን ሃብት አሸክመህ እየነዳህ ለመሄድ እንዲያበቃህ ምኞቴ ነው። ይህ ለሁልጊዜ እንዲሆን ለየሱስ ክርስቶስና ለቅዱስ ስሙ ሲሉ በብርድና በሙቀት፤ በድካምና በጥረት በመሰቃየት ሰማዕት የሆኑት ጭፍሮችህ እንዳንተው የተባረኩ ይሁኑ። አንተና እነርሱም የንጉሥ አማኑኤልን ፊት ለማየት ትችሉ ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳችሁ።

በኛ አገር አገባብህን ወሬ ሰማሁ። ይህ ወሬ እንደተሰማ ሰዎች በዘረፋ ላይ ባሉ ጊዜ እንደሚደሰቱት ሁሉ ታላቅ ደስታ ሆነ፤ ተመልሰህ መሄድህን በነገሩኝ ጊዜ ግን በጣም አዘንሁ። አምባሳደርህ ይመጣል ማለትን በሰማሁ ጊዜና እስካሁንም ድረስ መልካም ፈቃድህ ስለሆነ በጣም ተደሰትሁ። ያንዱ የእግዚአብሔር አብ ስም የጌታችን የመድኃኔ ዓለም የሱስ ክርስቶስ ስም የተባረከ ይሁን። ዝናህን ከሩቅ ሰማሁ፤ ከኔ ጋር ወዳጅነት በመጀመርህ እግዚአብሔር ይጠብቅህ። እኔ የምፈቅዳቸውን ነገሮች ብታስገኝልኝ እወዳለሁ። እንድታስገኝልኝም የምፈቅደው ቀጥሎ የተመለከቱትን ነው። የወርቅና የብር አንጥረኞች፤ ጎሬዴና ሌሎችንም የብረት መሣርያዎች እንዲሁም የራስ ጋሻ የሚሠሩ ባለእጆች፤ ግንበኞች፤ አታክልትና የወይን ተክልን ለመከባከብ የሚችሉ ባለሞያዎች፤ እንዲሁም ይህን የመሰለ ልዩ ልዩ ሞያ ያላቸው ሥራተኞች፤ ቤተ ክርስቲያኖችን በአረር ለመክደን የሚችሉ ባለሞያዎች፤ ቤቶችችን በስንበሌጥ ከመክደን እንድንድን የቤት መክደኛ ሸክላ ለማበጀት የሚችሉ ሠራተኞች። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሠራተኞች ሁሉ በጣም ያስፈልጉናል። ስለሌሉንም በጣም እናዝናለን። ነፍሱን እግዚአብሔር ይማርና አባቴ የተቀበረበት በሥላሴ ስም የሚጠራ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አሠርቻለሁ። ስለግድግዳዎቹ መልካምነት አምባሳደሮችህ ሊነግሩህ ይችላሉ፤ በቶሎ እንዲከደን ስለፈለግሁ በሰንበሌጥ አስከደንሁት። ስለዚህ ለያንዳንዱ ሞያ አሥር ሰው እንድትልክልኝ በእግዚአብሔር ስም እለምንሃለሁ። ስለዚህ የሠራተኞቹ ቁጥር ሊያንስ ወይም ሊበዛ አይገባውም። ሠራተኞቹ የፈቀዱትን ያህል ለመቆየት ይችላሉ ነገር ግን ለመመለስ የፈለጉ እንደሆነ የድካማቸውን ዋጋ ከፍዬ እንዲመለሱ እፈቅድላቸዋለሁ።

አሁን ደግሞ ሌላ ጉዳይ ላቀርብልህ እወዳለሁ። ከዚህ በፊት እስላሞችን መስለው በካይሮ ይንከራተቱ የነበሩትን ፈረንጆች እልክልሃለሁ። እነዚህን ሰዎች ወደክርስትና ሃይማኖት ያመጣሁዋቸው እኔ ነኝ፤ የዘይላን የአደንን፤ የምጽዋንና የሜካን መንገዶች ደህና አድርገው ስለሚያውቁ ወደተባሉት ቦታዎች ሊመሩህ ይችላሉ። ስለዚህ ደስ ይበልህ፤ በምኞትህ ያለው ሁሉ ደስ ያሰኘኛል። ይህን ደብዳቤ የጻፍሁልህ በምጽዋ ደሴት ላይ ምሽግ ለመሥራት ስለምትፈልግ እንድፈቅድልህ የጠየቅህ መሆንህን አምባሳደርህ ስለነገረኝ ነው። በምጽዋና በዳህላክ ላይ ቤተ ክርስቲያንና ምሽግ እንድትሠራ ፈቅጄልሃለሁ። በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ቄሶች እንድታስገባበት፤ ምሽጉንም የሚጠብቁና እነዚያን ርኩሶች የመሐመድ ልጆች የሚያስከትሉትን ሥጋት ለማስወገድ ብርቱ ጠባቂዎች እንድትልክ ፈቅጃለሁ። ይህን ጉዳይ ሳታከናውን ወደ ሕንድ እንዳትመለስ፤ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኑንና ምሽጉን ሳታሠራ እንዳታርፍ፤ ወይም ወደ ሕንድ እንዳትመለስ። ንጉሥ አማኑኤልና እኔ እንድንወዳጅ እግዚአብሔር ስለፈቀደ አንተ ስለምታደርገው ተግባር ሁሉ እኔና ጌታህ ንጉሥ አማኑኤል እናመሰግንሃለን። እነዚህ ሰዎች እስላሞችን ሳያስገቡ ክርስቲያኖች ብቻ ሆነው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ የሚገዙበትና የሚሸጡበት አንድ ገበያ ሥራላቸው። ይሁን እንጂ በዚያ ቦታ እስላሞች እንዲገዙ ወይም እንዲሸጡ ከፈለግህ አንተ ልትፈቅድላቸው ትችላለህ። ይህን በምጽዋ ካከናወንህ በኋላ ከዚህ በላይ እንደጠቀስሁት ወደዘይላ ተመልሰህ ቤተ ክርስቲያንና ምሽግ አሠራ። ዘይላ ወደ ኤደን ወደ አረብ አገርና ወደሌሎችም ቦታዎች የሚሄደው ምግብ ሁሉ የሚተላለፍበት ወደብ ስለሆነ እነዚያ አገሮች ከዘይላ የሚመጣው የተቋረጠባቸው እንደሆነ ምንም እንደማይኖራቸው የታወቀ ነው። ስለዚህ ይህን የላክሁብህን እርምጃ የወሰድህ እንደሆነ ሕዝቡ ስለሚራብ ሰው ሳይሞትብህ ወይም ውጊያ አስፈላጊ ሳይሆን ኤደንን የአረብ አገርንና ሌሎችንም ቦታዎች በእጅህ ልታስገባ ትችላለህ። እስላሞችን ለመውጋት በፈለግህ ጊዜ የሚያስፈልግህን ሁሉ ጠይቀኝ፤ እኔም ፈረሰኞችና ቀስተኞች እልክልሃለሁ፤ ስለዚህ እኔና አንተ በመተባበር እስላሞችንና አሕዛብን ለሃይማኖታችን ድል እንነሣቸዋለን። ወደ ሕንድ አገር በተመለስህ

ጊዜ የምጽዋ ወደብ ሃላፊ እንዲሆን ዶም ሩድሪጉ ድ ሊማን በዚያው ተወው፤ አንዳንድ የሚያጠራጥር ነገር በተገኘ ጊዜ አምባሳደሮችህ መሄዳቸውንና መምጣታታቸውን እያቋርጡ። እነዚህ አሁን የሚሄዱት መጀመርያ እዚህ የመጡት ናቸው። ወደዚህ አገር ተልከው የመጡት ያንተ ሰዎች ሁሉ ምንም እንኳ ጉድለት ቢኖርባቸውም እርስ በርሳቸው የሚዋደዱ ታላላቆችና መልካም ሰዎች ናቸው። ስለዚሁ ደግነታቸው ለሁሉም በተለይም ለዶም ሩድሪጉ ደ ሊማ ወሮታቸውን ብትከፍላቸው መልካም ነው። ዶም ሩድሪጉ አንዳንድ ጊዜ ከሚያደርገው ስህተት በስተቀር መልካም ሰው ነው፤ ንግግር የማያበዛ ከሌሎቹ ሁሉ የተሻለና ጓደኞቹም የሚያምኑት የተባረከ አገልጋይህ ነው። አባ ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ እግዚአብሔርን የሚያፈቅር ታማኝና ቅን ሕሊና ያለው ቅዱስ ሰው ስለሆነ ከሌሎቹ ሁለት ጊዜ የሚበልጥ ምስጋና አቅርብለት። ጠባዩን ስለማውቅ ያገረ ገዥነት ማዕርግ ሰጥቼው ይህንኑም ማዕርግ የሚያረጋግጥለት አንድ መስቀልና አንድ ዘንግ ሰጥቼዋለሁ። ከዚህም በላይ በኛ አገር ያንድ ገዳም ሃላፊ አድርገነዋል። ስለዚህ ለሹመት የሚያስመርጥ ጠባይ ያለው ሰው ስለሆነ የምጽዋና የዘይላ እንዲሁም የቀይ ባሕር ደሴቶችና የኛንም አገር ድንበሮች እንዲገዛ ሹመው። ጸሐፊው ዮሐንስ ኤሽኮላርም ሁሉጊዜ ንጉሡን የሚያገለግል ቅን ሰው ስለሆነ ይህን ደብዳቤና ሌሎቹንም የሚደርሱህን ዕቃዎች ስለረዳ የሚገባውን ወሮታ እንድትሰጠው። ሌሎችም የኤምባሲው ሠራተኞች ከትንሽ እስከ ትልቅ በሚገባቸው መሠረት ለያንዳንዳቸው ወሮታቸውን ክፈላቸው። በጎ ምግባርን ለመፈጸም በምታደርገው ጥረት እግዚአብሔር ሰላሙን ይስጥህ። ላንተና አብረውህ ላሉት ሁሉ እግዚአብሔር በጎ ነገር ያድርግላችሁ። ለሁሉም በጎ ምግባር ፈጽምላቸው፤ አንተንና እነርሱንም እግዚአብሔር በፀጋው ብርሃን ይምራችሁ። እርስ በርሳቸው የሚዋደዱትንና እንዲሁም ለማድረግ የሚጥሩትንም ወንድሞቻችንን እግዚአብሔር ይርዳቸው። እግዚአብሔር ከነርሱ ጋር ነው። እግሮቻችሁ አንድ ምድር ይርገጡ፤ ከመጥፎ ዓይን ያድናችሁ፤ እናንተን ከባሕር ሞገድ መርከቦቻችሁንም ከማዕበል ይጠብቃችሁ፤ ሌትም ሆነ ቀን በማናቸውም ሰዓት በክረምትም በበጋም እግዚአብሔር ጤንነታችሁን ይጠብቅላችሁ፤ ለዓለም ወለዓለም አሜን።

በረከቴን እልክልሃለሁ፤ ነገር ግን ሁልጊዜ እንደማደርገው ይህን በረከት የምልክልህ በዚህ ደብዳቤ ብቻ አይደለም። በያንዳንዱ የክርስቲያን መኖርያና አባቶቻችንም በሠርዋቸው ቤተ ክርስቲኖች የምንጸልየው ጸሎት እንዲህ ይላል። ለስግደት ሲሉ ባሕሮችን ወንዞችንና ሐይቆችን መጥፎ መንገድንም አቋርጠው ለሚመጡ ወንድሞቻችን ደህንነት ለእግዚአብሔር አምላክና ለልጁ ለየሱስ ክርስቶስ እንጸልያለን። ሁሉም ያንተው ናቸው፤ እግዚአብሔር በሰላማዊ ባሕር ይምራቸው፤ እግዚአብሔር አምላክ ሁሉንም ይጠብቃቸው። ዲያቆኖቹ ይህን ሲጸልዩ ቄሶቹ ደግሞ ቀጥሎ የተመለከተውን ይላሉ። እግዚአብሔር ከሁሉም ጋር ነውና ከናንተም ጋር ይሁን፤ ማናቸውንም በጎ ነገር እንዲሰጠን እግዚአብሔርን እንለምናለን። ወንድሞቻችን ለጊዜው በአደጋ ላይ ይገኛሉ፤ በሚያስፈልጋቸው መንገድ ለስግደት ይመጣሉ፤ እኛም አሁን የሚያስፈልገንን አግኝተናልና ይህንኑ ስጠን አምላክ ሆይ። ከዚህ በኋላ ዲያቆኖቹና ምዕመናኑ እንዲህ ይላሉ፤ አምላክ ሆይ ይቅር በለን። ሶስተኛው ቄስ እንዲህ ይላል፤ እግዚአብሔር በደህና በሰላማዊ ባሕር ያድርሳቸው፤ በሚመኙት አኳኋን እግዚአብሔን በደስታና በሰላም ከዘመዶቻቸው ይቀላቅላቸው። የልጁን የየሱስ ክርስቶስን ደስታ ለማየት ያብቃቸው። እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን፤ እናንተም ከርሱ፤ አሁንና ለዘለዓለም የሁልጊዜም ፀጋ ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሁኑ። ለዓለም ወለዓለም አሜን።

ስለዚህ በማናቸውም የቅዳሴ ሰዓት እጣን እየተጨሰ በየቤት ክርስቲያኑ ሁሉ ላንተ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ይጸለያል። የሚጸለየውም እግዚአብሔር በስግደታችን ጊዜ ከኛ ጋር እንዲሆን ነው። ይኸውም ስግደት ወደናንተም ሆነ ወደኛ የሚመጣልን ባሕር አቋርጦ ነው። ስለዚህ ደህንነትን እንድታገኙና መጥፎ ሰዎችንም ለወቃወም እንድትችሉ እንዲሁም አጉል ሃሳብ እንዳይገባችሁ ጸልዩ። በጌታችን በየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት የማያምኑትን እስላሞችንና አሕዛብን ለማጥፋት ስትመጡ ለጦርነት የሚያስፈልገውን ያህል ብዙ ስንቅና ወርቅ ሰውም እሰጣለሁ። ይህ እርዳታ የሚሰጠው በምጽዋ ብቻ ሳይሆን በዘይላና በአዳልም ጭምር እነዚያን ርኩሶች ከሐዲዎች የመሐመድ ልጆች ለመውጋት ለሚደረገው ጦርነት ሁሉ ነው። በእ

መቤታችን በቅድስት ማርያም እርዳታ እኔ ከዚህ በፊት ድል ነሥቻቸዋለሁ። አሁንም ባንድነት ድል እንነሣቸዋለን። እናንተ በባሕር ሆነን በመተባበር በሥላሴ ብርታት ወደፊት እንሄዳለን።

ምዕራፍ ሶስት፤ ከሆርሙዝ እስከ ኮቺም ድረስ ወደ ሕንድ ስላደረግነው ጉዞ።

ከሕንድ ጠቅላይ ገዥ ከሎፑ ቫሽ ድ ሳምፓዩ መርከብ ጓድ ሆነን ከሆርሙዝ ተነሣን፤ ከርሱ ጋር የሄድንበት ምክንያት ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ከኢትዮጵያ ያመጣን ኤይቶር ደ ሲልቬይራ በክረምቱ ወራት ምክንያት በአደን ወደብ ይገኙ የነበሩትን ከሜካ የመጡትን መርከቦች ለመጠበቅ ጋሌዎኖቹን አስነሥቶ በመሄዱ ምክንያት ነው። ከሆርሙዝ ወሽመጥ ስንወጣ ማዕበል በሌለ ጊዜ ብቻ ሊያሳልፍ የሚችለው የሕንድ ክረምት ገጥሞን ነበር። በሕንድ እንደደረስን የጌታችን የፖርቱጋል ንጉሥ ግዛት በሆነው በሻውል ምሽግ ደረስን። ይህ ሻውል የተባለ አገር በመልማት ላይ የሚገኝ ከካምባያ የሚመጣ ብዙ ስንዴ የሚገኝበት ላሞችና በጎች፤ ዶሮችና ልዩ ልዩ ዓይነት አሦች የሚገኙበት ብርቱ አገር ነው። ብዙዎቹ አሦች በሕንድ የፖርቱጋል ንጉሥ እንደራሴ ልጅ ዶም ሎሬንሶ ዳልሜዳ መርከብ በተጋጨበት የባሕር ሰላጤ ሲደርሱ ይሞታሉ። ከዚህም በላይ ፖርቱጌዞቹ ያለሙት ብዙ የሕንድ በለስና ልዩ ልዩ ፍራፍሬዎች ይገኛሉ።

እኛ ከደረስን ከጥቂት ቀኖች በኋላ ከሜካ የመጡትን መርከቦች ይጠብቅ የነበረው ኤይቶር ደ ሲልቬይራ ብዙ ወርቅ የተጫኑ ሶስት ታላላቅ መርከቦች ማርኮ መጣ። እነዚህ መርከቦች ከሕንድ ሸቀጥ ለመግዛት የሚመጡ ነበሩ። ከመርከቦቹ ጋር የተማረኩት እስላሞች ወጣቶቹ (ምሽጎቻችን ሁሉ በእስላሞች እንደተመሉ ናቸው) እያንዳንዳቸው አሥር ክሩዛዱሽ ተገምተው በፖርቱጋል ንጉሥ

ጋሌዎኖች ውስጥ እንዲያገለግሉ ተወሰዱ። ሌሎቹንም ሽማግሌዎቹንና በጋሌዎኖቹ ውስጥ ለማገልገል የማይችሉትን በአፈላማ ለመያዝ ወይም ሊያገለግሉት የፈለገ ሰው እንዲገዛቸው በማለት እያንዳንዳቸው በአሥር ክሩዛዱሽ ተገመቱ። ለመሸጥ ከተገመቱት ውስጥ ብዙ አይሁዶች ነበሩ። ከነርሱም አንዱ በአረብ አገር ፋርጣቅ በተባለ ቦታ ጠፍተው የነበሩትን ፖርቱጊዞች በቤቱ ተቀብሎ አክብሮ ያስተናገደ ነበር። ፖርቱጊዞቹ ወደሆርሙዝ የሚወስደውን መንገድ በመፈለግ ጠፍተው ግራ ገብቶዋቸው ሳሉ እግዚአብሔር ወደዚህ አይሁድ ቤት መራቸው። አይሁዱ ተቀብሎዋቸው ምግብና መጠጥ ልብስም ከመስጠቱ በላይ ለመንገዳቸው የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ ሰጣቸው። የዚያ አይሁድ በጎ ተግባር ሳይካስ እንዳያልፍ እግዚአብሔር ስላልፈቀደ እንዳጋጣሚ የዚያን ሰው እርዳታ ከተቀበሉት ፖርቱጊዞች መካከል አንዱ በዚያ ይገኝ ስለነበር አይሁዱ ከሌሎቹ ጋር ታሥሮ እንደተኛ አገኘው። ይህ ሰው የትውልድ አገሩ ቪዜው (ፖርቱጋል) የነበረ አንድ ድኃ ሰው ነበር። የአይሁዱን ርህራሄ በማሰብ ይህ ሰው በሐዘንና በበጎ ሐሳብ ተማረከ። ወዲያውኑ ወደ ጠቅላይ ገዥው ሄዶ ለርሱና ለሌሎቹም ፖርቱጊዞች በፋርጣቅ ግዛት ትልቅ አቀባበል ያደረገላቸውና ነፍሳቸውን ያዳነው አይሁድ ኤይቶር ዳ ሲልቬይራ ከያዛቸው እስላሞች ጋር በግዞት የሚገኝ መሆኑን ነገረው። ስለዚህ አይሁዱ በጋሌዎኑ ውስጥ ለማገልገል ዕድሜአቸው ከማይፈቅድላቸው ውስጥ ስለሆነ ለሌሎቹ ፖርቱጊዞች በተፈቀደው አኳኋን ለርሱም አይሁዱ በአሥር ክሩዛዱሽ ተገምቶ እንዲሸጥለትና ገንዘቡንም ከደሞዙ ላይ እየተቀነሰ ለመክፈል እንዲችል ይፈቀድለት ዘንድ ጠየቀ። ወዲውኑ ጠቅላይ ገዥው ወደ አይሁዱ መልእክተኛ ልኮ በዚያ ቁመው ከሚገኙት ሰዎች መካከል የሚያውቀው ሰው እንዳለ እንዲመርጥ ጠየቀው። አይሁዱም በዚያው የነበሩትን ሁሉ ከተመከለተ በኋላ በአገሩ እንደ ነበር ከተቀበላቸው ፖርቱጊዞች መካከል ያን የቪዜው ተወላጅ አስታወሰ። በዚያኑ ጊዜ አይሁዱ ለፖርቱጊዞቹና በዚያም አደገኛ ጉዞ ላይ አብረዋቸውም ለነበሩት እስላሞች ሁሉ በጎ ምግባር ስላደረገላቸው ለዚሁ ወሮታው እንዲሆን በማለት አይሁዱን ነፃ አውጥቶ ለዚያ ድኃ ፖርቱጊዝ ሰጠው። ይህ ሰው የአይሁዱን እጅ ይዞ ወደጋሌዎኖቹ

ወስዶት ለርሱና አብረውትም ለነበሩ ለሌሎች ፖርቱጊዞች ያደረገላቸውን ወሮታ ነግሮአቸው በምጽዋት ስም ሃምሳ ፓርዱዋሽ ሰበሰበለት። ከማናቸውም ዓይነት ተግባር ይልቅ የበለጠ ምስጋናና ወሮታ የሚገባው ለፖርቱጊዞቹ የተደረገው በጎ ተግባር በመሆኑ ክርስቲያኖቹ፤ እስላሞቹና አይሁዶቹም በሙሉ በግልጽ አስታውቀው ለወደፊቱ በያገራቸው እርዳታ ፈላጊዎች ፖርቱጊዞችን ያገኙ እንደሆነ የሚረዱዋቸው መሆናቸውን ተስፋ ሰጡ። ከዚህ ቦታ ተነሥተን በቅድስት ካተሪና በዓል ዋዜማ ዕለት ቅዳሜ ሕዳር 25 ቀን በጎዋ ከተማ ደረስን። ይህች ከተማ ከእስላሞች የተወሰደችው በቅድስት ካተሪና በዓል ዕለት ስለነበር በዚሁ ቀን እሁድ ዕለት ትልቅ ክብረ በዓል ተደርጎ በፖርቱጋል በአካለ ክርስቶስ (ኮርፑስ ክሪስቲ) በዓል የሚደረጉትን የመሰሉ ልዩ ልዩ ውድድሮች ተደረጉ። የኢትዮጵያ አምባሳደርና አብረውትም ከመጡት መነኩሴዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ያን የመሰለ አከባበር በማየታቸው ስለናንተ ክርስቲያንነት በበለጠ ልናምን ችለናል አሉን። በዚያች ከተማ ከሶስት ቀን በላይ አልቆየንም። የኢትዮጵያ አምባሳደር በጎዋ ከተማ ሶስት ባሮቹን ለትምህርት ተዋቸው። ሁለቱ ሰዓሊነትን ሁለቱ ደግም ጥሩንባ ነፊነትን እንዲያጠኑ ስለነበር የተዋቸው ምግባቸውና ትምህርታቸውም እንዳይጓደልባቸው ጠቅላይ ገዥው አዘዘ። ወደ ከናኖር ሄደን በዚያም ስድስት ቀን ቆየን። ማቴዎስ በያዕቆብ[1] ስም ያሠራውን ቤት ክርስቲያንና በዚያም ይገኝ የነበረውን መልካም መቃበሩን ባዩ ጊዜ በጣም ተደሰቱ።

ከዚህ ከናኖር ከተባለ ከተማና ምሽግ ተነሥተን በመርከብ ወደኮችም ተጉዘን በዚያም እንደደረስን ከዚህ በፊት እንደገለጽሁት ወደ ኢትዮጵያ ሲሄድ በመንገድ ሙቶ በካማራን ደሴት የተቀበረውን አጽሙን ያመጣሁትን የአምባሳደር ድዋርት ጋልቫውን ልጅ አንቶንዩ ጋልቫውን አገኘሁት። ወዲያውኑ ይህን ሰው መልዕክተኛ ልኬበት ያባቱን አጽም ያመጣሁለት መሆኔን ነገርሁት። እርሱም በጣም የተደሰተ ከመሆኑ በላይ አጽሙን ተቀብሎ በጉዞ ፍትሐት ሊያስቀብረው ስለፈለገ ከመርከቡ እንዳላወጣው ለመነኝ፤ እንዳሰበውም ብዙ ካህናት አስጠርቶ ጥዋፍ እየተበራ አጽሙን በታላቅ ክብር ተቀበለኝ። ከዚያም በኋላ ብዙ ከረጢት ስንዴና ብዙ በርሜሎች የወይን ጠጅ

ስጦታ አቅርቦ አባቱን በሚገባ አኳኋን በቅዱስ እንጦንዩስ ገዳም አስቀበረው። መርከበኞች ሬሣን አሣፍረው መሄድ ስለማይወዱ አጽሙ የመጣበት ሣጥን በገዳሙ የቀረ ለማስመሰል በመሠውያው በስተቀኝ በኩል አንድ ፉካ ቆፍረው በዚው ቀበሩት፤ ሰዎቹ ከሄዱ በኋላ ግን አውጥተው ወደውጭ አስቀመጡት። አንቶንዩ ጋልቫው ወደፖርቱጋል የሚሄድ ያንድ መርከብ አዛዥ ስለነበር ያባቱ አጽም የነበረበትን ሣጥን በመርከቡ ውስጥ አኖረው። በኮችም የቆየንበት ጊዜ ሶስት መርከቦችን በመጫንና የሚሄዱትንም ሰዎች በማሰናዳት አለፈ። እያንዳንዱ መርከብ በርበሬና ቅርንፉድ ከተጫነ በኋላ በተጨማሪ ዝንጅብል፤ ብስኩት፤ የዘንባባ ጠጅ፤ ባሩድና ስንቅም ለመጫን ሰላሳ ሌግዋ ርቆ ወደሚገኘው ወደካናኖር ሄደ። በጥር ወር መጀመርያ ሶስቱም መርከቦች በዚያው ተደርድረው ቆይተው አንደኛው ወዲያውኑ መንገድ ጀመረ።

ምዕራፍ አራት፤ ከካናኖር ወደ ሊዝቦን ስላደረግነው ጉዞና በመንገድም ስለገጠሙን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች።

ከኮችም ወደብ ከተጫኑት መርከቦች ውስጥ በመጀመርያ ከካና ኖር በጥር አራት ቀን 1527 ዓም ወደ ፖርቱጋል መንገድ የቀጠለው በትሪሽታው ቫሽ ደ ቬይጋ ይታዘዝ የነበረው አምባሳደር ዶም ሩድሪጉ ደ ሊማና የኢትዮጵያ አምባሳደር ሊቀ ካህናቱ ይጓዝብት የነበረው መርከብ ነበር። ይህ መርከብ ለመንገዱ የሚያስፈልገውን ማለት ዝንጅብል፤ ብስኩት፤ አረቄና አሣ ተጫነ። በአንቶንዩ ጋልቫው ይታዘዝ የነበረው እኔ የነበርሁበት መርከብ ደግሞ የመጀመርያው መርከብ ከተባለው ወደብ ከተነሣ በኋላ ደርሶ ወዲያውኑ ተዘጋጅተን ወደ ፖርቱጋል ጉዞአችንን ጥር 18 ቀን ጀመርን።

በኋላ እንደ ሰማሁት በመጨረሻ የተነሣው መርከብ ከኛ በኋላ አሥራ አምስት ቀን ወይም በመጀመርያ ከተነሣው መርከብ ሃያ

ዘጠኝ ቀን ዘግይቶ ነበር። መርከቦቹ ተጠባብቀው አብረው ለመሄድ ሳይቃጣሩ እያንዳንዳቸው አቅማቸው እስከሚፈቅድላቸው ድረስ በግሥጋሴ የባሕር ጉዞዋቸውን ቀጠሉ። በመርከባችን ሰገነት ላይ የነበረ የኛ ሰው ሚያዚያ ሁለት ቀን ጥዋት እንዲህ የሚል ቃል አሰማን፤ «ከወደፊታችን ሁለት ሌግዋ ያህል ርቆ አንድ መርከብ ይሄዳል።» ይህ ቃል በተሰማ ጊዜ በውቅያኖሱ መካከል ስለነበርን መርከቡ የማን መሆኑን ለማወቅ ተኝተው የነበሩትና ቁጭ ብለን የነበርነው ባንድነት በመንጋጋት ወደ መርከቡ ሰገነት ወጣን። ምንም እንኳ ጊዜው አጣርቶ ለማየት የማይቻልበት ቀን ቢሆንም ያ መርከብ ወደ ፖርቱጋል ለመሄድ ከሕንድ ከተነሡት መርከቦች አንዱ መሆኑ ተረጋገጠ። ወዲያውኑ አንድ መርከብ ከወደኋላችን የሚከተለን መሆኑን በሰገነቱ ላይ የነበረው ሰው ነገረን።

በዚህን ጊዜ ከፊታችን የነበረው መርከብ የኛን መለጠቅ በማየት ቁሞ ጠበቀን፤ እኛም ከሱ አጠገብ ከደረስን በኋላ የኋላኛውን መርከብ እንድንጠብቀው ተሰማምተን ከመሸ በኋላ ደረሰብን። ሶስቱ መርከቦች በተቀላቀሉ ጊዜ በመርከቦቹ መካከል ታላቅ ደስታ ሆኖ ስለጉዞዋችን መጠያየቅ እንዲሁም የፊተኛው መርከብ በምን ምክንያት ወደፊት እንደቀጠለ መጠየቅ ጀመርን። ሁላችንም አንዳች አደጋ ሳያገኘን በእግዚአብሔር ፈቃድ በጤንነት በመድረሳችንና ለዚሁም አምላክን የምና መሰግን መሆናችንን መወያየት ጀመርን። ከዚህ በኋላ መንገዳችንን ቀጥለን ሶስት ቀን አብረን ተጓዝን። በአንቶንዩ ጋልቫው ይታዘዝ የነበረው እኔ የነበርሁበት ሳንታ ማርያ ዱ ኤሽፒኙ የተባለው መርከብ ቀስ እያለ ስለነበር የሚሄደው ሌሎቹን ለመለጠቅ አልቻለም ነበር። ስለዚህ ከፊተኞቹ መርከቦች አንደኛው ጉዞውን ሲቀጥል ሌላው ግን ሊያነጋግረን ቁሞ ጠበቀን። በዚያ በደረስን ጊዜ ሰላምታ ተሰጣጥተን እንዲህ አለን፤ ሌላው መርከብ ቀድሞ ስለሚሄድ ልንጠብቃችሁ አልቻልንምና ይቅርታ አድርጉልን፤ ይልቁንም መርከባችሁ በጣም ቀስ ብሎ ስለሚሄድ ወደ ፖርቱጋል የምትሄዱ አይመስለንም። የመርከቡ አዛዥ ይህን ቃል ተናግሮን ጥሎን ስለሄደ በጣም አዘንን።

እኛም ውኃ ለመጫን ወደ ሳንታ ሄሌና ደሴት አመራን። ቀድመው የሄዱት ሁለቱ መርከቦች ይህችን ደሴት ጎብኝተው ነበር ያለፉት። የትንሣኤ በዓል ዕለት ማለት ሚያዚያ 21 ቀን 1527 ዓም ለሰኞ አጥቢያ ከመንፈቀ ሌሊት በኋላ በደሴቲቱ አጠገብ ደረስን። ወዲያውኑ ከደሴቲቱ ወደ ውቅያኖሱ የሚነፍስ ኃይለኛ ዝናም መጣል ጀመረ። የዝናሙን አመጣጥ በመመልከት አንዳንዶቹ በዚያን ሰዓት በደሴቲቱ ደረስን አሉ። ሌሎቹ ደግሞ ገና አልደረስንም አሉ። ነገሩን ሳናጣራ በመጠራጠር ጥቂት ቀኖች አለፉ፤ ነገር ግን ደሴቲቱን አልፈን መሄዳችንንና ውኃችንም ሊያልቅ የደረሰ መሆኑን ተረዳን። ውኃ ለመቆጠብ ስንል ምግባችንን አልቀቀልንም ነበር። የዚያኑ ጊዜ የእግዚአብሔር ምሕረት ስለወረደልን ሶስት ቀንና ሌሊት ብርቱ ነጎድጓድና ዝናም ስለጣለ በመርከቡ የሚጫን ሶስት ቀርበታ ውኃ፤ እንዲሁም ለኔም ሶስት ቀርበታ ተጠራቀመ። ከዚህም በላይ እያንዳንዱ መርከበኛ የግል ዕቃው የሚችለውን ያህል አጠራቀመ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ምግባችን አልተጓደለብንም ነበር።

በቴርሴራ[1] ደሴት አጠገብ በደረስን ጊዜ አንድ መርከብ በማየታችን የፈረንሳይ መርከብ መስሎን በጣም ደነገጥን። መርከቡ ከደሴቲቱ ወደ መካከል ውቅያኖስ ይሄድ ነበር። እኛም በተቻለን መጠን ወደ ጠረፉ ቀረብን። በመርከባችን ሰገነት ላይ የነበሩት የኛ ሰዎች በኳንኳ ሆነው ነፍሳቸውን ለማዳን ካንድ መርከብ ወጥተሙ ወደ ጠረፍ የሚቀዝፉ ሰዎችን ስላዩ ከሕንድ ያመጣነውን በመርከባችን ላይ ይገኝ የነበረውን ኳንኳ ወደባሕር ጥለው ጥቂት መርከበኞችና ረዳቶች ወደሰዎቹ ሄደው ዘጠኝ ሰዎች ማለት አምስት ፈረንጆችና አራት ባሮች በአደጋው ምክንያት በጣም ተጎድተው ነፍሳቸውን ሳያውቋት አገኙዋቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ኳንኳው ገንዳ መስሎ ካንድ ረጅም ግንድ ተጠርቦ ስለተሠራ ነው። እነዚህን ሰዎች አነባብረው ወደኛ አመጡዋቸው፤ በኛ ዘንድ በደረሱ ጊዜ ሬሶች ነበር የሚመስሉት። የኛ ሰዎች ወዲያውኑ ልብሳቸውን አውልቀውላቸው ደረቅ ልብስ አልብሰዋቸው አንዳንዶቹን በአልጋ ሌሎቹንም በእሳት ዳር አስተኙዋቸው። ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ ከሶስት ሰዓት በኋላ አንዳንዶቹም

ከአራት ሰዓት በኋላ ሌሎቹም በማግሥቱ ነፍሳቸውን አውቀውት መነጋገር ቻሉ።

በማግሥቱ ጎህ ሲቀድ በቴርሴራ ወደብ ደርሰን ወደ ወደቡ የሚመጡትን ወራሪ መርከቦች የሚጠብቁትን መርከቦች አየን። የኛ መርከቦች ወደ ደሴቲቱ ሲገሰግሱ በማየት የፈረንሳይ መርከቦች መስለናቸው እነርሱም ደንግጠው ወደኛ ሊመጡብን ነበር። ከውቅያኖሱ መካከል ያገኘናቸው እነዚያ ሰዎች ነፍሳቸውን ካወቁ በኋላ እነማን መሆናቸውን በመግለጽ ከኛ ጋር በነበረው ባንዱ በፖርቱጋል መርከብ ውስጥ ሲጓዙ የነበሩ ባንድ ደሴት አጠገብ በደረሱ ጊዜ ዶሮ ለመግዛት በኳንኳ የተላኩ የነበሩ መሆናቸውን ነገሩን፤ ወደ ደሴቲቱ ሲሄዱ ኳንኳው በመገልበጡ መርከቡ የት እንደደረሰ ያላወቁ መሆናቸውን ጨምረው ገለጹልን። መልሕቃችንን ተክለን በወደቡ አምስት ቀን ከቆየን በኋላ የተባሉት ሁለት መርከቦች በዚያው ደርሰው በመንገድ መሳሳት ምክንያት ከየብሱ ብዙ ርቀው የተጓዙ መሆናቸውን አስረዱን፤ እንዲያውም ንጉሣችን የፖርቱጋል ንጉሥን ባያስቡና የፈረንሳይ መርከብን ባይፈሩ ኖሮ ወደ ፖርቱጋል ጉዞዋቸውን ለመቀጠል ቆርጠው የነበሩ መሆናቸዋን ነገሩን። እግዚአብሔር እነርሱንና ባሮቻቸውን እኛንም በደህና በዚያ ስላደረሰን ምስጋናችንን ከማቅረባችን በላይ መርከባችን ወደኋላ በመቅረቱ ምክንያት ትተውን በመምጣታቸው በመጸጸት ይቅርታ እንድናደርግላቸው በእግዚአብሔር ስም ለመኑን። የቅዳሜ ስዑር ዕለት የሳንታ ሔሌናን ደሴት ማለፋቸውን ነገሩን፤ እኛም በማግሥቱ ማለት በትንሣኤ ዕለት በብርቱ ዝናም በዚያው ማለፋችንን ነገርናቸው። እነርሱም ባለፉበት ሌሊት በዚያ ቦታ ዝናም መጣሉን ነገሩን።

በባሕር ኃይላችን ደንብ መሠረት ባንድ ቦታ ሆኖ መጠባበቅ የተለመደ ነገር ስለነበር ከሚናሽ ጀራይሽ[2] የሚመጣ አንድ ካራቬል መርከብ ከቅዱስ ቶማስና ከካፕ ቬርድ ደሴቶችም ከብራዚልም የሚመጡ መርከቦችን በመጠበቅ በቴርሴራ ደሴት አስራ ስምንት ቀን ቆየን። በዚያ የነበሩት ካራቬል መርከቦች የፈረንሳይ መርከቦች

ሳያስፈራሩዋቸው ያለሥጋት ከኛ ጋር ተቀላቅለው እንዲሄዱ ተወሰነ። ምንም እንኳ ይህች ደሴት የስንዴ እናት ብትሆንም ዝናሙ በየቀኑ ያለመጠን ይጥል ስለነበር አዝመራውን ለማጨድ ወይም የታጨደውን ለመውቃት አልተቻለም ነበር። በዚች ደሴት እንደደ ረስን የመምጣታችንን ወሬ ለማሰማት አንድ መርከብ ወደንጉሣችን ዘንድ ተላከ። የምንጠብቃቸው መርከቦች ሁሉ ከተሰበሰቡ በኋላ ወደሊዝቦን መንገዳችንን ቀጠልን።

የሊዝቦንን ወደብ ሳናገኘው ሶስት ቀን ሙሉ ስንንቀ ዋለል ከቆየን በኋላ እንዲያውም በስህተት ወደእስፓኝ አውራጃ ወደጋሊዝያ እንደርሳለን እያልን ስናስብ አንድ ጥዋት የፖርቱጋልን ምድር ማየት ጀመርን። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ሐምሌ 24 ቀን በሊዝቦን የባሕር ክልል ውስጥ ገባን። በከይሽካይሽ ከመድረሳችን በፊት ከንጉሣችን የተላከ አንድ መርከብ መጥቶ ለጊዜው በሊዝቦን ገብቶ በነበር ወረርሺኝ በሽታ ምክንያት ከኢትዮጵያ አምባሳደር ጋር የመጣን ሁሉ በሊዝቦን እንዳንወርድ መከልከላችንን ነገረን። ወደ ሳንተረኝ የሚወስደን መርከብ እንዲያዝልንና ንጉሣችን እስከ ሚገኝበት እስከ ኩይምብራ ድረስ የሚያስፈልገንን ወጭ እንዲሰጠን አንድ የንጉሣችን አሽከር መጣ። የዚያን ዕለት መርከባችን በሊዝቦን ወደብ ፊት ለፊት መልሕቅ ተክሎ ስለቆመ በጣም ተደሰትን።

ምዕራፍ አምስት፤ ከሊዝቦን ወደ ኩይምብራ ስላደረግነው ጉዞ፤ በካር ናሽም ስለመቆየታችን።

መርከባችን በሊዝቦን በታጉስ ወንዝ ላይ መልሕቅ ተክሎ በንጉሣችን ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት እንደቆመ የዚያኑ ዕለት ማለት በቅዱስ ያዕቁብ በዓል ዋዜማ ዕለት እኛንና የኤምባሲውንም ሰዎች ወደሳንተረኝ ለመውሰድ ንብረታችንንም ወደ «ካዛ ደ ኢንዲያ» ለማድረስ መርከቦች መጡ። በጉዞው ላይ ከኔ ጋር የነበረ እኔ አኅት

የምሆነው ያንድ ወጣት ወንድም የኛን መምጣት በሰማ ጊዜ ከመር ከቦቹ ባንዱ ውስጥ ሆኖ ሊቀበለን መጣ። ይህ ወጣት ከሳንታ ማሪያ ዱዝ አሊቫይሽ ደብር ውጭ መሚገኘው በሳንቱዝ አ ኖቩ ገዳም ውስጥ የሚያገለግል ነበር። ወደ ካዛ ደ ኢንዲያ ያልሄደውን ዕቃችንን ማለት ልዩ ልዩ የአልጋ ብሶች፤ የሐር ልብሶች፤ ብዙ አዳዲስ ሸሚዞች፤ የጠረጴዛ ልብሶች፤ የራስ መሸፈኛዎችና ልዩ ልዩ ዓይነት ዕቃዎች እንዲቀበለን ሰጥተነው እርሱም የተባለውን ዕቃ በሙሉ አጠቃሎ በማግሥቱ በሠረገላ ወደ ቤቱ ለመውሰድ በሚሠራበት በሳንቱሽ ገዳም ውስጥ አኖረው። እኛም በተሰጡን መርከቦች ውስጥ ሆነን መንገዳችንን ቀጠልን። የተባለው ዕቃ በገዳሙ በቆየበት በማግሥቱ ሌሊት ሌቦች ገብተው ማናቸውንም ምርጥ የሆነውን ሁሉ ሠርቀው የማይረባውን ብቻ ተዉልን። ይህ የተሠረቀው የኔና የዘመዴ ዕቃ በጠቅላላው ከሃምሳ ክሩዛዱሽ በላይ ይገመት ነበር። በኩይምብራ በነበርንበት ጊዜ ስለተሰረቀብን ዕቃችን አንድ የግዝት ቃል መታተሙን ከብዙ ቀን በኋላ እስኪነግሩን ድረስ ይህን ነገር አልሰማንም ነበር።

በጀልባዎች ወደ ሳንታረኝ ሄደን በዚያም እንደደረስን አሽከር መልካም ማረፍያ ሰጠን። እኔና የኢትዮጵያ አምባሳ ደርን በአልፉንኾ አኑሮን፤ ዶም ሩድሪጉ ድ ሊማን ደግሞ በአባቱ ቤት በማርቪላ አኖረው። በዚህ ከተማ ስድስት ቀን በቆየንበት ጊዜ ውስጥ በፖርቱጋል ቄንጥ መልካም ልብሰ ለብሰን ነበር። የባሕሩ ጉዞ በጣም አድክሞን ስለነበር በቅሎና ሌላም ልዩ ልዩ አስፈላጊ ነገር ገዛን። አንድ ቀን ጊዜው ከመጠን በላይ ይሞቅ በነበረበት ዕለት ልክ ከጥዋቱ በአራት ሰዓት ሲሆን ከሳንተረኝ ከተማ ተነሣን።

ማደርያችን ለየብቻችን ስለነበረ ጉዞአችንን የጀመርነው ተለያ ይተን ነበር። የንጉሡ አሽከርና እኔ አብረን ስንሄድ የኢትዮጵያ አምባ ሳደር ከነጸሐፊዎቹ መነኩሴዎቹና ባሮቹ ጋር ባንድነት ሄደ። በምዕራፍ ሶስት እንደተገለጸው ኤይቶር ደ ሲልቬይራ ከማረካቸው እስላም ባሮች ውስጥ ሁለቱን ዶም ሩድሪጉ ለንጉሣችን አምጥቶ ነበር። እነዚህን ባሮች በንጉሣችን ፊት ለማቅረብ ፔሎት፤ ሰደርያ፤ ኮት፤

ሸሚዝ፣ ሱሪ፣ መጫሚያና ቆብ ሰጥቶዋቸው በሚገባ አኳኋን አጊጠው ነበር። የኢትዮጵያ አምባሳደር ከነአጀቡ በሙቀቱ ምክንያት ክፉኛ ደክሞት በጠባቡ መንገድ ይሄድ ነበር። የንጉሣችን አሽከር ከከተማው ወስዶኝ በሙቀቱ ብዛት በሞት አፋፍ ስለደረስሁ በአልሞንዳ ድልድይ አጠገብ አሳረፈኝ። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በዚህ ቦታ ብዙ ቀዝቃዛ ውኃ በሚገኝበት ማረፍያ አገኘሁ። ያረፍሁበት ቤት ባለቤት እንዳጋጣሚ ቅን ሰው ስለነበር አይዞህ እያለ ከማጽናናቱ በላይ በዚያ እንደደረስሁ ፍራፍሬና ቀዝቃዛ የወይን ጠጅ አቅርቦልኝ ወዲያውኑ ተንፈስ አልሁ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዶም ሩድሪጉ በፈረስ እየጋለበ መጥቶ በሙቀቱ ብርታት የኔ ባሮችና እስላሞቹ መርከብ ነጂዎቹም ሊሞቱብኝ ነውና እባካችሁ ስለ እግዚአብሔር ስትሉ በቅሎች ስጡኝ አለን። በዚያ ይገኙ የነበሩ በቅሎ ጫኞች አራት በቅሎች ጭነው ከዶም ሩድሪጉ ጋር ሄደው የተባሉትን ባሮችና እስላሞች አመጡዋቸው። ሰዎቹ በጣም ደክመው ስለነበር ከእስላሞቹ አንደኛው ፈጽሞ ስሜቱን እንዳጣ ቀረ። ምንም እንኳ ቅባት ቢቀቡትና ልዩ ልዩ ዓይነት መድኃኒት ቢያደርጉለትም ትኩሳቱን ሊያስታግስለት ስላልቻለ በእኩለ ሌሊት ላይ ሞተ። ይህን እስላም ለሞት ያደረሰው ያልለመደውን ልብስ መልበሱ ይሆናል ስንል ገመትን። ይህን ዓይነት አለባበስ የለመድነውን እኛን እንኳ ሙቀቱ በጣም አስቸግሮን ነበር። በሊዝቦን ገብተው በሽታ ይዘው መጥተዋል ተብለን ስለተጠረጠርን ምርመራ ተጀመረ፤ እኛም ያልገባን መሆናችንን ለማረጋገጥ በባል ደረባችን በንጉሡ አሽከር እየተመራን አንድ በአንድ ቃላችንን በመሃላ አጸናን። ሁላችንም ጤነኞች መሆናችንንና ከጤናማ አገርም መምጣታችን እንዲሁም በሊዝቦን ወይም በሽታ በገባበት በማናቸው ቦታ ያልደረስን መሆናችንን አረጋገጥን፤ የሆኖ ሆኖ ስለእስላሞቹ አስተያየታችንን በመግለጽ ምንም እንኳ ከሙቀት አገር የመጡ መሆናቸው የማይካድ ቢሆንም አለባበሳቸው እንደኛ ሳይሆን ግልድም አገልድመው ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን ሆነው ጸሐዩን እየሞቁ ስለሚሄዱ ሙቀቱን ያለመቻላቸው በልብስ በመታፈናቸው ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ስንል አስተያየታችንን ሰጠን። ነገር ግን ብዙ

ቀኖች ካለፉ በኋላ እንደተረዳው ያ ቀን በተለይ አደገኛ ቀን ስለነበር ሌሎች ሰዎችም በሙቀቱ ምክንያት ሙተዋል። ለምሳሌ በአሊቫይሽ (በኩይምብራ) የሴላሽ ገዳም ነዋሪ የነበረች አንዲት ሴት ልብስዋን አጥባ ከብዙ ሴቶች ጋር ሆና ከቦላው ሜዳ ስትመጣ ፎንቶራ በተባለ ቦታ በወይራ ተክል መግቢያ ላይ ሞተች ይባላል። እንዲሁም ዕድሜው በሃያ አራት ዓመት የሚገመት ተቀማጭነቱ በአቨይሩ የነበረ አንድ መነኩሴ ካንድ ሌላ መነኩሴ ጋር ከቦላው ወደፔናኮቫ ሲሄዱ በሙቀቱ ምክንያት ጋቪኙሽ በተባለ ከተማ አጠገብ ሞተ። ቦላው ሁለት ሌግዋ ፔናኮቫም አራት ሌግዋ ከኩይምብራ ርቀው ይገኛሉ። እስላሙ በሞተበት ሌሊት ከነበርንበት ቦታ አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኘው ጎልገ ወደተባለ ቦታ ሄድን። ከዚህም በኋላ ሙቀቱን በመፍራት ከኛ ጋር የነበረው የታመመውም እስላም እንዳይንገላታ በማለት ብዙ አንጓዝም ነበር። ከጎልገ ተነሥተን ቱማር፤ ከዚያም አልቪያዜር፤ ከዚያም አንሲያው አደርን። በዚህ ቦታ እንደደረስን የንጉሡ አሽከር ከኛ ተለይቶ ወደ ኩይምብራ ሄደ። እኛም መንገዳችንን ወደፊት ቀጥለን ስርናሽ ዱዝ አልዩሽ እንደደረስን እስከንጠራ ድረስ ከዚያ ቦታ እንዳንሄድ በማስጠንቀቅ ንጉሣችን ያዘዘን መሆኑን ተረዳን። ይህን በሰማን ጊዜ በእስላሙ ሞት ምክንያት የተነሣውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ይሆናል ይህ ትዕዛዝ የተሰጠን ስንል ገመትን። የሆነው ሆኖ በተባለው ቦታ ሃያ አምስት ቀን ከቆየን በኋላ ንጉሡ አምባሳደር ሩድሪጉንና እኔን አስጠርቶን ቀርበን እጁን ለመሳም ቻልን። ልዩ ልዩ ጥያቄዎች አቅርቦልን መልስ ሰጠን። ከሁለት ቀን በኋላ ሁላችንም እንድንሰናዳና ወደ ከተማው እንድንሄድ ታዘዝን።

ምዕራፍ ስድስት፤ ከስርናሽ ዱዝ አልዩሽ ወደ ኩይምብራ ስለመሄዳችንና ንጉሣችንም ስላደረገልን ከፍ ያለ አቀባበል።

ከንጉሡ ከተሰጠን ባልደረባ አማካይነት የሚያስፈልገንን ማናቸውንም ነገር እየተቀበልን ሰላሳ ቀን በስርናሽ ዱዝ አልዩሽ በቆየንበት ጊዜ አንድ ቀን በማለዳ የንጉሡ ቤተ መንግሥት አዛዥ ዲዮጉ

ሎፕሽ ደ ስከይራ ወደኛ ዘንድ መጣ። ይህ ሰው እኛ ወደ ኢትዮጵያ በሄድን ጊዜ የሕንድ ጠቅላይ ገዥ የነበረ ከመሆኑ በላይ እኛን ኢትዮጵያ ጠረፍ ድረስ ሸኝቶን ነበር። ስለዚህ ኤምባሲውን እርሱ ራሱ ያቀደው የግል ተግባሩ አድርጎ ይቆጥረው ነበር። ዶም ሩድሪጉንና የኢትዩጵያን አምባሳደር እንዲሁም እያንዳንዳችንን ሳመን። እኛን እንዲቀበለንና በሚገባም እንዲመግበን ንጉሡ ያዘዘው መሆኑን ነገረን። የቤተ መንግሥቱ ሰዎች በመላ መጥተው ሊቀበሉን ስለነበር ከርሱ ጋር ሆነን በሚዳው መንገድ ሄድን። እኛን ሳያማክረን ዲዩጉ ሎፕሽ ደ ስኬይራ በዚያው ምሳ እንዲዘጋጅ አዘዘ። የኢትዮጵያ አምባሳደር ጥቂት አሞት ስለነበር አልበላም፤ ነገር ግን የተቀረነው ከዲዎጉ ሎፕሽ ደ ስኬይራ ጋር ተመገብን። ከዚህ በኋላ መንገዳችንን ቀጠልን። ከከተማው አንድ ሌግዋ ያህል ርቆ በሚገኘው አንታኞል በተባለው መንደር እንደደረስን እኛን ለመፈለግና ሊቀበሉንም ብዙ ሰዎች ከቤተ መንግሥቱ መጥተው አገኘናቸው። ከዚህ ቦታ ጀምሮ ግማሽ ሌግዋ ርቆ እስከሚገኘው እስከ ሳው መርቲኙ ድረስ መንገዱ በሙሉ በኤጲስቆጶሶች፤ በመሳፍንትና በቤተ መንግሥቱ ሰዎች ተመልቶ ነበር።

በራፖላ በኩል መርተውን ፌጌይራ ደ ቬሊያ በተባለ መንገድ በሳንታ ክሩሽ ገዳም በር አልፈን በሩዋ ድ ክሩሽ፤ በአልሜዲና በር ባለው ካልሳዳ፤ በሩዋ ዳሽ ፉንጋሽ፤ በቅዱስ ክርስቶፎር መንገድ፤ በእመቤታችን ስም በሚጠራው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ አልፈን በንጉሣችን ቤተ መንግሥት ደረስን። የኢትዮጵያን አምባሳ ደር የቬላ ሬያል መስፍን እጁን ይዞት በንጉሡ ፊት አቅርቦት የንጉ ሣችንንና የእቴጌይቱን፤ እንዲሁም የካርዲናሉንና የልዑላንን እጅ አሳመው። ንጉሣችንም አምባሳደሩን ስለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ስለ እቴጌይቱ ስለልዑላንም ቤተሰቦች ጤንነት ጠየቀው። የኢትየጵያ ንጉሠ ነገሥት ስለ ግርማዊነታቸውና ስለ እቴጌይቱ ስለ ወንድሞቻ ቸውም ለመስማትና ለማወቅ የሚፈልግ መሆኑን ገለጸ። አምባሳደሩ ባደረገው ጉበኝትና በኤምባሲውም ንጉሣችን በጣም የተደሰተ መሆኑን ገልጾ፤ በዚህ ጉበኝት ላምላካችን ትልቅ አገልግሎት እንዲፈጸም ለነርሱም ማለት ለሁለቱም ነገሥታት በወንድማማችነት ታላቅ

ክብር እንዲያስከትልላቸው ሙሉ ተስፋ ያለው መሆኑን ጨምሮ ገለጸ። ንጉሣችን ንግግሩን በመቀጠል አምባሳደሩ የመሬቱንና የባሕሩን ጉዞ እንዴት እንደዘለቀውና በመርከቦቹና በልዩ ልዩ ቦታዎች መልካም አቀባበል ተደርጎለት እንደሆነ ጠየቀው። አምባሳደሩም መልሶ «የግር ማዊነትዎ በረከት ከፍ ያለ በመሆኑ ይህን የተቀበለ የእግዚአብሔን ፀጋ የተቀበለ ነው» አለ። አምባሳደሩና እኛ በመንገዱ ምክንያት የደከመን መሆናችንን ንጉሡ ተገንዝቦ ወደ ማረፍያችን እንድንሄድ አዘዘን። ስለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዜና ሰፊ ሃተታ እንድንሰጠው እንደገና የሚያስጠራን መሆኑን ነገረን።

በበቅሎቻችን ተቀምጠን በመጣንበት አኳኋን በኤጲስቆጶሶችና በመኳንንችም ታጅበን ወደኋላ ተመለስን። በቅዱስ ዶሚንጎስ ገዳም እንደደረስን ለአምባሳደሩ ማረፍያ ሰጥተውት የተባሉት ሰዎች ተመለሱ። ከሁለት ቀን በኋላ ኤጲስቆጶሶቹና የገዳሙ ቤተ ክርስቲያን ገበዝ ካንዳንድ ካህናት ጋር ሆኖ የኢትዮጵያን አምባ ሳደርንና አብረነው የነበርነውንም እኛን ወደቤተ መንግሥቱ ወሰዱን።

በንጉሣችን ፊት እንደቀረብን አምባሳደሩ ከወርቅና ከብር የተሠራ አንድ ዘውድና በሶስት ቋንቋዎች ማለት በኢትዮጵያ ቋንቋ፤ በአረብኛና በፖርቱጋልኛ እያንዳንዳቸው በሁለት ኮፒ የተጻፉ ደበዳቤዎች በወርቅ ግምጃ ኮሮጁ ውስጥ እንደተቀመጡ አቀረበ። ደብዳቤዎቹ በሁለት ኮሮጆ ውስጥ የተቀመጡ ሲሆኑ አንደኛው ነፍሱን ይማርና ለንጉሥ አማኑኤል ነበር። ሌላው ግን አሁን በዙፋን ላይ ላለው ለንጉሣችን ነበር የተላከው። የኢትዮጵያ አምባሳደር ሊቀ ካህናቱ ለንጉሡ እንዲህ አለው፤ «ጌታዬ ግርማዊ አጼ ልብነ ድንግል ይህን ዘውድና እነዚህን ደብዳቤዎች የላከው ነፍሳቸውን ይማርና ላባትዎ ለንጉሥ አማኑኤል ነበር። ዘውድ ካባት ወደ ልጅ እንጂ ከቶ ከልጅ ወደ አባት የማይተላለፍ ነው። ስለዚህ አጼ ልብነ ድንግል በአገሩና በግዛቱ ላይ የሚወደድበትን የሚፈራ በትንና የሚከበርበትን ዘውድ መላኩ አገሩና ግዛቱ ሕዝቡም የንጉሥ አማኑኤል ታዛዥ መሆኑን እንዲያውቁለት በመፍቀድ ነው። አጼ

ዳዊት የንጉሥ አማኑኤልን ሞት በሰማ ጊዜ እንዲህ አለ። ላባቴ ለንጉሥ አማኑኤል የተላከው ደብዳቤና ዘውድ ለንጉሥ ዶም ዮሐንስ ይሰጥ። ሌላ ደብዳቤም እጽፍለታለሁ።»

የተባለውን ዘውድና ደብዳቤ ለንጉሡ አበርክቶ እርሱም ተቀብሎ ለጸሐፊው ለአንቶንዩ ካርነይሩ ሰጠው። በኤምባሲው መምጣት ምክንያት በጣም የተደሰተ መሆኑን ንጉሣችን ገለጸ። አምባሳደሩና እኔ በሁለት ወርቅ ግምጃ ከረጢት ውስጥ የተቀመጡ ደብዳዎችና ለሮም ጳጳስ የተላከ አንድ ትንሽ የወርቅ መስቀል አቀረብንለት። ይህን ደብዳቤና መስቀል ንጉሣችን ከተመለከተ በኋላ ለኔ መልሶ ሰጥቶኝ እኔም ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ ለጳጳሱ እንድወስደው ታስቦ ነበር። ንጉሡም ደብዳቤውንና መስቀሉን ተቀብሎ ከሳመው በኋላ ለጸሐፊው ሰጠው። እንዲሁም ባባቱና በርሱ አማካይነት ይህን የመሰለ ታላቅ ተግባር ለእግዚብሔር በመከናወኑ ከፍ ያለ ምስጋናውን የሚያቀርብ መሆኑን፤ እንዲሁም ይህን የተጀመረውን ሥራ እግዚአብሔር ወደ ፍጻሜ እንደሚያደርሰው ተስፋ ያለው መሆኑን ገለጸ። ከዚህ በኋላ ደስ እስኝቶን ወደማረፍያችን ላከን። እስከዚህ ጊዜ ድረስ በየደረስንበት ቦታ ሁሉ ስለነበር የምንመገበው ንጉሡ ለአምባሳደሩ ድርጎ እንዲወጣለትና ከዚህም በላይ ሶስት በቅሎዎች ማለት አንድ ለርሱና ሁለት አብረውት ለነበሩ ሁለት መነኩሴዎች በወር ሰላሳ ክሩዛዱሽ ለምግቡ፤ ለበቅሎውም ሣር መግዣ በቀን አንድ ቱሽተው አዘዘለት። አንድ ምቹ አልጋ ከነሌሊት ልብሱ፤ የብር ሣህን፤ የጠረጴዛ ልብስና ማናቸውም ዓይነት ዕቃ እንዲሁም በዚያው ሆኖ የሚያገለግለው ፍራንሲሽኩ ፒርሽ የተባለ አሽከር አዘዘለት። ከዚህም አሽከር ሌላ አረብኛ የሚያውቅ የንጉሡ የክብር ዘበኛ ጓድ የነበረ ፍራንሲሽኩ ሌሙሽ የተባለ አንድ ሰው በማስተርጎምና ድርጎም በመቀበል እንዲረዳው ታዘዘለት።

ምዕራፍ ሰባት፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለንጉሥ አማኑኤል የጻፈው ደብዳቤ ትርጉም።

ሁልጊዜም በነበረውና መጀመርያም በሌለው በአብ ስም፤ ባንዱ እንዳባቱ በማይታየው የውቅያኖሶቹ መሠረት ከመጣሉ በፊት የከዋክብት ብርሃን በነበረው ያለወንድ ዘር ወይም ያለጋብቻ በድንግል ማህጸን በተጸነሰው በወልድ ስም፤ ማናቸሙንም ምስጢር በሚያውቀው ያለምሰሶ ከቆመው ከሰማይ በመጣው ምድርንም በዘረጋው በጰራቅሊጦስ ስም፤ እርሱ አንደኛ ወይም ሁለተኛ ሳይሆን ማናቸውንም ነገር በፈጠረው አምላክ የተገናኘ ሥላሴ ነው፤ ለሁሉም አንድ መከርና አንድ ቃል ነው። ለዓለም ወለዓለም አሜን።

ይህ ደብዳቤና ኤምባሲ የተላከው ከልብነ ድንግል ነው፤ ይህ ስም የጥምቀት ስሙ ሲሆን ከነገሠ በኋላ አጼ ዳዊት የተባለ የግዛቶቹ መሪ፤ እግዚአብሔር ያፈቀረው፤ የሃይማኖቱ ምሰሶ፤ የይሁዳ ነገድ ዘር፤ የዳዊት ልጅ፤ የሰሎምን ልጅ፤ የአምደ ጽዮን ልጅ፤ የዘርአ ያዕቆብ ልጅ፤ የበእደ ማርያም ልጅ፤ የናአድ የሥጋ ልጅ፤ የደጋው ኢትዮጵያና የሌሎችም ታላላቅ ግዛቶች ንጉሠ ነገሥት የሸዋ፤ የጋፋት፤ የፈጠገር የአንጎት፤ የቦራ፤ የባሊና የገንዝ፤ የሐዲያ፤ የቡግናና የጎጃም፤ የአማራና የበጌምድር፤ የደንብያና የዋግ እንዲሁም ንግሥተ ሳባ የነበረችበት የትግሬ አውራጃ፤ ግብጽን የሚያዋስነው የባሕር ነጋሹ ግዛት ንጉሥ። ይህ ደብዳቤ የተላከው ለንጉሥ አማኑኤል ነው። ሁል ጊዜ ድል የሚነሣው፤ በእግዚአብሔር ፍቅር በሚኖረው በካቶሊክ ሃይማኖት በጸናው የጴጥሮስና የጳውሎስ ልጅ፤ የፖርቱጋልና የአልጋርቭ ንጉሥ፤ የክርስቲያኖች ወዳጅ፤ የእስላሞችና የአሕዛብ ጠላት፤ የአፍሪካና የጊኒ፤ የማዳጋስካር፤ የቀይ ባሕር፤ የአረቢያ የፋርስ፤ የሆርሙዝ፤ የሕንድና በውስጡም የሚገኙ ከተማዎች ጌታ፤ የእስላሞችና የአሕዛብ ድል አድራጊና ዳኛ፤ የብዙ ምድሮች ጌታ። ያለጦርና ጋሻ በየሱስ ክርስቶስ በመረዳትና በሃይማኖቱም በማመን ብቻ

እስላሞችን ለፈጁት እንደውሻም ላባረሩዋቸው ለንጉሥ ዶም አማኑኤል ሰላም ለርስዎ ይሆን። የየሱስ ክርስቶስና የመድኃኔ ዓለም እናት አገልጋይ ለሆነችው ለባለቤትዎም ሰላም ይሁን። ለአበባዎቹ ለወንዶቹ ልጆችዎ ሰላም ይሁን። እንደ ቤተ መንግሥት ላጌጡት ለሴቶቹ ልጆችዎም ሰላም ይሁን። የቅዱሳን ዘር ለሆኑት ለቤተ ሰቦችዎም ሰላም ይሁን። በመጽሐፍት እንደተጻፈው የቅዱሳን ልጆች የተባረኩና በቤታቸውም በፀጋ ታላቅ ናቸው። ላማካሪዎችዎ፤ ላገልጋይዎችዎ ለመኳንንቶችዎና ለዳኞችዎ ሰላም ይሁን። ለታላላቅ ከተማዎችና በውስጣቸውም ለሚኖሩ ለክርስቲያኖች ብቻ (አይሁዶችና እስላሞች ሳይጨመሩ) ሰላም ይሁን። በክርስቶስ ላሉት ለገዳሞችዎና ለታላላቅ ሰዎች ሁሉ ሰላም ይሁን።

አባቴ ንጉሥ ሆይ፤ የማቴዎስን መምጣት በሰሙ ጊዜ ሊቀ ኤጲስቆጶሶችና ኤጲስቆጶሶች ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣንን አስጠሩ ማለትን ሰማሁ። ስለዚህ በጣም በመደሰቴ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ። እኔ ብቻ ሳልሆን ሕዝቤም ከኔው ጋር ተደስቶአል። ስለማቴዎስ በጠየቅሁ ጊዜ ከርስዎ አገር እንደተመለሰ በኢትዮጵያ ምድር ሲደር በደብረ ቢዘን ገዳም ሞተ ሲሉ ነገሩኝ። ይህን ሰው በአምባሳደርነት የላክሁት እኔ ሳልሆን በሞግዚትነት አገሩን ትመራ የነበረችው እቴጌ እሌኒ ነበረች። አባቴ ሞቶ ዘውዱን እንደጫንሁ ያሥራ አንድ ዓመት ወጣት ስለነበርሁ ስለኔ ሆና አገሩን የምታስተዳድርልኝ እርስዋ ነበረች። ማቴዎስ ከዚያ በፊት ነጋዴ የነበረ አብርሃም በሚያሰኝ መጠርያ የሚታወቅ ነበር። ነጋዴ መስሎ ሸቀጥ አስይዞ የእስላሞችን አገር አቋርጦ በማለፍ ደቡል ደረሰ፤ ነገር ግን የዚያ ቦታ እስላሞች ክርስቲያንነቱን ባወቁ ጊዜ ይዘው አሠሩት። ማቴዎስም በንደዚህ ያለ አደጋ ላይ መውደቁን በተረዳ ጊዜ የኔ አምባሳደር መሆኑንና ወደርስዎም የላክሁት መሆኔን በመግለጽ የሕንድ ጠቅላይ ገዥዎ ከግዞት እንዲያወጣው በመለመን ላከበት። ጠቅላይ ገዥውም ይህን እንደሰማና ይልቁንም ክርስቲያን መሆኑንና ሃብቱ ሁሉ ተወርሶ በእስር ቤት መግባቱን በሰማ ጊዜ ብዙ ሰዎችና መርከቦች ልኮ እስላሞቹ እንዲገደሉና ማቴዎስም በቶሎ ከግዞት ወጥቶ የታሠረበት ምክንያት እንዲጣራ አዘዘ።

ጠቅላይ እንደራሴውም ማቴዎስን «ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ የምትወስደው መልእክት ምንድን ነው?» ብሎ ሲጠይቀው መልእክቱን በገለጸ ጊዜ እንዲሄድ ፈቀደለት። ከዚህም በኋላ እርስዎ ፊት ቀርቦ እነሆ የክርስቶስ መስቀል ሲል መስቀሉን አበረከተዎ። ብዙም ነገሮች የነገረዎ ከመሆኑ በላይ የጠየቁትን ጥያቄ ዎች መለሰልዎ። ስለዚህ ግርማዊነትዎ (በደብዳቤዎ እንደተረዳሁት) ማቴዎስን አከብረው ታላቅ ሰው አደረጉት። እርሱም ወደዚህ አገር ከተመለሰ በኋላ በደብረ ቢዘን ገዳም ሞተ። ከርሱ ጋር የመጡ ፖርቱጌዞች እርስዎ የላኩትን ደብዳቤ አቀረቡልኝ። ደብዳቤውን ባቀረቡልኝ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገንሁ። እነርሱም ወደዚህ በመምጣታቸው እግዚአብሔርን አመሰገንሁ። በርስዎና በሕዝብዎ ተደስቻለሁ፤ ወደዚህ አገር የመጡት ፖርቱጌዞች በራሳቸው በእጃቸውና በደረታቸው ላይ ያደረጉትን መስቀል በማየት በጣም ተደሰትሁ።

የናንተን እምነት ጠይቄ ክርስቲያን መሆናችሁን በነገሩኝ ጊዜ እንዲሁም ከዚህ በፊት ወደዚህ ያልመጡ ሰዎች ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጣን ባሉኝ ጊዜ በጣም ተሸበርሁ። ወደኢትዮጵያ የሚወስደውን መንገድ ፈልገው ባለማግኘታቸው ተስፋ ቆርጠው ይልቁንም ነጎድጓድንና ከንቱ ልፋትን በመፍራት ወደ ሕንድ ለመመለስ ከቆረጡ በኋላ ሌሊት በኢትዮጵያ ምድር አግጣጫ በሰማዩ ላይ ቀይ መስቀል አዩ። ይህን መስቀል በመርከቡ የነበሩት መኳንንትና መርከበኞቹም ሰገዱለት። ይህን ምልክት ባዩ ጊዜ መንገዳቸውን የሚመራቸው እግዚአብሔር መሆኑን ተረዱ። እኔም በዚሁ በጣም ተደነቅሁ። በእውነተኛው ይህ ምልክትና ቃል የመጣው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰይጣን አይደለም። የመጣበትም ምክንያት እርስዎ ኤምባሲ እንዲልኩልኝ ለማሳሰብ ነው። «አንድ የፈረንጅ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሥ ይገናኛሉ፤ ሰላምታም ይሰጣጣሉ፤» የሚል በቅዱስ ፍቅጦር ትንቢት ላይ በቅዱሳት አበዋትም መጽሐፍ ውስጥ በነቢዩ ተሰጥቶአል። ይህ ትንቢት በኔ ጊዜ ይፈማል ብዬ ከቶ አልገመትሁም ነበር። ማናቸውንም ነገር እግዚአብሔር አውቆታልና ለስሙ ምስጋና ይድረሰው። እኔም ለርስዎ ለአባቴና

ለወዳጇ መልእክት እንድልክብዎ በማለት እግዚአብሔር ራሱ የርስዎን ኤምባሲ አዘዘልኝ።

ከዚህ በፊት ከክርስቲያን ንጉሥ መልእክተኛ አልደረሰኝም ነበር፤ አሁን ግን እርስዎ ቀረቡኝ፤ ከዚህ በፊት ወደኔ የመጡት እነዚያ ርኩሶች የመሐመድ ልጆች እስላሞች ብቻ ነበሩ። ሌሎቹም እግዚአብሔርን የማያውቁ ባሮች ነበሩ። ሌሎቹም በእንጨት፤ በእሳት፤ በጸሐይና በእባብም የሚሰግዱ ነበሩ። በእውነቱ ስለማያምኑ እውነቱን እንዲያገኙ በማለት በማስተማር ብዙ ለፍቼ ነበር። አሁን ግን በኔ ዘመነ መንግሥት የእረፍትና የሰላም ጊዜ ሆኖአል። በአገሬ ድግበር ሁሉ የሚያጋጥሙኝ እስላሞች ከቶ ቀና ብለው ሊያዩኝ አይደፍሩም፤ ወይም ፊታቸውን ከቶ ወደኔ አይመልሱም። የጦር ሹማምንቴ በሄዱበት ቦታ ሁሉ ድል ይነሣሉ። እኔም እንዲሁ ድል እነሣለሁ። እግዚአብሔር ቸርነቱን አልነሣኝም። በዳዊት መዝሙር እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎአል። «እግዚአብሔር በኃይልህ ተደስቶአል፤ በደህን ነትህ ንጉሡና ሌሎቹም ይደሰታሉ። ለያንዳንዳቸውም የጠየቁትን ይሰጣል፤ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።» ለርስዎ ላባቴ እግዚአብሔር ዓለምን ሰጠዎ። የአሕዛብንም አገር ለዘለዓለም ሰጠዎ። እስከ ኢት ዮጵያ ግዛት ድንበር ያሉት የሌሎች አሕዛብ አገሮች የርስዎ ግዛት ናቸው። እግዚአብሔር ብዙ ዓለሞች ሰጥቶኛል፤ ለዚሁም አመሰግ ነዋለሁ።

ልጆችዎ እውነቱን እንዲያውቁ በማለት ለርስዎ ታላቅ ቃል እናገራለሁ። እግዚአብሔር ለኔና ለርስዎ ማናቸውንም ነገር ስለሰጠን መደሰት አለብን። በክርስቶስ ላይ ባመጹት በነዚያ ከኃድያን እስላሞች እጅ የምትገኘውን የሩሳሌምን እግዚአብሔር በእጅዎ እስኪያስገባልዎ ድረስ ጸሎትውን አያቋርጡ። ይህ ከተከናወነ በኋላ ከርስዎ የበለጠ ኃይል ሊኖር አይችልም። ይህን ጉዳይ በጣም ሳስብ በትና ስጠብቀው ነበር፤ ሁላችንም የጌታችን የየሱስ ክርስቶስ መልእ ክተኞች ነን። ይህን ባከናወኑ ጊዜ የብዙ ሰዎች ምስጋና ይደርስዎታል።

አብርሃም የሚያሰኝ የቀድሞ ስሙን ለውጦ ማቴዎስ ይባል ከነበረው ሰው ጋር በላኩዋቸው መልእክተኞችዎ አማካይነት የርስዎ

መልእክት ደረሰኝ። ከነዚህ መልእክተኞች ሶስቱ በመንገድ ሞቱ፤ የሕንድ ግዛትዎ እንደራሴ ከመልእክተኞቹ ጋር እምጽዋ ድረስ መጥቶ ከባሕር ነጋሹ ጋር ከተገናኘ በኋላ መልእክተኞቹን ወደዚህ ላካቸው። የርስዎን ዝና ከነዚህ ሰዎች በሰማሁ ጊዜ በጣም ተደሰትሁ። የርስዎ ስም ከዓለም ከሚገኘው ሃብት ወይም ከማናቸውም የከበረ ድንጋይ የበለጠ ነው። የርስዎን ዝና የሰማሁት በታላቅ ደስታ ነው።

እኔ ሁለት መቶ ሺ ወርቅ እሰጣለሁ፤ ከዚህ በኋላ በወዳጅነት እንገናኛለን። የኔን ምኞት ለመፈጸም እርስዎ መልእክተኞች ሲልኩ እኔስ የሰላም መልእክተኛ ለምንድን ነው ያለመላኬ? ጌታችን የሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም እርስዎ አስቀድመው መልእክተኞች ወደኔ ላኩ። የክርስቶስ አንድ ልብና አንድ ፈቃድ እንደነበራቸው ሁሉ የርስዎ መልእክት በደረሰኝ ጊዜ በጣም ተደሰትሁ። ዕድሜ የማያውቀው ለዘለዓለም የሚኖረው አንዱ እግዚእብሔር እርስዎን አባቴን ንጉሥ አማኑኤልን ይጠብቅዎ።

በግርማዊነትዎ ትዕዛዝ እንደራሴዎ የላካቸው መልእክተኞች ሁሉም መልካም ሰዎች ናቸው። በዶም ሩድሪጉ ድ ሊማ አምባሳደርነት የመጡትን መልእክተኞች ሁሉ በክብር ተቀበልኋቸው። አምባሳደሩን በተለይ አስደሰትሁት። አባ ፍራንኪሽኩ አልቫርሽ ቅን ባነጋገሩና እንዲሁም ሃይማኖት ነክ በሆነ ጉዳይ ሁሉ እውነተኛ ሰው ሆኖ ስላገኘሁት ልዩ ክብርና ፍቅር አሳይቼዋለሁ። የግዛታችን ጠረፍ የሆኑትን ምጽዋን ዳህላክንና ዘይላን እንዲገዛና ወደ ክርስትናም እንዲመልሳቸው ይሾሙት ዘንድ እለምንዎታለሁ። እነዚህ ስማቸው የተጠቀሱትን ቦታዎች ለርሱ ሰጥተነዋል። ሥልጣን የሰጠነው መሆኑን ለማረጋገጥ መስቀልና ዘንግ በእጁ ሰጥተነዋል። ስለዚህ የተባሉት ቦታዎች ኤጲስቆጶስ ይሆን ዘንድ ይፍቀዱለት። ይህን ማዕርግ ለማግኘት የበቃው ችሎታ ያለው ሰው በመሆኑ ነው።

እርስዎም ጠላቶችዎን ከእግርዎ ሥር ለመጣል እንዲችሉ እግዚአብሔር በጎ ነገር ያድርግልዎ ያበርታዎም። እግዚአብሔር ዕድሜዎን ያርዝመው፤ እኔ ራሴ የምመኘውን የመሰለ በሰማያዊ

መንግሥት ስፍራ ያዘጋጅልዋ። በዓይኔ ያላየኋቸውን መልካም ነገሮች በጆሮዬ ሰማሁ አሁን ግን ዓይኖቼ ያላሰቡትን መልካም ነገሮች አዩ። እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ሁሉ በጎ ነገር እንደሚያደርግላቸው ሁሉ ለርስዎም እንዲሁ ያድርግልዎ። የርስዎ ቦታ በሕይወት መርከብ ላይ ይሁን። መኖርያዎም በቅዱሳን መኖርያ ትሆን አሜን።

የኔ አምባሳደር ሆኖ የምፈልገውን ነገር ሁሉ እንዲነግርዎ ሊቀ ካህናቱን ልኬዋለሁ። እንዲሁም የግል ጉዳዬ የሆነውን ለሮም ያለኝን ታዛዥነት እንዲገልጽልኝ አባ ፍራንሲሽኩን ወደ ሮም ጳጳስ ልኬዋለሁ። ትንሽ ልጅ የሚያደርገውን ሁሉ በመዘርዘር ለአባቱ እንደሚገልጸው ሁሉ እኔም አምባሳደሮች ሲልኩብኝ ማናቸውንም ነገር እንዲሁ እገልጻለሁ። እርስ በርሳችን እንድንረዳዳ ሁል ጊዜ ይጻፉልኝ። እርስዎ የላኩዋቸው ወደፊትም የሚልኳቸውን ሰዎች በምጽዋና በዳህላክ ደሴቶች ላይ በደረሱ ጊዜ እርስዎ የሚያዙትን ነገር ሁሉ ላደርግላቸው ዝግጁ ነኝ። ይህንንም የማደርገው እንድንረዳዳ ስለምፈልግ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ቦታዎች የኔ አገር ክፍሎች ስለሆኑ ዜጎችዎ በዚያ እንደደረሱ እኔም በዚያው እገኛለሁ። በዚያ የሚኖሩት አሕዛብና እስላሞች ብቻ ስለሆኑ ቤት ክርስቲያንና ክርስቲያን አይገኙም። ዜጎችዎ በኔ ግዛት ድንበር ላይ ስለሚሠፍሩ በጣም ተደስቻለሁ። ስለዚህ እርስዎ የለመኑትን የምፈጽም እንድንረዳዳ ነው።

በወርቅና በብር በመዳብና በብረት በአረርም ምስሎችን ለመሥራት የሚችሉ የጅ ጥበበኞች ይላኩልኝ። በኛ ፊደል መጽሐፍት ለማተም ይቻል ዘንድ የኛን ፊደል ለመቅረጽ የሚችሉ ጥበበኞች፤ እንዲሁም ለጌጥ የሚሆን የወርቅ ቅጠል ለመሥራት የሚችሉ ሠራተኞችም ይላኩልኝ። እነዚህ ሠራተኞች ሁሉ የኔ በጎ አስተያየት ሳይለያቸው ከኔ ዘንድ ይኖራሉ። በገዛራሳቸው ፈቃድ ወደገራቸው ለመሄድ የተነሡ እንደሆነ ላስቀራቸው የማልሞክር መሆኔን በሕያው እግዚአብሔር ልጅ በየሱስ ክርስቶስ ስም አረጋግጣለሁ። ይህን መልእክት መላኬ የርስዎን ደግ ሰውነትና መልካም ባሕርይ ስለማውቅ ነው። ይህ ለኔ የተደረገልኝ ውለታ ለአብርሃም እንደተደረገለት ይቆጠራል።

ስለዚህ ይህን ልመና ማቅረቤ በዚህ በመተማመን ነው፤ ለሚፈጸምልኝ አገልግሎት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ ነኝና ልመናዬን እንደነውር እንዳይቆጥሩብኝ እለምንዎታለሁ። እርስዎ አባቴ ነዎ፤ እኔም ልጅዎ። ስለዚህ ልጅ የጠየቀውን አባት እምቢ አይልም። እርስዎና እኔ እንደ ግድግዳ ግንብ ድንጋዮች የተያያዝን ነን። እንዲሁም የዓለም ጠቅላይ በሆነው በየሱስ ክርስቶስ የተሳሰርን ነን። እንዲሁም ከርሱ ጋር ያሉ ሁሉ እንደ ግንብ ግድግዳ ድንጋይ ባንድነት የተያያዙ ናቸው።

ምዕራፍ ስምንት፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዶም ዮሐንስ የጻፈው ደብዳቤ ትርጉም።

ሁሉን በሚችለው ሰማይንና ምድርን እንዲሁም የሚታዩትንና የማይታዩትን ነገሮች ሁሉ በፈጠረው በእግዚአብሔር ስም፤ የአብ ፈቃድና መካር ነቢይ በሆነው በእግዚአብሔር ወልድ ስም፤ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ከሆነው በነቢያት አፍ የሚናገረው ሐዋርያትም በሰማይና በምድር በባሕር ጥልቀት ውስጥ ለሚገኘው ለሥላሴ ምስጋና እንዲያቀርቡ በሚመራቸው በመንፈስ ቅዱስ በጰራቅሊጦስ ስም፤ አሜን።

የየሩሳሌም ነገሥታት የነበሩት የዳዊትና የሰሎሞን ዘር የሆንሁት እኔ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ልብነ ድንግል የናኦድ ልጅ፤ የበእደ ማርያም ልጅ፤ የዘርዐ ያዕቆብ ልጅ፤ ይህን ደብዳቤና ኤምባሲ እልክልዎታለሁ።

ይድረስ ለንጉሥ ዶም ዮሐንስ የፖርቱጋል ንጉሥ፤ የዶም እማኑኤል ልጅ፤ ሰላም ለርስዎ ይሁን፤ የጌታችን የየሱስ ፀጋም ለዘለዓለም ከርስዎ ጋር ይሁን። አባትዎ የነዚያን የመሐመድ ልጆች የእስላሞችን ኃይል የመስበራቸውን ዝና በነገሩን ጊዜ ስለከ

ርስትና ቤተ ሰብ ትልቅነትና የደህንነት ዘውድ በመኖሩ ለእግ ዚአብሔር ምስጋናዬን አቀረብሁ። በርስዎና በኔም ግዛት የሚገኙትን እስላሞችና አይሁዶች በመረዳዳት እንድናጠፋ የአባትዎ ኤምባሲ ሁለታችንን በበለጠ የሚያቀራርብና የሚያፋቅር መልእክት ይዞልኝ በመጣ ጊዜ በጣመ ተደሰትሁ። ይህ መልእክት ደርሶኝ በደስታ ላይ ሳለሁ የአባትዎን ሞት በሰማሁ ጊዜ ደስታዬ ወደ ሐዘን ተለወጠ። በቤተ መንግሥቴ የሚገኙት መኳንንት ሁሉ ከኔው ጋር አብረው አለቀሱ። ያባትዎን ዝና ሰምተው የተደሰቱት ካህናት ሁሉ በጣም ከማዘናቸው በላይ ሃዘኑን ወደ የገዳማቱ ሁሉ ወሰዱት።

ወንድሜ ሆይ፤ አንዳንድ ክርስቲያን ለስግደት ወደየሩሳሌም ወይም ወደሮም ወይም ወደ ሌላ ቦታ ሲሄዱ እስላሞች የሚጥሉባ ቸውን አደጋ አንዳንድ ጊዜ እሰማለሁ እንጂ ከዚህ በፊት ከማናቸውም የክርስቲያን አገር ወይም ከፖርቱጋል መንግሥት ወደኢትዮጵያ ከቶ አምባሳደር አልተላከም። ለመጀመርያ ጊዜ ከክርስቲያን አገር ወሬ የደረሰኝ በናንተ ወግ ቅዳሴ የሚያቀርቡ ካህናት አስከትሎ በመጣው ኤምባሲ አማካይነት ነው። ስለዚህ በዚህ በመደሰቴ በታላቅ ክብር ተቀበልኳቸው። ከዚህም በኋላ በታላቅ ክብርና በሰላም ወደ አገራቸው ላክኋቸው። በግዛቴ ድንበር በቀይ ባሕር ላይ በሚገኘው ወደብ ላይ በደረሱ ጊዜ ሊወስዳቸው የመጣውን የሕንድ እንደራሴዎን አላገኙትም። እርሱም በደብዳቤው እንደገለጸልኝ አልጠበቃቸውም። እንደራሴዎችዎን የሚለውጡት በየሶስት ዓመት ስለሆነ በርሱ ቦታ አዲስ ስላልተተካ እንደ ራሴው ሊቆይ ስላልቻለ መልእክተኞችዎ በዚሁ ምክንያት ብቻ የሚወስዳቸው መርከብ እስኪመጣላቸው ድረስ በመጠበቅ ጊዜውን ፈጁ። ስለዚህ እነዚህን አምባሳደሮችና የኔንም መልእክት የሚያደርሱልዎ የኔን መልእክተኞች ልኬልዎታለሁ። ወደ ሮም ጳጳስም መልእክተኛ ልኬአለሁ። ወንድሜ ሆይ፤ አባትዎ የጀመሩትን ወዳጅነት ይፈጽሙ ዘንድ እለምንዎታለሁ። በተለይም እኛ ክርስቲያን በመሆናችን እነዚያ ርኩሶች እስላሞች ስለሚመሳ ጠሩብን እርስዎ ሁልጊዜ አምባሳደሮችዎን እንዲልኩብኝ እለምንዎ ታለሁ። ከርስዎ እንጂ ለወደፊቱ ከግብጽና ከሌላም ቦታ የሚመ

ጡልኝል መልእክተኞች አልቀበልም። በሃይማኖቴ ምክንያት እስላሞች አይወዱኝም። እኔን የሚያከብሩኝ ብዙ ጥቅም ለሚያገ ኙበት ለንግዳቸውና ለሸቀጣቸው ሲሉ ነው። ለኔ ያላቸው ክብር ትንሽ ነው፤ በጣም የሚወዱትና የሚያከብሩት ወርቅ ነው፤ ይህንኑም ከአገሬ በዝቆሽ ነው የሚወስዱት። ለዚሁም እኔን አያመሰግኑኝም። እኔ ከነርሱ ጋር የምነግደው ከአባቶቼ በቆየው ልምድ መሠረት ነው። ጠርነት አስነሥቼ በሙሉ እንዳልፈጃቸው ያስገደደኝ ዋናው ምክንያት እግዚአብሔር አምላክ የነዚህ ርኩሶች ንብረት ያደረገው የጌታችን የየሱስ ክርስቶስ መቃብር የሚገኝበትን የየሩሳሌምን ቅዱስ መካን ያጠፋሉ የማለት ሥጋት ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን በግብጽና በሶርያ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያን ማጥፋታቸው አይቀርም ነበር። በዚሁ ምክንያትና በተለይም የሚረዳኝና የሚያጽናናኝ የክርስቲያን ንጉሥ በጎረቤቴ ስለሌለ በጣም ብስጭትና ሐዘን አድሮብኛል።

ወንድሜ ጌታዬ ሆይ፤ የኤውሮጳ ነገሥታት ምንም እንኳ ክርስ ቲያን ቢሆኑ በመተባበር ፈንታ እርስ በርሳቸው በመዋጋታቸው በጣም ቅር ያለኝ መሆኔን ልገልጽልዎ እወዳለሁ። በጎረቤቴ የክርስቲያን ንጉሥ ቢኖር ኖሮ ላንድ ሰዓት ጊዜ ያህል እንኳ ከርሱ አልለይም ነበር። ይህም እንዲሆን የሚፈቅደው እግዚአብሔር ስለሆነ ምን እንደ ምል ወይም ምን እንደማደርግ አላውቅም። ወንድሜ ጌታዬ ሆይ፤ ደብዳቤዎን ማየት እርስዎን እንደማየት አድርጌ የምገምተው ነገር ስለሆነ ሁልጊዜ መልእክተኛና ደብዳቤ ይላኩልኝ። የተራራቁ ሰዎች እርስ በርሳቸው ባላቸው ስሜት ምክንያት ከተቀራረቡ ሰዎች የበለጠ ፍቅር በመካከላቸው መኖሩ የታወቀ ነው፤ ለምሳሌ እኔ የርስዎን ወርቅና ብር ሳላይ ሁልጊዜ ከልብ የምወድዎ መሆኔ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ጌታችን የሱስ ክርስቶስ ወርቅና ብራችሁ ባለበት እኔም በዚያ እገኛለሁ ሲል በወንጌሉ እንደተናገረው ሁሉ እኔ ለርስዎ ያለኝ ፍቅር እንዲሁ ነው። እኔ ወርቄና ብሬ አድርጌ እንደም ገምትዎ እርስዎም ይህንኑ ግምት ይስጡኝ። ልብዎን ከልቤ ያስተ ሳስሩ። ጌታዬ ወንድሜ ሆይ፤ አዋቂ ነዎትና የነገርሁዎትን አይዘንጉ። እርስዎ ካባትዎ የበለጡ አዋቂ ነዎ ለማለት እደፍራለሁ። እንዲህም

ለመሆኑ እግዚአብሔርን እያመሰገንሁ ደስታዬንም «በግዛቱ ዙፋን ላይ የተቀመጠው አዋቂው የንጉሥ አማኑኤል ልጅ የተከበረ ይሁን» እያልሁ እገልጻለሁ። ጌታዬ ሆይ፤ አሕዛብና እስላሞች እነሆ ያስጉዎ፤ በእግዚአብሔር አርዳታ ሊያጠፉዋቸው ይችላሉና። ያባቴን ያህል ብርታት የለኝም ብለው አይስጉ፤ አምላክ ይረዳዎታልና። እንደ ባሕር አሸዋና እንደሰማይ ከዋክብት የበዛ ሠራዊት፤ ወርቅና ስንቅ አለኝ። እርስዎና እኔ በመተባበር የእስላምን ኃይል እንሰብራለን። ሠራዊቴን ከሚያሰለጥኑና መሣርያም ከሚሰጡ ሰዎች በስተቀር ሌላ እርዳታ አልጠይቅዎትም። እርስዎ ፍጹም ሰው ነዎ። አስራ ሁለት ዓመት የነገሠው ሰሎሞን ብርቱ ሰውና ካባቱም የበለጠ ጥበብ የነበረው ሰው ነበር። ባባቴ በአጼ ናኦድ ዙፋን በተተካሁ ጊዜ ሕፃን ነበርሁ። ግዚአብሔር ከአባቴ የበለጠ ኃይል ስለሰጠኝ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛቴን በሙሉ አስገብሬ በግዛቴ በሰላም እኖራለሁ። እግዚአብሔር ይህን የመሰለውን በጎ ነገር ስላደረገልኝ ባንድነት ልናመሰግነው ይገባናል። ጌታዬ ወንድሜ ሆይ፤ ቀጥሎ የተመለ ከቱትን ጉዳዮች ይስሙኝ።

ሐውልት የሚቀርጹ፤ መጽሐፍ አታሚዎች፤ ለማናቸውም ዓይነት ውጊያ የሚያስፈልጉትን ጦሮችና ልዩ ልዩ መሣርያዎች ሠሪዎች፤ ግንበኞች፤ አናጢዎች፤ መድኃኒት ቀማሚዎች፤ ሐኪሞች ቀዳጆች፤ ወርቅና ብር አንጥረኞች፤ የመዳብ ዕቃ ሠሪዎች፤ አፈርና ሸክላ መሥራት የሚያውቁ፤ ነፍጥ ሠሪዎችና እንዲሁም ለአገሬ የሚያስፈልጉትን ማናቸውንም ነገሮች መሥራት የሚችሉ የጅ ጥበብ ባለሞያዎች እንዲልኩልኝ እለምንዎታለሁ። ወንድም ወንድሙን እንደሚለምን ሁሉ እርስዎም በዚህ ጉዳይ እንዲረዱኝ እለምን ዎታለሁ። እግዚአብሔር ይርዳዎ፤ ከማናቸውም ክፉ ነገር ይጠበቅዎ። ቅዱሳን መሥዋዕት ባቀረቡለት ጊዜ እንደተቀበለው ሁሉ የርስዎንም ልመናና ጸሎት እግዚአብሔር ይቀበልዎ። እግዚአብሔር በመጀመርያ የአቤልን፤ ቀጥሎም ኖሕ በመርከቡ በነበረ ጊዜ ያቀረበለትን፤ አብርሃም በሜዲያን ምድር በነበረ ጊዜ ያቀረበለትን፤ ይስሐቅም ከመሃላው ዋሻ በሸሸ ጊዜ፤ ያዕቆብም በቤተ ልሄም ቤት፤ ሙሴም በምድረ ግብጽ፤ አሩምም በተራራ ላይ፤ የሁና የገልገሳ ልጅ ያሶምም፤

ገዲዮንም በባሕር ዳር፤ ማኑሄና ሚስቱም፤ ሳምሶን በምድረ በዳ በጫብሶ በሚገኝበት ጊዜ፤ ዮፍታህ በጦር ሜዳ ላይ፤ ቦሮምና ድልቦራ በደብረ ታቦር መሪውን ሴንሴራን በገጠመች ጊዜ፤ ሳሙኤልም፤ ነቢዩ ራማም፤ ዳዊትም በአውድማ ላይ፤ አርባኖም፤ ሰሎሞንም በጊቢኦን ከተማ፤ ኤልያስም በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ያንድ የሙት ሚስት ልጅን ባሥነሣ ጊዜ፤ ርብቃም በውኃ ጉድጓድ አጠገብ፤ የሆሳፋጥም በጦር ሜዳ ላይ፤ ምናሴም ኃጢአት ሠርቶ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰ በኋላ፤ ኢዮሲያም ከተመለሰ በኋላ በፋሲካ፤ ዳንኤልም በአንበሶች ጎሬ፤ ዮናስም በአሣነባሪው ሆድ ውስጥ፤ ሶስቱ ጓደኞች ስድራቅ ሚስሐቅና አብዲናጎ በነበልባል ውስጥ፤ ሐናም በታቦቱ ድንኳን ውስጥ ሆና፤ ከዘሩባቤል ጋር ሆኖ የከተማውን ግንብ አጥር የሠራው ነሕምያም፤ ማትያስም ከልጆቹ ጋር በዓለም ማዕዘን፤ ኤሳውም በተባረከ ጊዜ መሥዋዕት እንዳ ቀረቡለት ሁሉ የርስዎንም መሥዋዕትና ጸሎት ይቀበል። ሰላም ለርስዎ ይሁን። እርስዎንና በአገርዎ የሚገኙትን መካሮችዎን ሊቃነ ኤጲስ ቆጶሳትንና ኤጲስቆጶሳትን፤ ቄሶቹንና ዲያቆኖቹን፤ ሴቶቹንና ወንዶ ቹን፤ ሁሉንም በቅድስና እስማለሁ። የእግዚአብሔ ፀጋ የእመቤታችንና የአምላክ በረከት ከርስዎና ከሁሉም ጋር ይሁን።

ምዕራፍ ዘጠኝ፤ የብራጋ ኤጲስቆጶስ ለፍራንሲሽኩ አልቫርሽ ያቀረበለት ጥያቄና እርሱም የሰጠው መልስ።

እኛ በኩይምብራ ቤተ መንግሥት ሄደን በዚያ ጥቂት ጊዜ እንደቆየን ንጉሡ ወደ አልሜይሪኝ ሄዱ። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለሮም ጳጳስ ታዛዥነቱን እንድገልጽለት እንዲሁም አንድ ደብዳቤና የወርቅ መስቀል ለጳጳሱ እንዳደርስለት አደራ ብሎኝ ስለነበር ጉዜዬን ለመቀጠል እንዲፈቀድልኝ ወደ

አልሜይሪኝ እየሄድሁ ንጉሡን አሳስባቸው ነበር። ምንም እንኳ ግርማዊነታቸው የጉዳዩን ብርቱነት ያልዘነጉት ቢሆንም በፈረንሳይ አገር በሚደረገው ጦርነት ምክንያት መንገዱ አስጊ ነበር። ንጉሡ ከአልሜይሪኝ ወደ ሊዝቦን ከተመለሱ በኋላም እዚያው ድረስ እየሄድሁ አባስባቸው ነበር። ነገር ግን ከዚህ በፊት የተገለጸውን መልስ ብቻ ይሰጡኝ ነበር። በዚሁ ጊዜ ብራሽ ኔቱ በውጭ አገር የግርማዊነቻቸው አምባሳደር እንዲሆን ተሾመ፤ ነገር ግን የሚሄድበት አገር ስም አልተገለጸም። ከአምባሳደሩ ጋር እንድሄድ ግርማዊነታቸውን እንድለምናቸው ብራሽ ኔቴ ራሱ አሳሰበኝ። አምባሳደሩ ወደሮም መሄዱ ከተረጋገጠ በኋላ ከርሱ ጋር እንዲልኩኝ ግርማዊነታቸውን ለመንኳቸው። ብራሽ ኔቱ የሚሄደው ወደ ንጉሠ ነገሥት እንጂ ወደ ሮም አለመሆኑን ግርማዊነታቸው ነገሩኝ። ከተባለው አምባሳደር ጋር ሊልኩኝ አስበውበት የነበሩ መሆናቸውንም ጨምረው ገለጹልኝ። ነገር ግን ዶም መርቲኙን በቅርቡ ወደ ሮም ሊልኩት አስበው ስለነበሩ ከርሱ ጋር እንደምሄድ ተስፋ ሰጡኝ። በዚሁ ጊዜ ውስጥ በብራጋ የኤጲስቆጶስ ግዛት ውስጥ አንድ ክፍት ቦታ ስለነበር በግርማዊነታቸው ትዕዛዝ በተባለው ቦታ እንድተካ ሄጄ በነበርሁበት ጊዜ ኤጲስቆጶሱ ስለኢትዮጵያ ደጋግመው ይጠይቁኝ ነበር። እኔም የማውቀውን በተቻለ መጠን አስተካክዬ ስመልስ የኔ ቃል በሙሉ እንዲጻፍ አዘዙ። ጥያቄዎቹና መልሶቹ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው።

የብራጋ ኤጲስቆጶስ ሲኞር ዶም ዲዮጉ ድሶዛ ለፍራንሲሽኩ አልቫርሽ ያቀረቡለት ጥያቄዎች አባ ፍራንሲሽኩ ስለኢትዮጵያ በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ ያልተጠቀሱ ጉዳዮች ናቸው። ንጉሥ ዶም አማኑኤል ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄድ የሾሙት አምባሳደር ድዋርት ጋልቫው ስለሞተ በርሱ ምትክ ከተላከው ከዶም ሩድሪጉ ጋር ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ ነበር። ኤምባሲው በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ወደብ በምጽዋ (በሐርኪኮ አጠገብ) ሚያዚያ 27 ቀን 1520 ዓም ደርሰው ከዚያም ወመካከል አገር ገብተው ስድስት ዓመት ከቆዩ በኋላ ሚያዚያ 28 ቀን 1527 ዓም ከተባለው ወደብ መርከብ ይዘው ወደአገራቸው ተመለሱ። ከዚህ በኋላ ግርማዊ

የፖርቱጋል ንጉሥ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ያዘዙለትን ሥራ ለመቀበል ሐምሌ 30 ቀን 1529 ዓም ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ በብራጋ ከተማ ደረሰ።

ፍራንሲሽኩ አልቫርሽ እንዲህ አለ፤ «በኢትዮጵያ አብዛኛው ሰው በቀን አንድ ጊዜ ማለት ራት ብቻ ይመገባል። ቄሶችና መነኩሴዎች ዓቢይ ጾምን በጥብቅ ስለሚጾሙ ብዙዎቹ በሳምንት ሶስት ቀን ማለት ማክሰኞ፤ ሃሙስና ቅዳሜ ብቻ ይመገባሉ፤ የወይን ወይም የማር ጠጅ አይጠጡም፤ በነዚህ ፈንታ በሌላ ዓይነት ቅጠላቅጠል የተጠመቀ መጠጥ አለ። በዓቢይ ጾም ወራት ሥጋን፤ ወተትን፤ ቅቤን ወይም እንቁላልን በሞት ቢያስፈራሩዋቸው እንኳ አይቀምሱም። ጎመንና አንዳንድ ፍራፍሬም ይበላሉ። ወንዶችና ሴቶች ታላላቆችና ታናናሾች (ከልደት በዓል እስከ እመቤታችን ንጻት በዓል ካለው ጊዜ በስተቀር) ዓመቱን በሙሉ ረቡዕና አርብን ይጾማሉ። መነኩሴዎች፤ ቄሶች፤ ጨዋዎችና መኳንንትም ከቅዳሜና ከእሁድ በስተቅር ዓመቱን በሙሉ ይጾማሉ።

ወንጀለኛ እንደበደሉ መጠን ይገረፋል፤ አንዳንድ ጊዜም ዓይኖቹን ያወጡታል፤ እጁን ወይም እግሩን ይቆርጡታል እንጂ የሞት ፍርድ አይፈርዱበትም። ነገር ግን አንድ ወንጀለኛ ሁለት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ሲቀማ ስለተያዘ ሲያቃጥሉት አይቻለሁ። የአገሩ ጳጳስ ወይም ፓትርያርክ አቡን ይባላል፤ ትርጓሜውም አባት ማለት ነው። በንጉሠ ነገሥቱ ግዛቶች በሙሉ ከርሱ በስተቀር ተእዛዝ የሚሰጥ ሌላ ሰው የለም። ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ወይም ንጉሥ በሚያሰኝ መጠርያ ይታወቃል። በአገሩ ሐኪም ስለማይገኝ በሽተኞችን ይተኩሱዋቸዋል። ራስ ምታት ያለባቸውን ሰዎች ያግሙዋቸዋል። አንዳንድ ጊዜም በብርጭቆ ይነጥቁዋቸዋል። ለንጽሕና ኮሶ ይጠጣሉ።

በአገሩ በሙሉ ከአንድ ሺ ስድስት መቶ ቤተሰቦች በላይ ያለበት ከተማ አይገኝም፤ ይህን ያህል የሚገኙባቸው ከተማዎችም ጥቂት ናቸው። ዙርያቸውን በግንብ የተከበቡ ከተማዎች ወይም ግንቦች አይገኙም። ነገር ግን ለመቁጠር የሚያስቸግሩ ብዙ

መንደሮች በያለበት ይገኛሉ። አብዛኞዎቹ ወይም ብዙዎቹ ቤቶች አንድ ደርብ ብቻ ያላቸው ጠፍጣፋ የሣር ክዳን ያላቸው ክብ ናቸው። በቤቶቹ ዙርያ ብዙውን ጊዜ ትርፍ ቦታ አለ።

ብዙዎቹ ሰዎች በቁርበት ላይ ነው የሚተኙት፤ ሌሎችም በጠፍር አልጋ ላይ ይተኛሉ፤ ጠረጴዛ በየትም አይገኝም። የጠረጴዛ ልብስ ወይም የአፍ መጥረጊያ ፎጣ በሌለበት ገበታ ላይ ምግባቸውን አቅርበው ይመገባሉ። የሚተጣጠቡት በገበቴ ነው፤ የሚጠጡትም በወጭት ነው። ብዙዎች ሰዎች ጥሬ ሥጋ ይበላሉ፤ አንዳንዶችም በፍም ጠብሰው ወይም በእሳት ለብልበው ይበሉታል፤ እንጨት በማይገኝበት አገር ሥጋውን በኩበት እሳት ጠብሰው ይበሉታል። ብዙ ጥዋፍ ይገኛል፤ ሻማን ከሰም አይሠሩም፤ በአገሩ ዘይት አይገኝም፤ ነገር ግን ሂና የሚሉት ጣዕም የሌለው ወርቅ የሚመስል ነገር አለ፤ የሚሠራው ከአንድ ዓይነት ቅጠል ነው። በየወንዞቹ ከሚጸመዱት በስተቀር በአገሩ በሙሉ የባሕር አሣ አይገኝም። ምንም እንኳ ከዚያ የመጡ መነኩሴዎች ቢያወሩም ከቅዱስ እንጦንዮስ ማህበር በስተቀር የሌላ ማህበር ገዳም የለም።

የአገሩ ጨዋዎች፤ መነኩሴዎችና ካህናት ደህና ልብስ ይለብሳሉ፤ ተራው ሕዝብ ግን ሽርጥ ለብሶ አጎዛ ይደርባል። ብዙዎቹ ገዳሞች የተቆረቆሩት በከፍተኛ ቦታዎች ወይም በገደሎች ሥር ነው። ገዳሞቹ ከግብርና ከቀረጥ ብዙ ገቢ ያገኛሉ። በብዙዎቹ ገዳሞች ዓመቱን በሙሉ ሥጋ አይበሉም፤ እንዲሁም በአገሩ አሣ ስለማይገኝ ይህንም የሚበሉት አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው። በገዳሞቹና በቤተ ክርስቲያኖቹ የሚደረገው ቅዳሴ በመዝሙረ ዳዊትና በቅኔ ነው። በቤተ ክርስቲያኖቹ ሁሉ ሁለት መጋረጃዎች አሉዋቸው፤ አንደኛው በመቅደሱ በር ላይ ይገኛል፤ በዚህ በር ከቄሶች በስተቀር ማንም ሊገባ አይችልም። ሌላው ደግሞ በቤተ ክርስቲያኑ መካከል ተጋርዶአል። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመግባት የክህነት ሥልጣን ስለሚያስፈልግ ለዚሁ ብቻ ሲሉ ብዙ ጨዋዎችና መኳንንት ክህነት ይቀበላሉ።

ካህናቱ በቤተ ክርስቲያንና በገዳሞች በር ብቅ ይሉና ከወንጌል ወይም ከሐዋርያት መልእክት በሚያነበንብ ድምጽ ያነባሉ፤ ምዕመናኑንም የሚያቆርቡት በዚሁ ቦታ ሆነው ነው። ቀሳውስቱ የሚቆርቡት በመሠውያው ላይ ነው። ሥጋ ወደሙን ለማንም አያሳዩም፤ ሰሞነኛው ቄስ ቁርባን ለመቀበል በቀረበ ጊዜ በላይ የተቀመጠውን ትንሽ ሽራፊ ሕብስት ይወስድና ሌሎቹን ሁለቱን ትልልቅ ቁራሾች ለምዕመናኑ ይተውላቸዋል። ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ሰዎች ሁሉ በየቀኑ ይቆርባሉ፤ ለቁርባን እንጂ ለሌላ ጉዳይ ወደቤተ ክርስቲያን አይመጡም። ካቆረቡዋቸው በኋላ አፋቸውን የሚጉመጠመጡበት ቅዳሴ ጠበል ይሰጡዋቸዋል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መቀመጥ ለማንም አይፈቀድም፤ ጫማ አድርጎ መግባት በፍጹም ክልክል ነው። እክ ማለት ወይም በትፋት ክልክል ነው። በቤተ ክርስቲያን ውሻ ማስገባት አይፈቀድም። የሚናዘዙትና የኃጢአት ሥርየት የሚቀበሉት ቁመው ነው። ደብተራዎች ወይም መነኩሴዎች በቤተ ክርስቲያን ይጸልያሉ፤ መነኩሴዎች ትዳር አይዙም፤ ቄሶችና ደብተራዎች ግን ለማግባት ይችላሉ። ደብተራዎች በየቤታቸው ይመገባሉ፤ መነኩሴዎች ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማህበር ይበላሉ።

የቤተ ክርስቲያኖች መሪዎች ሊቀ ካህናት ይባላሉ። ደብተራዎች የሚኖሩት በቤተ ክርስቲያኖች አካባቢ በሚገኙ መንደሮች ነው። ልጆቻቸው እንደ አባቶቻቸው ደብተራዎች ይሆናሉ። የቄሶች ልጆች ግን ካልፈለጉ በስተቀር ያባቶቻቸውን ሞያ ለመከተል ግድ የለባቸው። ለቤተ ክርስቲያኖች አስራት አይከፈልም፤ ገቢያቸው የሚመጣው አድባራትና አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ካላቸው ርስት ነው። ካህናት የተከሰሱ እንደሆነ በተራው ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ይገደዳሉ። ሸሚዝ የሚመስል ትልቅ ቀሚስ ያጠልቁና ከመካከሉ ለራስ ማስገቢያ ያህል የተቀደደ ጨርቅ ይደርባሉ። ቄሶችና መነኩሴዎች ራሳቸውን ይላጫሉ፤ ቄሶች ግን በራሳቸው ላይ ምንም አይደፉም፤ ወይም አይጠመጥሙም። በቤተ ክርስቲያኖቹ ሁሉ ካንድ ጊዜ በላይ ቅዳሴ አይገቡም። ለምጽዋት ወይም ለሙታን አይቀድሱም።

አንድ ሰው በሞተ ጊዜ ቄሶቹ ጽናና መስቀል ቅዳሴ ጸበልም ይዘው መጥተው ጥቂት ከጸለዩ በኋላ ሬሳውን በቶሎ ይወስዱታል። በማግሥቱ መክፈልት ይቀርባል። በቤተ ክርስቲያኑ ገረገራ ማንም ወይም ምንም እንዳይገባ ለመከልከል ደጀሰላሙ ይዘጋል።

ንጉሠ ነገሥቱ የተወሰነ መኖርያ ስለሌለው በድንኳን ሆኖ ካንድ ቦታ ወደሌላ ይዘዋወራል። ባንድ ቦታ ከትሞ ሲያርፍ አምስት ወይም ስድስት ሺ ማለፊያና መናኛ ድንኳኖች ይተከላሉ። ከሃምሳ ሺ በላይ የሚሆኑ በቅሎኞችና ፈረሰኞች ንጉሠ ነገሥቱን ይከተላሉ። የንጉሠ ነገሥቱ ማዕድ ቤት ከንጉሣዊው ድንኳን በስተጓሮ በኩል ጥቂት እልፍ ብሎ ይገኛል።

ግብር የሚገባው ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው። ወጡ ወጥቁር የሸክላ ድስት ሲመጣ እንጀራው ደግሞ በእንጨት ገበታ ላይ ሆኖ በሐር መሸፈኛ ተሸፍኖ አሽከሮች በጭንቅላታቸው ላይ አኑረውት በክብር ያልፋል።

ንጉሠ ነገሥቱ ብዙ የቤተርስት ምድረ ስላለው ከዚያ የሚመጣው እንጀራ ለመኳንንትና ለድሆች ወይም ለገዳሞች ይሰጣል። ንጉሠ ነገሥቱ ከዚህ ሃብቱ ምንም ጥቅም አያገኝበትም። በአገሩ በሙሉ የስንዴና የገብስ እንጀራ ይገኛል። በሌሎች ክፍሎች ደግሞ በይበልጥ ማሽላ ይገኛል። እነዚህ እህሎች በማይገኙበት ቦታ ደግሞ ጤፍና ዳጉሳ፤ ሽንብራና አደንጓሬ፤ ባቄላና አተር ጎመናጎመ ኖችም ይገኛሉ። በአገሩ በሌሎች ክፍሎች ደግሞ ማናቸውም ዓይነት እህልና ጎመናጎመኖች በብዛት ይገኛሉ።

ምንጮች በያለበት ቢገኙም በጥርብ ድንጋይ አምረው የታነጹ አይገኙም። ንግሥታት ሳባና ሕንደኬ በኖሩበት በአክሱም ከተማ አምረው የታነጹ የውኃ ጉድጓዶችና ገንዳዎች ይገኛሉ። በዚህ ከተማ ማለፍያ ሆነው የተሠሩ የአንበሶችና የውሾች የበሮችና የሌሎችም ጥንታዊ ነገሮች ሐውልቶች አሉ። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ቅዱስ

ፊልጶስ አጥምቆት የክርስትናን ሃይማኖት በተቀበለው በጃንደረባዋ ምክር ንግሥት ሕንደኬ የክርስትናን ሃይማኖት የተቀበለችው በዚሁ ከተማ ነው።

በአገሩ በየትም ቦታ የድንጋይ ወይም የእንጨት ድልድይ አይ ገኝም። በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት አይሁዶች በፍጹም አይገኙም። በያለበት የሸንኮር አገዳ በብዛት ይገኛል። ነገር ግን ከዚህ አገዳ እንዴት ስኳር ሊሠራ እንደሚቻል ሕዝቡ አያውቅም። በየካቲት ወር በስለው በሚያዚያ ወር የሚደርቁ ወይንና ኮክ ይገኛሉ፤ ብርቱካንና ሎሚ ትርንጎም በብዛት ይገኛሉ። ጎመናጎመንን ስለማያለሙ እነዚህ በብዛት አይገኙም።

ልዩ ልዩ የዱር አራዊት ማለት አንበሳ፤ ነብር፤ የሕንድ ነብር፤ ተኩላ፤ አሳማ፤ ጎሽ፤ ቀበሮ፤ ደልጋ አንበሳ፤ እርያ፤ ጃርት፤ ጥርኝ፤ አጋዘን፤ ድኩላ ዝሆንና ሌሎችም የማናውቃቸው እንስሶች ይገኛሉ። ሁለቱ ያላየኋቸው የዱር አራዊት ድበና ጥንቸል ናቸው። «ከፔጋና ከኩኩ» በስተቀር በዓለም የሚገኙት ልዩ ልዩ ወፎች ሁሉ በአገሩ ይገኛሉ።

ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ዝንጀሮዎች በያለበት ይገኛሉ። ለምሳሌ በባሕር ነጋሹ ግዛት ሰራዌ በተባለ ቦታ በመከር ወራት ዝንጀሮዎች ተራራውን ዙረው እስኪሄዱ ድረስ ያባርሩዋቸዋል። የእህል መሰብሰ ቢያው ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ በዝንጀሮዎቹ መተላለፊያ ቦታ ላይ ሁለት ሰዎች በቀን ሲጠብቁ እንዲውሉ ይታዘዛሉ። ዝንጀሮዎች በሌሊት ስለማይሄዱ በዚህ ጊዜ ጠባቂዎች አያስፈልጉም። የመከሩ ወራት ካለፈ በኋላ ግን የጠባቂዎች አገልግሎት ስለማይፈለግ ዝንጀሮዎቹ በያለበት ሲፈነጩ ይታያሉ።

በጫካው ውስጥ ጦስኝ በብዛት ይገኛል፤ ከጥድና ከበለስ በስተቀር በኛ አገር የሚበቅሉትን የመሰሉ ዛፎች በዚህ አገር አይገኙም። እንዲሁም «ሜሎን፤ ኪውካምበር፤ ራዲሽም» አይገኝም። በአገሩ የወርቅ ወይም የብር ገንዘብ ስለሌለ ሕዝቡ የሚገበያየው

ዕቃ በዕቃ በመለዋወጥ ነው። ወይም እንደገንዘብ በሚገምቱት በአሞሌ ይገበያያሉ። የተልባ እግር ይገኛል፤ ነገር ግን ቃጫ የለውም። ከተልባ እግር ልብስ ሊሠራ እንደሚቻል ሕዝቡ አያውቅም። ጥጥ በብዛት ስለሚገኝ ይህንኑ እየፈተሉ ልብስ ይሠራሉ። ብዙ ባለቀለም ልብስ ባገሩ ይገኛል፤ በደጋው የሚኖረው ሕዝብ ማቅ ይለብሳል።

ቤተ ክርስቲያኖች ምንም እንኳ ግድግዳቸው ማለፊያ ሆኖ የተሠራ ባይሆንም አምረው የታነጹ ናቸው። በግድግዳዎቹ ላይ ምንም አያኖሩባቸውም፤ ጣርያዎቹን በረጃጅም ምሰሶዎች ይደግፉዋቸዋል። ወርቅ ብር መዳብና ቆርቆር ይገኛል፤ ነገር ግን ሕዝቡ ከምድር ቆፍሮ አውጥቶ በጥቅም ማዋል አያውቅም።

ከጤነኛው ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ብዙ የሥጋ ደዌ በሽተኞች ይገኛሉ፤ እንዲያውም አንዳንድ በጎ አድራጊ ጤነኞች ምዕመናን በእጃቸው ቁስላቸውን ያጥቡላቸዋል። በአገሩ በሙሉ ማር ይገኛል፤ ቀፎዎቻቸውን የሚሰቅሉት በቤታቸው ውስጥ ሲሆን ለንቦቹ መግቢያና መውጪያ ግድግዳውን ይበሱታል። አንዳንድ ጊዜም ንቦቹ በዋናው በር ሲገቡና ሲወጡ እንዲያውም በቤቱ ውስጥ ሲበሩ ይታያሉ። በንቦቹ ምክንያት ቤቱን ለቆ የሚሄድ ሰው የለም። ይህ ከሆነ ግን ንቦቹም ለቀው ይሄዳሉ። ብዙ ቀፎዎች በተለይም በየገዳማቱ ተሰቅለው ይታያሉ። በየተራሮቹና በየጫካው ብዙ ንብ ይገኛል፤ ገበሬዎች ብዙ ቀፎ አጥነው በየጫካው ይሰቅሉና ንቦቹ ከገቡ በኋላ ወደቤታቸው ያመጡዋቸዋል።

ምዕመናን በቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ወይም ከገረገራዎች ውስጥ ወይም ውጭ በቅዳሴ ጊዜ ስለማይቀመጡ ብዙዎች ሰዎች መቋሚያ አላቸው። ከቅዳሴ ውጭ እስኪሆን ድረስ እያንዳንዱ ሰው በማቋሚያው ላይ ይደገፋል። በየቤተ ክርስቲያኖቹ የጌታችን፤ የእመቤታችን፤ የሐዋርያትና የአበው፤ የመላእክትና የቅዱሳን ምስሎች በየግድግዳዎቹ ላይ ተሰቅለዋል። የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስል ግን በየቤት ክርስቲያኖቹ ሁሉ ይገኛል። ከእንጨት ወይም ከድንጋይ የተሠሩ

ምስሎች የሉም፤ በየቤተ ክርስቲያኖቹ ብዙ መጻሕፍት ይገኛሉ፤ የተጻፉትም ክርስትና ለመጀመርያ በተሰበከበት በትግሬ ግዛት ቋንቋ ነው።[1] በዚህ አገር ደብዳቤ መለዋወጥ ወይም በፍርድ ቤት ማናቸውንም ነገር መጻፍ የተለመደ ነገር አይደለም። የፍርድ ጉዳይ ሁሉ የሚፈጸመው በንግግርና በቀላጤ አማካይነት ብቻ ነው። የንጉሠ ነገሥቱን ሃብት ሲረከቡና ሲያስረክቡ ብቻ ጉዳዩን በጽሑፍ ሲያሰፍሩት አይቻለሁ።

መኳንንቱ ገበሬዎችን ባያጠቋቸው ኖሮ በአገሩ ውስጥ ብዙ እህል ሊመርት ይችል ነበር። ገበሬዎቹ ሠርተው ያተረፉትን ሃብታሞች የሚወስዱባቸው መሆናቸውን በመረዳት ለችግራቸው ማሸነፊያ ያህል ብቻ ያመርታሉ። በንጉሠ ነገሥቱ ከተማ ብቻ እንጂ ልኳንዳ በሌላ ቦታ ከቶ አላየሁም። አንድ ሰው ፍሪዳ ለማረድ በፈለገ ጊዜ ከአገረ ገዥው አስቀድሞ ፈቃድ መጠየቅ አለበት። ብዙዎች ሰዎች በመሃላ ጊዜ እንኳ ቢሆን እውነት አይናገሩም። ነገር ግን በንጉሠ ነገሥቱ ስም የማሉ እንደሆነ እውነተኛነታቸው የተረጋገጠ ነው። ውግዘትን በጣም ይፈራሉ፤ የሚጎዳቸውን ነገር እንዲፈጽሙ ቢታዘዙ እንኳ ውግዘቱን በመፍራት ብቻ ይፈጽሙታል።

መሃላ የሚፈጸመው ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው፤ የሚምሉት ሰዎች ከሁለት ቄሶች ጋር ሆነው ወደቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ። ቄሶቹ ጽናውን ይዘው ሲያጥኑ የሚምለው ሰው በቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ እጁን ያኖራል። ቄሱ ቀጥሎ የተመለከቱትን የመሃላ ቃሎች አንድ በአንድ ሲያዝ መሃዩ አሜን ይላል።

<u>ቄሱ፤</u> «እውነቱን እናገራለሁ፤ ሃሰት የተናገርሁ እንደሆነ አንበሳ የዱር አራዊትን እየያዘ እንደሚለባ ሁሉ የኔንም ነፍስ ዲያቢሎስ ይብላት፤ ስንዴ በወፍጮ እንደሚፈጭ ሁሉ የኔንም ነፍስ ዲያቢሎስ ይፍጫት።»

መሃዪ፤ «አሜን»

ቄሱ፤ «እንጨት በእሳት እንደሚማገድ ሁሉ የኔም ነፍስ በገሃነም እሳት ተማግዳ አመድ ትሁን።»

መሃዪ፤ «አሜን»

ቄሱ፤ «ሃሰት የተናገርህ እንደሆነ ይህ ሁሉ መሃላ ይድረስብህ፤ እውነት የተናገርህ እንደሆነ ግን ዕድሜህ በክብር ይረዝማል። እግዚአብሔር ነፍስህን በገነት ከብሩካን ጋር ያሳርፉታል።»

መሃዪ፤ «አሜን»። ይህ ስነ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ የማለው ሰው ሊመሰክር ይችላል።

የትንሳኤ፤ የዕርገት፤ የጰራቅሊጦስ፤ የስግደት፤ የግዝረት፤ የጥምቀትና ሌሎችም የቅዱሳት በዓሎች አከባበር ከኛው ጋር በቀንና በጊዜ ይስማማል። ከኛው አከባበርም የማይስማሙ አሉ። የዓመቱ የመጀመርያ ቀን የቅዱስ ዮሐንስ ራስ በተቆረጠበት ቀን በመስከረም 29 ቀን ነው። በአንድ ዓመት አሥራ ሁለት ወሮች አሉ። እያንዳንድ ወር ሰላሳ ቀን ነው። በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ስድስት ቀን፤ በተራው ዘመን ግን አምስት ቀኖች ያሉበት ጳጉሜን የተባለ ጊዜ አለ፤ ትርጓሜውም የዓመት ፍጻሜ ማለት ነው። ጳጉሜን ስድስት ቀን ሲሆን በኛም ቀን መቁጠርያ አንድ ቀን ትርፍ አለ።

በሕማማት ሳምንት በውሉ ጥቁር ወይም ሰማያዊ ልብስ ይለብሳሉ። ይሁዳ ጌታችንን በመሳም ነው አሳልፎ የሰጠው በማለት በሐዘን እርስ በርሳቸው አይነጋገሩም። በየቤተ ክርስቲያኖቹ ግድግዳዎች ላይ ብዙ ምስሎች ተስለው ቢታዩም በመስቀሎች ላይ የክርስቶስ መስቀል ምስል አይታይም። ይህ የማይታይበት ምክንያት የክርስቶስን ስቅለት ልናይ የሚያበቃን ብጽዕና የለንም ብለው ስለሚያምኑ ነው። ቄሶችና መነኩሴዎች መኳንንትም ሁሉ በፈረስም ሆነ በእግራቸው ሲሄዱ በእጃቸው መስቀል ይይዛሉ። ተራው ሕዝብ ግን በአንገቱ ላይ ትንሽ መስቀል ያንጠለጥላል። እያንዳንዱ ቄስና መነኩሴ በትንሽ የመዳብ ዕቃ ጸጠል ይይዝና ወደተጠራበት ቤት ሲሄድ በዚያ የሚገኙትን ሁሉ ይረጫቸዋል። ለማዕድ ከመቅረባቸው በፊት ምግብና መጠጥ የቀረበባቸውን ዕቃዎች ይረጩዋቸዋል።

ዋናው የመከላከያ መሣርያ ጦር ነው፤ ጎራዴዎች በብዛት አይገኙም፤ የደረት መከለያ ጋሻ አልፎ አልፎ ቢገኝም መናኛ ነው። እንዲሁም መሆኑን የነገሩኝ የኛው ፖርቱጌዞች ናቸው። ወስፈንጥርና ቀስት በብዛት ይገኛል። ቀስቶቹ እንደኛዎቹ ላባ የለባቸውም። የራስ መከለያ ባርኔጣ ብዙ አላየሁም። አንዳንድ ቢገኙም ሕዝቡ ፖርቱጌዞችን ካወቀ በኋላ ያገኘው ነው። ብዙዎች ሰዎች ጋሻ አላቸው፤ እኛ ከሰጠናቸው ከሁለቱ በስተቀር በአገሩ በሙሉ የአለሎ መወርወርያ መድፍ የለም። እኛ በመጣን ጊዜ ከቱርክ ነጋዴዎች የገዙዋቸው አስራ ሁለት ነፍጦች ነበሩ። ነፍጥ በተገኘ ጊዜ በተጠየቀው ዋጋ እንዲገዛና ወታደሮችም አተኳኮሱን እንዲማሩ ንጉሠ ነገሥቱ አዞዋል።

መናኛ ጥሩንባዎች ይገኛሉ፤ እንዲሁም ከካይሮ የሚመጡ ነጋሪቶች አሉ፤ ከበሮና አታሞ ጽናጽልም አላቸው። ዋሽንትና መሰንቆም አላቸው፤ እነዚህን መሣርያዎች ይዘው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት እየቀረቡ ይዘፍናሉ፤ ነገር ግን ዘፈናቸውና የሙዚቃውም ዜማ ደስ አያሰኝም። አገሩ ደጋና ቆላ ቢሆንም በጠቅላላው ለምለም ነው። በበረዶ የተሸፈኑ ተራራዎች የሉም፤ ነገር ግን በብዙ ቦታ በተለይም በሜዳዎች ላይ ኃይለኛ አመዳይ ይጥላል። በአገሩ በውሉ ብዙ የቅንድ ከብቶች ይገኛሉ።

ምንም እንኳ በአቅራቢያው ብደርስም የአባይን ወንዝ አላየሁም፤ በአንድ ቀን የምንጓዘው መንገድ ከአራት ወይም ከአምስት ሌግዋ አይበልጥም። ከኔ ጋር የተጓዙ አንዳንድ ባልደረቦቼ የአባይ ወንዝ የሚነሣበትን ቦታ ጎብኝተዋል። ወንዙ የሚነሣው በጎጃም ግዛት ከሚገኙ ታላላቅ ሐይቆችና ከዚያም ወደግብጽ አገር የሚሄድ መሆኑን ነግረውኛል። በሐይቆቹ ውስጥ ደሴቶች መኖራቸውንም ጨምረው ነግረውኛል። በግብጽ አገር የናይል ወንዝ የሚሞላው ከመስከረም 15 ቀን ጀምሮ እስከ ጥቅምት ወር በጨረሻ ድረስ ነው ይባላል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የኢትዮጵያ ክረምት ከሰኔ አጋማሽ ጀምሮ እስከ መስከረም አጋማሽ ድረስ ስለሚቆይ ነው። በነዚህ ወራት በኢትዮጵያ በሚጥለው ብርቱ ዝናም ምክንያት የናይል ወንዝ ግብጽን ያጥለቀልቃል።

ንጉሠ ነገሥቱ ወይም ሌላ ማንም ሰው ቢሆን በበቅሎ ወይም በፈረስ ላይ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሲደርስ ራቅ ብሎ ይወርድና ቦታውን እስኪያልፍ ድረስ በእግሩ ይሄዳል። ከቤተ ክርስቲያኑ በጣም እልፍ ካለ በኋላ በበቅሎው ወይም በፈረሱ ይቀመጣል። ንጉሠ ነገሥቱ ከነአጀቡ ሲጓዝ ስምንት ቄሶች ታቦት ተሸክመው አብረው ይጓዛሉ። ታቦቱን በቃሬዛ ላይ አኑረው ስምንቱ ቄሶች በአራት በአራት ተራ እየገቡ ያጉዙታል። ከታቦቱ ፊት አንድ ቄስ ጽና ይዞ ሲያጥን ከርሱ በፊትም ምርዋ እየመታ የሚሄድ አንድ ዲያቆን አለ። ቀድመው የሚሄዱ ሰዎች እንዳሉ መንገድ ይለቃሉ። በፈረስ የሚሄዱም ይወርዱና ለታቦቱ እጅ ይነሣሉ።

ከንጉሠ ነገሥቱና ከአቡነ ማርቆስ ቤት በስተቀር የወይን ጠጅ በየትም አይገኝም። በሌላ ቦታ ቢገኝም በድብቅ የተዘጋጀ ነው። ምዕመናኑን የሚያቆርቡበት ደሙ የሚዘጋጀው ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው። አስር ቀን ያህል ዘቢብ በውኃ ውስጥ ይዘፈዝፋሉ። በዚህ ጊዜ ውስጥ አብጦ የሚቆየውን ዘቢብ ከውኃው ውስጥ አውጥተው ጠፈፍ እስኪል ድረስ ካቆዩት በኋላ በጨርቅ ይሸፍኑትና ይጨምቁታል።

የኢትዮጵያ ፈረሶች የጋሊስያ (እስፓኝ) ፈረሶችን የሚመስሉ መናኞች ናቸው። ከአረብ አገር የሚመጡት ፈረሶች ግን በጣም ማለፊያዎች ናቸው። ይሁን እንጂ በጣም ረጃጅሞቹንና የሚያምሩትን የግብጽ ፈረሶችን አይተካከሉም። ከግብጽ አገር ብዙ ባዝራዎች እያስመጡ ብዙ መኳንንት በቤታቸው ፈረስ ያረባሉ። ውርንጫዎቹ ከሶስት ቀን በላይ እንዲጠቡ አይፈቀድላቸውም። አብዛኞቹንም ወዲያው ይጋልቡዋቸዋል። ጠቦቶቹን ውርንጫዎች ከናታቸው አርቀው ያስሩዋቸዋል። ብዙ ላሞች ስላሉዋቸው ለውርንጮቹ የላም ወተት ያጠጡዋቸዋል።

አምላክ ይመስገን።

ማ ስ ታ ወ ሻ

ከሚቀጥሉት ማስታወሻዎች አንዳንዶቹ «ፕሬስተር ጆን ኦቭ ዘ ኢንዲስ» ከሚለው የሃክሊዩት ሶሳየቲ እትም የተወሰዱ ናቸው። ይህንኑም ለማስታወቅ በማለት ባንዳንድ ቦታ (ሃ፡ሶ) የሚል ማሳጠርያ ይነበባል።

ምዕራፍ 1

[1] ይህ ስም ተጣርቶ ሳልታወቀ አንድ የክርስቲያን አገርን ለሚገዛ ንጉሥ ኤውሮፓውያን የሰጡት መጠርያ ነበር። ከብዙን ፍለጋ በኋላ ይህ ንጉሥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆኑ ተረጋገጠ። ሃተታውን ቀጥሎ በተመለከተው መጽሐፍ ማንበብ ነው። F. ZARNCKE: Der Priester Johannes (Abhandlungen Der Königl. Sächsischen Gesellschaft Der Wissenschaft, Göttingen, VII, 1879).

[2] ለቢዛንቲን ነዋሪዎች ኦቶማን እስላሞች ቱርኮች የተሰጠ የአረብኛ ስያሜ።

[3] ይህ ቃል የተመረጠበት ምክንያት ያማርኛውን ስሜት በበለጠ ለማብራራት ስለሆነ የፖርቱጋልኛውን ትርጉም ለመከተል ከተ ፈለገ ያንድ መድፍ ጥይት ርቀት ብሎ ለማንበብ ይቻላል።

ምዕራፍ 2

[1] እስላሞች የሚደፉት ሰፊ ቆብ።

[2] አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ያለው የጉዞ መለኪያ።

ምዕራፍ 9

[1] ይህ ቦታ የት እንደነበር አጣርቶ ለማወቅ አልተቻለም።

ምዕራፍ 11

[1] ስልሳ ስድስት ሴንቲ ሜትር የሆነ የርዝመት መለኪያ።

[2] ዘፈንን በመከተል የሚጨፍሩት ጥንታዊ የፖርቱጋል ዳንስ።

ምዕራፍ 15

[1] አልቫርሽ የአረብ እረኞች ቢላቸውም እነዚህ ሰዎች ነገዳቸው ያልታወቀ ኢትዮጵያውያን ናቸው።

[2] ይህ ቃል ከምን ወይም ከየት እንደተወረሰ አጣርቶ ለማወ ቅ አልተቻለም።

[3] ለትግሬ ገዥዎች የሚሰጥ የማዕርግ ስም።

ምዕራፍ 19

[1] 14 ሊትር የሚይዝ የፈሳሽ መለኪያ።

ምዕራፍ 25

[1] በሱዌዝ ስላጤ በስተ ምስራቅ በኩል በአረቢያ የሚገኝ ትንሽ ወደብ።

[2] ይህ ቦታ የት እንደሆነ አጣርቶ ለማወቅ አልተቻለም።

ምዕራፍ 36

[1] እንዳ ሚካኤል (አድዋ።)

ምዕራፍ 37

በዚህ መጽሐፍ መቅድም እንደተገለጸው አልቫርሽ ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ብዙ ሃተታ አልተወልንም። እርሱና ሌሎች ፖርቱጌዝ ጸሐፊዎች ግዕዝን ካልዳይስጥ ብለውታል። ለምሳሌ በዳሚያው ድ ጎይሽ ጽሑፍ ይኸው ቃል ይነበባል። (Fides, Religio Moresque Aethiopicum, 1541 Coimbra).

ምዕራፍ 38

[1] በዚህ ምዕራፍ አልቫርሽ የሚሰጠው ሃተታ ግራኝ (ኤአ) 1535 ያወደመውን ጥንታዊ ሕንጻ ሁኔታ የሚገልጽ ነው።

[2] እነዚህ ቁጥራቸው አስራ አምስት የሆነ ወንበሮች በጥንት ጊዜ ነገሥታት ዘውድ ሲጭኑ የሚቀመጡባቸው ሳይሆኑ አይቀሩም።

[3] 66 ሴንቲሜትር ርዝመት ያለው ጥንታዊ የርዝመት መለኪያ።

[4] የክርስቶስን አምስት ቁስሎች የሚያስታውሱ በፖርቱጋል አርማና ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚታዩ አምስት የጋሻ ምስሎች።

[5] በአክሱም ሐውልት ላይ ተቀርጾ የሚገኘው ይህ ፊደል የሂሚያር ወይም የሳባ ፊደል የሚባለው ነው።

ምዕራፍ 39

[1] ከከተማው እልፍ ብሎ የሚገኘው የካሌብ መቃብር የሚባለው ሳይሆን አይቀርም።

[2] ተደርድረው የሚገኙ ጠርሙስ መሰል እንጨቶችን በኳስ እየመቱ በመጣል የሚደረግ ጨዋታ።

[3] ፒራሚድ።

ምዕራፍ 42

[1] ይህ ቦታ የት እንደሆነ አጣርቶ ለማወቅ አልተቻለም።

ምዕራፍ 45

[1] ንጉሣዊ ሃብት ጠባቂ (ሃ፡ሰ)

[2] በአዋሽና በጊቤ ወንዞች መካከል የሚገኝ አሁን ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ተደርቦ በወለጋ ድንበር ያለ ቀበሌ።

ምዕራፍ 48

[1] በፖርቱጋልኛው የሚነበበው ቃል ሊሹ ድ ቫካ ሲሆን የመጀመርያው ቃል ትርጉም ጉድፍ ወይም ቆሻሻ ነው። ስለዚህ በፖርቱጋልኛው ጽሑፍ መሠረት ትርጓሜው የከብት እበት ይሆናል። ነገር ግን ለብርንዶና ለጹለት ማጣሚያ የሚውል ከሆነ ሀሞት መሆን አለበት።

ምዕራፍ 61

[1] በፖርቱጋልኛው የመጀመርያ እትም ላይ የደረሰ ስህተት ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ ይህን ቃል እስራኤላውያን ሲሉ ማንበብ ነው።

ምዕራፍ 63

[1] ሐይቅ።

[2] አሁን አምባሰል የሚባል ከደሴ አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ።

ምዕራፍ 64

[1] የአርዲቦ ቀላይ።

[2] ስለዚህና ስለጥንታዊው የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ከአልቫርሽ በስተቀር ሌላ ኤውሮፓዊ ጸሐፊ አላተተም።

ምዕራፍ 65

[1] የት እንደነበረ ለማወቅ አልተቻለም።

[2] ለእንጎትና ለአማራ ገዥዎች ይሰጥ የነበር የማዕርግ ስም። ትርጉሙም ከብት መዝጋቢ ወይም የወረገኑ ሹም ማለት ነው።

ምዕራፍ 66

[1] የእንጨት አለሎን በእንጨት መዶሻ እየገጩ በማንከባለል የሚደረግ ጨዋታ።

[2] ወንጭት።

[3] 828 ሊትር

ምዕራፍ 67

[1] 1 አልኬይር 13 ሊትር።

ምዕራፍ 71

[1] ይህ ቁጥር ስህተት ሳይሆን አይቀርም። በምዕራፍ 76 እና 80 የተጠቀሰው ቁጥር ትክክለኛ ይመስላል።

ምዕራፍ 74

[1] በእንግሊዝኛ ተርኪ የሚባል በመጀመርያ በአሜሪካ የረባ ትልቅ ዶሮ።

ምዕራፍ 75

[1] የፖርቱጋልኛው Hiale Huchia Abeton ስሜት ስለማይሰጥ የሃክሊዮት ሶላየቲን ግምት በዚህ መጽሐፍ ላይ አስፍረነዋል።

ምዕራፍ 76

[1] ነፍጥ የሚለው ቃል ከፖርቱጊዞች መምጣት በፊት በኢትዮጵያ የታወቀ የደንጊያ መወርወርያ መሣርያ ነው። (Basset: Étude sur l'histoire d'Ethiopie).

[2] ወይም ኮንጎ።

ምዕራፍ 77

[1] እጅጌውና ከላዱ በሰፊ ሽንሽን ጨርቅ የሚያልቅ ጥብቆ።

[2] ከለስላሳ ቆዳ የተሠራ ሶሉ ስስ የሆነ ምቹ መጫሚያ።

[3] እስከ ጉልበት በላይ የሚደርስ ቦት መጫሚያ።

ምዕራፍ 79

[1] አንድ የሕንድ ወደብ።

ምዕራፍ 81

[1] አልቫርገዝ ሌቦች የሚላቸው እነዚህ ሰዎች ከንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ጥቂት ራቅ ብለው የሚሄዱ በጥንት ጦር ሥልት

መሠረት «ፋኖ» የሚባሉት ናቸው። (Eadie: An Amharic Reader, Cambridge, 1924).

ምዕራፍ 84

[1] የስላቭ ቋንቋ የሚናገሩ ነገዶች የሚኖሩበት ምስራቃዊና የባልካን ቀበሌ ኤውሮፓ።

[2] ፈረንሳይ የሚለውን ቃል አልቫርሽ በመደጋገም ቢጽፍም የዚህን አገር የጂኦግራፊ አቀማመጥና የፖሊቲካ አወሳሰን የሚያውቅ አይመስልም።

ምዕራፍ 103

[1] የአረብኛ የማዕርግ መጠርያ። አቡኑ የሚሰብኩት በአረብኛ እንጂ በአገሩ ቋንቋ አለመሆኑን ደራሲው በሌላ ምዕራፍ ነግሮናል። ከኩቪሊያ ጋርም የሚናገሩት በአረብኛ ሳይሆን አይቀም።

ምዕራፍ 104

[1] የዚህ ሰው የመጀመርያ ስም በፖርቱጋልኛ ፔሮ ወይም ፔድሮ ሲሆን የአማርኛውን እኩያ ለመስጠት በማለት በዚህ ምዕራፍና በሌሎችም ቦታዎች ይህ ስም ተመረጠ።

[2] የበርበር ነገዶች የሚኖሩበት የሰሜን አፍሪካ ክፍል ጥንታዊ ስም።

[3] ይህ ቦታ አሁን በአልጄርያ ይገኛል።

[4] ቱኒዚያ አልጄርያና ሞሮኮ በመድበል የሚጠሩበት የአረብኛ ስም።

[5] ማዳጋስካር።

ምዕራፍ 106

[1] የእንስሶችን ፊት በሚመስል «ማስክ» ፊትን በመሸፈን ኤግዞቲክ ልብስ በመደረብና በመደሰት በዓመት አንድ ቀን በኤውሮፓና በሌሎችም ቦታዎች የሚከበር በዓል። ይህ ልምድ ከዘመነ ክርስትና በፊት ጀንቶ የቆየ ነው።

ምዕራፍ 109

[1] አዲ ባሮ

ምዕራፍ 113

[1] የዝቋላ ተራራ

ምዕራፍ 114

[1] ምንም እንኳ በስህተት ይህን ስም ቢጽፍም ዝቅ ብሎ እንደ ሚነበበው አልቫርሽ ስህተቱን አርሞታል።

[2] በራሙዚዮ እትም መሠረት ይህ ቁጥር 19ሺ መሆን አለበት። በዚህ መጽሐፍ ላይ የሚነበበው ቁጥር ከመጀመርያው የሊዝቦን እትም የተወረሰ ነው። እስላሞች የሚማርኩዋቸው ኢትዮ ጵያውያን ለባርነት ብቻ ሳይሆን በወታደርነትም ወደ ልዩ ልዩ አገሮች ይላኩ ነበር። (Diogo de Couto: Décadas da Ásia. Vol: 4, Bk 6, Ch6).

ምዕራፍ 118

[1] በምዕራፍ 45 ተመልከት

ምዕራፍ 128

[1] በራሙዚዮ እትም መሠረት 5000

ክፍል ሁለት

ምዕራፍ 1

[1] ፓርዳው፤ ጥንታዊ የፖርቱጋል ሕንድ ገንዘብ።

ምዕራፍ 3

[1] ይህ ያዕቆብ የተባለው ሰው አምባሳደር ማቴዎስን ተከትለው ወደ ሊዝቦን ከሄዱት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነው። ከአምባ ሳደሮቹ ጋር ከሊዝቦን ወደ ጎዋ ሲሄድ በመንገድ ታሞ ስለሞተ ማቴዎስ በዚህ ቦታ አስቀበረው።

ምዕራፍ 4

[1] ከአዞርስ አርኪፔላጎ ታላቁ ደሴት

[2] የብራዚል አውራጃ

ምዕራፍ 9

[1] በግዕዝ